# ፍኖተ ብርሃን


## 1ኛ መጽሐፍ (ብሉይ ኪዳን)

አዘጋጅቶ ያቀረበው
ዓሥራት ገብረ ማርያም

አዲስ አበባ
1986 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

"በቀድሞ ዘመን በሕዝቡ መካከል ሐሰተኞች ነቢያት እንደነበሩ እንዲሁም በእናንተ መካከል ሐሰተኞች መምህራን ይኖራሉ፤ እነርሱ ጥፋት የሚያስከትል ሐሰተኛ ትምህርት በስውር ያስገባሉ፤ የዋጃቸውንም ጌታ እስከ መካድ ደርሰው በፍጥነት ጥፋት ይመጣባቸዋል። በዚህ ዐይነት ብዙዎች የነርሱን አሳፋሪ መንገድ ይከተላሉከእነርሱም አድራጎት የተነሣ የእውነት መንገድ ይሰደባል። " (2ኛ ጴጥ ም.2 ቁ. 1–2)



ዓሥራት ገብረማርያም

"ጌታ የኾነውን ክርስቶስን በልባችሁ አክብሩት፤ በእናንተ ስላለው ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቃችሁ ኹሉ መልስ ለመስጠት ዝግጁዎች ኹኑ። " (1ኛ ጴጥ. ም.3 ቁ. 15)

## ማውጫ፣

ገጽ


መግቢያ ........................................ 9

ኦሪት ዘፍጥረት ........................................ 13

በትንቢትነት ወይም በምሳሌነት ከተነገሩ ጉዳዮች መካከል .......... 14

ልዩ ልዩ ጥያቄዎችና ለጥያቄዎቹም የተሰጡ መልሶች .............. 16

ኦሪት ዘጸአት ........................................ 44

በምሳሌነት ከተነገሩ ጉዳዮች መካከል ............................ 45

ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ........................................ 47

ኦሪት ዘሌዋውያን ........................................ 58

ምሳሌ ወይም ምልክት የኾኑ ጉዳዮች ............................ 59

ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ........................................ 62

ኦሪት ዘኍልቍ ........................................ ...

በምሳሌነት የቀረቡ ኹኔታዎች ........................................ 65

ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ........................................ 66

ኦሪት ዘዳግም ........................................ 74

ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ........................................ 75




www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ ........ 84
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 85
መጽሐፈ መሳፍንት........ 90
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 91
መጽሐፈ ሩት........ 97
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 97
አንደኛ ሳሙኤል........ 98
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 99
ኁለተኛ ሳሙኤል........ 102
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 102
አንደኛ ነገሥት........ 107
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 107
ኁለተኛ ነገሥት........ 110
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 110
አንደኛ ዜና መዋዕል........ 111
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 112
ኁለተኛ ዜና መዋዕል........ 114
ጥያቄና መልስ........ 115



መጽሐፈ ዕዝራ........ 116
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 116
መጽሐፈ ነህምያ........ 118
ጥያቄና መልስ........ 119
መጽሐፈ አስቴር........ 120
ጥያቄና መልስ........ 120
መጽሐፈ ኢዮብ........ 121
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 122
መጽሐፈ መዝሙር........ 127
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 128
መጽሐፈ ምሳሌ........ 139
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 140
መጽሐፈ መክብብ........ 146
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 146
መጽሐፈ መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን........ 149
ጥያቄና መልስ........ 150
ትንቢተ ኢሳይያስ........ 152
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው........ 152



www.ethiopianorthodox.org

ትንቢተ ኤርምያስ .................................................... 165

ጥያቄዎችና መልሶቻቸው .................................................... 166

ሰቆቃወ ኤርምያስ1 .................................................... 169

ጥያቄና መልስ .................................................... 170

ትንቢተ ሕዝቅኤል .................................................... 171

ጥያቄዎችና መልሶቻቸው .................................................... 171

ትንቢተ ዳንኤል .................................................... 173

ጥያቄዎችና መልሶቻቸው .................................................... 173

ትንቢተ ሆሴዕ .................................................... 177

ጥያቄና መልስ .................................................... 178

ትንቢተ ኢዩኤል .................................................... 178

ጥያቄና መልስ .................................................... 178

ትንቢተ አሞጽ .................................................... 179

ጥያቄና መልስ .................................................... 179

ትንቢተ አብድዩ .................................................... 180

ጥያቄና መልስ .................................................... 181

ትንቢተ ዮናስ .................................................... 182

ጥያቄና መልስ .................................................... 182

ትንቢተ ሚኪያስ .................................................... 184

ጥያቄና መልስ .................................................... 184

ትንቢተ ናሆም .................................................... 186

ጥያቄና መልስ .................................................... 186

ትንቢተ ዕንባቆም .................................................... 187

ጥያቄና መልስ .................................................... 187

ትንቢተ ሶፎንያስ .................................................... 188

ጥያቄና መልስ .................................................... 188

ትንቢተ ሐጌ .................................................... 189

ጥያቄና መልስ .................................................... 189

ትንቢተ ዘካርያስ .................................................... 190

ጥያቄና መልስ .................................................... 190

ትንቢተ ሚልክያስ .................................................... 191

ጥያቄና መልስ .................................................... 191

ተከራካሪዎች ያልተቀበሏቸው መጻሕፍት .................................................... 192

መጽሐፈ ጦቢት .................................................... 193

ጥ ያ ቄዎችና መልሶቻቸው .................................................... 193

መጽሐፈ ዮዲት .................................................... 196






www.ethiopianorthodox.org

ጥያቄና መልስ..................................................196

ተረፈ አስቴር..................................................197

ጥያቄና መልስ..................................................197

መጽሐፈ ጥበብ ..................................................197

ጥያቄዎችና መልሶቻቸው..........................................198

መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ሢራክ ..................................200

ጥያቄና መልስ..................................................201

ተረፈ ዳንኤል ..................................................202

ጥያቄዎችና መልሶቻቸው..........................................202

ትንቢተ ባሮክ ..................................................204

አንደኛና ኹለተኛ መጽሐፈ መቃብያን ..........................204

የይሁዳ ንጉሥ የምናሴ ጸሎት ......................................204



# መግቢያ

በቅዱሳት መጻሕፍት እውነተኛነትና በጥንታዊትዋ ቤተክርስቲያን መሰረታዊ እምነት ላይ ብዙ መናፍቃን በየጊዜው ተነሥተው የቅዱ ሳት መጻሕፍትን አባባሎች በመጥቀስ ክርክር አንሥተው የነበረና አሁን ም ክርክር የሚያነሡ ወገኖች ያሉ መኾናቸው የሚታወቅ ነው። ሐዋርያ ው ቅዱስ ጴጥሮስ በመጀመርያ መልእክቱ ምዕራፍ 3 ቁ. 15 ላይ "ጌታ የኾነውን ክርስቶስን በልባችሁ አክብሩት በእናንተ ስላለው ተስፋ ምክ ንያት ለሚጠይቃችሁ ኹሉ መልስ ለመስጠት ዝግጁዎች ኹኑ" ባለው መሠረት ለጥያቄዎች ኹሉ ተገቢውን መልስ ለመስጠት መዘጋጀት አለ ብን እንጂ በቅን ልቦናም ኾነ በተንኮል ለምንጠየቀው ጥያቄ መልስ የማ ንሰጥ መኾን የለብንም።

ከኹሉ አስቀድሞ መታወቅ የሚኖርበት ጉዳይ ግን ስለእግዚአ ብሔር ባሕርይ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚሰጡትን መግለጫዎች አምላክ የሚገልጽልንን ያኽል ካልኾነ በቀር ከእኛ ከውስኖቹ ፍጥረቶች የአስተሳሰብ ዐቅም በላይ መኾኑ ነው።

ቅዱሳት መጻሕፍት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ። እነር ሱም :- የሕግ የታሪክ የጥበብና የትንቢት መጻሕፍት ናቸው በአጠቃላይ ግን በብሉይና በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይከፈላሉ። የአከፋፈሉም ዝር ዝር እንደሚከተለው ነዉ።

## የሕግ መጻሕፍት :- አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት

1. ኦሪት ዘፍጥረት

2. ኦሪት ዘጸአት

3. ኦሪት ዘሌዋውያን

4. ኦሪት ዘኊልቊ



www.ethiopianorthodox.org

5. ኦሪት ዘዳግም

## የታሪክና የሕግጋት መጻሕፍት

1.መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ

2.መጽሐፈ መሳፍንት

3. መጽሐፈ ሩት

4. 1ኛ ሳሙኤል

5. 2ኛ ሳሙኤል

6. 1ኛ ነገሥት

7. 2ኛ ነገሥት

8. 1ኛ ዜና መዋዕል

9. 2ኛ ዜና መዋዕል

10.መጽሐፈ ዕዝራ

11. መጽሐፈ ነህምያ

12. መጽሐፈ አስቴር

## የጥበብ መጻሕፍት

1. መጽሐፈ ኢዮብ



2. መጽሐፈ መዝሙር

3. መጽሐፈ ምሳሌ

4. መጽሐፈ መክብብ

5. መኃልየ መኃልይ

## የነቢያት መጻሕፍት

1. ትንቢተ ኢሳይያስ

2. ትንቢተ ኤርምያስ

3. ትንቢተ ሕዝቅኤል

4. ሰቆቃወ ኤርምያስ

5. ትንቢተ ዳንኤል

6. ትንቢተ ሆሴዕ

7. ትንቢተ ኢዩኤል

8. ትንቢተ አሞጽ

9. ትንቢተ አብድዩ

10. ትንቢተ ዮናስ

11. ትንቢተ ሚክያስ

12. ትንቢተ ናሆም



www.ethiopianorthodox.org

13. ትንቢተ ዕንባቆም

14. ትንቢተ ሶፎንያስ

15. ትንቢተ ሐጌ

16. ትንቢተ ዘካርያስ

17. ትንቢተ ሚልክያስ

## ተከራካሪዎች ያልተቀበሉአቸው መጻሕፍት

1. መጽሐፈ ጦቢት
2. መጽሐፈ ዮዲት
3. ተረፈ አስቴር
4. መጽሐፈ ጥበብ
5. መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ሲራክ
6. ተረፈ ዳንኤል
7. ትንቢተ ባሮክ
8. 1ኛ መጽሐፈ መቃብያን
9. 2ኛ መጽሐፈ መቃብያን
10. የይሁዳ ንጉሥ የምናሴ ጸሎት



## ኦሪት ዘፍጥረት

ይህ መጽሐፍ በዚህ ስም የተጠራበት ምክንያት ስለ አፈጣጠር ታሪክ የሚያወሳ በመኾኑ ነው። መጽሐፉም ኀምሳ ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፋፍሎአል።

ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 5 ድረስ ስለዓለም አፈጣጠር፣ የሰው ልጅ በኀጢአት ስለመውደቁና እንዲሁም ስለመጀመሪያዎቹ አባቶች ዕድሜ በዝርዝር ይገልጻል። በዚሁ ክፍል ውስጥ ለሰው ልጅ የተሰጠውን የፈቃድና የፍላጎት ነጻነት ያመለክታል።

ከምዕራፍ 6 እስከ ምዕራፍ 11 ድረስ ስለሰዎች ኀጢአት መብዛት እና በዚሁም ምክንያት እግዚአብሔር ተቆጥቶ ኖኅንና ቤተሰቡን ብቻ አስተርፎ ኹሉንም በጥፋት ውሃ ያጠፋቸው መኾኑን የሚገልጽ ታሪክ ነው ። እንዲሁም ሰዎች የባቢሎንን ግንብ ለመሥራት ስላቀዱ እግዚአብሔር ቋንቋቸውን እንደደባለቀባቸው ተገልጾአል።

ከምዕራፍ 12 እስከ ምዕራፍ 26 ድረስ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳንና አብርሃም የኮሎዶጎሞርንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ነገሥታት በጦርነት የማሸነፉ ታሪክ ነው። ከዚያም ሲመለስ የልዑል እግዚአብሔር ካህን ከነበረው ከሳሌም ንጉሥ ከመልከጼዴቅ ጋር ተገናኝቶ ዓሥራት እንደከፈለው ተገልጾአል። ከሎጥና ከኹለቱ ልጆቹ በቀር በናሪዎቹ ኀጢአት ምክንያት ስለሰዶምና ገሞራ ጥፋትና እንዲሁም እግዚአብሔር ለይስሐቅ ስለገባለት ቃል ኪዳን የሚያወሳ ታሪክ ይገኝበታል።

ከምዕራፍ 27 እስከ ምዕራፍ 50 ድረስ የያዕቆብን ታሪክ የያዘ ኾኖ እግዚአብሔር ለአባቶቹ የገባውን ቃል ኪዳን ለእርሱም የገባለት መኾኑንና እንዲሁም ከያዕቆብ ልጆች አንዱ የኾነውን የዮሴፍን ታሪክ የሚያወሳ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

## በትንቢትነት ወይም በምሳሌነት ከተነገሩት ጉዳዮች መካከል

ሀ. "በአንተና በሴቲቱ መካከል ጠላትነት አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ" (ዘፍ. ም.3 ቁ.15) የዚህን ትንቢት ተፈጻሚነት በሚከተሉት ጥቅሶች እን መ ልከት ፣ " ነገርግን የተወሰነው ዘመን በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ እርሱም ከሴት ተወ ለደ።" (ገላ. ም.4.ቁ.4)

"ዲያብሎስ ከመጀመሪያው አንሥቶ ኀጢአት ስለሚሠራ ኀጢአትን የሚሠራ ኹሉ ከዲያብሎስ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የተገለጠውም የዲያብሎስን ሥራ ለማፍረስ ነው።" (1ኛ ዮሐ. ም.3.ቁ.8)

"ዘንዶውንም ይዞ ሺ ዓመት አሰረው ይህም ዘንዶ ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን የሚባለው የቀድሞው እባብ ነው።" (ራ.ዮሐ. ም. 20 ቁ.2)

ለ. የልዑል እግዚአብሔር ካህን የነበረው የሳሌም ንጉሥ መልከጼዴቅ ኅብስትና የወይን ጠጅ ለአብርሃም አመጣለት፣ ባረከውም (ዘፍ. ም.14 ቁ.18፤ አብርሃምም ዓሥራት ከፈለው ቁ.20)

የዚህንም ምሳሌነት በሚከተሉት ጥቅሶች እንመልከ "እንደመልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ እግዚአብሔር ማለ።" (መዝ 110 ቁ.4)

"መልከጼዴቅ የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነው፤ ይህ መልከጼዴቅ አብርሃም ነገሥታትን አሸንፎ ሲመለስ በመንገድ ተገናኝቶ ባረከው። አብርሃምም ከያዘው ነገር ኹሉ ዐሥራት አውጥቶ ሰጠው፤ መልከጼዴቅ አባትና እናት ወይም የትውልድ ሐረግ የለውም፤ ለዘመኑ መጀመሪያ ለሕይወቱ መጨረሻ የለውም፤ ይህ መልከጼዴቅ የእግዚአብሔር ልጅ ምሳሌ በመኾን ለዘላለም ካህን ኾኖ ይኖራል።" (ዕብ. ም. 7. ቁ. 1 – 3)



ኅብስትና ወይን ማቅረቡ ደግሞ፣ ጌታ በዕለተ ሐሙስ ማለት በስቅለቱ ዋዜማ ላቀረበው ወይም ለሰጠው ኅብስትና ወይን ምሳሌ ነው።(ማቴ. ም.26 ቁ. 26–27)

ሐ. "አንተና ከአንተ በኋላ የሚመጣው ዘርህ የምትጠብቁት ቃል ኪዳን ይህ ነው፤ በመካከላችሁ ያሉት ወንዶች ኹሉ መገረዝ አለባቸው፤ የብልታችሁን ሸለፈት ትገረዛላችሁ፣ ይህም በእኔና በእናንተ መካከል ላለው ቃል ኪዳን ምልክት ይኾናል።" (ዘፍ.ም.17. ቁ.10–11) ምሳሌነቱ ለጥምቀት መኾኑ "ከእርሱም ጋር አንድ በመኾን ተገርዛችኋል፤ ይህም መገረዛችሁ ኀጢአተኛውን ሥጋ ለማስወገድ በክርስቶስ የተደረገ ነው እንጂ ሰው ሠራሽ መገረዝ አይደለም። ምክንያቱም በተጠመቃችሁ ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ተቀበራችሁ።" (ቆላ.ም.2.ቁ. 11–12)

መ. "እግዚአብሔርም የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያ ምድር ኺድ፤ እዚያ በማሳይህ አንድ ኮረብታ ላይ እርሱን መሥዋዕት አድርገህ አቅርብልኝ አለው።" (ዘፍ.ም. 22.ቁ.2) "አብርሃም ዙሪ ያውን በተመለከተ ጊዜ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ(ሐረግ) የተያዙ አንድ በግ አየ፣ ኼዶ በጉን አመጣና በልጁ ፈንታ መሥዋዕት አድርጎ አቀረበው።" (ቁ.13)

የይስሐቅ በሚወደው አባቱ ለመሥዋዕትነት መቅረብ ምሳሌነቱ የእግዚአብሔር አብ ወልድን ለዓለም መድኀኒትነት ከመስጠቱ ጋር ተመሳሳይ ነው። (ዮሐ.ም.3.ቁ. 17)

እንዲሁም የበጉ በይስሐቅ ምትክ መሠዋት የጌታ ለኀጢያተኞች ቤዛ ከመኾን ጋር ተመሳሳይ ነው። (2ኛ. ጢሞ. ም 2.ቁ.6)

ሠ .የያዕቆብ ልጆች ወንድማ ቸውን ዮሴፍን ሸጠውት ወደ ግብጽ ተወስዶ ችግ ር ከደረሰበት በኋላ በመ ጨረሻ በግብጽ ምድር ትልቅ ሰው ለመኾን መብቃቱና በረኀቡ ዘመን የግብጽን ሕዝብና ወገኖቹን ከችግር ማዳኑ ምሳ ሌነቱ በሥጋ ወገኖቹ የኾኑ አይሁድ በጌታ ላይ ያደረሱት ግፍና በስቅለ ቱና በሞቱ ለዓለም መድኀኒት መኾኑን የሚያመለክት ነ ው።



www.ethiopianorthodox.org

## ልዩ ልዩ ጥያቄዎችና ለጥያቄዎቹም የተሰጡ መልሶች

1. የእግዚአብሔር ዳኝነትና ኹሉን ነገር ዐዋቂነቱ ወደፊት ለሚፈጸሙት ድርጊቶች ኹሉ እንደመኾኑ በጎ ተግባርን መፈጸም ምንም ጥቅም የለውም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰነውን ውሳኔ የሰው በጎ ተግባር ሊለውጠው አይችልምና በማለት ትችት የሚያቀርቡ ወገኖች አሉ።

የእግዚአብሔር ዳኝነት የሰውን ልጅ በጎ ተግባር ዋጋ የሚያሳጣው አይደለም። ማነኛውም ሰው የሚጸድቅ ወይም የሚኰነን መኾኑ በእግዚአብሔር ዘንድ አስቀድሞ መታወቁና በቅድሚያም ፍርድ መሰጠቱ እግዚአብሔር ለጽድቅ ወይም ለኩነኔ ምክንያት ኾነ ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ደግሞ ኹሉም ይድን ዘንድ እንጂ ማንም እንዲጠፉ አይፈልግም።

የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድና ነጻ ፍላጎት ስላለው ለመዳን ቢፈልግ በጎ ተግባርን ይፈጽማል፤ ስለድኅነት ግድ የሌለው ከኾነ ደግሞ በፍላጎቱ ይመራል። እንደየተግባሩ ደግሞ ፍርዱን ይቀበላል።

የእግዚአብሔርንም ዐዋቂነት ጊዜና ቦታ አይወስነውም። ስለዚህ ነው እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ሰው የወደፊት ኹኔታ አስቀድሞ የሚያውቀው እንጂ አስቀድሞ ማወቁ ግን የሰውን የወደፊት ዕድል ወሰነ ማለት አይደለምና አለመኾኑን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

2. ኹሉም ነገር አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚታወቅ እንደ መኾኑ አንድ ሰው ከሚጠፉት ማለት ከሚፈረድባቸው ሰዎች አንዱ የሚኾነው ያንን ኹናቴ እግዚአብሔር ስላዘጋጀለት ነው፣ የሰው ልጅ ዕድል ፈንታ የሚገኘው በግል ጥረት ብቻ ሳይኾን በአምላካዊ ፈቃድም ጭምር ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰው ኹሉ ይድን ዘንድ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ከኾነ ለሰው ኹሉ የመዳንን ዕድል ሊሰጠው በተገባ ነበር የሚሉ ወገኖች አሉ።



እግዚአብሔር ኹሉንም ነገር አስቀድሞ የሚያውቅ መኾኑ ግልጽ ነው። እርሱ ከፈቀደ ደግሞ ማንንም ሰው ለማዳን ከሃሊ ነው። ይኹን እንጂ የመዳንን ጸጋ ተገቢ ላልኾነ ሰው ቢሰጥ ስጦታውን ያለቦታው ማስቀመጡና መብቱ ላልኾነ ሰው መስጠቱ ይኾናል። እግዚአብሔር ግን ኹሉንም ነገር የሚያስቀምጠው በተገቢው ቦታ ነው። እግዚአብሔር ጽድቅ ለማይገባቸው ሰዎች ጽድቅን መከልከሉ ለባሪያዎቹ ደኅንነትን የማይፈልግ ኾኖ ሳይኾን እነዚያ ሰዎች ለጽድቅ ተገቢ አለመኾናቸውን አስቀድሞ ስለሚያውቀው ነው።

ወደፊት ሊኾን የሚችለውን አስቀድሞ ማወቅ ደግሞ ለኹናቴም ምክንያት መኾን አይደለም። ለምሳሌ አንድ ሐኪም የአንድን ሕመምተኛ ኹናቴ በመመልከት ያሕመምተኛ በዚያ ሕመሙ የሚሞት ወይም ከሕመሙ የሚድን መኾኑን የሚያውቅበት ጊዜ ሊኖር ይችል ይኾናል። ይህን በማወቁ ብቻ ሕመምተኛው በሚሞትበት ጊዜ ሐኪሙ ለሕመምተኛው መሞት ምክንያት ኾነ ማለት አይደለም። በዚሁም ዐይነት የአንድን ሰው አለመዳን ቀድሞ ማወቁ ያ ሰው እንዳይድን የእግዚአብሔር ፍላጎት ነው ማለት አይደለም። አስቀድሞ ማወቅን በፍላጎት ላይ ልንመሠርተው አይገባም፤ ምክንያቱም ዕውቀት አንድ ነገር ነው፣ ፍላጎት ደግሞ ሌላ ነገር ነውና። ለምሳሌ ይሁዳ የጥፋት ሰው እንደነበረ ጌታ አስቀድሞ ያውቅ ነበር። ይኹን እንጂ ይሁዳ የጥፋት ሰው እንዲኾን ጌታ ፈለገ ማለት አይደለም። በዚሁም ዐይነት ወደፊት እግዚአብሔር የሚኾነውን ነገር ኹሉ ማወቁ ያ ኹናቴ እንዲኾን ፈለገ ማለት አይደለም። ለሰው ልጆችም ነጻ ፈቃድን ስለሰጣቸው የፈለጉትን ድርጊት ቢያደርጉ አይ ከለከላቸውም እንጂ ክፉው ኹናቴ የሚደርሰው በእግዚአብሔር ውሳኔ አይደለምና አለመኾኑን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

3. የእግዚአብሔር ዳኝነትና የወደፊቱን ኹናቴ በቅድሚያ ማወቅ በፍጥረቱ ኹሉ ላይ እንደመኾኑ የኀጢአትና የክፉ ኹናቴዎች በዓለም ላይ መገኘት በጠያቂዎቹ አስተሳሰብ እርሱ የፈቀዳቸው እስከኾኑ ድረስ ለምን በሰዎች ላይ ይፈርዳል ብለው የሚጠይቁ ሰዎች አሉ።

የኀጢአት በዓለም ላይ መገኘት ልንረዳው የማንችለው ምሥጢር ነው። ይህ ኹናቴ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለመኾኑ ግልጽ ቢኾንም ከሰው ልጅ አስተሳሰብ በላይ ነው። ይኹን እንጂ ለኀጢአቱ ሥራ ኀላፊው በተ



www.ethiopianorthodox.org

ሰጠው ነጻ ፈቃድና ነጻ ፍላጎት መሠረት የሰው ልጅ ነው እንጂ እግዚአብሔር አይደለም። በዚህ ጉዳይ ላይ ቃለ እግዚአብሔር ምን እንደሚል ቀጥለን እንመልከት, "ሰው በሚፈተንበት ጊዜ እግዚአብሔር ፈተነኝ አይበል። እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱም ማንንም አይፈትንም ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው የሚፈተነው በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው።" (ያዕ. ም. 1.ቁ.13–14) እንዲሁም በሌላ ጊዜ እንዲህ ብሏል :- "እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው።" (ሮሜ ም.1 ፥ ቁ..28)

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ጐጂና ጠቃሚ የኾኑትን ተግባሮች ለይቶ ከገለጸላቸው በኋላ የፈለጉትን ድርጊት የማድረግ ነጻ ፈቃድ የሰጣቸው በመኾኑ ሰዎች ኹሉ እንደየግል ተግባራቸው ይፈረድላቸዋል ወይም ይፈረድባቸዋል እንጂ አስቀድሞ ማወቁ ግን ለፍርዱ ምክንያት አይደለም። ለፍርዱ ግን ምክንያት የሚኾነው ተግባራቸው ነው።

4. የሰዎች ክፉ ተግባር አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ታውቆ በፍርዱ ውስጥ ስለሚኾን እነዚያ ጥፋተኞች በጥፋታቸው በኀላፊነት ሊጠየቁ አይገባም፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ፍርድ ሊቃወሙ አይችሉምና ብለው የሚተቹ ሰዎች አሉ።

የኀጢአተኞችን የወደፊት ተግባር አስቀድሞ በማወቅ መፍረድና የኀጢአተኞች ለክፉ ተግባራቸው ተጠያቂነት የሚቃረኑ ጉዳዮች አይደሉም። ለምሳሌ የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ታልፎ መሰጠት ከዘመናት በፊት በእግዚአብሔር የተወሰነ ቢኾንም አሳልፎ የሰጠው ግን ከኀላፊነት ነጻ ይኾናል ማለት አይደለም። እግዚአብሔርም የአሳልፎ ሰጪውን ክፉ ዝንባሌ አስቀድሞ በማወቅ የዘላለማዊ ዐላማውን በሥራ ላይ ለማዋል ተጠቅሞበታል። እነዚህም የእግዚአብሔር ፍርድና የሰው ልጅ በክፉ ተግባሩ ተጠያቂነት ሳይቃረኑ በአንድነት እንደሚገኙ ቃለ እግዚአብሔር እንዲህ በማለት አረጋግጦአል። "የሰው ልጅስ እንደ ተወሰነው ይኼዳል፤ ነገር ግን አሳልፎ ለሚሰጠው ለዚያ ሰው ወዮለት" (ሉቃ. ም. 22፥ ቁ. 22)



ስለዚህ እግዚአብሔር ወደፊት የሚሠራውን ክፉ ተግባር በቅድሚያ ዐውቆ ተገቢውን ፍርድ መስጠቱ የእርሱ ዕውቀት ጊዜ የማይወስነው በመኾኑ ነው እንጂ ኀጢአት እንዲሠራ እርሱ አስቀድሞ ወሰነ ማለት አይደለም።

5. እግዚአብሔር በቅድሚያ ዐውቆትና ወስኖት፥ እንዲሁም ትንቢት አናግሮበት በተፈጸመው ድርጊት ምክንያት እንደ ይሁዳ ባለ ሰው ላይ እንደምን ሊፈረድበት ይገባል ብለው የሚጠይቁ ሰዎች አሉ።

እንደ ይሁዳ አሠራር ያለውን ድርጊት የፈጸመ ሰው ኹሉ ባለው የነጻ ፈቃድና የነጻ ፍላጎት አማካይነት እንደፈጸመው ይቆጠራል፤ ነጻነቱን ማንም ሳይወስድበትና አድራጎቱንም ማንም ሳያስገድደው የሚያደርገው ነው። እንደ ይሁዳ ያሉትን የክፉ አድራጊዎችንም ኾነ የሌሎችን በጎ አድራጊዎች ኹኔታ እግዚአብሔር አስቀድሞ ማወቁ የእርሱ ዕውቀት በጊዜ ያልተወሰነ በመኾኑ ነው እንጂ ነጻ ፈቃድና ነጻ ፍላጎት ያለውን ሰው የጽድቅን ወይም የኩነኔን መንገድ እንዲከተል ያስገድደዋል ማለት አይደለም። የሰው ልጅ ደግሞ ደጉንና ክፉውን ለይቶ የማወቅ ችሎታና ነጻ ፈቃድ ያለው እስከኾነ ድረስ ለሚፈጽማቸው ድርጊቶች ኹሉ ተጠያቂ ነው።

6. "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።" (ዘፍ ም.1 ቁ.1)

"በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።" (ዮሐ. ም.1 ፥ ቁ.1)

"ስለሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን፥ በዐይኖቻችንም ያየነውን፥ የተመለከትነውንም፥ እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን።" (1ኛ ዮሐ. ም.1፥ ቁ.1)

በሦስቱ ጥቅሶች ውስጥ መጀመሪያ ተብሎ የተነገረው ቃል ግንኙነትና ልዩነቱ እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።



www.ethiopianorthodox.org

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ማለቱ በመጀመሪያው ቀን ወይም ከሌሎቹ ፍጥረቶች በፊት ማለቱ ነው።

በመጀመሪያ ቃል ነበረ የሚለው መነሻ የሌለው መጀመሪያ ማለት ነው። እግዚአብሔር ወልድ ከሦስቱ መለኮታዊ አካሎች አንዱ ማለት የአብና የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው በመኾኑ ቀድሞም የነበረ አሁንም ያለና ወደፊትም የሚኖር እንጂ በአንድ በተወሰነ ጊዜ የጀመረ አለመኾኑን ለመግለጽ ብሎ ነው እዚህ ላይ መጀመሪያ ያለው።

በሦስተኛው ጥቅስ ላይ ከመጀመሪያው የነበረ የሚለው ደግሞ በሰውነት ተገልጾ ደቀ መዛሙርቱ ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ማለት ነው።

7. በኦሪት ዘፍጥረት ም. 1 ፥ ቁ. 3 ላይ "እግዚአብሔርም ብርሃን ይኹን አለ፤ ብርሃንም ኾነ። እግዚአብሔርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት አለው፤ ማታም ኾነ ጥዋትም ኾነ አንድ ቀን" ካለ በኋላ ከቁጥር 14 እስከ 16 ደግሞ "እግዚአብሔርም አለ፣ ቀንንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይኹኑ፤ ለምልክቶች፥ ለዘመኖች ፥ ለዕለታት፥ ለዓመታትም ይኹኑ፤ በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር ብርሃናት ይኹኑ፤ እንዲሁም ኾነ። እግዚአብሔርም ኹለት ታላላቅ ብርሃናትን አደረገ፣ ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሠለጥን፥ ትንሹ ብርሃን በሌሊት እንዲሠለጥን ከዋክብትንም ደግሞ አደረገ" በመባሉ ቀንና ሌሊትን ለመለየት የሰማይ ብርሃናት የተፈጠሩት በአራተኛው ቀን ከኾነ በመጀመሪያው ቀን ተፈጠረ የተባለው ብርሃን እንዴት ቀኖችን አስቆጠረ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ብርሃን የተፈጠረው በመጀመሪያው ቀን ወይም በመጀመሪያው የፍጥረት ጊዜ ቢኾንም የአራተኛው ቀን አባባል ግን በመጀመሪያ የፈጠረውን ብርሃን ሥርዓት እንዲይዝ አደረገው ለማለት ነው። እንደ አራተኛው ቀን ሥነ ሥርዓትን አልያዘም ለማለት ካልኾነ በቀር ብርሃን በመጀመ ሪያው ቀን የተፈጠረ በመኾኑ ቀንና ሌሊት መጠቀሳቸው ሊያስገርመን አይገባም። ኾኖም ይህ የተጠቀሰው አንድ ቀን የመጀመሪያዎቹ ፍጥረቶች የተፈጠሩበት ጊዜ እንጂ ኻያ አራት ሰዓት ብቻ አለመኾኑን ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የሚስማሙበት ነው።



በኦሪት ዘፍጥረት ም.1 ቁ.1 ላይ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ካለ በኋላ እንደገና በቁጥር 8 ላይ እግዚአብሔር ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠራው፣ የብሱንም ምድር ብሎ ጠራው ማለቱ የመጀመሪያው ስለ አፈጣጠርና ኹለተኛው ደግሞ ሥነ ሥርዐት ማስያዝ መኾኑን የሚያመለክት ነው እንጂ የተለያዩ ጉዳዮች ኾነው አይደለም መጀመሪያ በአጠቃላይ፥ በኋላ ግን በዝርዝር መግለጽ ማለት ነው። ለምሳሌ ዕፀዋት ተፈጠሩ የተባለው ገና ፀሐይ ከመፈጠርዋ በፊት በሦስተኛው ቀን ነው።

ማታም ኾነ ፣ ቀንም ኾነ፣ አንድ ቀን ማለቱ ኻያ አራት ሰዓቶችን ብቻ ለማመልከት ሳይኾን ጊዜያትና ዘመናት የሚቆጠሩት ቀንና ሌሊት ተፈራርቀው መኾኑ በሰው ኹሉ ዘንድ የተለመደ በመኾኑ አንድ የአፈጣጠር ጊዜ አልፎ ኹለተኛው የአፈጣጠር ጊዜ የሚተካበትን ጊዜ ለማመልከት ነው።

8. በኦሪት ዘፍጥረት ም. 1፥ ቁ.26 ላይ እግዚአብሔርም አለ "ሰውን በመልካችንና በአምሳያችን እንፍጠር" ካለ በኋላ በትንቢተ ኢሳይያስ ም. 40 ቁ.18 ላይ "እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ" ይላል። እንዲሁም በኦሪት ዘጸአት ም. 24 ቁ. 9–10 ሙሴ፥ አሮን፥ ናዳብና አብዩድ ከእስራኤል ሰባ ሽማግሌዎች ጋር ወጥተው እግዚአብሔርን እንዳዩ ተገልጾአል። በዮሐንስ ወንጌል ም.4 ቁ. 24 እና ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.3 ቁ.17 መሠረት እግዚአብሔር መንፈስ በመኾኑ በኦሪት ዘጸአት ም.33 ቁ.20 ፥ በዮሐንስ ወንጌል ም.1 ቁ. 18 እና በመጀመሪያ ወደ ጢሞቴዎስ በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልዕክት ም.6 ቁ.16 ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔርን ማንም ያየው ሰው አለመኖሩንና እግዚአብሔርንም አይቶ በሕይወት ለመኖር የማይቻል መኾኑ ስለተገለጠ እነ ሙሴ እግዚአብሔርን አዩት ከተባለው ጥቅስ ጋር ለምን ተለያየ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በዚህ ጉዳይ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በኹለት ዐይነት አስተሳሰብ ይለያያሉ።



www.ethiopianorthodox.org

የመጀመሪያዎቹ ወገኖች እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጡር ማለት ሰውን እንደሚመስልና ነቢያትና ጻድቃንም ሊያዩት እንደቻሉ ያምናሉ። ለዚሁ እምነታቸው ከሚያቀርቡአቸው ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

1. በኦሪት ዘፍጥረት ም.1 ቁ.26 ላይ "ሰውን በመልካችንና እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር" ማለቱ የእግዚአብሔር መልክ ልክ እንደ ሰው መልክ መኾኑን ያመለክተናል።

2. በኦሪት ዘጸአት ም.33 ቁ. 18–23 ላይ እግዚአብሔር ክብሩን እንዲያሳየው ሙሴ ለለመነው ልመና መልስ ሲሰጠው "እስካልፍ ድረስ እጄን በላይህ እጋርዳለሁ፤ እጄንም ፈቀቅ አደርጋለሁ፤ ጀርባዬንም ታያለህ" ማለቱ እግዚአብሔር የሰው ዐይነት አቋም ኖሮት በስተጀርባው ለመታየት መቻሉን ነው።

3. በኦሪት ዘኍልቍ ም.12 ቁ.8 ላይ እግዚአብሔር ከአሮንና ከማርያም ጋር የተግሣፅ አነጋገር በተነጋገረ ጊዜ የእግዚአብሔርን መልክ እንደሚያይ ለሙሴ መስክሮለታል።

4. " ለእግዚአብሔር ዐይን፥ ጕሮ፥ እጅ ፥ እግር እንዳለው የተነገረው ኹሉ ስለ እግዚአብሔር በከበሩ መጻሕፍት የተጻፈው ኹሉ የታመነ፥ የተረዳ ነው፤ የተናገርነው ኹሉ ለእግዚአብሔር አለው" ተብሎ በቅዱስ አትናቴዎስ ጽሑፍ መገለጹ እግዚአብሔር በእኛ ሰውነት ውስጥ የሚገኙት የአካል ክፍሎች ያሉትና አቋሙ ኹሉ ሰውን እንደሚመስል ያመለክተናል። (ሃይ. አበ. ገጽ 88)

የኹለተኛዎቹ ወገኖች አስተሳሰብ ደግሞ እንደሚከተለው ነው። በመልካችንና እንደ አምሳያችን ማለት ሥጋዊ ሰውነታችን እግዚአብሔርን ይመስላል ማለት ሳይኾን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በምድር በፈጠረው ፍጥረት ኹሉ ላይ የበላይነትን ስለሰጠውና የማትሞት ነፍስን በመስጠት ከሌሎቹ ፍጥረቶች ስላስበለጠው፥ እንዲሁም የሰው ልጅ አልጠበቀውም እንጂ እንደ እግዚአብሔር ጻድቅና ቅዱስ እንዲኾን ፈጥሮት ስለነበረ በእግዚብሔር አምሳያ ተፈጠረ ተባለ።



በልዩ ልዩ ጊዜዎች አንዳንድ የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔርን ያዩት በተለያየ ኹኔታ ኾኖ ነው እንጂ እግዚአብሔርን ራሱን ያየው ማንም የለም። ይህንን አባባል ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በኦሪት ዘጸአት ም.33ቁ.18–21 በሚነበበው ቃለእግዚአብሔር የሙሴን ልመናና የእግዚአብሔርን መልስ እንመልከት።

"ሙሴም እባክህን ክብርህን አሳየኝ አለ፤ እግዚአብሔርም እኔ መልካምነቴን ኹሉ በፊትህ አሳልፋለሁ፤ የእግዚአብሔርንም ስም በፊትህ አውጃለሁ፤ ይቅርም የምለውን ይቅር እላለሁ፤ የምምረውንም እምራለሁ አለ። ደግሞም ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ። "

እንግዲህ ቀደም ተብሎ በተጠቀሰው ጥቅስ ከሌሎቹ ነቢያት ኹሉ የበለጠ ለእግዚአብሔር ቅርብነት እንዳለው እግዚአብሔር ራሱ የመሰከረለት ሙሴ የእግዚአብሔርን መልክ ያያል የተባለው በሕልሙ ሳይኾን በውኑ እግዚአብሔርን መሰል ኹናቴ ያያል ማለት ነው።

ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.1 ቁ.1 እና 2 ላይ እንዲህ ተብሎአል።

"ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ልዩ ልዩ መንገድ ለአባቶቻችን በነቢያት አማካይነት ተናግሮ፥ ኹሉን ወራሽ ባደረገውና ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን።"

ይህ አባባል በግልጽ የሚያስረዳው እግዚአብሔር ለነቢያትና ለደጋግ ሰዎች የተገለጸላቸው በተለያየ መንገድ እንጂ በአንድ ዓይነት መንገድ አለመኾኑን ነው።

በዚህም መሠረት ለሙሴ በእሳት ነበልባል መልክ ተገልጾለታል፤ ለኢሳያስ በራእይ በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦና የልብሱ ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ታይቶታል። እንዲሁም ለዳንኤል በራእይ በሽማግሌ ሰው መልክ ታይቶታል። (ዘጸ. ም.3 ቁ.2–6 ፥ኢሳ. ም.6 ቁ.1 ዳን. ም.7 ቁ. 13)



www.ethiopianorthodox.org

ሙሴም ለእስራኤል ልጆች ገለጻ ባደረገላቸው ጊዜ እግዚአብሔርን ያላዩ መኾናቸውን ዘርዝሮ ያስረዳቸው በሚከተለው ኹናቴ ነው።

"እናንተም ቀርባችሁ ከተራራው በታች ቆማችሁ ነበር፤ እስከ ሰማይም መካከል ድረስ እሳት በተራራው ይነድድ ነበር፤ ጨለማና ደመና፥ ድቅድቅ ጨለማም ነበር። እግዚአብሔርም በእሳት ውስጥ ኾኖ ተናገራችሁ የቃልን ድምፅ ሰማችሁ፤ መልክ ግን አላያችሁም፤ ድምፅን ብቻ ሰማችሁ እግዚአብሔር በኮሬብ በእሳት ውስጥ ኾኖ በተናገራችሁ ጊዜ መልክ ከቶ አላያችሁምና እጅግ ተጠንቀቁ እንዳትረክሱ።" (ዘዳ. ም.4 ቁ.11–12 እና ቁ.15)

የእግዚአብሔርን መልክ አይቶ በሕይወት ለመኖር አለመቻሉ ብቻ ሳይኾን በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለተነጋገረ ብቻ እንኳ ፊቱ በጣም በማንጸባረቁ የእስራኤል ልጆች የሙሴን ፊት ማየት ያቃታቸው መኾኑን በኦሪት ዘጸአት ም.34 ቁ. 30–35 እንመልከት።

እግዚአብሔር መንፈስ በመኾኑ በሕዋሳቶቻችን አማካይነት ልናውቀው የምንችል አንድ ነገር፥ ወይም የአንድ ነገር አንድ ክፍል ወይም ኹሉም አይደለም ይህም ማለት የማይከፋፈልና የማይለያይ፥ መቀላቀልና መሰባሰብ የሌለበት፥ በዐይን ሊታይ የሚችል ውሱን ትርኢት ያይደለና በሰውነታችን ሕዋሳት ሊዳሰስ የማይቻል ነው። ይህም በመኾኑ ለውሱን ነገሮች የሚሰጡት እንደ ክብደት፥ የመጠን ትንሽነትና ትልቅነት የመሳሰሉትን መግለጫዎች መስጠት ተገቢ አይደለም። ስለዚህ ነው ነቢዩ ኢሳይያስ "እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ? ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ?" ያለው (ኢሳ. ም. 40 ቍ.18)

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የእግዚአብሔር እጆች ጣቶች ዐይኖችና ጆሮዎች ተብለው የተነገሩበት ምክንያት ሊገባን በሚችል በሰው ልጅ ቋንቋ ካልኾነ በቀር እግዚአብሔር መንፈስ እንደመኾኑ የመንፈስን ድርጊት ልንረዳ የማንችል በመኾናችን ነው እንጂ እግዚአብሔር በሰው ልጆች ቅርጽ ውሱን የኾኑ የአካል ክፍሎች አሉት ለማለት አይደለም።



በዚህም መሠረት የእግዚአብሔር እጅ ሲባል ኃይሉ፥ ጥበቡና ደግነቱ፥ መለኮታዊ ጥበቃውና እንዲሁም የእግዚአብሔር ኃይለኛ ቅጣት ማለት ለመሆናቸው የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት።

ኀይሉ ለመኾኑ፣ "በጸናች እጅና በተዘረጋች ክንድ እስራኤልን ከመካከላቸው አወጣ" ብሏል።

ጥበቡና ደግነቱ ለመኾኑ :- "አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው" ብሎአል። (መዝ 105 ቁ. 25)

መለኮታዊ ጥበቃው ለመኾኑ :- "አቤቱ ነፍሴን ለእጆችህ እሰጣለሁ" ተብሎአል (መዝ. 31 ቁ. 5)

ኀይለኛ ቅጣት ለመኾኑ :- "በቀንና በሌሊት እጅህ ከብዳብኛለች" ተብሎአል። (መዝ 32. ቁ.4) የእግዚአብሔር ዐይንና ጆሮ ተብሎ በሚነገርበት ጊዜ ደግሞ በሰማይም ኾነ በምድር የሚደረገውን ማንኛውንም ድርጊት ኹሉ እንደሚያውቀው ለመግለጽ መኾኑን ለመረዳት የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

"የእግዚአብሔር ከሰማይ ተመለከተ የሰውንም ልጆች ኹሉ አየ ከማደሪያው ቦታ ኾኖ በምድር ወደሚኖሩ ኹሉ ተመለከተ።" (መዝ.33 ቁ.13–14)

"ጆሮን የተከለው አይሰማምን? ዐይንን የሠራው አያይምን?" (መዝ. 94 ቁ.9)

"ማንኛውም ፍጡር ከእግዚአብሔር ሊደበቅ አይችልም ኹሉም ለዐይኖቹ የተጋለጠና ያልተሰወረ ነው" (ዕብ. ም.4.ቁ.15)

ስለእግዚአብሔር ፊት የተነገሩትን ጥቅሶች በሚመለከት ደግሞ ለአብርሃም፣ ለሙሴ፣ ለዳንኤልና ለሌሎችም የእግዚአብሔር ወዳጆች አምላክ በሰው መልክ የተገለጠላቸው መኾኑ ይታወሳል። ይኹን እንጂ በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 33 ቁጥር 20 እና በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ቁ. 18 ላይ በተገለጠው መሠረት እግዚአብሔርን ማንም ያየው ሰው አለ



www.ethiopianorthodox.org

መኖሩንና ማንም ደግሞ እግዚአብሔርን አይቶት በሕይወት ሊኖር የሚችል ሰው ባለመኖሩ እነዚያ እግዚአብሔርን አዩ ተብሎ የተነገረላቸው የእግዚአብሔር ወዳጆች እግዚአብሔርን አዩት ወይም ደግሞ እግዚአብሔር እንደሰው ልጅ ውሱን የኾነ መልክና ቅርጽ አለው ለማለት አይደለም። እነዚያም የተጠቀሱት የእግዚአብሔር ሰዎች ታማኞቹ ለኹኑ ባርያዎቹ መልካም ፈቃዱን ለመግለጽ ሲል አንዳንድ ጊዜ የሚገልጥበትን ጊዜያዊ የኾነውን የሰውነት ቅርጽ አዩ እንጂ እግዚአብሔርን አላዩም።

## የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት

ቅዱስ ጎርጎርዮስ፥ ገባሬ ተአምራት :- "የሰውን ባሕርይ እስኪ ዋሐድ፥ ዘመዳቸውም ኾኖ ሰውን ኹሉ ወደ እርሱ እስኪያቀርብ ድረስ ሰው ፊትህን አይቶ ሕያው መኾን አይቻለውም ነበር።" (ሃይ. አበ. ገጽ 45)

ቅዱስ ጎርጎርዮስ፥ የእንዚናዙ :- "በባሕርየ መለኮቱ የማይታይ ሲኾን እርሱም የሌለበት ቦታ የሌለ ሲኾን በቦታው ኹሉ ሙሉ የሚኾን እርሱ እንደምን ይታያል?" (ገጽ 215)

ቅዱስ ቄርሎስ፥ ዘእስክንድርያ :- "መለኮት ልክ፥ መጠን የለውምና በአንደበት ሊነገር አይቻልም፤ ልቡናም መርምሮ አይደርስበትም።" (ሃይ አበ ፥ ገጽ 276)

"ሥጋን በመልበስ ሰው ባይኾንና በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ባይገለጥ ኖሮ ፍጡራን ሊያዩት ባልቻሉም ነበር፤ ሊያዩት የማችሉም ሰዎች ብቻ አይደሉም፤ መልካቸው ልዩ ልዩ የሚኾን የሚያመሰግኑ ረቂቃን የሚኾኑ በሰማይ ያሉ መላእክትም በነበረበት ባሕርዩ ያዩት ዘንድ ባልቻሉም ነበር እንጂ።" (ሃይ. አበ ገጽ፥ 300)

አባ ሕርያቆስ፥ዘብህንሳ :-" መጠንና መመርመር የሌለበት እሳተ መለኮት በሆድሽ አደረ። በምድራዊ እሳት እንመስለው ዘንድ አይገባም፤ለእሳትስ መጠን አለው፤ ልክም አለው። መለኮት ግን ይህን ያኽላል፣ይህንም ይመስላል ሊባል አይቻልም። ለመለኮት እንደ ፀሐይና እንደ ጨረቃ ክበብ፥ እንደ ሰውም መጠን ያለው አይደለም፤ ድንቅ ነው እንጂ፤ የሰው ሕሊና፥ የመላእክትም አእምሮ በማይደርስበት በአርያም የሚኖር ነው እንጂ። ለመለኮት ወርድና ቁመት፥ ላይና ታች፥ ቀኝና ግራ ያለው አይደለም፤ በኹሉ የመላ ነው እንጂ። ለመለኮት የሚዘረጋበትና የሚሰበሰብበት ያለው አይደለም፤ ግዛቱ ባገር ኹሉ ነው እንጂ ለመለኮት በላይ ጠፈር በታችም መሠረት ያለው አይደለም፤ ጠፈሩ እርሱ፥ መሠረቱም እርሱ ነው እንጂ። ለመለኮት ከምድር ከውስጥም የኾነውን ያነሣ ዘንድ ማጐንበስ፥ ራስንም ዝቅ ማድረግ ያለበት አይደለም፤ ለጴጥሮስ እንዳሳየው ኹሉ በእጁ የተያዘ ነው እንጂ። ለመለኮት በሚታይ ገንዘብ፥ በሚወሰንም ገንዘብ ደረትና ፊት የኋላም ጀርባ ያለው አይደለም፤ በነደ እሳት የተሸፈነ ነው እንጂ። ነደ እሳት ግን እርሱ ነው። መለኮትስ ንጹሕና ጽሩይ ብሩህም ነው።" (ቅዳሴ ማርያም ቁ. 47–53)

ቅዱስ ጎርጎርዮስ፥ (የኑሲሱ) :-"ሰማይን የፈጠረ ይህ ነው። ምድርንም የፈጠረ ይህ ነው። ለመለኮቱ ጥንት (መሠረት የለውም፤ላይ የለውም ታችም የለው ም፤ ርዝ መት የለውም፤ ቁመት የለውም፤ ቀኝ የለውም፤ ግራም የለውም፤ መካከል የለውም፤ በዓለም ዳርቻ ኹሉ የመላ ነው እንጂ።" (የጎርጎርዮስ ቅዳሴ ቁ.10)

በዚህም መሠረት ኹለቱ ወገኖች በየበኩላቸው የሌላው አስተሳሰብ ልክ አለመኾኑን በማመን እምነታቸውን ሲያብራሩ :- የመጀመሪያዎቹ ወገኖች ለእግዚአብሔር መልክና ቅርጽ እንደሌለው መናገር እግዚአብሔርን ዝርው ነው ብሎ ማመን ነው ሲሉ ኹለተኛዎቹ ወገኖች ደግሞ እኛ መርምረን ልንደርስበት የማንችለው ረቂቅ አካል ያለው ከመኾኑ በቀር ለእግዚአብሔር መልክና ቅርጽ ወስኖ መናገር እግዚአብሔርን ውሱን እንደኾነ ማመን ስለኾነ ትክክል አይደለም በማለት ኹለቱም ወገኖች የተ ለያዩ ማስረጃዎችን እያቀረቡ ይከራከራሉ።

9. በኦሪት ዘፍጥረትም ም. 1 ቁ. 31 ላይ "እግዚአብሔርም ያደረገውን ኹሉ አየ፤ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ" ካለ በኋላ በምዕራፍ 6 ቁ. 6 ላይ ደግሞ " እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፤ በልቡም አዘነ" በማለቱ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።



www.ethiopianorthodox.org

የፈጠረውን ፍጥረት መልካም እንደኾነ ያየው አፈጣጠሩን ነው እንጂ የሰው ልጅ ከዚያ በኋላ ኀጢአት አይሠራም ወይም ደግሞ የሰው ልጅ ወደፊት ኀጢአተኛ እንደሚኾን እግዚአብሔር አያውቅም ለማለት አይደለም። እግዚአብሔር የዕውቀት ኹሉ ምንጭ በመኾኑ ለነቢያት፥ ለጻድቃን፥ ለወዳጆቹና ለሌሎችም ሰዎች ወደፊት የሚኾነውን ኹናቴ በራእይና በሕልም የገለጸላቸውና የሚገልጽላቸው እርሱው ነው። እግዚአብሔር የጸጸትና የኀዘን ስሜቶች የሌሉበት መኾኑ ቢታወቅም ለሰው ልጆች በሚገባ ቋንቋ ለመግለጽ ታስቦ ተጸጸተ፥ አዘነ፥ ተባለ። ወደፊት የሚኾነውን ኹሉ ያውቃል፤ ባደረገውም ነገር ከቶ አይጸጸትም፤ ኾኖም ከኀጢአት ርቀን የጽድቅን መንገድ ብቻ እንድንከተል የእግዚአብሔር ፍላጎት ነው። ይህንኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሰው ልጅ ቋንቋ ለመግለጽ ታስቦ ተጸጸተ፤ አዘነ ተባለ። አንዳንዶች እንደሚመስላቸው በእውነት የተጸጸተ ቢኾን ኖሮ ቀድሞ ከፍ ያደረገውንና የወደደውን፥ ነገር ግን በኀጢአቱ ምክንያት የሞት ፍርድ የፈረደበትን የሰውን ልጅ ለማዳን ሥጋ ለብሶ ቤዛ ባልኾነውም ነበር። ይህም ቤዛነት ቀድሞ የነበረው የእግዚአብሔር ፍቅር ያልተለወጠና በእግዚአብሔርም ዘንድ መለወጥና መጸጸት አለመኖራቸውን ያረጋግጥልናል።

በዚህም መሠረት ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒነት የሌላቸው መኾናቸውን ተረድተን ከመሳት እንጠንቀቅ።

10. በኦሪት ዘፍጥረት ም.2 ቁ.2 ላይ :- "እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ዐረፈ" ካለ በኋላ በትንቢተ ኢሳይያስ ም. 40 ቁ.28 ላይ ደግሞ "እግዚአብሔር አይደክምም፤ አይታክትም" በማለት ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።

እግዚአብሔር ዐረፈ የተባለው ፍጥረቱን ፈጥሮ ከፈጸመ በኋላ መፍጠሩን አቆመ ለማለት ነው እንጂ የድካም ዕረፍት ዐረፈ ለማለት አይደለም።

11. በኦሪት ዘፍጥረት ም. 2. ቁ. 17 ላይ "መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" ተብሎ የተነገረ ሲኾን በም.5 ቁ. 5 ላይ ደግሞ አዳም የሞተው በ930 ዓመቱ መኾኑ ተገልጾአል። የእግዚአብሔር ቃል የማይለወጥ እንደመኾኑ እንዴት አዳም የተከለከለውን ፍሬ በበላ ጊዜ አልሞተም ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።



እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው እርሱ ብቻ በሚያውቀው ዘዴ በሕይወት ሊያኖረው እንጂ እንዲሞት ያልነበረ መኾኑ ይገመታል። መኖርን ወይም መሞትን እንዲመርጥ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ነጻ ፈቃድን ሰጠው። ኀጢአትን ሠርቶ መሞትን ስለመረጠ ግን የሞት ፍርድ የተፈረደበት "አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ" ተብሎ ነው (ዘፍ. ም. 3. ቁ. 11) ከእርሱ በበላህ ቀን የተባለው በበላበት ቀን ይሞታል ማለት ሳይኾን ከዚያን ቀን ጀምሮ የሞት ኀይል በሰው ላይ መሠልጠኑን ለማመልከት ነው። (ሮሜ. ም.5 ቁ. 12–21) ሞት ሲባል ደግሞ ሥጋዊ ሞት ማለት የነፍስ ከሥጋ መለየት ብቻ አይደለም። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. 2 ቁ. 1 ላይ "እናንተ በበደላችሁና በኀጢአታችሁ ምክንያት ሞታችሁ ነበር" በማለት በደልንና ኀጢአትን እንደሞት የሚቆጥራቸው መኾኑን ገልጾአል።

ስለዚህ አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስ ከበሉበት ቀን ጀምሮ የሞት ፍርድ በእነርሱ ላይ ሰለጠነ ለማለት ነውና ኹለቱ ጥቅሶች ልዩነት የላቸውም።

12. በኦሪት ዘፍጥረት ም. 3 ቁ. 21 "እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሔዋን ቆዳ ልብስ አለበሳቸው" በምዕራፍ 9 ቁ. 23 ላይ "ሴምና ያፌትም ልብስ በስተኋላቸው በትከሻቸው ያዙ፤ ወደ ድንኳኑም የኋሊት ኼዱና የአባታቸውን ራቁትነት እንዳያዩ ፊታቸውን አዙረው ሐፍረተ ሥጋውን ሸፈኑ፤" በትንቢተ ዕንባቆም ም. 2 ቁ. 5 ደግሞ " ተዋርዶ ሐፍረተ ሥጋው ሲገለጥ ለማየት ለባልንጀራህ ጠንካራ መጠጥ የምትሰጥና እስኪሰክርም ድረስ የምታጠጣው አንተ ሰው ወዮልህ" የሚሉት ሦስት ጥቅሶች የሚያመለክቱት ራቁትነት በእግዚአብሔርም ኾነ በሰው ዘንድ ጸያፍ መኾኑን ሲኾን በትንቢተ ኢሳይያስ ም. 20 ላይ እንደሚነበበው ነቢዩ ኢሳይያስ ጫማውንና የማቅ ልብሱን እንዲያወልቅ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ተገልጦአል። ነቢዩ ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ እርቃኑን በባዶ እግሩ ይመላለስ ነበር ተብሏል። እግዚአብሔርም "አገልጋዬ ኢሳይያስ እርቃኑን በባዶ እግሩ ሦስት ዓመት ሙሉ ሲመላለስ ነበር፤ በግብጽና በኢትዮጵያ ላይ የሚደርስባቸውም ምልክት ይኸው ነው" ብሎአል።



www.ethiopianorthodox.org

ታዲያ እግዚአብሔር እንዴት ኢሳይያስን ራቁቱን እንዲኾን አዘዘው።

እግዚአብሔር ኢሳይያስን ያዘዘው ከላይ ያለውን የማቅ ልብሱን እንዲያወልቅ ነው እንጂ የሐፍረተ ሥጋ መሸፈኛ የኾነውን ከውስጥ የለበሰውን ልብስ እንዲያወልቅ አይደለም። የዚህ ትእዛዝ ዓላማ በግብጽና በኢትዮጵያ ላይ ሊደርስባቸው ያለውን ውርደት ለማመልከት ነው። ይህም እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት ወደፊት ሊፈጸም ያለውን ኹናቴ ከሚገልጽባቸው አንዱ መንገድ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች የወደፊቱን ኹናቴ በምሳሌ ለመግለጽ ነው እንጂ ለማራቆት ብሎ አይደለም።

በዚህም መሠረት ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

13. "እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ኾነ።" (ዘፍ. ም.3 ቁ. 22)

የተከለከለውን ዛፍ ፍሬ ቢበላ እንደሚሞት ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ሲኾን አሁን ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አፍርሶ ያንን ፍሬ በመብላቱ አዳም እንደ እግዚአብሔር ዐዋቂ የመኾን ዕድል ካጋጠመው ትእዛዝ አፍራሹነቱ ጠቀመው እንጂ አልጐዳውም የሚል ትችት ይሰነዘር ይኾናል።

አዳም በትእዛዝ አፍራሽነት ኀጢአት ከመውደቁ በፊት ክፉ ነገር መኖሩን አያውቅም ነበር። ክፉ ነገር ሊገለጥለት የበቃውና በዕራቁትነቱ ሐፍረት የተሰማው አትብላ የተባለውን ፍሬ በመብላት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ካፈረሰ በኋላ ነው።

የመጀመሪያው አዳም በትእዛዝ አፍራሽነቱ ለአጠፋው ጥፋትና ለበደለው በደል ምንም ኀጢአት የሌለበት ክርስቶስ ዳግማዊ አዳም ኾኖ በቤዛነት መሞቱ አዳምን ወደ ቀድሞ ርስቱ ለመመለስ ነው። (ሮሜ. ም. 5 ቁ. 17)



አዳም ኀጢአትን እስካልሠራበት ጊዜ ድረስ ማለት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በማፍረስ የሞትን ፍርድ እስካልተቀበለበት ጊዜ ድረስ ክፉ ነገርን ስለአላየ ክፉውን ከደጉ ለይቶ ለማወቅ አይችልም ነበር። ከዚያ በኋላ ግን የተፈጥሮ ዳኛ የኾነው ሕሊናው በደለኛነቱን ስለገለጸለት ክፉ የሠራ መኾኑን ለማወቅ ቻለ።

ሰይጣንም በእባብ አድሮና እባብን መስሎ ክፉንና ደግን በማወቅ እንደ እግዚአብሔር ትኾናላችሁ በሚል የማግባቢያ ቋንቋ የተከለከለውን ፍሬ በልተው ትእዛዝ አፍራሽነትን የመሰለ ክፉ ነገር እንዲያውቁ አድርአቸዋል። አዲስ ያወቁት ዕውቀት ክፉውን ነገር ነው እንጂ ደጉ ነገርማ ቀድሞውንም ቢኾን ከእነርሱ ጋር ነበር።

አዳምም ትእዛዝ በማፍረሱ የሞትን ፍርድ በራሱና በዘሩ ኹሉ ላይ እንዲደርስ አድርጓል፤ እርግማንንም ተረግሞአል። ኑሮውም በግንባሩ ላብ ማለት በከፍተኛ ድካም እንዲኾን ተደርጓል።

ስለዚህ አዳም ክፉ ነገርን ማወቁ የሕሊና ዕረፍትን እየነሣ ከሚያሰቃየው በቀር ምንም የጠቀመው ነገር እንደሌለ መገንዘብ አለብን። ክፉ ነገር በማይታወቅበት ዓለም ውስጥ ኖሮ ቢኾን ያለምንም ችግርና ያለ ምንም ጭንቀት በደስታ በኖረ ነበር። እርሱ ግን የእባብን ምክር በማስማት ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ተቃራኒ የኾነ ድርጊት በማድረጉ የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል፤ እርግማንን ተረግሞአል፤ እንዲሁም በጊዜው ክፉ ነገርን የማወቅ ችግር ደርሶበታል።

ስለዚህ ትእዛዝ አፍራሽነቱ ጐዳው እንጂ ምንም እንዳልጠቀመው መረዳት አለብን።

14. "እግዚአብሔር አምላክም አለ፥ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ኾነ፤ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፥ ደግሞ ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፥ ለዘላለምም ሕያው ኾኖ እንዳይኖር፥ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከዔደን ገነት አስወጣው፤ የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ" (ዘፍ. ም. 3 ቁ. 22–23)



www.ethiopianorthodox.org

አዳም ሕያው ኾኖ ለዘላለም ቢኖር እግዚአብሔርን ምን ይጐዳ ዋልና ነው እንደዚህ ያለውን ውሳኔ የወሰነበት ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ማንኛውም ፍጡር ቢኾን ራሱን ይጐዳል እንጂ እግዚአብሔርን ሊጐዳ አይችልም። የእግዚአብሔር አባባልግን ኹለት አማራጭ ትርጓሜዎች አሉት።

የመጀመሪያው ትርጓሜ ደጉንና ክፉውን ለይታ ከምታስታውቀዋ ዛፍ በቀር በገነት ያሉትን የዛፍ ፍሬዎች ኹሉ እንዲበላ ተፈቅዶለት ነበር ይህም ማለት ከሕይወት ዛፍም እንዲበላ ተፈቅዶለት ነበር ማለት ነው። ምክንያቱም በኦሪት ዘፍጥረት ም.2 ቁ. 9 ላይ በገነት ከነበሩት ዛፎች መካከል የሕይወት ዛፍም የነበረ መኾኑ ተገልጾ ሳለ በቁ. 16 እና 17 ላይ እንደተገለጸው ክፉውንና ደጉን ለይቶ ከሚያስታውቀው በቀር በገነት ውስጥ ከሚገኙት ዛፎች ፍሬ ኹሉ እንዲበላ የተፈቀደለት መኾኑ ነው።

እግዚአብሔር ቸርና ሰውን የሚወድድ በመኾኑ አዳም ከነኀጢአቱና ከተላለፈበትም የእርግማን ፍርድ ጋር ለዘላለም በመኖር የሰይጣን ተገዢ እንዲኾን ስላልፈቀደና በልጁ ቤዛነት በኋላ ዘመን ሊያድነው ስለፈቀደ የሕይወት ዛፍን እንዳይበላ የሕይወት ዛፍ ካለበት ከገነት እንዲወጣ አደረገው። ያለበለዚያ ግን ጌታ የማይሞተውን የሰውን ሥጋ ለብሶ በመሞት ቤዛ ባልኾነውም ነበር።

ሌላው ትርጓሜ ደግሞ የሕይወት ዛፍ ይተባለው ምሰሌያዊ አነጋገር ነው እንጂ እውነተኛ ዛፍ አይደለም። የመኖር ዕድል ተሰጥቶት የነበረው አዳም በኀጢአቱ ምክንያት ከዘላለም ሕይወት ወደ ሟችነት መዛወሩን ያመለክታል የሚል ነው። ይህን አባባል ሐዋርያው ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ ሲያጠናክረው እንዲህ ብሏል "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለዉን ጆሮ ያለው ይስማ፤ ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወ ት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ"። (ራ.ዮ.ም.2 ቁ:7 )

ስለዚህ በኦሪት ዘፍረት ም: 3 ቍ. 22 – 23 የተነበበው ጥቅስ የሚያመለክተው ከላይ ከተገለጹት ትርጓሜዎች አንዱን ነው እንጂ ሌላ አለመኾኑን ተረድተን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።



15. በኦሪት ዘፍጥረት ም.4. ቁ:15 ላይ " እግዚአብሔርም ቃየንን ያገኘው ኹሉ እንዳይገድለው ምልክት አደረገለት" የሚለው በምዕራፍ 9 ቁ :6 ላይ "የሰውን ደም የሚያፈስስ ኹሉ ደሙ ይፈስሳል።" ከሚለው አባባል ጋር ተቃራኒ ይመስለን ይኾናል።

አብዛኞዎቹ የሕግ አንቀጾች የሚደነገጉት ለነዚያ ጉዳዮች አስፈላጊ የኾኑ ኹናቴዎች ሲከሠቱ ነው። በዚህም መሠረት ከቃየን በፊት ሌላ ነፍሰ ገዳይ ስላልነበረና ነፍሰ ገዳይንም በሚመለከት ገና ሕግ ያልተደነገገ በመኾኑ እግዚአብሔር በኋላ በኖኅ ዘመን የሰጠውን ሕግ በቃየን ላይ እንዲሠራ አላደረገውም። ኾኖም በምድር ላይ ኰብላይና ተቀበዝባዥ እንዲኾን በእርግማን ቅጣት ሊቀጣ የበቃው የሕሊናው አስተዋይነት የተፈጥሮ ዳኛ ኾኖ ከነፍሰ ገዳይነት ሊገታው ይገባ ስለነበረና ይህም ባለመኾኑ ነው። ምንም እንኳ ቃየን በነበረበት ዘመን የሰውን ደም የሚያፈስስ ደሙ ይፈስሳል የሚለው የወንጀለኛ መቅጫ ደንብ ባለመደንገጉ ቃየንን ያገኘው ኹሉ እንዳይገድለው እግዚአብሔር ምልክት ቢያደርግለት ቅጣቱ የተለየ ይኹን እንጂ ሳይቀጣው አላለፈም። ይህንንም ምክንያት ሲያብራራ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሏል "ሕግ የሌላቸዉ አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸውም እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፥ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው አሳባቸው እርስ በርሱ ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።" (ሮሜ ም.2 ቁ:14—151)

ጌታ ለፈሪሳውያን ጥያቄ በሰጠው መልስ ላይ በተፈጥሮ ሕግ ማለት በሕሊና ፍርድና በቀጥታ በተሰጡት ሕጎች መካከል ልዩነቱን ሲያመለክት "ዕውሮች ብትኾኑማ ኖሮ ኀጢአት ባልኾነባችሁም ነበር፤ አሁን ግን እናያለን ስለምትሉ ኀጢአተኞች ኾናችሁ ትቀራላችሁ አላቸው።" (ዮ. ም.9 ቁ:41 )

በምዕራፍ 15 ቁ:22 ላይ ደግሞ፤ "እኔ መጥቼ ባልነገራቸው ኖሮ ኀጢአት ባልኾነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን ለኀጢአታቸው ምክንያት የላቸ ውም።" ብሏል።

ስለዚህም የትክክለኛ ፍርድ ባለቤት የኾነው ፈጣሪ አምላክ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ባልነበረበት ጊዜ በኋላ ዘመን በተሰጠው ሕግ ላይ



www.ethiopianorthodox.org

ተመርኩዞ ቅጣትን ላለመወሰንና ኾኖም ግን በሕሊና ሕጋቸው መሠረት ተገቢውን ቅጣት ለመወሰን ያደረገው እንጂ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒዎች ኾነው አይደሉም።

16. በኦሪት ዘፍጥረት ም.5 ቁ: 24 ላይ ሔኖክ አካኼዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና፤ እንዲሁም በኹለተኛው መጽሐፈ ነገሥት ም.2. ቁ:11 ላይ "ሲኼዱም እያዘገሙም ሲጫወቱ እነሆ፣የእሳት ሠረገላና የእሳት ፈረሶች በመካከላቸው ገብተው ከፈሉአቸው፤ኤልያስም በአውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ወጣ።" በሚሉትና በዮሐንስ ወንጌል ም.3 ቁ:13 ላይ " ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም" በሚለው ጥቅስ መካከል ያለ ውግንኙነትና ልዩነት እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

እነዚህን ተቃራኒ መሰል ጥቅሶች በሚመለከት ኹለት የተለያዩ ወይም አማራጭ ትርጓሜዎች ይቀርባሉ።

የመጀመሪያው ትርጓሜ :- ከሰው ልጆች መካከል ማንም ወደ ሰማይ ወጥቶ እግዚአብሔርንና ሰማያዊ ኹኔታዎችን ካየ በኋላ ወደዚህ ዓለም ተመልሶ የተናገረ ወይም የመሰከረ የለም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሰማያዊ እንደመኾኑና በመለኮታዊ ጠባዩም በኹሉም ቦታ የሚገኝ እንደ መኾኑ ስለሰማያዊ ኹናቴ ይናገራል። የጥቅሱንም አመጣጥ ብናስተውል በቁጥር 12 ላይ "ስለምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ።" ካለ በኋላ ነው ማንም ወደ ሰማይ የወጣ የለም ያለው። ሔኖክና ኤልያስ እግዚአብሔር ወደ ሰማይ አወጣቸው እንጂ በራሳቸው ወደ ሰማይ ወጥተው እግዚአብሔርንና የሰማዩን ኹናቴ ከአዩ በኋላ ወደ ምድር ተመልሰው ምስክርነት የሚሰጡ አይደሉም። እንዲያውም አንድ ልጁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የገለጸው ከመኾኑ በቀር እግዚአብሔርን ማንም ያላየው መኾኑ በዮሐንስ ወንጌል ም.1 ቁ:18 ላይ ተገልጾአል።

ኹለተኛው ትርጓሜ :- በአንዳንድ የሃይማኖት ሰዎች ዘንድ ሰባት ሰማያት እንዳሉ ይነገራል። በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ ቢኾን ስንት መኾናቸው አልተገለጸም እንጂ ሰማዮች መኖራቸው ተጠቁሟል። ለምሳሌ በመጽሐፈ ነህምያ ምዕራፍ 9 ቁ:6 ላይ የሰማያት ሰማይ መኖሩ ተገልጾአል።



ኹለተኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው በሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.12 ቁ: 2 - 4 ስለ ሦስተኛው ሰማይ ተጠቅሶአል። በዚህም መሠረት እነ ኤልያስ የወጡበት ሰማይና ጌታ የተናገረው ሰማይ የተለያዩ ሰማዮች ናቸው ማለት ነውና ጥቅሶቹ ተቃራኒዎች አይደሉም።

17. በኦሪት ዘፍጥረት ም.6 ቁ:3 ላይ "እግዚአብሔርም መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፣ እርሱ ሥጋ ነውና ዘመኖቹም መቶ ኻያ ዓመት ይኾናሉ አለ" ካለ በኋላ በምዕራፍ 11 ቁ:10 – 32 እንደተዘረዘረው ደግሞ ብዙዎች ሰዎች ከመቶ ኻያ ዓመት ዕድሜ በላይ የኖሩ መኾናቸው በመገለጹ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።

መቶ ኻያው ዓመት የተወሰነው ኀጢአተኞችን ኹሉ ለንስሓ መግቢያ ጊዜ ዕድል ለመስጠት ስለ ጥፋት ውሃ ለኖኅ ከተነገረበት ጊዜ ጀምሮ ኖኅ መርከቢቱን ሠርቶ ወደ መርከብ ውስጥ እስከገባበት ድረስ ያለው ጊዜ ነው እንጂ የሰው ኹሉ ዕድሜ በመቶ ኻያ ዓመት ተወሰነ ማለት አይደለም።

ኖኅ የአምስት መቶ ዓመት ሰው የነበረ መኾኑ በምዕራፍ 5 ቁ:32 ላይ ተገልጾ ሳለ በምዕራፍ 7 ቁ:6 ላይ የጥፋት ውሃ በምድር ላይ በመጣ ጊዜ ኖኅ የስድስት መቶ ዓመት ዕድሜ ስለነበረው ከላይ የተጠቀሰው ጊዜ አንድ መቶ ኻያ ዓመት መኾኑ ቀርቶ አንድ መቶ ዓመት ብቻ ማለት ይኾናል የሚል ክርክር የሚያነሣ ሰው ሊኖር ይችላል።

በምዕራፍ 5 ውስጥ የተገለጸው የትውልድ ሐረግን በሚመለከት እንጂ ስለጥፋት ውሃ የሚያወሳ አይደለም። ኖኅ ሦስቱን ልጆቹን መውለድ የጀመረው ወይም የጨረሰው ዕድሜው አምስት መቶ ዓመት በነበረው ጊዜ ነው ማለት ነው እንጂ ስለጥፋት ውሃ የተነገረው በዚያን ጊዜ ነው ማለት አይደለም።

ስለዚህ የአምስት መቶ ዓመት ዕድሜና የስድስት መቶ ዓመት ዕድሜ ጉዳይ የተነሡባቸው ምክንያቶች የተለያዩ በመኾናቸው የመቶ ኻያ ዓመቱን ውሳኔ ከኹለቱ ኹናቴዎች ጋር ማያያዝ ተገቢ አይደለም።



www.ethiopianorthodox.org

18. በኦሪት ዘፍጥረት ም.6 ቁ:4 ላይ "ከዚያ በኋላ የሕግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ" ሲል የእግዚአብሔር ልጆች የተ ባሉት እነማን ናቸው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ከአዳም ልጆች መካከል የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት የሴት ልጆች ሲኾኑ የሰው ልጆች የተባሉት ደግሞ የቃየን ልጆች ናቸው። የእግዚአብሔር ልጆችም የተባሉት በነፍስ ገዳይነቱ ከተወገዘው ከቃየን ልጆች ለመለየት ነው። ይህንኑም መሠረት በማድረግ ወንጌላዊው ሉቃስ የመድኀኒታችንን የዘር ሐረግ በሚዘረዝርበት ጊዜ ሴት የአዳም ልጅ ካለ በኋላ አዳም የእግዚአብሔር ልጅ ማለቱን በሉቃስ ወንጌል ም.3 ቁ:38 እንመልከት።

አንዳንድ ሰዎች እንደመሰላቸው ደግሞ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት መላእክት ናቸው። ይህ ግን ትክክለኛ አስተሳሰብ አለመኾኑን ለመገንዘብ የመድኀኒታችንን ማረጋገጫ እንመልከት። በትንሣኤ ሙታን የማያምኑት ሰዱቃውያን ጌታን በጠየቁት ጊዜ "መጻሕፍትንና የእግ ዚአብሔርን ኀይል ካለማወቃችሁ የተነሣ ትስታላችሁ፤ ሙታንስ ሲነሡ እንደ እግዚአብሔር መላእክት ይኾናሉ እንጂ አያገቡም ወይም አይ ጋቡም" ብሎ መልስ ሰጥቶአቸዋል። (ማቴ. ም.22 ቁ:29 – 30) በእ ርግጥ በመጽሐፈ ኢዮብ ም.1 ቁ:6 ላይ መላእክት የአምላክ ልጆች ተብ ለው መጠራታቸው ተመዝግቦአል። ይህ ግን ለሌላ ጉዳይ ነው እንጂ ጋብቻን በተመለለከተ ስላልኾነ ከአሁኑ አባባል ጋር ተመሳሳይ አይደ ለም።

ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት የሴት ልጆች የሰው ልጆች የተባሉት ደግሞ የቃየን ልጆች መኾናቸውን ማወቅ አለብን።

19. በኦሪት ዘፍጥረት ም.6 ቁ:9 ላይ ኖኅ፥ በሉቃስ ወንጌል ም.1 ቁ:6 ላይ ደግሞ ዘካርያስና ኤልሣቤጥ ጻድቃን የተባሉ ሲኾኑ በመዝሙር 14 ቁ:1 እና ወደ ሮሜ ሰዎች በተላከው በሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.3 ቁ:12 እንዲሁም በመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት ም.1 ቁ:7 – 10 ላይ ደግሞ ማንም ጻድቅ የሌለ መኾኑ ተገልጾአል። በዚህም ምክን ያት ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።



ሐዋርያው ጳውሎስ የሰውን ኹሉ ኀጢአተኛነት በበለጠ ሲያብራራ "ስለዚህ በአንድ ሰው ምክንያት ኀጢአት ወደ ዓለም እንደገባና በኀጢአ ትም ምክንያት ሞት እንደገባ እንዲሁም ኹሉም ኀጢአትን ስላደረጉ ሞት በሰው ኹሉ ላይ ደረሰ" ብሏል። (ሮሜ ም.5 ቁ:12) እንዲሁም በመጽሐፈ ኢዮብ ም.15 ቁ:15 ላይ በእግዚአብሔር ፊት ሰማያት እንኳ ንጹሓን እንዳልኾኑ ተገልጾአል።

ኖኅ፥ ዘካርያስና ኤልሣቤጥ በጊዜያቸው ከነበሩት ሰዎች ተሽለው በመገኘታቸው ጻድቃን ተባሉ እንጂ ከእግዚአብሔር ፍጹምነት ጋር ሲነ ጻጸር አሁንም ቢኾን ማንም ጻድቅ የለም። ለምሳሌ ሙሴን የመሰለ ታላ ቅ ነቢይና የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጅ በመሪባ ውሃ ጉዳይ መበደሉ ይታወሳል። እንዲሁም በምሳሌነት የሚጠቀሰው ታላቁ ንጉሥ ዳዊት በኦሪዮ ላይ ባደረሰው ግፍ ምክንያት ቅጣትና ተግሣጽ የደረሰበት መኾኑን በኹለተኛው መጽሐፈ ሳሙኤል ም.12 ቁ:1 – 23 እንመልከት። ይኸው ዳዊት ነው " ከልቤ የምወደውን ፈቃዴንም የሚፈጽመውን የእሴ ይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ" ተብሎ በእግዚአብሔር የተመሰከረለት። (የሐ. ሥ.ም. 13 ቁ: 22) ይህ አባባል የሚያመለ ክተው ማነኛውም ሰው ጻድቅ የሚል ቅጽል ስም የሚሰጠው ከሌሎች ሰዎች ጋር በማነጻጸር ነው እንጂ ፍጹም የኾነ ጽድቅ ያለው ሰው አለ ለማለት አለመኾኑን ነው። በዚህም መሠረት ሙሴም ኾነ ዳዊት የሚታወ ቁት የእግዚአብሔር የቅ ርብ ወዳጆች በመባል ነው።

ስለዚህ አንዳንድ ሰዎች በየዘመኑ ከሚገኙት ሌሎች ሰዎች ጋር በማ ነጻጸር ጻድቃን ይባላሉ እንጂ ከእግዚአብሔር በቀር ፍጹም ጻድቅ አይ ገኝም። ይህንንም አባባል ሐዋርያው ዮሐንስ በመጀመሪያ መልእክቱ ም.1 ቁ: 8 ላይ ሲያረጋግጥው "ኀጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናታልላለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም" ብሏል።

20. በኦሪት ዘፍጥረት ም.6 ቁ:19 ላይ "ከአንተ ጋር በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ሥጋ ካለው ከሕያው ኹሉ ኹለት ኹለት እያደረግህ ወደ መርከብ ታገባለህ፤ ተባትና እንስት ይኹን" ይልና በምዕራፍ 7 ቁ:2 እና 3 ላይ ደግሞ "ከንጹሕ እንስሳ ኹሉ ሰባት ሰባት ተባትና እንስት፥ ንጹሕ ካል ኾነ እንስሳም ኹለት ኹለት ተባትና እንስት፥ ከሰማይ ወፍ ደግሞ ሰባት



www.ethiopianorthodox.org

ሰባት ተባትና እንስት እያደረግህ በምድር ላይ ዘር ይቀር ዘንድ ለአንተ ትወስዳለህ" በማለቱ አባባሎቹ ልዩነት ያላቸው ይመስላል።

ኹለቱ የአምላክ ትእዛዞች ተቃራኒዎች ሳይኾኑ የመጀመሪያው ትእዛዝ በአጠቃላይና ኹለተኛው ትእዛዝ ደግሞ በዝርዝር የቀረበ ነው። ይህ መኾኑንም ለማረጋገጥ በምዕራፍ 7 ቁ:8 እና 9 ላይ "ከንጹሕ እንስሳ፥ ንጹሕም ካልኾነው እንስሳ፥ ከወፎችና በምድር ከሚንቀሳቀሰ ውም ኹሉ እግዚአብሔር ኖኅን እንዳዘዘው ኹለት ኹለት ተባትና እን ስት እየኾኑ ወደ ኖኅ መርከብ ውስጥ ገቡ" የሚለውንና በተመሳሳይ ኹኔ ታም ከቁጥር 13 እስከ 16 የተዘረዘረውን ብንመለከት ኹለት ኹለት ተብሎ እናገኘዋለን።

ስለዚህ ሰባት የተባለው የእንስሳቱ ዐይነት ብዛት ሲኾን ኹለት ኹለ ት ማለቱ ደግሞ ተባትና እንስት መኾን ያለባቸው መኾኑን ለመግለጽ ነውና ጥቅሶቹ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

21. በኦሪት ዘፍጥረት ም.9 ቁ: 25 ላይ "ከነዓን ርጉም ይኹን፤ ለወንድ ሞቹም የባሪያዎች ባሪያ ይኹን" ተብሎ በአባቱ በካም ፈንታ የተረገመ ሲኾን በትንቢተ ሕዝቅኤል ም.18 ቁ:20 ላይ "ኀጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች፤ ልጅ የአባቱን ኀጢአት አይሸከምም፤ የጻድቁ ጽድ ቅ በራሱ ላይ ይኾናል" ተብሎ በመነገሩ አባባሎቹ ተቃራኒዎች ይመስሉ ን ይኾናል።

በመጀመሪያ ኖኅ የካምን ስም ሳይጠራ የከነዓንን ስም በመጥራት የተራገመው በዚሁ ምዕራፍ ቁ:1 ላይ እግዚአብሔር አምላክ የኖኅን ልጆች ስለባረካቸው እግዚአብሔር የባረከውን ደግሞ እርሱ ሊረግም ስለማይችል ነው። ኾኖም ግን ካም አንድ ዐይነት ቅጣት የሚገባው ኾኖ ስላገኘው የሚወደውንና ተስፋ የሚያደርገውን ልጁን ረገመበት።

በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳ እርግማኑ የከነዓንን ስም በመ ጥራት ቢፈጸም ከነዓንን ራሱን ለመርገም ሳይኾን የከነዓን ልጆች ማለት ከነዓናውያን ወደፊት ምን እንደሚያደርጉና ምን እንደሚደርስባቸው የሚናገር ትንቢት ነው። እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጆች የከነዓንን ምድር እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል። (ዘፍ.ም. 15 ቁ: 16)



በኦሪት ዘሌዋውያን ም.18 ቁ: 24 — 25 ላይ "በእነዚህ ኹሉ ከፊታቸሁ የማሳድዳቸው አሕዛብ ረክሰዋልና በእነዚህ ነገሮች ኹሉ አትርከሱ። ምድሪቱም ረከሰች፤ ስለዚህ ኀጢአትዋን በእርስዋ ላይ እመ ልሳለሁ፤ ምድሪቱም የሚኖሩባትን ሰዎች ትተፋለች" የሚለውና በኦሪት ዘዳግም ም.9 ቁ:5 ላይ ደግሞ "ምድራቸውን ትወርሳት ዘንድ የምት ገባው ስለ ጽድቅህና ስለልብህ ቅንነት አይደለም። ነገር ግን አምላክህ እግዚአብልር ከፊትህ በሚያጠፋቸው በእነዚያ አሕዛብ ኀጢአት ምክ ንያትና ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ፥ ለያዕቆብም የማለላቸ ውን ቃል ይፈጽም ዘንድ ነው" ተብለው የተነገሩት ጥቅሶች የኖኅን ትንቢ ታዊ አነጋገር ያረጋግጣሉ። ይህም በመኾኑ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ እን ዳልኾኑ መታወቅ ይኖርበታል።

22. በኦሪት ዘፍጥረት ም.11 ቁ:36 ላይ ሎጥ የአብርሃም የወንድሙ ልጅ መኾኑ ተገልጾ ሳለ በምዕራፍ 14 ቁ:14 ላይ ወንድሙ የተባለው እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።በአይሁድ ልማድ በዚህ ረገድ ግን በብዙ የምሥራቅ አገሮች ልማድ የቅርብ ዘመድ የኾነ ሰው ወንድም ወይ ም እኅት መባሉ የተለመደ ባህል ነው። ለምሳሌ ሲዴቅያስ የኢዮአኪን አጐት መኾኑ በኹለተኛው መጽሐፈ ነገሥት ም.24 ቁ:17 የተገለጸ ኾኖ ሳለ በኹለተኛው ዜና መዋዕል ም.31 ቁ:10 ላይ ወንድሙ ተብሎ እናገ ኘዋለን።

ስለዚህ ሎጥና አብርሃም የቅርብ ዘመዳሞቹ ስለኾኑ በባህሉ መሠ ረት ወንድማማች ተብለዋል ማለት ነውና ጥቅሶቹ ርስበርሳቸው የሚቃረ ኑ ኾነው አይደለም።

23. በኦሪት ዘፍጥረት ም.12 ቍ. 11 እንዲሁም በም. 20 ቍ. 2 ላይ አብርሃም ሚስቱን ሣራን እኅቴ ናት እንዳለው ኹሉ ልጁ ይስሐቅም በም ዕራፍ 26 ቁ:7 ላይ ሚስቱን ርብቃን እኅቴ ናት በማለት ዋሽቶአል። ሐሰ ትን መናገር የእግዚአብሔር ወዳጆች በመባል ከሚታወቁት ከአብር ሃም ና ከይስሐቅ የሚጠበቅ አድራጎት ነው ወይ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በአንድ በኩል ከእግዚአብሔር በቀር የሰው ልጅ ፍጹምነት የሌለው መኾኑ በተራ ቁጥር 19 የተዘረዘረው እንደተጠበቀ ኾኖ በሌላ በኩል ደግሞ አብርሃምም ኾነ ይስሐቅ ውሸትን የተናገሩ አይደሉም። ሣራ



www.ethiopianorthodox.org

ከእናቱ ባትወለድም የአብርሃም የአባቱ ልጅ መኾንዋ በምዕራፍ 20 ቁ:12 ላይ ተገልጾአል። ቀደም ተብሎ በተራ ቁጥር 22 ላይ እንደ ተገለ ጸው በምሥራቅ አገር ሕዝብ ባህል የቅርብ ዘመድ የኾነ ሰው ወንድም ወይም እኅት መባሉ የተለመደ በመኾኑና ርብቃም የይስሐቅ አጐት የልጅ ልጅ ስለኾነች እኅቴ ብሎ ጠራት (ዘፍ. ም.11 ቁ:26 እና ም.24 ቁ:27 )

24. በኦሪት ዘፍጥረት ም.17 ቁ:8 ላይ "በእንግድነት የምትኖርባት የከነዓን ምድር ኹሉ ለዘላለም ግዛት ይኾንህ ዘንድ ከአንተም በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ፤ አምላክም እኾናቸዋለሁ:" ብሎ ፈጣሪ አምላክ ለአብርሃም የገባውን ቃል መነሻ በማድረግ ይህ የተሰጠው ተስፋ በሙሉ የተፈጸመ አይደለም፤ ምክንያቱም አብርሃም በእንግድነት እንጂ አልኖ ረባትም፤ ዘሩም ቢኾን በከፊል እንጂ በሙሉ አላገኘውም፤ ያውም ለዘላለም አይደለም በማለት የሚተቹ ወገኖች አሉ።

ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ ለልጆቹ መሰጠቱን የሚያመለክት ነው። ይህም ተስፋ እንዴት ተፈጻሚነትን እንዳገኘ ለመረዳት የኢያሱ ወልደ ነዌንና የሳሙኤልን መጻሕፍት ማንበብ ያስፈልጋል። ይኹን እንጂ እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው የገባውን ቃል ኪዳን ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ የሚያውለው እነርሱም በበኩላቸው የእግዚአብሔርን ትሕዛዝ ሲያከብሩ ብቻ መኾኑንና ያለበለዚያ ግን ጠላቶቻቸው የደረሰባቸው ዕድል ፈንታ እነርሱም እንደሚደርስባቸው የተነገራቸው መኾኑን በኦሪት ዘሌዋውያን ም.18 ቁ:24 እና 28 ም.26 ቁ: 15 — 41 መመልከት እንችላለን። እስራኤላውያንም በአምልኮተ እግዚአብሔርና በሕገ እግዚአብሔር ስላል ጸኑ እንኳን ሌላ ተጨማሪ አገር ለዘላለም ሊሰጣቸው ይቅርና ያው የተሰጣቸውም ተወስዶባቸዋል።

25. በኦሪት ዘፍጥረት ም.19 ቁ:31 — 36 የተገለጸው ኹናቴ የሚያመለክተው ሎጥ የወይን ጠጅ ጠጥቶ በመስከር ከኹለት ሴቶች ልጆቹ ጋር የዘሙት ኀጢአት መሥራቱን ሲኾን በኹለተኛው የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት ም.2 ቁ:7 — 8 እንደተገለጸው ሎጥን ጻድቅ ብሎ ማመስገኑ ተገቢ ነው ወይ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ቀደም ተብሎ በተራ ቁጥር 19 ላይ እንደተገለጸው ከአንድ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ፍጹም ጻድቅ ሰው በዚህ ዓለም ላይ የለም ተብ



ሎአል። ማንኛውም ሰው ጻድቅ የሚል ቅጽል ስም የሚሰጠው በዘመኑ ወይም በአካባቢው ከሚገኙት ሰዎች ጋር በማወዳደር ነው እንጂ ፍጹም ጻድቅ ሰው አለ ለማለት አይደለም። ሐዋርያው ዮሐንስ በመጀመሪያ መልእክቱ ም.1 ቁ:8 ላይ በገለጸው መሠረት ኀጢአት የለብንም ብንል ሐሰተኞች ነን እንዳለው ማንኛውም ሰው ቢኾን ኀጢአት የሌለበት ሊኖር አይችልምና ሎጥ ጻድቅ በመባሉ በፍጹም ከኀጢአት የነጻ ነው ለማለት አለመኾኑ መታወቅ ይኖርበታል። በሌላ በኩል ደግሞ ሎጥ በፈጸመው የዝሙት ኀጢአት ተጸጽቶ ንስሓ በመግባት የእግዚአብሔርን ይቅርታ አግኝቶ መኾን አለበት። ምክንያቱም የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች ኹሉ መጻሕፍቱን በሚጽፉበት ጊዜ እንዳይሳሳቱ የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ያልተለያቸው መኾኑን የምናምን እስከኾነ ድረስ ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልእክቱ ሎጥን ጻድቅ በሚልበት ጊዜ ስሕተት የሌለበት መኾኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

26. በኦሪት ዘፍጥረት ም.25 ቁ:23 ላይ እግዚአብሔር ለርብቃ ሲነግራት ሕዝብ ከሕዝብ ይበረታል፤ ታላቁም ለታናሹ ይገዛል በማለት ያዕቆብና ትውልዱ ከኤሳውና ከትውልዱ የተሻለ የወደፊት ተስፋ እንዳለው አመልክቶአታል። ይኹን እንጂ ይህንን በረከት ለመታደል ያዕቆብና እናቱ ርብቃ የተጠቀሙበት ዘዴ ማጭበርበር፥ መዋሸትና ማታለል መኾኑ በም.27 ላይ ተዘርዝሮአል። ታዲያ ጊዜው ሲደርስ እንደሚፈጸም አስቀድሞ በትንቢት መልክ የተነገረው ጉዳይ ሥራ ላይ የሚውለው በማጭበርበርና በማታለል ዘዴ እንዲኾን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበርን ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ማንኛውም ኹናቴ አምላክ ብቻ በሚያውቀው መንገድ ሊፈጸም ሲችል የሰው ልጅ ከአስተሳሰቡ ውሱንነት የተነሣ በእግዚአብሔር ያልተፈቀደለትን ድርጊት ያደርጋል። የያዕቆብ ከወንድሙ መብለጥ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ይኹን እንጂ የእርሱና የእናቱ አድራጎት ግን በሕገ እግዚአብሔር የተደገፈ አይደለም። ተፈጻሚነቱ በትንቢት የተነገረለትን ውጤት ለማምጣት ሕገወጥ የኾነ ዘዴን መጠቀም ተገቢ ነው ማለት አይደለም። ለምሳሌ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት ሕማምን ተቀብሎ እንደሚሞት አስቀድመው ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ትንቢት የተናገሩ ቢኾንም አሳልፎ የሰጠው ይሁዳና የሞት ፍርድ ያስፈ



www.ethiopianorthodox.org

ጸሙበት አይሁድ ግን ተገቢ የኾነ ሥራ ሠሩ ማለት አይደለም። ይህም አለመ ኾኑን ሲያረጋግጥ ጌታ ለጲላጦስ ጥያቄ መልስ በሰጠበት ጊዜ "ከላይ ሥልጣን ባይሰጥህ ኖሮ በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልኖረህም ነበር፤ ስለዚህ ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኀጢአቱ የባሰ ነው" ብሎታል። (ዮሐ. ም.19 ቁ:11) እንዲሁም ለደቀ መዛሙርቱ ወደፊት የሚደርስበትን ኹናቴ አስቀድሞ በነገራቸው ጊዜ "የሰው ልጅስ ስለእርሱ በተጻፈው መሠረት ይኼዳል፤ ነገር ግን የሰው ልጅን አሳልፎ ለሚሰጥ ለዚያ ሰው ወዮለት፤ ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር" ብሎአቸዋል። (ማቴ. ም. 26 ቁ:24 )

ስለዚህ እግዚአብሔር የሚመለከተው የሰውን ልጅ ዝንባሌ እንጂ በደግ ወይም በክፉ ሥራው አማካይነት የተገኘውን የመጨረሻ ውጤት አይደለም።

በዚህም መሠረት የያዕቆብና የእናቱ የመዋሸትና የማታለል ሥራ በሕገ እግዚአብሔር የተደገፈ አይደለም።

27. በኦሪት ዘፍጥረት ም.36 ቁ:31 ላይ እንደተገለጸው "በእስራኤል ልጆች ላይ ንጉሥ ከመኖሩ በፊት በኤዶም አገር የነገሡ ነገሥታት እነዚህ ናቸው" በማለቱና በእስራኤል ሕዝብ ላይ ንጉሥ መንገሥ የጀመረው በነቢዩ በሳሙኤል ጊዜ የመጀመሪያው የእስራኤል ሕዝብ ንጉሥ ኾኖ በተቀባው በሳኦል ስለኾነ ይህ አባባል የሚያመለክተው መጽሐፉን የጻፈው ሙሴ ሳይኾን ሳኦል ከነገሠ በኋላ የተነሣ ሌላ ጸሐፊ መኾን አለበት የሚል ሰው ይኖር ይኾናል።

ይህ አባባል ግን ኹለት አማራጭ ትርጉሞች አሉት እንጂ እንዲሁ በነጠላው የሚወሰድ አይደለም።

የመጀመሪያው አማራጭ ትርጓሜ በኦሪት ዘፍጥረት ም.17 ቁ:6 ላይ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ ሲሰጠው "እጅግም አበዛሃለሁ፤ ሕዝብም አደርግሃለሁ፤ ነገሥታትም ከአንተ ይወጣሉ" ባለውና እንዲሁም ደግሞ በዚሁ ምዕራፍ ቁ:16 ላይ ስለሣራ ሲናገር "የአሕዛብ እናት ትኾናለች፤ የአሕዛብም ነገሥታት ከእርስዋ ይወጣሉ" ባለው መሠረት ከእስራኤል ሕዝብ መካከል ወደፊት ነገሥታት ኾነው የሚሾሙ ሰዎች



የሚኖሩ መኾናቸውን ስላመነ ሙሴ አስቀድሞ ስለ እስራኤል ነገሥታት ተናግሮአል የሚል ነው።

ኹለተኛው ትርጓሜ ደግሞ ነገሥታት በሚልበት ጊዜ ማንኛውም የእስራኤልን ሕዝብ በበላይነት የሚያስተዳድር ማለቱ ነው እንጂ ንጉሥ ማለቱ አይደለም የሚለው አባባል ነው። ምንም እንኳ በሳሙኤል ዘመን በፊት በእስራኤልላይ ንጉሥ ያልነገሠ መኾኑ ቢታወቅ ለምሳሌ በመጽሐፈ መሳፍንት ም.17 ቁ:6 ላይ "በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፤ ሰውም ኹሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር" ማለቱ እንደእነ ሙሴና እንደእነኢያሱ ያሉ በእግዚአብሔር የተመረጡ መሪዎች አልነበሩም ለማለት ነው።

በእነዚህም ኹለት አማራጭ ትርጓሜዎች መሠረት ኦሪት ዘፍጥረትን ሙሴ አልጻፈው ይኾናል የሚለውን ጥርጣሬ ከአስተሳሰባችን ማስወገድ ይኖርብናል።

28. በኦሪት ዘፍጥረት ም.46 ቁ:26 እና 27 ላይ "ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብጽ የገቡት ሰዎች ኹሉ ከጉልበቱ የወጡት ከልጆቹ ሚስቶች ሌላ ኹላቸው ስድሳ ስድስት ናቸው፤ በግብጽ ምድር የተወለዱት የዮሴፍም ልጆች ኹለት ናቸው፤ ወደ ግብጽ የገቡት የያዕቆብ ቤተሰዎች ኹሉ ሰባ ናቸው" ካለ በኋላ በሐዋርያት ሥራ ም.7 ቁ:14 ላይ የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ሰማዕት እስጢፋኖስ ባደረገው ዝርዝር መግለጫ " ዮሴፍም አባቱን ያዕቆብንና ሰባ አምስት ነፍስ የነበረውን ቤተዘመድ ኹሉ ልኮ አስጠራ" በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል። ተቃራኒዎች አለመኾናቸውን ግን ቀጥለው በተመለከቱት ዝርዝር ኹኔታዎች እንመልከት።

ስድሳ ስድስት የተባሉት የያዕቆብ ቤተሰቦች ቁጥር የልጆቹን ሚስቶች አይጨምርም። ከዐሥራ አንዱ የያዕቆብ ልጆች መካከል የይሁዳ ሚስት አስቀድማ መሞትዋን በኦሪት ዘፍጥረት ም.38 ቁ:12 ላይ ለመመልከት እንችላለን። እንዲሁም በምዕራፍ 46 ቁ:10 ላይ የስምዖንን ልጆች በሚዘረዝርበት ጊዜ የመጨረሻውን ልጅ የከነዓናዊትዋ ልጅ ስለሚል በዚሁ ምክንያት የስምዖንም ሚስት እንደሞተች ይገመታል።



www.ethiopianorthodox.org

አሁን እንግዲህ ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብጽ የመጡት የያዕቆብ የልጆቹ ሚስቶች ዘጠኝ ብቻ በመኾናቸው ከስድሳ ስድስቱ ጋር በማዳመር ሰባ አምስት ለማለት ነውና ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒዎች አይደሉም።

## ኦሪት ዘጸአት

ይህ መጽሐፍ በዚህ ስም የተጠራው የእስራኤል ልጆች ከምድረ ግብጽ የመውጣታቸውን ታሪክ ስለሚናገር ነው። በአርባ ምዕራፎች የተከፋፈለ ኾኖ ብዙ ጉዳዮች አሉበት። በአጠቃላይ መልኩ ግን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 4 ድረስ ሲኾን ምንም እንኳ የፈርዖንና የግብጽ ሕዝብ ጭቆና የጠነከረበት ቢኾን ከዮሴፍ ሞት ጀምሮ እስከ ሙሴ ልደት ድረስ የእስራኤል ሕዝብ በሚያስገርም ኹናቴ በቁጥር መብዛቱ፥ የሙሴ በልዕልቲቱ አማካይነት በቤተ መንግሥት ማደግ፥ ለወገኖቹ በማገዝ አንዱን ግብጻዊ ከገደለ በኋላ ወደ ምድያም መሸሹ፥ እዚያም ሚስት አግብቶና ልጆችን ወልዶ ለብዙ ጊዜ መቆየቱና በመጨረሻም ወደ ግብጽ ተመልሶ ወገኖቹን ከባርነት ነጻ እንዲያወጣ በእግዚአብሔር የመጠራቱን ታሪክ የሚያወሳ ነው።

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 5 እስከ ዐሥራ አንድ ሲኾን የሙሴና የአሮን በፈርዖን ፊት ቆመው የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ ጌታን ለማምለክ ከግብጽ የመውጣት ፈቃድ ይሰጣቸው ዘንድ መጠየቃቸው፥ ይህንን በመጠየቃቸው በእስራኤል ልጆች ላይ የበለጠ ጭቆና መደረጉ ፥ በግብጾች እምቢተኛነት ምክንያት በግብጽ ሕዝብ ላይ ስለደረሱት ዐሥር ተከታታይ መቅሰፍቶች የሚያወሳ ነው።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 12 እስከ 15 ሲኾን በዚህ ክፍል ከመጨረሻው በግብጻውያን ላይ ከደረሰው ከበኩር ልጆች ሞት በኋላ ግብጻውያን እስራኤላውያንን እንዲወጡላቸው እንዳስቸኰሉአቸው፥ የእስራኤል ልጆች የጠየቁአቸውን ወርቅና ልብስ ኹሉ እንደሰጡአቸውና ከግብጽ እንደወጡ፥ በኋላ ግን ግብጾች እንደገና ሐሳባቸውን በመለወጥ እስራኤላውያንን እንደተከታተሉአቸውና እግዚአብሔር ግን ቀይ ባሕርን



ለኹለት በመክፈል የእስራኤል ልጆች እንዲሻገሩ ካደረገ በኋላ ይከታተሉአቸው የነበሩትን ግብጾችን በውሃው ውስጥ ሰጥመው እንዲሞቱ ማድረጉ ተገልጾአል። እንዲሁም በዚሁ ክፍል ሙሴና የእስራኤል ልጆች የምስጋና መዝሙር መዘመራቸው ተገልጾአል።

አራተኛው ክፍል ከምዕራፍ 16 እስከ 40 ድረስ ሲኾን በዚህ ክፍል በሲና ተራራ ላይ፤ እግዚአብሔር ለሙሴ ዐሥሩ ትእዛዛት የተጻፉበትን ጽላት መስጠቱ፥ እንዲሁም የዓለማዊና የመንፈሳዊ መተዳደሪያ ደንቦች መስጠታቸው፥ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ለመቀበል ሙሴ ወደ ሲና ተራራ ላይ ወጥቶ በነበረ ጊዜ የእስራኤል ልጆች ጣዖት በማምለክ እግዚአብሔርን ማስቆጣታቸው ተገልጾአል። እንዲሁም ከሰማይ መና እንደዘነበላቸው ተነግሮአል።

## በትንቢትነት ወይም በምሳሌነት ከተነገሩ ጉዳዮች መካከል

ሀ/ ቁጥቋጦው በእሳት ተያይዞ ሳለ ምንም አለመቃጠሉን ሙሴ ተመለከተና፥ "ይህ እንዴት አስገራሚ ኹኔታ ነው? ቁጥቋጦውስ እንዴት አይቃጠልም " አለ። (ዘጸ. ም.3 ቁ: 2 — 3)

ቅዱስ ኤፍሬም እመቤታችንን ባመሰገነበት ድርሳኑ ድንግል ማርያም በኮሬብ ተራራ ላይ እሳት እየነደደ ሳለ ጫፎችዋ ሳይቃጠሉ ሙሴ ባያት ቁጥቋጦ ትመሰላለች ብሏል። ጌታን በመውለድዋ ማኅተመ ድንግልናዋ አለመለወጡን ሲያመለክተን ነው። (ውዳሴ ማርያም የማክሰኞና የሐሙስን ይመለከቷል)

ለ/ ሙሴ ወገኖቹን ከግብጽ ሕዝብ ጭቆና ነጻ ሊያወጣቸው ኀላፊነትን እንደወሰደ ጌታ ምእመናንን ከሰይጣን ተገዢነት ነጻ አውጥቶአል። (ዘጸ. ም.7 ቁ:6, ሮሜ ም.4 ቁ:24 - 25, ኤፌ. ም.2 ቁ:13 - 18)



www.ethiopianorthodox.org

ሐ/ ሙሴ ወገኖቹን በቀይ ባሕር መካከል አሳልፎ ከመስጠም ማዳኑ በጥምቀት አማካይነት ከኀጢአት ነጻ እንደምንወጣ ምሳሌነት አለው። (ዘጸ. ም.14 ቁ:21 – 25, የሐ.ሥ. ም.22 ቁ:16)

መ/ "ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ አለቆች ኹሉ ጠርቶ እንዲህ አላቸው ቤተሰባችሁ ኹሉ የፋሲካን በዓል እንዲያከብር ከእናንተ እያንዳንዱ የበግ ወይም የፍየል ጠቦት መርጦ ይረድ።" (ዘጸ. ም.12 ቁ:21 )

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የፋሲካው በግ በክርስቶስ የተተካ መኾኑን ሲያመለክት "አሁን እንደኾናችሁ ኹሉ እርሾ እንደሌለበት እንደ አዲስ ሊጥ እንድትኾኑ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ፤ ምክንያቱም የፋሲካችን በግ የኾነው ክርስቶስ ስለእኛ ተሠውቶአል" ብሎአል። (1ኛ ቆሮ.ም.5 ቁ:7 )

እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ብሎአል እንደ ምታውቁት እናንተ የተዋጃችሁት ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚጠፋ ነገር፥ በብር ወይም በወርቅ አይደለም፤ እናንተ የተዋጃችሁት ነውር እንደሌለው ንጹሕ በግ በኾነው በክርስቶስ ክቡር ደም ነው። (1ኛ ጴጥ. ም.1 ቁ:18 – 19 )

ሠ/ "እነሆ እኔ በሲና ተራራ በዐለት ላይ በፊትህ እቆማለሁ፣ አንተም ዐለቱን ምታው ሕዝቡም የሚጠጡት ውሃ ከውስጡ ይፈልቃል። ሙሴም በእስራኤል አለቆች ፊት እንደዚሁ አደረገ።" (ዘጸ. ም.17 ቁ:6 )

ዐለቱ የክርስቶስ ምሳሌ እንደኾነ የሚገልጸውን የቅዱስ ጳውሎስን አባባል ቀጥለን እንመልከት "ወንድሞች ሆይ አባቶቻችን ደመና ከበላያቸ ውኾኖ ይመራቸው እንደነበረና ኹሉም ቀይ ባሕርን እንደተሻገሩ ላስታውሳችሁ እወዳለሁ። የሙሴ ተባባሪዎች ለመኾንም በዚህ ደመናና በዚህ ባሕር ተጠመቁ ኹሉም አንድ ዐይነት መንፈሳዊ ምግብ ተመገቡ። ኹሉም አንድ ዓይነት መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ የጠጡትም ይከተላቸው ከነበረው ከዚያ ከመንፈሳዊ ዐለት ነበር፤ ያም ዐለት ራሱ ክርስቶስ ነበር። (1ኛ ቆሮ. ም. 10 ቁ:1 – 4)





**29. በኦሪት ዘጸአት ም.2 ቁ:12 ላይ እንደሚነበበው ሙሴ ለአንድ እስራኤላዊ በማገዝ አንዱን ግብጻዊ የገደለው መኾኑ ተነግሮአል። አይሁዶችም ኾኑ ክርስቲያኖች ሙሴን የሚያውቁት በነቢያት አለቃነቱ ወይም በነቢያት ቀዳሚነቱ ነው: እንደዚህ ያለው ነፍስ ገዳይ እንዴት ይህን መሰሉ ሃይማኖታዊ የሹመት ደረጃ ሊኖረው ተገባ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።**

በሐዋርያት ሥራ ም.7 ቁ: 20 - 40 ቀዳሚ ሰማዕት እስጢፋኖስ ለአይሁድ ስለሙሴ ገለጻ ባደረገበት ንግግሩ ዘርዝሮ እንዳስረዳው በልዕልቲቱ በፈረዖን ልጅ ተወስዶ ካሳደገችው በኋላ የግብጾችን ጥበብ ኹሉ በመማር ያደገ ኾኖ ፍርድ የመስጠትና ወንጀለኛን የመቅጣትም መብትና ልምድ የነበረው መኾኑን ያመለክታል። ከዚያም በላይ ያንን ግብጻዊ በገደለ ጊዜ ሙሴ የነበረውን እምነት እስጢፋኖስ ሲያመለክት "ወንድሞቹም እግዚአብሔር በእጁ መዳንን እንዲሰጣቸው የሚያስተውሉ ይመስለው ነበር፤ እነርሱ ግን አላስተዋሉም።" ብሏል። (የሐ.ሥ.ም.7 ቁ:25)

ግብጻዊውን የገደለው በእስራኤላዊው ላይ ግፍ ሲሠራ አይቶት ግፈኛውን ለመበቀል ብሎ ነው እንጂ በተፈጥሮው ነፍስ ገዳይ ስለነበረ አይደለም። እንዲያውም በኦሪት ዘኁልቁ ም.12 ቁ:3 ላይ በምድር ካሉ ሰዎች ኹሉ ሙሴ እጅግ ትሑት ሰው እንደነበረ ተገልጾአል። እንዲሁም በዚሁ ምዕራፍ በቁጥር 7 እና 8 ላይ እግዚአብሔር በአሮንና በማርያም ላይ በተቆጣ ጊዜ "ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም፤ እርሱ በቤቴ ኹሉ የታመነ ነው፤ እኔ አፍ ለአፍ በግልጽ እናገረዋለሁ፤ በምሳሌም አይደለም፤ የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል፤ በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለምን አልፈራችሁም?" በማለት አምላክ ራሱ የመሰከረለት ሰው ነው። እንደዚህ ተደርጎ በእግዚአብሔር የተመሰገነው ሙሴ ግብጻዊውን የገደለው በነበረው የሕግ አዋቂነትና ሥልጣን ወንጀለኛውን ለመቅጣት ብሎ ነው እንጂ በተፈጥሮው ነፍስ ገዳይ አለመኾኑን ተረድተን ነፍስ ገዳይ ነው የሚለውን አስተሳሰብ ማስወገድ ይኖርብናል።



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ጥፋተኞችን ለመቅጣት በልዩ ልዩ መንገድ የሚጠቀም በመኾኑ ነው በኦሪት ዘጸአት ም.12 ቁ:29 ላይ እንደ ተገለጸው በእግዚአብሔር ፈቃድና በሙሴ ተአምር ማድረግ አማካይነት የግብጽ በኵር ኹሉ እንዲሞት የተደረገው። ይህን አባባል የሚያጠናክረው ሌላው ምሳሌ ደግሞ በኦሪት ዘኍልቍ ም.25 ላይ እንደ ተተገለጸው ከጣዖት አምላኪዎች ወገን የነበረችውን አንዲት ምድያማዊት ሴት ወደ እስራኤል ማኅበር ወደ ድንኳኑ ይዟት የገባውን አንድ እስራኤላዊ ሰውና ሴቲቱን የአሮን የልጅ ልጅ ማለት የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ ስለገደላቸው እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው መግለጫ ነዉ "እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ የካህኑ የአሮን ልጅ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ በቅንአቴ በመካከላቸው ቀንቶአልና ቁጣዬን ከእስራኤል ልጆች መለሰ፤ እኔም የእስራኤልን ልጆች በቅንአቴ አላጠፋሁም። ስለዚህ እነሆ፥ የሰላሜን ቃል ኪዳን እሰጠዋለሁ፤ ለአምላኩም ቀንቶአልና ለእስራኤልም ልጆች አስተሰርዮአልና ለእርሱ፥ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ ለዘላለም ክህነት ቃል ኪዳን ይኾንለታል።" (ዘኍ. ም. 25 ቁ:10 – 13)

በዚሁም ዐይነት ሙሴ ግብጻዊውን ከገደለ በኋላ ለእግዚአብሔር ቅርብ ለመኾንና ለእስራኤልም ሕዝብ መሪ ለመኾን በቃ እንጂ ግብጻዊውን በመግደሉ መቼም ቢኾን የተወቀሰበት ጊዜ የለምና ሙሴን ነፍስ ገዳይ ነው ከሚለው አስተሰሰብ መቆጠብ ይኖርብናል።

30. በኦሪት ዘጸአት ም.3 ቁ: 21- 22 ላይ "በግብጻውያን ፊት ለዚህ ሕዝብ ሞገስን እሰጣለሁ፤ እንዲህም ይኾናል በኼዳችሁ ጊዜ ባዶ እጃችሁን አትኼዱም፤ ነገር ግን እያንዳንዲቱ ሴት ከጐረቤትዋ፥ በቤ ትም ካለችው ሴት የብር ዕቃ፥ የወርቅ ዕቃ፥ ልብስም ትለምናለች፤ በወንዶችና በሴቶች ልጆቻችሁ ላይ ተደርጉታላችሁ፤ ግብጻውያንንም ትበዘብዛላችሁ" ያለ ሲኾን በምዕራፍ 20 ቁ:17 ደግሞ "የጐረቤትህን ቤት አትመኝ፤ የጐረቤትህን ሚስት፥ ሎሌውንም፥ ገረዱንም፥ በሬውንም አህያውንም፥ ከጐረቤትህ ገንዘብ ኹሉ ማነኛውንም አትመኝ" ተብሎ ከታዘዘው ትእዛዝ ጋር ተቃራኒ ይመስለን ይኾናል።

እያንዳንድዋ እስራኤላዊት ሴት ከጐረቤትዋ ብርን፥ ወርቅንና ልብስን መጠየቅዋ ከዐሥሩ የእግዚአብሔር ትእዛዛት አንዱን እንደማፍረስ ኾኖ መቈጠር የለበትም።



ከኹሉ አስቀድሞ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ግን የእስራኤል ሴቶች የብርና የወርቅ ዕቃ እንዲሁም ልብስ እንዲጠይቁ ያዘዛቸው የትእዛዛቱና የሕግጋቱ ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር መኾኑ ነው። የሕግጋቱ ኹሉ ባለቤት እርሱ እንደመኾኑ እርሱ በፈቀደውና እርሱ ብቻ ትክክለኛነቱን በሚያውቀው መንገድ ትእዛዛቱን የሚያስተላልፍባቸው ጊዜዎች አሉ። እኛ ውሱኖች እንደመኾናችን ውሱንነት የሌለውን የፈጣሪን ትእዛዝ ከመቀበል አልፈን አወዛጋቢ ጥያቄ ማቅረብ የለብንም።

እግዚአብሔር ደግሞ ለተጨቋኞች ትክክለኛ ፍርዱን የሚሰጥ መኾኑን መርሳት የለብንም። ግብጾች እስራኤላውያንን ለብዙ ዓመቶች እያስጨነቁ ሲያሠሩአቸው የኖሩት ምንም ደመወዝ ሳይከፍሉአቸው ነበር። የእግዚአብሔር ትእዛዝ ግን የሚለው እንዲህ ነዉ "ድኻና ችግረኛ የኾነውን ምንደኛ ከወንድሞችህ፥ ወይም በምድርህ፥ በአገርህ ደጅ ውስጥ ከሚቀመጡት መጻተኞች ቢኾን አታስጨንቀው፤ ድኻ ነውና ነፍሱም ጠንክራ ትፈልገዋለችና ወደ እግዚአብሔር እንዳይጮኽብህ ኀጢአትም እንዳይኾንብህ ደመወዙን ፀሐይ ሳይገባ በቀኑ ስጠው።" (ዘዳ. ም.24 ቁ:14 - 15)

ስለዚህ ከጐረቤቶቻቸው አስገድደው ሳይኾን ለምነው የወሰዱት ብዙ ወርቅና ልብስ በሕይወት ዘመናቸው ኹሉ ከለፉበት የድካማቸው ዋጋ ከፊሉን ነው እንጂ ተገቢ ዋጋቸውን እንኳን ያላገኙ መኾናቸው ታውቆ የራሳቸው ያልኾነውን ንብረት ተመኝተው በመውሰድ ከዐሥሩ የእግዚአብሔር ትእዛዛት አንዱን እንዳፈረሱ ኾኖ መቈጠር የለበትም። በሌላ በኩል ደግሞ ወደፊት የሚፈጸመው ማነኛውም ኹናቴ ከእግዚአብሔር ፈቃድና ከእርሱ ቁጥጥር ውጪ የማይደርስ በመኾኑና ኹሉም ነገር በእርሱ ዘንድ አስቀድሞ የሚታወቅ በመኾኑ እግዚአብሔር በኦሪት ዘፍጥረት ም.15 ቁ:14 ላይ "በባርነት በሚገዙአቸው ሕዝብ ላይ እኔ እፈርዳለሁ፤ ከዚያም በኋላ በብዙ ሀብት ይወጣሉ" በማለት ቀደም ብሎ ለአብርሃም ገልጾለታል።

በዚህም መሠረት እስራኤሎች ከግብጾች ለምነው የወሰዱት ንብረት ከዐሥሩ ትእዛዞች አንዱን እንዳፈረሱ ተደርጎ መታሰብ የለበትም።



www.ethiopianorthodox.org

31. በኦሪት ዘጸአት ም.4 ቁ:21 ላይ እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ እንዳጸናው የተነገረ ሲኾን በም.8 ቁ:15 ደግሞ ፈርዖን ራሱ ልቡን እንዳጸና በመገለጹ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒዎች ይመስሉን ይኾናል።

ፈጣሪአችን ሥርዐተ አልባ አምላክ ባለመኾኑ ነው እንጂ እርሱ ምንም የሚሳነው ነገር እንደሌለ መታወቅ አለበት። ትክክለኛ ዳኛ በመኾኑ ለሰው ልጅ መሉ የፈቃድ ነጻነትን ከሰጠውና ጠቃሚና ጐጂ ኹኔታዎችን ለይቶ ካመለከተው በኋላ የሰውን ልጅ ለዝንባሌውና ለፍላጎቱ ይተወዋል እንጂ ያልፈለገውን አድራጎት እንዲያደርግ አያስገድደውም። በዚህም መሠረት ወደፈርዖን ሙሴንና አሮንን ልኮ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከታምራትና ከምልክት ጋር እንዲያስተምሩ ከማድረጉ በቀር የፈርዖን ልበ ደንዳናነት እንዲለወጥ አላደረገም። እርሱ ከፈለገ የፈርዖንን አስተሳሰብ ለመለወጥ የሚችል ኾኖ ሳለ ይህን ባለማድረጉ የፈርዖንን ልብ አጸና ተባለ። እግዚአብሔር መቼም ቢኾን በቅዱሳት መጻሕፍትና በመምህራን አማካይነት ሕግጋቱን ከማቅረቡ በቀር ማንንም ሰው የማያስገድድ መኾኑን ለመረዳት የሚከተሉትን ኹለት ጥቅሶች እንመልከት።

"ሕዝቤ ግን ቃሌን አልሰሙኝም፤ እስራኤልም አላዳመጠኝም፤ እንደልባቸው ሥራ ተውኋቸው፤ በልባቸውም ሐሳብ ኼዱ።" (መዝ.81 ቁ:11- 12)

"ስለዚህ እርስ በርሳቸው አሳፋሪ ድርጊቶችን እንዲፈጽሙ እግዚአብሔር ርኩሰት ለሞላበ ለክፉ ምኞታቸው ተገገርዎች እንዲኾኑ ተዋቸው።" (ሮሜ. ም.1 ቁ:24)

ሰው ኹሉ ንስሓ ገብቶ እንዲድን እንጂ ማንም እንዳይጠፋ የእግዚአብሔር ፍላጎት መኾኑ በመጀመሪያ ወደ ጢሞቴዎስ በተላከው በሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.2 ቁ:4 እና በኹለተኛው የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት ም.3 ቁ:9 ላይ የተገለጸ ቢኾንም ጠቃሚና ጐጂ የኾነውን ነገር ለይቶ ለሚያውቀው ለሰው ልጅ የጽድቅና የኩነኔ መንገዶች ተዘጋጅተውለት እርሱ የመረጠውን መንገድ ይከተል ዘንድ ነጻፈቃድ የተሰጠው መኾኑ በኦሪት ዘዳግም ም.30 ቁ:19 እና በመጽሐፈ ሢራክ (ም.15 ቁ:11 – 17 )ተዘርዝሮ ይገኛል።



ስለዚህ እግዚአብሔር የፈርዖንን ልበ ደንዳናነት አስቀድሞ ያውቀው ቢኾንም ልቡን እንዳያጸና ባለማድረጉና ለሰው ኹሉ የሰጠውን የፈቃድ ነጻነት ስለፈቀደለት የፈርዖንን ልብ አጸና ተባለ እንጂ ለፈርዖን ግትርነት እግዚአብሔር ምክንያት ኾነ ማለት አይደለም።

32. በኦሪት ዘጸአት ም.9 ቁ:6 ላይ " የግብጽ ከብት ኹሉ ሞተ " ካለ በኋላ በቁ: 20 ደግሞ " ከፈርዖንም ባሪያዎች የእግዚአብሔርን ቃል የፈራ ባሪያዎቹንና ከብቶቹን አሸሸ" የሚል በመኾኑ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒዎች ይመስሉ ይኾናል።

በዚህ ገለጻ ላይ ከብት ኹሉ ሞተ የሚለው ልባቸውን ስላጸኑት ግብጾች ማለት ነው እንጂ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸውንማ እግዚአብሔር እንደሚጠብቃቸው የታወቀ ነው።

ለምሳሌ በኢያሪኮ ግንብ ውስጥ ትኖር የነበረችው ረዓብ የተባለችው ጋለሞታ በእግዚአብሔር ኀይል እስራኤል የኢያሪኮን ከተማ እንደሚይዙ አምና የእስራኤልን ሰላዮች በመሸሸግዋ ከቤተሰብዋ ጋር ለመዳን ችላለች። (ኢያ. ም.2 ቁ:1 – 21፥ ም.6 ቁ:17–25፥ ዕብ. ም.11 ቁ:31፥ ያዕ. ም.2 ቁ:25)

በዚሁም ዐይነት ከግብጻውያኑ መካከል የእግዚአብሔርን ቃል በመፍራት ባሪያዎቻቸውንና ከብቶቻቸውን ያሸሹት ሊድኑላቸው ችለዋል ማለት ነው።

33. በኦሪት ዘጸአት ም.13 ቁ:13 ላይ "ከአህያ የተወለደውን በኩር የበግ ጠቦት በመተካት ከእግዚአብሔር እጅ ትዋጁታላችሁ፤ አህያውን ለመዋጀት ካልፈለጋችሁ ግን አንገቱን ሰበሩት ማለቱ ለምንድነው? በዚህ አድራጎትስ ምን ዐይነት አምልኮተ እግዚአብሔር ተከናወነ?

ቀደም ተብሎ በም.11 ቁ:5 ላይ በተላለፈው በእግዚአብሔር ፍርድ መሠረት በግብጽ ምድር ከሰውና ከእንስሳ በኩር የኾነ ኹሉ እንዲሞት መደረጉ ይታወሳል። ይህንኑ መነሻ በማድረግ በዚሁ በምዕራፍ 13 ቁ:12 እና 13 ላይ ከእስራኤል ወገን የበኩር ልጅ ኹሉ በገንዘብ ይዋጃል፤ ንጹሕ እንስሳ የኾነ እንደኾነ ለመሥዋዕትነት ይቀርባል፤ እርሱም



www.ethiopianorthodox.org

ለሌዊ ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጠ መኾኑን በኦሪት ዘኍልቁ ም.18 ቁ : 17 - 18 እና በኦሪት ዘዳግም ም.19 ቁ : 19- 20 ተገልጾአል። ንጹሕ ያልኾነውን እንስሳ ግን ለመሥዋዕትነት ንጹሕ በኾነ እንስሳ እንዲዋጅ ታዝዞአል። አሁን እንግዲህ ከሰው ወገን በኩር የኾነ ኹሉ በገንዘብ እንዲዋጅ፥ ለመሥዋዕትነት ንጹሕ የኾነው እንስሳ እንዲሰጥ፥ ንጹሕ ያልኾነው እንስሳ ደግሞ ንጹሕ በኾነ እንስሳ እንዲዋጅ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው።ይህ ትእዛዝ የእግዚአብሔር ትእዛዝ በመኾኑ ያለምንም አማራጭ መፈጸም ያለበት ጉዳይ ነው። በዚሁ በኦሪት ዘጸአት ም.13 ቁ:2 ላይ እንደተገለጸው ከእስራኤል ሕዝብም ኾነ ከእንስሳቱ በኩር ኾኖ የተወለደ ኹሉ የእግዚአብሔር ነው። በዚህም መሠረት በኩር ኾኖ የተወለደውን የሚዋጀውን መዋጀትና የሚሰጠውን ደግሞ መስጠት እንጂ ያለበለዚያ ግን የራስ ያልኾነውን ለራስ እንደማስቀረት ይቆጠራል። ይህም በመኾኑ ቀደም ተብሎ በኦሪት ዘጸአት ም.13 ቁ:13 ላይ የተጠቀሰው ጥቅስ የሚያመለክተው የአህያው ባለቤት የራሱ ያልኾነውን የአህያ በኩር የራሱ ንብረት አድርጎ ማኖር ኀጢአት እንዳይኾንበት ያንን አህያ እንዲገድለው ታዝዟል።ይህም ትእዛዝ ሕግ አፍራሽነት እንዳይኖር ፍቱን የኾነ መከላከያ ነው። ምንም እንኳን የሰው ልጅ የፈለገውን መንገድ እንዲከተል ሙሉ ነጻነት እግዚአብሔር የሰጠው ቢኾን እግዚአብሔር ግን ማንም እንዲጠፋ ስለማይፈቅድ ለሰው ልጆች የተለያዩ ዘዴዎችን ያመቻችላቸዋል። በስስታምነት የእግዚአብሔርን ድርሻ ለራሱ ማስቀረት ከጀመረ የሌላ ፍጡር ጓደኛውንም ንብረት መስረቅ፥ መዝረፍ ወይም መቀማት ዝንባሌ የማይከተልበት ምክንያት አይኖርም።

ስለዚህ ዐይኑ ሳስቶበት የእግዚአብሔር ድርሻ የኾነውን በኩር በማስቀረት ልማድ ኾኖበት ለሌላ ተመሳሳይ ኀጢአት ከመዳረግ ይልቅ ያንን ዐይኑ የሳሳበትን አህያ እንዲገድል ታዘዘ እንጂ የአህያው ግድያ ለማንኛውም ለሌላ ጉዳይ የሚያገለግል ኾኖ አይደለም።

በሌላ በኩል ደግሞ ያ አህያው በኩር የወለደችለት ሰው ሌላ ንጹሕ እንስሳ የሌለው ኾኖ የሚዋጅበት በማጣት የሚቸገር ከኾነ ያንን በመግደል ብቻ ቀላል መፍትሔ እንዲኾንለት እግዚአብሔር ያመቻቸለት ዘዴ ነው።



34. በኦሪት ዘጸአት ም.16 ቁ : 35 ላይ "የእስራኤል ልጆች ወደሚኖሩበት ምድር እስኪመጡ ድረስ አርባ ዓመት መና በሉ፤ ወደ ከነዓን ምድር ድንበር እስኪመጡ ድረስ መና በሉ" ካለ በኋላ በመጽሐፈ ኢያሱ ም.5 ቁ :1- 12 በሚነበበው ቃል እግዚአብሔር ደግሞ መናው የቆመው እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ መኾኑ ተገልጾአል። ኦሪት ዘጸአትን የጻፈው ሙሴ መኾኑ የሚታመን ሲኾን እርሱም የሞተው እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ከመሻገራቸው በፊት ነው። ይህ እንዲህ ከኾነ እንዴት አድርጎ ነው መናው የሚቆምበትን ጊዜ ዐውቆ አስቀድሞ የጻፈው? ወይስ ደግሞ መጽሐፉን የጻፈው ሙሴ ሳይኾን ከእርሱ በኋላ የተነሣ ሰው ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ለዚህ ጥያቄ ከኹለት አማራጭ መልሶች አንዱ ወይም ኹለቱም መልሶች ሊኾኑ የሚችሉት የሚከተሉት ኹለት ትርጓሜዎች ናቸው።

ሙሴ የጻፋቸው ጽሑፎች ኹሉ የሚገልጹት በጊዜው የተደረጉትንና በዐይኑ ያያቸውን ኹናቴዎች ብቻ ሳይኾን ከእርሱ በፊትና ከእርሱ በኋላም የተደረጉትንና የሚደረጉትንም ድርጊቶች የሚያጠቃልል ነው። ለምሳሌ ከዘመነ ፍጥረት ጀምሮ እርሱ እስከተነሣበት ዘመን ድረስ የነበረውን ኹናቴ የጻፈው የእግዚአብሔር መንፈስ ስለገለጸለት ነው እንጂ እርሱ ከዘመነ ፍጥረት ጀምሮ የነበረ ሰው ኾኖ አይደለም። በዚሁም ዐይነት ለእስራኤል ልጆች መና የሚወርድላቸው ወደ ምድረ ከነዓን እስኪደርሱ ድረስ ብቻ ነው ብሎ የእግዚአብሔር መንፈስ በገለጸለት መሠረት በትንቢት መልክ ተናገረው።

ኹለተኛው ትርጓሜ ደግሞ በመጽሐፈ ኢያሱ ም.13 ቁ:8 እና 29 ላይ ለሮቤል፥ ለጋድና እንዲሁም ለግማሹ የምናሴ ነገዶች ዮርዳኖስን ሳይሻገሩ ሙሴ ርስት እንዳከፋፈላቸው ተነግሮአል። ምናልባት ለእነዚህ ርስትን ላከፋፈላቸው ነገዶች መና መውረዱ ቆሞ ሊኾን ይችላል። ለእነዚያ ነገዶች ከቆመ ሌሎቹም ኹሉ ድርሻቸውን ማለት ርስታቸውን ሲያገኙ እንደሚቆም ስላመነ የሚቆምበትን ጊዜ ዐውቆ ተናገረ።

35. በኦሪት ዘጸአት ም.20 ቁ:4 "በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድር በታች በውሃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ"" ካለ በኋላ በምዕራፍ



www.ethiopianorthodox.org

25 ቁ:18 ላይ: "ኹለት ኪሩቤል ከተቀጠቀጠ ወርቅ ሥራ፤ በስርየት መክደኛውም ላይ በኹለት ወገን ታደርጋቸዋለህ" የሚለው ተቃራኒ ይመ ስል ይኾናል።

የመጀመሪያው ትእዛዝ እግዚአብሔርን ትቶ ምስሎችን ማምለክ ማለት ነው ኹለተኛው ትእዛዝ ግን የታቦት አጠባበቁን ሥነ ሥርዐት ለማ ሳየት እንጂ በተለየ ለዚያ ለምስሉ እንዲሰገድለት ወይም እንዲመለክ ለማለት አይደለም።

ስለዚህ በመጀመሪያው ጥቅስ ላይ የተነገረው አባባል ማለት የተ ሰጠው ትእዛዝ የሚያመለክተው ምስል እንዳይሠሩ በፍጹም ተከልክለ ዋል ማለት ሳይኾን የተከለከሉት ግን ምስሉን የሚሠሩት ሊሰግዱለትና ሊያመልኩት የኾነ እንደኾነ ብቻ ነው።

36. በኦሪት ዘጸአት ም.20 ቁ:5 ላይ "በሚጠላኝ እስከ ሦስተኛና አስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኀችጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ነኝ" በሚለውና በትንቢት ሕዝቅኤል ም.18 ቁ:4 ላይ " እነሆ፥ ነፍሳት ኹሉ የእኔ ናቸው፤ የአባት ነፍስ የእኔ እንደኾነ ደግሞ የልጅ ነፍስ የእኔ ናት፤ ኀጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች" በሚለው መካከል ልዩነት ያለ ይመስል ይኾናል።

አብዛኛውን ጊዜ አባቶች መልካምም ኾነ ክፉ ጠባያቸውን ለል ጆቻቸው ያስተላልፋሉ። አንዱ በመማሩና ሌላው ግን ባለመማሩ፥ ወይም ደግሞ የመኖሪያ፥ ያካባቢ፥ የጓደኞችና የኅብረተሰብ፥ እንዲሁም የባህል ተጽዕኖ ካልለወጠው በቀር ልጅ የአባቱን ጠባይ መከተሉ የተ ለመደ ነው። ይህ እስከኾነ ድረስ ደግሞ ማለት የአባቱን በደለኛነት እስከተከተለ ድረስ እግዚአብሔር አባቱን እንደቀጣ ልጁንም መቅጣቱ የሚያስገርም አይደለም።

በትንቢት ሕዝቅኤል ኹሉም በኀጢአቱ ብቻ ይፈረድበታል የተባለው አባቱ ኀጢአተኛ ኾኖ ልጁ ግን የጽድቅ መንገድ የሚከተል ቢኾን፥ ወይም አባቱ የጽድቅን መንገድ የሚከተል ኾኖ ልጁ ግን የኀ ጢአትን መንገድ የሚከተል ቢኾን በዚህ ጊዜ ነው እግዚአብሔር ለኹ ሉም እንደየሥራው ዋጋውን የሚሰጠው። ኹለተኛው ትርጓሜ ደግሞ



በኦሪት ዘጸአት የተነገረው በዚህ ዓለም እግዚአብሔር ክብሩን የሚገል ጽበት የዚህ ዓለም ቅጣት ሲኾን በትንቢተ ሕዝቅኤል የተነገረው ግን በሚመጣው ዓለም ስላለው ዘላለማዊው ፍርድ ነው። ለምሳሌ የእ ስራኤል ልጆች እግዚአብሔርን ቅር ባሰኙ ጊዜ በጦርነት መሸነፍ፥ መማ ረክና መሰደድ ሲያጋጥማቸው ምንም ያልበደሉት ልጆቻቸውም አብረው ከእነርሱ ጋር ተሰደዱ፤ ተማረኩ፤ ተቸገሩ እንጂ በወላጆቻቸው ላይ የመ ጣው ቅጣት እነርሱም አልቀረላቸውም። ይኹን እንጂ በዚህም ዓለም ላይ ቢኾን እግዚአብሔር ቅን ታዛዦቹን ሳያስታውሳቸው የማይቀር መኾ ኑን ለመገንዘብ በምርኮኛነት ላይ የነበሩትን የአስቴርን፥ የመርዶክዮስን፥ የነህምያን የዳንኤልን፥ የሦስቱን ወጣቶች፥ የጦቢትንና የቤተሰቡን ታሪክ መመልከት ተገቢ ነው።

37 በኦሪት ዘጸአት ም.21 ቁ:2 ላይ "ዕብራዊ ባርያ ብትገዛ ስድስት ዓመት ያገልግልህ፤ በሰባተኛው ዓመት ያለምንም ዕዳ ነጻ እንዲወጣ አድርገው" በቁ: 20 - 21 ላይ "አንድ ሰው ወንድም ኾነ ሴት ባርያውን በብትር ቢመታና ወዲያው ቢሞትበት መቀጣት ይገባዋል፤ ነገር ግን አገልጋዩ በአንድ ቀን ወይም በኹለት ቀን ውስጥ ባይሞት አሳዳሪ ጌታው በሞት አይቀጣም፤ ባርያውን ማጣቱ ራሱ ቅጣት ነው" ፥ በቁ: 26 - 27 ደግሞ "አንድ ሰው የወንድ ወይም የሴት ባርያውን ዐይን መትቶ ቢያጠፋ ስለ ዐይኑ ካሣ ባርያውን ነጻ ይልቀቅ። በዚሁ ዐይነት አንድ ጥርሱን እንኳ ቢሰብር ስለ ጥርሱ ካሣ ባርያውን ነጻ ይልቀቀው" ተብሏል።

እነዚህ ከላይ የተነበቡት ጥቅሶች የሚያመለክቱት ባርነት ሕጋዊ መኾኑን ነው። እንዴት እግዚአብሔር ትክክለኛ ዳኛ ሲኾን አንድ ሰው ባሪያ አሳዳሪ ፥ ሌላው ሰው ደግሞ ባሪያ እንዲኾን ፈቃዱ ኾነ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ሰዎች ወደባርነት የሚገቡት በተለያየ መንገድ መኾኑን ከቅዱሳት መጻሕፍት እንረዳለን።

አንደኛ/ በባርነት በመወለድ በባሪያ ነጻ መውጣት ዘመን "ጌታው ሚስት የምትኾነው ሴት ሰጥቶት ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወልዳለት ከኾነ ሴትየዋ ከነልጆችዋ የጌታው ትኹን " (ዘጸ. ም.21 ቁ:4 )



www.ethiopianorthodox.org

ኹለተኛ/ ሰው በራሱ ፈቃድ ባሪያ መኾን ሲፈልግ "ባሪያው ግን ጌታዬን ሚስቴንና ልጆቼን እወዳለሁ እርነት አልወጣም ብሎ ቢናገር፥ ጌታው ወደ ፈራጆች ይውሰደው፤ ወደ ደጁም ወደ መቃኑ አቅርቦ ጆሮውን በወስፌ ይብሳው፤ ለዘላለምም ባሪያው ይኹን" (ዘጸ ም.21 ቁ:5 — 6)

ሦስተኛ/ በሌብነት :- ሰው በሬ ወይም በግ ቢሰርቅ፥ ቢያርደው ወይም ቢሸጠው በበሬው ፋንታ አምስት በሬዎች በበጉም ፋንታ አራት በጎች ይክፈል። ሌባው ቤት ሲምስ ቢገኝ እርሱም እስኪሞት ቢመታ በመታው ሰው ላይ የደም ዕዳ አይኾንበትም ሌባው የሚከፍለው ቢያጣ ስለሰረቀው ይሸጥ" (ዘጸ. ም.22 ቁ:1 — 3)

አራተኛ/ በገንዘብ በመግዛት "ወንድ ባሪያና ሴት ባሪያ መግዛት ብትፈልግ ግን በዙሪያችሁ ካሉት ከእነርሱ ከአሕዛብ ወንድና ሴት ባሪያዎችን ግዙ።" (ዘሌ. ም.25 ቁ:44)

"አንተም ወንድምህን ዕብራዊውን ወይም ዕብራዊቱን ብትገዛ ስድስት ዓመት ያገልግሉህ፤ በሰባተኛውም ዓመት ከአንተ ዘንድ አርነት አውጣው" (ዘዳ. ም.15 ቁ:12)

እንግዲህ በዚህ መልኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነገረው የባርነት ኹኔታ ምክንያቶች አሉት እንጂ ዝም ተብሎ አንዱ ሰው በሌላ ሰው ላይ ወየም አንድ ወገን በሌላ ወገን ላይ የሚያደርገው ግፈኛ ጭቈና አይደለም። ይህም ባለመኾኑ ነው በኦሪት ዘጸአት ም.21 ቁ:16 ላይ "ሊሸጠው ወይም ባሪያ አድርጎ ሊገዛው አስቦ ሰውን አፍኖ የሚወስድ ኹሉ በሞት ይቀጣ" የተባለው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለባርነት የተገለጸው ኹናቴ በአሠሪና በሠራተኛ መካከል ያለውን የሥራ ውል ይመስላል እንጂ አንዱ ወገን ሌላውን ወገን በግዴታ የሚጨቁንበት አሠራር አይደለም።

ለአንድ አሳዳሪ በባሪያነት ያደረው ሰው መብት እንደማነኛውም ሰው መብት የሚከበርለት መኾኑን ሲያመለክት በኦሪት ዘጸአት ም.21 ቁ:20 ላይ እንደተገለጸው "ሰውም ወንድ ባሪያውን ወይም ሴት ባሪያውን



በበትር ቢመታ ቢሞትም ፈጽሞ ይቀጣ" ይላል። እንዲያውም አንድ የባሪያ አሳዳሪ ባሪያውን መትቶ ዐይኑን ወይም ጥርሱን የጐዳው እንዳኾነ በካሣ መልክ ባሪያውን ከጊዜው በፊት ነጻ እንዲያወጣው ታዝዞአል።

ጌታው የመታው ባርያ በአንድና በኹለት ቀኖች ውስጥ ሳይሞት ቀርቶ ከዚያ በኋላ ቢሞት ጌታው አይገደልም መባሉ ጌታው ባሪያውን የመግደል ዕቅድ ያልነበረው መኾኑን ስለሚያመለክት ነው።

የኦሪት ሕግ ከመደንገጉ በፊት የነበረው ኹናቴ አንድ በባሪያነት ያደረ ሰው ሰብአዊ መብቱ ኹሉ ተገፍፎ እንደ ዕቃ ከመቈጠር ምንም አይቀረውም ነበር። የግብጽ ሕዝብ በእስራኤል ሕዝብ ላይ የፈጸመው የጭቈና ግፍ በዚያን ጊዜ በባሪያ ላይ ይደረግ የነበረው የጭቈና አገዛዝ ምሳሌ ነው።

አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነገረው የባሪያና ያሳዳሪው ሕግ የሚያመለክተው ግን የባሪያን መብት ለማስከበር የታወጀ ሕግ ነው እንጂ ባሪያን ከሰብአዊ ፍጡር ለማሳነስ የተደነገገ አይደለም።

ማንንም ሰው አፍኖ በመውሰድ ባሪያ ለማድረግ መሞከርና በሪያውን በመምታት መግደል የሞት ቅጣት የሚያስቀጡ መኾናቸው በእግዚአብሔር ዘንድ በባሪያና በባሪያ አሳዳሪ መካከል ልዩነት የሌለ መኾኑን ያመለክተናል።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ም.5 ቁ:17 ላይ እንደገለጸው እርሱ የመጣው ሕግን ለመፈጸም እንጂ ለመሻር አይደለም ብሎአል። በዚህም መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ገላትያ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.3 ቁ:28 ላይ "አይሁዳዊ ወይም ግሪክ፥ ባሪያ ወይም ጌታ፥ ወንድ ወይም ሴት ሳይባል በክርስቶስ ኢየሱስ ኹሉም አንድ ነው" ብሏል።

ስለዚህ የባሪያና የጌታ ግንኙነት በዘመናችን ያለውን የሠራተኛና የአሠሪ ግንኙነትን ስለሚመስል በአስተሳሰባችን ውስጥ ያለው የጨቋኝና የተጨቋኝ ግንኙነት ዐይነት አለመኾኑን መገንዘብ አለብን። አስተሳሰባችንንም በዚያው መጠን መለወጥ ይኖርብናል።



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርም በኦሪቱ የባሪያና የባሪያ አሳዳሪን ሕግ ከደነገገ በኋላ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በባሪያና በጌታ መካከል ልዩነት የሌለ መኾኑን በሐዋርያው ጳውሎስ አማካይነት በመግለጽ ፈጽሞታል፤ ወይም ፍጹም አድርጎታል። (ኹለተኛ መጽሐፍ ጥያቄና መልስ ቁ: 98 ይመለከቷል)

## ኦሪት ዘሌዋውያን

ኻያ ሰባት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በስምንት ልዩ ልዩ ክፍሎች ይከፋፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 7 ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ስለሚቀርቡት የመሥዋዕት ዐይነቶች ማለት ስለ እንስሳት፥ ስለአእዋፍ፥ ስለዱቄት፥ ስለ ዘይትና ስለ ዕጣን አቀራረብ የሚዘረዝር ሲኾን የሚቀርቡባቸውም ምክንያቶች ከእግዚአብሔር ደኅንነትን ለመለመን፥ እግዚአብሔርን ለማመስገንና፥ ስለካህናት ወይም ስለሕዝቡ የበደል ዕዳ መኾናቸውን የሚገልጽ ነው።

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 8 እስከ 10 ነው። እርሱም ለጌታ አገልጋይነት አሮንና ልጆቹ እንዴት የክህነት ሹመትን እንደተሾሙ፥ የዘይት መቀባቱ ሥነ ሥርዓት፥ ከዚያም ለሰባት ቀኖች ከድንኳኑ እንዳ ይወጡ መደረጉ፥ ናዳብና አቢሁ ሥነ ሥርዐት በማፍረሳቸው የተፈጸመ ባቸው ቅጣት ተዘርዝሮ ተገልጾአል።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 11 እስከ 14 ነው። ይኸውም ስለሚበሉና ስለማይበሉ እንስሶች፥ ሴቶች ከወለዱ በኋላ መንጻት ስለሚገባቸው፥ በሰው፥ በልብስና በቤት ላይ ስለሚደርስ ለምጽ የሚዘረዝር ነው።

አራተኛው ክፍል ምዕራፍ 15 እና 16 ነው። ከወንድም ኾነ ከሴት ሰውነት ስለሚፈስ ርኩሰት የመንጻት ሥነ ሥርዓት፥ ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንድ ቀን የራሱንና የሕዝቡን ኀጢአት ለማስተስረይ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ስለሚገባበት ስለ ኀጢአት ስርየት ቀን የሚገልጽ ነው።



አምስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 17 እስከ 19 ነው። በዚህ ክፍል ደም መብላትና ደሙ ሳይፈስ ታንቆ የሞተውን እንስሳ መብላት መከልከሉ፥ የተከለከሉ ጋብቻዎችና፥ የግብረ ሥጋ ግንኙነቶች፥ እንዲሁም ልዩ ልዩ ሕግጋት ይገኙበታል።

ስድስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 20 እስከ ምዕራፍ 22 ድረስ ነው። የአረማውያን አምልኮና የተለያዩ የጥንቆላ ሥራዎች መከልከልና ወደ ጠንቋዮች የሚኼዱ ሰዎች የሚደርስባቸው ቅጣት፥ ካህናት የተቀደሱ መኾን እንደሚገባቸውና ማንኛውም አካለ ጎደሎ የኾነ ሰው ለክህነት አገልግሎት እንዳይሾም መከልከሉ ተዘርዝሮአል።

ሰባተኛው ክፍል ምዕራፍ 23 እና 24 ነው። በዚህ ክፍል የጌታ ልዩ ልዩ ሕጎችና በዓላት መደንገግ፥ በኪዳኑ ታቦት ፊት ለፊት ባለው ቦታ በየቀኑ የወይራ ዘይት መብራት መበራት ያለበት መኾኑ፥ ለእግዚአብሔር ስለሚቀርብ የኅብስት መባ፥ በእግዚአብሔር ላይ ድፍረት በሚያደርጉ ሰዎች ላይ መፈጸም ያለበት ቅጣት ተዘርዝሮአል።

ስምንተኛው ክፍል ከምዕራፍ 25 እስከ 27 ነው። በዚህ ክፍል፥ ስለሰባተኛው ዓመት ምድሪቱን ማሳረፍ፥ ስለኢዮቤልዩ በዓል ሕግጋትና ሥነ ሥርዓት፥ ለተለያዩ የእግዚአብሔር ሕግጋት በመታዘዝ ስለሚገኘው በረከትና ባለመታዘዝ ስለሚመጣው ቅጣት፥ እንዲሁም ስለ ስእለት የተደነገጉትን ሕጎች የሚዘረዝር ነው።

## ምሳሌ ወይም ምልክት ከኾኑ ጉዳዮች መካከል

ሀ. "ሰው ከበግ ወይም ከፍየል መንጋዎቹ አንዱን ለሚታጠል መሥዋዕት ማቅረብ ቢፈልግ ምንም ነውር የሌለበት ተባዕት ይኹን።" (ዘሌ. ም.1 ቁ:10)

ነውር የሌበት መኾኑ ለክርስቶስ ምሳሌ መኾኑን ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲያመለክት እንዲህ ብሏል "ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮ አችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይኾን፥ ነውርና እድፍ እን



www.ethiopianorthodox.org

ደሴለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታው ቃላችሁ።" (1ኛ ጴጥ. ም. 1 ቁ:18 – 19)

"እግዚአብሔር ከሚመለከበት ድንኳን ውስጥ ኾኖ ሙሴን ጠራ ው፤ እንዲህ ብሎም አዘዘው የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር መሥዋ ዕት በሚያቀርቡበት ጊዜ ሊጠብቁት የሚገባ ሥርዓት ይህ ነው እያንዳን ዱ ሰው ከቀንድ ከብትም ኾነ፥ ከበግ ወይም ከፍየል ወገን ማነ ኛውንም ዐይነት መሥዋዕት በሚያቀርብበት ጊዜ ይኸውም ከቀንድ ከብቱ መካከል አንዱን ለሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ ቢፈልግ ምንም ነውር የሌለበ ትን ኮርማ መርጦ ያምጣ።" (ዘሌ. ም.1 ቁ:1 – 31)

ወደዕብራውያን የተላከው መልእክት ም.9 ቁ.11 – 14 ክርስቶስ የእንስሳትን መሥዋዕትነት በራሱ መሥዋዕትነት የተካው መኾኑን ሲያ መለክት እንዲህ ይላል "ነገር ግን ክርስቶስ አሁን ለሚኾኑት መልካም ነገ ሮች ሊቀ ካህናት ኾኖ መጥቶአል፤ እርሱ የገባባት ድንኳን ትልቅና ፍጹ ም ናት፤ ይህች ድንኳን፣ በሰው እጅ ያልተሠራችና ከዚህ ፍጥረት ያል ኾነች ናት። እርሱ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በማያዳግም ኹኔታ የራሱን ደም ይዞ ገባ እንጂ የፍየሎችንና የኮርማዎችን ደም ይዞ አልገባም፤ በዚህ ዐይ ነት የዘላለም ደኅንነትን አስገኘልን። የፍየሎችና የኮርማዎች ደም፥ ለመ ሥዋዕት የተቃጠለች ጊደር ዐመድ በረከሱ ሰዎች ላይ ሲረጭ ከሥጋዊ ርኩሰት አንጽቶ የሚቀድሳቸው ከኾነ፥ በዘላለም መንፈስ አማካይነት ራሱን ነውር የሌለበት መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀረበው የክ ርስቶስ ደምማ ሕያው እግዚአብሔርን እንድናገለግል ኅሊናችንን ከሞተ ሥራ እንዴት ይበልጥ ያነጻ!"

ለ. "ክርስቶስ የእውነተኛይቱ ቅድስት ምሳሌ ወደኾነችውና በሰው እጅ ወደተሠራችው ቅድስተ ቅዱሳን አልገባም፤ እርሱ አሁን ስለእኛ በ እግዚአብሔር ፊት ለመታየት ወደ ሰማይ ገባ። የአይሁድ ሊቀ ካህናት የራሱ ያልኾነውን ደም ይዞ በየዓመቱ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባ ነበር፤ ክስቶስ ግን ራሱን ብዙ ጊዜ መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ አልገባም። ....... ክርስቶስ የብዙዎችን ኀጢአት ለማስወገድ አንድ ጊዜ ተሠውቶ አል፣ ደግሞም ኀጢአትን ለመሸከም ሳይኾን፥ እርሱን የሚጠባበቁትን ለማዳን ኹለተኛ ጊዜ ይገለጣል።" (ዕብ. ም.9 ቁ.24 – 25 እና 28)



ስለዚህም ነው ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር 40 ቁ.6 ላይ "መሥዋዕ ትንና ቁርባንን አልወደድህም፤ ሥጋን አዘጋጀህልኝ፤ የሚቃጠለውንና ስለኀጢአት የሚቀርበውን መሥዋዕት አልሻህም" ሲል ትንቢት የተናገ ረው።

ይህንኑ አባባል ለማጠናከር ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.13 ቁ: 11 - 12 ላይ እንዲህ ተብሏል "የአይሁድ ሊቀ ካህናት የኀጢአት ይቅርታን የሚያስገኘውን የእንስሳት ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባል፤ የእንስሳቱ በድን ግን ከሰፈሩ ውጪ ይቃጠላል፤ እን ዲሁም ኢየሱስ ሕዝቡን በገዛ ራሱ ደም ለመቀደስ ከከተማው በር ውጪ መከራ ተቀበለ።"

ሐ. በኦሪት ዘሌዋውያን ም.23 ቁ: 5 - 14 የታዘዘው የፋሲካ በዐል ምሳሌነቱ የክርስቶስን የማዳን ሥራ መኾኑን ሲያመለክት ሐዋርያው ጳው ሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው በመጀመሪያ መልእክቱ ም.5 ቁ:7 ላይ "የፋሲካችን በግ የኾነው ክርስቶስ ስለ እኛ ተሠውቶአል" ብሎአል።

መ. በኦሪት ዘሌዋውያን ም.23 ቁ: 15 - 24 ላይ የተዘረዘረው መከር በገባ በ50ኛው ቀን የሚከበረው በዓል መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ በወ ረደበት በጰንጠቆስጤ በዐል ማለት ጌታ በተነሣ በ50ኛው ቀን በሐዋር ያት ላይ መንፈስ ቅዱስ ከመውረዱና ለቤተ ክርስቲያን ሦስት ሺ ነፍስ ከመጨመሩ ጋር ምሳሌነት አለው። (የሐ.ሥ.ም.2)

ሠ. በኦሪት ዘሌዋውያን ም.25 ቁ: 8 - 55 የተዘረዘረው የኢዮቤልዩ በዓል ሥነ ሥርዓት ባሪያዎችን ነጻ ማውጣት፥ ለችግረኞች ብድር ማበ ደርና ባለዕዳዎችም ዕዳ እንዳይከፍሉ ይቅርታ ማድረግ ስለሚገኝበት ጌታ ችን በቤዛነቱ ኀጢአታችንን ኹሉ ይቅር ከማለቱ ጋር ምሳሌነት አለው።

ረ. በኦሪት ዘሌዋውያን ም.16 ቁ:20 ላይ የተገለጸው የሕዝቡን ኀጢአት ተሸክሞ ወደበረኻ የሚላከው ዐዛዜል ጌታ እኛን ከሰይጣን ተገዢነት ነጻ ለማውጣት ለእኛ ቤዛ ከመኾኑ ጋር ምሳሌነት አለው።



www.ethiopianorthodox.org

# ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

38. በኦሪት ዘሌዋውያን ም.11 ላይ እንደተመለከተው የእስራኤል ሕዝብ አንዳንድ እንስሳትን አርዶ እንዳይበላ የተከለከለው እነዚያ እንስሳት ርኩሶች ስለኾኑ ነው መባሉ ወደ ሮሜ ሰዎች በተጻፈው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.14 ቁ:14 ላይ ማንኛውም ምግብ በራሱ ርኩሰት የሌለበት መኾኑ ከተገለጸው አገላለጽ ጋር እንዴት ማስታረቅ ይቻላል? እንዲሁም ለምጻም መኾንና ሬሳ መንካትስ እንዴት ርኩሰትን ሊያመጡ ቻሉ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል። (ሌዋ. ም.11 ቁ:39፥ ም.13 ቁ:3 ፥ ዘኁ. ም.19 ቁ:11)

የሙሴ ሕግ ርኵሰትን በኹለት ይከፍለዋል። አንዱ የነፍስ ርኵሰት ሲኾን ኹለተኛው ደግሞ የስሜት ርኵሰት ነው። የነፍስ ርኵሰት የሚባለው በወዲያኛው ዓለም ሊያስቀጣ የሚችል የኀጢአት ሥራ ነው። የስሜት ርኵሰት የሚባለው ደግሞ ሥጋን የሚያረክስ ነው። ለምሳሌ ከእግዚአብሔር አገልግሎትና ከኅብረተሰብ ማኅበራዊ ኑሮ የሚያገልለው የለምጽ በሽታ እንደ ሥጋ ርኵስት ይቈጠራል።

የአንዳንድ እንስሳት ሥጋ ደግሞ አንድም ለጤንነት የሚስማማ ባለመኾኑና እንስሳቱም አስጸያፊ ወይም አስጠሊ በመኾናቸው እንደ ርኵሶች ተቈጥረዋል። እርሱም የሥጋ ርኵሰት ነው። ሌላው የአንዳንድ እንስሳት ሥጋ መከልከል መክንያት ደግሞ እነዚያን እንስሳት አረማውያን ለባዕድ አምልኮና ለተለያዩ የጥንቈላ ሥራዎች ይጠቀሙባቸው ስለነበረ ያ ልማድ የእንስሳቱን ሥጋ ከመብላት ጋር ተከትሎ እንዳይመጣ ጥንቃቄ ለማድረግ ሲባል ነው።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንደ ወላጅ አባት እየተንከባከበና እየቀጣ ይመራው በነበረበት ዘመን በአስቸኳይ የሚቀጣበት የአባት አርጩሜ በለምጽ በሽታ ማስደንገጥ ነበር። ለምሳሌ በኦሪት ዘኊልቈ ም:12 ቁ: 10 - 15 ላይ የሙሴና የአሮን እኅት ማርያም በወንድምዋ በሙሴ ላይ ባደረሰችው በደል ምክንያት ሰባት ቀን በሚቈይ የለምጽ በሽታ መቀጣትዋ ተገልጾአል።እንዲሁም በኹለተኛው ዜና መዋዕል ም.26 ቁ :19 - 21 ላይ እንደተ ነለጠው የይሁዳ ንጉሥ ዖዝያን



በሕግ ያልተፈቀደለትን የዕጣን ማጠን ተግባር ስለተዳፈረ በለምጽ በሽታ ተቀጥቶአል። በለምጽ በሽታ የተመታ ሰው ኹሉ ከሰው ተለይቶ የብቸኝነት ኑሮ መኖር ነበረበት። ከማኅበራዊ ኑሮና ከመንፈሳዊ አገልግሎት መታገዱ በሥጋው ላይ ርኵሰትን እንዳመጣበት አስቈጠረው።

የልብስና የግድግዳ ለምጽ ደግሞ በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ ብቻ የሚታወቅ እንጂ በሌላ ሕዝብ ዘንድ የማይታወቅ ነው። በዚህም መሠረት እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ሥነ ሥርዓት ከሚያስጠብቅባቸው መንገዶች መካከል እንደኾኑ ይገመታል።

ሬሳ እንዳይነኩ የተከለከሉበትና ሬሳ መንካትም እንደመርከስ የታወጀበት መክንያት በዚያን ጊዜ በጣዖት አምላኪዎች አረማውያን ካህናት ዘንድ በሰፊው የተለመደው አሠራር ወደ አይሁድ ሕዝብ እንዳይዛመት ጥንቃቄ ለማድረግ ሲባል ነው። ይህም በአረማውያን ዘንድ የነበረው አስጸያፊ ልማድ የሟቾችን አጥንት ለጥንቈላቸው መጠቀሚያ ማድረግ ነበር።

ሌሎች ትርጓሜዎች ደግሞ እነዚያ ያለበቂ ምክንያት የተከለከሉ የሚመስሉትና እንደ ርኩስ የተቈጠሩት ጉዳዮች ኹሉ እግዚአብሔር በመጀመሪያ የመታዘዝን ጥቅምና ያለመታዘዝን ጉዳት ለማሳየት ለአዳም የበለሱን ፍሬ መብላት እንደከለከለው ኹሉ የእስራኤልንም ሕዝብ ሥነ ሥርዓት ለማስያዝ የታዘዙ ትዕዛዞች ናቸው እንጂ ሌላ ሊኾን አይችልም ይላሉ።

39. በኦሪት ዘሌዋውያን ም.19 ቁ: 16 ላይ "በባልንጀራህ ደም ላይ አትቁም" የሚለው ትእዛዝ ምን ማለት ነው?

ወዳጅህ፥ ጐረቤትህ፥ ጓደኛህ ወንድምህ ወይም ማንኛውም ሰው ለሞት የሚዳረግ፥ ደሙ የሚፈስስ መኾኑን እያየህ ከሞት እንዲድን እርዳው እንጂ ዝም ብለህ አትተወው ማለት ነው ሲሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ተርጉመውታል። ይህም ማለት አንድን ሰው ልታድነው የምትችልበት መንገድ ካለህ ለራስህ እንኳን የሚያሰጋህ ቢኾን ለማዳን ፍጠን እንጂ ዝም ብለህ አትመልከት። ለምሳሌም ያኽል ሌቦችና ዘራፊዎች፥ ወይም አደገኛ አውሬዎች ሊያጠቁት ሲሞክሩ ስታይ ልታ



www.ethiopianorthodox.org

ድነው ሞክር እንጂ ዝም ብለህ አትመልከት። አንድ ሰው በሐሰት ተከስሶ በዳኛ ፊት በሚቆምበት ጊዜ እርሱን ለማዳን የምታውቀው እውነት ካለ የምታውቀውን ተናገር፥ መስክር እንጂ በሐሰት ክስ ሲፈረድበት ዝም ብለህ አትመልከት።

ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ ም.4 ቁ:17 ላይ "መልካም ነገር ማድረግን እያወቀ የማያደርገው ሰው አለማድረጉ ኀጢአት ይኾንበታል" የሚለዉ አባባል እላይ ከተሰጠ ው ትርጓሜ ጋር ተመሳሳይነት አለው።

## ኦሪት ዘኍልቍ

ይህ መጽሐፍ 36 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በዚህ ስም የተጠራበት ምክንያት የእስራኤልን ልጆች እንዲቆጥር እግዚአብሔር ሙሴን ያዘዘው በመኾኑና ስለአቈጣጠሩም ታሪክ የሚዘረዝር በመኾኑ ነው። መጽሐፉም በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የሚከፋፈል ሲኾን እነርሱም የሚከተሉት ናቸ ው

የመጀመሪያው ክፍል ሕዝቡ ከምድረ ግብጽ ከወጣበት ከኹለተኛው ዓመት ከመጀመሪያው ወር ይጀምራል። በዚህም ክፍል ከተስፋ ምድር በስተሰሜን በኩል እስከሚገኘው እስከቃዴስ በርኔ ድረስ ያለውን የጉዞ ታሪክ ያወሳል። እንዲሁም የከነዓንን ምድር እንዲመረምሩ ከተላኩት ዐሥራ ኹለት ሰላዮች መካከል ከካሌብና ከኢያሱ በቀር ሌሎቹ ዐሥሩ ሰላዮች በተናገሩት የማስፈራሪያ ቃል ሕዝቡ እምነተ ቢስ ኾኖ በማጉረምረሙ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሊያጠፋቸዉ የነበረና በሙሴ አማላጅነት ብቻ ሳያጠፋቸዉ እንደቀረ ተዘርዝሮአል። የሐሰት ወሬ ያመጡትን ዐሥር ሰላዮች እግዚአብሔር ቀሰፋቸው። በዚሁም ምክንያት በምድረ በዳ አርባ ዓመት ሙሉ ሲንከራተቱ ከርመው ኹሉም እንደሚሞቱና ከኻያ ዓመት በታች ያሉት ልጆቻቸው ብቻ ምድሪቱን እንደሚወርሱ የእግዚአብሔር ፍርድ ተላለፈ።

በኹለተኛው ክፍል የሕዝቡን የጉዞና ድንኳን የተከሉባቸውን ቦታዎች ታሪክ ይዘረዝራል። በዚህ ፍል ው(ጥ ቆሬና ጓደኞቹ በፈጸሙት ዐመፅ የደረሰባቸው ቅጣትና የሙሴ እኅቱ ማርያምም በኢትዮጵያዊት



ሚስቱ ምክንያት በሙሴ ላይ በፈጸመችው ዐመፅ የደረሰባትን ቅጣት የሚናገር ታሪክ ይገኝበታል። እንዲሁም የሕዝቡ ማጉረምረምና በመጨረሻም የማርያም ሞት በዚሁ ክፍል ውስጥ ተገልጿል።

በሦስተኛው ክፍል የሞዐብ ንጉሥ ባላቅ በበለዐም አማካይነት እስራኤልን ለማስረገም ቢሞክርም እግዚአብሔር ግን ከመርገም ይልቅ እንዲባርከው የአስደረገ መኾኑ ተገልጾአል፤ ከዚያም የሕዝቡ ጉዞ በአጭሩ ከመገለጹም በላይ የመሬቱን ክፍፍል በሚመለከት ድንጋጌዎች ተዘርዝረዋል።

## በምሳሌነት ከቀረቡ ኹናቴዎች መካከል

ሀ. በኦሪት ዘኍልቁ ም.17 ላይ ከ12 የእስራኤል ነገዶች መካከል በአንድ ሌሊት የአሮን በትር ብቻ ለምልማ፥ እንቡጥ አውጥታ በማበብ የበሰለ የለውዝ ፍሬ አፍርታ መገኘትዋን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለወንድ ዘር ፅንሳ ከመውለድዋ ኹናቴ ጋር ሲያመሳስል ቅዱስ ኤፍሬም እመቤታችንን ባመሰገነበት ድርሳኑ እንዲህ ብሏል "አምላክን የወለድሽልን አንቺ ሳይተከሏት እንደበቀለችው ውሃ ሳያጠጡአት እንደ ለመለመችው፥ እንዳበበችውና እንደአፈራችው የአሮን በትር ነሽ።" (ውዳሴ ማርያም ዘዕለተ እሑድ ይመለከቷል።)

ለ. በኦሪት ዘኍልቁ ም.21 ቁ :4 - 9 ላይ እንደተገለጸው የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ በማጉረምረም እግዚአብሔርን ቅር ባሰኙ ጊዜ መርዘኛ እባብ ልኮባቸው ብዙዎቹ እየተነከሱ ሞተዋል። ቀሪዎቹ የእግዚአብሔርን ይቅርታ በለመኑ ጊዜ ሙሴ የነሐስ እባብ በእንጨት ላይ ሰቅሎ ያንን የተመለከተ ኹሉ እንደሚድን በመንገር እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት በእባቡ ተነክሶ የነበረ ሰው ኹሉ የተሰቀለውን የነሐስ እባብ በመመልከት ሊድን ችሏል። ጌታ በዮሐንስ ወንጌል ም.3 ቁ: 14 - 15 ይህን ኹናቴ ከራሱ ስቅለት ጋር ሲያመሳስለው እንዲህ ብሏል "ሙሴ በበረኻ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ የሰው ልጅ ከፍ ብሎ ሊሰቀል የሚገባው በእርሱ የሚያምን ኹሉ የዘላለምን ሕይወት ያገኝ ዘንድ ነው።"



www.ethiopianorthodox.org

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

40. በኦሪት ዘኍልቊ ም.1 እና ም.26 የተደረጉት ቆጠራዎች ውጤቶቻቸው ለምን ተለያዩ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ልዩነቶቹን በዝርዝር እንመልከት

| | | |
|---|---|---|
| የሮቤል ነገድ | 46500 | ም.1ቁ.21 |
| የሮቤል ነገድ | 43730 | ም.26 ቁ. 7 |
| የስምዖን ነገድ | 59300 | ም. 1 ቁ.23 |
| የስምዖን ነገድ | 22200 | ም.26 ቁ.14 |
| የጋድ ነገድ | 45650 | ም. 1 ቁ.25 |
| የጋድ ነገድ | 40500 | ም. 26 ቁ.18 |
| የይሁዳ ነገድ | 74600 | ም. 1 ቁ.27 |
| የይሁዳ ነገድ | 76500 | ም.26 ቁ.22 |
| የይሳኮር ነገድ | 54400 | ም. 1 ቁ.29 |
| የይሳኮር ነገድ | 64300 | ም.26 ቁ.25 |
| የዛብሎን ነገድ | 57400 | ም. 1 ቁ.31 |
| የዛብሎን ነገድ | 60500 | ም.26 ቁ.27 |
| የዮሴፍ ነገድ ኤፍሬም | 40500 | ም. 1 ቁ.33 |
| የዮሴፍ ነገድ፣ ኤፍሬም | 32500 | ም.26 ቁ.37 |



| | | |
|---|---|---|
| የዮሴፍ ነገድ፣ ምናሴ | 32200 | ም. 1 ቁ.35 |
| የዮሴፍ ነገድ፣ ምናሴ | 52700 | ም.26 ቁ.34 |
| የብንያም ነገድ | 35400 | ም. 1 ቁ.37 |
| የብንያም ነገድ | 45600 | ም.26 ቁ.41 |
| የዳን ነገድ | 62700 | ም. 1 ቁ.39 |
| የዳን ነገድ | 64400 | ም.26 ቁ.43 |
| የአሴር ነገድ | 41500 | ም. 1 ቁ.41 |
| የአሴር ነገድ | 53400 | ም. 26 ቁ.47 |
| የንፍታሌም ነገድ | 53400 | ም.1 ቁ.43 |
| የንፍታሌም ነገድ | 45400 | ም. 26 ቁ.50 |
| ድምር | 603550 | ም. 1 ቁ.46 |
| | 601730 | ም.26 ቁ.51 |

የመጀመሪያው ቆጠራ በኦሪት ዘጸአት ም.38 ቁ.26 ላይ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ በመኾኑ ምናልባት ቀደም ተብሎ የተቆጠረውን ቆጠራ ዝርዝር ከመግለጹ በቀር አዲስ ቆጠራ ያልተደረገ ሊኾን ይችላል። እንደዚያ ከኾነ ደግሞ አዲሱ ቆጠራ ከቀድሞው ቆጠራ ቀንሶ መገኘቱ ሊያስገርመን አይገባም። ምክንያቱም በኦሪት ዘኍልቊ ም.14 ቁ:29 ላይ እንደተገለጸው ከምድረ ግብጽ ከወጡት መካከል ከኻያ ዓመት ዕድሜ በላይ የነበረው ሰው ኹሉ ከኢያሱና ከካሌብ በቀር ቀድሞ እንደሚሞት እንጂ ማንም ወደ ተስፋ ምድር እንደማይገባ በመወሰኑና ከቀድሞው ቆጠራ ጊዜ በኋላ በተጠቀሰው የዕድሜ ክልል ውስጥ የነበሩት ሰዎች ስለሞቱ ነው። ከቀድሞው ቈጠራ በኋላ በልዩ ልዩ መቅሰፍት



www.ethiopianorthodox.org

ያለቁ ሰዎች ብዙዎች ናቸው። ለምሳሌ በኦሪት ዘኍልቍ ም.25 ቁ.9 ላይ በመቅሰፍት የሞተው ሰው ብዛት ኻያ አራት ሺ መኾኑ ተገልጾአል፡ እንዲሁም በሌላ ጊዜ ዓሥራ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሰዎች እንደተቀሰፉ በኦሪት ዘኍልቍ ም.16 ቁ:49 ላይ ተገልጾአል። ምንም እንኳ በድምሩ ሲታይ በኦሪት ዘጸአት ም.38 ቁ.26 እና በኦሪት ዘኍልቁ ም.1 ቁ :46 ላይ ከታየው የሕዝብ ብዛት 603550 በኦሪት ዘኍልቍ ም. 26 ቁ.51 ላይ ወደ 601730 ዝቅ ይበል እንጂ ብዙዎቹ ነገዶች ከመቀነስ ይልቅ ዕድገት አሳይተዋል። ይህም የኾነበት ምክንያት በአንድ በኩል ከቀደሞው ቆጠራ በኋላ በተወሰነው የዕድሜ ክልል ውስጥ የነበሩ ብዙ ሰዎች ያልነበሩባቸው በመኾኑና በሌላ በኩል ደግሞ መቅሰፍቱ ያጠቃቸው የተወሰኑትን ነገዶች ስለነበረ አንዳንድ ነገዶች ዕድገት ሲያሳዩ ሌሎች ደግሞ ቀንሰዋል።

41. በኦሪት ዘኍልቍ ም.12 ቁ:3 ላይ በምድር ካሉ ሰዎች ኹሉ ይልቅ ሙሴ እጅግ ትሑት ሰው ነበር በመባሉ ይህን መጽሐፍ የጻፈው አንድም ሙሴ ሳይኾን ሌላ ሰው መኾን አለበት፣ ይህ ካልኾነ ደግሞ እንዴት በሦስተኛ ሰው አነጋገር ራሱን በማመስገን ይጽፋል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

አንድ ሰው ክስ የተመሠረተበት እንደኾነ ወይም ያላጠፋውን ጥፋት እንዳጠፋ ተደርጎ በሚወራበት ጊዜ ራሱን ከዚያ ክስ ንጹሕ ለማድረግ መሞከር የተለመደ የሰው ልጅ ጠባይ ነው። በዚህም መሠረት ወንድሙ አሮንና እኅቱ ማርያም በአንድ በኩል የውጪ አገር ሴት ማግባቱን በመቃወም በሌላ በኩል ደግሞ በመሪነቱ ቀንተውበት በወንድማቸው በሙሴ ላይ ስለተነሡበት እግዚአብሔር የግድ ስላዘዘው ነው እንጂ እርሱ ያን ሹመት የማይፈልግ ትሑት ሰው የነበረ መኾኑን ለመግለጽ ሲል ነው እንጂ ራሱን ለማመስገን ፈልጎ አይደለም። (ዘጸ.ም.4 ቁ:1 — 23)

ለምሳሌ መድኀኒታችን "መኾኑን ከእናንተ መካከል እኔን ኀጢአተኛ ነህ ብሎ የሚወቅሰኝ ማነው?" ብሎ በጥያቄ መልክ ምንም ኀጢአት የሌለበት መኾኑን ለአይሁድ የገለጸላቸው ሊገድሉት የሚፈልጉት ያለምክንያት መኾኑን ሊያስረዳቸው ፈልጎ ነው። (ዮሐ.ም.8 ቁ.46)



እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ አንዳንድ ትምክሕተኞችን ለማጋለጥ ሲል "እነርሱ የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን? እኔ ከእነርሱ ይበልጥ የክርስቶስ አገልጋይ ነኝ" በማለት የገለጸ መኾኑን ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ኹለተኛ በላከው መልእክቱ ም.11 ቁ:23 ላይ መመልከት እንችላለን።

በሦስተኛ ሰው አነጋገር ማቅረብ ደግሞ ያነጋገርና ያጻጻፍ ስልት ነው እንጂ መጽሐፉን የጻፈው እርሱ ሳይኾን ቀርቶ አይደለም። ለምሳሌ መድኀኒታችን ስለራሱ በተናገረባቸው በአብዛኞዎቹ ጊዜያት ወልድ እንደዚህ ነው፤ ወይም ወልድ እንደዚህ ያደርጋል ብሎ መናገሩን ማስተዋል እንችላለን። እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ኹለተኛ ባላከው መልእክቱ ም.12 ላይ ራሱ ስላየው ራእይ በሚናገርበት ጊዜ የክርስቶስ የኾነ አንድ ሰው ዐውቃለሁ ብሎ ስለሦስተኛ ሰው የሚናገር በማስመሰል የገለጸ መኾኑን ልንመለከት እንችላለን።

ስለዚህ ሙሴ በሦስተኛ ሰው ስለራሱ የጻፈው የአጻጻፍ ስልት በመኾኑና ራስን በማመስገን የመከላከያ ሐሳብ ማቅረብ የተለመደ ኹናቴ ነው እንጂ መጽሐፉን የጻፈው ሙሴ ሳይኾን ቀርቶ አይደለም። ጥያቄና መልስ ተራ ቁጥር 88 እና 121 ይመለከቷል።

42. በኦሪት ዘኍልቍ ም.16 ቁ:27 እና 32 ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር በቆሬ በዳታንና በአቤሮን ላይ በተቆጣ ጊዜ እነርሱ ከነቤተሰባቸው ሕፃናትም ሳይቀሩ መሬት ተከፍቶ ውጦአቸዋል። እንዲሁም በመጽሐፈ ኢያሱ ም.7 ቁ:24 እና 25 ላይ አካን የተባለውን የዛራ ልጅ ለእርሱ ካለው ኹሉ ጋር ወግረው በእሳት እንዳቃጠሉት የተነገረ ሲኾን በኦሪት ዘዳግም ም.24 ቁ.16 ላይ ግን ለሕዝቡ በተሰጠው ሕግ "አባቶች ለልጆች አይገደሉ፤ ነገር ግን ኹሉ እያንዳንዱ በኀጢአቱ ይገደል።" በመባሉ አባባሎቹ ተቃራኒዎች ይመስላሉ።

ለሰዎች የተሰጠው ሕግ ማነኛውም ዳኛ ጥፋቱን ባጠፋው ሰው ላይ እንጂ በሌላ ሰው ላይ እንዲፈርድ አልተፈቀደለትም። እግዚአብሔር ግን ሕጉን የሰጠ እርሱ እንደመኾኑና የወንጀሉንም መጠን በትክክል የሚያውቀው እርሱ በመኾኑ እኛ ውስኖቹ ልንረዳው በማንችለው በእርሱ አስተሳሰብና በእርሱ ውሳኔ መሠረት በቤተሰብ ኹሉ ላይ የሚፈርድበት



www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ አለ። እንደሚታወቀው የእግዚአብሔር ዕውቀት በጊዜና በቦታ የማይወሰን በመኾኑ እነዚያ ቤተሰቦች አብሮ እንዲጠፉ ከማድረግ ይልቅ እንዲኖሩ ቢደረጉ ወደፊት ምን ዐይነት ሰዎች እንደሚኾኑ አስቀድሞ ስለሚያውቅ በቤተሰቡ ኹሉ ላይ ፈርዶአል። እኛ ግን ውሱኖች እንደመኾናችን የወደፊቱን ኹናቴ አስቀድመን ስለማናውቅ በእግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ ገብተን ሐሳብ ለመስጠት አንችልምና ከመሳሳት እንጠንቀቅ። (ቁ:46 እና 56 ይመለከቷል)

43. በኦሪት ዘኍልቊ ም.22 ቁ.20 እንደተነገረው እግዚአብሔር ለበለዓም በሕልም ተገልጾለት ሊጠሩት ከመጡት ሰዎች ጋር እንዲኼድ ከፈቀደለት በኋላ በቁ:21 — 33 እንደተገለጸው ደግሞ እግዚአብሔር ተቆጥቶበት አንድ መልአክ በመንገዱ ላይ መቆሙ ተገልጾአል። እንዲኼድ እግዚአብሔር ከፈቀደለት በኋላ በመኼዱ እግዚአብሔር የተቆጣበት ለምንድነው? ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በዚሁ ምዕራፍ በቁጥር 12 ላይ የተመለከትን እንደኾነ እግዚአብሔር በለዓምን እንዳትኼድ ብሎ ከልክሎት የነበረ መኾኑን እንገነዘባለን። ይኹን እንጂ እግዚአብሔር አምላክ የሰውን ልጅ ከፈጠረ በኋላ ሙሉ የፈቃድ ነጻነት የሰጠው በመኾ⸱ አንዳንድ ድርጊቶች እግዚአብሔር የማይፈቅዳቸው መኾናቸውን ለሰው ልጅ ከማመልከቱ በቀር የሰው ልጅ አንድን ድርጊት እንዲያደርግ ወይም እንዳያደርግ አያስገድደውም። በዚህም መሠረት የሞዓቡ ንጉሥ ብዙ ስጦታ እሰጥሃለሁ ብሎ በድጋሚ በላከበት ጊዜ በበልዓም ዘንድ የመኼድ ፍላጎት ስለተፈጠረ እንዲኼድ ፈቀደለት እንጂ የበለዓም አካኼድ ግን በእግዚአብሔር የተደገፈ አልነበረም።

ምንም እንኳ አንዳንድ ኹናቴዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ያልተደገፉ ቢኾኑ የሰው ልጅ የሚፈልገውን ድርጊት ላለመከልከል እግዚአብሔር ከቅሬታ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ የእስራኤል ልጆች ንጉሥ አንግሥልን ብለው ነቢዩን ሳሙኤልን መላልሰው በጠየቁት ጊዜ እግዚአብሔር የፈቀደላቸው ከቅሬታ ጋር መኾኑን ሲያመለክት ነቢዩ ሆሴዕ "በቅሬታዬ ንጉሥን ሰጠሁህ በቁጣዬም ሻርሁት።" ብሏል። (ሆሴ. ም.13 ቁ:11 ፥ 1ኛ ሳሙ. ም.8 ቁ.7 እና 22፥ ም.12 ቁ.12 – 13) እንዲሁም ፈሪሳውያን ለጠየቁት ጥያቄ ጌታ በሰጣቸው መልስ ሙሴ



ሚስቶቻቸውን ለመፍታት በፈለጉ ጊዜ ሁሉ የፍቺ የምስክር ወረቀት ሰጥተው ለመፍታት እንደሚችሉ የጻፈላቸው የልባቸውን ደንዳናነት አይቶ ነው እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድስ እንደዚያ ኾኖ አይደለም ብሎ አቸዋል። (ማር. ም.10 ቁ:2 — 10)

በዚህም ዐይነት እግዚአብሔር አስቀድሞ በለዓምን አትኺድ ካለው በኋላ የመኼድ ፍላጎት ያለው መኾኑን የሰውን ጥልቅ ሐሳብ የሚያውቀው አምላክ ስለተገነዘበው እንዲኼድ ከቅሬታ ጋር ቢፈቅድለትም ከንጉሡ ጋር በሚኼድበት ጊዜ እግዚአብሔር የሚፈቅድለትን ንግግር ብቻ እንዲናገር አስጠነቀቀው። እግዚአብሔርም የተቆጣበት ምክንያት ከንጉሡ በሚያገኘው ስጦታ ተደልሎ የእስራኤልን ሕዝብ ለመርገም ፍላጎት የነበረው መኾኑን ስላወቀበት ነው።

44.በኦሪት ዘኍልቊ ም.25 ቁ:9 ላይ በመቅሰፍት የሞተው ኻያ አራት ሺሕ ሰው ነበር ሲል በመጀመሪያ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.10 ቁ.8 ላይ እንደተገለጸው ደግሞ በአንድ ቀን የሞቱት ኻያ ሦስት ሺሕ ናቸው ስለተባለ ኹለቱ አባባሎች የተለያዩት ለምንድነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በኦሪት ዘኍልቊ የተነገረው በመቅሰፍቱ የሞቱትን ሰዎች ብዛት ሲኾን በሐዋርያው መልእክት የተገለጸው ግን በአንድ ቀን ብቻ የሞቱትን ሰዎች ብዛት ነውና ኹለቱ አባባሎች ርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

45. በኦሪት ዘኍልቁ ም.31 ላይ እስራኤላውያን ምድያማውያንን እንደደመሰሱአቸው የተነገረ ኾኖ ሳለ በመጽሐፈ መሳፍንት ም.6 ደግሞ ምድያማውያን እስራኤላውያንን አሸንፈው እንደገዙአቸው ተገልጾአል። ማድያማውያን ቀደም ብለው የተደመሰሱ ከኾነ እንዴት አድርገው እስራኤላውያንን አሸንፈው ሊገዙአቸው ቻሉ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ምድያማውያን በአንድ አካባቢ ብቻ ሳይኾን በብዙ ቦታዎች ተበታትነው ስለሚኖሩ እስራኤላውያን ኹሉንም አላጠፉአቸውም ነበር። ከዚህም ሌላ እስራኤላውያን ማሸነፋቸውን ባዩ ጊዜ ብዙዎቹ ምድያማውያን ከጦርነት ሸሽተው ተደብቀው ሲኖሩ ከጊዜ ብዛት በመዋለድ



www.ethiopianorthodox.org

ሊበዙ ችለው መኾን አለበት። እነርሱም በእስራኤል ላይ የበቀል እርምጃ
ለመውሰድ አጋጣሚ ጊዜን ሲጠባበቁ የኖሩ ናቸው። ይህንን የበቀል
እርምጃ ለመውሰድ አመቺ ጊዜ ይጠባበቁ እንደነበረ ልንረዳ የምንችለው
ለምሳሌ በመጽሐፈ መሳፍንት ም. 6 ቁ: 3 – 4 "እስራኤል ዘር በዘሩ
ጊዜ ምድያማውያን፥ አማሌቃውያንና በምሥራቅ የሚኖሩ ሰዎች ይመ
ጡባቸውና በእነርሱ ላይ ይሰፍሩ ነበር" የሚለውን አባባል በመመልከት
ነው። የእስራኤል ልጆች የሕግ አፍራሻነት በደል በሚፈጽሙበት ጊዜ
ኹሉ ምን እንደሚደርስባቸው ነቢዩ ሙሴ ሲያስጠነቅቃቸ "እግዚአ
ብሔር ከጠላቶችህ ፊት የተመታህ ያደርግሃል፤ በአንድ መንገድ ትወጣ
ባቸዋልህ፤ በሰባት መንገድ ከእነርሱ ትሸሻለህ" ብሏል። (ዘዳ. ም.28
ቁ:25)

የእስራኤል ልጆች በኀጢአተኛነታቸው እግዚአብሔርን በበደሉ
ጊዜ ኹሉ መሸነፍና መዋረድ እንደሚደርስባቸው የተገለጸላቸው ለመ
ኾኑ በኦሪት ዘዳግም ም.28 ቁ:15 – 46 እና በመጽሐፈ ኢያሱ ም.23
ቁ:12 – 13 መመልከት እንችላለን።

46. በኦሪት ዘኍልቁ ም.31 ቁ: 17 ላይ ምንም ጥፋት የሌለባቸውን ከል
ጆች ወንዶችን ኹሉና ከሴቶች ደግሞ ወንድን በመኛታ የሚያውቁትን
ኹሉ ግደሉ የሚለው የሙሴ ትእዛዝ በትንቢት ዳንኤል ም.9 ቁ.14 ላይ
"እግዚአብሔር በሚሠራው ኹሉ ጻድቅ ነው" ከሚለውና እንዲሁም
በመዝሙር 7 ቁ.11 ላይ "እግዚአብሔር የእውነት ዳኛ ነው" ከሚለው
ጋር እንዴት ሊታረቅ ይችላል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ወንዶችንና ለመውለድ የተዘጋጁትን ሴቶች እንዲገድሉ ትእዛዝ
የተላለፈው ወደፊት በእነርሱ ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን ኹናቴ
በማሰብ ነው። ሴቶቹ የሚወልዱአቸው ልጆች ወደፊት አድገው ለሕዝቡ
እንቅፋት ስለሚኾኑ ኀጢአት ከመድረሱ በፊት ለኀጢአት መንገድ
ሊከፍት የሚችለውን እንቅፋት ማስወገድ አስፈላጊ በመኾኑ ነው።

በመጽሐፈ ኢያሱ ም.6 ላይ እንደተገለጸው እስራኤላውያን የኢ
ያሪኮን ከተማ በያዙ ጊዜ ረዓብ ከተባለችው ሴት በቀር አንድም እንዳ
ያስተርፉና ኹሉንም እንዲገድሉ ታዘዋል። ይህም የኾነበት ምክንያት
ጣዖት ማምለክን ለእስራኤል ልጆች እንዳያስተምሩ ጥንቃቄ ለማድረግ



ሲባል ነው። እግዚአብሔርም ሰዎችን ለመቅጣት በልዩ ልዩ መንገድ
ይጠቀማል። አንዳንድ ጊዜ ወረረሽኝ፥ ሌላ ጊዜ ጦርነት በሌላ ጊዜ
ደግሞ የመሬት መንቀጥቀጥና ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ ኹኔ ታዎችን
ጥፋተኛውን ለመቅጫ ይጠቀምባቸዋል። ኢያሱም ከነዓናውያንን
ቢተዋቸው ኖሮ የጣዖት ማምለክ ባህላቸውን ለእስራኤል ልጆች ባስ
ተማሩ ነበር።

በዚህም መሠረት እግዚአብሔር ጻድቅና እውነተኛ ፍርድን ፈራጅ
መኾኑ ባይካድም የእርሱ ዕውቀት ጊዜና ቦታ የማይወስነው በመኾኑ
ወደፊት ሊከሠት ከሚችል ችግር ለመከላከል አስቀድሞ ፍርድ የሚሰ
ጥበት ጊዜ መኖሩ ሊያስገርመን አይገባም። ስለዚህ የሙሴም ትእዛዝ
ቢኾን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ አለመኾኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

47. በኦሪት ዘኍልቍ ም.35 ቁ:19 ላይ ደም ተበቃይ ነፍስ ገዳይን
እንዲገድለው የተፈቀደለት ሲኾን ወደ ሮሜ ሰዎች በተላከው የቅዱስ
ጳውሎስ መልእክት ም.12 ቁ:19 ላይ "ቁጣን ለእግዚአብሔር ተው እን
ጂ ራሳችሁ አትበቀሉ" ከሚለው ጋር እንዴት ሊታረቅ ይችላል ተብሎ
ይጠየቅ ይኾናል።

እነዚህ ኹለት ጥቅሶች ልዩነት ያላቸው ኾኖ ሳይኾን ጌታ በማቴዎስ
ወንጌል ም.5 ቁ:17 ላይ እንደገለጸው ሕጋትን ፍጹም ለማድረግ
እንደመጣ ከሰጠው ትምህርት ጋር ግንኙነት አለው።

በኦሪቱ ሕግ የተገለጸው የበቀል ጉዳይ ማንንም ሰው ያለበቂ ምክ
ንያት መግደል የማይገባ መኾኑን ለመግለጽ ነው። ከዚያ በፊት ግን ሰዎ
ች ዝም ብለው እርስ በርሳቸው ይገዳደሉ ስለነበር ያንን ለመከልከል ታስ
ቦ ዘመዱ የተገደለበት ሰው ብቻ ለመበቀል እንደሚችል ተፈቅዶለት ነበ
ር። በሮሜ ም.12 ቁ:19 ላይ በተገለጸው መሠረት በቀል መከልከሉ ለግ
ድያም ኾነ ለሌላ ክፉ አድራጎት ምክንያት የኾነውን አሠራር ማለት የአፍ
አዊውን ድርጊት ብቻ ሳይኾን የውሳጣዊውን ስሜት ኹሉ ለመግታት
ታስቦ ነው። ለምሳሌ ጌታ አትግደል የሚለውን ትእዛዝ ካመለከተ በኋላ
እኔ ግን በወንድሙ ላይ የሚቈጣ እንኳን ይፈረድበታል እላችኋለሁ ብሎ
አል። (ማቴ. ም.5 ቁ.21)



www.ethiopianorthodox.org

ቁጣ ጠብን አስከትሎ ወደ ግድያ ሊያመራ ስለሚችል አስቀድሞ ቁጣን ማስወገዱ የነፍስ ገዳይነቱን መንሥኤ ያስወግዳል ማለት ነው። በዚሁም ዐይነት በቀል ላለመበቀል ለእግዚአብሔር መተው የግድያን ማለት የነፍሰ ገዳይነትን መንሥኤ ስለሚያጠፋ ነፍሰ ገዳይነትም በዚያው መጠን ይጠፋል ማለት ነው። ቁጣንና የበቀልን ስሜት ማስወገድ አትግደል ለሚለው ሕገ እግዚአብሔር ተፈጻሚነት ዋናዎቹ መፍትሔዎችናቸው።

በዚህም መሠረት ጌታ አትግደል የሚለውን ሕገ እግዚአብሔር ፍጹም ለማድረግ አትቈጣ በማለቱና ያለምክንያት መገዳደልን መተው ከተለማመዱ በኋላ በቀልን መከልከሉ የመጀመሪያውን አትግደል የሚለውን ሕግ ለማጠናከር ከመኾኑ በቀር ጥቅሶቹ ርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ኾነው አይደለም። በኹለተኛው መጽሐፍ ማለት በሐዲስ ኪዳን ቁጥር 1 የጥያቄ መልስ ላይ እንደተመለከተው በብሉይ ኪዳን የሰውን አስተሳሰብ ለሐዲስ ኪዳን ለማዘጋጀት ሲባል ዘመዱ የተገደለበት ሰው እንዲበቀል ቢፈቀድለትም አትግደል የሚለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ፍጹም ለማድረግ አትቈጣና አትበቅል የሚሉት ትእዛዛት ታክለለውበታልና ይህ መኾኑን ተረድተን ጥቅሶቹ ርስ በርሳቸው የማይስማሙ አለመኾናቸውን መገንዘብ ይኖርብናል።

## ኦሪት ዘዳግም

ይህ መጽሐፍ በዚህ ስም የተጠራበት ምክንያት በኦሪት ዘጸአት፣ በኦሪት ዘሌዋውያንና በኦሪት ዘኍልቊ የቀረቡትን ሕግጋትና ትእዛዛት በስብከት መልክ ስለሚደግማቸው ነው። መጽሐፉም ሠላሳ አራት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፋፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 3 ድረስ ሲኾን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረጋቸውን ድርጊቶች በዝርዝር የሚያመለክት ነው።



ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 4 እስከ 26 ሲኾን በዚህም ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጣቸውን ሕጎችና ደንቦች በድጋሚ የሚተረጉም ነው።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 27 እስከ 30 ድረስ ሲኾን በዚህም ክፍል የግብረገባዊ ሕጎችን ማረጋገጥና የሕግ ፈጻሚነት ምክሮች ይገኙበታል።

አራተኛው ክፍል ከምዕራፍ 31 እስከ ምዕራፍ 34 ድረስ ሲኾን በዚህም ክፍል ኢያሱ የሙሴ ተተኪ ኾኖ ስለመሾሙ፥ የሙሴ የመጨረሻ ምክርና ለሕዝቡ ያቀረበው ቡራኬ፥ በም.18 ቁ.15 ስለክርስቶስ የተነበየው ግልጽ ትንቢት፥ የሙሴ መዝሙር፥ እንዲሁም የሙሴ ሞትና የመቃብሩ ቦታ አለመታወቅ ታሪክ ይገኙበታል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

48. በኦሪት ዘዳግም ም.2 ቁ.19 ላይ እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች የአሞንን መሬት አልሰጣችሁም ያለ ሲኾን በመጽሐፈ ኢያሱ ም.13 ቁ:24 — 25 እስራኤሎች የአሞንን መሬት እንደወሰዱ በመነገሩ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒዎች ይመስሉ ይኾናል።

አሞራውያን ከአሞናውያን ጋር በጦርነት ተጋጥመው በማሸነፋቸው የአሞናውያንን አገር ወስደው ነበር። በመጽሐፈ መሳፍንት ም.11 ቁ:11 — 28 መሠረት እስራኤላውያን አገሩን የወሰዱት በዚያን ጊዜ ይገዙት ከነበሩት ከአሞራውያን ነው እንጂ ከአሞናውያን ባለመኾኑ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒዎች አይደሉም።

49. በኦሪት ዘዳግም ም.7 ቁ.3 ላይ እስራኤላውያን የውጪ አገር ሰዎችን እንዳያገቡ የታዘዙ ሲኾኑ በመጽሐፈ ሩት ም.1 ቁ.4 እና ም.4 ቁ.13 ላይ ግን እስራኤላውያን የውጪ አገር ሰዎችን አግብተው በማግባታቸውም አልተወቀሱበትም። እንዲሁም ንጉሥ ሰሎሞን የግብፁን ንጉሥ የፈርዖንን ልጅ እንዳገባ በአንደኛ ነገሥት ም.3 ቁ:1 ላይ በመገለጹ እነዚህ ኹለቱ ኹኔታዎች ተቃራኒዎች ይመስሉ ይኾናል።



www.ethiopianorthodox.org

የውጪ አገር ሴቶችን እንዳያገቡ የተከለከሉት እነዚያ የውጪ አገር ሴቶች ወደጣዖት አምላኪነት እንዳይጐትቱአቸው ለመጠንቀቅ ሲባል ነው እንጂ ይህ የማይኾን ከኾነ ግን ማግባት አልተከለከሉም። ለምሳሌ እስራኤሎች ከምድያማውያን ጋር በተዋጉ ጊዜ ወንድ የኾነውን ኹሉ ከሕ ፃን ጀምሮ እንዲሁም ወንድን በመኝታ ያወቀች ኹሉ ሳትቀር እንዲገ ድሉና ወንድ ያላወቁትን ሴቶች ግን ለራሳቸው እንዲያስቀሩ የታዘዙ መኾናቸውን በኦሪት ዘኍልቁ ም.31 ቁ:18 መመልከት እንችላለን።

ከላይ እንደተገለጸው እስራኤላውያን የሌላ አገር ሴቶች ያገቡ እንደ ኾነ ሴቶቹ ወደአምልኮ ጣዖት ይስቡአቸው ይኾናል ተብሎ የተሰጋው ስጋት ምን ያኽል እውነት መኾኑን ልንረዳ የምንችለው በመጀመሪያው መጽሐፈ ነገሥት ም.11 ቁ:1 — 8 እንደተገለጸው ብዙ የውጪ አገር ሴቶችን ባገባው በንጉሥ ሰሎሞን ላይ የደረሰውን ኹናቴ በመመልከት ነው። ለእነዚያ ለውጪ አገር ሴቶች ሲል በጥበብና በሀብት ያበለጸገውን ፈጣሪውን ትቶ ጣዖትን አመለከ።

50. በኦሪት ዘዳግም ም.7 ቁ:6 ላይ "ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አንተ ቅዱስ ሕዝብ ነህና፥ በምድር ፊት ከሚኖሩ አሕዛብ ኹሉ ይልቅ ለእርሱ ለራሱ ሕዝብ ትኾንለት ዘንድ አምላክህ እግዚአብሔር መረጠህ" የሚል ሲኾን ፡ በምዕራፍ 10 ቁ:17 ላይ "እንግዲህ አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ፥ የጌቶችም ጌታ፥ ታላቅ አምላክ፥ ኀያልም፥ የሚ ያስፈራም፥ በፍርድ የማያዳላ፥ መማለጃም የማይቀበል ነው" ተብሎ አል።

በትንቢት ኤርምያስ ም.32 ቁ:19 ላይ ደግሞ "በምክር ታላቅ፥ በሥራም ብርቱ ነህ፤ ለኹሉም እንደመንገዱና እንደሥራው ፍሬ ትሰጥ ዘንድ ዓይኖችህ በአዳም ልጆች መንገድ ኹሉ ተገልጠዋል" ተብሎአል።

በሐዋርያት ሥራ ም.10 ቁ:34 — 35 "ጴጥሮስም አፉን ከፍቶ እንዲህ አለ፤ እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንደማያዳላ ነገር ግን በአሕዛብ ኹሉ እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደኾነ በእውነት አስተዋልሁ።"



ወደገላትያ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.6 ቁ17 ላይ "ራሳችሁን አታታልሉ፤ በእግዚአብሔር ላይ መቀለድ አይቻልም፤ ምክንያቱም ሰው የሚያጭደው የዘራውን ነው" ተብሎአል።

ታዲያ በመጀመሪያ የተጠቀሰውን የእስራኤል ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ ተለይቶ የመመረጥ ጉዳይ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ኹሉ እን ደየሥራቸው እንጂ ያለምክንያት የማይመርጥ ወይም የማይተው መኾኑን ከሚገልጹት ጥቅሶች ጋር እንደምን ለማስታረቅ ይቻላል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.9 ቁ:1 — 5 ላይ የእስራኤልን ልጆች ተመራጭነት በሚመለከት ምን እንዳለ እንመልከት " የክርስቶስ እንደመኾኔ መጠን እውነትን እናገራለሁ እንጂ አልዋሽም፤ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራው ሕሊናዬም እንደማልዋሽ ይመ ሰክርልኛል። ትልቅ ኀዘንና የማያቋርጥ ጭንቀት በልቤ አለ፤ በሥጋ ዘመ ዶቼ ስለኾኑት ወገኖቼ ከክርስቶስ ተለይቼ የእግዚአብሔር እርግማን ቢደ ርስብኝ በወደድሁ ነበር። እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ ናቸው፤ እግዚአብሔር እነርሱን ልጆቹ አደረጋቸው፤ ክብሩን ገለጠላ ቸው፥ ቃል ኪዳን ገባላቸው፤ ሕግን ሰጣቸው፤ እውነተኛውን አምልኮ አሳያቸው፤ የተስፋውንም ቃል ሰጣቸው። እነርሱ በትውልዳቸው ከነገድ አባቶች የመጡ ናቸው፤ ክርስቶስም በሥጋ የመጣው ከእነርሱ ነው፤ እርሱ ከኹሉ በላይ የኾነ የተባረከ አምላክ ነው።"

እዚህ ላይ የተመዘገበውና ክርስቶስንም ባለመቀበላቸው የተወሰ ደባቸው የአይሁድ ተመራጭነት በሚከተለው ኹናቴ ተዘርዝሮአለ።

አንደኛ/ እስራኤላውያን መኾናቸዉ :- ይኸውም አባታቸው ያዕቆብ በሕልሙ ሲታገል ከቆየ በኋላ ካልባረክኸኝ አልለቅህም በማለቱ እስራ ኤል የሚል ስም ሰጥቶት ባርኮታል። ያዕቆብ ማለት ተረከዝን ያዥ ማለት ሲኾን እስራኤል ማለት ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ማሸነፍ ማለ ት ነው። ስለዚህ እስራኤል ለሚለው ቃል ያዕቆብ የተባረከበት ስም በመ ኾኑ ለተመራጭነታቸው አንድ መንገድ ነው ማለት ይኾናል። (ዘፍ. ም.32 ቁ:24 — 28)



www.ethiopianorthodox.org

ኹለተኛ/ የእግዚአብሔር ልጅነታቸው:- ከግብጽ ባርነት ነጻ አውጥቶ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ልጁ አድርጎታል። ይህንንም አባባል በሚከተሉት ማስረጃዎች እንመልከት። "ፈርዖንንም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ እስራኤል የበኩር ልጄ ነው፤ ይገዛልኝ ዘንድ ልጄን ልቀቅ አልሁህ፤ አንተም ትለቀው ዘንድ እንቢ አልህ፤ እነሆ፥ እኔ የበኩር ልጅህን እግድላለኹ ትለዋልህ (ዘጸ. ም.4 ቁ:22 – 23)

"እስራኤል ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት፤ ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት" (ሆሴ. ም.11 ቁ:1)

ሦስተኛ/ ክብር የተገለጸላቸው መኾኑ :- በሲና ተራራ ላይ የነበረውና በኋላም በምድረ በዳ አብሮአቸው የተጓዘው የእግዚአብሔር ክብር ማለት ነው። ይኸውም ክብር በታቦቱ የሳጥን መክደኛ ላይ ኾኖ በየጊዜው በመካከላቸው ልዩ ልዩ ምልክቶችን አሳይቶአል። ይህም የእግዚአብሔር ክብር ወደባቢሎን እስከተማረኩበት ጊዜ ድረስ አልተለያቸውም (ሕዝ. ም.10 ቁ:4 እና 18 ፥ ም.11 ቁ:22 – 23)። እንደገና ደግሞ በክርስቶስ ሰውነት በመካከላቸው ተገኘ (ዮሐ. ም.1 ቁ:14)

አራተኛ/ ቃል ኪዳን :-ይህ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው የበረከት ቃል ኪዳን ነው። (ዘፍ. ም.12 ቁ:1 – 3 ፥ ም.17 ቁ:1 – 8 ፥ ም. 22 ቁ : 15—17)

አምስተኛ/ ሕግ የተሰጣቸው መኾኑ:- በሲና ተራራ ላይ ሕገ እግዚአብሔር የተሰጠው ለእስራኤል ሕዝብ ነው። (ዘጸ. ም.19 – 40)

ስድስተኛ/ አምልኮተ እግዚአብሔር:- በመጀመሪያ በምስክሩ ድንኳን፥ በኋላ ደግሞ በሰሎሞን ቤተ መቅደስ ውስጥ ይከናወን የነበረው የአምልኮተ እግዚአብሔር ሥነ ሥርዓት የተሰጠው ለእስራኤል ሕዝብ ነው። (ዘጸ. ም.19 – 40 ፥ 1ኛ ነገ. ም.8 – 9)

ሰባተኛ/ ተስፋ :- በብሉይዘመ ን ብዙ ተስፋ ተሰጥቶአቸው ነበር። (ዘፍ. ም.35 ቁ :12 ፥ ዘጸ. ም. 3 ቁ:15 — 17 , 20 — 22)



ስምንተኛ/ አባቶች:- እንደ አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብና ሌሎችም ዝነኞች የእምነት አባቶች የነበሩአቸው በመኾኑ የእነዚያ አባትነት ለእግዚአብሔር በረከት እንደሚያበቃቸው ያምኑ ነበር። ለክርስቲያኖች ግን ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ አባት እንደሌላቸው በማቴዎስ ወንጌል ም.23 ቁ:9 ተገልጾአል።

ዘጠነኛ/ ክርስቶስ በሥጋ የመጣው ከእነርሱ ነው።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ለእስራኤል ሕዝብ ተመራጭነት ምልክት ናቸው ብሎ ሐዋርያው ጳውሎስ ያቀረባቸው ነጥቦች ናቸው።

የአይሁድ ሕዝብ እንደ አጋጣሚ ኾኖ እንደነ እነአብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብን የመሳሰሉ ለእግዚአብሔር ቅርብ የኾኑ አባቶች ስለ ነበሩባቸውና ከመካከላቸውም ብዙ ደጋግ ሰዎች ስለነበሩባቸው እግዚአብሔር ለነዚያ ደጋግ አባቶቻቸው የገባውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ሲል መረጣቸው እንጂ ከሌሎች ወገኖች ለይቶ ለእነርሱ በማድላት የመረጣቸው አይደለም። ይህም ብቻ ሳይኾን እግዚአብሔር አንዱን ወገን አበርትቶ ሌላውን ወገን የማጥቃት ኀይል እንዲኖረው የሚያደርገው ለአጥቂው ወገን በማድላቱ ሳይኾን ተጠቂውን ወገን በአጥቂው አማካይነት ለመቅጣት አስቦ ነው። ስለዚህም እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የተናገረውን እንመልከት።

"አምላክህ እግዚአብሔር ከፊትህ ካወጣቸው በኋላ፣ ስለጽድቁ እወርሳት ዘንድ ወደዚች ምድር እግዚአብሔር አገባኝ ስትል በልብህ አትናገር፤ እነዚህን አሕዛብ ስለኀጢአታቸው እግዚአብሔር ከፊትህ ያወጣቸዋል። ምድራቸውን ትወርሳት ዘንድ የምትገባው ስለጽድቅህና ስለልብህ ቅንነት አይደለም፤ ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ከፊትህ በሚያጠፋቸው በእነዚያ አሕዛብ ኀጢአት ምክንያትና ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ፥ ለያዕቆብም የማለላቸውን ቃል ይፈጽም ዘንድ ነው" (ዘዳ. ም.9 ቁ:4 – 5)

እግዚአብሔርም ለሚወዱትና ትእዛዙን ለሚጠብቁ ቃል ኪዳኑንና ምሕረቱን እስከ ሺሕ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ የታመነ አምላክ መኾኑ በኦሪት ዘዳግም ም.7 ቁ:9 ላይ ተገልጾአል።



www.ethiopianorthodox.org

በዚህም መሠረት የአባቶቻቸው የእነአብርሃም የታማኝነት ዋጋ ለልጆቻቸው ለእስራኤል ሕዝብ ቢተላለፍም እንኳ ልጆቻቸው ግን ለእግዚአብሔር ሕግ ያላቸው ታማኝነት የጸና እስካልኾነ ድረስ በተመራጭነታቸው ሊቀጥሉ አይችሉም። ስለዚህም ነው እግዚአብሔር የሚቀጥለውን ማስጠንቀቂያ የሰጣቸው።

"ተመልከት ዛሬ በፊትህ ሕይዋትንና መልካምነትን፥ ሞትንና ክፉትን አኑሬአለሁ። በሕይወት እንድትኖር፥ እንድትበዛም፥ አምላክህም እግዚአብሔር ልትወርሳት በምትገባባት ምድር እንዲባርክህ አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድድ ዘንድ በመንገዱም ትኼድ ዘንድ ትእዛዙንና ሥርዓቱን ፍርዱንም ትጠብቅ ዘንድ ዛሬ እኔ አዝዝሃለሁ። ልብህ ግን ቢስት፥ አንተም ባትሰማ ብትታለልና ለሌሎች አማልክት ብትሰግድ፥ ብታመልካቸውም ፈጽማችሁ እንደምትጠፉ እኔ ዛሬ እነግራችኋለሁ፤ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ትወርሳት ዘንድ በምትገባባት ምድር ዘመናችሁን አታስረዝሙም።" (ዘዳ. ም.30 ቁ.15 – 18)

የእስራኤል ሕዝብ ግን ለተመራጭነቱ ብቁ ኾኖ ባለመገኘቱ ስደትና ምርኮ ያጋጠመው ከመኾኑም በላይ ነቢዩ ሆሴዕ በእስራኤል ሕዝብ ቦታ ሌላ ወገን የሚተካ መኾኑን ሲያመለክት "ምሕረት የሌላትን እምራለሁ፤ ሕዝቤ ያልኾነውንም አንተ ሕዝቤ ነህ እለዋለሁ፤ እርሱም አንተ አምላኬ ነህ ይለኛል" ብሎአል። (ሆሴ. ም.2 ቁ.25)። ይህም የሚ ያመለክተው ወንጌል በመጀመሪያ የተሰበከው ለአይሁድ ሕዝብ ቢኾንም እነርሱ የማይቀበሉት ከኾነ በኋላ ነው ለዓለም ሕዝብ በመላ እንዲሰበክ የተደረገው።

አሁን እንግዲህ የአባቶችን በጐ ተግባር እስከ ሺ ትውልድ ድረስ ለመክፈል ታማኝ የኾነው አምላክ የእስራኤል ሕዝብ ምርጥ ሕዝብ ቢያደርገውም ይህ ምርጥ ሕዝብ መኾንና የእግዚአብሔርም በረከትና ጸጋ ከእርሱ አለመለየት ሊቀጥል የሚችለው የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ረገድ ያለበትን ግዴታ የሚያሟላ ኾኖ ሲገኝ ብቻ መኾኑ ተመላልሶ ተገልጾአል። ከዚያም ሌላ የእስራኤል ሕዝብ በሌሎች ሕዝቦች ላይ ድልን የመጐናጸፍ ዕድል ያጋጠመው እነዚያን ተሸናፊዎቹን ወገኖች እግዚአብሔር በእስራኤል አማካይነት ሊቀጣቸው ስለፈለገ ነው እንጂ ለእስራኤል ሕዝብ አዳልቶ አይደለም። ይህም በመ



ኾኑ ቀደም ተብለው የተዘረዘሩት ጥቅሶች የተለያየ ትርጉም ያላቸው ከመኾናቸው በቀር እርስበርሳቸው የሚቃረኑ አባባሎች አይደሉም። እግዚአብሔር የትክክለኛ ፍርድ ባለቤት መኾኑና ለማንም የማያዳላ ፈራጅ መኾኑ ማንም ሊያስተባብለው የማይችል እውነት ነው። የሰዎችንም ዋጋ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ለመክፈል ታማኝ አምላክ በመኾኑ የእስራኤልን ሕዝብ ተመራጭ ሕዝብ ያድርገው እንጂ በተመራጭነቱ ለመቀጠል የእግዚአብሔርን ግዴታዎች ማሟላት እንደነበረበት ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታል። እግዚአብሔርም ቅን ታዛዦች የሚኾኑትን ሰዎች ኹሉ ተገቢ የኾነ ቦታዎቻቸውን ይሰጣቸው ነበር እንጂ እስራኤላውያን ስላልኾኑ ብቻ ዋጋ የነሣቸው አይደሉም። ለምሳሌ በምሳሌነት የሚጠቀሰው ኢዮብን የመሰለ ታላቅ ጻድቅ እስራኤላዊ አልነበረም። ለመድኀኒታችን ምሳሌ ኾኖ የተጠቀሰው መልከጼዴቅ የተባለው የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን እስራኤላዊ አልነበረም። በሌላ በኩል ደግሞ የእስራኤል ልጆች ኀጢአት በሚበዛበት ጊዜ እግዚአብሔር እነርሱን ከሚቀጣባቸው መንገዶች አንዱ በጦርነት እንዲሸነፉ ማድረግ ነበር። (ኢያ. ም. 7 ፥ ምሳ. ም. 2 ቁ.11–15 ፥ ም.3. ቁ. 7–8 ፥ 12–14፥ ም.4 ቁ. 1–3 ፥ ም.6 ቁ. 1–6 ፥ ም. 13 ቁ. 1፥ 1ኛ ሳሙ. ም. 31)። በጦርነቱም አሸንፈው አገራቸውን በመያዝ የሚገዙአቸው፥ የሚማርኩአቸው ወይም የሚገድሉአቸው ኢአማንያንና ጣዖት አምላኪዎች መኾናቸው የሚያመለክተው እግዚአብሔር አንዱን ወገን አሸናፊ ሌላውን ወገን ደግሞ ተሸናፊ የሚያደርገው አሸናፊው ወገን ለእግዚአብሔር ታማኝ በመኾኑ ሳይኾን ነገር ግን እግዚአብሔር ተሸናፊውን ወገን በአሸናፊው አማካይነት ለመቅጣት ፈቅዶ ነው።

ስለዚህ ከላይ በቀረቡት ዝርዝር ማስረጃዎች መሠረት እርስ በርሳቸው ተቃራኒ የሚመስሉት ጥቅሶች ተቃራኒ አለመኾናቸውን ተረድተን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

51. በኦሪት ዘዳግም ም. 18 ቁ 15 እና 18 ላይ እንደተገለጠው እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ያስነሣላቸዋል ተብሎ የተነገረውን አባባል በዮሐንስ ወንጌል ም. 5 ቁ. 46 በሐዋርያት ሥራ ም. 3 ቁ. 22 እና ም. 7 ቁ. 37 ላይ ስለጌታችን ስለመድ ሮኒ ታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተነገረ ተደርጎ መቅረቡ



www.ethiopianorthodox.org

በመድኀኒታችን መለኮታዊ ክብር ከምናምነው እምነት ጋር እንዴት ይታረቃል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ሙሴ ለጌታ እንደምሳሌ መቅረቡ ምንም የሚያስገርመን ጉዳይ መኾን የለበትም። ምክንያቱም ለምሳሌ በትንቢተ ሆሴዕ ም. 11 ቁ. 1 ላይ ልጄን ከግብጽ ጠራሁት ተብሎ ስለ እስራኤል የተነገረውን በመጽ ቀስ ወንጌላዊው ማቴዎስ በም. 2 ቁ. 15 ላይ ለጌታ እንደተነገረ አድርጎ አቅርቦታል።

በሙሴ በተጻፈው ኦሪት ዘፍጥረት ም. 3 ቁ. 15 ላይ እግዚአብ ሔር እባብን የረገመው በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ ብሎ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደገላትያ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም4. ቁ. 4 ላይ "ጊዜው ሲደርስ ከሴት የተወለደውን ልጁን እግዚአብሔር ላከልን" በማለት የሙሴን ጽሑ ፍ አገናዝቦታል። ሌላው ሙሴ ከጌታ ጋር በተመሳሳይነት የቀረበበት ኹና ቴ ደግሞ ሙሴ በመሪነቱ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ሕዝብ የባርነት ቀንበር እንዳወጣ ኹሉ ጌታም በቤዛነቱ ዓለምን ከሰይጣን ባርነት ነጻ አውጥቷል።

ብዙ ጊዜ ተመላልሶ እንደተገለጠው እንደማንኛውም ሰው ስለጌታ በሚነገርበት ጊዜ ኹሉ መለኮት በተዋሐደው ትስብእቱ መኾኑ መረሳት የለበትም።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሰጠው ትርጓሜ ደግሞ እንደሚከተለው ነው።

"ስለሚሰሙት ሰዎች የአእምሮ ደካማነትም በወገኖቹ ኹሉ ዘንድ እንደ ሙሴ ነው አለ ስለሚሰሙት ሰዎች የአእምሮ ዳካማነት ነው እንጂ በሙሴ ለምን ይመስለው ነበር? ይኸን ነገር ከመስማት ጕሮዋቸውን እንዳይከለክሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ካመኑ በኋላ ዕብራውያን በዚህ ሰው በሙሴ የሚያምኑት እምነት የሚያከብሩት ክብር ጥቂት አይ ደለምና ሰው ስለኾነ ስለዚህ በሙሴ መስሎ ይናገር ጀመረ። ከዚህ በኋላ አምላክነቱን በየጥቂቱ ተናገረ። ለሙሴ ገዥ ፈጣሪ መኾኑን እስኪያስረ ዳቸው ድረስ በመገኖቹ ላይ እንደ ሙሴ ነው በማለቱ በፊት ከእርሱ ጋር



አስተካክሎት ነበር የሙሴ ወገኖች ሕዝብ ናቸውና።" (ሃይ. አበ. ገጽ 224)

ስለዚህ ጌታ በሙሴ ምሳሌነት መቅረቡ ከላይ በተመለከተው የአ ቀራረብ ዘይቤ ለማቅረብ ተብሎ ነው እንጂ የጌታን መለኮታዊ ክብር ለመካድ ታስቦ አይደለምና አለመኾኑን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠን ቀቅ።

52. በኦሪት ዘዳግም ም. 24 ቁ. 1 ላይ "አንድ ሰው አንዲት ሴት ካገባ በኋላ አንድ ነውር አግኝቶባት ቢጠላት የተፈታችበትን ምክንያት የሚ ገልጽ የፍቺ ደብዳቤ ጽፎ በመስጠት ከቤቱ ያባርራት" የተባለ ሲኾን በማ ቴዎስ ወንጌል ም. 19 ቁ. 9 ላይ ግን "አንድ ሰው በዝሙት ምክ ንያ ት ካልኾነ በቀር ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ሚስት ቢያገባ አመንዝራ ነው" በመ ባሉ ኹለቱ ጥቅሶች የሚቃረኑ ይመስለን ይኾናል።

የመጀመሪያውን ጥቅስ በመመልከት ብቻ እግዚአብሔር በኦሪቱ ሕግ ውስጥ መፋታትን የፈቀደ ሊመስለን አይገባም። በዚህ ጉዳይ ላይ ፈጣሪ አምላክ በነቢዩ አማካይነት ምን ዐይነት መግለጫ እንዳቀረበልን ቀጥለን እንመልከት። "እናንተ የምታደርጉት ሌላው ነገር ይህ ነው፤. ለቅሶና ዋይታ በበዛበት እንባ የእግዚአብሔርን መሠዊያ ትሸፍናላችሁ፤ ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር ዳግመኛ መሥዋዕታችሁን አይመለከትም፤ በደስታም አይቀበለውም። ስለምን መሥዋዕታችንን አይቀበለውም ብላ ችሁ ብትጠይቁም ምክንያቱ ይህ ነው፤ በወጣትነታችሁ ጊዜ ላገባ ችኋቸው የሕግ ሚስቶቻችሁ የገባችሁላቸውን ቃል ኪዳን አፍርሳችኋል፤ እነርሱ እኮ የቃል ኪዳን ጓደኞቻችሁ ነበሩ፤ እናንተ ግን በእግዚአሔር ፊት በቃል ኪዳን ባገባችኋቸው ሚስቶቻችሁ ላይ ተንኰል በመሥራት ታማኝነታችሁን አጓድላችኋል። ታዲያ እግዚአብሔር እናንተና ሚስቶ ቻችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ እንዲኖራችሁ አድርጎ አልነበ ረምን? በዚህስ የእርሱ ዓላማ ምን ነበር? ዋና ዓላማው የእግዚአብሔር ሕዝቦች የኾኑ ልጆችን እንድትወልዱ በመፈለግ ነበር፤ ስለዚህ ከእናንተ እያንዳንዱ ለሚስቱ የገባውን ቃል ኪዳን ላለማፍረስ ልዩ ጥንቃቄ ያድ ርግ። እኔ የባልና ሚስትን መፋታት እጠላለሁ፤ ከእናንተ አንዱ እንኳ ይህን ዐይነት ክፉ የኾነ የመፋታት ተግባር መፈጸሙን አልወድለትም፤ ስለዚህ ለሚስቶቻችሁ ታማኞች ለመኾን የገባችሁላቸውን ቃል ኪዳን



www.ethiopianorthodox.org

ላለማፍረስ ልዩ ጥንቃቄ አድርጉ ይላል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር።" (ሚል. ም.2 ቁ. 13–16) ይህ ከኾነ ታዲያ በኦሪት ዘዳግም ም. 24 ቁ. 1 ላይ ለምን መፋታትን ፈቀደ? ለዚህ ጥያቄ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ዐይነት መልስ እንደሰጠ ቀጥለን እን መልከት።

ፈሪሳውያን ጌታን ሊፈትኑት ፈልገው ስለፍቺ ጉዳይ በጠየቁት ጊዜ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ሲፈጥር ወንድና ሴት አድርጎ ከፈጠረ በኋላ ሰው አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር ይተባበራል በማለቱ አንድ ሥጋ ይኾናሉ እንጂ ኹለት አይደሉም ስለዚህ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየው ብሏቸዋል። ፈሪሳውያንም ይህን የጌታን መልስ ከሰሙ በኋላ ታዲያ ሙሴ ለምን እንድንፈታ ፈቀደልን ብለው በድጋሚ ለጠየቁት ጥያቄ "ሙሴማ የልባችሁን ድንዳኔ አይቶ ሚስቶቻችሁን እንድትፈቱ ፈቀደላችሁ እንጂ ከጥንት ጀምሮ ግን እንዲህ አልነበረም" ብሎአቸዋል።

ስለዚህ ቀደም ተብሎ በነቢዩ ሚልክያስ አማካይነት በተሰጠው መግለጫና በኋላም በጌታችን በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በተደረገው ማብራሪያ መሠረት በኦሪቱም ሕግ ቢኾን ካለዝሙት ምክንያት በቀር መፋታት ያልተፈቀደ መኾኑን ልንረዳ ይገባል። በኦሪት ዘዳግም ም.24 ቁ. 1 ላይ የፍቺው ምክንያት በግልጽ ባይነገርም እንኳ እንደ መድኀኒታችን አባባል ዝሙት ሳይኾን አይቀርም። ይህም በመኾኑ ታዲያ በኦሪቱ ሕግ ዝም ተብሎ መፋታት ያልተፈቀደ መኾኑን በመረዳት ኹለቱ ጥቅሶች የማይቃረኑ መኾናቸውን እንገነዘባለን።

## መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ

ይህ መጽሐፍ ኻያ አራት ምዕራፎችን የያዘ ኾኖ የእስራኤል ሕዝብ እንደምን በእግዚአብሔር ተአምር የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገሩ፥ በግዝረት ኮረብታ ላይ የእስራኤል ልጆች መገረዝ፥ የፋሲካ በዓል መከበር፥ አሁንም በእግዚአብሔር ተአምር የኢያሪኮ ከተማ በእስራኤል ሕዝብ መወረር፥ እስራኤላውያን በአካባቢያቸው ከነበሩ አሕዛብ ጋር ተዋግተው ኹለት ጦርነቶችን ማሸነፋቸው፥ በእስራኤል ነገዶች መካከል የከነዓን



ምድር መከፋፈል፥ ኢያሱ ለሕዝቡ የሰጠው ጠቃሚ ምክርና በመጨረሻም የኢያሱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ታሪክ ይገኝበታል።

ከዚህ መጽሐፍ የምናገኘው ትምህርት እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ዘራቸው ያንን መሬት እንደሚወርስ የገባላቸው ቃል ኪዳን መፈጸሙንና የእግዚአብሔር ቃል የማይታጠፍ መኾኑን ነው። ኢያሱም ማለት አዳኝ ማለት እንደመኾኑ ምሳሌነቱ ለመድኀኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

53. በመጽሐፈ ኢያሱ ም.1 ቁ.5 ላይ እግዚአብሔር ለኢያሱ "በሕይወትህ ዘመን ኹሉ ማንም አይቋቋምህም፤ ከሙሴ ጋር እንደኾንኩ እንዲሁ ከአንተ ጋር እኾናለሁ፤ አልጥልህም፤ አልተውህም" ያለው ኾኖ ሳለ በምዕራፍ 9 ላይ እንደሚነበበው የገባዖን ሰዎች ኢያሱን አታልለው አንድ ቃል ኪዳን እንዲገባላቸው ሲያደርጉ እንዴት በቃሉ መሠረት እግዚአብሔር ሳይጠብቀው ቀረ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ምንም እንኳ መንፈሳዊ ሰውነታችን በጎ ተግባርንና ስሕተት የሌለበትን ሥራ ለመሥራት የዘወትር ምኞቱ ቢኾን የሰው ልጅ ጠላት መቼም ቢኾን ከማሰናከል ስለማይመለስ አብዛኛውን ጊዜ ከፍላጎታችን የተለዩ ተግባሮችን አከናውነን እንገኛለን። ይኹን እንጂ የጠላትን መሰናክል ለመቋቋም እንድንችል ማንኛውንም ሥራ ከመጀመራችን በፊት የፈጣሪን እርዳታ የለመንን እንደኾነ ሥራችን ኹሉ የተቃና እንደሚኾንና እግዚአብሔር ከስሕተት እንደሚጠብቀን የታመነ ነው።

እግዚአብሔር ደግሞ ለሰው ልጅ ነጻ ፈቃድን የሰጠው በመኾኑ እርዳታውን የሚሰጠን እኛም ያንን እርዳታ ፈላጊዎች ኾነን ስንገኝ ብቻ ነው። እንደ ኢያሱ ያለ ለእግዚአብሔር ቅርብ የኾነ ሰው በሚያከናውናቸው ድርጊቶች ኹሉ በቅድሚያ የእግዚአብሔርን ምክርና ፈቃድ መጠየቅ ነበረበት እንጂ ዝም ብሎ በራሱ ሐሳብ ብቻ ማንኛውንም ርምጃ መውሰድ ባልተገባውም ነበር። በእግዚአብሔር ፈቃድ ያልተደረገ ድርጊት ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ውጤቱ ያማረ አይኾንም።



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ኢያሱም ከእነዚያ ሰዎች ጋር የቃል ኪዳን ውል ሲዋዋል የእግዚአብሔርን ፈቃድና ምክር ስላልጠየቀ ወይም እርዳታውን ስላለለመነ መታለል ደረሰበት እንጂ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ያልጠበቀ ኾኖ አይደለም (ጥያቄና መልስ ቁ:131 ይመለከቷል)

54. በመጽሐፈ ኢያሱ ም.2 ቁ:1 ላይ ረዓብ ወይም ራኬብ ጋለሞታ እንደነበረች የተገለጸ ሲኾን በማቴዎስ ወንጌል ም.1 ቁ:5 ላይ ሰልሞን ቦዔዝን የወለደው ከእርስዋ መኾኑ ተነግሮአል። ከይሁዳ ነገድ አለቆች አንዱ ከእንደዚህች ያለች ጋለሞታ ጋር መጋባቱ ወይም ከእርስዋ መውለዱ ሕጋዊ ነው ወይ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በማቴዎስ ወንጌል የተጠቀሰችው ራኬብ ያቺ ዘማዊትዋ ረዓብ ለመኾንዋ ምንም ማስረጃ የለንም። በሌላ በኩል ደግሞ በመጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ 2 ላይ እንደተገለጸው ራኬብ በእስራኤል አምላክ አምና በንስሐ የተመለሰች መኾንዋን ከሰላዮቹ ጋር ባደረገችው ንግግር ለመረዳት ይቻላል። እንዲሁም በዚሁ ምክንያት ከአማንያንና ከጻድቃን ጋር የተቆጠረች መኾንዋን ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.11 ቁ:31 ላይና በሐዋርያው የያዕቆብ መልእክት ም.2 ቁ:25 ላይ ተገልጾአል። ታዲያ በንስሓ የተመለሰችና እንዲያውም በእምነትዋና በበጎ ተግባርዋ ቅዱሳት መጻሕፍት የመሰከሩላት ከኾነች ሰልሞንን ማግባትዋ ለምን ያስገርመናል?

በተለያዩ የጌታ ምሳሌዎች እንደተገለጸው ንስሓ የሚገባ ሰው ኹሉ ምሕረትን ያገኛል። ለምሳሌ በሉቃስ ወንጌል ም.15 ቁ:7 ላይ ንስሓ መግባት ከማያስፈልጋቸው ዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሓ በሚገባ አንድ ኀጢአተኛ ምክንያት በመንግሥተ ሰማይ ደስታ ይኾናል ብሏል። እንዲሁም በሠራተኞች መቀጠር ምሳሌ ላይ በማለዳ፥ በሦስት ሰዓት፥ በስድስት ሰዓት፥ በዘጠኝ ሰዓትና በአሥራ አንድ ሰዓት ሥራ የጀመሩት ሠራተኞች ኹሉ እኩል የተከፈላቸው መኾኑ ተገልጾአል። ማቴ. ም.20 ቁ:1 — 15)

ስለዚህ ረዓብ ወይም ራኬብ የተባለችው ጋለሞታ ንስሓ ገብታ ወደ እግዚአብሔር የተመለሰች እስከኾነች ድረስ ኀጢአትዋም ይቅር የተባለላት በመኾንዋ ሰልሞንን በማግባትዋ ሊያስገርመን አይገባም፤ ምክንያቱም ንስሓ መግባት የኀጢአት መደምሰስ ምልክት ነውና። የሐ. ሥ.ም.3 ቁ:19 )



55. በመጽሐፈ ኢያሱ ም.6 ቁ: 2 — 5 እግዚአብሔር ኢያሱን ለስድስት ቀኖች በየቀኑ አንድ ጊዜ ካህናት በታቦቱ ፊት ቀንደ መለከት እየነፉ ከሰልፈኞች ጋር የኢያሪኮን ግንብ እንዲዞሩና በሰባተኛው ቀን ግን ሰባት ጊዜ እንዲዞሩ አዝዞታል። የኢያሪኮ ግንብ የፈረሰው በእግዚአብሔር ተአምር መኾኑ ግልጽ ኾኖ ሳለ ግንቡ ከመፍረሱ በፊት እነዚህ ኹሉ እንቅስቃሴዎች እንዲደረጉ እግዚአብሔር የፈለገው ለምንድነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

እስራኤላውያን ከነዓናውያንን ከመፍራታቸውና በእግዚአብሔርም ላይ ያላቸውን እምነት ካለማጠናከራቸው የተነሣ ይህ ትምህርት ለእነርሱ አስፈላጊ ነበር። ይህም የኢያሪኮን ግንብ የመዞሩ ጉዳይ ለእስራኤላውያን እምነትና ትዕግሥት ፈተና ሲኾን ለኢያሪኮ ሕዝብ ግን ለምስክርነት ጠቃሚ ኾኗል። ካህናት ታቦቱን ተሸክመው ቀንደ መለከቱን እየነፉ ከሰልፈኞች ጋር በየቀኑ በሚዞሩበት ጊዜ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያለ መኾኑን አስመስክረዋል። በተለየም በሰባተኛው ቀን ሕጋዊ የዕረፍት ቀን ኾኖ ሳለ ሰባት ጊዜ አድካሚ የኾነ ጉዞ በማድረጋቸው ለኹላቸውም ኀይለኛ ፈተና ነበር። በእምነትም የኢያሪኮ ከተማ ግንብ አጥር ወደቀ።

በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤላውያን ኢያሪኮን በጦርነት አሸንፈው እንዲይዙት ቢደረጉ ኖሮ እኛ በጀግንነታችን ያዝነው በማለት ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ከማቅረብ ይልቅ በትዕቢት ኀጢአት በወደቁ ነበር። ለምሳሌ ሙሴና አሮን ለእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር ውሃ ይስጣችኋል በማለት ፈንታ እኛ እንሰጣችኋለን ስላሉ ነው አርባ ዓመት ሙሉ በተስፋ ወደተጠባበቁት ወደ ተስፋ ምድር ከመግባት የተከለከሉት።

በዚህም መሠረት የእስራኤል ሕዝብ በአንድ በኩል እምነቱ እንዲጠናከር በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔርን ክብር ለራሱ ዝና ለማዋል በመቃጣት እንዳይጐዳ ብሎ ነው ያኹሉ እንቅስቃሴ ያስፈለገው።



www.ethiopianorthodox.org

56. በመጽሐፈ ኢያሱ ም.6 ቁ: 21 ላይ እስራኤላውያን የኢያሪኮን
ከተማ በያዙ ጊዜ "በከተማዩቱ የነበሩትን ኹሉ፥ ወንዱንና ሴቱን፥ ሕፃ
ኑንና ሽማግሌውን፥ በጉንና አህያውን በሰይፍ ስለት ፈጽመው አጠፉ
ተብሎአል። በመዝሙር 7 ቁ:11 ላይ "እግዚአብሔር የእውነት ዳኛ ነው
እና በራዕየ ዮሐንስ ም.16 ቁ:7 ላይ ደግሞ "ፍርዶችህ እውነትና ጽድቅ
ናቸው" ተብሎ ተገልጾአል። እግዚአብሔር የእውነት ዳኛ በመኾኑ ፍር
ዶቹ ኹሉ ትክክል መኾናቸውን የምናምን ከኾነ እንዴት ተደርጎ ነው
ለእስራኤል ሕዝብ ደኅንነት ሲባል ብቻ በሰላም ዐርፎ በአገሩ የሚገኘው
የከነዓን ሕዝብ ጥፋት የተፈረደበት ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

እግዚአብሔር ኹሉን ቻይ ብቻ ሳይኾን ኹሉንም ዐዋቂ ነው። ዕው
ቀቱም ያለፈውንና በአሁኑ ጊዜ ያለውን ኹኔታ ብቻ ሳይኾን ወደ ፊት
የሚደርሰውን ኹናቴና የሚደረገውን ድርጊት የሚያጠቃልል ነው። ለም
ሳሌ ከሦስቱ የኖኅ ልጆች ካም በአባቱ ላይ በደል በፈጸመ ጊዜ ለኖኅ እግ
ዚአብሔር ገልጾለት ወደፊት የከነዓን ሕዝብ ምን ዓይነት ሕዝብ እንደ
ሚኾን በመዘርዘር ትንቢታዊ እርግማን ረግሞታል። ስለዚህ እግዚአ
ብሔር አስቀድሞ ለአብርሃም ልጆች የከነዓንን ምድር ርስት አድርጎ እን
ደሚሰጣቸው ቃል የገባላቸው ወደፊት የከነዓን ሕዝብ ምን ዓይነት ሕዝ
ብ እንደሚኾን አስቀድሞ ስላወቀው ነው። ይህም ማለት የከነዓንን ሕዝብ
ደምስሶ የእስራኤልን ሕዝብ መተካት ያስፈለገው በጥፋታቸው ምክንያት
ከነዓናውያንን ለማጥፋት እንጂ ለእስራኤላውያን ለማድላት አይደለም።
በከነዓናውያን ላይ የተፈጸመው ቅጣት በእስራኤላውያን አማካይነት ይኹ
ን እንጂ በኖኅ ጊዜና እንዲሁም በሰዶምና በጎሞራ ላይ እንደተፈጸሙት
ያሉ ቅጣቶች ሊፈጸሙ በቻሉ ነበር።

የከነዓን ሕዝብ ጠፍቶ የእስራኤል ሕዝብ አገሩን እንዲወርስ የተ
ወሰነበት ምክንያት ሲገለጽ እንዲህ ተብሏል "ምድራቸውን ትወርሳት
ዘንድ የምትገባው ስለጽድቅህና ስለልብህ ቅንነት አይደለም፤ ነገር ግን
አምላክህ እግዚአብሔር ከፊትህ በሚያጠፋቸው በእነዚያ አሕዛብ ኀጢ
አት ምክንያትና ለአባቶችህ ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የማለላቸ
ውን ቃል ይፈጽም ዘንድ ነው" (ዘዳ. ም.9 ቁ:5)

ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ያፈነገጠ እንደኾነ ግን የእስራኤልንም
ሕዝብ እንደሚቀጣው ያስጠነቀቀው መኾኑን በአሪት ዘዳግም ም.4 ቁ:



23 – 27, ም.8 ቁ:19 – 20 ም.30 ቁ:17 – 19 መመልከት እንችላ
ለን።

እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ብቻ የሚያዳላ ቢኾን ኖሮ ያንን
ማስጠንቀቂያ ባልሰጣቸውም ነበር። ማስጠንቀቂያ መስጠት ብቻ ሳይኾን
በትእዛዝ አፍራሽነታቸው ምክንያት በጠላቶቻቸው ተሸንፈውና ተማ
ርከው በምርኮኛነት ለብዙ ዘመናት በዓለም በመላ ተበታትነው መኖራቸ
ው የታወቀ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ማንንም ቢኾን የሚመርጠው
ወይም የሚቀጣው ለምርጫው ወይም ለቅጣቱ ተገቢ ኾኖ ሲያገኘው
ነው እንጂ ከነዓናውያንን ለመቅጣት እስራኤላውያንን በመላኩ እግዚአብ
ሔር ለእስራኤላውያን እንዳደላ ኾኖ መገመት የለበትም። ለምሳሌ የመ
ጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ ሳኦል የተሸነፈው ጣዖት አምላኪዎች በነ
በሩት በፍልስጥኤማውያን ነው።

ስለዚህ ፍልስጥኤማውያን ሳኦልን ለመቅጫ የእግዚአብሔር በትር
እንደነበሩ ኹሉ እንዲሁም ከነዓናውያን እንዲቀጡ የተደረጉት በእስራ
ኤሎች አማካይነት ነውና ከዚህ የተለየ አስተሳሰብ ሊኖረን አይገባም።
(ጥያቄና መልስ ቁ: 42 እና 46 ይመለከቷል)

57. በመጽሐፈ ኢያሱ ም.10 ቁ:12 – 13 "እግዚአብሔርም በእ
ስራኤል ልጆች እጅ አሞራውያንን አሳልፎ በሰጠ ቀን ኢያሱ እግዚአብ
ሔርን ተናገረ፤ በእስራኤልም ፊት እንዲህ አለ፤

በገባዖን ላይ ፀሐይ ትቁም፤ በኤሎንም ሸለቆ ጨረቃ። ሕዝቡም
ጠላቶቻቸውን እስኪበቀሉ ድረስ ፀሐይ ቆመ፤ ጨረቃም ዘገየ" የሚል
ሲኾን በመጽሐፈ ምሳሌ ም.8 ቁ:27 ላይ "እግዚአብሔር ሰማያትን በዘ
ረጋ ጊዜና በቀላያት ፊት ክበብን በደነገገ ጊዜ አብሬው ነበርኩ" የሚለው
ና በዘመናዊው የሳይንስ ትምህርት ደግሞ የምትዞረዋ መሬት እንጂ ፀሐ
ይና ጨረቃ አለመኾናቸው በመረጋገጡ እንዴት ነው ፀሐይና ጨረቃ
መቆማቸው የተነገረው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ቅዱሳት መጻሕፍት የሚጻፉት ለሕዝብ እንደመኾኑ ሕዝብ በሚገባ
ውና በሚያውቀው ቋንቋ እንጂ ከዚያ በተለየ በሳይንስ ቋንቋ አይደለም።
በዚህም መሠረት መጻሕፍቱ በተጻፉበት ዘመን ብቻ ሳይኾን በዛሬውም



www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ ቢኾን በሕዝብ ዘንድ የተለመደው አነጋገር ፀሐይ ወጣ ጀምበር ጠለቀች እንጂ መሬት ዞረች ማለት አይደለም። እግዚአብሔርም ደግሞ አስፈላጊ ኾኖ በሚያገኘው ጊዜ የመሬትን እንቅስቃሴ በማቆም የዓለምን የተፈጥሮ ኺደት የማይቆጣጠርበት ምንም ምክንያት የለም። በተመሳሳይ ኹኔታ በኹለተኛው መጽሐፈ ነገሥት ም.20 ቁ:9—12 የፀሐይ ጥላ ዓሥር ርምጃ ወደኋላ ተመልሶአል። እንዲሁም በማቴዎስ ወንጌል ም.27 ቁ:45 ከቀኑ ሰድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ኹሉ ላይ ጨለማ መኾኑ ተገልጾአል። ደግሞስ የተፈጥሮን ዕለታዊ ኺደት ሕግ የፈጠረው እግዚአብሔር እርሱ ራሱ የፈጠረውን ኺደት ለማዘግየትም ኾነ ወይም ለማፍጠን ምን ይሳነዋል? "በእግዚአብሔር ዘንድ ኹሉ ነገር ይቻላል" (ማቴ. ም.19 ቁ:26 )

## መጽሐፈ መሳፍንት

ከኢያሱ ሞት በኋላ ለተወሰኑ ዘመናት ማለት ንጉሥ መንገሥ እስከ ጀመረበት ጊዜ ድረስ በእስራኤል ላይ የፈረዱት ሰዎች መሳፍንት የሚል ስም የተሰጣቸው ሲኾን መጽሐፉም የእነዚሁኑ ሰዎች ያገዛዝ ታሪክ የያዘ በመኾኑ መጽሐፈ መሳፍንት የሚል ስም ተሰጥቶታል። በኻያ አንድ ምዕራፎች ተከፋፍሎ ምንም እንኳን የኹለቱ መሳፍንት ማለት የኤሊና የሳሙኤል ስሞች በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ባይገኙ የቀሩት የዐሥራ ኹለቱ መሳፍንት ስምና ሥራ ግን በመጽሐፉ ውስጥ ተዘርዝሮአል። ምናልባት ኤሊና ሳሙኤል በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ስማቸውና ሥራቸው ተመዝግቦ የማይገኝበት ምክንያት እነርሱ የቤተ መቅደስም ሊቃነ ካህናት የነበሩ በመኾናቸው ሊኾን ይችላል። ከዚህ ቀጥሎ የመሳፍንቱ ስም ዝርዝር ተገልጾአል።

1/ የካሌብ የወንድሙ ልጅ ጎቶንልያል (ም.3 ቁ:10 )

2/ ናዖድ (ከብንያም ነገድ) (ም.3 ቁ:15 )

3/ ዲቦራ (ም.4 ቁ:4 )

4/ ጌዴዎን (ም.6 ቁ:11 )



5/ አቤሜሌክ (ም.9 ቁ.22 )

6/ ቶላ (ከይሳኮር ነገድ) (ም.10 ቁ:1)

7/ ኢያዕር (ም.10 ቁ.3)

8/ ዮፍታሔ (ም.11 ቁ:1 )

9/ ኢብጻን (ም.12 ቁ.8)

10/ ኤሎም (ም.12 ቁ:11 )

11/ ዐብዶን (ም.12 ቁ:13 )

12/ ሶምሶን (ም.13 ቁ:24 )

13/ ኤሊ (1ኛ. ሳሙ. ም.4 ቁ:18 )

14/ ሣሙኤል (1ኛ ሳሙ. ም.7 ቁ:15 )

አብዛኞዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እንደተስማሙበት ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በነቢዩ ሳሙኤል እንደኾነ ይታመናል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው፣

58. በመጽሐፈ መሳፍንት ም.3 ቁ:15 "የእስራኤልም ልጆች ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤ እግዚአብሔርም ብንያማዊውን የጌራን ልጅ ግራኙን ሰው ናዖድን አስነሣላቸው" ያለ ሲኾን ይህ ሰው ግን የሞዓቡን ንጉሥ ኤግሎምን የገደለው በተንኰል ዘዴ ተጠቅሞ ነው። ታዲያ እስራኤልን ለማዳን የተመረጠው ሰው ዕቅዱን በእንደዚህ ያለ በተንኰል ዘዴ ሥራ ላይ ማዋል ነበረበት ወይ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል። (ቁ:15 — 20 )



www.ethiopianorthodox.org

እንደዚህ ያለውን የተንኰል ዘዴ ከያዕቆብ ልጆች መካከል ስምዖንና ሌዊ ተጠቅመውበታል። እነርሱም የእኅታቸውን የዲናን ክብረ ንጽሕና በግድ የወሰዱ ስለኾነ ወንዶቻቸው ኹሉ እንዲገረዙ ካሳመኑአቸውና ከተገረዙ በኋላ በቁስል ላይ እያሉ አቅም ያልነበራቸውን ኹሉ በመግደል በሴኬም ሰዎች ላይ የበቀል እርምጃ ወስደዋል (ዘፍ. ም.34 ) እንዲሁም በእስራኤል ላይ ዲቦራ ትፈርድ በነበረበት ዘመን የከነዓንን የሠራዊት አለቃ ሲሣራን እያኤል የተባለችው የሐቤር ሚስት እቤትዋ አስገብታ ካስተኛችው በኋላ ካስማ በጆሮው በኩል በመቸንከር ገድላዋለች (መሳ. ም.4 ) በመጽሐፈ ዮዲት ምዕራፍ 12 ብንመለከት ደግሞ ዮዲት ተብላ የምትጠራው መልከ ቀናይቱ የምናሴ ሚስት እንዴት አድርጋ የናቡከደነፆርን የጦር አዛዥ አዘናግታ አንገቱን እንደቆረጠችው እናነባለን።

እነዚህ ኹሉ ሰዎች የፈጸሙት አድራጎት የእስራኤልን ልጆች ለማዳን የጀግንነት ሥራ እንደሠሩ እንጂ ጥፋትን እንዳጠፉ አድርጎ መጽሐፍ ቅዱስ አልፈረደባቸውም። በሌላ በኩል ደግሞ አንድ የጦር መሪ ወይም የጦርነት ጀግና ጠላቱን ለማጥቃት በማዘናጋትና በተንኰል ዘዴ የሚጠቀም መኾኑ የተለመደ ነው።

ስለዚህ ናዖድ የተጠቀመበት ስልት እርሱና እርሱን የመሰሉ ተዋጊዎች የሚጠቀሙበት ዘዴ ስለኾነ ለተመረጠበት ሥራ ተገቢ የኾነ እንጂ ተገቢ ያልኾነ ሥራ እንዳልሠራ መገንዘብ አለብን።

59. በመጽሐፈ መሳፍንት ም.8 ቁ:27 ላይ "ጌዴዎን ኤፉድ አሠራ፤ በከተማውም በዖፍራ አኖረው፤ እስራኤልም ኹሉ ተከትሎ አመነዘረበት፤ ለጌዴዎንና ለቤተሰቡም ወጥመድ ኾነ" የተባለ ሲኾን ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.11 ቁ:32 — 33 ጽድቅን አደረጉ ተብለው ከተመሰገኑት ሰዎች አንዱ ኾኖ በመመስገኑ እንዴት ጣዖትን ያመለከና ያስመለከ ሊመሰገን ቻለ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ጌዴዎን በንስሓ ወደአምላኩ የተመለሰ መኾኑን የሚያመለክተው በዚሁ በመጽሐፈ መሳፍንት ም.8 ቁ:32 ላይ "የኢዮአስም ልጅ ጌዴዎን በመልካም ሽምግልና ሞተ" ማለቱ ነው። ንስሓ ለሚገባ ደግሞ እግዚአብሔር ይቅር እንደሚለው ሲያመለክት ነቢዩ ኢዮኤል እንዲህ ብሏል "አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ በጾም፥ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ፤ ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ፤ አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ፥ ቁጣው የዘገየ፥ ምሕረቱ የበዛ፥ ለክፋትም የተጸጸተ ነውና ወደእርሱ ተመለሱ" (ኢ.ዮ. ም.2 ቁ: 12 — 13 )



በእነዚህም ማስረጃዎች መሠረት ጌዴዎን በንስሐ ወደ እግዚአብሔር የተመለሰ በመኾኑና በንስሐ የሚመለስን ሰው ደግሞ እግዚአብሔር እንደሚሰማው የታመነ በመኾኑ ጌዴዎንም ከጻድቃን ጋር መቈጠሩ ሊያስገርመን አይገባም።

60. በመጽሐፈ መሳፍንት ም.11 ቁ:31 ላይ ዮፍታሔ "በእውነት የአሞንን ልጆች በእጄ አሳልፈህ ብትሰጠኝ ከአሞን ልጆች ዘንድ በደኅና በተመለስሁ ጊዜ ሊገናኘኝ ከቤቴ ደጅ የሚወጣው ማናቸውም ለእግዚአብሔር ይኾናል፤ ለሚቃጠልም መሥዋዕት አቅርበዋለሁ ብሎ ለእግዚአብሔር ስእለት ተሳለ" ባለው መሠረት በመጀመሪያ ከቤቱ የወጣችው አንዲት ልጁ ብቻ ስለኾነች በቁጥር 39 ላይ እንደተገለጸው "እንደተሳለው አደረገባት" ይላል።

በኦሪት ዘዳግም ም.12 ቁ:31 ላይ "እግዚአብሔር የሚጠላውን ርኩስት ኹሉ እነርሱ ለአማልክቶቻቸው አድርገዋልና፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን ደግሞ ለአማልክቶቻቸው በእሳት ያቃጥሉአቸዋልና አንተ ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር እንዲህ አታድርግ" የሚለውን ትእዛዝ የተላለፈውን ሰው ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.11 ቁ:31 ላይ የጽድቅን ሥራ ሠሩ ተብሎ ስማቸው ከተዘረዘረው ሰዎች መካከል የዮፍታሔም ስም ይገኝበታል። ታዲያ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ተቃራኒ የኾነውን አድራጎት እንደ አረማውያን ሥርዓት ሰውን ለመሥዋዕትነት ያቀረበው ዮፍታሔ እንዴት የጽድቅን ሥራ ከሠሩ ሰዎች ጋር ሊያዳብለው በቃ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

መሥዋዕት ተብሎ በሚነገርበት ጊዜ በመቃጠል የሚቀርበው መሥዋዕት ብቻ ኾኖ መታሰብ የለበትም። ፍላጎትን መግታት፥ ንብረትን ለእግዚአብሔር ማስረከብ፥ እንዲሁም ሰውነትን ለእግዚአብሔር አገልግሎት ማዘጋጀት መሥዋዕትነት ነው። ቀጥለው የተዘረዘሩት ጥቅሶች ይህንን አባባል ያጠናክራሉ።



www.ethiopianorthodox.org

"የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው" (መዝ.51 ቁ፡ 17 )

"ሰውነታችሁን ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ" (ሮሜ.ም. 12 ቁ:1 )

"የመዓዛ ሽታና የተወደደ መሥዋዕት የሚኾነውን ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ።" (ሮሜ ም.12 ቁ:1 )

"መዓዛ ሽታና የተወደደ መሥዋዕት የሚኾነውን ለእግዚአብሔርም ደስ የሚያሰኘውን ስጦታችሁን ከአፍሮዲጡ ተቀብዬ ተመልሼአለሁ።" (ፊልጵ. ም.4 ቁ.18 )

"እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ኾናችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትኾኑ መንፈሳዊ ቤት ለመኾን ተሠሩ።" (1ኛ ጴጥ. ም.2 ቁ:5 )

በነዚህም ማስረጃዎች መሠረት መሥዋዕት ማለት የሚታረድ መሥዋዕት ብቻ አለመኾኑ ግልጽ ነው።

እግዚአብሔር አብርሃምን ለመፈተን ልጁን ይስሐቅን ለሚቃጠል መሥዋዕት እንዲያቀርበው ከጠየቀው በኋላ ይስሐቅን መሠዋት አግባብ ስላልኾነ በምትኩ በግ የሰጠው መኾኑንና የሰው ልጅ በሚቃጠል መሥዋዕትነት መቅረብ የሌለበት መኾኑን ዮፍታሔ የማያውቅ አይደለም (ዘፍ: ም: 22 ቍ. 1-19 ) እንዲሁም በኦሪት ዘኁልቍ ም: 18 ቍ.15 - 16 ምንና ምንን መሥዋዕት ማቅረብ እንደሚገባና ሰውንና ንጹሕ ያልኾኑ እንስሳትን ግን መቤዠት ማለት በምትኩ የተወሰነ ገንዘብ መስጠት እን ደሚገባ የተገለጸውን ዮፍታሔ የማያውቀው አይደለም። ይህም በመኾኑ ዮፍታሔ ሕግ የሚያዝዘውን እንጂ ሕገወጥ ሥራ እንዳልሠራ የታመነ ነው። ዮፍታሔ ልጁን ለሚቃጠል መሠዋዕት አቅርቦአታል የሚለው የአንዳንድ ምሁራን አስተያየት ዘመኑ ያለፈበት ኾኗል።



ብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እንደተስማሙበት ዮፍታሔ ልጁን ለነቢዩ ሳሙኤልና ለሐና ዕድሜ ልክዋን እንድታገለግል ሰጥቶአታል እንጂ ለሚቃጠል መሥዋዕትነት አላቀረባትም። ይህ ባይኾን ኖሮ ማለት ልጁን ለሚቃጠል መሥዋዕት አቅርቦአት ቢኾን ኖሮ ከነቢያትም ኾነ ከካህናት ተቃውሞ በደረሰበት ነበር። ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ብዙ ምሳሌዎችን ማቅረብ የሚቻል ቢኾንም ለጊዜው ግን የሚከተሉትን ሦስት ምሳሌዎች ብቻ ማቅረብ በቂ እንደሚኾን ይታመናል።

አንደኛ ምሳሌ :-ንጉሥ ዳዊት በኦሪዮ ላይ ታላቅ በደል በፈጸመ ጊዜ ነቢዩ ናታን መጥቶ ገሥጸው (2ኛ ሳሙ. ም. 12 ቁ: 1 – 14)

ሁለተኛ ምሳሌ :- የእስራኤል ንጉሥ ኢዮርብዓም የእስራኤልን ሕዝብ ጣዖት እንዲያመልክ ባስደረገ ጊዜ ከይሁዳ አንዱ የእግዚአብልር ሰው ተልኮ እንዲወቅሰውና እንዲገሥጸው ተደርጓል (1ኛ ነገ.ም.13 )

ሦስተኛ ምሳሌ :- አዝያን የተባለው የይሁዳ ንጉሥ ከካህናት በቀር ለሌላ ሰው ያልተፈቀደውን ሥልጣንተዳፍሮ ወደ መቅደስ ውስጥ በመግባት በዕጣንመሠዊያው ላይ ስላጠነ ካህናት ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል (2ኛ ዜ.መ. ም.26 )

አሁን እንግዲህ በዮፍታሔ ላይ ከላይ የተጠቀሱት ዓይነት ተግሣጽ ወይም ተቃውሞ እንደተሰነዘረበት አለመገለጹ ሕገ እግዚአብሔርን ተላልፎ ልጁን ለሚቃጠል መሥዋዕት አለማቅረቡን የሚያመለክት ነው። ዮፍታሔ ግን ከጦርነቱ በተመለሰ ጊዜ ለልጁ አዝኖ ልብሱን መቅደዱና ልጁም ለድንግልናዬ ላልቅስለት ማለትዋ ሕይወትዋን በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልጋይነት ከመለየትዋ በቀር እንደገና ወደ አባትዋ ቤት የማትመለስና ባልም አግብታ ትዳር የማትመሠርት በመኾንዋ ነው እንጂ ሌላ አይደለም።

በእነዚህም ከላይ በተዘረዘሩት ማስረጃዎች መሠረት ዮፍታሔ በልጁ ላይ ሕገ እግዚአብሔርን የሚቃረን ድርጊት እንዳላደረገ ስለሚታመን በዕብራውያን መልእክት መመሰገኑ የሚያስገርም አይደለም።



www.ethiopianorthodox.org

61 በመጽሐፈ መሳፍንት ም.13 ላይ የእስራኤልን ልጆች ከጠላቶቻቸው ሊያድናቸው ሶምሶን ከእግዚአብሔር የተላከ መኾኑ የተገለጸ ሲኾን ከምዕራፍ ዐሥራ አራት እስከ ዐሥራ ስድስት እንደተነገረው ደግሞ የሶምሶን ድርጊት የእግ ዚአብሔርን ትእዛዝ ተቃራኒ ኾኖ ተገኝቶአል። ታዲያ እንደህ ያለ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ያፈነገጠሰው እንዴት ከእግዚ አብሔር ተላከ ተባለ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በሶምሶን በኩል የታየው ክፉ ነገር ከሰው ልጅ ደካማነት የተነሣ የሚደርስ ኹናቴ ነው። ኾኖም እግዚአብሔር ዕቅዱን ሥራ ላይ ለማዋል በተለያዩ ኹናቴዎችና ዘዴዎች ኹሉ ይጠቀማል። ምናልባት በዚያን ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ በጣም በኀጢአት የተበከለ ከመኾኑ የተነሣ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሥራ ላይ ለማዋል ከሶምሶን የተሻለ ሰው በሕዝብ መካከል ያልነበረ ሊኾን ይችላል።

ስለዚህም እግዚአብሔር ለሶምሶን ታላቅ ተውህቦዎችን የሰጠው እርሱ ለዚያ ብቁ በመኾኑ ሳይኾን ለሕዝቡ መዳን ብሎ ነው። እግዚአብሔርም ሶምሶንን በጥፋቱ ሳይቀጣው ያላለፈ መኾኑን በምዕራፍ 16 ላይ ልንረዳ እንችላለን።

62 በመጽሐፈ መሳፍንት ም.16 ቁ.30 ላይ ሶምሶን ራሱን እንደገደለ የተነገረ ሲኾን ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.11 ቁ.32 ላይ ከተጠቀሱት ምእመናን መካከል መኾኑ እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የሶምሶንን አሟሟት የተመለከትን እንደ ኾነ በጥፋቱ ተጸጽቶና በንስሓ ተመልሶ የነበረ መኾኑን እንገነዘባለን። አሟሟቱ ራሱን ለመግደል ያደረገው ሳይኾን በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ብሎ ያደረገው ነው። አንድ ጀግና ደግሞ በጠላቶቹ ላይ በሚዘምትበት ጊዜ ምናልባት ግዳጁን ለመወጣት በሚያደርገው ተጋድሎ እርሱም ሊሞት እንደሚችል በመገመት በሕይወቱ ቆርጦ ነው ወደ ጦር ሜዳ የሚኼደው። የሶምሶንም ድርጊት ከዚህ የተለየ አይደለም። ሶምሶንም ለሀገሩና ለወገኑ ሲል ሕይወቱን መሠዋቱ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም መዳን ሲል ቤዛ ከመኾኑ ጋር ምሳሌነት አለው።



በዚህም መሠረት በዕብራውያን መልእክት ም.11 ቁጥር 33 ላይ ጽድቅን አደረጉ ተብሎ ከተነገረላቸው ሰዎች መካከል ሶምሶንም መጤ መሩ ሊያስገርመን አይገባም።

## መጽሐፈ ሩት

አራት ምዕራፎች ያሉት ኹኖ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በመሳፍንት ዘመን በእስራኤል አገር ረኀብ ኹኖ ስለነበረ ከይሁዳ ነገድ የኾነ አቤሜሌክ የተባለ ሰው ኑኃሚን ከተባለች ሚስቱና መሐሎንና ኬሌዎን ከተባሉት ኹለት ወንዶች ልጆች ጋር ወደ ሞዓብ አገር ኼዶ ነበር። አቤሜሌክ ከሞተ በኋላ ኹለቱ ልጆች የሞዓብ ሴቶችን አግብተው ኹለቱም ልጅ ሳይወልዱ ሞተዋል። ከዚያ በኋላ ኑኃሚን ወደሀገርዋ በተመለሰች ጊዜ ሩት የተባለችው የልጅዋ ሚስት ተከትላት ኼደች። ከዚያም ቦዔዝ የተ ባለውን የአቤሜሌክ ዘመድ አግብታ ኢዮቤድ የተባለውን የዳዊትን አያት ወልዳለች።

ከዚህ መጽሐፍ ታሪክ የምንማረው ቁም ነገር የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ ከአንዲት የሞዓባዊት ሴት በተወለደ ሰው አማካይነት መኾኑ እግዚአብሔር አንዱን ሰው ከሌላውና አንዱን ዘር ደግሞ ከሌላው የማይለይ መኾኑን ነው።

## ጥያቄና መልስ

63. በመጽሐፈ ሩት ም.4 ቁ:20 ላይ በነአሶንና በዳዊት መካከል አራት ትውልድ ብቻ እነርሱም ሰልሞን፥ በዔዝ፥ ኢዮቤድና እሴይ እንደኾኑ ተገልጾአል። በኦሪት ዘኊልቊ ም.1 ቁ:7 ላይ የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን በሙሴ ዘመን የነበረ መኾኑን ያመለክታል።

ከሙሴ ዘመን እስከ ዳዊት ዘመን ድረስ ያለው ጊዜ ደግሞ ከአራት መቶ ዓመቶች በላይ መኾኑ በመጀመሪያው መጽሐፈ ነገሥት ም.6 ቁ.1



www.ethiopianorthodox.org

ላይ በመገለጹ እንዴት አራት ትውልድ ብቻ ኾነ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በመጽሐፈ ሩት ላይ የተዘረዘረው የዘር ሐረግ ዋና ዋናዎቹን የነገድ መሪዎች ብቻ በመጥቀስ ሌሎቹን ሰዎች የተወ ይመስላል።

ሌሎች ትርጓሜዎች ደግሞ እንደሚሉት በነአሶንና በዳዊት መካከል ባለው የዘር ሐረግ ውስጥ ብዙ የስም ሞክሼዎች ስለነበሩ ለሞክሼዎቹ ኹሉ አንዳንድ ስሞች ብቻ በመውሰድ የዘር ሐረጉ ዝርዝር አጠረ እንጂ እንደዚያ በአራት ትውልድ ብቻ ባልተወሰነም ነበር ይላሉ።

ስለዚህ ለጥያቄው መልስ ከላይ የተዘረዘሩትን ኹለት አማራጭ ትርጓሜዎች ይመለከቷል።

## አንደኛ ሳሙኤል (አንደኛ ነገሥት)

ይህ መጽሐፍ በሳሙኤል ስም መጠራት የጀመረው ከሰባዎቹ የአይሁድ ሊቃውንት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ በኋላ ነውእንጂ ከዚያ በፊት ግን ከመጽሐፈ ነገሥት አልተለየም ነበር። ስለዚህም ነው በቅንፍ ከጐኑ መጽሐፈ ነገሥት የተባለው። ይህም አባባል እስከ ኹለተኛው ነገሥት ድረስ ይቀጥላል። መጽሐፉም በሳሙኤል ስም የተጠራባቸው ምክንያቶች አንደኛ በሳሙኤል የሕይወት ታሪክ ስለሚጀምርና ኹለተኛ ደግሞ በብዙ ምሁራን ዘንድ እንደሚታመንበት የጻፈው ሳሙኤል በመኾኑ ነው። ይህ መጽሐፍ ስለ ሳሙኤል በስእለት ለቤተመቅደስ መሰጠት፥ የቃል ኪዳኑ ታቦት በፍልስጥኤማውያን መማረኩ፥ ፍልስጥኤማውያን የቃል ኪዳኑን ታቦት በመማረካቸው የደረሰባቸው ችግርና በዚህም ምክንያት ታቦቱን እንዲመለስ ማድረጋቸው፥ እንዲሁም የመጀመሪያው የእስራኤል ሕዝብ ንጉሥ የሳኦል ታሪክ ይገኝበታል። ሳኦልም ከአማሌቃውያን ጋር ባደረገው ጦርነት እግዚአብሔር የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ሳይጠብቅ ቀርቶ ትእዛዝ አፍራሽ በመኾኑ እርሱ ተሽሮ በምትኩ ንጉሥ ዳዊት ቅብዓተ ንግሥ እንዲቀባ መደረጉ ተገልጾአል።



ከመጽሐፉ የተወሰነው ክፍል በናታን ወይም በጋድ እንደተጻፈ ይገመታል። (1ኛ. ዜ.መ. ም.29 ቁ:29 )

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

64. በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ምዕራፍ 16 ቁጥር 2 ላይ ዳዊትን ቅብዐ ንግሥ እንዲቀባው ሳሙኤልን እግዚአብሔር በላከው ጊዜ እኔ የመጣሁት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለመሠዋት ነው ብለህ ተናገር ብሎ የሚያዝዘው ሲኾን በመዝሙር 119 ቁ:104 እና ቁ:128 ላይ ደግሞ "የሐሰትን መንገድ ኹሉ ጠላሁ" በማለ እንዴት ሳሙኤል ሐሰትን እንዲናገር እግዚአብሔር አዘዘው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ሐሰት ማለት አንድ ሰው የተደረገውን ድርጊት እንዳልተደረገ፣ ያልተደረገውን እንደተደረገና ወደፊት ሊያደርግ ያቀደውን ድርጊት እንዳላሰበበት፣ ሊያደርግ ያላቀደውን ድርጊት ደግሞ ሊያደርግ እንዳቀደ በማስመሰል ሰሚውን በው ለማሳመን መሞከር ነው። የሳሙኤልን ኹናቴ የተመለከትን እንደኾነ ግን መሥዋዕት ለመሠዋት ያቀደ መኾኑን እንገነዘባለን። ምናልባት መሥዋዕት ለመሠዋት ብቻ ነው የመጣኸው ወይስ ሌላም ዕቅድ አለህ ተብሎ ቢጠየቅ፣ ለመሥዋዕት ብቻ ነው የሚል መልስ ቢሰጥ ኖሮ ዋሸ ለማለት በተቻለ ነበር። እርሱ ግን የኼደዉ ለኹለት ጉዳዮች ማለት ዳዊትን ለማንገሥና መሥዋዕትም ለመሠዋት ስለነበረ ዋሸ ለማለት አይቻልም።

65. በአንደኛ ሳሙኤል ም. 21 ቁ:1 ላይ ዳዊት የመጣው ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ አሒሜሌክ ነው የተባለ ሲኾን በማርቆስ ወንጌል ም.2 ቁ: 26 ላይ ደግሞ ዳዊት የመጣው ወደ አብያታር ነው ተብሏል። ታዲያ እነዚህ ኹለቱ አባባሎች ለምን ተለያዩ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

አብያታር የአሒሜሌክ ልጅ በመኾኑ የክህነቱን አገልግሎት የሚያከናውኑት በአንድነት ኾነው ነበር። ከአባቱ በኋላ የሊቀ ካህናትነቱን ሥልጣን የተረከበው አብያታር ነው። (1ኛ ሳሙ. ም.22 ቁ:20 — 23 እና ም.23 ቁ:6 )



www.ethiopianorthodox.org

ዳዊት የተገናኘው አብያታርንም ቢኾን አሒሜሌክን ተገናኘ የተባለው ግን ሊቀ ካህናቱ አሒሜሌክ ስለነበረ ነው።

66. በአንደኛ ሳሙኤል ም.28 ቁ:7 — 25 በዝርዝር እንደታየው ሳኦል እግዚአብልር በራቀው ጊዜ መናፍስትን ወደምትጠራ ሴት ኼዶ ነቢዩን ሳሙኤልን እንዳስነሣችለት ተገልጾአል። በኦሪት ዘዳግም ም.18 ቁ:11 -12 ደግሞ "መናፍስትን የሚጠራ በአንተ ዘንድ አይገኝ፤ ይህንን የሚያደርግ ኹሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው" የሚል ኾኖ ሳለ እንዴት መናፍስትን የምትጠራ ጠንቋይ ሳሙኤልን የሚያኽል ታላቅ ነቢይ ለመጥራት ቻለች ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የመናፍስት ጠሪዋ ታሪክ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግቦ የሚገኘው የእግዚአብሔር ሥልጣን በቅዱሳንና በርኩሳን መናፍስት ኹሉ ላይ መኾኑን ለማመልከት ነው።

ለምሳሌ ሐሰተኛ ትንቢትን በማናገር ንጉሥ አክዓብን እንዲያሳስት ለሰይጣን እግዚአብሔር የፈቀደለት መኾኑን በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ም.22 ቁ:19 — 22 እንመልከት።

በመጽሐፈ ኢዮብ ም.1 ቁ:12 ላይ በኢዮብ ላይ ያንን ኹሉ ችግር እንዲያደርስ ለሰይጣን ተፈቅዶለታል።

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ቁ: 32 ላይ ከተፈወሱት ሕመምተኞች የወጡት አጋንንት ወደ አሳማ መንጋዎች እንዲገቡ ጌታ ፈቅዶላቸው አሳማዎቹንም ወደውሃ ውስጥ ገብተው ሰጥመው እንዲሞቱ አድርገዋቸዋል።

ለዚህ ድርጊት ኹለት ዓይነት የተለያዩ ትርጓሜዎች ይሰጣሉ።

የመጀመሪያው ትርጓሜ እግዚአብሔር ዕቅዱን በሥራ ላይ ለማዋል በሚፈልግበት ጊዜ በልዩ ልዩ መንገድ የሚጠቀም መኾኑ ግልጽ ነው። ለምሳሌ የእግዚአብሔር ሰዎች የተባሉት እስራኤላውያን በበደሉ ጊዜ በጦርነት እንዲሸነፉና እንዲማረኩ ይደረጉ የነበሩት አግዚአብሔርን ሳይኾን ጣዖትን በሚያመልኩ ወገኖች ነበር። እነዚያ አረማውያን የእስራኤ



ልን ሕዝብ ለማጥቃት የቻሉት እነርሱ ከእስራኤል ሕዝብ የተሻሉና በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደዱ ስለነበሩ አይደለም። ነገር ግን እነርሱ እስራኤልን የመቅጫ አንድ መንገድ ስለነበሩ ብቻ ነው። በዓይንዶር የነበረችውም መናፍስት ጠሪ እንደነ ሳሙኤል ባለ የቅዱሳን መናፍስት ላይ ሥልጣን ኖሯት ሳይኾን ሳሙኤል ተገልጾ በሳኦል ላይ የተወሰነውን ፍርድ እንዲነግረው የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለነበረ ነው። ሳሙኤልም በእርስዋ ሥልጣን የተነሣ አለመኾኑን ለመገንዘብ ሳሙኤል ሲነሣ ባየችው ወይም ያየችው በመሰላት ጊዜ ታላቅ ፍርሃትና ድንጋጤ ደርሶባት እማ ልክት ከምድር ሲወጡ አየሁ ብላ መጮኋን በቁጥር 12 እና 13 ላይ መመልከት እንችላለን። እርስዋም እየጠራች የምታስመጣቸው ርኩሳን መናፍስትን እንጂ የሞቱ ሰዎችን ነፍሳት አለመኾኑ በዚህ ሊታወቅ ይቻ ላል።በሌላ ጊዜ ፍርሀትና ድንጋጤ ደርሶባት የማታውቀው ጠንቋይ በየጊዜው ትጫወት የነበረው ከምታመ ልካቸው ከርኩሳን መናፍስት ጋር ብቻ ስለነበረ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በዚያን ጊዜ ተነሥቶ ሳኦ ልን ያነጋገረው ሳሙኤልን ራሱን መኾኑን ሲያመለክት ኢያሱ ወልደ ሲራክ እንዲህ ብሏል "ካንቀላፋም በኋላ እንደገና ስለንጉሡ ሞት ትንቢት ተናገረ" (ሲራ. ም.46 ቁ.23 )

ኹለተኛው ትርጓሜ ደግሞ ሳኦል ድምፁን ከመስማቱ በቀር ያንን ሳሙኤል ነው ወይም የሳሙኤል ነፍስ ነው የተባለውን በዐይኑ አላየውም። ጠንቋይዋም ብትኾን ሳሙኤልን መስሎ ስለመጣባት ደነገጠች እንጂ በሳሙኤል መልክ የመጣው ራሱ ሳሙኤል ሳይኾን ርኩስ መንፈስ ነው የሚል ነው። እንዲያውም ጠንቋይዋ የፈራችና የተንቀጠቀጠችው የሳኦልን ማንነት ስላወቀች ነው እንጂ ርኩሳን መናፍስቱንማ የለመደቻቸው ስለኾነ አትፈራቸውም። ይኽም ለመኾኑ የሚሰጠው ማስረጃ በዚሁ በአንደኛ ሳሙኤል ም.28 ቁ:12 እና 13 ላይ "ሴቲቱም ሳሙኤልን ባየች ጊዜ በታላቅ ድምፅ ጮኸች፤ አንተ ሳኦል ስትኾን ለምን አታለልኸኝ ብላ ተናገረችው" ካለ በኋላ ንጉሡ ደግሞ አትፍሪ ማለቱ ነው። ይህም የኾነበት ምክንያት ሳኦል ቀደም ብሎ ጠንቋዮችንና መናፍስት ጠሪዎችን አጥፍቶ የነበረ በመኾኑ አሁንም እኔን ይገድለኛል ወይም ያስገድለኛል ብላ ስለፈራች ጮኸች፤ ተንቀጠቀጠች። በዚህም መሠረት የመናፍስት ጠሪዋ ድርጊት ከላይ በተገለጡት አማራጭ ትርጓሜዎች ይተረጐማል እንጂ ትእዛዛቱና ድርጊቶቹ ርስ በርሳቸው የሚጋረጉ ኾነው አይደለም።



www.ethiopianorthodox.org

# ኹለተኛ ሳሙኤል (ኹለተኛ ነገሥት )

ይህ መጽሐፍ ከአንደኛው መጽሐፍ ጋር ተመሳሳይ በመኾኑ በሳሙኤል ስም ይጠራ እንጂ የጻፈው ነቢዩ ጋድ ወይም ነቢዩ ናታን እንደ ኾነ ይገመታል። ኻያ አራት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ ዳዊት በይሁዳ ነገድ ላይ ለሰባት ዓመቶች ተኩል መንገሡ፥ ሌሎቹም የእስራኤል ነገዶች ኹሉ ከተገዙለት በኋላ የኢያቡሳውያንን አሸንፎ በማባረርና ኢየሩሳሌምን መናገሻ ከተማው በማድረግ በእስራኤል ነገዶች ኹሉ ላይ ለሠላሳ ሦስት ዓመቶች መንገሡ፥ በሚስቱ ላይ የዘሙት ኀጢአት ከሠራ በኋላ ለራሱ ሚስት ሊያደርጋት ፈልጎ በኦሪዩ ላይ ዳዊት የሠራው ግፍ፥ ማለት ኦሪዩን በጦርነት ግንባር አስገድሎ ሚስቱን መውረሱ፥ በዚሁም ምክንያት ከእግዚአብሔር በኩል የተሰነዘረበት ተግሣጽና ቅጣት፥ ልጁ አቤሴሎም በጠላትነት ተነሣሥቶ መንግሥቱን በመቀናቀን በጦርነት እንዳጠቃውና በመጨረሻም አቤሴሎም በጦርነት ተሸንፎ ከተገደለ በኋላ ዳዊት ወደ ቀድሞ ገናናነቱ መመለሱ በሰፊው ተዘርዝሮአል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

67. በኹለተኛው ሳሙኤል ም.8 ቁ:13 - 15 ላይ "ዳዊት የጨው ሸለቆ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ዐሥራ ስምንት ሺ ሶርያውያንን ገድሎ በተመለሰ ጊዜ ከምንጊዜውም ይበልጥ ዝናው ገነነ፤ በመላው ኤዶምያስም ብዙ የጦር ሰፈሮችን አቋቋመ፤ በዚያም የሚኖሩ ሕዝብ የእርሱ ተገዢዎች ኾኑ፤ እግዚአብሔር ዳዊትን በኼደበት ኹሉ ድልን እንዲቀዳጅ አደረገው። በዚህ ዐይነት ዳዊት የመላው እስራኤል ንጉሥ ኾኖ ሕዝቡ ዘወትር ትክክለኛ ፍትሕ ማግኘት እንዲችሉ ጥረት ያደርግ ነበር" ካለ በኋላ በአንደኛ ዜና መዋዕል ም.18 ቁ:12 - 14 ደግሞ "የጽሩያ ልጅ አቢሻይ ኤዶማውያንን በጨው ሸለቆ ውስጥ ድል አድርጎ ከእነርሱ መካከል ዐሥራ ስምንት ሺሕ የሚኾኑትን ገደለ፤ በመላው የኤዶምያስ ግዛት ውስጥ የጦር ሰፈሮችን አቋቋመ፤ በዚያም የሚኖሩ ሕዝብ የንጉሥ ዳዊት ገባሮች ኾኑ፤ እግዚአብሔር ዳዊትን በኹሉ ስፍራ ድል አድራጊ አደረገው። ዳዊትም በመላው እስራኤል ላይ ነገሠ፤ ሕዝቡም ኹል ጊዜ አድልዎ የሌለበት ፍትሕ እንዲያገኝ አደረገ" በማለቱ ኹለቱ አባባሎች ለምን ተለያዩ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በኹለተኛው ሳሙኤል ዳዊት ሲል በአንደኛ ዜና መዋዕል አቢሻይ ማለቱ አብዛኛውን ጊዜ አድራጊና አስደራጊ በአንድ ስም ስለሚነገሩ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው ቤት ሠራ ሲባል ቤቱን ባለሙያዎች ማሠራቱን እንጂ ራሱ መሥራቱን የሚያመለክት አይደለም። በዚሁም ዐይነት አቢሻይ በዳዊት ታዝዞ የመራው ጦርነት ዳዊት እንዳደረገው ተቆጠረ እንጂ ኹለቱ አባባሎች ልዩነት ኖሯቸው አይደለም። (ኹለተኛ መጽሐፍ ... ቁ:15፥ 35 ይመለከቷል )

እንዲሁም በአንድ ቦታ ሶርያውያን ሲል በሌላ ቦታ ደግሞ ኤዶማውያን ማለቱ ኹለቱ ወገኖች በአንድነት ስለተሰለፉ ነው። ይህንኑም ለመረዳት ከዜና መዋዕሉ ጥቅስ አንድ ቁጥር ቀደም ብለን ማለት በቁጥር 11 ላይ ብንመለከት "ንጉሥ ዳዊትም እነርሱን ወስዶ ከኤዶም፥ ከሞአብ፥ ከዓሞን፥ ከፍልስጥኤምና ከአማሌቅ ማርኮ ካመጣቸው ከወርቅ፥ ከብርና ከነሐስ ከተሠሩ ዕቃዎች ጋር ለአምልኮ ሥነ ሥርዐት መገልገያ እንዲኾኑ አደረጋቸው" የሚል ኾኖ እናገኘዋለን።

68 . በኹለተኛው ሳሙኤል ም.10 ቍ:18 ላይ ዳዊት ሶርያውያንን በጦርነት ባሸነፈ ጊዜ ሰባት መቶ ሰረገለኞችና አርባ ሺ ፈረሰኞች ገደለ ሲል በአንደኛ ዜና መዋዕል ም.19 ቍ:18 ደግሞ የገደለው ሰባት ሺሕ ሠረገለኞችና አርባ ሺ እግረኞች ናቸው በማለቱ ለምን ልዩነት ተፈጠረ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ሠረገለኞች በሚልበት ጊዜ ኹለተኛ ሳሙኤል ላይ የተጠቀሰው የሠረገላውን ብዛት ሲኾን ዜና መዋዕል ላይ ግን በያንዳንዱ ሠረገላ ውስጥ የነበሩት ዓሥር ሰዎች በመኾናቸው በድምሩ ሰባት ሺ ሰዎች ናቸው ማለት ነውና ኹለቱ ጥቅሶች ልዩነት የላቸውም።

69. በኹለተኛ ሳሙኤል ም.14 ቍ:27 ላይ አቤሴሎም ሦስት ወንዶችና አንዲት ሴት ልጅ የነበሩት መኾኑ ሲገለጽ በምዕራፍ 18 ቍ:18 ላይ





www.ethiopianorthodox.org

ደግሞ ምንም ልጅ አልነበረውም ስለተባለ ይህ ልዩነት ለምን ተከሠተ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በምዕራፍ 18 ቍጥር 18 ላይ አቤሴሎም ልጆች እንዳልነበሩት የሚገልጸው አባባል የሚያመለክተው ለመታሰቢያ ሐውልት ከማቆሙ በፊት ልጆቹ ኹሉ ሞተውበት የነበረ መኾኑን ነው።

70. በኹለተኛ ሳሙኤል ም.19 ቍ:16 — 23 ንጉሥ ዳዊት ሳሚ የሚባለው ብንያማዊ ላደረሰበት በደል የማይበቀለው መኾኑን በማረጋገጥ እንደማለለት የተነገረ ሲኾን በአንደኛ መጽሐፈ ነገሥት ም.2 ቍ:8 — 9 ልጁ ሰሎሞን እንዲበቀለው አደራ ያለው መኾኑ እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ዳዊት በቀልን ለመበቀል አልፈለገም እንጂ ገና በመጀመሪያ በሰደበው ጊዜ ከዳዊት ተከታዮች መካከል የጽሩያ ልጅ አቢሳ ሳሚን ለመግደል የጌታውን የዳዊትን ፈቃድ ጠይቆ ነበር ( 2ኛ. ሳሙ. ም.16 ቍ: 9 —10 ) ዳዊትም ለአቢሳ ጥያቄ በሰጠው መልስ ላይ እግዚአብሔር ዳዊትን ስደበው ብሎ ያዘዘው ስለኾነ ተወው ይርገመኝ ነው ያለው። እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ በደለኞችን ለመበቀል ወይም ለሌላ እርሱ ለሚፈልገው ጉዳይ በክፉዎች ሰዎች የሚጠቀምበት ጊዜ አለ። እነዚያ ክፉ ሰዎች ግን ክፉ ድርጊታቸውን የሚፈጽሙት ከልባቸው ክፋት የተነሣ እንጂ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ብለው አይደለም። የሳሚና የአስቆሮቱ ይሁዳም አድራጎት ይህንኑ የመሰለ ነው። እግዚአብሔርም ለክፉ ፍላጎታቸው ተዋቸው እንጂ ያንን ክፉ አድራጎት እንዲፈጽሙ አላዘዛቸውም። (መዝ.81 ቍ:.12 )

ለምሳሌ የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት መድኀኒታችን ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሕማማትን በመቀበልና በመሞት ለእኛ ቤዛ እንደሚኾነን አስቀድመው ነቢያት ትንቢት የተናገሩ መኾናቸው ግልጽ ነው። ይኹን እንጂ ለጌታ ሕማምና ሞት ከአይሁድ ካህናት ጋር በመተባበር ታላቅ አስተዋፅዖ ያደረገው ይሁዳ ገንዘብ ወዳድነት እንጂ ከዚያ የተለየ አስተሳሰብ አልነበረውም።



ዳዊት አትሞትም ብሎ ከማለለት በኋላ እንደገና ልጁን ሰሎሞንን እንዲበቀለው ማዘዙ የማርያምንና የሙሴን ኹናቴ ይመስላል። ማርያም በወንድምዋ በሙሴ ላይ አድማ ባስነሣችበት ጊዜ እግዚአብሔር ስለ ተቆጣባት ሙሴ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ቢለምንላትም "ፈራጆችን አትስደብ፤ የሕዝብህንም አለቃ አትርገመው፤" የሚለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባለማክበርዋ እግዚአብሔር ሳይቀጣ አላለፋትም። በዚሁም ዓይነት ዳዊት ራሱ ለተሰደበው ስድብ በግሉ ይቅርታ ቢያደርግም በሌላ በኩ ነት ዳዊት ራሱ ለተሰደበው ስድብ በግሉ ይቅርታ ቢያደርግም በሌላ በኩል ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ስላላከበረ ደግሞ በዚያ በኩል ስላለው ቅጣት ይቅርታ ማድረግ አልቻለም (ዘጸ. ም.22 ቍ:28 )

71. በኹለተኛው ሳሙኤል ም.24 ቍ:1 ላይ "የእግዚአብሔር ቊጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፤ ዳዊትንም ኺድ እስራኤልንና ይሁዳን ቊጠር ብሎ በላያቸው አስነሣው" ይልና ከቍጥር 10 እስከ 18 ደግሞ ዳዊት ቈጠራ በማድረጉ ተጸጽቶ የእግዚአብሔርን ይቅርታ መለመኑና እግዚአብሔርም ከሦስት ቀኖች የቸነፈር ቅጣት በኋላ ይቅርታ ያደረገ መኾኑ ተገልጾአል። በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ ም.21 ቍ:1 ላይ "ሰይጣንም በእስራኤል ላይ ተነሣ፤ እስራኤልንም ይቈጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው" ተብሎአል።

ታዲያ በመጀመሪያው አባባል ሕዝቡን እንዲቈጥር ያዘዘው እግዚአብሔር እንደኾነ ተነገሮ ሳለ በእግዚአብሔር የታዘዘውን ሥራ በመሥራቱ ለምን ተጸጸተ፥ እግዚአብሔርስ ለምን እንደጥፋት ቈጥሮበት ቀጣው? በሌላ በኩል ደግሞ በመጽሐፈ ሳሙኤል ዳዊትን ያዘዘው እግዚአብሔር ነው ከተባለ በኋላ በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ደግሞ ዳዊትን ያንቀሳቀሰው ሰይጣን ነው መባሉ እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ሕዝቡን እንዲቆጥር እግዚአብሔር ዳዊትን አነሣሣው የተባለው ማንኛውም ድርጊት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊፈጸም ስለማይችል ነው። ይህም ማለት እግዚአብሔር ለዳዊት የሕዝብ ቆጠራ ውሳኔ ምክንያት ኾነው ማለት ሳይኾን ሕዝቡን የመቁጠር ክፉ ሐሳብ በዳዊት ልብ ውስጥ በተፈጠረ ጊዜ ፍላጎቱን እንዲያደርግ ተወው እንጂ አልከለከለውም ማለት ነው። ይህም የሚኾንበት ምክንያት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሙሉ የፈቃድ ነጻነት የሰጠው በመኾኑ ነው። የመጽሐፈ ሳሙኤልን ጥቅስ ትክ ብለን ብናስተውል ዳዊት ሕዝቡን እንዲቆጥር የእግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

ፈቃድ አለመኾኑን ልንረዳ እንችላለን፤ ምክንያቱም ጥቅሱን የሚጀምረው "የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ" በማለትና ከዚያም በቆጠራው ምክንያት በእግዚአብሔር ተወስኖ የደረሰው ቅጣት በቂ ማስረጃ ነውና። በተመሳሳይ ኹኔታ በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 4 ቍ፡ 21 ላይ እግዚአብሔር የፈረዖንን ልብ አጸና የተባለው ፈርዖን ልቡን ግትር በሚያደርግበት ጊዜ ለፍላጎቱ ተወው ማለት ነው እንጂ ለፈርዖን ግትርነት እግዚአብሔር ኀላፊ ነው ማለት አይደለም።

ስለዚህም በዳዊት ልብ ውስጥ ሕዝብን የመቁጠር ፍላጎት ያሳደረው ሰይጣን እንጂ እግዚአብሔር እንዳልኾነ እንገነዘባለን። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሙሉ የፈቃድ ነጻነት የሰጠው መኾኑን ሲያመለክት ኢያሱ ወልደ ሲራክ፥ "እሳትንና ውሃን በፊትህ አኑሮልሃል፤ እጅህን ወደመረጥኸው ክተት" ብሏል። (ሲራ. ም.15 ቍ:16)

72. በኹለተኛው ሳሙኤል ም.24 ቍ:13 - 15 እንደሚነበበው ዳዊት በበደለ ጊዜ የእግዚአብሔር ቅጣት ማለት ቸነፈር በሕዝቡ ላይ ወርዶ ሰባ ሺ ሰው እንደሞተ ተገልጾአል።

ታዲያ ዳዊት በበደለ እንዴት በሕዝቡ ላይ ቅጣት ተወሰነበት ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

እግዚአብሔር አንድን በደለኛ ሕዝብ ለመቅጣት በተለያዩ መንገዶች ይጠቀማል። ዳዊት በበደለበት ዘመን ምናልባት ሕዝቡ እግዚአብሔርን ቅር የሚያሰኙ በደሎችን በመፈጸም ለመቀጣት ተገቢ ኾኖ ሊኾን ይችላል። እንደ አጋጣሚ ኾኖ የቅጣቱ ቀጥተኛ ምክንያት የዳዊት ኀጢአት ይኹን እንጂ ከዚያም በተለየ መንገድ ለጥፋቱ ቅጣት የተቀበለ ነበር። ለምሳሌ ፈርዖን ልቡን ባደነደነና የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ባልተቀበለበት ጊዜ የግብጽ ሕዝብም አብሮት እስራኤልን በመጨቈን ተባብሮ ስለበረ ቅጣቱ በኹሉም ላይ ደርሶአል። በሌላ በኩል ደግሞ የነነዌ ከተማ ሕዝብ ከንጉሡ ጋር አብሮ በንስሓ በተመለሰ ጊዜ የእግዚአብሔር ይቅርታ ተደርጎላታል።

በዚህም መሠረት ዳዊት እግዚአብሔር ያልፈቀደውን የሕዝብ ቈጠራ በማድረግ እግዚአብሔርን ቅር ባሰኘበት ጊዜ ከእስራኤልም ሕዝብ



አብዛኞዎቹ እግዚአብሔርን የሚያስቈጣ በደል በደለው ስለነበረ በዳዊት በደል መነሻነት ሲቀጡ በቅተዋል እንጂ በዳዊት በደል ብቻ የተቀጡ አይደሉም።

## አንደኛ ነገሥት (ሦስተኛ ነገሥት)

ይህን መጽሐፍ የጻፈው ማን እንደኾነ በትክክል የታወቀ ባይኾንም በአይሁድ አባባል ነቢዩ ኤርምያስ እንደጻፈው ይነገራል። ሌሎች ደግሞ ንጉሥ ሰሎሞንና ንጉሥ ሕዝቅያስ የነገሡ ዘመናቸውን ታሪክ ሲጽፉ ነቢዩ ኢሳይያስና ነቢዩ ኤርምያስ የነበሩበትን ዘመን ታሪክ ጽፈዋል ይላሉ። ከሰባዎች ትርጓሜ በፊት አንደኛና ኹለተኛ መጽሐፈ ነገሥት አንድ መጽሐፍ እንጂ ኹለት አልነበሩም። ለኹለት የተከፈለው በሰባዎቹ ትርጓሜ ጊዜ ነው።

አንደኛ ነገሥት 22 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ የሰሎሞን መንገሥ፥ ቤተ መቅደስን መሥራቱ፥ በብዙ ነገር ገናና መኾኑ፥ በኋላ ዘመን በኀጢአት መውደቁ፥ ከሰሎሞን ሞት በኋላ መንግሥቱ ለኹለት መከፈሉ፥ ኢየሩሳሌምን መናገሻው ያደረገው የይሁዳ መንግሥት የብንያም ነገዶች ብቻ ሲቀሩለት የቀሩት ዐሥሩ ነገዶች ግን ወደሰማርያ መሰባሰባቸውና እንዲሁም በኹለቱ ግዛቶች የነገሡትን ነገሥታት ታሪክ የሚመለከት ነው።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

73. በአንደኛ ነገሥት ም.4 ቍ:26 ላይ "በአርባ ሺሕ ጋጥ የሚገቡ የሠረገላ ፈረሶችና ዐሥራ ኹለት ሺሕ ፈረሰኞች ነበረው" ካለ በኋላ በኹለተኛው ዜና መዋዕል ም.9 ቍ:25 ላይ ደግሞ "ሰሎሞንም ለፈረሶችና ለሠረገሎች አራት ሺ ጋጥ ዐሥራ ኹለት ሺ ፈረሰኞች ነበሩ" በማለቱ ኹለቱ አባባሎች ለምን ተለያዩ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።



www.ethiopianorthodox.org

የመጀመሪያው ጥቅስ የሚያመለክተው የፈረሶቹን ብዛት ሲኾን ኹለተኛው ጥቅስ ግን የሚያመለክተው እያንዳንዱን ዐሥር ፈረስ የሚ ይዝ የጋጦችን ብዛት ነው።

74. በአንደኛ ነገሥት ም.5 ቊ:16 ላይ በሠራተኞች ላይ የተሾሙት ሦስ ት ሺ ሦስት መቶ ናቸው ይልና በኹለተኛ ዜና መዋዕል ም.2 ቊ:2 ላይ ደግሞ ሦስት ሺ ስድስት መቶ ናቸው በማለቱ ልዩነት ያለው ይመስለን ይኾናል።

በመጽሐፈ ነገሥትና በመጽሐፈ ዜና መዋዕል የተገለጹት የአለቆች ብዛት ጸሐፊዎቹ ሊገልጹ የፈለጉት ጉዳይ በዘር በጕሣና በሹመት ደረጃቸው የተለያየ ቍጥር ይኑራቸው እንጂ በመጨረሻ ላይ ግን ወደተ መሳሳይ ቍጥር ይደርሳሉ።

በአንደኛ ነገሥት ም.5 ቊ:16 ላይ የተጠቀሱት ሦስት ሺ ሦስት መቶ አለቆች በምዕራፍ 9 ቊ:23 ላይ ከተጠቀሱት አምስት መቶ ኀምሳ አለቆች ጋር ሲደመሩ ሦስት ሺ ስምንት መቶ ኀምሳ ይኾናሉ።

በኹለተኛው ዜና መዋዕል ም.2 ቊ:2 ላይ የተጠቀሱት ሦስት ሺ ስድስት መቶ አለቆች በምዕራፍ 8 ቍጥር 10 ዐይነተኛች አለቆች ተብ ለው ከተጠቀሱት ኹለት መቶ ኀምሳ ጋር ሲደመሩ ሦስት ሺ ስምንት መቶ ኀምሳ ስለሚኾኑ ልዩነት የላቸውም ማለት ነው።

75. በአንደኛው መጽሐፈ ነገሥት ም.7 ቊ: 26 ላይ የናሱ ክብ ኩሬ ኹለት ሺ የባዶስ መስፈሪያ እንደሚይዝ የተነገረ ሲኾን በኹለተኛው ዜና መዋዕል ም.4 ቊ:5 ላይ ደግሞ ሦስት ሺ የባዶስ መስፈሪያ ይይዝ ነበር ስለተባለ ልዩነት ያለ ይመስል ይኾናል።

በተጠቀሰው ኩሬ ውስጥ በየጊዜው የሚቀመጠው ኹለት ሺ የባዶስ መስፈሪያ መኾኑን የመጀመሪያው ጥቅስ የገለጸ ሲኾን ኹለተኛው ጥቅስ ግን የገለጸው ዕቃው እስከ አፉ ቢሞላ ምን ያኽል ሊይዝ የሚችል መኾ ኑን ለማመልከት ነው።



76. በአንደኛ ነገሥት ም.15 ቊ:16 ላይ "በአሳና በእስራኤል ንጉሥ በባኦስ መካከል በዘመናቸው ኹሉ ሰልፍ ነበር" ካለ በኋላ ኹለተኛ ዜና መዋዕል ም.15 ቊ:19 ላይ "አሳ እስከ ነገሠበት እስከ ሠላሳ አምስተኛው ዓመት ድረስ ሰልፍ አልነበረም" በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስ ሉ ይኾናል።

በኹለተኛ ዜና መዋዕል ም.16 ቊ:1 ላይ ብንመለከት "አሳ በነገሠ በሠላሳ ስድስተኛው ዓመት የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ በይሁዳ ላይ ወጣ" ስለሚል ባኦስም የነገሠው በዚያን ጊዜ ኾኖ ጦርነቱም ከዚያን ጊዜ ጀም ሮ ተነሣ ማለት ነውና ተቃራኒ አይደለም።

77. በአንደኛ ነገሥት ም15 ቊ:33 ላይ "በይሁዳ ንጉሥ በአሳ በሦ ስተኛው ዓመት የአኪያ ልጅ ባኦስ በእስራኤል ኹሉ ላይ በቴርሳ ንጉሥ ኾኖ ኻያ አራት ዓመት ነገሠ" የሚለውና በኹለተኛ ዜና መዋዕል ም.16 ቊ: 1 ላይ "አሳ በነገሠ በሠላሳ ስድስተኛው ዓመት የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ በይሁዳ ላይ ወጣ" የሚሉት እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስሉን ይኾናል።

በኹለተኛው ዜና መዋዕል የተጠቀሰው ሠላሳ ስድስት ዓመት የይ ሁዳና የእስራኤል ነገሥታት ተለያይተው ለየራሳቸው መንግሥት ከመ ሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ ማለት ነው እንጂ ያለበለዚያማ ባኦስ የነገሠው ኻያ አራት ዓመት ብቻ መኾኑ እየታወቀ እስከ ሠላሳ ስድስተኛው የአሳ ዘመነ መንግሥት ድረስ ቆየ ማለት ያስመስላል።

78. በአንደኛ ነገሥት ም.18 ቊ:1 ላይ "ከብዙ ቀንም በኋላ በሦስተኛው ዓመት ኺድ ለአክአብ ተገለጥ፤ በምድር ላይም ዝናብ እሰጣለሁ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤልያስ መጣ" የሚለውና በሉቃስ ወንጌልም .4 ቊ: 25 ላይ "በኤልያስ ዘመን ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ሰማይ ተዘግቶ ሳለ" ተብሎ የተነገረው ጥቅስ ልዩነት የፈጠሩ ይመስሉን ይኾ ናል።

በመጀመሪያው ቅጥስ ላይ ዝናቡ ያቆመው ሦስት ዓመቱ ነው አላ ለም። እዚህ ላይ በሦስተኛው ዓመት የተባለው ኤልያስ ወደ ሰራጵታ ከኼደበት ጊዜ ጀምሮ ማለት ነው። ወደ ሰራጵታም የኼደው ወዲያው



www.ethiopianorthodox.org

ዝናቡ እንደቆመ ሳይኾን ለአንድ ለተወሰነ ጊዜ ከቆየ በኋላ መኾኑን በአንደኛ ነገሥት ም.17 ቍ:1 – 10 በመመልከት ልንረዳ እንችላለን።

## ኹለተኛ ነገሥት (አራተኛ ነገሥት)

በኻያ አምስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ኾኖ ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 17 ድረስ ስለይሁዳና ስለእስራኤል መንግሥታት እስከ የእስራኤል መንግሥት በአሦር መንግሥት መማረክ ድረስ ይዘረዝራል። ምዕራፍ 18 እስከ መጨረሻው ድረስ ደግሞ ስለይሁዳ መንግሥት እስከ ናቡከደነፆር ምርኮ ድረስ ያለውን ታሪክ ይዘረዝራል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

79. በኹለተኛው መጽሐፈ ነገሥት ም.9 ቍ: 1 - 10 ኢዩ የአክዓብን ቤት እንዲያጠፋ እግዚአብሔር ያዘዘው መኾኑ የተነገረ ሲኾን በትንቢተ ሆሴዕ ም.1 ቍ:4 ላይ ደግሞ እግዚአብሔር ኢዩን ሊበቀለው እንደሚፈልግ ተገልጾአል። ታዲያ እንዴት የታዘዘውን ትእዛዝ በመፈጸሙ እግዚአብሔር ሊበቀለው ፈለገ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ቀደም ተብሎ በሌላ ርእስ ሥር እንደተገለጸው አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር የሚመለከተው የሰውን ልጅ አፍአዊ ድርጊት ብቻ ሳይኾን ውሳጣዊ ዝንባሌውንም ጭምር ነው። ምንም እንኳን ኢዩ የአክአብን ቤት በማጥፋት ረገድ ብዙ እርምጃ ቢወስድ ይህ ድርጊቱ ግን የበቀል ፍላጎት እንጂ ለሕገ እግዚአብሔር ቀናተኛ በመኾን አይደለም። ይህንኑም ለመረዳት በኹለተኛው መጽሐፈ ነገሥት ም.10 ቍ:29 – 31 መመልከት እንችላለን። ምንም እንኳን እግዚአብሔር የአክዓብን ቤት እንዲያጠፋ ኢዩን መሣሪያ ቢያደርገው ኢዩም በኀጢአቱ መቀጠት ይኖርበታል።

ስለዚህ የልብን ጥልቅ ሐሳብ የሚያውቀው አምላክ የኢዩን የግል በቀል ዝንባሌ በመመልከቱ ኢዩን ሊበቀለው ፈለገ።



80. በኹለተኛው መጽሐፈ ነገሥት ም.15 ቍ:30 ላይ ኢዮአታም ኻያ ዓመት የነገሠ መኾኑ ሲነገር በዚሁ ምዕራፍ በቍጥር 33 ላይ ደግሞ የነገሠው ዓሥራ ስድስት ዓመት ብቻ እንደኾነ በመግለጹ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል።

በዚሁ ምዕራፍ በቍጥር 5 ላይ እንደተገለጸው አባቱ በለምጽ በሽታ ስለተቀጣ በሕዝቡ ላይ የሚፈርደው ኢዮአታም ነበር።

ስለዚህ ኻያ ዓመት የተባለው አባቱ በለምጽ በሽታ ታሞ እስከ ሞተበት ቀን ድረስ ያለውን ጊዜ በመቁጠር ሲኾን ዓሥራ ስድስት ዓመት የተባለው ግን ከአባቱ ሞት በኋላ ከነገሠበት ጊዜ ጀምሮ ነውና በዚህም መሠረት እነዚያ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒዎች አይደሉም።

81. በኹለተኛው መጽሐፈ ነገሥት ም.24 ቍ:8 ላይ ኢዮአኪን መንገሥ በጀመረ ጊዜ የዐሥራ ስምንት ዓመት ጕልማሳ ነበር ካለ በኋላ በኹለተኛ ዜና መዋዕል ም.36 ቍ:9 ላይ ደግሞ የስምንት ዓመት ልጅ ነበር በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።

አንዳንድ ነገሥታት ልጆቻቸውን ለማስለመድ ሲሉ በሕይወት ዘመናቸው ከእነርሱ ጋር አብረው የንጉሥነቱን ሥራ ያሠሩአቸዋል። ከላይ የተጠቀሰውም የመጀመሪያው ጥቅስ ከአባቱ በኋላ የነገሠበትን ጊዜ ሲኾን የኹለተኛው ጥቀስ ግን ከአባቱ ጋር ኾኖ አብሮ ይፈርድበትንም ጊዜ በመጨመር ነው።

## አንደኛ ዜና መዋዕል

አንደኛና ኹለተኛ ዜና መዋዕል የተጻፉት ከባቢሎን ምርኮ በኋላ በካህኑ በዕዝራ ነው። ከሰባዎቹ ትርጓሚዎች በፊት አንድ መጽሐፍ እንጂ ኹለት አልነበሩም። በመጨመር ወይም በመቀነስ ከመጽሐፈ ነገሥት አንዳንድ ልዩነቶች አሉባቸው። አንደኛው ዜና መዋዕል 29 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በኹለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፋፈላል።

www.ethiopianorthodox.org

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 9 ድረስ የዘር ቆጠራን የሚመለከት ነው።

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 9 እስከ ምዕራፍ 29 ድረስ የሳኦል መንግሥት ወድቆ የዳዊት መንግሥት መቋቋሙንና በመጨረሻም ዳዊት መንግሥቱን ለልጁ ለሰሎሞን ማስረከቡን የሚያመለክት ነው።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

82. በአንደኛ ዜና መዋዕል ም.3 ቍ:19 ላይ ዘሩባቤል የፈዳያ ልጅ ሲባል በመጽሐፈ ዕዝራ ም.3 ቍ:2፥ ም.5 ቍ.2፥ በመጽሐፈ ነህምያ ም.12 ቍ:1፥ በትንቢት ሐጌ ም.1 ቍ: 1, በማቴዎስ ወንጌል ም. 1 ቍ:12 ላይ ዘሩባቤል እንዴት የሰላትያል ልጅ ተባለ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል በአይሁድ ልማድ አንዳንድ ጊዜ ልጆች በአባታቸው ሳይኾን በአያታቸው ስም ይጠራሉ። ለምሳሌ በኦሪት ዘፍጥረት ም.24 ቍ:24 እና 47 ላይ ላባን የባቱኤል ልጅ መኾኑ ከተነገረ በኋላ በኦሪት ዘፍጥረት ም.29 ቍ:5 ላይ የናኮር ልጅ መኾኑ ተገልጾአል።

ሰላትያልም የዘሩባቤል አያት መኾኑን ለመረዳት በአንደኛ ዜና መዋዕል ም.3 ቍ:18 ላየ መመልከት እንችላለን።

83. በአንደኛ ዜና መዋዕል ም.10 ቍ:13 ላይ "ሳኦል ለእግዚአብሔር ታማኝ ኾኖ ባለመገኘቱ ምክንያት ሞተ፤ እርሱ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም እምቢ አለ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመጠየቅ ፈንታ የሙታን መናፍስት ጠሪዎችን በመጠየቅ መመሪያ ለማግኘት ሞከረ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በሞት ቀሠፈው፤ መንግሥቱም ወደ እሴይ ልጅ ወደ ዳዊት እንዲተላለፍ አደረገ" የሚለው አባባል ከእግዚ..ብሔር ጸሎት ተቀባይነት ጋር ተቃራኒ አይኾንም ወይ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል። ሳኦል ኀጢአት መሥራቱን አምኖ እግዚአብሔር ይቅርታ እንዲያደርግለት ይለምንለት ዘንድ ሳሙኤልን ቢማጸነው ምንም አማራጭ ሳይሰጠው እምቢብሎት መኼዱን በ1ኛ. ሳሙ. ም.15 ቍ: 24 — 29 ይመለከቷል።



በየጊዜው እንደተገለጸው እግዚአብሔር ..ሰው ልጅ ሙሉ የፈ
ቃድና የፍላጎት ነጻነትን ሰጥቶታል። ደጉንና ..ፉውን ለይቶ የማወቅ
ችሎታም አለው።

በአንደኛ ሳሙኤል ም.10 ቍ: 8 ላይ ..ሙኤል ሳኦልን ከቀባው
በኋላ የሚቃጠለውንና ለደኅንነት የሚኾነውን ..ኅብረት ማሥዋዕት ለማ
ቅረብ አንተን ወደማገኝበት ወደ ጌልጌላ ቀድመ.. ትኼዳለህ፤ እኔ መጥቼ
ምን ማድረግ እንደሚገባህ እስክነግርህ ድረስ ..ሰባት ቀን በዚያው ቆይ"
ያለው ኾኖ ሳለ በሰባተኛው ቀን ሳሙኤል ከ..መምጣቱ በፊት የሚቃጠ
ለውንና ለደኅንነት የሚኾነውን መሥዋዕት በ..ቅረቡ ወዲያው ሳሙኤል
መጥቶ ሳኦል የሠራው ሥራ ትክክል አለመ..ንና በዚህ የእግዚአብሔ
ርን ትእዛዝ በማፍረሱ ..ጠለ መንግሥቱ ..ጸናና ለሌላ ሰው የሚሰ
ጥበት መኾኑን በመግለጥ አስጠንቅቆት ነበር። (1ኛ ሳሙ. ም.13 ቍ:8
– 10 )

በአንደኛው ሳሙኤል ም.15 ቍ: 1- 3 ..ኦል በዐማሌቃውያን ላይ
ጦርነት እንዲከፍትና ከእነርሱም ሰዎችንም .. እንስሳትን አንዳችም ሳያ
ስተርፍ እንዲያጠፉ ከእግዚአብሔር ታዞ ሳለ ..ሁንም እንደገና የእግዚአ
ብሔርን ትእዛዝ በማፍረስ የዐማሌቅን ንጉ.. አጋግን በሕይወት ማርኮ
ምርጥ ምርጥ የኾኑትን በጎች የቀንድ ከብቶ.. የሰቡ ሰንገዎችንና ጥቦቶ
ችን ሳያጠፋቸው ቀረ። በጌልጌላ በፈጸመው ..ለመታዘዝ ኀጢአት ማስጠ
ንቀቂያ ቢሰጠውም እንደገና በዐማሌቃው.. ላይ ባደረገው ጦርነት ስለ
ደገመው ወደፊትም ዕድል ቢሰጠው ከዚ.. ..ተሻለ እንደማይኾን ተረጋገ
ጠ። በዚህም ምክንያት ነቢዩ ሳሙኤል በ..ያወላውል አነጋገር የእግዚ
አብሔርን ውሳኔ ለሳኦል ሲነግረው እንዲ.. ብሎታል "በእግዚአብሔር
ላይ ማመፅ እንደሟርተኛነት፥ የትዕቢት እ..ከኛነትም ጣዖትን በማምለክ
ኀጢአት እንደመሥራት ይቈጠራል፤ አ..ንም የእግዚአብሔርን ቃል
ንቀሃልና እግዚአብሔርም ንጉሥ እንዳትኾ.. ናቀህ።" (1ኛ ሳሙ. ም.15
ቍ:23 )

በአንድ በኩል የእግዚአብሔር ዕውቀ.. በጊዜ የተወሰነ ባለመኾኑና
ሳኦል ይቅርታ እንኳ ቢደረግለት ወደፊ.. የማይሻሻል መኾኑን እግዚ
አብሔር አስቀድሞ የሚያውቀው በመኾ.. በሌላ በኩል ደግሞ ከእስ
ራኤል ሕዝብ መካከል ተመርጦ ለንጉ..ት የበቃው ሳኦል ከእርሱም



www.ethiopianorthodox.org

በኩል ከማንኛውም ተራ ሰው በላይ ስለሚጠበቅበትና ለሚጠበቅበት ኹና ቴ ብቁ ኾኖ ባለመገኘቱ ጸሎቱ ወይም ልመናው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀር ቶአል። ለምሳሌ ሙሴን የሚያኽል ታላቅ ነቢይና የእግዚአብሔር ባለ ሟል በመሪባ ውሃ ጉዳይ በፈጸመው በደል ምክንያት ወደተስፋ ምድር እንዳይገባ ስለተፈረደበት ይቅርታ ተደርጎለት ወደተስፋ ምድር ለመግ ባት ይችል ዘንድ እግዚአብሔርን ቢለምን ያልተፈቀደለት ያጥፋት ከእ ርሱ የሚጠበቅ የነበረ በመኾኑ ነው። (ዘዳ. ም.3 ቁ: 23 - 27 ) ብዙ ከተሰጠው ብዙ ይጠበቅበታል። (ሉ. ም. 12 ቁ:48 )

ስለዚህ እግዚአብሔር ብዙ ከተሰጠው ሰው ብዙ ስለሚጠብቅና በእ ስራኤል ሕዝብ ኹሉ ላይ የመንግሥ ታላቅ ክብር የተሰጠው ሳኦል የሚ ጠበቅበትን ለማሟላት ብቁ ኾኖ ባለመገኘቱ ጸሎቱ ተሰሚነት ሊያገኝ አልቻለም እንጂ እግዚአብሔር ከልብ የተጸለየ ጸሎትን የማይቀበል ኾኖ አይደለም። (ጥያቄና መልስ ቁ:128 ) ይመለከቷል።

## ኹለተኛው ዜና መዋዕል

ይህ መጽሐፍ 36 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ዘጠኝ ድረስ ሲኾን እርሱም የሰሎሞን ሀብታምነት፥ ቤት መቅደስን ማሳነጹ፥ ቤት መቅደሱንም ሲያ ሠራ የፈጀው ገንዘብና በምድር ታላቅ ክብር ያለው መኾኑና ስለ ሰሎሞን ገናናነት ስለሰማችውና በሀይንዋ ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ስለመጣችው ስለንግሥተ ሳባ ተዘርዝሮአል።

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 10 እስከ 16 ድረስ ሲኾን በውስጡ ም ከሰሎሞን ሞት በኋላ የልጁ የሮብዓም መንገሥ፥ በሮብዓምም ዘመን መንግሥቱ ለኹለት መከፈሉ፥ መከፋፈሉን ለመቋቋም ለጦርነት በተዘጋ ጀ ጊዜ እግዚአብሔር በነቢዩ በሸማዕያ አማካይነት በወንድሞቻቸው በእ ስራኤል ላይ እንዳይዘምቱ ማስጠንቀቁና እነርሱም ማስጠንቀቂያውን ሰምተው ወደ የቤታቸው መመለሳቸው፥ የይሁዳ ንጉሥ አቢያ የእስራኤ ልን ንጉሥ ኢዮርብዓምን ማሸነፉ፥ እንዲሁም የይሁዳ ንጉሥ አሳ ኢትዮ



ጵያውያንን ድል ማድረጉና ከእስራኤል ጋር ሲዋጋበትም የይሁዳ ንጉሥ ቤንሀዳድ እንዲረዳው ስጦታ በመላኩ በነቢዩ አናኒ አማካይነት ከእግ ዚአብሔር ወቀሳ የደረሰበት መኾኑ ተዘርዝሮዋል።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 17 እስከ ምዕራፍ 21 ሲኾን በእር ሱም ውስጥ ኢዮሣፍጥ የአባቱን ዙፋን መውረሱ፥ የእስራኤልን ንጉሥ አክዐብን ለመርዳት ከመውጣቱ በፊት የእግዚአብሔርን መንገድ መከተሉ፥ የዐሞንና የሞአብ ሰዎች በኢዮሣፍጥ መንግሥት ላይ በተነሡ ጊዜ በእግዚአብሔር ኀይል መደምሰሳቸው፥ ኢዮሣፍጥ ከሞተ በኋላ ልጁ ኢዮራም ዙፋኑን መውረሱ፥ እርሱ የአባቱን መንገድ የማይከተል በመኾኑ ነቢዩ ኤልያስ እንዲያስጠነቅቀው መደረጉ በመጨረሻም ስምንት ዓመት ከነገሠ በኋላ በከባድ የአንጀት በሽታ መሞቱ ተዘርዝሮአል።

አራተኛው ክፍል ከምዕራፍ 22 እስከ ምዕራፍ 36 ድረስ ሲኾን በዚህ ክፍል ውስጥ የቀሩት የሌሎች ነገሥታት ታሪክ እስከ ናቡከደነፆር ምርኮ ድረስ ተዘርዝሮ ይገኛል።

## ጥያቄና የጥያቄ መልስ

84. በኹለተኛው ዜና መዋዕል ም.2 ቁ: 13 እና 14 ላይ "እናቱ ከዳን ወገን የኾነችና አባቱ የጢሮስ ሰው የኾነውን ብልሃተኛውን ሑራምን ልኬልሀለሁ" የሚለውን ሐሳብ በአንደኛ ነገሥት ም.7 ቁ: 14 ላይ እና ቱ ከንፍታሌም ወገን የኾነች ነች በመባሉ ለምን ኾነ፤ አባባሎች ተለያዩ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የሑራም እናት በኹለቱም ነገዶች የተወለደች መኾን አለባት። አባ ትዋ ከዳን ነገድ ቢኾን እናትዋ ከንፍታሌም ነገድ ትኾናለች፤ ወይም ደግ ሞ አባትዋ ከንፍታሌም ነገድ ቢኾን እናትዋ በዳን ነገድ ነች ማለት ነውና ኹለቱ አባባሎች ልዩነት አይኖራቸውም።



www.ethiopianorthodox.org

## መጽሐፈ ዕዝራ

ይህን መጽሐፍ የጻፈው ካህኑ ዕዝራ ነው: መጽሐፉም ዐሥር ምዕራፎች ያሉት ሲኾን በኹለት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፋፍሎአል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 6 ድረስ ኾና በውስጡ የፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ የእስራኤል ልጆች ወደ ሀገራቸው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ሲል የደነገገው አዋጅ ይገኝበታል። ይህን ያደረገበት ዋነኛው ምክንያት በከለዳውያን ዘንድ ተሰሚነት በነበረው በነቢዩ ዳንኤል አማካይነትና በተለይም ነቢያት ለምሳሌ እነ ኢሳይያስ ስለ ጢሮስ የተነበዩትን ትንቢት እንዲረዳ አድርጎት ስለነበረ ነው የሚል አስተሳሰብ አለ። በአዋጁም ትእዛዝ ያስተላለፈውና ጥሪ ያደረገው ለእስራኤል ሕዝብ ስለነበረ ከተመላሾቹ አብዛኛዎቹ በዘሩባቤል መሪነት የይሁዳና የብንያም ነገዶች እንደነበሩ ተገልጾአል። ለቤተመቅደሱ ሥራ የሚያገለግል ቈሳቍስም ሰጥቶአቸዋል።

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 7 እስከ ምዕራፍ 10 ድረስ ሲኾን በ ዚህ ክፍል ሌሎችም በዕዝራ መሪነት ወደ ኢየሩሳሌም መመለሳቸው፥ በዕዝራ አማካይነት የሃይማኖት ተሐድሶ መደረጉ ተዘርዝሮአል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

85. ከምርኮ ወደ ሀገራቸው ወደ ኢየሩሳሌም ስለተመለሱት የእስራኤል ሰዎች በመጽሐፈ ዕዝራ ምዕራፍ ኹለት ላይ የተገለጸው ዝርዝር ድምር 29818 በመጽሐፈ ነህምያ ምዕራፍ ሰባት ላይ ከተሰጠው የዝርዝር ድምር 31089 ጋር ለምን ልዩነት ሊኖር ቻለ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ይህ ልዩነት ሊኖር የቻለው በዕዝራ ጊዜ የነበረው አመዘጋገብና በነህምያ ጊዜ የተደረገው አመዘጋገብ የተለያየ በመኾኑ ነው። የስም ዝርዝር በሚወሰድበት ጊዜ ምንአልባት አንዳቸው ጌቶቻቸው ነጻ ያወጡአቸውን ባሪያዎች በዝርዝራቸው ውስጥ አላስገቡ ሊኾን ይችላል። ማለትም አንዳቸው የመዘገቡትን ሌላው በመርሳትም ይኹን ወይም በሌላ ምክንያት ሳይመዘግበው ቀርቶ ሊኾን ይችላል። ይሁን እንጂ በዕዝ. ም.2 ቍ: 65 እና በነህምያ ም.7 ቍ: 67 ላይ 42360 በማለት በመ[illegible]ረሻው ቍጥር ላይ ስለተስማሙ ልዩነት የላቸውም ማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜ አንዱ ዘንድ ያሉት ስሞች ሌላው ዘንድ ካሉት ስሞች ልዩነት መታየቱ እስራኤሎችና ሌሎች የምሥራቅ አገር ሰዎች በመጠሪያ ስም ወይም በማዕረግ ስም ወይም ደግሞ በቤተሰብ ስም ሊጠሩ ስለሚችሉ ነው።

86. በመጽሐፈ ዕዝራ ም.7 ቍ:6 ላይ "ዕዝራ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር በሰጠው በሙሴ ሕግ ፈጣን ጸሐፊ ነበረ፤ የአምላኩም የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ ነበረችና ንጉሡ የሻውን ኹሉ ሰጠው" በማለቱ እንዴት ራሱን ያመሰግናል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ይህ አባባል ራስን ለማመስገን የተነገረ ሳይኾን የራስን ማንነት ለመግለጽ የተነገረ በመኾኑ በዚሁ ዓይነት መውሰድ [illegible]ኖርብናል። ሌላ ሰው ሊገልጸው የማይችለው እስኪኾን ድረስ ስለራሱ ማንነት መግለጹ ተገቢ ነው እንጂ ራስን ማመስገን አይደለም። ቍ:41, 88, 121 ይመለከቷል።

87. በመጽሐፈ ዕዝራ ምዕራፍ 10 ቍጥር 49 ላይ "እነዚህ ኹሉ ባዕዳን ሴቶችን አግብተው የነበሩ ናቸው፤ እነርሱም ያገቡአቸውን ባዕዳን ሴቶች ኹሉ ፈትተው ከነልጆቻቸው አባረሩ" የሚለው አባባል በመጽሐፈ ሩት ም.4 ላይ እንደተገለጸው ቦዔዝ ሞአባዊትዋን ሩትን አግብቶ የዳዊትን አያት ኢዮቤድን ከመውለዱ ጋር እንዴት ሊታረቅ ይችላል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ባዕዳን ሴቶችን ማግባት የተጠላው በዘር ልዩነት ምክንያት ሳይኾን እነዚያ ባዕዳን ሴቶች ለባሎቻቸው የጣዖት ማምለክን ሥራ ስለሚያስተምሩአቸው ነው እንጂ እግዚአብሔር አንዱን ዘር ከሌላው የሚመርጥ ኾኖ አይደለም። እነዚያ የተጠቀሱት ሚስቶችም ለባሎቻቸው ኀጢአት ምክንያቶች እንደኾኑ ለመረዳት የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት፥ "ከዚህም በኋላ ከዔላም ጐሣ የየሒኤል ልጅ ሽካንያ ዕዝራን እንዲህ አለው፥ በእርግጥ እኛ ባዕዳን ሴቶችን በማግባት በእግዚአብሔር ላይ የነበረንን እምነት አጓድለናል፤ ይህም ኹሉ ኾኖ አሁንም ለእስራኤል ተስፋ አለ፤



www.ethiopianorthodox.org

አሁን እንግዲህ እነዚህን ባዕዳን ሴቶች ከነልጆቻቸው ማስናበት እንደሚ ገባን ለአምላካችን ቃል እንግባ፤ አንተና የእግዚአብሔርን ሕግ የሚያ ብሩ ሌሎችም የምትሰጡንን ምክር ኹሉ እንፈጽማለን የእግዚአብሐር ሕግ የሚያዝዘውን ኹሉ እናደርጋለን።" (ም.10 ቍ: 2 - 3 ) ይህ አባባል የሚያመለክተው እነዚያ የባዕድ ሴቶችን ያገቡት ሰዎች ከአምልኮተ እግዚአብሔር ርቀው የነበሩ መኾናቸውን ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሩት የሰማይንና የምድርን ጌታ ለማምለክ ወስና የነበረች መኾኑን ለመረዳት የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት "ሩትም እን ዲህ አለቻት፥ ተለይቼሽ እንድመለስ አታስገድጅኝ፤ አብሬሽ እንድኼድ ፍቀጂልኝ፤ አንቺ ወደምትኼጂበት ኹሉ እኼዳለሁ፤ አንቺ በምትኖሪ በት እኖራለሁ፤ ከአሁን ጀምሮ ሕዝብሽ ሕዝቤ ነው፤ አምላክሽም አም ላኬ ነው።" (ሩት ም.1 ቍ:16 )

በዚህም መሠረት ሩት ለቦዔዝ የሃይማኖት መሰናክል የምትኾን ሳይ ኾን የእርሱን አምልኮት የምትከተል በመኾንዋና በመጽሐፈ ዕዝራ ከተ ጠቀሱት ሴቶች የተለየች በመኾኗ ኹለቱ ኹናቴዎች የሚቃረኑ አይደሉ ም።

## መጽሐፈ ነህምያ

ይህን መጽሐፍ የጻፈው ዕዝራ መኾኑን አንዳንዶች የሚያምኑ ቢኾ ኑም አብዛኞች ግን የጻፈው ነህምያ ነው በሚለው ሐሳብ ይጸናሉ። መጽ ሐፉም 13 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በሦስት ትልልቅ ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ምዕራፍ 1 ና ምዕራፍ 2 ሲኾን በውስጡ ነህ ምያ የሚመለስበት ምክንያት የኢየሩሳሌም ቅጽሮች በመፍረሳቸውና በሮቹም በእሳት በመቃጠላቸው እነርሱን ለማሠራት መኾኑ ተገልጾአል።

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ ሦስት እስከ ምዕራፍ ስድስት ድረስ ሲኾን ምንም እንኳ ከአካባቢው የአይሁድ ጠላቶች ተቃውሞ ቢሰነዘር ነህምያ ቅጽሮቹንና በሮቹን ለማሠራት መቻሉ ተገልጾአል።



ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 7 እስከ ምዕራፍ 13 ድረስ ሲኾን በውስጡም የሃይማኖት ተሐድሶ መከናወኑን ይዘረዝራል።

## ጥያቄና መልስ

88. በመጽሐፈ ነህምያ ም.5 ቍ: 14 - 18 ላይ ነህምያ ከራስ ወዳድነት ነጻ እንደኾነና ከእርሱ በፊት የነበሩ የሕዝብ ገዢዎች ግን ሕዝብን ይበ ድሉ እንደነበረ ዘርዝሮ ማስረዳቱ እንዴት እንደ ግብዝነት ሳይቆጠርበት ቀረ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በጥያቄና መልስ ተራ ቍጥር 41፥ 86፥ 121 በዝርዝር እንደተገ ለጸው አንድ ጸሐፊ ስለራሱ ገለጻ በሚያደርግበት ጊዜ ራሱን የሚያመሰ ግን ቢመስልም እንኳ ጽሑፉን ለሚሰሙ ወይም ለሚያነቡ ሰዎች ጠቃ ሚ ኾኖ የሚገኝ ከኾነና ያን ታሪክ ደግሞ ከራሱ በቀር ሌላ ሰው የማያቀ ርበው እስከኾነ ድረስ ስለራሱ ዘርዝሮ ማስረዳቱ የሚያስመሰግን እንጂ የሚያስወቅስ አይደለም።

ሌሎችም የእግአብሐር ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት ስለራሳቸው ገለጻ ያደረጉ ስለኾነና በዚያም ያልተወቀሱበት ስለኾነ የነህምያም ስለራሱ አገ ላለጽ ከዚያ የተለየ ሊኾን አይችልም።

ለምሳሌ በኦሪት ዘኍልቍ ም.12 ቍ: 3 ላይ ነቢዩ ሙሴ፥ በትንቢት ዳንኤል ም.6 ቍ: 3 ላይ ነቢዩ ዳንኤል፥ ኹለተኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው መልእክትም ም. 11 ቍ :17 - 21 ሐዋርያው ጳውሎስ ስለራ ሳቸው ምስጋና መሰል ገለጻዎችን አድርገዋል። እነዚህም መጻሕፍት በተ ጻፉባቸው ወቅቶች የመንፈስ ቅዱስ መሪነት ያልተለየ መኾኑን ስለምና ምን የነህምያም አጻጻፍ ከነዚያ የተለየ አይደለም።



www.ethiopianorthodox.org

## መጽሐፈ አስቴር

ይህ መጽሐፍ 10 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፋፈለ ነው።

የመጀመሪያው ክፍል ም.1 እና ም.2 ሲኾን በውስጡም ንጉሥ አርጤክስስ ሚስቱን ፈትቶ አባትና እናት አልባ ኾና በአጎትዋ ልጅ በመርዶክዮስ አሳዳጊነት ያደገችውን አስቴር የተባለችውን አይሁዳዊት ምርኮኛ ንግሥት አድርጎ በመሾም ማግባቱን መርዶክዮስም በንጉሡ ላይ ታቅዶ የነበረውን የግድያ ሴራ ማጋለጡ ተዘርዝርዋል።

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 3 እስከ 5 ድረስ ሲኾን በውስጡም የሃማን ወደ ከፍተኛ የሹመት ደረጃ መድረስ፥ ሲገባና ሲወጣ መርዶክዮስ የማይሰግድለት መኾኑን በተረዳ ጊዜ ከቁጣው የተነሣ የአይሁድን ዘር በሙሉ በአንዲት ቀን ለማጥፋት ከንጉሡ ፈቃድ መቀበሉ ተገልጾአል።

ሦስተኛው ክፍል ደግሞ ከምዕራፍ 6 እስከ ምዕራፍ 10 ድረስ ሲኾን በአስቴር አማካይነት የሃማን ዕቅድ መሰናከሉና የአይሁድ ሕዝብ ከጥፋት መዳኑ፥ ከዚያም የአይሁድ ጠላቶች ኹሉ መደምሰሳቸው ተዘርዝርዋል።

ይህን መጽሐፍ የጻፈው በትክክል ባይታወቅም ኾኖም ግን ጸሐፊው መርዶክዮስ ነው የሚለው አባባል በብዙዎች ዘንድ የታመነበት ነው።

## ጥያቄና መልስ

89. መጽሐፈ አስቴር በእግዚአብሔር መሪነት ላለመጻፉ ማስረጃ የሚኾነው በመጽሐፉ ውስጥ አንድም ጊዜ የእግዚአብሔር ስም የሌለበት መኾኑ ነው የሚሉ አሉ።



በመጽሐፉ ውስጥ የጌታ ስም በግልጽ ባይኖርም እንኳ ድርጊቶቹ ኹሉ የእግዚአብሔር እጅ ያለባቸው መኾኑን ስለሚያመለክት በእግዚአብሔር እስትንፋስ ለመጻፉ አስተማማኝ ነው። የጽሑፉ አቀራረብ በችግር ላይ የወደቁትን ሕዝቦቹን እግዚአብሔር እንደሚያጸናቸውና ከችግር እንደሚያወጣቸው በግልጽ የሚያመለክት ነው፡ የመርዶክዮስ ለሃማን አለመስገድና ለአስቴርም ያስተላለፈው መልእክት የሚያመለክተው የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ በግዚአብሔር ደግነትና መግቦት ያምን የነበረ መኾኑን ነው።

አስቴር ወደንጉሥ ላለመቅረብ ፍራቻዋን በገለጸችለት ጊዜ በሰጣት መልስ "አንቺ፣ በንጉሥ ቤት ስለኾንሁ ከአይሁድ ኹሉ ይልቅ እድናለሁ ብለሽ በልብሽ አታስቢ። በዚህ ጊዜ ቸል ብትይ ዕረፍትና መዳን ለአይሁድ ከሌላ ስፍራ ይኾንላቸዋል፤ አንቺና ያባትሽ ቤት ግን ትጠፋላችሁ " በማለት የእግዚአብሔርን እርዳታ አመልክቶአታል። አስቴርም የሦስት ቀኖች ጾምና ጸሎትን ያወጀችው የእግዚአብሔርን ጸሎት ተቀባይነት ስላመነች ነው። (ም. 4 ቍ: 12 -16 )

ስለዚህ እንደ አጋጣሚ የእግዚአብሔር ስም ሳይጠራ ቢቀርም የእግዚአብሔር እርዳታዎች በሙላት ስለሚገኙበት መጽሐፉ ያለእግዚአብሔር እስትንፋስ ተጻፈ ከማለት ብንቆጠብ ይበጃል።

## መጽሐፈ ኢዮብ

ይህን መጽሐፍ የጻፈው ማን እንደኾነና በስንተኛው ዘመን እንደ ተጻፈ በትክክል አይታወቅም። የመጽሐፉን መጀመሪያና መጨረሻ ሙሴ እንዳዘጋጀው ይገመታል። የመጽሐፉም ዋና ታሪክ ምንም ዐይነት ችግር ቢደርስበት ጻድቁ ኢዮብ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት አለማጓደሉ ነው። መጽሐፉም አርባ ኹለት ምዕራፎች አሉት።



www.ethiopianorthodox.org

# ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

90. በመጽሐፈ ኢዮብ ም .1 ቊ: 6 እና ም. 2 ቊ: 1 ላይ እንደተገለጸው የእግዚአብሔር ልጆች ማለት ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም በመጡ ጊዜ ሰይጣንም እንዲሁ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም በመካከላቸው መጣ ይላል። በዚህ አባባሉ መጽሐፈ ኢዮብ ልብ ወለድ ታሪክ እንጂ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈ አለመኾኑ የሚታወቀው በሃይማኖት ሰዎች እምነት ሰይጣን በኀጢአቱ ምክንያት ከነበረው ሥልጣን ተሽሮ የተጣለ ከኾነ እንዴት አድርጎ ከቅዱሳን መላእክት ጋር ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ቻለ ብለው የሚጠይቁ ወይም የሚተቹ ወገኖች አሉ።

መላእክትንም ኾነ ሰይጣናትን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር በአንድ ቦታ ውሱን አይደለም።

እግዚአብሔር ውሱን አለመኾኑን ከሚያረጋግጡት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

"ሰው በስውር ቢሸሽግ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር" (ኤር. ም.23 ቊ:24 )

"በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን እነሆ ሰማይ፥ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም፤" (1ኛ ነገ. ም.8 ቊ:27 )

" እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ሰማይ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዐይነት ነው? የማርፍበትስ ስፍራ ምድር ነው? " (ኢሳ. ም.66 ቊ:1 )

"አቤቱ አንተ እነሆ የቀድሞውንና የኋላውን ዐወቅህ.... ከመንፈስህ ወዴት እኼዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደሰማይ ብወጣ፥ አንተ ከዚያ ነህ፤ ወደሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ፤ እንደንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ፥ እስከባሕር መጨረሻም ብበርር፥ በዚያ እጅህ ትመራኛለች፤ ቀኝህም ትይዘኛለች፤" (መዝ.139 ቊ.5 – 10)።



እግዚአብሔር ለቅዱሳን ወይም ለርኩሳን መናፍስት፥ ለደጋግ ወይም ደጋግ ላልኾኑ ሰዎች ውሱን የኾነ አካል ያለው መስሎ በሚገለጽበት ጊዜ አንዳንድ ኹናቴዎችን ለመግለጽ፥ ለማናገር፥ ለማስተማር ወይም ለማሳመን ሲል ነው እንጂ መለኮታዊ ክብሩስ እንደዚያ ውሱን ኾኖ አይደለም።

የኢዮብን ታማኝነት ለሌሎች ለማስረዳት ለቅዱሳንና ለርኩሳን መናፍስት መገለጥ ነበረበት። እንዲሁም በየዘመናቱ ለየልዩ ቦታዎች ለአዳም፥ ለኖኅ፥ ለአብርሃም፥ ለይስሐቅ፥ ለያዕቆብ፥ ለዮሴፍ፥ ለሙሴና ለሌሎችም ነቢያት እንደተገለጠው ኹሉ ለቃየን፥ ለአቢሜሌክ፥ ለፈርዖን፥ ለላባን፥ ለበልዓም፥ ለናቡከደነፆርና ለሌሎችም ተገልጿአል። ለደጋግዎቹ የሚገለጽላቸው መልካም ተስፋን ለመስጠት ሲኾን ደጋግዎች ላልኾኑት የሚገለጽላቸው ደግሞ በተቃራኒው ለውሳኔ ለቅጣት ወይም ደግሞ ለወደፊቱ ብሩህ ተስፋ የሌላቸው መኾኑን ለመግለጽ ነው።

በእነዚህም ከላይ በተዘረዘሩት ማስረጃዎች መሠረት ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔር ፊት እንደሚቆሙ ኹሉ ርኩሳን መናፍስትም በፊቱ የሚቆሙበት ጊዜ መኖሩንና ለደጋግ ሰዎችም እንደሚገለጠው ኹሉ ደጋግ ላልኾኑ ሰዎችም እንደሚገለጥ በመገንዘብ በዚህ ምክንያት መጽሐፈ ኢዮብ ልብወለድ ታሪክ ነው የሚለውን አባባል ከአስተሳሰባችን ማስወጣት ይኖርብናል።

91. በመጽሐፈ ኢዮብ ምዕራፍ ሦስት ላይ የታየው ኹናቴ ብስጭትን፥ ቁጣንና እርግማንን የሚያመለክት ሲኾን ለኢዮብ ከሚነገርለት ታጋሽነት እና ኹሉን ነገር ለእግዚአብሔር ፈቃድ መተው፥ ትሩፋቱና ጻድቅነቱ ጋር አብሮ የማይኼድ ተግባር ስለሚኾን እነዚህ የተጠቀሱት በጎ ተግባሮች አሉት ብሎ እርሱን በምሳሌነት መጥቀስ አግባብ አይደለም ብሎ የሚተች ይኖር ይኾናል።

አንድ ማስታወስ ያለብን ጉዳይ በምዕራፍ ሦስት የተጠቀሰውን ንግግር የተናገረው የምሥራቅ አገር ሰው መኾኑ ነው። በምሥራቃውያን ዘንድ



www.ethiopianorthodox.org

ድ ስለአንድ ኹናቴ ገለጻ ለማድረግ ማጋነን የተለመደ ባህል ነው። ስለዚህ ምንም እንኳን ችግሩን ሊቋቋሙት የሚችሉ ቢኾኑ የችግራቸውን መጠን ለመግለጽ አነጋገራቸውን በማጋነን ያቀርቡታል። ለምሳሌ በምዕራፍ 1 ቊ.21 ላይ ስለሀብቱ መጥፋትና ስለልጆቹ መሞት በተነገረው ጊዜ "ራቁቴን ከእናቴ ማሕፀን ወጥቻለሁ፣ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ፤ እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔርም ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይኹን፤" ያለውና በምዕራፍ 2 ቊ: 10 ላይ ሚስቱ ተስፋ የሚያስቆርጥ ንግግር በተናገረችው ጊዜ በሰጠው መልስ "አንቺ ከሰነፎች ሴቶች እንደ አንዲቱ ተናገርሽ፤ ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን፤ ክፉ ነገርንስ አንቀበልምን?" ያለው ኢዮብ ነው በምዕራፍ ሦስት ላይ የተወለደበትን ቀን የረገመው። የችግሩን መጠን በማጋነን መልክ ከማቅረቡ በቀር በችግሩ ምክንያት አንዳችም እግዚአብሔርን ቅር የሚያሰኝ ነገር አልተናገረም። ከኢዮብ ይልቅ ባነጋገራቸው እግዚአብሔርን ቅር ያሰኙት ሦስቱ የኢዮብ ወዳጆች በመኾናቸው ጌታ የሚከተለውን መመሪያ ሰጥቶአቸዋል።

"እግዚአብሔር ቴማናዊውን ኤልፋዝን እንደባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅንን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና ቁጣዬ በአንተና በኹለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነድዶአል። አሁን እንግዲህ ሰባት ወይፈኖችና ሰባት አውራ በጎች ይዛችሁ ወደባሪያዬ ወደ ኢዮብ ዘንድ ኺዱ፤ የሚቃጠልንም መሥዋዕት ስለ ራሳችሁ አሳርጉ፤ ባሪያዬም ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፤ እኔም እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደረግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ፤ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና" (ኢዮ. ም.42 ቊ:7 - 8 )

ኢዮብ እንደዚህ ተደርጎ በእግዚአብሔር ዘንድ የተመሰከረለት ጻድቅ እንጂ እግዚአብሔርን ቅር የሚያሰኝ ትዕግሥተ ቢስ ሰው አልነበረም።

አንድን ነገር በማጋነን አነጋገር ማቅረብ የተለመደ የምሥራቃውያን ባህል መኾኑን ለማረጋገጥ የሚከተለውን ተጨማሪ ማስረጃ እንመልከት።

"የተወለድሁባት ቀን የተረገመች ትኹን እናቴ እኔን የወለደችባት ቀን የተባረከች አትኹን። ወንድ ልጅ ተወልዶልሃል ብሎ ለአባቴ የም



ሥራች ነገሮ ደስ ያሰኘው ሰው የተረገመ ይኹን። ያም ሰው እግዚአብሔር ሳይጸጸት እንደገለበጣቸው ከተሞች ይሁን፤ በማለዳም ልቅሶን በቀትርም ጩኸትን ይስማ፤ እናቴ መቃብር ትኾነኝ ዘንድ ማሕፀንዋም ዘወትር ይዞኝ ያቆይ ዘንድ በማሕፀን ውስጥ አልገደለኝምና። ድካምንና ጣርን አይ ዘንድ ዘመኔም በእፍረት ታልቅ ዘንድ ስለ ምን ከማሕፀን ወጣሁ" (ኤር. ም.20 ቊ:14 -18 )

ይህንን የማጋነን ንግግር የተናገረው ነቢዩ ኤርምያስ ነው በዚሁ በትንቢተ ኤርምያስ ም.1 ቊ: 5 " በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፤ ከማሕፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፤ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ" ብሎ ፈጣሪ አምላክ የመሰከረለት።

በዚህም መሠረት በምዕራፍ ሦስት ላይ የተመለከተው የኢዮብ አነጋገር ከልማድና ከባህል ጋር የተያያዘ በመኾኑ ነው እንጂ ትዕግሥተ ቢስነት አይደለም።

92. በመጽሐፈ ኢዮብ ም.14 ቊ: 7 - 10 "ዛፍ ቢቈረጥ ደግሞ ያቈጠቍጥ ዘንድ ቅርንጫፉም እንዳያልቅ ተስፋ አለው። ሥሩም በምድር ውስጥ፥ ግንዱም በመሬት ውስጥ ቢሞት ከውሃ ሽታ የተነሣ ያቈጠቍጣል፤ እንደ አትክልት ቅርንጫፍ ያወጣል። ሰው ግን ይሞትና ይጋደማል፤ ሰውም ነፍሱን ይሰጣል፤ እርሱስ ወዴት አለ? በማለቱ ኢዮብ በሚመጣው ዓለም ሕይወት አያምንም፤ ወይም ተስፋ አያደርግም የሚል ሐሳብ ይሰነዘር ይኾናል።

ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ መሠረት ኢዮብ እንደዚያ በማለቱ የሚመጣውን ሕይወት ተስፋ አያደርግም ማለት ሳይኾን ኹሉም እንደሚያውቀው አንድ ሰው ከሞተ በኋላ እንደገና ተነሥቶ ከመሞቱ በፊት በዚህ ዓለም ላይ ያደርጋቸው የነበሩትን እንቅስቃሴዎች ኹሉ አያደርግም ለማለት ነው እንጂ በትንሣኤ ሙታን ረገድ ግን የእርሱን እምነት ለመገንዘብ የሚቀጥለውን ጥቅስ እንመልከት

"ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ።" (ኢዮ. ም. 19 ቊ:26 )



www.ethiopianorthodox.org

93. በመጽሐፈ ኢዮብ ም.38 ቁ: 1 -7 እንዲህ ይላል። "እግዚአብሔር በዐውሎ ነፋስ ውስጥ ኾኖ ለኢዮብ መለሰ፤ እንዲህም አለ፤ ያለ ዕውቀት በሚነገር ቃል ምክርን የሚያጨልም ይህ ማነው? እንግዲህ እንደሰው ወገብህን ታጠቅ፤ እጠይቅሃለሁ፤ አንተም ተናገረኝ። ምድርን በመሠረትሁ ጊዜ አንተ ወዴት ነበርህ? ታስተውል እንደ ኾንህ ተናገር። ብታውቅስ መስፈሪያዋን የወሰነ፥ በላይዋስ የመለኪያ ገመድ የዘረጋ ማነው? አጥቢያ ኮከቦች በአንድነት ሲዘምሩ፥ የእግዚአብሔር ልጆች ኹሉ እልል ሲሉ፥ መሠረቶችዋ በምን ላይ ተተክለው ነበር? የማዕዘንዋንስ ድንጋይ ያቆመ ማነው?"

ከላይ በተገለጸው አባባል የእግዚአብሔር ልጆች ማለት መላእክት ፍጥረቶች ኹሉ ከመፈጠራቸው በፊት ነበሩ ማለት ነውን? ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በኦሪት ዘፍጥረት ም.1 ቁ:1 መሠረት እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠረው ሰማይንና ምድርን ነው። የመላእክት መኖሪያቸው ሰማይ መኾኑ በማቴዎስ ወንጌል ም.22 ቁ:30 ላይ ተገልጿል። መሬት ለሰው መኖሪያ ኾና ከመዘጋጀትዋና ሰውም ከመፈጠሩ በፊት መላእክት ተፈጥረው ነበር፤ ምክንያቱም በመጀመሪያ ሰማይ ሲፈጠር የሰማይ ሠራዊትም አብረው ተፈጥረዋልና። (መዝ.33 ቁ:6 ) በኦሪት ዘፍጥረት ም.1 ቁ:2 መሠረት ምድር ባዶና ምንም ያልነበረባት ጨለማ የነበረች ኾና ብርሃን ተፈጥሮላትና ሣርና ቡቃያዎች እንድታበቅል የተደረገችው በሦስተኛው ቀን ወይም በሦስተኛው የፍጥረት ጊዜ ነው። እንግዲህ እንዲህ ከኾነ እግዚአብሔር ለኢዮብ የተናገረው ምድርን ከውሃ በመለየት መኖሪያ እንድትኾን ያዘጋጀበትን ጊዜ መኾን አለበት። ከፃክብትና የእግዚአብሔር መላእክት ሰማይ በተፈጠረበት ጊዜ የተፈጠሩ ስለኾኑ ሌሎቹን ፍጡሮች እግዚአብሔር ሲፈጥር ድንቅ የኾነ ሥራውን በመመልከት አድናቆታቸውን በመዝሙርና በእልልታ ገልጸዋል ማለት ነው።





አብዛኞዎቹ መዝሙሮች በዳዊት ስለተዘጋጁ፥ ስሙም የዳዊት መዝሙር በመባል ስለተለመደ መዝሙሮቹ ኹሉ በዳዊት የተጻፉ ይመስላል። ሌሎችም ጸሐፊዎ የጻፏአቸው መዝሙሮች አሉባቸው እንጂ መቶ ኀምሳዎቹም መዝሙሮች የዳዊት አይደሉም። የመዝሙሮቹ ብዛት መቶ ኀምሳ ሲኾን ከነዚህ የዳዊት መኾናቸው በግልጽ የተነገረላቸው ሰባ ሦስቱ ናቸው። በሌሎችም ስም የተነገሩ መዝሙሮች አሉ። ከነዚህም ለምሳሌ መዝሙር ሰባ ኹለት የሰሎሞን ሲኾን መዝሙር ዘጠና ደግሞ የሙሴ ነው።

መጽሐፈ መዝሙርን ባለበት ኹናቴ ያዘጋጀው ካህኑ ዕዝራ ነው።

መዝሙሮቹም እንደየጸሎተኛው ስሜት በተለያዩ ኹናቴዎች የተከፋፈሉ ናቸዉ መ ዝ ሙር ስድስት፥ ሠላሳ ኹለት፥ ኀምሳ አንድ፥ አንድ መቶ ኹለት፥ መቶ ሠላሳና መቶ አርባ ሦስት የንስሓና የኀጢአት ስርየት ጸሎት ናቸው። ከነዚሁም ጋር መዝሙሮች 38 እና ሰማንያ ስድስት ተመሳሳይ ናቸው።

ሌሎችም የተጨነቁ ሰዎች፥ ፈተና ያስነሱቸው፥ ኀዘን ያጠቃቸው፥ በመጨቄን፥ በመሳደድና በመዋረድ የተሰቃዩ ሰዎች የሚጸልዩአቸው መዝሙሮች፥ የፍርሐትና የፈተና ጊዜ መዝሙሮች፥ የምስጋና መዝሙሮች፥ እግዚአብሔርን የማክበር መዝሙሮች፥ የአምልኮ ቤትን የመናፈቅ መዝሙሮች፥ የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚገልጹ መዝሙሮች፤ ቃለ እግዚአብሔርን የማወቅ ጥቅም የሚገልጹ መዝሙሮች፥ ስለትንሣኤ ሙታንና ስለ መጨረሻው ፍርድ የሚመለከቱ መዝሙሮች፥ ስለክርስቶስና ስለክርስትና ዘመን የሚገልጹ የትንቢት መዝሙሮች፥ በተለየ ስለዳዊት ገለጻ የሚያደርጉ የታሪክ መዝሙሮች ይገኙባቸዋል።



www.ethiopianorthodox.org

94. በመዝሙር 19 ቍ:7 ላይ "የእግዚአበሔር ሕግ ፍጹም ነው ነፍስ
ይመልሳል" የሚል ሲኾን በሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ
ሰዎች ም.7 ቍ:6፥ ወደ ገላትያ ሰዎች ም.2 እና 3 የቀድሞው ሕግ
ደካማ እንደኾነና ጠቃሚ እንዳልኾነ ስለተገለጸ እነዚህ ኹለት አባባሎች
ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የጠቀሰው ለመድኀኒታችን ምሳሌነት የተደነ
ጉትን ለምሳሌ ስለኀጢአት ስርየት እንስሳትን ለመሥዋዕትነት ማቅረብ
የመሳሰሉትን እንጂ አጠቃላይ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ማለቱ አይ
ደለም። ይህም የሚኾንበት ምክንያት ለጌታ ምሳሌነት የተደነገጉት ሕግ
ጋት ጌታ ራሱ ከመጣ በኋላ አስፈላጊ አይደሉምና ነው። በዚህም መሠረ
ት ጥቅሶቹ ተቃራኒዎች አይደሉም።

95. በመዝሙር ውስጥ ልዩ ልዩ ቦታዎች ከሃይማኖታዊ ስሜት ጋር አብ
ሮ ሊኼድ የማይችልና ራሱ ጸሐፊው የጥላቻ፥ የበቀልና የቅናት ስሜቱን
የገለጸበትና የተራገመበት እንደመኾኑ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት
የተጻፈ ነው ለማለት ይቻላል ወይ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ይህ አስተያየት ከተሰጠባቸው ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙ
ባቸዋል።

"አቤቱ የሚበድሉኝን በድላቸው፤ የሚዋጉኝንም ተዋጋቸው። ጥሩ
ርና ጋሻ ያዝ፤ እኔንም ለመርዳት ተነሥ። ሰይፍህን ምዘዝ፤ የሚያሳድ
ዱኝንም መንገዳቸውን ዝጋ፤ ነፍሴን መድኀኒትሽ እኔ ነኝ በላት።
ነፍሴን የሚሹ ኹሉ ይፈሩ፤ ይጐስቀሉም፤ ክፋትን በእኔ ላይ የሚያስቡ
ይፈሩ፤ ወደ ኋላቸውም ይበሉ። በነፋስ ፊት እንዳለ ትቢያ ይኹኑ፤
የእግዚአብ ሔርም መልአክ ያስጨንቃቸው መንገዳቸው ዳጥና ጨለማ
ይኹን፤ የእ ግዚአብሐርም መልአክ ያሳድዳቸው። በከንቱ ያጠፉኝ
ዘንድ ወጥመዳ ቸውን ሸሽገውብኛልና፥ ነፍሴን በከንቱ አበሳጭተዋልና።
ያላወቁት ወጥ መድ ይምጣባቸው፤ የሸሸጉትም ወጥመድ ይያዛቸው፤
በዚህ ወጥመድ ውስጥ ይውደቁ።" (መዝ.35 ቍ:1 — 8 )



"ሞት ይምጣባቸው፤ በሕይወት ሳሉ ወደ ሲኦል ይውረዱ፤ ክፋት
በማደሪያቸውና በመካከላቸው ነውና።" (መዝ.55 ቍ:15 )

"በላዩም ኀጢአተኛን ሹም፤ ሰይጣንም በቀኙ ይቁም። በተምዋገ
ተም ጊዜ ተረትቶ ይውጣ፤ ጸሎቱም ኀጢአት ትኹንበት ዘመኖቹም
ጥቂት ይኹኑ፤ ሹመቱንም ሌላ ይውሰድ። ልጆቹም ድኻ አደግ ይኹኑ፤
ሚስቱም መበለት ትኹን። ልጆቹም ተናውጠው ይቅበዝበዙ፥ ይለም
ኑም፤ ከስፍራቸውም ይባረሩ። ባለዕዳም ያለውን ኹሉ ይበርብረው፤ እን
ግዶችም ድካሙን ኹሉ ይበዝብዙት። የሚያግዘውም አያግኝ፤ ለድኻ
አደግ ልጆቹም የሚራራ አይኑር። ልጆቹ ይጥፉ፤ በአንድ ትውልድ
ስሙ ይደምሰስ። የአባቶቹ ኀጢአት በእግዚአብሐር ፊት ትታሰብ፤ የእ
ናቱም ኀጢአት አትደምሰስ። በእግዚአብሔር ፊት ኹልጊዜ ይኑሩ፤
መታሰቢያቸው ከምድር ይጥፉ። ምሕረትን ያደርግ ዘንድ አላሰበምና
ችግረኛንና ምስኪንን፥ ልቡ የተሰበረውንም ሰው ይገድል ዘንድ አሳደደ።
መርገምን ወደደ፤ ወደ እርሱም መጣች፤ በረከትንም አልመረጠም፤ ከእ
ርሱም ራቀች። መርገምን እንደ ልብስ ለበሳት፤ እንደ ውሃም ወደ
አንጀቱ፥ እንደ ቅባትም ወደ አጥንቱ ገባች። እንደሚለብሰው ልብስ፥
ኹልጊዜም እንደሚታጠቀው ትጥቅ ይኹን።" (መዝ.109 ቍ: 6 - 19)
"ሕፃናትሽን ይዞ በዐለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው የተመሰገነ ነው።" (መዝ.
137 ቍ:9 )

በተራ ቍጥር 90 ላይ የተጠቀሰው የልማድና የባህል ጉዳይ እንደ
ተጠበቀ ኾኖ በመዝሙር ውስጥ በልዩ ልዩ ቦታዎች በእርግማን መልክ
የቀረቡት አነጋገሮች በእግዚአብሐርና በመሲሑ ጠላቶች ላይ የተነገረ
ትንቢትና በሰው ልጅ ጠላት በሰይጣን ላይ ነው እንጂ ዳዊትማ ለጠላቶቹ
ደግን እንጂ ክፉን የማይመልስ ሰው እንደነበረ በሕይወቱ ላይ ተነሥ
ተውበት የነበሩት የንጉሥ ሳኦልና የልጁ የአቤሴሎም ሞት የቱን ያኽል
እንዳሳዘነው ማስተዋል ብቻ በቂ ማስረጃ ነው። (2ኛ ሳሙ. ም.1 ቍ :
11 - 27፥ ም.18 ቍ:33 )

የተነገሩትም እርግማን መሰል ትንቢቶች እንዴት ተፈጻሚነትን እን
ዳገኙ በሐዋርያት ሥራ ም.1 ቍ: 15 - 20 እና ወደሮሜ ሰዎች በተላከ
ው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.11 ቍ: 9 - 10 ላይ ተገልጾአለ።



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ በመዝሙር ውስጥ የተነገሩት እርግማን መሰል አነጋገሮች ትን ቢትና በሰይጣን ላይ የተደረጉ እርግማኖች እንጂ ከጥላቻ፥ ከበቀልና ከቅናት ስሜት የመነጩ አለመኾናቸውን ተረድተን ከመሳሳት እንጠን ቀቅ።

96. በመዝሙር 45 ቍ: 2 ላይ "ውበትህ ከሰው ልጆች ይልቅ ያም ራል፤" ተብሎ ስለጌታችን የተገለጸ ሲኾን በትንቢተ ኢሳይያስ ም.53 ቍ: 2 ላይ ግን "መልክና ውበት የለውም፤ ባየነው ጊዜ እንወድደው ዘን ድ ደም ግባት የለውም" በመባሉ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።

ኹለቱም ጥቅሶች የተነገሩት ስለጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክር ስቶስ መኾኑ ግልጽ ነው።

በመዝሙር 45 ላይ እንደተገለጸው ኹሉ ጌታ መልከ ቀና የነበረ መኾኑ በታሪክ ጸሐፊዎች እንኳ የተረጋገጠ ነው።

በአይሁድ አገር ተጠባባቂ ገዥ የነበረ ፒሌንቱሎ የተባለ ሰው ለጢ ባርዮስ ቄሣር የጻፈውን ደብዳቤ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ኦርቶዶክስ ሃይ ማኖት በተሰኘው መጽሐፋቸው በገጽ 108 እና 109 ላይ ያቀረቡት አቀ ራረብ እንደሚከተለው ነው።

"ለጢባርዮስ ቄሣር ሰላም ለአንተ ይኹን ግርማዊነትህ ይፈልገው የነበረው መልስ ይኸውልህ፥ በእነዚህ ክፍለ ሀገሮች እጅግ የተለየ ሥል ጣን ያለው አንድ ሰው ታይቷል። ታላቁ ነቢይም ብለው ይጠሩታል ደቀ መዝሙሮቹም የእግዚአብሔር ልጅ እያሉ ይጠሩታል። ስሙ ኢየሱስ ነው። እንደ እውነቱ ከኾነ ቄሣር ሆይ ስለዚህ ስለ ክርስቶስ በየዕለቱ ተአ ምራታዊ ነገሮች ይሰማሉ። ሙታንን ያስነሣል፤ ማናቸውንም ደዌና ሕመ ም ይፈውሳል፤ እንዲሁም ጥልቅ በኾነ ትምህርቱ በሙሉ ኢየሩሳሌምን አስደንቋታል። አቋመ ሰውነቱ ግርማ ያለውና መልኩም አንጸባራቂ ጸጋ የተሞላበት በመኾኑ ማናቸውም የተመለከተው ሰው ኹሉ ይወደዋል ይፈ ራዋልም እንዳንዱም ቀላ ያለው መልኩና መኻል ለመኻል ተከፍሎ የሚ ታየው ጢሙ የሚሰጠው ውበት ፍጹም ግምት የሌለው ነው።



የፊቱ ቅርጽ፥መልአ ካዊ ዐይኖቹና የጥቁር ወርቃማ ጸጉሮቹም ኣወራረድ በሚሰጡት የተንጸባረቀ ውበት ማንም ሰው ቢኾን ለረዥም ጊዜ አትኩሮ ሊመለከተው አይችልም። እሱም የሚመስለው እናቱን ቢኾን እስዋም ደግሞ በዚህ ክፍለ ሀገር በማንም ላይ ያልታየ ውበትና የትሕትና መልክ ያላት ናት።"

የጌታ መልከ ቀናነት በዚህ ዓይነት የተገለጸ ሲኾን በትንቢተ ኢሳ ይያስ ም.53 ቍ: 2 ላይ "መልክና ውበት የለውም፤ ባየነው ጊዜ እንወደ ው ዘንድ ደም ግባት የለውም፤" ተብሎ መነገሩ ግን ጌታ መልከ እንደ ሌለው ሰው መቈጠሩንና መናቁን ለማመልከት ነው። ነቢዩ ሊገልጽ የፈለ ገው የእኛን አመለካከት እንጂ የጌታን እውነተኛ መልክ አይደለም። የጌ ታን ትክክለኛ መልክ ለማየት የሰው ልጅ ዐይኑ ታውሮበት ማለቱ ነው። ስለዚህም አገላለጹን በተቃራኒ ምሳሌዎች አቅርቦታል። ገለጻውንም ሲጀ ምር "የሰማነውን ማን አምኖአል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጾ አል?" በማለት ይጠይቃል። በዚህ ረገድ የእኛ ዕውቀትና የእኛ አመለካ ከት እውነተኛውን ሳይኾን እውነት ያልኾነውን ኹናቴ ለመኾኑ ነቢዩ በቍጥር 4 እና 5 ላይ የሰጠውን ገለጻ እንመልከት።

"በእውነት ደዌአችንን ተቀበለ ሕማማችንንም ተሸከሞአል፤ እኛ ግን እንደተመታ፥ በእግዚአብሔር እንደተቀሰፈ እንደተቸገረም ቈጠር ነው። እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቈሰለ፤ ስለበደላችን ደቀቀ፤ የደኅንነ ታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን።"

ስለዚህ በመዝሙር 45 እና በትንቢተ ኢሳይያስ ም.53 ላይ የቀ ረቡት የጌታ መልክ አገላለጽ በተለያየ ምክንያትና በተለያየ ትርጉም የቀ ረቡ ናቸው እንጂ እርስበርሳቸው የሚቃረኑ አባባሎች አይደሉም።

97. በመዝሙር 51፡ ቍ: 11 ላይ "ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ ላይ አት ውሰድብኝ" ያለ ኾኖ ሳለ በዮሐንስ ወንጌልም.7 ቍ: 39 ላይ ደግሞ ኢየ ሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበር" ስለሚል መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ከወረደበት ከበዐለ ኀምሳ በፊት ለማንም ያልተሰ ጠ ስለሚመስል ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።



www.ethiopianorthodox.org

መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ዘመናት ሁሉ የነበረ ለመኾኑ ምንም የሚ ያጠራጥር ነገር የለም። ቅዱሳን አባቶች ደጋግ ሰዎችና ነቢያት ወደፊት በሚመጣው በመሲሑ እንዲያምኑ መንፈስ ቅዱስ ያስተምራቸው ነበር። ለምሳሌ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ብሎአል። "እነርሱ ግን ዐመፁ፤ ቅዱስ መንፈሱንም አስመረሩ" (ኤሳ. ም.63 ቍ:10)

ሐዋርያው ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስ በዘመነ ኦሪት ነቢያትን ይረዳ እንደነበረ ሲያመለክት፥ "ማነኛውም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አል መጣም፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ" ብሏል። (2ኛ ጴጥ. ም.1 ቍ:21) የሐዋርያትን ሥራ ም. 2 የተመለከተ ሰው ሐዋርያው ዮሐንስ ምን ማለ ቱ እንደኾነ ሊገነዘብ ይችላል። የመጀመሪያዎቹ የክርስትና ሃይማኖት አስተማሪዎች ማለት የጌታ ደቀ መዛሙርት በተሰበሰቡበት በያንዳንዳ ቸው ላይ መንፈስ ቅዱስ ወርዶባቸው በሌላ ቋንቋ መናገራቸው ተገልጸ አል። መንፈስ ገና አልወረደም ነበር የተባለው ይህ ነው እንጂ በዘመነ ብሉይ መንፈስ ቅዱስ ለማንም አልተሰጠም ማለት አይደለም። ሐዋር ያትና የቤተ ክርስቲያን አባሎች ሁሉ መንፈስ ቅዱስ አብሮአቸው ያለ መኾኑ የተሰማቸውን ያኸል ግን የኦሪቱ ሰዎች አይሰማቸውም ነበር። (ዮሐ.ሥ. ም.10 ቍ:44 – 45 )

የኦሪቱና የሐዲሱ ሌላው ልዩነት ደግሞ በኦሪቱ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ማንም ሰው እንዳይጠቀምበት የታሸገ የጕድጓድ ውሃ ዓይነት ሲኾ ን የሐዲሱ ግን ሁሉም እንዲጠቀምበት የኾነ ፈሳሽ ውሃ ዓይነት ነው።

ሦስተኛው ልዩነት ደግሞ በኦሪት ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ይሰጡ የነበሩት ለተወሰኑ ሰዎች ለምሳሌ እንደነቢያትና የሃይማኖት አገልጋዮች ብቻ የነበረ ሲኾን በሐዲሱ ሥርዓት ግን ጌታ፥ ባሪያ፥ ወንድ ወይም ሴት ሳይለይ ለኹሉም ይሰጣል። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ "እግዚአብሔር ሰውን ከሰው እንደማያበላልጥና እንደማያዳላ አስተዋል ሁ" ያለው። (የሐ.ሥ. ም.10 ቍ:34 ) ይህም የኾነው አስቀድሞ በነቢዩ በኢዮኤል የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው።

"ከዚህም በኋላ እንዲህ ይኾናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ኹሉ ላይ አፈስሳለሁ፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፣ ሽማ



ግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፣ ጐበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፤ ደግ ሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስ ሳለሁ።" (ኢዩ ም.2 ቍ:28 – 29 )

38 በመዝሙር 76 ቍ: 10 ላይ "የሰው ቁጣ ያከብርሃል ካለ በኋላ በመልእክተ ያዕቆብ ም.1 ቍ: 20 ላይ "የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ክብ ር አይሠራም በማለቱ ሁለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ናቸው ይባል ይኾና ል።

በመጀመሪያ የተጠቀሰው ቁጣና በኹለተኛ የተጠቀሰው ቁጣ የተለያዩ ትርጉሞች አሉአቸው። የመጀመሪያው ትርጓሜ ጠላቶች በእ ግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ያላቸው ቁጣ ሲኾን እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ የበቀል እርምጃ በሚወስድበት ጊዜ ኀያልነቱንና ክብሩን የሚገልጽ ከመ ኾኑም በላይ በእግዚአብሔር በዎች ዘንድ የሚመሰገንበትና በጠላቶች ዘንድ ደግሞ የሚፈራበት በመኾኑ የሰው ቁጣ ያከብርሃል ተብሏል። ለዚ ህም አባባል የሚከተሉትን ሦስት ምሳሌዎች እንመልከት።

በኦሪት ዘጸአት ም.10 ቍ:28 ላይ ፈርዖን ሙሴ ከእኔ ዘንድ ኺድ፤ ፊቴን ባየህበት ቀን ትሞታለህና ፊቴን እንዳታይ ተጠንቀቅ" በማለት ከተ ቈጣው በኋላ ነው የግብጽ በኵር ሁሉ እንዲሞት የተደረገውና የግብጽ ሠራዊትም በባሕር ውስጥ ሰጥሞ እንዲሞት የተደረገው። ከዚያ ቀደም ብሎ በምዕራፍ 9 ቍ:13 - 16 እግዚአብሔር ለሙሴ መመሪያ ሲሰጠው እንዲህ ብሎታል። "ሙሴ ማልደህ ተነሣ፤ በፈርዖንም ፊት ቆመህ በለው የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እንዲያገለግሉኝ ሕዝ ቤን ልቀቅ። በምድር ሁሉ እንደ እኔ ያለ እንደሌለ ታውቅ ዘንድ በሰው ነትህ፥ በባሪያዎችህም፥ በሕዝብህም ላይ መቅሠፍቴን ሁሉ አሁን እል ካለሁ። አሁን እጄን ዘርግቼ አንተን ሕዝብህንም በቸነፈር በመታሁህ ነበር፤ አንተም ከምድር በጠፋህ ነበር፣ ነገር ግን ኀይሌን እገልጥብህ ዘን ነበር፤ አንተም ከምድር በጠፋህ ነበር፣ ነገር ግን ኀይሌን እገልጥብህ ዘን
ድ፥ ስሜም በምድር ሁሉ ላይ ይነገር ዘንድ ስለዚህ አስነሥቼሃለሁ።"

ኹለተኛው ምሳሌ ደግሞ በመጽሐፈ አስቴር መ.3 ላይ እንደተገ ለጸው ንጉሥ አርጤክስስ በሹመት ያከበረው ሃማ የተባለ ባለሥልጣን መርዶክዮስ በሚባል አንድ አይሁዳዊ ላይ ስለተቈጣ ብቻ የአይሁድ ሕዝብ በሙላ እንዲገደል ትእዛዝ ካስተላለፈ በኋላ እግዚአብሔር የመርዶ ክዮስንና የወገኖቹን ጸሎት ሰምቶ የታቀደው ጥፋት በአይሁድ ሕዝብ ላይ



www.ethiopianorthodox.org

ሳይኾን በሃማና በወገኖቹ ላይ እንደተፈጸመ ከምዕራፍ 7 እስከ 9 ድረ ተዘርዝሮ ይገኛል።

ሦስተኛ ምሳሌ በትንቢተ ኢሳይያስ ም.36 ላይ እንደተገለጸ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም በትዕቢት ተነሣሥቶ በይሁዳ ንጉሥ በሕዝ ያስና በሕዝቡ ላይ የቁጣና የንቀት ቃሉን ከመሰንዘሩም በላይ እግዚአ ሔርንም ስለተዳፈረ ውድቀቱ የተፋጠነበት መኾኑን በም.37 ላይ መ ልከት እንችላለን።

ኹለተኛው የቁጣ ትርጓሜ ማለት "የሰው ቁጣ የእግዚአብሔር ጽድቅ አይሠራም" የሚለው አንድ ሰው ኀጢአትን በመሥራቱ ምክ ያት ቢቈጣ ያ ቁጣው ኀጢአትን እንጂ ጽድቅን አያመጣለትም ማለት ነው። ለምሳሌ ጌታውን አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ በንስሓ የፈጣሪውን ይቅ ርታ በመለመን ፈንታ በራሱ ማለት በሠራው ኀጢአት በመቈጣት ራሱን የመግደል ድጋሚ ኀጢአት ሠራ እንጂ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አላ ኘም።

ስለዚህ ኹለቱ የቁጣ ዓይነቶች የተለያየ ትርጉም አላቸው እንጂ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

99. በመዝሙር 78 ቍ.65 ላይ "እግዚአብሔርም የወይን ስካር የተወ ው ኀያል ሰው ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፤" ይልና በመዝሙር 121 ቍ: 3 እና 4 ላይ ደግሞ "ጠባቂህ አይተኛም፤ እነሆ፥ እስራኤልን የሚ ጠብቅ አያንቀላፋም" በማለቱ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል።

ስለ እግዚአብሔር የሚነገሩት የሰው ልጅ የተፈጥሮ ጠባዮች በሰው ልጅ አስተሳሰብና አሠራር ላይ የሚታዩ ኹናቴዎች ናቸው እንጂ እነዚያ ኹናቴዎች የእግዚአብሔር ጠባዮች ኾነው አይደለም። ለምሳሌ አንድ ሰው በእንቅልፍ ላይ ከኾነ ወይም ከስካር ሳይነቃ ባለበት ጊዜ ከኹነ ማናቸውንም ድርጊት አያደርግም፤ ምክንያቱም ገና ከእንቅልፉ ወይም ከስካሩ አልነቃምና ሲነቃ ግን ማድረግ የሚያስፈልገውን ጉዳይ ያደር ጋል። ለምሳሌ ከላይ በመዝሙር 78 ቍ:65 ላይ የተጠቀሰውን አባባል ኋላ በኋላ በቍ :66 ላይ "ጠላቶቹንም በኋላቸው መታ፤ የዘላለምንም



ኀሣር ሰጣቸው" ይላል። እንግዲህ እግዚአብሔር በትዕግሥት ኀጢአ ተኞችን ሳይቀጣ ለብዙ ጊዜ መቈየቱን እንደ እንቅልፍ የቈጠረው በመኾ ኑ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። አይተኛም፤ አያንቀላፋም የተባለው ግን ትክ ክለኛ አባባል ነው።

ለመጀመሪያው ጥቅስ ተጨማሪ አባባሎችን ለመጥቀስ ለምሳሌ አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ በሚቈጣበት ጊዜ በቀልን ይበቀላል ወይም ይቀጣል። ይህ የሰው ልጅ ጠባይ ስለኾነ ስለ እግዚአብሔርም በሰው ላይ መቈጣት በሚነገርበት ጊዜ ያንን ሰው እግዚአብሔር የሚቀጣው መኾኑን ያመለክተናል።

በኦሪት ዘኍልቍ ም.12 ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር በአ ሮንና በማርያም ላይ በተቆጣ ጊዜ ማርያምን በለምጽ በሽታ ቀጥቶአታ ል።

አንድ ሰው ደግሞ በሠራው ሥራ የተጸጸተ እንደኾነ ያንን የተጸ ጸተበትን ሥራ ለማረም የሚችል ከኾነ ያርመዋል እንጂ አይተወውም። ምንም እንኳን እግዚአብሔር የማይጸጸት መኾኑ ቢታወቅ በሰው ልጆች ቋንቋ ተጸጸተ በሚባልበት ጊዜ በዚያ ጉዳይ ላይ አንድ ነገር እንደ ሚያደ ርግ ለመገንዘብ ይቻላል።

በኦሪት ዘፍጥረት ም.6 ቍ:6 ላይ እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ ካለ በኋላ በምዕራፍ 7 የሰውን ልጅ በጥፋት ውሃ እንዳጠፋው ተገልጾአል።

በመጀመሪያው መጽሐፈ ሳሙኤል ም.15 ቍ: 11 ላይ እግዚአ ብሔር ሳኦልን በማንገሤ ተጸጸትሁ ካለ በኋላ ሳኦልን ሽሮ በምትኩ ዳዊት እንዲነግሥ አደረገ።

በትንቢት ዮናስ ም .3 ቍ: 10 ላይ "እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳ ቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ፤ እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘን ድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገባቸውም" ይላል። በዚህ ጉዳይ ላይ ሌሎችም ብዙ ተመሳሳይ ኹናቴዎችን መጥቀስ ይቻላል። ነገር ግን ለማስረጃነት ያኽል ለጊዜው እነዚህ የተጠቀሱት ጥቅሶች በቂ ናቸው።



www.ethiopianorthodox.org

100. በመዝሙር 78 ቍ:67 — 68 ሌሎች ሳይጠቀሱ ዮሴፍ ኤፍሬም ይሁዳ የተጠቀሱት ለምንድነው ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል።

የዮሴፍን ድንኳን ተዋት ያለው ዮሴፍ አባቱንና ወንድሞቹ ከችግር ያዳነ በመኾኑ በእርሱ ስም የዓሥራ ሁለቱን ነገድ ድንኳን ለማ ት ፈልጎ ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ በመጀመሪያው ዜና መዋዕ ም.5 ቍ: 1 — 2 መሠረት ብኵርና ለዮሴፍ ነገድ የተሰጠ በመኾ ለሌሎቹም ተጠሪ ለመኾን በቅቷል። ኤፍሬም ደግሞ ምንም እንኳ ከዮሴ ፍ ልጆች መካከል የምናሴ ታናሽ ቢኾን በኦሪት ዘፍጥረት ም.48 ቍ.14 — 19 እና በትንቢተ ኤርምያስ ም.31 ቍ:9 መሠረት ብኵ ርናው የኤፍሬም መኾኑ ስለታወቀ የእርሱ ስም ተጠቅሶአል። ይሁን እንጂ ምንም በኵር ቢኾን ለንጉሥነት ዙፋን የተመረጠው የይሁዳ ነገድ በመኾኑ በመዝ.78 ቍ: 67 — 68 ላይ "የኤፍሬምን ወገን አልመረጠ ውም፤ የይሁዳን ወገን ግን መረጠ" ተብሏል።

101. በመዝሙር 82 ቍ: 6 ላይ "እኔ ግን አማልክት ናችሁ ኹላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ አልሁ" ካለ በኋላ በትንቢተ ኢሳይያስ ም.45 ቍ:5 ደግሞ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔም ሌላ ማንም የለም፤ ከእኔም በቀር አምላክ የለም" በሚሉት ጥቅሶች መካከል ልዩነት የተፈጠረ ይመስል ይኾናል።

በመጀመሪያው ጥቅስ ላይ ተናጋሪው የዳኞች ዳኛ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር አማልክት ናችሁ ያላቸው የሕዝብ መሪዎችን፥ ፈራ ጆችን ወይም ዳኞችን ነው። በዚሁ መዝሙር በቍጥር 1 ና 2 ላይ ብን መለከት "እግዚአብሔር በአማልክት ማኅበር ቆመ፤ በአማልክትም መካ ከል ይፈርዳል። እስከ መቼ ሐሰትን ትፈርዳላችሁ? እስከ መቼስ ለኀጢ አተኞች ፊት ታደላላችሁ?" ብሎ የወቀሳ ጥያቄ ከጠየቀና በሚሰጡትም ቅንነት የጐደለው ፍርድ ከወቀሳቸው በኋላ ነው አማልክት ናችሁ ያላ ቸው። ይህም ማለት በሕዝብ ላይ ፍርድን እንድትፈርዱ ሥልጣን የሰጠ ኋችሁ እኔን ወክላችሁ በመኾኑ የአምላክን ፍርድ የምትፈርዱ አማል ክት ናችሁ እየተባለ ለምን ትክክለኛ ፍርድ አትፈርዱም ብሎ ሊወቅ ሳቸው የፈለገ መኾኑን ከማመልከቱ በቀር ከዚያ የተለየ ትርጉም እንደሌ ለው ግልጽ ነው።



ለዚህም አባባል ማስረጃ ይኾኑ ዘንድ የሚከተሉትን ጥቅሶች እን መልከት።

"እግዚአብሔርም ሙሴን አለው እይ፥ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድ ርጌሀለሁ።" (ዘጸ. ም.7 ቍ:1 )

"በፍርድ አድልዎ አታድርጉ፤ ታላቁን እንደምትሰሙ ታናሹንም እንዲሁ ስሙ፤ ፍርድ ለእግዚአብሔር ነውና።" (ዘዳ. ም.1 ቍ:17 )

"ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አትፈርዱምና፥ እርሱም በፍርድ ነገር ከእናንተ ጋር ነውና፥ የምታደርጉትን ተመልከቱ።" (2 ዜ.መ. ም.19 ቍ:6 )

102. በመዝሙር 145 ቍ : 13 ላይ "መንግሥትህ የዘላለም መንግሥት ናት፤ ግዛትህም ለልጅ ልጅ ነው፤" ካለ በኋላ በመጀመሪያይቱ የሐዋር ያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ም.15 ቍ: 24 እና 28 ላይ "በኋላም መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአብ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ኹሉና ሥልጣንን ኹሉ፥ ኀይልንም በሻረ ጊዜ ፍጻሜ ይኾ ናል.... ኹሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ኹሉ በኹሉ ይኾን ዘን ድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ኹሉን ላስገዛለት ይገዛል" በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ከመምሰላቸውም በላይ አብ ከወልድ የበለጠ ሥልጣን ያለ ው ይመስል ይኾናል።

ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የክርስቶስን መንግሥት በሦስት ዓይነት ያቀርቡታል።

የመጀመሪያው:- ክርስቶስ አምላክ ስለኾነ መለኮታዊ ገዢነቱን የሚ መለከት እንደመኾኑ ይህ ገዢነት ወይም ንጉሥነት ዘላለም ከእርሱ ጋር የሚኖር እንጂ ለማንም ታልፎ የማይሰጥ ንጉሥነት ነው። የእግዚአብሔር ወልድን ዘላለማዊ ንግሥ በሚመለከት ወደ ዕብራውያን በተላከው መል እክቱ ም.1 ቍ: 8 ላይ እንዲህ ተብሏል " አምላክ ሆይ ዙፋንህ እስከ ዘላ ለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግሥትህም በትር የቅንነት በትር ነው።"



www.ethiopianorthodox.org

በትንቢተ ኢሳይያስ ም.44 ቍ:6 ላይ "የእስራኤል ንጉሥ እ ዚአብሔር፥ የሚቤዠም የሠራዊት ጌታ እንዲህ ይላል እ ኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፤ ከእኔ ሌላ አምላክ የለም" ተብሎ የተገለጸውን አባባ በራዕየ ዮሐንስ ም.22 ቍ:12 እና 13 ላይ ሲደግመው እንዲህ ብሏ "እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለያንዳንዱም እንደሥራው መጠን እከፍል ዘ ድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ፤ አልፋና ኦሜጋ፥ ፊተኛውና ኋኋኛው፥ መጀ ሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። " ይህ ነው መለኮታዊ ንጉሥነቱን የሚ መለከተው።

ኹለተኛው ዐይነት ንጉሥነት ሥጋን የለበሰ የእግዚአብሔር ልጅ ኾኖ በተቤዠው ሕዝቡ ላይ ያለው እልቅናና ጌትነት እንደመኾኑ ይህም ዘላለማዊ ንግሥ እንጂ ለማንም ታልፎ የማይሰጥ ንጉሥነት ነው።

ይህን በሚመለከት ሐዋርያው ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ ም.7 ቍ: 16 እና 17 ላይ እንዲህ ብሏል:- "ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሙም፤ ፀሐ ይም፥ ትኩሳትም ኹሉ ከቶ አይወርድባቸውም፤ በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይኾናልና፤ እግዚአብሔርም እንባዎችን ኹሉ ከዐይናቸ ው ያብሳል።"

በምዕራፍ 22 ቍ: 3 ላይ "ከእንግዲህ ወዲህ መርገም ከቶ አይኾ ንም። የእግዚአብሔርና የበጉም ዙፋን በእርስዋ ውስጥ ይኾናል፤ ባርያዎቹም ያመልኩታል፤ ፊቱንም ያያሉ፤ ስሙም በግንባሮቻቸው ይኾናል" ብሏል።

ሦስተኛው ዐይነት ንግሥ በፈቃዱ ለሰው ቤዛ ለመኾን ራሱን በአ ህያ ላይ እስከማስቀመጥ ድረስ ለፈጸመው ትሕትና ያገኘው ሥልጣን ነው። "ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው ሥልጣን ኹሉ በሰማ ይና በምድር ተሰጠኝ።" (ማቴ. ም.28 ቍ:18)

እንግዲህ ይህ ሥልጣን የሰውን ልጆች ለመቤዠት የነበረው ሥል ጣን እንደመኾኑና ቤዛ የመኾኑና የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነት ነጻ የማ ውጣቱ ጉዳይ እስካለቀ ድረስ ያን ሥልጣን ማቈየት አስፈላጊ ባለመኾኑ ያንን ሥልጣን ነው የሚያስረክበው። ከአብ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለው መለኮታዊ ሥልጣኑ ግን ለማንም ታልፎ የማይሰጥ ዘላለማዊ ሥልጣን



ው። ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው በመኾኑ በፍጹም ሰውነቱ ሥልጣኑን እግዚአብሔር ሰጠ ተባለ።

ሌላው በአንደኛ ቆሮንቶስ ም.15 ቍ: 28 ላይ "ኹሉ ከተገዛለት ኋላ ግን እግዚአብሔር ኹሉ በኹሉ ይኾን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ኹሉን ላስገዛለት ይገዛል፤" የሚለው ደግሞ መድኀኒታችን ከሦስቱ አካላት አንዱ በመኾን የሰውን ልጅ ለማዳን የወሰደውን የመሲህነት ኀላ ፊነት እንዳስረከበ ኹሉ በዚሁ የሰውን ልጅ ለማዳን ሲል በለበሰው ሥጋ ታዛዥ ለመኾን የፈቀደ መኾኑን ሲያመለክት ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊ ልጵስዩስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. 2 ቍ: 6 - 8 እንዲህ ብሏል እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከ ልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፤ ነገር ግን የባርያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ኾኖ ራሱን ባዶ አደረገ፤ በምስሉም እንደሰ ው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፤ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት ታዛዥ ኾነ።"

ይህም ማለት ጌታ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው የባሕርይ አም ላክ ኾኖ ሳለ ለሰው ልጅ ደኅንነት ሲል ለክብሩና ለጌትነቱ የማይገባውን የባርያውን ሥጋ ለብሶ በዚያው በለበሰው ሥጋ ሕማምና ሞትን መቀ በሉንና እንደ ሰው መታዘዝን ሲፈጽም ተቀዳሚ የሌለኝ ቃለ እግዚ አብሔር በመኾኔ ይህን አላደርግም አላለም ማለት ነው። (ጥያቄና መልስ ቍ:104፥ 112 እና በኹለተኛው መጽሐፍ ቍ: 8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥ 57፥ 61፥ 63፥ 72፥ 74፥75፥84፥89፥91፥92፥93፥102፥ ይመለከቷል።

## መጽሐፈ ምሳሌ

ይህ መጽሐፍ ሠላሳ አንድ ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በአምስት ክፍ ሎች ይከፋፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 9 ድረስ ሲኾን በውስጡም ስለጥበብ ገለጻ የተደረገበትና ጥበብንም መማር እንደሚጠቅ ምና አለመማር እንደሚጐዳ ተነግሮአል። (ምዕራፍ 8 ቍ:22 )



www.ethiopianorthodox.org

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 10 እስከ ምዕራፍ 22 ሲኾን በ ስጡም በእግዚአብሔር ፈቃድ እያንዳንዱ መስመር ልብን ለማደስ፥ ጠ ይን ለማረም፥ አስተሳሰብን ለማጐልመስና ተግባርን ሥነ ሥርዓት ለማ ያዝ ትምህርቶችን የሚሰጡ የተለያዩ ምሳሌዎችን የያዘ ነው።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 22 ቍ: 17 እስከ ምዕራፍ 24 ድረ ሲኾን በውስጡም በቀላል የስብከት መንገድ ጥበብን ለመማር፥ ትእ ዞች፥ ምክሮችና መመሪያዎች ቀርበዋል።

አራተኛው ክፍል ከምዕራፍ 25 እስከ ምዕራፍ 29 ድረስ ሲኾ ይህ ክፍል "እነዚህም ደግሞ የይሁዳ ንጉሥ የሕዝቅያስ ሰዎች የቀዳ አቸው የሰሎሞን ምሳሌዎች ናቸው" በማለት ይጀምራል። ይህም የሚ መለከተው በዘመኑ ከነበሩ ነቢያት አንዱ አማካይነት በንጉሥ ሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት የሰሎሞን ጽሑፎች የተሰበሰቡ መኾናቸውን ነው።

አምስተኛው ክፍል ምዕራፍ 30 እና 31 ሲኾን የመጀመሪያው የ ቄ ልጅ አጉር ለኢትኤልና ለኡካል የተናገራቸው ነገሮችና ኹለተኛው ደግሞ እናቱ ያስተማረችው የንጉሥ ልሙኤል ቃል ነው።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

103 በመጽሐፈ ምሳሌ ም.2 ቍ: 20 - 22 በደጋግ ሰዎች መንገድ ኺድ፤ የጻድቃንን አካኼድ ጠብቅ፤ ቀጥተኞች በምድር ይቀመጣሉና፤ ፍጹማንም ይኖሩባታል። ክፉዎች ግን ከምድር ይጠፋሉ፤ ሕግ ተላላ ፊዎች ከእርስዋ ይነጠቃሉ" ተብሏል።

ብዙ ክፉዎችና ሕግ ተላላፊዎች ሰዎች የዚህ ዓለም ኑሮአቸው ተሳክቶላቸው በዚህች ምድር ላይ ረጅም ዕድሜ ይኖራሉ። በአንጻሩ ደግ ሞ ብዙ ደጋግ ሰዎች በዚህ ዓለም የድኽነት ኑሮ የሚኖሩ ከመኾናቸውም በላይ በዚህች ምድር ላይ አጭር ዕድሜ ብቻ የሚኖሩ ጥቂቶች አይደ ሉም።



እንደዚህ ከኾነ ታዲያ በዚህች ምድር የሚኖሩት ደጋጎች ናቸው፤ ክፉዎች ግን ከዚህ ምድር ይነጠቃሉ የተባለው እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ምድር የተባለችው የትኛዋ ናት? መኖርስ የተባለው ለስንት ዘመን ነው?

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በማቴዎስ ወንጌል ም.5 ቍ: 5 ላይ "የዋሆች ምድርን ስለሚወርሱ ደስ ይበላቸው" ብሎ መድኀኒታችን የገለጸው ገለጻ ተመሳሳይነት ስላለው ትክ ብሎ መመልከቱ ይጠቅማል። እንዲሁም በመዝሙር 37 ቍ:11፥ 29፥ 34 ላይ የተነገሩትን ተመሳሳይ አባባሎች ይመለከቷል።

ማነኛውም ሰው ደግም ኾነ ክፉ በዚህ ዓለም ላይ የሚኖርባቸው ዓመቶች ውሱኖች መኾናቸው የታወቀ ነው። ስለዚህ በመጽሐፈ ምሳሌ ላይ የተነገረው የመኖር ትርጉም ይህ እኛ የምናውቀው የዚህ ዓለም መኖር ሊኾን አይችልም። በማቴዎስ ወንጌል ም.5 ቍ: 5 ላይና በመዝሙር 37 ቍ: 11፥ 29፥ 34 የተገለጹትን አባባሎች መሠረት በማድረግ ከትንሣኤ ሙታን በኋላ የጻድቃን መኖሪያቸው ሰማይ ሳይኾን ምድር ነች የሚሉ ወገኖች አሉ። ይህችውም ምድር በኹለተኛይቱ የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት ም.3 ቍ: 13 እና በራእየ ዮሐንስ ም. 21 ቍ:1 መሠረት አሁን ያለችው ምድር ከጠፋች በኋላ የምትለወጠው አዲስ ምድር ነች ይላሉ።

የቅዱሳት መጻሕፍትንና የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ትምህርት መሠረት በማድረግ ከትንሣኤ ሙታን በኋላ የጻድቃን መኖሪያቸው ሰማይ እንጂ ምድር አለመኾንዋ የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ነው። ይህንን አባባል ከሚደግፉት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

"ይህ እንደ ድንኳን ጊዜያዊ የኾነው ሥጋችን ሲፈርስ በሰው እጅ ሳይኾን በእግዚአብሔር እጅ የተሠራ ዘላለማዊ መኖሪያ በሰማይ እንዳለን እናውቃለን" (2ኛ ቆሮ.5:1)



www.ethiopianorthodox.org

"እግዚአብሔር ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አስነሥቶ በሰማያዊ ሥፍራ አብሮ አስቀምጦናል" (ኤፌ. ም.2 ቍ: 6 )

"ወንጌል ከተሰበከላችሁ ከመጀመሪያው ጊዜ አንሥቶ በሰማይ የተዘጋጀላችሁን ተስፋ በመጠባበቅ ላይ እንዳላችሁ እናውቃለን" (ቆላ. ም.1 ቍ:5 )

እንዲሁም ለዕብራውያን በተላከው መልእክት የአቤል፥ የሔኖክ፥ የአብርሃምና የሣራ ታሪክ ከተጠቃቀሰ በኋላ እንደመጻተኛ ተቈጥረው "ያንን የመጡበትን አገር አስበው ቢኾኑኖሮ ሊመለሱ በቻሉ ነበር፤ አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊውን አገር ይናፍቃሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ በእነርሱ አያፍርም፤ ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና" ተብሏል። (ዕብ. ም.11 ቍ:15 - 16)

"ያልፋል ወይም ይጠፋል የማይባል ነውርና ነቀፋ የሌለበት የዘላለም ሕይወት ለእናንተ በሰማይ ተዘግጅቶ ይቆያችኋል።" (1ኛ ጴጥ. ም.1 ቍ: 4 )

ቀደም ተብሎ በቀረቡት ጥቅሶች ውስጥ ምድር የሚለው ቃል መንግሥተ ሰማያት ለማለት የተነገረ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው እንጂ ቃል በቃል መወሰድ ያለበት አይደለም። ለምሳሌ በራእየ ዮሐንስ ም.21 ቍ: 2 እና 10 ላይ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ስትወርድ አየሁ በሚልበት ጊዜ ስለቤተክርስቲያን የተናገረው ምሳሌያዊ አነጋገር ነው እንጂ በቀጥታ ኢየሩሳሌም ማለት አይደለም። እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል ም.15 ቍ: 1 እና 5 ላይ "እኔ የወይን ግንድ ነኝ፤ አትክልተኛውም አባቴ ነው፤ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ ሲል ምሳሌያዊ አነጋገር ነው እንጂ ቃል በቃል መወሰድ ያለበት አይደለም። በሌላ ጊዜ ደግሞ "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱትና እኔ በ3 ቀኖች እሠራዋለሁ" ሲል በቀጥታ ቤተ መቅደሱን ማለቱ አለመኾኑ ግልጽ ነው። (ዮሐ. ም.2 ቍ:19 ) ሌሎችም ብዙ ተመሳሳይ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል።

ስለዚህ ምድርን ይወርሳሉ ሲል መንግሥተ ሰማይን ይወርሳሉ ማለቱ እንጂ በቀጥታ ምድርን ማለቱ አይደለም።



መንግሥተ ሰማይም ምድር የተባለችበት ምክንያት ይህች ምድር አልፋ ለመኖሪያነት በምድር የምትተካ ስለኾነ፥ ወራሾችዋም የምድር ጻድቃን ስለኾኑና የምትወረሰውም በምድር በተሠራው በጎ ተግባር ስለ ኾነ ነው።

ወደ መጀመሪያው ጥያቄ እንመለስና ደጋግ ሰዎች በምድር ይኖራሉ ክፉዎች ግን በሞት ይነጠቃሉ የተባሉት በምድር ምሳሌነት ስለተነገረላት ስለመንግሥተ ሰማያት ነው እንጂ ስለዚህች እኛ ስለምናውቃት ምድር ማለት አይደለምና አለመኾንዋን ዐውቀን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

104. ጥበብ " ከኹሉ በፊት ጌታ ፈጠረኝ " አለች (ምሳ. ም.8 ቍ.22)

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው የመጀመሪያ መልእክቱ ም.1 ቍ: 24 ላይ በገለጸው መሠረት ጥበብ የተባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲኾን እንዴት ጌታ ፈጠረኝ አለ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ያለ እርሱ ፈጣሪነት ምንም የተፈጠረ ነገር የሌለና አብን በመልክ የሚመስለውና በክብር የሚተካከለው ወልድ የተፈጠረ ነው ማለት ድፍረትም ኀጢአትም ነው።

ተፈጠረ የተባለው ግን የሰውን ዘር ለማዳን በለበሰው ሥጋ ነው። በዚህም መሠረት ነው "ጥበብ ለራስዋ ቤት ሠራች" ተብሎ የተገለጸው (ምሳ. ም.9 ቍ: 1 )። የኑሲሱ ቅዱስ ጎርጎዮስም "ክርስቶስ ማለት ፈጣሪና ፍጡር በአንድ አካልና አንድ ባሕርይ አንድ የኾነ ማለት ነው" ብሏል። (ሃይ. አበ. ገጽ 119 )

የቂሣርያው ቅዱስ ባስልዮስ ከፍጥረቱ አስቀድሞ እግዚአብሔር ፈጠረኝ ያለውን የሰሎሞንን ቃል ሲተረጕም እንዲህ ብሏል "የጽድቅ የሕይወት ጐዳና እኔ ነኝ፤ በእኔ ካልኾነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ ማንም ማን የለም አለ፤ የእግዚአብሔር አብ ቃል ይህ አንድ ገገር ነው፤ ዳግመኛም እርሱ በነቢይ ቃል እግዚአብሔር ፈጠረኝ ለፍጥረቱ ተቀዳሚ አደረገኝ አለ። ሰው ከእግዚአብሔር ተወለደ ተብሎ እንደተጻፈ ሰው እንደ



www.ethiopianorthodox.org

መኾኑ በሥጋ ስለተወለደው ልደት ይህን ተናገረ።" (ሃይ. አበ. ገ 107)

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ይህን ጥቅስ በተረጐመበት ድርሰቱ እንዲ ብሏል "በምሥጢር አንድ ሲኾን በንባብ እርስ በርሱ የተለያየ ይ ስላል፤ እግ ዚአብሔር ከፍጥረት ኹሉ አስቀድሞ ፈጠረኝ፤ ዓለም ከ ብታም ኹሉ ሳይፈጠር አስቀድሞ ተወለድኩ። የተወለደ ሲኾን እንደም ተፈጠረ? ካልተፈጠረስ ባልተወለደም ነበር፤ ቀዳማዊ አምላክ ሲኾ እንደምን ተፈጠረ ይባላል? እኛም የምንወልደውን የምንፈጥረ አይደለም እኛ ፍጡራን ነን የምንወልዳቸው እነርሱም ደግመኛ፤ ፍጠ ራን ናቸው። ያልተፈጠረ እግዚአብሔር ቃል ግን መወለዱ ከፍጡ አባት አይደለም፤ እርሱም የተፈጠረ አይደለም፤ ከተፈጠረስ በኋላ ከተ ወለደ ቀድሞ እንደምን ተፈጠረ? ዳግመኛ ከተፈጠረ በኋላ እንደም ተወለደ? ተፈጠረ መባሉ ሰው በመኾኑ ምሥጢር ይፈጸማል፤ ስለዚህም አስቀድሞ ደኃራዊ ልደቱን ተናገረ፤ ቅሩባን የሚኾኑ ሰዎችን ልቡና ደስ ሊያሰኝ ወዶ፤ ስለዚህም የሰውነቱን ነገር ይናገር ጀመር። (ሃይ አበ ገጽ 186 )

ቅዱስ ቄርሎስ የመጽሐፈ ምሳሌን ም.8 ቍ:22 ጥቅስ በተረጐ መበት ድርሰቱ እንዲህ ብሏል።

"ጥበብ ለራሷ ቤት ሠራች በሰባት አዕማድም አጸናችው ተብሎ እንደተጻፈ፤ ጥበብም የተባለ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ እግዚ አብሔር ቃል ነው፤ የሠራችው ቤት የተባለም ከድንግል ፈጥሮ የተዋ ሐደው ሥጋው ነው ይህም በነፍስ በሥጋ ፍጹም የሚኾን ትስብእቱ ነው፤ ሰባቱ አዕማድም ሰባቱ የሐዲስ ሕግ መጻሕፍት ናቸው፤ ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ክርስቶስ አምላክ ሰው በመባል ሳይለይ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ኾነ።" (ሃይ አበ. ገጽ 260 )

"ጥበብ ተፈጠረ ይኸውም ቃል ነው። ከፍጥረት አስቀድሞ የነበረ ቃል ሥጋ በመኾኑ ይህ አምላክ ያለ መለወጥ ከንጽሕት ድንግል ከነሣው ሥጋ ጋር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ኾኖአልና የእግዚአብሔር ፍጥረቶ ች ከጥበብ ተገኝተው በባሕርያቸው ጸንተው ይኖራሉና አሁን ግን ጥበብ ከፍጥረት አስቀድሞ የነበርኩ እኔን ጌታ ፈጠረኝ አለች። የተገኘ ባሕ



ርይን ገንዘብ ልታደርግ ሰው ኾነች አብ ፈጠረኝ አላለችም፤ ጌታ ፈጠ ረኝ አለች እንጂ። ወልድ አባቱን ብቻ ለማመልከት በሚናገርበት ጊዜ አባቴ ይለዋል፤ ተገኘ ባሕርይን ገንዘብ በማድረጉ እርሱ ራሱ ሰው ኾነ፤ ስለዚህም ጌታ ፈጠረኝ አለ፤ አባቴ ፈጠረኝ አላለም።" (ሃይ. አበ. ገጽ 298 )

በሌላ በኩል ደግሞ ወልድ የእግዚአብሔር ጥበቡ ሲኾን የእግዚ አብሔር ጥበብ ዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር አለ እንጂ የተፈጠረ ሊኾን አይችልም። በዚህም መሠረት ፈጠረ የተባለው ቃል በሌሎች ደግሞ ወለ ደ ወይም ገንዘብ አደረገ ተብሎ ተተርጕሟል።

የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ቴዎዶስዮስ ይህን ጥቅስ ሲተረጉም እንዲህ ብሏል "ጠቢብ ሰሎሞን እግዚአብሔር ቃል ያለወ ንድ ዘር ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋ አየ፤ ወልድ ሰው ከመኾኑ አስቀድሞ አንድ እንደ ኾነ ሰው ከኾነ በኋላም ከሥጋ ጋር አንድ አካል በመኾን እርሱ አንድ እንዲኾን ባየ ጊዜ ስለዚህ ሰሎሞን ይህ ቅዱ ስ ሥጋ እንደተናገረ አድርጎ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ አስቀድሞ የነበረ ልኾን አደረገኝ አለ ብሎ ተናገር፤ በብዙ አንቀጽ ጥበብ ተብሎ የተነ ገረለት አካላዊ ቃል የተዋሐደው ይህ ሥጋ ነውና" (ሃይ. አበ. ገጽ 349) (ጥያቄና መልስ ቍ.102፥ 112፥ እና 2ኛ መጽሐፍ ቍ: 8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥ 57፥ 61፥ 63፥ 72፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥ 102፥ ይመለከቷል።

105. በመጽሐፈ ምሳሌ ም.26 ቍ: 4 ላይ "ለሞኝ ሰው እንደ ሞኝነቱ መልስ አትስጠው፣ አንተም ደግሞ እንደ እርሱ እንዳትኾን" ካለ በኋላ በቍጥር 5 ላይ ደግሞ :- "ብልህ የኾነ እንዳይመስለው ለሞኝ ሰው እን ደሞኝነቱ መልስ ስጠው፤" በማለቱ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል።

የመጀመሪያው አባባል የሚያመለክተው ሞኝ ሰው ከሞኝነቱ የተነሣ ለሰሚው የማያስደስት ንግግርን ሊናገር ስለሚችል የእርሱን አነጋገር ተከ ትሎ በዚያው ዓይነት መልስ መስጠት ከሞኙ ሰው አለመሻል ስለሚኾን መልስ አለመስጠቱ ይመረጣል ማለት ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ኹለተኛው አባባል ደግሞ አንድ ሞኝ ሰው ያዋቂ አነጋገር የተናገ መስሎት አንድ ዐይነት ትችት በሚያደርግበት ጊዜ መልስ ሳይሰጠወ ዝም ከተባለ ከእርሱ እኩል ዐዋቂ ያለ ስለማይመስለውና ራሱን ስለሚ ያታልል መልስ ሊሰጠው ይገባል ማለት ነው።

በዚህም መሠረት ኹለቱ አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይ ደሉም።

## መጽሐፈ መክብብ

ይህ መጽሐፍ ዐሥራ ኹለት ምዕራፎችን የያዘ ኾኖ ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር ተመሳሳይ ነው። ምንም እንኳ ንጉሥ ሰሎሞን እንደጻፈው ቢነገር የሌሎች ጸሐፊዎችም እጅ እንዳለበት ይገመታል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

106. በመጽሐፈ መክብብ ም.3 ቍ: 19 - 21 ‹ሰው ልጆችና የእነስሳ ዕድል ፈንታ አንድ ነው፣ ድርሻቸውም ትክክል ነው፤ አንዱ እንደሚ ሞት ሌላውም እንዲሁ ይሞታል፤ የኹሉም እስትንፋስ አንድ ነው፤ ኹሉም ከንቱ ነውና ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም። ኹሉ ወደ አንድ ቦታ ይኼዳል፤ ኹሉ ከአፈር ነው፤ ኹሉም ወደ አፈር ይመለሳል። የሰ ው ልጆች ነፍስ ወደ ላይ እንደምትወጣ የእንስሳም ነፍስ ወደ ታች ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማን ነው?" ካለ በኋላ በምዕራፍ 12 ቍ: 7 ላይ "አፈረም ወደነበረበት ምድር ሳይመለስ፥ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ" በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።

በምዕራፍ 3 ቍ.19 – 21 ከተዘረዘረው አባባል በፊት ከቍጥር 16 ጀምረን የተመለከትን እንደኾነ :- "እኔ ግን አሁን የማስተውለው ከፀ ሐይ በታች በሕግ ቦታ ወንጀል በጻድቅ ቦታ ኀጢአተኛ አለ፤..... የሰው ልጆችም እንዲህ የሚያደርጉት እግዚአብሔር ምንነታቸውን ሊያሳያ



ውና አንዱ በሌላው ላይ የሚፈጽመው አድራጎት ከአውሬ ያልተሻለ መኾኑን ሊገልጽላቸው እንደኾነ አሰብሁ፤" የሚል በመኾኑ ከቍጥር ሥራ ዘጠኝ እስከ ኻያ አንድ ድረስ የተዘረዘረው ጥቅስ የሚያመለክተው ሰው ልጆች በሚፈጽሙአቸው ክፉ ድርጊቶች ከአውሬ የማይሻሉ መኾ ቸውን ለመግለጽ ነው እንጂ የመጽሐፈ መክብብ ጸሐፊ በኦሪት ዘፍ ረት ም.2 ቍ: 7 መሠረት እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር የሕይወት እስ ትንፋስ እፍ ያለበት መኾኑንና የእንስሳት ነፍሳቸው ግን ደማቸው መኾኑ ኦሪት ዘሌዋውያን ም.17 ቍ: 10 - 11 ላይ የተገለጹትን የማያውቅ ኾኖ አይደለም። ስለዚህም ነው ሥጋችን ወደ ተፈጠረበት ወደ ምድር እንደሚመለስና ነፍሳችን ደግሞ ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር እንደ ሚመለስ በም.12 ቍ: 7 ላይ የገለጸው። ሥጋችንን አፈር ያለበትንም ምክንያት ለመረዳት ወደ ኦሪት ዘፍጥረት ም.2 ቍ: 7 እና ም.3 ቍ.19 የተመለከትን እንደኾነ እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር አበጅቶ የሕይወት እስትንፋስ እፍ በማለት ካከበረው በኋላ ኀጢአት በመሥራቱ ሲረግመው አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ የሚል ኾኖ እናገኘዋለን።

ሰው ከሞተ በኋላ በሥጋው ላይ የሚደርሰው መፍረስና መበስበስ ከእንስሳት ሥጋ ጋር ተመሳሳይ ስለኾነ ሊያወዳድረው ችሏል። በምዕራፍ 3 ቍ: 21 ላይ "የሰው ልጆች ነፍስ ወደላይ እንደምትወጣ፥ የእንስሳም ነፍስ ወደ ታች ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማነው?" የሚ ለው ይህንን ኹናቴ የሚያውቁ ብዙ አይደሉም ለማለት ነው። በተመ ሳሳይ አነጋገር ነቢዩ ኢሳይያስ "የሰማነውን ነገር ማን አመነን? የእግዚአ ብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠ?" ብሏል። (ኢሳ.ም.53 ቍ:1)

ሰው ከሞተ በኋላ ዳግመኛ ወደዚህ ዓለም ተመልሶ እንደ ቀድሞው የማይኖር መኾኑ ሌላው ከእንስሳት ጋር የተመሳሰለበት ጉዳይ ነው።

107. በመጽሐፈ መክብብ ም.11 ቍ: 1 ላይ "እንጀራህን በውሃ ላይ ጣለው፤ ከብዙ ቀኖች በኋላ ታገኘዋለህና" የሚል ሲኾን በማቴዎስ ወን ጌል ም.6 ቍ: 11 እና በሉቃስ ወንጌል ም.11 ቍ: 3 ደግሞ ጌታ የዕለት እንጀራችንን ስጠን ብለን እንድንጸልይ አስተምሮናል

በአንድ በኩል ያለንን እንጀራ በውሃ ላይ እንድንጥለውና ከብዙ ቀኖች በኋላ የሚመለስልን በመኾኑ እንድንጠባበቅ የተነገረን ሲኾን በሌላ



www.ethiopianorthodox.org

በኲል ደግሞ በየዕለቱ እንጀራ እንዲሰጠን እግዚአብሔርን እንድንለም የተነገረን እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚነገሩት ልዩ ልዩ አነጋገሮች ኹ ቸውም ቃል በቃል መወሰድ ያለባቸው ሳይኾኑ ብዙ ምሳሌያዊ አነጋገ ች ይገኙባቸዋል።

ይህ በመጽሐፈ መክብብ የተነገረው ጥቅስ የሚያስተምረን ቸ ነትን፥ ርኅራኄንና እንግዳ ተቀባይነትን ነው። እነዚህንም ድርጊቶች ስ ደርግ ዋጋችንን እንደምናገኝ ተስፋ ይሰጠናል። የዚሁ መጽሐፍ ጸሐ ነው በሌላ ቦታ የሚቀጥለውን አባባል ያለው። "ከእንጀራው ለድኻ ሰ ቷልና ርኅሩኅ ሰው የተባረከ ይኾናል።" (ምሳ. ም.22 ቍ:9 )

ጌታም እነዚህን አባባሎች በመደገፍ እንዲህ ብሏል "ግብዣ ባ ረግህ ጊዜ ድኾችንና ጐንድሾችን፥ ጸንካሶችንም፥ ዕውሮችንም ጥራ የሚመልሱት ብድራት የላቸውምና ብፁዕ ትኾናለህ፤ በጻድቃን ትንሣ ይመለስልሃልና።" (ሉቃ. ም.14 ቍ:13 — 14 )

የዕለት ምግባችንን ስጠን ብለን እንድንጸልይ ጌታ ስላስተማረ ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በኹለት ዐይነት አተረጓጐም ይለ ያያሉ።

የመጀመሪያዎቹ ወገኖች የዕለት ምግባችንን ስጠን ብለን ዛሬ የምንጸልየው ስለሰማያዊ ምግባችን ማለት የመንግሥተ ሰማዩ ዕድል ፈን ታችን በየዕለቱ እያደገ እንዲኼድ ነው እንጂ ምድራዊው ምግብማ አስ ቀድሞ የተሰጠን በመኾኑ ስለዚያ መጸለይ አስፈላጊ አይደለም ይላሉ።

ሌሎች ወገኖች ደግሞ ይህ ጸሎት ስለዓለማዊ ምግባችን የእግዚአ ብሔርን በረከት መለመን መኾኑን አምነው የቀዱሳት መጻሕፍትን ማስረ ጃዎች ያቀርባሉ።

ለምሳሌ በኦሪት ዘፍጥረት ም.28 ቍ: 20 ላይ ያዕቆብ ስዕለቱን ከተሳለባቸው ጉዳዮች አንዱ እግዚአብሔር የሚበላውን እንጀራ ይሰጠው ዘንድ ነው።



ንጉሥ ሰሎሞን በምሳሌ መጽሐፉ ም.30 ቍ: 8 ላይ "ከንቱነትንና ሐሰተኛነትን ከእኔ አርቃቸው፤ ድኽነትንና ባለጸግነትን አትስጠኝ፤ ነገር ግን የሚያስፈልገኝን እንጀራ ስጠኝ" ብሏል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በመጀመሪያ ወደ ጢሞቴዎስ በላከው መልእክቱ ም. 6 ቍ: 7 - 8 ላይ "ወደዚህ ዓለም ምንም ይዘን አልመ ጣንም፤ ከዚህም ዓለም ይዘነው የምንኼድ ምንም ነገር የለም፤ የምንበላ ውንና የምንለብሰውን ካገኘን ይበቃናል" ብሏል።

አሁን እነግዲህ በዚህም ሆነ በዚያ እንጀራህን በውሃ ላይ ጣለው ያለው ሰሎሞን እንጀራ ስጠኝ ብሎ ሲጸልይ እናገኘዋለን። እንዲሁም የዕለት እንጀራችንን ስጠን ብለን እንድንጸልይ ያስተማረን ጌታ ደግሞ በዚህ ዓለም ሳይኾን በወዲያኛው ዓለም ዋጋችንን እንደምናገኝ ተስፋ በመስጠት ምጽዋት እንድንመጸወት ያስተምረናል።

ስለዚህ በውሃ ላይ እንጀራን መጣል ማለት ለውለታችን መልስ ሳንጠብቅ መመጽወት ወይም መቸር ማለት በመኾኑና ፈጣሪ አምላክን ለምነን በእርሱ ፈቃድ ከምናገኘው እንጀራ ደግሞ ለድኾች መመጽወት ይገባናል ማለት ነው እንጂ ኹለቱ አባባሎች ግን እርስ በርሳቸው የሚቃ ረኑ አይደሉም።

## መጽሐፈ መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን

ይህ መጽሐፍ በስምንት ምዕራፎች የተከፋፈለና ሰሎሞን የጻፈው ኾኖ እንደሌሎቹ መጻሕፍት ኹሉ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈ መኾኑን ቤተ ክርስቲያን ታምናለች። በኹለት እጮኛዎች ወይም በባልና በሚስት መካከል የሚደረገው የፍቅር አገላለጽ ምሳሌነቱ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን የፍቅር መጠን እንዲያውም ለቤተ ክርስቲያን ሲል ሕይወቱን አሳልፎ እስከመስጠት ድረስ ያለውን ፍቅር የሚያሳይ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

## ጥያቄና መልስ

108. በመጽሐፈ መኃልይ ውስጥ የተዘረዘረው የወንድና የሴት የፍ
አገላለጽ ሰሎሞን ከብዙ ሴቶች ጋር የዝሙት ግንኙነት ስለነበረው ያ
ስሜቱን የገለጸበት አነጋገር ነው እንጂ ያንን መጽሐፍ በቃለ እግዚአ
ሔር ስም ከሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ጋር አብሮ ማቅረ
ተገቢ አይደለም ብለው የሚተቹ ወገኖች ይኖሩ ይኾናል።

ይህ መጽሐፍ እንደሌሎቹ መጻሕፍት ኹሉ በመንፈስ ቅዱ
መሪነት የተጻፈ መኾኑን ቤተ ክርስቲያን የምታምነውና የምታስተምረ
ትምህርት ነው።

በኹለት እጮኛዎች ወይም በባልና በሚስት መካከል የሚደረገ
የፍቅር አገላለጽ ምሳሌነቱ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያ
ውን የፍቅር መጠን እንዲያውም ለቤተ ክርስቲያን ሲል ሕይወቱን አሳል
ፎ እስከመስጠት ድረስ ያለውን ፍቅር የሚያሳይ ነው።

ብዙዎቹ የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች በየጊዜው በወንድና
በሴት ማለት በባልና በሚስት እንዲሁም በሙሽራና በሙሽሪት በማስመ
ሰል ተጠቅመዋል። ለዚህም የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

ልቤ መልካም ነገርን አፈለቀ፤ እኔ ሥራዬን ለንጉሥ እነግራለሁ፤
አንደበቴ እንደ ፈጣን ጸሐፊ ብዕር ነው። ውበትህ ከሰው ልጆች ይልቅ
ያምራል፤ ሞገስ በከንፈሮችህ ፈሰሰ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ለዘላለም
ባረከህ፤ ኀያል ሆይ፥ በቁንጅናህና በውበትህ ሰይፍህን በወገብህ ታጠ
ቅ።" (መዝ.45 ቍ:1 – 3 )

"የምድር ባለጠጎች አሕዛብ በፊትሽ ይማለላሉ። ለሐሴቦን ንጉሥ
ልጅ ኹሉ ክብርዋ ነው፤ ልብስዋ የወርቅ ማጐናጸፊያ ነው" (መዝ.45
ቍ.12 – 13 )



"አንቺ ያልወለድሽ መካን ሆይ፥ ዘምሪ፤ አንቺ ያላማጥሽ ሆይ፥
እልል በዪ፤ ጩኺም፤ ባል ካላት ይልቅ ፈት የኾነቺቱ ልጆች በዝተዋ
ልና ይላል እግዚአብሔር።" (ኢሳ. ም.54 ቍ:1 )

በትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 16 ላይ በእግዚአብሔርና በእስ
ራኤል ሕዝብ መካከል ያለው ግንኙነት እንዴት በባልና በሚስት እንደ
ሚመሰልና ሚስቲቱ ደግሞ ለባልዋ ታማኝ ሳትኾን እንደቀረች በዝርዝር
ይገልጻል።

"ልጆቼ ሆይ ምንም እንኳ እናታችሁ ከእንግዲህ ወዲህ ሚስቴ
ባትሆንም እኔም የእርስዋ ባል ባልሆንም "እባክሽ ግመንዘርሽንና መሴሰ
ባትሆንም እኔም የእርስዋ ባል ባልሆንም "እባክሽ ማመንዘርሽንና መሴሰ
ንሽን ተይ" ብላችሁ ምከሩአት። ባትመለስ ግን እንደተወለደችበት ቀን
እርቃንዋን አስቀራታለሁ፤ እንደ ደረቀ ባዶ ምድር አደርጋታለሁ፤
በውሃ ጥማትም ትሞታለች። ሐፍረተቢስ ከሆነች ዘማዊት ሴት የተወለዱ
ስለኾኑ ለልጆችዋም አልራራላቸውም። እርስዋ ራስዋ "ወደ ውሽሞቼ
እሄዳለሁ፤ እነርሱ ምግብና ውሃ ከሱፍና ከቀጭን ሐር የተሠራ ልብስ፥
የወይራ ዘይትና የወይን ጠጅ ይሰጡኛል" ብላለች።

ስለዚህ መንገድዋን በእሾኽ እዘጋዋለሁ፤ መውጫ በር እንዳታገ
ኝም ዙሪያውን በግንብ አጥራለሁ። ውሽሞችዋን ለማግኘት ትሮጣለች፤
ነገር ግን ልትደርስባቸው አትችልም፤ በብርቱ ትፈልጋቸዋለች፤ ነገር
ግን አታገኛቸውም፤ ከዚህ በኋላ "ከአሁኑ ኑሮዬ ይልቅ የድሮው ይሻለ
ኛል፤ ስለዚህ ወደቀድሞው ባሌ እኼዳለሁ ትላለች።" (ሆሴ. ም.2
ቍ:27 )

"ዮሐንስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ ማንም ሰው እግዚአብሔር ካልሰ
ጠው በቀር ምንም ነገር ሊኖረው አይችልም፤ ከእርሱ በፊት ተልኬ
አለሁ እንጂ እኔ መሲሕ አይደለሁም ብዬ እንደነገርሁአችሁ እናንተ
ራሳችሁ ምስክሮቼ ናችሁ። ሙሽሪት ያለችው ሰው ሙሽራ ነው የሙ
ሽራው ሚዜ ግን ከሙሽራው አጠገብ ቆሞ የሙሽራውን ድምፅ በመ
ስማት ይደሰታል፤ ስለዚህ የእኔም ደስታ አሁን ፍጹም ኾኖአል" (ዮሐ.
ም.3 ቍ:27 – 29 )



www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.5 ቍ: 31 እና 32 ላይ "ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱ ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ ይህ ምሥጢር ታላ ነው፤" ካለ በኋላ :- "እኔ ግን ይህንን የምለው ስለ ክርስቶስና ስለቤተክ ስቲያን ነው" በማለት የባልና የሚስት አንድነትና ፍቅር የክርስቶስና የ ተክርስቲያን ግንኙነት ምሳሌ መኾኑን አመልክቶናል።

በእነዚህም ከላይ በተገለጹት ምሳሌዎች መሠረት የመኃልየ መ ልይ መጽሐፍ አገላለጽ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለ የግ ኙነት ምሳሌ እንጂ ሌላ ዐይነት ትርጕም እንዳለው ኾኖ መወሰድ የለበት ም።

## ትንቢተ ኢሳይያስ

ይህ መጽሐፍ በ66 ምዕራፎች የተከፋፈለ ኾኖ ልዩ ልዩ ዜናዎችና ትንቢቶች ተነግረው ብዙዎቹም ትንቢቶች በየጊዜአቸው ተፈጽመዋል። ለእስራኤል ልጆች ብዙ ማስጠንቀቂያዎች ተሰጥተዋል። በተለየ ግን ስለ መድኀኒታችን ሰው መኾንና ሕማማችንን መቀበል ግልጽ የኾኑ ትንቢ ቶችን በመናገሩ ወንጌላዊው ነቢይ ተብሎ እስከ መጠራት በቅቶአል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

109. በትንቢተ ኢሳይያስ ም.1 ቍ: 15 - 16 ላይ "እጆቻችሁን ወደ እኔ ብትዘረጉ ዐይኔን ከእናንተ እሰውራለሁ፤ የቱንም ያኽል ጸሎት ብታ በዙ አልሰማችሁም፤ ይልቁንስ ታጥባችሁ ንጹሕ ኹኑ፤ ክፉ ሥራችሁን ኹሉ ከፊቴ አስወግዱ፤ በደል መፈጸማችሁንም ተዉ" የሚለው አባባል በትንቢተ ዘካርያስ ም.3 ቍ: 12 -13 "ስለዚህም እግዚአብሔር ወደ ሰሜን ኺጂ ለእስራኤል እንድነግራት ያዘዘኝ ይህ ነው፤ እምነት የማይጣ ልብሽ እስራኤል ሆይ ወደ እኔ ተመለሺ፤ እኔ ምሕረቴ የበዛ ስለኾንሁ አልቈጣም፤ በአንቺ ላይ የምቈጣው ለዘላለም አይደለም። አንቺ በደለኛ መኾንሽንና አምላክሽ በኾነው በእግዚአብሔር ላይ ማመፅሽን ብቻ እመ



ኚ፤ ከባዕዳን አማልክት ጋር በየለምለሙ ዛፎች ሥር የገለሙት ርኵሰት መፈጸምሽንና ለሕጌም ያለመታዘዝሽን ተናዘዢ፤ ይህን የተናገርሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ" ከሚለው ጋር እንዴት ሊታረቅ ይችላል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ም.7 ቍ: 21 ላይ በማያሻማ ቋንቋ "በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚፈጽ ም ነው እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ኹሉ መንግሥተ ሰማያት የሚ ገባ አይደለም" ብሏል። በትንቢተ ኢሳይያስ ላይ የተጠቀሰው ጥቅስ በማ ቴዎስ ወንጌል ከተጠቀሰው ጥቅስ ጋር ተመሳሳይ ነው እንጂ በትንቢተ ዘካርያስ ከተጠቀሰው ጥቅስ ጋር የሚቃረን አይደለም።

ለምሳሌ አንድ ሰው ሀብታም ለመኾን ብዙ ቢመኝ ነገር ግን ሀብታም ለመኾን የሚያበቃውን ጥረት ባያደርግ በምኞቱ ብቻ ሀብታም ለመኾን ይችላልን? በዚሁም ዐይነት አንድ ሰው ኃጢአት መሥራቱን እየቀጠለ እባክህ አምላክ ሆይ ይቅር በለኝ ቢል ይቅርታ ሊያገኝ ይች ላልን። ወይስ ደግሞ አንድ ሰው በጭቃማ መሬት ላይ ተራምዶ እግሩን ከታጠበ በኋላ ተመልሶ በጭቃው ላይ ቢራመድ ተመልሶ በጭቃ መለወ ሱ ይቀራልን?

እንግዲህ በንስሓ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ከለመኑ በኋላ ተመልሶ ኀጢአት ቢሠሩ ንስሓ መግባቱ ምንም ጥቅም የለውም ለማለት ነው እን ጂ ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ኾነው አይደለም።

ለዚህ አባባል ግልጽ ማስረጃ የኾነውን የሚቀጥለውን ጥቅስ እንመ ልከት።

"ክፉ ሰው ከሠራው ኀጢአት ኹሉ ተመልሶ ትእዛዞቼን ኹሉ ቢጠ ብቅ፥ እውነትንና ፍርድን ቢሠራ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም፤ የሠራው በደል ኹሉ አይታሰብበትም፤ በሠራው በጎ ሥራ ሕያው ኾኖ ይኖራል።....

ነገር ግን ደግ ሰው በጎ ሥራ መሥራቱን ትቶ ክፉ ሰው የሚሠራቸ ውን የርኵሰት ሥራዎች ኹሉ ቢሠራ በሕይወት የሚኖር ይመስላችኋ



www.ethiopianorthodox.org

ልን? ያደረጋቸው በጎ ሥራዎች አይታሰቡለትም፤ ባለመታመኑና ኀጢ ተኛ በመኾኑ ይሞታል (ሕዝ. ም.18 ቊ: 21፥ 22፥ 24)

ንስሓ መግባትና የእግዚአብሔርን ይቅርታ መለመን ደግሞ ዳ መኛ የቀድሞውን ኀጢአት ላለመሥራት መወሰን ነው እንጂ ኀጢአት መሥራትን ሳያቆሙ የእግዚአብሔርን ይቅርታ መለመን ማለት አይደ ለም።

በዚህም መሠረት በትንቢተ ኢሳይያስ ም.1 ቊ:15 ላይ የተጠ ቀሰው ጥቅስ ኀጢአት መሥራታችሁን ሳታቆሙ የምትለምኑት ይቅርታ ተስሚነት የለውም ማለት ሲኾን በትንቢተ ዘካርያስ ም.3 ቊ: 12 - 13 የተነገረው ደግሞ ኀጢአት መሥራትን አቁሞ ስላለፈው ኀጢአት ይቅር ታ ቢለምኑ እግዚአብሔር ይቅርታ የሚያደርግ መኾኑን ለመግለጽ ነውና ኹለቱ አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

110. በትንቢተ ኢሳይያስ ም. 7 ቊ: 14 ላይ "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምል ክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳ ለች፤ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች፤" ተብሎ ስለጌታ ልደት የተ ነገረውን ትንቢት የክርስትና ጠላቶች የመድኅኒታችንን ያለወንድ ዘር መወለድ ታሪክ ዋጋ እንዳይኖረው ለማድረግ ሲሉ የሚያቀርቡት ትችት የሚከተለው ነው።

በዕብራይስጡ ቋንቋ "አልማ" የሚለው ቃል ወጣት ሴት ልጅ ማለት ስለኾነ ይህቺ ወጣት ድንግል ልትኾን ወይም ድንግል ላትኾን ማለት ባል ያገባች ወይም ባል ያላገባች ልትኾን ስለምትችል በጥቅሱ ላይ የተመለከተው ድንግልናን አያመለክትም በማለት ይከራከራሉ።

በጥቅሱ ላይ የተመለከተው "አልማ" የሚለው ቃል በመጽሐፈ ምሳሌ ም.30 ቊ: 18 እና 19 ላይ ከተነገረው ጋር ተመሳሳይ ነውና ድን ግልና ማለት ለመኾኑ ምንም ማስረጃ የለም ይላሉ።

የመጽሐፈ ምሳሌውም አባባል እንደሚከተለው ነው። "ከአስተሳሰቤ በላይ የኾኑ ሦስት ነገሮች አሉ፤ በውኑ ላስተውላቸው የማልችል አራት ናቸው፤ እነርሱም በ ሰማይ ላይ የንስር መንገድ፥ በቋጥኝ ላይ የእባብ



መንገድ፥ በውቅያኖስ መካከል የመርከብ መንገድ፥ ከወጣት ሴት ጋር የወንድ መንገድ።"

በዕብራይስጡ ቋንቋ "አልማ" የሚለው ቃል ወጣት ሴት ወይም ድንግል ተብሎ ሊተረጐም የሚችል በመኾኑ ብቻ የጉዳዩ አመጣጥ እን ኳ ድንግልናን የሚያመለክት ቢኾን ስለድንግል የተነገረውን ባል ስላገባች ሴት እንደተነገረ አድርጎ ማቅረብ አግባብ አይደለም።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በዕብራይስጡ ቋንቋ "አልማ" የሚለ ው ቃል የተነገረላቸውና ደናግል ልጃገረዶች የነበሩ ለመኾናቸው የሚከ ተ ሉትን ማስረጃዎች እንመልከት።

በኦሪት ዘፍጥረት ም.24 ቊ: 43 - 44 "እነሆ እኔ በውሃው ምንጭ አጠገብ ቆሜአለሁ፤ ውሃ ልትቀዳ ለምትመጣውም ድንግል ጥቂት ውሃ ከእንስራሽ አጠጪኝ ስላት እርስዋም አንተ ጠጣ፤ ደግሞም ለግመሎችህ እቀዳለሁ የምትለኝ እግዚአብሔር ለጌታዬ ልጅ ያዘጋጃት ሚስት እርስዋ ትኹን" በሚለው ጥቅስ ውስጥ ድንግል ተብሎ የተተረጐመው በመጀመ ሪያው ቋንቋ በዕብራይስጡ በትንቢተ ኢሳይያስ ም.7 ቊ: 14 ላይ ድን ግል ተብሎ ከተተረጐመው ጋር አንድ የኾነው "አልማ" የሚለው ቃል ነው።

በኦሪት ዘጸአት ም.2 ቊ: 8 ላይ "ብላቴናይቱም ኼዳ የሕፃኑን እናት ጠራች" ተብሎ ትንሽ ልጅ ስለነበረችው ስለ ሙሴ እኅት ስለ ማርያም የተነገረው የዕብራይስጡ ቃል በትንቢተ ኢሳይያስ ም.7 ቊ.14 ላይ የተ ጠቀሰው "አልማ" የሚለው ቃል ነው።

በመዝሙር 68 ቊ:25 ላይ "ከበሮን በሚመቱ ወጣት ሴቶች (ደናግል) መካከል" የሚለው ቃል የዕብራይስጡ "አልማ" ነው።

በመጽሐፈ መኃልይ ም.1 ቊ: 3 ላይ ደናግል የሚለው ቃልና በም ዕራፍ 6 ቊ:8 ላይ ወጣት ሴቶች ልጆች ተብለው የተተረጐሙት በትንቢተ ኢሳይያስ ም.7 ቊ.14 ላይ ድንግል ተብሎ የተተረጐመው በዕብራይስጡ ቋንቋ "አልማ" የሚለው ቃል ነው።



www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ኹሉ ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎ ሲተረጐሙ አንድ ጊዜ ድንግል፥ አንድ ጊዜ ወጣት ሴት ልጅ በሌላ ጊ ደግሞ ብላቴና ተብለው ተተርጕመዋል እንጂ ባል ያገባች ሴት ልጅ ተ ለው የተተረጐሙበት ጊዜ የለም።

ወንጌላውያን ማቴዎስና ሉቃስም በኢሳይያስ የተነገረውን ትንቢ እንዴት ተፈጻሚነትን እንዳገኘ ሲያብራሩ መድኀኒታችን ያለ አባት ከ ናት ብቻ መወለዱን በዝርዝር ገልጸዋል። (ማቴ. ም.1 ቍ: 18፥ ሉቃ ም.1 ቍ:34 — 35)

"እኔ ወንድ የማላውቅ ድንግል ስኾን እንዴት ልወልድ እችላለሁ ብላ ድንግል ማርያም መልአኩን ገብርኤልን በጠየቀችው ጊዜ የሰጣት መልስ ባል ካገባሽ በኋላ ትወልጂአለሽ ብሎ ሳይኾን "መንፈስ ቅዱስ በ ንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑል ኀይልም ይፀልልሻል" ብሎ ነው። (ሉቃ ም.1 ቍ:35 )

ደግሞስ የጥቅሱን አባባል ብንመለከት ጌታ ምልክት ይሰጣችኋል መባሉ ባል ያገባች ሴት ልጅ የወለደች እንደኾነ እንዴት ምልክት ሊኾን ይችላል? አግብተው የሚወልዱ ብዙ ሴቶች ስላሉ የአንድዋ መውለድ ምንም ምልክት ሊኾን አይችልም። ምልክት ተብሎ የተነገረውና ምልክትም ሊኾን የሚችለው ባል ያላገባችና ከወንድ ጋር በግብረ ሥጋ ያልተገናኘች ድንግል የወለደች እንደኾነ ብቻ ነው።

ስለዚህ ከላይ በቀረቡት ማስረጃዎች መሠረት በትንቢተ ኢሳይስ ም.7 ቍ:14 ላይ የተነገረው በዕብራይስኖ ቋንቋ "አልማ" የሚለው ቃል ድንግል እንጂ ባል ያገባች ሴት አለመኾንዋን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ። (ጥያቄና መልስ ቍ:4 ኹለተኛ መጽሐፍ)

111. በትንቢተ ኢሳይያስ ም.38 ቍ:1 — 6 እንደተገለጸው ንጉሥ ሕዝቅያስ የመሞቻው ጊዜ መድረሱ በነቢዩ ኢሳይያስ አማካይነት ከእግዚአብሔር ቢነገረው ምርር ብሎ በማልቀስ ስለጸለየ በዕድሜው ላይ ዐሥራ አምስት ዓመቶች ተጨምሮለታል። በሉቃስ ወንጌል ም.2 ቍ:29 ላይ ደግሞ ስምዖን የተባለው ጻድቅ ከዚህ ዓለም ሕይወት ወደ ሟችነት እግዚአብሔር እንዲያስናብተው የጸለየ መኾኑ ተገልጾአል። እንዴት አን



ጻድቅ እንዳይሞት ሲጸልይ ሌላው ደግሞ በቶሎ እንዲሞት ጸለየ ተብ ሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ሞት ሲባል ነፍስ ከሥጋ መለየት አንድ ዐይነት ሞት ኾኖ ኹለተኛ ውና የከፋው ሞት ግን ሰው በዚህ ዓለም በኖረበት ዘመን ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃ ተግባር ባለማከናወኑ ዘላለማዊ የስቃይ ፍርድ መቀበሉ ነው።

ክርስቶስ በሞቱ ሞትን ድል ነሥቶልናል ብለን የምናምን ከኾነና እኛም በእምነታችን የጸናን ከኾንን ለምን ሞትን እንደቅጣት አድርገን እንወስደዋለን ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የሞት አጀማመሩ ለቅጣት መኾኑ የሚታወስ ነው። አዳም አትብላ ተብሎ የተከለከለውን ፍሬ በበላ ቀን የሞት ፍርድ በሰው ልጆች ኹሉ ላይ ሠለጠነ። ብዙዎችንም በጥፋታቸው ለመቅጣት ተፈልጎ እንዲሞቱ የተደረጉ ለመኾናቸው በቅዱሳት መጻሕፍት በልዩ ልዩ ቦታዎች ተገል ጾአል። ለምሳሌ የኖኅ ዘመን ሰዎች የሰዶምና ገሞራ ሰዎች፥ ዳታንና አቤ ሮን ከነተባባሪዎቻቸው፥ እንዲሁም ሐናንያና ሰጲራ በሞት የተቀጡ ናቸ ው። (ዘፍ.ም.7፥ ም.19 ዘኁ.ም.16፥ የሐ.ሥ.ም.5 ) ሐዋርያው ጳው ሎስም "የኀጢአት ዋጋው ሞት ነው" ብሏል። (ሮሜ ም.6 ቍ:23 )

ይህንንና የመሳሰሉትን ኹናቴዎች በመመልከት ነው ሰው ሞትን የሚፈራውና የሚጠላው። በሌላ በኩል ደግሞ ከቤተሰብ፥ ከዘመድ፥ ከጓደኛና ወዳጅ ለመጨረሻ ጊዜ መለየቱ በጣም ስለሚያስደነግጠውና ስለሚያሳዝነው ሰው ሞትን አይወድም። ምንም እንኳን ኹሉም ባይኾኑ ብዙዎች ደጋግ ሰዎችም ሞትን አይፈቅዱትም።

እኛ በዚህ ዓለም ባለንበት ጊዜ በዓይናችን የምናየው ሞት ነፍስ ከሥጋ በመለየቱ የሥጋ በድን መኾን እስከኾነ ድረስ ለወዲያኛው ዓለም ዝግጁ ባለመኾኑ ኹለተኛው ሞት የሚያስጋው መኾኑን የሚጠራጠር ሰው ካልኾነ በቀር በእምነቱና በተግባሩ ዝግጁ የኾነ ሰው ግን ለወዲ ያኛው ዓለም ተስፋ ይጓጓል እንጂ አይፈራም። ይህንንም በሚቀ ጥሉት ጥቅሶች ልንረዳ እንችላለን።



www.ethiopianorthodox.org

"የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ዘንድ የተከበረ ነው።" (መዝ.1
ቍ:15 )

"ጌታ ሆይ፥ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለ
ዐይኖቼ በሰዎች ኹሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና።" (ሉ
ም.2 ቍ:29 — 31 )

"እኔ ግን መሥዋዕት ለመኾን ተቃርቤአለሁ፤ ከዚህ ዓለም ተለይ
የምኼድበት ጊዜ ደርሷል፤ ጦርነትን በመልካም ተዋግቼአለሁ፤ ሩጫ
እስከመጨረሻው ሮጬአለሁ፤ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ። ከእንግዲ
ወዲህ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶ ይጠብቀኛል፤ ይህንንም አክሊል ቅ
ፈራጅ የኾነው ጌታ በዚያን ቀን ይሰጠኛል፤ ይህንንም ለእኔ ብቻ ሳይኾ
የእርሱን መገለጥ ለሚወዱ ኹሉ ይሰጣቸዋል።" (2ኛ ጢሞ. ም.4 ቍ:
— 8)

"ፈተናን ታግሶ የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም እግዚ
አብሔር በቃል ኪዳኑ መሠረት ለወዳጆቹ የሚሰጠውን የሕይወት አክ
ሊል ይቀበላል።" (ያዕ. ም.1 ቍ:12 )

እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ላይ ክብሩን ለመግለጽ ሲል አንዳንድ
ጊዜ የሞትን ፍርድ ከመወሰኑ በቀር የመጀመሪያው ሞት ማለት ነፍስ
ከሥጋ መለየት በመኾኑና ለማንም የማይቀር በመኾኑ እንደ ከፍተኛ ቅጣ
ት የሚቈጠረው አይደለም። ስለዚህ ነው ጌታ :- "ሥጋችሁን የሚገድሉ
ትን አትፍሩ፤ ነፍሳችሁን ግን ለመግደል አይችሉም" ያለው። (ማቴ.
ም.10 ቍ: 28 )

አንዳንድ ጊዜ ለቀሪው ደኅንነት ሲል አንዳንድ ሰዎችን ወይም
አንዳንድ ወገኖችን እንዲሞቱ ያደርግ ይኾናል። ነገር ግን ከወዲያኛው
ዓለም ዘላለማዊ ሕይወት ጋር ሲነጻጸር የሰው ዕድሜ በጣም አጭር በመ
ኾኑ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ በሞት መቅጣትን አስፈላጊ ኾኖ አያገኘ
ውም። እኛ ግን አስተሳሰባችን ውሱን በመኾኑ አንዳንድ ክፉ
አድራጊዎችን ለምን እግዚአብሔር በሞት አልቀጣቸውም ብለን
የትዕግሥተቢስነት ሐሳብ የምንሰነዝርባቸው ጊዜያት ጥቂት አይደሉም።



እንግዲህ እግዚአብሔር ለንጉሥ ሕዝቅያስ የዓሥራ አምስት ዓመት
ዕድሜ የጨመረለት በአንድ በኩል የቅን ታዛዥዎቹን ጸሎት የሚቀበል
መኾኑንና ክብሩን ለመግለጽ ሲኾን በሌላ በኩል ደግሞ በንጉሥ ሕዝ
ቅያስ አማካይነት ከተማይቱን ከአሦር ንጉሥ እጅ ለመታደግ ነው እንጂ
እንደ ንጉሥ ሕዝቅያስ ላለ የእግዚአብሔር ወዳጅ የዚህ ዓለም ሕይወት
ከወዲያኛው ዓለም ሕይወት የሚሻለው ኾኖ አይደለም። (ኢሳ. ም.38
ቍ:5 — 5)

112. በትንቢት ኢሳይያስ ም.42 ቍ:6 - 8 "እኔ እግዚአብሔር በጽድቅ
ጠርቼሃለሁ፤ እጅህንም እይዛለሁ፤ እጠብቅህማለሁ፤ የዕውሩንም ዓይን
ትከፍት ዘንድ የተጋዘውንም ከግዞት ቤት በጨለማም የተቀመጡትን ከወ
ሂኒ ቤት ታወጣ ዘንድ፥ ለሕዝብ ቃል ኪዳን ለአሕዛብም ብርሃን አድርጌ
እሰጥሃለሁ። እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ስሜም ይህ ነው፤ ክብሬን ለሌላ፥
ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም" በም.50 ቍ: 4 - 7
"የደከመውን በቃል እንዴት እንደምደግፍ ዐውቅ ዘንድ ጌታ እግዚአብ
ሔር የተማሩትን ምላስ ሰጥቶኛል፤ ማለዳ ማለዳ ያነቃኛል፤ እንደ ተማ
ሪዎችም ትሰማ ዘንድ ጆሮዬን ያነቃቃል። ጌታ እግዚአብሔር ጆሮዬን
ከፍቷል፤ እኔም ዓመፀኛ አልነበረሁም፤ ወደ ኋላዬም አልተመለስሁም።
ጀርባዬን ለገራፊዎች ጉንጬንም ለጠጉር ነጪዎች ሰጠሁ፤ ፊቴንም ከው
ርደትና ከትፋት አልመለስሁም። ጌታ እግዚአብሔር ይረዳኛልና ስለ
ዚህ አልታወክሁም፤ ስለዚህም ፊቴን እንደ ባልጩት ድንጋይ አድርጌዋ
ለሁ፤ እንዳላፍርም አውቃለሁ" በም.52 ቍ: 13 ላይ "እነሆ ባሪያዬ በማ
ስተዋል ያደርጋል፤ ይከብራል፤ ከፍ ከፍም ይላል፤ እጅግ ታላቅም ይኾ
ናል" በም.53 ቍ: 6 ላይ "እኛ ኹላችን እንደ በጎች ተቅበዘበዝን ጠፋን፤
ከእኛ እያንዳንዱ ወደገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የኹላችንን
በደል በእርሱ ላይ አኖረ።" በቍጥር 10 ላይ "እግዚአብሔርም በደዌ
ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፤ ነፍሱን ስለ ኀጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ
ዘሩን ያያል፤ ዕድሜውም ይረዝማል፤ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ
ይከናወናል" በቍ:12 ላይ "ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፤
ከኀያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶ
አልና፤ ከዓመፀኞችም ተቈጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኀጢአት
ተሸከመ፤ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ።" ተብለው በተገለጹት የተለያዩ ትን
ቢቶች የወልድ ክብር ከአብ ክብር ያነሰ ተደርጎ እንደተነገረ የሚመ



www.ethiopianorthodox.org

ስላቸው ወግኖች የሚከተሉትን ጥቅሶች ትክ ብለው ሊመለከቱአቸው ይ ባል።

"ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይኾናል፤ ስሙም ድንቅ፥ መካር፥ ኀይል አምላክ፥ የዘላ ለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል" (ኢሳ. ም.9 ቍ:6 )

"አንቺም ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካ ከል ትኾኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላ ለም የኾነ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚኾን ይወጣልኛል።" (ሚክ. ም.5 ቍ:2 )

"የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እነሆ፥ መጥቼ በመካከልሽ እኖራለሁና ዘምሪ፥ ደስም ይበልሽ ይላል እግዚአብሔር። በዚያም ቀን ብዙ አሕዛብ ወደ እግ ዚአብሔር ይጠጋሉ፤ ሕዝብም ይኾኑኛል፤ በመካከልሽ እኖራለሁ፤ የሠ ራዊት ጌታ እግዚአብሔርም ወደ አንቺ እንደ ላከኝ ታውቂአለሽ።" (ዘካ. ም.2 ቍ: 10 - 11 )

በተለያዩ አርእስት እንደተገለጸው እግዚአብሔር ወልድ ከሦስቱ መለኮታውያን አካላት አንዱና ፈጣሪ አምላክ መኾኑ ፃታወቀ ቢኾንም የሰውን ልጅ ለማዳን የእኛን ሥጋ በመልበሱ ስለእርሱ በሚነገርበት ጊዜ እንደ አምላክነቱም እንደሰውነቱም መነገሩ ሊያስገርመን አይገባም፤ ምክንያቱም የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ተግባራዊ የኾነው ባለ መቀላቀል፥ ባለመደባለቅ፥ ባለመለያየት፥ ባለመለዋወጥ፥ ባለመጠፋ ፋትና ባለመዋዋጥ ነውና። ይህም በመኾኑ በአንድ ቦታ የእግዚአብሔር ባሪያና የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንደተባለ ኹሉ በሌላ ቦታ ደግሞ ድንቅ፥ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባትና የሰላም አለቃ መባሉን እናስተውል። የሰውን ልጅ ሥጋ የለበሰ እንደመኾኑ ሕማም እንዲቀበል ያደረገው እግዚአብሔር ነው ቢባልም የእርሱ ክብር ከአብ ክብር የማያንስ መኾኑን ለማመልከት ደግሞ በትንቢት ኢሳይያስ ም.53 ቍ:12 ላይ "እርሱ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአል" ተብሎአል።

ነቢዩ ዘካርያስም ያ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በሰው ልጆች መካከል ሊኖር ያቀደው እግዚአብሔር እንጂ ሌላ አለመኾኑን ሲያመለክት "የጽ



ዮን ልጅ ሆይ እነሆ መጥቼ በመካከልሽ እኖራለሁና ዘምሪ፤ ደስም ይበ ልሽ ይላል እግዚአብሔር" በማለት አረጋግጦአል።

የእግዚአብሔርና የመሲሑ ግንኙነትም በአምላክና በፍጡሩ ወይም በአገልጋዩ መካከል ያለና የመሲሑ ድርጊቶችም በእግዚአብሔር ሥል ጣን ሥርና በእርሱም ፈቃድ ብቻ እንደኾኑ የሚመስላቸው ወገኖች ይኖ ሩ ይኾናል።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው እግዚአብሔር ወልድ ከተዋሕዶ በኋላ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ኾኗል። ፍጹም ሰው በመኾኑ ለሞት ታልፎ ቢሰጥም ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ የሚሰጠው ግን በገዛ ፈቃዱ ነው እንጂ ማንም አስገድዶት አይደለም። ስለዚህም ነው ጌታችን መድ ኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ም.10 ቍ: 17- 18 ላይ ነፍሱን ሊያኖራትም፥ ሊያነሣትም የሚችለው እርሱ ራሱ ብቻ መኾኑን የገለጸው።

ጌታም በሰውነቱ ለመለኮት ተገቢ ክብሩን መስጠት ስላለበት ባሪያ ወይም አገልጋይ ተባለ፤ እንዲሁም በፈጣሪና በፍጡር መካከል ያለ ግንኙነት መሰል አነጋገር ተነገረለት። በመለኮት ያልተዋጠው ትስብእት የመለኮትን ክብር ቢገልጽም መቼም ቢኾን መለኮት ከትስብእት የተለየ በት ጊዜ አይገኝም።

ወልድ የሰውን ሥጋ ለብሶ ለሰው ልጅ ቤዛ እንዲኾን የተላለፈው መለኮታዊ ውሳኔ በሰብአዊ ቋንቋ በሚገለጥበት ጊዜ ያንን ኹሉ መከራ እንዲቀበል የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር ተብሏል።

እግዚአብሔር ለእርሱ የክብር ቦታ ሰጠው የሚለውን አባባል በምንመለከትበት ጊዜ ሟችና በስባሽ የኾነው የሰው ልጅ ሰውነት ከመለ ኮት ጋር ተዋሕዶ ማድረጉ ለትስብእት ክብር የተሰጠው መኾኑን ያመ ለክተናል። ከሟችነት ወደ ሕያውነት ከሰውነት ደግሞ ወደ አምላክነት ደረጃ ከፍ ማለት በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

ስለዚህ ስለጌታ የተነገሩት በአንድ ፍጡር ላይ እንጂ በፈጣሪ ላይ ሊነገሩ የማይገባቸው ቋንቋዎች መነገራቸው ያልተጠፋፋውን የመለኮ



www.ethiopianorthodox.org

ትንና የትስብእትን ውሕደት የሚያመለክቱ በመኾናቸው ሊያስገርሙን ሊያስደንግጡንም አይገባቸውም።

ጥያቄናመልስ ቍ:102፥ 104፥ እና በኹለተኛው መጽሐፍ ቍ:8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥57፥61፥63፥ 72፥74፥75፥ 84፥89፥ 91 ፥92፥93፥102 ይመለከቷል።

113. በትንቢተ ኢሳይያስ ም.45 ቍ:7 ላይ "ብርሃንን ሠራሁ ጨለማውንም ፈጠርሁ፤ ደኅንነትን እሠራለሁ፤ ክፋትንም እፈጥራለሁ፤ እነዚህን ኹሉ ያደረግሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ" ያለውን አባባል ነቢዩ አሞፅ ሲያጠናክረው በም.3 ቍ:6 ላይ:- ክፉ ነገር በከተማ ላይ የመጣ እንደኾነ ያደረገው እግዚአብሔር አይደለምን? ካለ በኋላ በምዕራፍ 5 ቍ:15 ላይ "ክፉውን ጥሉ፤ መልካሙንም ውደዱ" የሚል ኾኖ እና ገኘ ዋለን። በሌላ በኩል ደግሞ ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ ም.1 ቍ:13-14 እንዲህ ብሏል "ሰው በሚፈተንበት ጊዜ እግዚአብሔር ፈተነኝ አይበል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ክፉ አድራጎትን እንዲያደርግ ሊፈተን አይቻልም፤ እርሱም ማንንም አይፈትንም። እያንዳንዱ ሰው የሚፈተነው በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው።"

ታዲያ በአንድ በኩል እግዚአብሔር ራሱ የፈጠረውን ነገር እንዴት ጥሉት ይለናል? በሌላ በኩል ደግሞ ክፉ ነገርን የፈጠረ እርሱ ኾኖ ሳለ እግዚአብሔር ፈተነን እንዳንልና የፈተናዎቹ ምክንያቶች እኛው ራሳችን ነን መባሉ እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ችግር፥ ክፉ ነገር፥ ወይም ፈተና ሲባል ኹለት ዐይነት ነው።

አንዱ ዐይነት ችግር ለሃይማኖታችን ጽናትና ለደኅንነታችን ሲባል በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመጣ ችግር ነው። ይህንኑ ችግርና ፈተናን በሚመለከት ነው ጻድቁ ኢዮብ "ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን፤ ክፉ ነገርንስ እንቀበልምን?" ያለው። (ኢዮ. ም.2 ቍ:10)

ሌላው ዐይነት ችግር ደግሞ ከበደላቸው የተነሣ በኀጢአተኞች ላይ የሚደርስ ችግር ነው። ክፉ ነገርን ጥሉ ያለው ኀጢአትን ጥሉ ማለቱ ነው። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ያዕቆብ "ሰው በሚፈተንበት ጊዜ እግዚአ



ብሔር ፈተነኝ አይበል" ያለው። ነቢዩ አሞፅ የተናገረው ስለኹለቱም ዐይነት ችግር ነው። ሐዋርያው ያዕቆብ ግን የተናገረው ስለሁለተኛው ዐይነት ችግር ብቻ ነው።

በመጽሐፈ ሲራክ ም.15 ቁ: 16 - 17 እንደተገለጸው ሰው በፊቱ ሕይወትና ሞት አሉለት፤ ከኹለቱ መካከል ደግሞ እርሱ የመረጠው ይሰጠዋል ተብሎ ለሰው ልጆች የተሰጠውን ነጻ ፈቃድ መሠረት በማድረግ ነው ሐዋርያው ያዕቆብ ማንንም ሰው እግዚአብሔር ፈተነኝ አይበል በማለት ሰው ኹሉ ለኀጢአቱ ኀላፊ መኾኑን ያረጋገጠው።

በሌላ በኩል ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙውን ጊዜ የተጻፉባቸውን ዘመናት ኹናቴ ያመለክታሉ። ለምሳሌ ይህ ትንቢት በተጻፈበት ዘመን የነበረው ቂሮስ የተባለው የፋርስ ንጉሥ ስለነበረና የፋርስ ሰዎች ደግሞ በደግነትና በክፋት አማልክት ማለት በኹለት አማልክት ያምልኩ ስለነበረ ክፋትንና ደኅንነትን ፈጠርሁ በሚልበት ጊዜ ኹሉንም የፈጠርሁ አንዱ አምላክ እኔ ብቻ ነኝ ብሎ ለቂሮስ የሚናገር መኾኑን ያመለክተናል። ለዚህም አባባል ማስረጃ የሚኾነው ቀደም ብሎ ከቀረበው ጥቅስ በፊት "እግዚአብሔር ለቂሮስ እንዲህ ይላል" የሚለው አጀማመር ነው።

በእነዚህም ከላይ በተዘረዘሩት መግለጫዎች መሠረት የቀረቡት ጥቅሶች ልዩ ልዩ ትርጓሜ አላቸው እንጂ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም። ጥያቄና መልስ ቍ:114፥ 118፥ 120፥ 140፥ እና ከኹለተኛው መጽሐፍ ቍ: 94ፉይመለከቷል

114. በትንቢት ኢሳይያስ ም.63 ቍ:17 ላይ "አቤቱ ከመንገድህ ለምን አሳትኸን? እንዳንፈራህም ልባችንን ለምን አጸናህብን?" ካለ በኋላ በትንቢት አሞፅ ም.2 ቍ: 4 ላይ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የእግዚአብሔርን ሕግ ጥለዋልና፥ ትእዛዙንም አልጠበቁምና፥ አባቶቻቸውም የተከተሉት ሐሰታቸው አስቷቸዋል። ስለዚህ ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የይሁዳ ኀጢአት መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም" በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስሉ ይኾናል።



www.ethiopianorthodox.org

የመጀመሪያው አባባል እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ያስታል ማለት ሳይኾን የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ጸጋ ችላ በማለት በተደጋጋሚ ኀጢ አት በሚሠራበት ጊዜ እንደፈለገ ያደርግ ዘንድ ይተወዋል ማለት ነው፤ የሰው ልጅ ደግሞ የፈቃድ ነጻነት ስላለው በፍላጎቱ ወደ ስሕተት በሚ ወድቅበት ጊዜ ለስሕተቱ እግዚአብሔር ምክንያት እንደኾነ መገመት የለ በትም። ልቡንም በክፉ ሥራ ላይ በሚያጠናክርበት ጊዜ እግዚአብሔር አይከለክለውም፤ ምክንያቱም ነጻ ፈቃድን ሰጥቶታልና። በዚሁ በተሰጠ ው ነጻ ፈቃድ ምክንያት ቀናውን መንገድ ትቶ የስሕተቱን አቅጣጫ በሚ ከተልበት ጊዜ እግዚአብሔር ስላልከለከለውና በፍላጎቱ መሠረት እንዲ መራ ስለፈቀደለት እግዚአብሔር እንዳሳተው አድርጎ በመገመቱ ነው በመጀመሪያ የተጠቀሰው አባባል የተገለጸው። ስለዚህም ነው በትንቢተ ሕዝቅኤል ም.14 ቍ: 9 ላይ "ነቢዩም ቢታለል፥ ቃልንም ቢናገር ያንን ነቢይ ያታለልሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ እጄንም በእርሱ ላይ እዘረጋለ ሁ፤ ከሕዝቤም ከእስራኤል መካከል አጠፋዋለሁ" የተባለው። እንዲሁም በምዕራፍ 20 ቍ: 25 ላይ "ደግሞም መልካም ያልኾነውን ሥርዓት በሕይወት የማይኖሩበትንም ፍርድ ሰጠኋቸው" ብሏል።

እንግዲህ እነዚህ አባባሎች እግዚአብሔርን ትተው ለሰይጣን ተገዢ ለመኾን በሚፈልጉበት ጊዜ ሰይጣንና ሠራዊቱ ወደ ፈለጉት አቅጣጫ እንዲመሩአቸው ይፈቅድላቸዋል ማለት ነው። ማንኛውም ሰው በተሰጠ ው ነጻ ፈቃድና በምርጫው መሠረት እግዚአብሔርን ትቶ ለሰይጣን ተገዢ መኾንን በመምረጡ የእግዚአብሔርን ጸጋ እስከተገፈፈ ድረስ የሰይጣንን ፈቃድ ይፈጽማል ማለት ነው። የሰይጣን ፈቃድና ፍላጎት ምን ዐይነት እንደኾነ ለማመልከት መድኀኒታችን ቀጥሎ ያለውን ማብራሪያ ሰጥቷል

"እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ልጆች ናችሁ፤ ፍላጎታችሁም የአባታችሁን ምኞት መፈጸም ነው፤ እርሱ ከመጀመሪያ አንሥቶ ነፍሰ ገዳይ ነበር፤ እውነት በእርሱ ስለሌለ ከእውነት ጋር ምንም ግንኙነት የለ ውም፤ እርሱ ሐሰተኛና የሐሰት አባት ስለኾነ ሐሰት በሚናገርበት ጊዜ ከገዛ ራሱ አውጥቶ ይናገራል።" (ዮሐ. ም.8 ቍ.44) በእርግጥ የሰይጣ ንን ፈተና ለመቋቋም የማንችልበት ጊዜ ሊኖር ይችል ይኾናል። (ሮሜ. ም.7 ቍ.12 – 24) ይኹን እንጂ ያን ጊዜ በጾምና በጸሎት የእግዚአብ



ሔርን ዕርዳታ ከጠየቅን ሰይጣንን ለማሸነፍ እንችል ዘንድ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ብርታቱን ይሰጠናል። (ማቴ. ም.17 ቍ:21 ም.26 ቍ:41)

ጥያቄና መልስ ቍ:113 ፥ 118፥ 120፥ 140 እና ከኹለተኛው መጽሐፍ ቍጥር 94 ይመለከቷል።

## ትንቢተ ኤርምያስ

ይህ መጽሐፍ 52 ምዕራፎችን የያዘ ኾኖ ትንቢቱ ያተኰረው በእስ ራኤል ሕዝብ ላይ ብቻ ሳይኾን በጐረቤት አገሮችም ጭምር ነው። ስለእ ስራኤል ልጆች በደለኛነት ትንቢት ከመናገሩም በላይ በንስሓ እንዲመለ ሱ አስጠን ቅቆአቸዋል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

115. በትንቢተ ኤርምያስ ም.1 ቍ:4 - 5 ላይ "የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ :- በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፤ ከማ ሕፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፤ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ" በሚለውና ወደ ገላትያ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.6 ቍ:7 ላይ ፤ "ራሳችሁን አታታልሉ፤ በእግዚአብሔር መቀለድ አይቻል ም፤ ምክንያቱም ሰው ኹሉ የሚያጭደው የዘራውን ነው" በተባለው አባባል መካከል ያለው ልዩነት እንዴት ይታረቃል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረ በኋላ ሙሉ የፈቃድ ነፃነትን ከመስጠቱ ጋር የትኛው ድርጊት ወደ ልማት የትኛው ድርጊት ደግሞ ወደ ጥፋት የሚያመራ መኾኑን በመግለጽ በትእዛዛት አስጠንቅቆታል። ይህንንም ኹሉ ካደረገ በኋላ በመጨረሻ ላይ የተግባሩ ውጤት ምን እን ደሚመስል ሲያመለክት «በዚህ ነገር አትደነቁ፤ ምክንያቱም በመቃብር ውስጥ ያሉት ኹሉ የእርሱን ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል። መል ካም የሠሩ ከሞት ተነሥተው በሕይወት ይኖራሉ፤ ክፉ የሠሩ ግን ከሞት ተነሥተው ይፈረድባቸዋል።" ብሏል። (ዮሐ. ም.5. ቍ 28–29)



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ከኾነ ታዲያ እንዴት ተደርጎ ነው ኤርምያስ ከማሕፀን ከመውጣቱ በፊት የተቀደሰውና ለአሕዛብ ነቢይ ኾኖ የተሾመው?

ቅዱስ ማለት የተለየ ማለት ነው። ኤርምያስም ለእግዚአብሔር አገልግሎት ስለተለየ ተቀደሰ ተባለ።

አሁን እንግዲህ ወደ ጥቅሱ መጀመሪያ እንመለስና እግዚአብሔር ለኤርምያስ ምን እንዳለው እንመልከት። "ገና በእናትህ መሕፀን እን ድትፀነስ ከማድረጌ በፊት ዐውቄሃለሁ።"

ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ዕውቀት ጊዜ የማይወስነው መኾኑን ነው። ይህም ማለት እኛ እያንዳንዳችን ከመወለዳችን በፊት ማንነታችንን ማለት ወደፊት ምን ዐይነት ሰዎች እንደምንኾን እግዚአብሔር ጠንቅቆ ያውቃል ማለት ነው። ስለዚህ አስቀድሞም ቢኾን ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለየን እንድንኾን ማድረጉ ሊያስገርመን አይገባም።

በዚህም መሠረት ኤርምያስ ወደፊት ተወልዶ በሚያድግበት ጊዜ ምን ዐይነት ሰው እንደሚኾን እግዚአብሔር አስቀድሞ ስላወቀው ለአሕዛብ ነቢይ እንዲኾን ቀደም ተብሎ የእግዚአብሔር ውሳኔ ተላለፈ።

ኤርምያስ ለተመራጭነቱ ብቁ የሚያደርገውን በጎ ተግባር በሥራ ከማሳየቱ በፊት ተመራጭ መኾኑ አያስገርምም፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ዘንድ ተፈላጊ የሚኾነው በጎ ተግባር ወደፊት በኤርምያስ ሕይወት ውስጥ እንደሚከሠት እግዚአብሔር አስቀድሞ ዐውቆታልና።

እንደሰው አስተሳሰብ ቢኾን ኖሮ ኤርምያስ ማንነቱን በተግባር ከማሳየቱ በፊት ሊመረጥ ባልተገባውም ነበር፤ ምክንያቱም የሰው ልጅ ዕውቀት ውሱን በመኾኑ ነው። ይህም ማለት እግዚአብሔር በትንቢት መልክ ካልገለጸለት በቀር አንድ ሰው ገና ያልተወለደ ፅንስ ይቅርና ከተወለደ በኋላ እንኳ ይህ ሕፃን ወደፊት እንደዚህ ይኾናል ብሎ ለማወቅ አይችልም። የእግዚአብሔር ዕውቀት ግን ከዚያ የተለየ በመኾኑ በሰው አስተሳሰብ መሠረት ልንወስነው አንችልም።



ስለዚህ እግዚአብሔር እንደ ሰው ልጆች በዕውቀቱ ውሱን ባለመኾኑ ኤርምያስን ገና ከመወለዱ በፊት መምረጡ ሊያስገርመን አይገባም።

116. በትንቢተ ኤርምያስ ም. 23 ቍ. 23 እና 24 ላይ "እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም። ሰው በስውር ቢሸሽግ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የምላሁ እኔ አይደ ለሁ ምን? ይላል እግዚአብሔር» ተብሎ በነቢዩ ጽሑፍ የተገለጸ ሲኾን በማቴዎስ ወንጌል ም. 18 ቍ. 20 ላይ :- "ኹለት ወይም ሦስት ኾነው በስሜ በሚሰበሰቡበት ሥፍራ እኔ በመካከላቸው እገኛለሁ" በማለቱ እነዚህ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል።

እግዚአብሔር በኹሉም ቦታ የሚገኝ ሙሉ እንጂ በአንድ ቦታ የተወሰነ አምላክ አለመኾኑን ከሚገልጹት ልዩ ልዩ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

"በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ፥ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም፤ ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ።" (1ኛ ነገ. ም. 8 ቍ. 27) በዚያ በቤተመቅደስ ሲሰባሰቡ በቅድስናውና በበረከቱ በመካከላቸው ይገኛል ማለት ነው።

ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወ ርድ፥ በዚያ አለህ፤ እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ፥ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር፥ በዚያ እጅህ ትመራኛለች፤ ቀኝህም ትይዘኛለች።" (መዝ. 139 ቍ. 7–10)

"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ሰማይ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዐይነት ቤት ነው? የማርፍበትስ ስፍራ ምንድር ነው? (ኢሳ. ም. 66 ቍ. 1)

በእነዚህ ከላይ በቀረቡት ማስረጃዎች መሠረት እግዚአብሔር ውሱን ያልኾነና በኹሉም ቦታ የሚገኝ መኾኑ ከተገለጸ "ኹለት ወይም ሦስት



www.ethiopianorthodox.org

ኾነው በስሜ በተሰበሰቡበት ቦታ እኔ በመካከላቸው እገኛለሁ" የሚለ
የጌታ አባባል እንዴት ይተረጐማል?

ቀደም ተብሎ በቀረበው የንጉሥ ሰሎሞን ጸሎት እግዚአብሔር
በተሠራው ቤተ መቅደስ የማይወሰን መኾኑን ከገለጸ በኋላ፥ ነገር ግን በዚ
ህ ቤተ መቅደስ ተሰባስበን የምናደርገው ጸሎት ተቀባይነትን ያግኝ ብሎ
ለጸለየው ጸሎት እግዚአብሔር መልስ ሲሰጠው የእስራኤል ልጆች
ሕግጋቱን የሚጠብቁ እስከ ኾነ ድረስ ቤተ መቅደሱን እንደሚቀድሰውና
ስሙም ለዘላለም በዚያ እንደሚኖር ገልጾለታል። ስለዚህ በእግዚአብሔር
ስም በዚያ በቤተ መቅደስ ሲሰባሰቡ በቅድስናውና በበረከቱ በመካከላ
ቸው ይገኛል ማለት ነው። (1ኛ ነገ. ም.9)

በትንቢተ ኢሳይያስ በተጠቀሰው ጥቅስ ላይ :- እግዚአብሔር በሰ
ማይም ኾነ በምድር ውሱን አለመኾኑን ከገለጸ በኋላ ነገር ግን ወደዚህ
ወደትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው
እመለከታለሁ" ብሏል። (ኢሳ.ም. 66 ቁ. 2) ይህ አባባል እንደሚያመ
ለክተው ምንም እንኳ እግዚአብሔር በኹሉም ቦታ ሙሉ እንጂ ባንዲት
ቦታ ብቻ ውሱን አለመኾኑ የታወቀ ቢኾን በማንኛውም ቦታ ለሚገኝ ማኅ
በር ወይም ግለሰብ በረከት የሚገባው ኾኖ ሲገኝ በጸጋውና በበረከቱ የማ
ይለየው መኾኑን ነው።

በማቴዎስ ወንጌልም የተገለጸው በመካከላቸው መገኘት ኀይሉን፥
ክብሩንና ምሕረቱን ያድላል ማለት ነው እንጂ እርሱ የሌለበት ቦታ አለ
ለማለት አይደለምና አለመኾኑን ዐውቀን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

117. በትንቢተ ኤርምያስ ም. 32 ቁ. 34 ላይ "የይሁዳን ሕዝብ
ኀጢያት ለማሠራት ይህን ኹሉ ያደርጋሉ ብዬ ከቶም አላሰብሁም ነበር"
በሚባልበት ጊዜ የእግዚአብሔር ዕውቀት ጊዜ የማይወስነው ከመኾኑ
ጋር እንዴት ሊታረቅ ይችላል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

እንደሚታወቀው መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ዋናው ዐላማ ለሰዎች
የመንፈሳዊ መመሪያ እንዲኾን ታስቦ ነው። አባባሎቹ ከሰው ልጆች ቋን
ቋ ጋር ተመሳሳይ ሊኾኑ ይገባል። ያለበለዚያ ግን ሰዎች የማይረዱአቸው
ይኾናሉ። ይህም በመኾኑ እግዚአብሔር ባደረገው ድርጊትና በወሰነው



ውሳኔ የማይጸጸት መኾኑ ቢታወቅም ለምሳሌ በኦሪት ዘፍጥረት ም. 6
ቁ. 6 ላይ "እግዚአብሔር በምድር ላይ ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ።"
የሚለውና በትንቢተ ዮናስ ም. 3 ቁ. 10 "እግዚአብሔርም ከክፉ
መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ፤ እግዚአብሔርም ያደርግባ
ቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገባቸውም።" የሚሉት
አባባሎች የተገለጹት ለሰው ልጆች በሚገባ ቋንቋ ለመነገር ስለተፈለገ
ነው እንጂ እግዚአብሔር የሚጸጸት ኾኖ አይደለም።

አንድ ጌታ አገልጋዩን በሚያዝዝበት ጊዜ አድርግ ወይም አታድርግ
ተብሎ ለአገልጋይ የሚተላለፈው ትእዛዝ በአገልጋይ በኩል ተግባራዊ
እንደሚኾን የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። ያ አገልጋይ የጌታውን ትእዛዝ
ያፈርሳል ተብሎ በጌታው ዘንድ ብቻ ሳይኾን በሌሎች ሰዎች ዘንድ እንኳ
የማይታሰብ ነው። ጌታውም ትእዛዙ በአገልጋዩ ዘንድ አለመከበሩን ሲመ
ለከት ምናልባት በዚህ ጉዳይ ላይ በመጀመሪያ ከሚናገራቸው ንግግሮች
መካከል አገልጋዬ እንደዚህ አድርጎ ትእዛዜን ያፈርሳል ብዬ አላሰብሁም
ነበር የሚል ሊኾን ይችላል። ይህንንም የሚለው ትእዛዙን ባስተላለፈ
ጊዜ ያ አገልጋይ ወደፊት ትእዛዙን የማያከብር መኾኑን ስለማያስብና ያን
ንም አስቀድሞ ሊያውቅ የማይችል በመኾኑ ነው።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የወደፊት ዝንባሌና
ተግባር አስቀድሞ የሚያውቅ ቢኾን መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በሰው
ልጆች ቋንቋ በመኾኑ "ይህን ኹሉ ያደርጋሉ ብዬ አላሰብሁም ነበር"
ብሎአል።

ይህም ማለት እኔ አምላካቸው የሰጠኋቸውን ትእዛዝ ማክበር ነበረባ
ቸው ማለት ነው እንጂ ትእዛዙን እንደሚያፈርሱ አስቀድሜ አላውቅም
ነበር ማለቱ አይደለምና አለመኾኑን ተረድተን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

## ሰቆቃወ ኤርምያስ

ይህ መጽሐፍ በአምስት ምዕራፎች የሚከፋፈል ኾኖ ስለ ኢየሩ
ሳሌም መከበብና መውደቅ፥ በዚህም ጊዜ በሕዝቡ ላይ የደረሰው ችግር፥
እናቶች ልጆቻቸውን እስከመብላት ያደረሰው ረኀብ፥ ኢየሩሳሌ ም



www.ethiopianorthodox.org

በጠላት እጅ ስትወድቅ እንዴት የብዙዎች በተለይም የካህናትና የነቢያት መገደል፥ እንዲሁም ነቢዩ ራሱ የደረሰበት ችግርና በምርኮኛነ ትም የደረሰባቸው ችግር ያሳዘነው መኾኑን ዘርዝሮ የጻፈው ነው።

## ጥያቄና መልስ

118. በሰቆቃወ ኤርምያስ ም. 3 ቁ. 38 ላይ "መልካምም ኾነ ክፉ ነገር ኹሉ የሚፈጸመው በልዑል እግዚአብሔር ትእዛዝ አይደለምን?" የሚል ሲኾን በመልእክተ ያዕቆብ ም.1 ቍ. 13 እና 14 ላይ "ሰው በሚፈ ተንበት ጊዜ እግዚአብሔር ፈተነኝ አይበል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በክፉ ነገር አይፈተንም፤ እርሱም ማንንም አይፈትንም፤ ነገር ግን እያ ንዳንዱ ሰው የሚፈተነው በገዛ ራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው" በመ ባሉ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።

በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ ክፉ ነገር በሚባልበት ጊዜ ኹለት የተ ለያዩ ኹናቴዎችን ያመለክተናል።

የመጀመሪያው ኹናቴ እግዚአብሔር በሰዎች ላይ እንዲደርሱ የሚ ፈቅዳቸው ችግሮች ናቸው። ለምሳሌ በኢዮብ ላይ እንደደረሰው ዐይነት ችግር ማለት ነው። (ኢዮ. ም.2 ቍ. 6)

ኢዮብም ለሚስቱ አነጋገር መልስ በሰጠበት ጊዜ "ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን፤ ክፉ ነገርንስ አንቀበልምን?" ብሎአታል። ይህም ማለት ጊዜያዊ የኾነው ችግርና መከራ ማለት ነው።

ኹለተኛው ኹናቴ ደግሞ በመልእክተ ያዕቆብ ም.1 ቍ. 13 እና 14 ላይ የተገለጸው ክፉ ነገር ነው። ይኸውም በሰዎች ላይ የሚደርሰው ጊዜያዊ መከራና ችግር ሳይኾን ኀጢአትን የመሥራት ክፉ ነገር ማለት ነው።

ስለዚህ ኹለቱ ጥቅሶች የተለያዩ ትርጉሞች አሉአቸው እንጂ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም። (ጥያቄና መልስ ቍ. 113፥ 114፥ 120፥ 140 እና ከኹለተኛው መጽሐፍ ቍ. 94 ይመለከቷል።)



## ትንቢተ ሕዝቅኤል

ይህ መጽሐፍ 48 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ ነቢዩ ትምህርቱን ግዳረስ ስላለበት ኀላፊነት ስለ ኪሩቤል ያለመው ሕልም፥ አይሁድ ኀጢአታቸው ምክንያት ወደፊት ስለሚደርስባቸው ችግርና እንዲሁም አይሁድ ጐረቤቶች በነበሩት አገሮች ላይ የተነገሩ ትንቢቶችን የያዘ ነው።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

119. በትንቢተ ሕዝቅኤል ም. 12 ቍ. 13 ላይ ስለሴዴቅያስ ትንቢት ሲነገር "መረቡን ዘርግቼ አጠምደዋለሁ፤ በዐይኑ ሳያያት ወደሚሞትባት ወደባቢሎን ከተማ አመጣዋለሁ" ተብሎአል።

ወደ ባቢሎን ከተማ የሚመጣ ከኾነ እንዴት ባቢሎንን በዐይኑ ሳያያት ይሞታል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ወደ ትንቢተ ኤርምያስ ም. 39 ቍ. 7 ላይ ብንመለከት "ከዚህም ኹሉ በኋላ የሴዴቅያስን ዐይኖች አውጥቶ በሰንሰለት በማሳሰር እየጐተተ ወደ ባቢሎን ይዞት ኼደ" ተብሎ እናገኛ ለን።

ስለዚህ ሴዴቅያስ ወደ ባቢሎን ከመኼዱ በፊት ዐይኖቹ እንዲወጡ በመደረጋቸው ባቢሎንን ሊያያት አልቻለም።

120. በትንቢተ ሕዝቅኤል ም. 20 ቍ. 25 ላይ "መልካም ያልኾነውን ሥርዓት በሕይወት የማይኖሩባትንም ፍርድ ሰጠኋቸው" የሚለው አባባል በቍጥር 11 ላይ "ሰው ቢያደርገው ኖሮ በሕይወት የሚኖርበትን ሥርዓ ትቴንም ሰጠኋቸው፤ ፍርዴንም አስታወቅኋቸው" ከሚለው አባባል ጋር ተቃራኒ ይመስለን ይኾናል።



www.ethiopianorthodox.org

ቀደም ተብሎ በልዩ ልዩ ተመሳሳይ ጥያቄዎች እንደተገለጸው ሰው ኹሉ ይድን ዘንድ እንጂ ማንም እንዲጠፋ የእግዚአብሔር ፍላጐት አይደለም። በዚህም ምክንያት የመዳኛውን መንገድ ያቀርብለታል። ይኹን እንጂ የሰው ልጅ ምንም ያኽል የመዳኛ መንገድ ቢቀርብለት ያንን ችላ ብሎ ወደ ጥፋት የሚወስደውን መንገድ በሚከተልበት ጊዜ ለፍላጎቱ ስለሚተወው ማለትም የሰው ልጅ የፈቃድና የፍላጎት ነጻነት ያለው በመኾኑና እግዚአብሔር ሊያስገድደው ስለማይፈቅድ ያን የጥፋት መንገድ እግዚአብሔር እንደሰጠው ተቆጠረ እንጂ ክፉ ሥራ እንዲሠራ አስገደደው ማለት አይደለም።

በመዝሙር 81 ቍጥር 8 እና 11–12 ላይ "ሕዝቤ ሆይ፥ ስማኝ እነግርሃለሁ፤ ሕዝቤ ቃሌን አልሰሙኝም፤ እስራኤልም አላዳመጠኝም። እንደልባቸው ተውኋቸው፤ በልባቸው አሳብ ኼዱ" የሚለው ጥቅስ የላይኛውን አባባል ያጠናክራል።

ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንን ጉዳይ ሲያብራራ እንዲህ ብሏል። "ሰዎች በክፋታቸው እውነት እንዳይታወቅ ሲያደርጉ በኀጢአታቸውና በክፋታቸው ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጥባቸዋል። ...እነርሱ እግዚአብሔርን አውቀውት ሳለ ለእርሱ የሚገባውን ክብርና ምስጋና አልሰጡትም፤ በአሳባቸው ከንቱ ኾኑ፤ የሚያስተውል ልቦናቸው ጨለመ፤ ጥበበኞች ነን ሲሉ ሞኞች ኾኑ ... ስለዚህ እግዚአብሔር እርስ በርሳቸው አሳፋሪ ድርጊቶችን እንዲፈጽሙ ርኵሰት ለሞላበት ለክፉ ምኞታቸው ተገዢዎች እንዲኾኑ ተዋቸው።" (ሮሜ 1:18 -24)

በዚህም መሠረት እግዚአብሔር በቅድሚያ ደግና ክፉ ነገሮችን እንድናውቅ ከማድረጉ በቀር የፍላጎት ነጻነትን ስለሰጠን ማንኛውንም መንገድ እንድንከተል አያስገድደንም። ይኹን እንጂ ማንኛ ውም ድርጊት ያለእርሱ ፈቃድ ስለማይፈጸም ለድርጊቶቻችን ኹሉ እግዚአብሔርን ምክንያት ማድረግ የተለመደ አባባል ነው። (ጥያቄና መልስ ቍ. 113 ፥ 114፥118፥140 እና ከኹለተኛው መጽሐፍ ቍ. 94 ይመለከቷል።)



# ትንቢተ ዳንኤል

ይህ መጽሐፍ በ12 ምዕራፎች የተከፋፈለ ኾኖ ስለነቢዩ ዳንኤል የሕልም ትርጉም ዐዋቂነትና የእርሱም ራእይ እንዴት አድርጎ ክርስቶስ የሚመጣበትን ጊዜ አስተካክሎ መናገሩን የሚያመለክት ነው።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

121. በትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ ነቢዩ ዳንኤል ራሱን የሚያ መሰግንባቸው የተለያዩ ቦታዎች ይገኛሉ። ለምሳሌ የሚከተሉትን እን መልከት

"ንጉሡ በተነጋገራቸው ጊዜ ከብላቴኖቹ ኹሉ እንደ ዳንኤል፥ እንደ አናኒያ፥ እንደ ሚሳኤልና እንደ አዛርያ ያለ አልተገኘም።" (ዳን.ም.1. ቍ.19)

"የሕልም ተርጓሚዎች አለቃ ብልጣሶር ሆይ የቅዱሳን አማልክት መን ፈስ በአንተ ውስጥ እንዳለ፥ ከምሥጢርም ኹሉ የሚያስቸግርህ እንደ ሌለ ዐውቄአለሁና ያለምሁትን የሕልሜን ራእይ ፍቺውን ንገረኝ።" (ዳን. ም.4 ቍ.9)

የቅዱሳን አማልክት መንፈስ ያለበት ሰው በመንግሥትህ ውስጥ አለ፤ በአባትህም ዘመን እንደ አማልክት ጥበብ ያለ ጥበብና ማስተዋል፥ ዕውቀትም ተገኘበት፤ አባትህም ንጉሡ ናቡከደነፆር የሕልም ተርጓሚዎችና የአስማተኞች፥ የከለዳውያንና የቃላተኞች አለቃ አደረገው።" (ዳን. ም.5 ቍ:11)

"ዳንኤልም መንፈስ ስላለው ከአለቆችና ከመሳፍንት በለጠ፤ ንጉሡም በመንግሥቱ ኹሉ ላይ ይሾመው ዘንድ አሰበ።" (ዳን. ም.ም.6 ቍ.3)



www.ethiopianorthodox.org

"አንተ እጅግ የተወደድህ ነህና በልመናህ መጀመሪያ ላይ ትእዛ ወጥቶአል፤ እኔም እነግርህ ዘንድ መጥቼአለሁ፤ አሁንም ነገሩን መርም ር፤ ራእዩንም አስተውል።" (ዳን.ም.9 ቍ.23)

እርሱም እጅግ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ፥ እኔ ዛሬ ወደ አንተ ተልኬአለሁና የምነግርህን ቃል አስተውል፤ ቀጥ ብለህም ቁም አለኝ።" (ዳን.ም. 10 ቍ.11 )

እንደዚህ አድርጎ ስለራሱ በሚተችበት ጊዜ ዝና፥ ክብርና ምስጋና ፈልጎ እንዳደረገው አያስመስልበትምን? ይህስ ከኾነ ደግሞ ዳንኤልን ለሚያኽል ታላቅ ነቢይ ይህ የግብዝነት አነጋገር ተገቢ የኾነ ተግባር ነውን? ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ለሰሚው ጠቃሚ ዕውቀትን የሚሰጥ እስከ ኾነ ድረስ አንድ ጸሐፊ ስለራሱ ገለጻ በማድረግ የሚያቀርበው ጽሑፍ አስፈላጊ ነው። ይህንንም ዘዴ ብዙ ታዋቂ ጸሐፊዎች ተጠቅመውበታል።

ለተቀባዩ ማለት ለሰሚው ጠቃሚ የኾነና ከራሱ በቀር ሌላ ሰው ሊያቀርበው የማይችለው እስከ ኾነ ድረስ አንድ ጸሐፊ ስለራሱ የሚያቀርበው ገለጻ የሚያስመሰግን እንጂ የሚያስወቅስ አይደለም። (ጥያቄና መልስ ቍ:41 እና 88 ይመለከቷል)

122 በትንቢተ ዳንኤል ም.8 ቍ:13 እና 14 ላይ "ከቅዱሳኑም አንዱ ሲናገር ሰማሁ፤ ለተናገረው ለቅዱሱም ኹለተኛው ቅዱስ ስለዘወትሩ መሥዋዕት፥ መቅደሱና ሠራዊቱ ይረገጡ ዘንድ ስለሚሰጥና ስለሚያጠፋ ኀጢአት የኾነው ራእይ እስከመቼ ይኾናል? አለው። እርሱ እስከ ኹለት ሺሕ ሦስት መቶ ማታና ጠዋት ድረስ ነው፤ ከዚያ በኋላ መቅደሱ ይነጻል አለኝ" ይልና በምዕራፍ 12 ቍ: 1 እና 12 ደግሞ፤ "የዘወትሩም መሥዋዕት ከቀረ ጀምሮ፥ የጥፋትም ርኩሰት ከቆመ ጀምሮ ሺ ኹለት መቶ ዘጠና ቀን ይኾናል። የሚታገስ እስከ ሺ ሦስት መቶ ሠላሳ አምስት ቀንም የሚደርስ ምስጉን ነው" በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች የተለያዩ ከመም ሰላቸውም በላይ ማታና ጥዋት የተባሉትን ቀኖች በዓመት በመለወጥና ኹለት ሺ ሦስት መቶ ዓመት በማድረግ ለጥቅሶቹ ልዩ ልዩ ትርጓሜዎችን የሚሰጡ ወገኖች አሉ። በሚያደርጉትም የትርጓሜ ሙከራ የጊታን



ዳግመኛ መምጫ ጊዜ ከልዩ ልዩ የጊዜው ኹናቴ ጋር በማያያዘ የሚያ ውቁት ይመስላቸዋል።

መድኀኒታችን ተመልሶ የሚመጣበትን ጊዜ ማንም ሊያውቀው የሚችል ሰው አለመኖሩ በማርቆስ ወንጌል ም.13 ቍ:32 ላይ የተገለጸ ኾኖ ሳለ ስለሌላ ጉዳይ በትንቢት የተገለጸውን የጊዜ ርዝመት የሒሳብ ስሌቶችን እያዘጋጁ ልናውቀው ያልተፈቀደልንን ጊዜ የሚያውቍ ማስመሰል ራስን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስተካከል መሞከርና ራስን ማታለል ነው።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የጉዳዩ አመጣጥና አካኼድ የሚያ መለክተው ካልኾነ በቀር ቀን የሚለው ቃል በመጣ ቍጥር ወደ ዓመት መተርጐም አስፈላጊም፥ አግባብም አይደለም። ያለበለዚያማ በኻያ አራት ሰዓቶች ርዝመት ላለው ጊዜ ወይም ከጧት እስከ ማታ ላለው ጊዜ ቀን ከሚለው የተለየ ሌላ ቃል ማግኘት ይኖርብናል ማለት ይኾናል። ይህ ግን አለመኾኑን ለመረዳት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት ልዩ ልዩ ማስረጃዎች መካከል ጥቂቶቹን እንመልከት።

በኦሪት ዘፍጥረት ም.42 ቍ:17 ዮሴፍ ወንድሞቹን ለሦስት ቀን ያሰራቸው መኾኑ ተገልጾአል።

"ሙሴም በተራራው ላይ አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ቆየ።" (ዘጸ. ም.24 ቍ:18)

በመጀመሪያው መጽሐፈ ነገሥት ም.12 ቍ:5 ላይ ሮብዓም ሕዝቡን ነሦስት ቀኖች በኋላ እንዲመለሱ ነገራቸው ይላል።

በመጽሐፈ አስቴር ም.4 ቍ:16 ላይ አስቴር የሦስት ቀን ጾም እንዳወጀች ተነግሮአል።

"ከመልካም ሽቱ መልካም ስም፥ ከመወለድ ቀንም የሞት ቀን ይሻላል።" (መክ. ም.7 ቍ:1)

www.ethiopianorthodox.org

"ዮናስም በዓሣው ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ነበረ።" (ዮና. ም.2 ቊ:1)

"አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጾመ በኋላ ተራበ" (ማቴ. ም.4 ቊ:2)

ከላይ በተዘረዘሩት ማስረጃዎች ውስጥ የሚገኘው ቀን የሚለው ቃል በዓመት ሊተረጐም የማይችል መኾኑ ግልጽ ነው። በዚሁም ዓይነት ኹለት ሺ ሦስት መቶ ማታና ጥዋት የተባለው አባባል በቀኖች እንጂ በዓ መቶች የሚተረጐም አይደለም።

ጌታ ዳግመኛ ስለሚመጣበት ጊዜ ኹናቴ በሚመለከት በማቴዎስ ወንጌል ም.24 ቊ:36 - 51 ቍጥር ውስጥ በዝርዝር እንደተገለጸው ትነ ቢትን በግልጽ ለማወቅ የሚቻለው የትንቢቱ ጊዜ ደርሶ ትንቢቱ ሲፈጸም ብቻ በመኾኑ ያ ከመኾኑ በፊት ግን የተነገረውን ትንቢት ለአንድ መሠረታዊ እምነት (ዶግማ) መነሻ ማድረግ ወደ አልታሰበ የክሕደት አዘቅት መውደቅ ሊኾን ስለሚችል ብርቱ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል።

በመሠረቱ እነዚህ የተቀጠሱት ኹለት ሺ ሦስት መቶ ቀኖች ንጉሥ አንጥያኮስ የጥፋት እጁን በኢየሩሳሌምና በእስራኤል ሕዝብ ላይ ከዘረ ጋበት ከግሪክ መንግሥት የግዛት ዘመን ከመቶ አርባ ሦስት ዓመት ጀምሮ እስከሞተበት እስከ መቶ አርባ ዘጠኝ ዓመት ድረስ ያለው ጊዜ ነው። (1ኛ መቃ. ም.1 ቊ:21 ፥ ም.6 ቊ:16) ይህም የተጠቀሰው ጊዜ ከክር ስቶስ ልደት በፊት ከ171 እስከ 165 ድረስ ነው።

በአንጥያኮስ የተፈጸመው ቤተ መቅደስን ማርከስ፥ መሥዋዕቱን ማስቀረት፥ ንዋየ ቅዱሳቱን መዝረፍና የአይሁድን ሕዝብ ማስፈጀት ዝር ዝር ኹናቴ የተገለጸው በመጀመሪያው መጽሐፈ መቃብያን ከምዕራፍ 1 ቊ:1 እስከ ምዕራፍ 6 ቊ:16 ድረስ ነው። ስለ ቤተ መቅደሱ መንጻት ደግሞ በዚሁ በአንደኛ መቃብያን ም.4 ቊ:36 - 61 ተገልጾአል።

በትንቢተ ዳንኤል ም.12 ቊ:11 ላይ የተገለጸው አንድ ሺ ኹለት መቶ ዘጠና ቀን ቤተ መቅደሱን በማርከስ የጣዖት ሐውልት እንዲቋቋ ምበት ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በይሁዳ መቃብዮስ አማካይነት ቤተ መቅ



ደሱ እስከነጻበት ጊዜ ድረስ ነው። በቊ:12 ላይ የተጠቀሰው አንድ ሺ ሦስት መቶ ሠላሳ አምስት ቀኖች የተባለው ደግሞ ምናልባት አንጥያኮስ ፋርስን አገር ለመዝረፍ ኼዶ የነበረበትን ጊዜ በመጨመር ነው። እስከ ሺ ሦስት መቶ ሠላሳ አምስት ቀን የሚታገስ ምስጉን ነው የተባለው የንጉሥ አንጥያኮስ ወታደሮች የሃይማኖት ሕግና ሥርዓት እንዲሻር ያስገድ ዱ ስለነበረ ነው።

በትንቢተ ዳንኤል ም.9 ቊ:24 - 27 ውስጥ የተገለጹት የሱባዔ ቀኖች በዓመት በመለወጥ ቢተረጎሙም በምዕራፍ 8 እና 12 የተነገሩት ቀኖች ግን ጧትና ማታ ተብለው በዝረዝር ስለተገለጹ ቀን እንጂ ዓመት አይደሉም።

## ትንቢተ ሆሴዕ

ይህ መጽሐፍ በዐሥራ አራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ኾኖ በውስጡም ስለእስራኤል ልጆች ጣዖት ማምለክ፥ የእግዚአብሔርን ሕግ ባለመጠበቃቸው ወቀሳና ለሕጉ ታዛገሮች ለኾኑት ደግሞ የክርስቶስ አዳኝነት ተስፋ ተሰጥቶበታል።

## ጥያቄና መልስ

123. በትንቢተ ሆሴዕ ም.11 ቊ:1 ላይ "እስራኤል ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት፤ ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት ተብሎ የተነገረውን ታሪካዊ ዜና ወንጌላዊው ማቴዎስ በምዕራፍ 2 ቊ:15 ላይ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረ ትንቢት እንደኾነ አድርጎ ማቅረቡ ትክክል አይደለም ይባል ይኾናል።

ወንጌላዊው ተመሳሳይ የኾኑ ነገሮችን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በሚጠቅስበት ጊዜ ያልተብራሩ ነገሮች ይብራራሉ፤ የራቁ ነገሮችም ይቀርባሉ።



www.ethiopianorthodox.org

ሄሮድስ ሕፃን ጌታ ኢየሱስን ለመግደል ፈልጎ እንደነበረ ኹሉ ፈ
ዖንም እስራኤልን ለማጥፋት አስቦ እስራኤሎች በጉዞ ላይ እያሉ የግብ
ሠራዊት እንዲከተላቸው አድርጎ ነበር።

በፈርዖን ጭቈና ምክንያት እስራኤል ከምድረ ግብጽ ወጣ። ወ
ግብጽ ተሰዶ የነበረው ጌታም ከግብጽ ወጣ።

በሄሮድስ ማሳደድ ምክንያት ወደ ግብጽ ተሰዶ የነበረው ጌታች
ልጄን ከግብጽ ጠራሁት የተባለው በርኅብ ምክንያት ወደ ግብጽ ተሰ
የነበረው የእስራኤል ሕዝብ ልጄን ከግብጽ ጠራሁት በተባለለት አባባ
መገለጹ ሊያስገርመን አይገባም።

ብዙ ትንቢቶች በሚነገሩበት ጊዜ ከአንድ ትርጓሜ በላይ ስለሚ
ኖራቸው ማለት ያ የተነገረው ትንቢት ስለ አንድ ጉዳይ ብቻ ሳይኾን ከአ
ንድ ለበለጡ ጉዳዮች ሊኾን ስለሚችል በረኀብ ምክንያት ወደ ግብጽ የተ
ሰደደው የእስራኤል ሕዝብና በሄሮድስ ምክንያት ወደ ግብጽ የተሰደደው
ጌታችን ኹለቱም በአንድ አባባል ልጄን ከግብጽ ጠራሁት ተብሎ ተነገ
ሮላቸዋል።

## ትንቢተ ኢዮኤል

ይህ መጽሐፍ በ3 ምዕራፎች የተከፋፈለ ኾኖ በአይሁድ ሕዝብ ላይ
ወደፊት ስለሚመጣው ችግር ካህናት በጾምና በጸሎት የእግዚአብሔርን
ምሕረት እንዲለምኑ፥ ሕግ አፍራሾች የእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚደ
ርስባቸውና ታዛዦች ግን ደኅንነት እንደሚጠብቃቸው ይናገራል።

## ጥያቄና መልስ

124. በትንቢተ ኢዮኤል ም.2 ቍ:32 ላይ "የእግዚአብሔርን ስም የጠራ
ኹሉ ይድናል" የሚል ሲኾን በማቴዎስ ወንጌል ም.7 ቍ:21 ላየ ደግሞ
"ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ኹሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት
አይገባም። ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባው ግን በሰማይ ያለውን



የአባቴን ፈቃድ የሚፈጽም ነው" በማለቱ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒ
ይመስሉን ይኾናል።

በትንቢተ ኢዮኤል ላይ የእግዚአብሔርን ስም የጠራ ኹሉ በሚ
ልበት ጊዜ በእግዚአብሔር ያመነና ትእዛዛቱንም የፈጸመ ለማለት ነው
እንጂ ዝም ብሎ ብቻ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ማለት አይደለም
የእግዚአብሔርን ስም የጠራ ይድናል ካለ በኋላ "እግዚብሔርም እንደ
ተናገረ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም መድኅኒት ይገኛል" ብሏል።
ይህም የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም ሕማማትን ተቀብሎ ሞቶ በመ
ነሣት መድኅኒት በኾነን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመንን እንደኾነ እን
ድናለን ማለት ነው። ይኹን እንጂ እምነትም ኾነ ጸሎት ያለበጎ ተግባር
ዋጋ አይኖራቸውም። ነቢዩ የእግዚአብሔርን ስም የጠራ በሚልበት ጊዜ
ያ የእግኢዘብሔርን ስም የሚጠራው ሰው በእግዚአብሔር ያመነ መኾኑን
በመገንዘብ ነው ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ስም ለመጥራት በቅድሚያ
ማመን ይኖራልና ነው። በተለየ ግን የእግዚአብሔርን ስም መጥራት
ማለት እግዚአብሔርን መለመን ወይም መጸለይ ማለት ነው። ስለዚህም
ነው ጌታ ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ በር አንኳኩ
ይከፈትላችኋል" ያለው። (ማቴ. ም.7 ቍ:7)

በዚህም መሠረት ኹለቱ ጥቅሶች የተለያየ ትርጓሜ አላቸው እንጂ
እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

## ትንቢተ አሞጽ

ይህ መጽሐፍ 9 ምዕራፎችን የያዘ ኾኖ የፍልስጥኤምና የእስራኤል
ሕዝብ ኀጢአት በመብዛቱ ማስጠንቀቂያ፥ በሳምራውያን ላይ የእግዚ
አብሔር ቁጣና እንዲሁም ለእስራኤል ልጆች የወንጌሉ ተስፋ ይገኝ
በታል።



www.ethiopianorthodox.org

## ጥያቄና መልስ

125. በትንቢተ አሞጽ ም.13 ቍ:2 ላይ እግዚአብሔር በነቢ አማካይነት ለእስራኤል ሕዝብ "በዓለም ከሚኖሩ ሕዝቦች ኹሉ እኔ የ ረጥሁት እናንተን ብቻ ነው" የሚል ሲኾን ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.10 ቍ:12 ላይ "እንግዲህ አንዱ እግዚአ ሔር የኹሉም ጌታ ስለኾነ በአይሁዳዊና በአረማዊ መካከል ምንም ል ነት የለም፤ እርሱም ባለጸጋ ስለኾነ፥ ለሚለምኑት ኹሉ በረከቱን አብዝ ይሰ ጣል" በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል።

ቀደም ተብሎ በጥያቄና መልስ ተራ ቍጥሮች 50 እና 56 ላይ የእስራኤልን ልጆች ምርጫ በሚመለከት የተዘረዘረውን ኹናቴ መለ ብሎ መመልከት ጠቃሚ ነው።

ባለፉት ገለጻዎች እንደተዘረዘረው እንደ አጋጣሚ ኾኖ እስራኤሎች በጣም ለእግዚአብሔር ታዛዦች የነበሩ አባቶች ስለነበሩአቸው ልጆ ቸውም እንደ እነርሱ ታዛዥዎች ኾነው ቢገኙ ምርጥ ሕዝብ ሊያደር ጋቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር። ይኹን እንጂ ትእዛዝ አፍራሾች ኾነ ቢገኙ ግን የጠላቶቻቸው ዕድል ፈንታ እንደሚያጋጥማቸው ማስጠን ቂያ ተሰጥቶአቸዋል። በዚህም መሠረት ከእግዚአብሔር ትእዛዞች አፈን ጠው ኀጢአት በሠሩ ጊዜ በጠላቶቻቸው እጅ ተሸንፈውና ተዋርደው በምርኮኛነት ተበታትነዋል።እግዚአብሔርም ከዚያ በኋላ ሰውን የመ ረጫው መንገድ በዘር መኾኑ ቀርቶ በተግባር ስለኾነ የክርስትና ሃይማኖት ተቀብለው የእግዚአብሔር ቅዱሳን ለመኾን ከበቁት አብዛኛ ዎቹ አይሁዶች ሳይኾኑ የአረማውያን ወገኖች የነበሩ ናቸው።

እስራኤሎች በእግዚአብሔር እርዳታ ሌሎችን ወገኖች ሊያሸን የቻሉበት ሌላው ምክንያት ደግሞ እነዚያን ተሸናፊዎቹን ወገኖች በእስ ራኤሎች አማካይነት እግዚአብሔር ሊቀጣቸው ስለፈለገ ነው እንጂ አንዱን ዘር ከሌላው ዘር በመለየትና ለአንዱ በማዳላት አይደለም። እንደ ዚያማ ቢኾን ኖሮ እስራኤሎች በጠላቶቻቸው እጅ ባልተሸነፉም ነበር።



ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን የሚመርጠው በተግባሩ እንጂ በትው ልዱ አለመኾኑን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

## ትንቢተ አብድዩ

ይህ መጽሐፍ አንድ ምዕራፍ ብቻ ያለው ኾኖ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ጠላት በተነሣ ጊዜ የኤዶም ሕዝብ በመርዳት ፈንታ ዝም ብሎ ብቻ በመመልከትና እንዲያውም ወራሪውን በመርዳቱ ምክንያት የእግዚአብ ሔር ቅጣት እንደሚደርስበት የሚናገር ትንቢት ነው።

## ጥያቄና መልስ

126. ቀደም ተብሎ በየጊዜው እንደተገለጸው የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር ሕግ ተገዢ ኾኖ በኖረበት ጊዜ ኹሉ ኑሮው የተቃናለት ከመኾኑም በላይ ማንኛውም ጠላት ሊቋቋመው አልቻለም። የመሸነፍና የመማረክ ችግር የሚደርስበት ከእግዚአብሔር ትእዛዞች ባፈነገጠ ጊዜ ብቻ ነበር። ይህም አባባል ትክክል መኾኑን ለመገንዘብ በኦሪት ዘዳግም ም.8 ቍ:18 - 20 የተገለጸውን መግለጫ እንመልከት "ለአባቶችህ የማለውን ቃል ኪዳን ያጸና ዘንድ ሀብት ለማከማቸት እርሱ ጉልበት ሰጥ ቶሃልና አምላክህን እግዚአብሔርን አስብ። አምላክህን እግዚአብሔርን ብትረሳ፥ ሌሎችንም አማልክት ብትከተል ብታመልካቸውም፥ ፈጽሞ እንደምትጠፉ እኔ ዛሬውኑ እመሰክርባችኋለሁ። የአምላካችሁን የእግዚአ ብሔርን ቃል ስላልሰማችሁ እግዚአብሔር ከፊታችሁ እንደሚ ያጠፋቸ ው እንደ አሕዛብ እንዲሁ እናንተም ትጠፉላችሁ።"

በዚህ ጥቅስ መሠረት የእስራኤል ሕዝብ መሸነፍና ምርኮ የደረ ሰበት በኀጢአቱ ምክንያት መኾኑን እንረዳለን። የእስራኤልን ሕዝብ ያሸ ነፉት ወገኖች ከእስራኤል የበለጠ ለእግዚአብሔር ቅርብነት የነበራቸው ኾነው ሳይኾን እነርሱ እስራኤልን ለመቅጫ የእግዚአብሔር አርጩሜ በመኾናቸው ብቻ ነው። ለዚህም ማስረጃ የሚኾነው በትንቢተ አሞጽ ም.13 ቍ:2 ላይ "በዓለም ከሚኖሩ ሕዝቦች ኹሉ እኔ የመረጥሁት



www.ethiopianorthodox.org

እናንተን ብቻ ነው፤ በምትሠሩት ኀጢአት ኹሉ የምቀጣችሁ ስለዚህ ነው" የሚለው ጥቅስ ነው።

እንግዲህ እስራኤሎች በኀጢአታቸው እንዲቀጡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ኹኖ ሳለ ይህን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሥራ ላይ በማዋላቸው በኤዶም ሰዎች ላይ ቅጣት እንደሚደርስባቸው ትንቢት መነገሩ ለምን ድነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በጥያቄና መልስ ተራ ቍጥር 79 እንደተገለጸው አግዚአብሔር የሚመለከተው የአንድን ኹናቴ ውጤት ብቻ ሳይኾን የአድራጊውን ውስጣዊ ዝንባሌ ጭምር ነው። በዚህም መሠረት ምንም እንኳ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ በሌሎች ወገኖች አማካይነት እንዲቀጣ ፈቃዱ ቢኾን የእነዚያ የእስራኤል ጠላቶች ዝንባሌ ግን የክፋትና የበቀል ፍላጎት ስለኾነ እግዚአብሔር እንደዚህ ያሉትን ይቅር አይላቸውም። በኤዶም ላይ የተነገረውም ትንቢታዊ ማስጠንቀቂያ የዚሁ ዐይነት ኹናቴ መኾኑን እንገነዘባለን።

## ትንቢተ ዮናስ

ይህ መጽሐፍ በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ኾኖ የነነዌ ከተማ ሰዎች በንስሓ የተመለሱ እንደኾነ እግዚአብሔር በምሕረቱ ሊያድናቸው ፈቅዶ ነቢዩ ዮናስ ለመኼድና ለማስተማር ያልፈለገ መኾኑ ቢነገርም ሳይወድ በግድ ኼዶ እንዲያስተምር የተደረገና ለነነዌ ከተማ ሰዎችም ምሕረት የተደረገላቸው መኾኑ ተነግሮአል።

## ጥያቄና መልስ

127 በትንቢተ ዮናስ ም.2 ቍ:1 "ዮናስም ሦስት ቀንና ሶስት ሌሊት በዓሣው ሆድ ውስጥ ኖረ" የሚለውን ታሪክ በምሳሌነት ወስዶ መድኀኒታችን በማቴዎስ ወንጌል ም.12 ቍ:40 ላይ እንዲሁም የሰው ልጅ በከርሠ መቃብር ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል ብሏል።



መድኀኒታችን በከርሠ መቃብር የቈየው ከዓርብ ማታ ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ማታ ለእሑድ አጥቢያ እኩል ሌሊት ድረስ ብቻ መኾኑ የታወቀ ነው። በዚህም ኹናቴ በከርሠ መቃብር ውስጥ የቈየው አንድ ቀንና ኹለት ሌሊት ወይም አንድ ሌሊት ተኩል ኾኖ ሳለ እንዴት ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ተባለ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የቅዱሳት መጻሕፍትን አባባሎች ለመረዳት እንድንችል ከሚረዱን ኹናቴዎች መካከል የጊዜው ያነጋገር ልማዶች ይገኙባቸዋል። በዚህም መሠረት ለምሳሌ በኦሪት ዘፍጥረት ም.42 ቍ:17 ላይ ዮሴፍ ወንድሞቹን ለሦስት ቀን አሰራቸው ካለ በኋላ በቍ:18 – 19 ደግሞ በሦስተኛው ቀን እንደፈታቸው ተነግሮአል።

በኹለተኛው ዜና መዋዕል ም.10 ቍ:5 ላይ ሮብዓም ሕዝቡን ወደ እርሱ እንዲመለሱ የነገራቸው ከሦስት ቀን በኋላ ሲኾን በቍ:12 ላይ እንደተገለጸው የተመለሱት በሦስተኛው ቀን ነው።

በመጽሐፈ አስቴር ም.4 ቍ:16 ላይ ንግሥት አስቴር እርስዋና ወገኖችዋ አይሁድ የሦስት ቀንና የሦስት ሌሊት ጾም እንዲጾሙ ካወጀች በኋላ በሦስተኛው ቀን ንጉሡንና ባለሟሉን የጋበዘችበት ድግስ ማዘጋጀትዋ በምዕራፍ 5 ላይ ተዘርዝሮ ተገልጾአል።

ክፍልፋይ ቁጥሮችን በሙሉ በቍጥር አጠጋግቶ መናገር የተለመደ በመኾኑ ዮሴፍ ወንድሞቹን ለሦስት ቀን አሰራቸው የተባለው በሦስተኛው ቀን ተፈትተዋል።

ሮብዓም ከሦስት ቀን በኋላ የሰጠው ቀጠሮ በሦስተኛው ቀን ተከናውኖአል።

አስቴር ያወጀችው የሦስት ቀን ጾም በሦስተኛው ቀን ግን ተደግሶበታል።

በዚሁም ዓይነት ስለጌታ የተነገረው ሦስት ቀን ዓርብና ቅዳሜ ኹለት ቀኖች ሲኾኑ እሑድ የተነሣበት ቀን በመኾኑ ሦስተኛ ቀን ተብሏል። ዓርብ ከሰዓት በኋላ ጀምሮ አንድ ቀን፥ ቅዳሜ ኹለተኛ ቀን፥ ለእ



www.ethiopianorthodox.org

ሑድ አጥቢያ ሌሊት ሦስተኛ ቀን መኾኑ ነው። ጌታም ለደቀ መዛ ርቱ በገለጸላቸው አገላለጽ ወደ ኢየሩሳሌም የሚኼድ፥ ከሽማግሌዎች ከካህናት አለቆችና ከጸሐፊዎች ብዙ ሕማም የሚደርስበት፥ የሚገደል በሦስተኛውም ቀን ከሞት የሚነሣ መኾኑን በማቴዎስ ወንጌል ም.16 ቍ:21 ፥ ም.20 ቍ:18 — 19፥ ማር. ም.9 ቍ:31፥ ም.10 ቍ:33 - 34፥ ሉቃ. ም.9 ቍ:22፥ ም.18 ቍ:31 — 33፥ ም.24 ቍ:6 — 7 ዘ ዝሮ አስረድቷቸዋል።

ስለዚህ ሦስተኛ ቀን የተባለው አባባል ከዓርብ ጀምሮ ሲቈጠር ሦስተኛ ቀን ስለሚኾን ምንም ስሕተት የሌለበት መኾኑ ግልጽ ነው። ምንም እንኳ ከዓርብ እስከ እሁድ ያሉት ቀኖች ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ባይኾኑ በተለምዶ አነጋገር ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት የሚባል ስም የተሰጣቸው በመኾኑ እንደ ስሕተት መቈጠር የለበትም። ስለዮናስም በተነገረው አባባል ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ከማለቱ በቀር መቼ ዓሣው እንደዋጠውና መቼ ደግሞ እንደተፋው በዝርዝር ስላልተገለጸ ምናልባት የጊዜው ርዝመት ከጌታ ሞትና ትንሣኤ ጋር እኩል ሊኾን ይችል ይኾ ናል። ይህ ከኾነ ደግሞ ባህላዊና ልማዳዊ አነጋገር በመኾኑ አባባሉ ስሕ ተት የሌለበትና ከጌታ አባባል ጋር ተመሳሳይ ነው ማለት ነው።

## ትንቢተ ሚክያስ

ይህ መጽሐፍ በሰባት ምዕራፎች የተከፋፈለ ኾኖ በሰማርያ ስለሚደርስ ችግር የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር ሕግ ባለመታዘዙ ወደፊት ስለሚደርስበት ችግርና ክርስቶስ ሲመጣ በዓለም ላይ ሊሰፍን ስላለው ሰላም ትንቢት ተነግሮበታል።

## ጥያቄና መልስ

128. በትንቢተ ሚክያስ ም.3 ቍ: 1 - 4 ላይ "እናንተ የእስራኤል ሕዝብ መሪዎች ይህን አድምጡ ትክክለኛ ፍርድን ማወቅ ይገባችሁ አልነበ ረምን? እናንተ ግን መልካሙን ጠልታችሁ ክፉውን ወደዳችሁ፤



ሕዝቤን በቁመናቸው ቆዳቸውን ገፈፋችሁ፤ ሥጋቸውንም ከአጥንታቸው ለያችሁ፤ የሕዝቤን ቆዳ ገፈፋችሁ፤ ሥጋቸውንም ቅርጥፍ አድርጋችሁ በላችሁ፤ አጥንታቸውንም ሰባብራችሁ በማሰሮ እንደሚቀቀል ሥጋ ቈራረጣችኋቸው፤ እናንተም ተጨንቃችሁ ወደ እግዚአብሔር የምት ጮኹበት ጊዜ ይመጣል፤ ነገር ግን እርሱ አይመልስላችሁም፤ ክፉ ሥራ ስለሠራችሁ ልመናችሁ አይሰማም» ካለ በኋላ በም.7 ቍ:18 - 19 ላይ ደግሞ "እግዚአብሔር ኀጢአትን የሚደመስስና ከመከራ የተረፉትን ወገኖቹን በደል ይቅር የሚል አንተን የሚመስል አምላክ የለም፤ ዘላለማዊ ፍቅርህን ለእኛ ለማሳየት ስለምትደሰት ቁጣህ ብዙ ጊዜ አይቆ ይም። እንደገና ምሕረት ታደርግልናለህ፤ በእግርህ ሥር ኀጢአታ ችንን ረግጠህ ወደ ጥልቅ ባሕር ትጥለዋልህ በማለቱ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።

እግዚአብሔር የሰውን ጸሎት የሚቀበል መኾኑ በተለያዩ ጊዜያት ተገልጾአል። ይሁን እንጂ የሕዝብ መሪዎች በኾኑ ሰዎች ላይ እግዚአ ብሔር የተለየ አስተያየት አለው። ለምሳሌ ሙሴ በመሪባ ውሃ ጉዳይ እግዚአብሔርን ቅር ካሰኘ በኋላ ምንም እንኳ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ቢለምን ይቅርታ ሳይደረግለት ቀርቶ ወደተስፋ ምድር ከመ ግባቱ በፊት እንዲሞት ተደርጓል። ሳኦል ከአማሌቃውያን ጋር ባደረገው ጦርነት የእ ግዚአብሔን ትእዛዝ በማፍረሱ ይቅርታ እንኳ ቢለምን ይቅርታ አልተደረገለትም። እግዚአብሔር አንድን ሰው ከሕዝብ መካከል መርጦ መሪ ካደረገው በኋላ ከማንኛውም ተራ ሰው ይልቅ ከዚያ ከሕዝብ መሪ ላይ የበለጠ ይጠብቅበታል። ብዙ ከተሰጠው ላይ ብዙ የሚጠብቅ በመኾኑ አንድ መሪ ጥፋትም በሚያጠፋበት ጊዜ ቅጣቱ ከፍተኛ ይኾናል። (ተራ.ቍ:83 ተመልከት)

ስለዚህም በመጀመሪያ የተጠቀሰው ጥቅስ ስለሕዝብ መሪዎች የተነገረ ሲኾን ኹለተኛው ጥቅስ ግን ለኹሉ የተነረ ነው እንጂ ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ኾነው አይደለም።



www.ethiopianorthodox.org

## ትንቢተ ናሆም

ይህ መጽሐፍ ሦስት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ የይሁዳ ሕዝብ ከአሦራውያን እጅ ነጻ እንደሚወጣና ስለ ነነዌ ጥፋት ትንቢት ተነ ግሮ በታል።

### ጥያቄና መልስ

129. በትንቢተ ናሆም ም.1 ቍ:12 እና 15 ላይ "ሕዝቤ ሆይ፥ ምንም እንኳ ከዚህ በፊት መከራ ያጸናሁባችሁ ቢኾንም ከእንግዲህ ወዲህ አላደርግባችሁም። የይሁዳ ሕዝብ ሆይ፥ ክፉዎች ጠላቶችህ ፈጽሞ ስለ ተደመሰሱ ከእንግዲህ አገርህን ከቶ አይወሩአትም፤ ስለዚህ ዓመት በዓሎችህን በደስታ አክብር፥ ስእለትህንም ለእግዚአብሔር ስጥ።"

የእስራኤል ሕዝብ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ስደትና መከራ ተለይቶት የማያውቅ እንደመኾኑ ከእንግዲህ ወዲህ መከራ አላጸናባችሁም የሚለው አባባል እንዴት ትክክል ሊኾን ይችላል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

አንድ ማወቅ የሚኖርብን ጉዳይ እግዚአብሔር የሚሰጣቸው ተስፋዎች አብዛኛውን ጊዜ ከግዴታ ጋር የተያያዙ መኾናቸውን ነው።

ለምሳሌ በመጽሐፈ መዝሙር 132 ቍ:11 እና 12 ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን ሲገባ: "ከልጆችህ አንዱን አነግሥዋለሁ" ካለ በኋላ "ልጆችህ ቃል ኪዳኔንና የምሰጣቸውን ትእዛዝ ከጠበቁ ልጆቻቸው ከአንተ በኋላ ለዘላለም ይነግሣሉ" ብሎታል። እንደ ሚታወቀውም የዳዊት የልጅ ልጆች የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስላላከበሩ መንግሥታቸው ፈርሶአል። በዚሁም ዐይነት ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ ላይ ከእንግዲህ ወዲያ የተባለው በእግዚአብሔር ትእዛዛት ጸንተው የኖሩ እንደኾነ ማለት ነውና ሊያስገርመን አይገባም።



## ትንቢተ ዕንባቆም

ይህ መጽሐፍ ሦስት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ የአይሁድ ሕዝብ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ባለመፈጸሙ ሊደርስበት ስላለው ችግር ከለዳውያን በሚገዙአቸው ሕዝብ ላይ ባደረሱት ግፍ ምክንያት የሚደርስባቸው ቅጣትና እንዲሁም አምላክ ለሕዝቡ ይቅርታ ያደርግ ዘንድ ነቢዩ ያደረገው ጸሎት ይገኝበታል።

### ጥያቄና መልስ

130. በትንቢተ ዕንባቆም ም.2 ቍ:5 ላይ "የሀብት ብዛት ሰውን ያታልላል፤ ለሀብት የሚስገበገቡም ሰዎች ትዕቢተኞች ናቸው፤ በአንድ ስፍራም ዐርፈው አይቀመጡም፤ ሞትና መቃብር በቃኝ ማለትን አን ደማያውቁ እነርሱም በቃኝ ማለትን አያውቁም፡ መንግሥታትን የሚወርሱትና ሕዝቦችን የሚማርኩት ለዚህ ነው" ተብሎ ሰዎችን መማረክ የተነቀፈ ሲኾን ቀደም ተብሎ በኦሪት ዘዳግም ም.20 ላይ ደግሞ ሙሴ በእግዚአብሔር ስም ለእስራኤል ልጆች መመሪያ ሲሰጣ ቸው ሰዎችን በምርኮ እንዲወስዱ ነግሮአቸዋል።

በዚህ ዐይነት ኹለቱ አባባሎች እንዴት እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ኾኑ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

እግዚአብሔር የሚመለክበትን መንግሥት ለማቋቋም በሚደረገው ጉዞና ተጋድሎ እስራኤሎች እንቅፋት የሚኾኑባቸውን ወገኖች ኹሉ እንዲያጠፉ ያለዚያም ምርኮኞች እንዲያደርጉ ታዝዘዋል። ይህንንም በሚያደርጉበት ጊዜ ኹሉ የእግዚአብሔር እርዳታ አልተለያቸውም። ይህም እግዚአብሔር ለተለየ ዐላማ ያዘዘውና በእርሱ እርዳታም ጭምር የተደረገ ጦርነት እንደመኾኑ ከሌሎች ከተራ ጦርነቶች የተለየ ነው። ሌላው ዐይነት ምርኮ ግን አንዳንድ አምባ ገነን አገሮች ወይም የሀገር መሪዎች በግፍና በጭካኔ ተነሣሥተው የሌላውን ሀገር በመውረር ሕዝብን የሚማርኩበት ምርኮ ነው። ይህ የዚህ ዐይነቱ ምርኮ ነው በትንቢተ ዕንባቆም የተነቀፈው።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት ኹለት የተለያዩ የምርኮ ዐይነቶች በመኾናቸው እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

## ትንቢተ ሶፎንያስ

ይህ መጽሐፍ ሦስት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ የአይሁድ ሕዝብ በንስሓ እንዲመለስ ምክር፥ በአካባቢ ለሚገኙ ሕዝብ ማስጠንቀቂያ ፥ ስለነነዌ ጥፋትና አሕዛብ ኹሉ የክርስትና እምነት የሚቀበሉ ለመኾናቸው የተነገረ ትንቢት ነው።

### ጥያቄና መልስ

131 በትንቢተ ሶፎንያስ ም.1 ቍ.6 ላይ:- "ከእኔ የራቁትን፥ እኔን መከተል የተውትንና ወደእኔ መጥተው እኔ እንድመራቸው ያልጠየቁኝን አጠፋለሁ" የሚል ሲኾን በመጽሐፈ ሢራክ ም.15 ቍ.11–17 እንደተዘረዘረው የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ላይ በሚፈጽማቸው ድርጊቶች ኹሉ ከማንኛውም ተጽዕኖ ነጻ መኾኑን ያመለክታል። ይህም በመኾኑ ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስለን ይኾናል።

የሰው ልጅ የፈቃድና የፍላጎት ነጻነት አለው የተባለው የማይፈልገውን ድርጊት እንዲያደርግ አይገደድም ማለት ነው እንጂ በሚፈጽመው ክፉ ተግባር አይቀጣም ማለት አይደለም። ክፉ አድራጎቱ የማይጐዳው ቢኾንማ "እሳትንና ውሃን በፊትህ አኑሮልሃል፤ እጅህን ወደመረጥከው ክተት፤ ሰው በፊቱ ሕይወትና ሞት አሉለት ከኹለቱ መካከል እርሱ የመረጠው ይሰጠዋል" ባልተባለም ነበር። (ሢራ.ም.15 ቍ.17–18) ኾኖም አብዛኛውን ጊዜ ቅጣቱ የሚፈጸመው በዚህ ዓለም ሳየኾን በወዲያኛው ዓለም ነው። አልፎ አልፎ ግን አምላክ ክብሩን ለመግለጽ በሚፈልግበት ጊዜ በዚህ ዓለም ላይ ቅጣት የሚሰጥበት ጊዜ ይኖራል። በሌላ በኩል ደግሞ ሥጋዊ ፍላጎታችን መንፈሳዊ ፍላጎታችንን ሲያሸንፈው የእግዚአብሔርን እርዳታ ብንለምን ከጸላኤ ሠናይ ተጽዕኖ ያድነናል።

በዚህም መሠረት ከላይ የቀረቡት አባባሎች እርስ በርሳቸው ሚቃረኑ አይደሉም። (ጥያቄና መልስ ቍ.53 ይመለከቷል)

## ትንቢተ ሐጌ

ይህ መጽሐፍ ኹለት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ ከባቢሎን ምርኮ መልስ በኋላ የተጻፈ ነው። መጽሐፉም ስለ ቤተ መቅደስ ዕድሳት፥ የወንጌል ድል ማድረግና የዓለምን ሕዝብ ማሰባሰብ ትንቢት ይገኝበታል።

### ጥያቄና መልስ

132. በትንቢተ ሐጌ ም.1 ቍ.4 ላይ:- «ሕዝቤ ሆይ፥ የእኔ ቤት ፈርሶ ሳለ፥ እናንተ ተሸላልመው በተሠሩ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን? የሚል ሲኾን በኹለተኛው መፍሐፍ ሳሙኤል ም.7 ላይ እንደተገለጸው ዳዊት ቤተ መቅደስን ለመሥራት በጠየቀ ጊዜ እግዚአብሔር ከሰጠው መልስ መካከል እኔ እስከ ዛሬ በድንኳን ኖርኩ እንጂ በቤተ መቅደስ አልኖርኩምና ስለዚህ አንተ አትሠራልኝም ብሎታል። እንዲሁም በትንቢተ ኢሳያስ ም.66 ቍ.1 ላይ:- "ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረጋገጫ ናት፤ ታዲያ ለእኔ ምን ዓይነት ቤት ትሠሩልኛላችሁ? የማርፍበትስ ቦታ ምን ዓይነት ነው?" በማለቱ አባባሎቹ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስላል።

በመጀመሪያ ለዳዊት ቤተ መቅደሱን እንዳይሠራ እግዚአብሔር የከለከለው ቤተ መቅደስ እንዲሠራ ባለመፈለጉ ሳይኾን ዳዊት በሕይወት ዘመኑ ኹሉ በጦርነት ላይ ስነለበረና ሰላም ስላልነበረው እግዚአብሔር ለዳዊት ልጅ ለሰሎሞን የሰላም ዘመን ሰጥቶት ቤተ መቅደሱን እርሱ እንዲሠራ ስለፈቀደ ነው።

በትንቢተ ኢሳይያስ ም.66 ቍ.1 ላይ የተጠቀሰው ጥቅስ ግን የእግዚአብሔርን ውሱን አለመኾን የሚያመለክት መልእክት ነው።


www.ethiopianorthodox.org

ሰሎሞን ቤተ መቅደስን ሠርቶ ባስመረቀበት ዕለት በጸለየው ጸሎት እግዚአብሔር ያቺን ቤተ መቅደስ የተቀደሰች እንዲያደርጋትና ምእመናንም በዚያች ቤተ መቅደስ ኾነው ለሚያቀርቡት ጸሎት ኹሉ ተሰሚነትን እንዲያገኙ ተማጽኖአል። እግዚአብሔርም ለጸሎቱ መልስ ሲሰጠው እርሱና የእስራኤል ልጆች ኹሉ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ጸንተው እስከኖሩ ድረስ ስሙ በቤተ መቅደሱ እንዲኖር የቀደሰው መኾኑ ንና በቤተ መቅደስም ተገኝቶ የሚደረገው ጸሎት ተሰሚነትን እንደሚያገኝ ቃል ገብቶለታል። ይህ ግን ተግባራዊ የሚኾነው የእስራኤል ልጆች በሕገ እግዚአብሔር ጸንተው እስከኖሩ ድረስ ብቻ ነው። የእስራኤል ልጆች ከብዙ ችግርና ስደት በኋላ በንስሓ ወደፈጣሪያቸው ተመልሰው ስለነበረ ቤተ መቅደሱ እንዲታደስ በነቢዩ በሐጌ አማካይነት አስታወሳቸው። (ሐጌ ም.1 ቍ.4)

## ትንቢተ ዘካርያስ

ይህ መጽሐፍ በ14 ምዕራፎች የተከፋፈለ ኾኖ አይሁድ ከምርኮ እንደሚመለሱና ቤተ መቅደሱ እንደገና እንደሚሠራ፥ ካህንም እንደሚሾምለት፥ ስለክርስቶስ መምጣት፥ በመለኮቱ ከአብ ጋር የተካከለ መኾኑን፥ የአይሁድ ሕዝብ በሃይማኖት ረገድ የቀረበባቸው ወቀሳ፥ ስለክርስቶስም ግልጽ በኾኑ ምልክቶች ትንቢቶች ተነግረዋል።

## ጥያቄና መልስ

133. በትንቢተ ዘካርያስ ም.13 ቍ.2 እና 3 ላይ "በዚያን ጊዜ የጣዖታትን ስሞች ከምድሪቱ ላይ አስወግዳለሁ፤ ዳግመኛም የሚያስታውሳቸው አይኖርም፤ ከዚያም በኋላ ነቢይ ነኝ ብሎ የሚነሣ ቢኖር የገዛ አባትና እናቱ በእግዚአብሔር ስም ሐሰት ስለተናገርህ ሞት ይገባሃል ብለው ይፈርዱበታል፤ በድፍረት ትንቢት ለመናገር ቢሞክር የገዛ አባትና እናቱ በጦር ወግተው ይገድሉታል" በሚለው አንጻር በትንቢተ ኢዩኤል ም.2 ቍ.28 ላይ:- "ከዚህ በኋላ መንፈሴን በሰው ኹሉ ላይ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም



ሕልም ያልማሉ፤ ወጣቶቻችሁም ራእይ ያያሉ" ስለሚል ኹለቱ አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስሉን ይኾናል።

የመጀመሪያው አባባል የሚያመለክተው የአረማውያንን ጣዖት አምልኮትና ከእርሱም ጋር ተያይዘው የሚገኙትን ውሸቶች በጣዖት አምልኪዎቹ ዘንድ ትንቢት ተብለው የተሰየሙትን ሲኾን በኹለተኛው ጥቅስ ግን በበዐለ ኀምሳ ቀን ስለወረደው መንፈስ ቅዱስ የተነገረ ትንቢት ነው።

ስለዚህ ኹለቱ አባባሎች ለተለያዩ ጉዳዮች የተነገሩ ናቸው እንጂ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

## ትንቢተ ሚልክያስ

ይህ መጽሐፍ አራት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ የአይሁድ ካህናት ሥነ ሥርዓት ባለማክበራቸው፥ ሕዝቡ ደግሞ የአይሁድ ሴቶችን ትቶ አይሁድ ያልኾኑ ሴቶችን በማግባቱ መወቀሱና እንዲሁም ስለጌታ መምጣት ትንቢት ተነግሮበታል።

## ጥያቄና መልስ

134. በትንቢተ ሚልክያስ ም.4 ቍ.1 ላይ:- " የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ትዕቢተኞችና ክፉ አድራጊዎች እንደገለባ በእሳት የሚጋዩበት ቀን ቀርቦአል፤ በዚያን ጊዜ ከእነርሱ ማንም ሳይተርፍ ተቃጥለው ይጠፋሉ" በሚለውና በራእየ ዮሐንስ ምዕራፍ 14 ቍ.9–11 ላይ:- "ለአውሬና ለምስሉ የሚሰግድ፥ በግምባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ደግሞ በቁጣው ጽዋ ሳይቀላቀል ከተዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል፤ በቅዱሳንም መልእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሠቃያል፤ የሥቃያቸውም ጢስ ለዘላለም እስከዘላለም ድረስ ይወጣል፤ ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት የሚቀበሉ ኹሉ ቀንና ሌሊት



www.ethiopianorthodox.org

ዕረፍት የላቸውም" በሚለው ኹለት ጥቅሶች መካከል ልዩነት ያለ ይ
ለን ይኾናል።

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የሚቀጣባቸው ኹለት መንገዶች አ
አንዱ በዚህ ዓለም ላይ ክብሩን ለመግለጽ ወይም ወዶጆቹን ጊዜ
የአባትነት ቅጣት ለመቅጣት የሚፈቅደው ችግርና መከራ ሲኾን ኹ
ኛውና የከፋው ቅጣት ግን በሚመጣው ዓለም ኀጢአተኛን የሚቀ ጣ
ዘላለማዊ ስቃይ ነው። ይህም የገሀነመ እሳት ቅጣት ኹለተኛው ሞ
ይባላል። በትንቢተ ሚልክያስ ላይ የተገለጸው ተቃጥሎ መጥፋት ማለ
ዘላለማዊውን የገሀነመ እሳት መሠቃየት ማለት እንጂ ከመኖር ወደ አለ
ኖር መዞር ማለት አይደለም።

በዚህም መሠረት ከላይ የቀረቡት ኹለት ጥቅሶች በተለያየ አባባ
ከመቅረባቸው በቀር እርስበርባቸው የሚቃረኑ አይደሉም። (ጥያቄ
መልስ ቍ. 5 ኹለተኛ መጽሐፍ ይመለከቷል)።

## አንዳንድ ተከራካሪዎች ያልተቀበሉአቸው መጻሕፍት

ስለ እነዚህ መጻሕፍት ጉዳይ በትምህርተ መለኮት መጽሐ
የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት በሚለው ምዕራፍ ውስጥ በዝርዝር የተ
ለጸ ስለኾነ አሁን እንደገና በዚህ መጽሐፍ በድጋሚ ገለጻ ማቅረብ አስፈ
ላጊ ኾኖ ባለመገኘቱ ታልፏል። እዚህ ግን ስለአጠቃላይ ኹናቴ ብቻ
መግለጫ ይሰጣል።



## መጽሐፈ ጦቢት

ይህ መጽሐፍ ዐሥራ አራት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ ስለአንድ ሃይማኖተኛ አባት፥ ታማኝና ታዛዥ ስለኾነና የመልአክንም እርዳታ ስላገኘ ልጅ ታሪክ ሲኾን በስደት ከነበሩት አይሁዶች መካከል እንደነበረ ይገመታል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

135. በመጽሐፈ ጦቢት ም.1 ቍ.1 እና 2 ላይ ሽማግሌው ጦቢት በአሶር ንጉሥ በሰልምናሶር ዘመን የተማረከ ነው ከነገደ ንፍታሌም ኾኖ በሚልበት ጊዜ በኹለተኛው መጽሐፈ ነገሥት ም.15 ቍ.29 ላይ ደግሞ የንፍታሌምን ነገድ የማረከው ቴልጌልቴልፌልሶር ነው ስለሚል በመጽሐፈ ጦቢት የተነገረው ታሪክ ትክክል አይደለም ይባል ይኾናል።

በሁለተኛው መጽሐፈ ነገሥት ም.16 እና ም.18 ቍ.9 ላይ በግልጽ እንደተነገረው የእስራኤልን አገር ሁሉ በማጥፋት ምርኮ የተደረገው በንጉሡ በሰልምናሶር ዘመን ነው። በምዕራፍ 15 ቍ.29 ላይ የተነገረው ግን ከአሁን ቀደም ሊጠቁም እንደተሞከረው አንዳንድ የምሥራቅ አገር ነገሥታት ልጆቻቸውን ለማለማመድ አስቀድመው አብ ረዋቸው የንጉሥነቱን ሥራ ያሠሩአቸው ስለነበረ ልጁ ቴልጌል ቴልፌልሶር ነው የተባለው አንድም በዚህ ምክንያት ነው፤ ያለበለዚያም በዚያን ጊዜ አንድ ሰው በተለያዩ ስሞች መጠራቱ የተለመደ ስለነበር ቴልጌልቴልፌልሶር የሚለው ለሰልምናሶር ኹለተኛ ስሙ ሊኾን ስለሚ ችል ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒ አይደሉም።

136. በመጽሐፈ ጦቢት ም.3 ቍ.8 ላይ የራጉኤል ልጅ ሳራ ሰባት ባሎች አግብታ ከሰባቱ አንዳቸው እንኳን እንደባልና ሚስት አብረው ሳይተኙ ሰባቱንም አስሞዳዮስ የተባለ ሰይጣን እንደገደላቸው ተገልጾአ ል። ርኩሳን መናፍስት እንዴት አድርገው ነው የሰውን ነፍስና ሥጋ ለማለያየት ሥልጣን ወይም ችሎታ ያገኙት ተብሎ ይጠየቅ ይኾና ል።



www.ethiopianorthodox.org

ሰይጣንም ኾነ ማንኛውም ሌላ ፍጡር ከእግዚአብሔር ካልተፈቀደለት በቀር በማንምና በምንም ላይ ምንም ለማድረግ ሥልጣንም ኾነ ችሎታ የለውም። እግዚአብሔር ሲፈቀድላቸው ግን በቅዱሳት መጻሕፍት በልዩ ልዩ ቦታዎች እንደተገለጸው ርኩሳን መናፍስት ተመሳሳይ ችሎታዎች እንደነበሩአቸው ተገልጾአል።

ይህንንም አባባል ግልጽ ከሚያደርጉት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ምሳሌዎች ይገኙባቸዋል።

በማቴዎስ ወንጌል ም.8 ቍ.32 ላይ እንደተገለጸው ዕሪያዎቹን የገደሉ ርኩሳን መናፍስት ናቸው።

በማቴዎስ ወንጌል ም.9 ቍ.32 ላይ አንዱን ሰው ድዳ ያደረገው ጋኔን መኾኑ ተገልጾአል።

በማቴዎስ ወንጌል ም.17 ቍ.15 ላይ ጋኔን እንዴት አድርጎ ሰውን ወደ እሳትና ወደ ውሃ የሚጥል መኾኑን መመልከት ይቻላል።

በዮሐንስ ወንጌል ም.8 ቍ.44 ላይ ሰይጣን ነፍሰ ገዳይ ነው ተብሏል።

ከላይ በተዘረዘሩት ልዩ ልዩ ማስረጃዎች መሠረት ርኩሳን መናፍስት ሰውን ለመጉዳት ሥልጣን እንዳላቸው እንገነዘባለን። ይሁን እንጂ ያንን ሥልጣን የሚያገኙት እግዚአብሔር ሲፈቅድላቸው ነው እንጂ በራሳቸው ኀይል አይደለም። ከፉዎችን ለመቅጣትና ደጋጎችን ደግሞ ለማስተማር ሲባል ነው ሰይጣን በሰዎች ላይ ችግርን እንዲያደርስ የሚፈቀድለት። ለምሳሌ ሰይጣን በጻድቁ በኢዮብ ላይ ያን ኹሉ ችግር እንዲያደርስ የተፈቀደለት የኢዮብን ታማኝነት ለማሳየት እና በታጋሽነቱም ለሰው ኹሉ ምሳሌ እንዲኾን ስለተፈለገ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በሐዋርያት ሥራ ም.19 ቍ.16 መሠረት ርኩስ መንፈስ በሊቀ ካህናቱ በአስቄዋ ልጆች ላይ አይሎባቸው እያነቀ ያቆሰላቸው የጌታን ስም በእምነት ሳይኾን በአስማት መልክ ሊጠቀሙበት ስለፈለጉ ነው።

አሁን እንግዲህ ምናልባት እነዚያ ሰባቱ የሳራ እጮኛዎች በሞት እንዲቀጡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ኾኖ ይኾናል። በዚህም ምክንያት


www.ethiopianorthodox.org

ለጦቢያ ሚስት እንድትኾን የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደኾነ ይገመታል። ለዚህም ማስረጃ የሚኾነው በምዕራፍ 6 ቍ.18 ላይ መልአኩ ሩፋኤል ለጦቢያ ሲነግረው "አትፍራ ሳራ ከቀድሞ ጀምራ ለአንተ እንድትኾን የተወሰነች ነች፤" ብሎ መናገሩ ነው።

137. በመጽሐፈ ጦቢት ም.6 ቍ.17 ላይ በተነገረው መሠረት የዓሣውን ልብና ጉበት በዕጣን በማጤስ ሰይጣንን ለማባረር መሞከር የጥንቈላ ሥራ በመኾኑ ይህንን በታሪክ የሚያቀርበውን መጽሐፍ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ተጻፈ ለማለት አስቸጋሪ ከመኾኑም በላይ የዚህ የጥንቈላ ሥራ አሠራር አዘጋጅና መካሪ የኾነውን ሰው ደግሞ የእግዚአብሔር መልአክ ነው ለማለት የማይመስል ጉዳይ ነው ተብሎ ይተች ይኾናል።

መጽሐፉ በጥንቈላ የሚያምን ሳይኾን በምዕራፍ 8 ቍ.1–3 የተደረገውን ገለጸ ብንመለከት ሰይጣኑን አባርሮ ይዞ ያሠረው መልአኩ ሩፋኤል ነው እንጂ የተጤሰው መድኀኒት አይደለም። መልአኩ ግን ለጦቢያ ያንን የተጠቀሰውን ዘዴ የመከረበት ምክንያት በጊዜው የነበረውን አስተሳሰብ በቀላሉ ለማስወገድ ስለማይቻል ማለት እርሱም እንደቀድሞዎቹ ሰባት የሳራ እጮኛዎች ሰይጣን ይገድለኛል ብሎ ስለ ሚፈራና ሩፋኤል ደግሞ ሊረዳው የሚችል መልአክ መኾኑን ገና ያልገለጸለት ስለነበረ እና አስተሳሰቡም ውሱን በመኾኑ መድኀኒት በማስመሰል ማግባባት ስለነበረበት ነው።

ያልኾነ አስተሳሰብን በማሰብ የታመሙ ሰዎች ሊድኑ የሚችሉት አስተሳሰባቸውን ለመለወጥ የሚቻልበት ዘዴ ሲገኝ ብቻ መኾኑ የታወቀ ነው። ለምሳሌ የኢያሪኮ ከተማ ግንብ በአንድ ቀን መፍረስ ሲችል ሰባት ቀኖች መዞር ያስፈለገው ለእስራኤላውያን አስተሳሰብ ሲባል ብቻ ነው። (ተራ ቍጥር 55 ተመልከት)

ሳአል ነፍሳትን ለመጥራት ትችላለች ብሎ ባመነባት ባልተለመደ ዘዴ ሳሙኤል ተገልጾለት ኀጢአቱንና ወደፊት የሚኾነውን ኹናቴ እንዲነግረው አምላክ የፈቀደ ከኾነ የወጣቱን የጦቢያን አስተሳሰብ ለማስተካከል መልአኩ ሩፋኤል የተጠቀመበት ዘዴ የሚያስገርም አይደ ለም።

## መጽሐፈ ዮዲት

ይህ መጽሐፍ ዐሥራ ስድስት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ የናቡከደነፆር ጦር መሪ ሆሎፎርኒስን ራሱን ቈርጣ በመግደል ዮዲት የተባለች ሴት እንዴት አድርጋ የኢየሩሳሌምን ከተማ እንዳዳነች የሚናገር ታሪክ ነው። ጸሐፊው በስደት ከነበሩት አይሁዶች መካከል ነው።

### ጥያቄና መልስ

138. በዮዲት መጽሐፍ ውስጥ የተመለከተው የውሸታምነት የአታላይነትና የነፍሰ ገዳይነት ታሪክ እንደመኾኑ እንዴት ይህ መጽሐፍ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈ ነው ብለን ከሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እንቈጥረዋለን ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በዮዲት አማካይነት የተፈጸመው ድርጊት ወገኖችዋን ለማዳን ካደረገችው የጦርነት ስልቶች አንዱ ነው እንጂ እንደማታለልና እንደ ነፍሰ ገዳይነት መቈጠር የለበትም። ለምሳሌ በመጽሐፈ መሳፍንት ም.3 ከቍጥር 15 እስከ 31 ብንመለከት የእስራኤል ልጆች ሞዓባውያንን ያሸነፉት ናዖድ ምሥጢር ያለው አስመስሎ የሞዓቡን ንጉሥ ዔግሎምን በብልኀት ከገደለው በኋላ ነው።

ስለዚህ ጠላትን አዛናግቶ መግደል ከጦር ስልቶቹ አንዱ ነው እንጂ እንደማታለል መቈጠር የለበትም።



## ተረፈ አስቴር

መጽሐፈ አስቴርን የተሟላ የሚያደርገው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለው ታሪክ የተጨመረበት እንደኾነ ብቻ ነው።

### ጥያቄና መልስ

139. በመጽሐፈ አስቴር ም.5 ቍ. 2 ላይ "ንጉሡም ንግሥቲቱ አስቴር በወለሉ ላይ ቆማ ባየ ጊዜ በዓይኑ ሞገስ አገኘች ንጉሡም በእጁ የነበረውን የወርቁን ዘንግ ለአስቴር ዘረጋላት፤ አስቴርም ቀርባ የዘንጉን ጫፍ ነካች" የሚል ሲኾን በተረፈ አስቴር ም.5 ቍ.1 "ንጉሡ በቁጣ ተመለከታት" ስለሚል ኹለቱ አባባሎች ለምን ተለያዩ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ኹለቱ አባባሎች ተለያይተው ሳይኾን የመጀመሪያው አባባል የጉዳዩን የመጨረሻ ውጤት የሚናገር ሲኾን ኹለተኛው አባባል ግን የድርጊቱን ዝርዝር ኹናቴ የሚገልጽ ነው።

## መጽሐፈ ጥበብ (ጥበብ ሰሎሞን)

ይህ መጽሐፍ በ19 ምዕራፎች የተከፋፈለ ኾኖ በመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ዘንድ ስለዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ማንነት የተለያዩ አስተያየቶች ተሰጥተውበታል። አንዳንዶቹ እንደሚሉት አጻጻፉ የግሪኮችን አጻጻፍ ዘዴ የተከተለ በመኾኑ የግሪክን ቋንቋ በተማረ አይሁዳዊ የተጻፈ ነው ይላሉ። የጻፈው ሰሎሞን ነው የሚሉት ሰዎች የሚያቀርቡት ማስረጃ በምዕራፍ 9 ቍ.7 እና 8 ላይ የሚገኘውን ጥቅስ ነው:- "በሕዝብህ ላይ ንጉሥ እኾንና በወንዶችና በሴቶች ልጆችህም ላይ ፈራጅ እኾን ዘንድ መርጠኸኛል። በቅዱስ ተራራህ ላይ ቤተ መቅደስን ከመጀመሪያ ባዘጋጀሃትና መኖሪያህ በኾነችው ከተማ ደግሞ መሠዊያን እሠራ ዘንድ አዝዘኸኛል። «በዚህም መሠረት ጸሐፊው ሰሎሞን ነው የሚለው አባባል ያመዝናል።



www.ethiopianorthodox.org

140. በመጽሐፈ ጥበብ ም.1 ቍ.13 ላይ ሞት የእግዚአብሔር ሥራ አይደለም፤ የሕይወት መጥፋት ለእግዚአብሔር አስደሳች አይደለም የሚል ሲኾን ቀደም ተብሎ በኦሪት ዘዳግም ም.30 ቍ.19 ላይ "በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን፥ በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ" በመባሉ ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስል ይኾናል።

በመጽሐፈ ጥበብ ም.1 ቍ.13 ላይ ከሚገኘው ጥቅስ በፊት ቍ.12 ብንመለከት "የጥፋትን ኑሮ በመኖር ሞት እንዲመጣ አታድርጉ፤ በሥራችሁም ጥፋትን አትጋብዙ" ካለ በኋላ ነው " ሞት የእግዚአብሔር ሥራ አይደለም" ያለው። በልዩ ልዩ ኹናቴዎች ተመላልሶ እንደ ተገለጸው ማነኛውም ድርጊት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አይፈጸምም ወይም አይደርስም። ይህን ማለት ግን ክፉ ኹናቴ እንዲደርስ የእግዚአብሔር ፍላጎት ነው ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ለኛ የፈቃድ፣ የፍላጐትና የምርጫ ነጻነትን ሰጥቶናል። ይኹን እንጂ ማንም ሰው እንዲጠፋ ባለመፈለጉ አስቀድሞ ያስጠነቅቀናል። ለምሳሌ አዳምና ሔዋንን ዕፀ በለስን እንዳይበሉና እንዳይሞቱ አስጠንቅቆአቸው ነበር፤ ነገር ግን መብላት ስለመረጡ የሞቱ ፍርድ ጸንቶባቸዋል። ታዲያ እዚህ ላይ የሞቱን ፍርድ በራሳቸው ላይ ያመጡት እነሱው ራሳቸው ናቸው ወይስ እግዚአብሔር ነው? በዚሁም ዐይነት በገዛ ሥራችን ሞትንና ፈተናን እንጋብዛለን እንጂ ያ ሞትና ወይም ፈተና እንዲመጣ የእግዚአብሔር ፍላጎት ኾኖ አይደለም። ይህንኑ አባባል ሲያብራራ ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ ም.1 ቍ.13–14 "ሰው በሚፈተንበት ጊዜ እግዚአብሔር ፈተነኝ አይበል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በክፉ ነገር አይፈተንም፤ እንዲያውም እርሱ ማንንም አይፈትንም፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው የሚፈተነው በገዛ ራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው" ብሏል።

በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ሰውን የማዳን ፍላጎትና ሰዎች ግን በገዛ ሥራቸው ወደጥፋት የሚኼዱ መኾናቸውን የሚያመለክተውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባባል እንመልከት:- "ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ ኢየሩሳሌም፥ ኢየሩሳሌም ሆይ፥ አንቺ ነቢያትን



የምትገድዪ ወደ አንቺ የተላኩትንም በድንጋይ የምትወግሪ፥ ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ ሥር እንደምትሰበስብ፥ እኔም የአንቺን ልጆች ለመሰብሰብ ስንት ጊዜ ወደድሁ እናንተ ግን አልፈለጋችሁም።" (ማቴ. ም.23 ቍ.37)

ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሰው ኹሉ ይድን ዘንድ ፍላጎቱ ቢኾን በሰው ድርጊት ውስጥ ገብቶ ማንም ሰው ያልፈለገውን ድርጊት እንዲያደርግ የማያስገድደው መኾኑን ነው። ጥያ ቄና መልስ ቍ.113፥114፥118፥120 እና ከኹለተኛው መጽሐፍ ቍ.92 ይመለከቷል።

141. በመጽሐፈ ጥበብ ም.11 ቍ.11–12:- "እነዚህን እስራኤልን እንደሚቀጣ አባት መከርካቸው። እኒህን ግብጻውያንን ግን ርኅራኄ እንደሌለው ንጉሥ ተከትለህ በረበርህ፤ በዚህ ርኅራኄ በሌለው ንጉሥ እንደሌለው ንጉሥ ተከትለህ በረበርህ፤ በዚህ ርኅራኄ በሌለው ንጉሥ" ካለ በኋላ በቍ.24፥25 እና 27 ላይ:- "አንተ እምሳል አጠፋኻቸው» ካለ በኋላ በቍ.24፥25 እና 27 ላይ:- "አንተ

የግብጾችና የእስራኤሎች ኹኔታ የተለያየ ነው እንጂ እግዚአብሔር ግብጻውያንን በመጥላትና እስራኤላውያንን በመውደድ ከዘር ዘር የሚለይ ኾኖም አይደለም።

እግዚአብሔር በአንድ ሕዝብ ላይ ቅጣት ከማምጣቱ በፊት በመልአክተኞቹ አማካይነት አስቀድሞ ያስጠነቅቀዋል። በዚህም መሠረት ምንም እንኳ እግዚአብሔር በግብጾች ላይ ዘጠኝ የተለያዩ መቅሰፍቶችንና ታምራትን በማሳየት እስራኤሎችን እንዲለቅ በሙሴና በአሮን አማካይነት ቢያስጠነቅቀውም ፈርዖን የእግዚአብሔርን ማስጠ ንቀቂያ ባለመቀበሉ ኀይለኛ ቅጣት እንዲደርስበት ተደርጓል። እስራኤሎች ግን በግብጾች ተጨቍነው ብዙ ችግር ደርሶባቸው ነበር። ኾኖም አንዳንድ ጊዜ በሚፈጽሙአቸው ጥፋቶች መጠነኛ ቅጣት "ቃሉን እስማ ዘንድ ደርሶባቸዋል። በእነርሱ ላይ የደረሰው ቅጣት



www.ethiopianorthodox.org

እስራኤልንስ እለቅቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማን ነው? እግዚአብሔር
አላውቅም እስራኤልንም ደግሞ አልለቅም" ካለው ከፈርዖን ቅጣ
የተለየ ነው። (ዘጸ.ም.5 ቊ.2)

እስራኤሎች በደረሰባቸው ጭቈና ወደ እግዚአብሔር ጩኸታቸ
ውን በሚያሰሙበት ጊዜ ግብጾች ግን እግዚአብሔርን አናውቅም በማለት
የድፍረት ንግግር ይናገሩ የነበሩ ናቸው። በኹለቱ ዘሮች መካከል በነበረ
ው ጨቋኝነትና ተጨቋኝነት እግዚአብሔር ፍርዱን በሚሰጥበት ጊዜ
አንዱ ወገን የእግዚአብሔርን እርዳታ የሚለምን ሲኾን ሌላው ወገን ግን
እግዚአብሔርን አላውቅም ብሎ በኀጢያቱ ለመኖር የመረጠ ነው።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር በፍጥረቱ መካከል ለዩነት ባያደርግ
ከጥፋቱ በማይመለሰው ወገን ላይ ተገቢውን ቅጣት በሚሰጥበት ጊዜ
ርኅራኄ እንደሌለው ንጉሥ ተብሎ የተነገረው ሰው በሚገባው ቋንቋ
ለመግለጽ ነው እንጂ እግዚአብሔር እንደሰው ጨካኝ ኾኖ አይደለም።
ዐሥር የተለያዩ ቅጣቶችን እስኪያመጣባቸው ድረስ እግዚአብሔር
መታገሡ ግብጾች በንስሓ እንዲመለሱና ይቅርታ እንዲያደግላቸው
ስለፈቀደ ነው እንጂ የመጨረሻውን ቅጣት ቀደም ብሎ ሊያመጣባቸው
ምንም ባልተሳነው ነበር። ይህም የሚያመለክተው ማነኛውም ሰው ቢኾን
እንዲድን እንጂ እንዳይጠፋ የእግዚአብሔር ፈቃድ መኾኑን ነው።

## መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ሲራክ

ይህ የጥበብ መጀመሪያ መጽሐፍ በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈ ኾኖ
በጸሐፊው የልጅ ልጅ ወደ ግሪክ ቋንቋ የተተረጐመ ነው። መጽሐፉም
51 ምዕራፎች አሉት።



## ጥያቄና መልስ

2. በመጽሐፈ ሲራክ ምዕራፍ 12 ቊ.4 ላይ:- "ምጽዋትህን ለደጋግ
ች እንጂ ለኀጢአተኞች አትስጥ" የሚል ሲኾን በማቴዎስ ወንጌል
5 ቊ.44 ላይ :- "ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሙአችሁንም
ርቁ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፤ ስለሚያሳድዱአችሁም
ዩ" በመባሉ ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስለን ይኾ
ል።

በመጽሐፈ ሲራክ የተጠቀሰው ለኀጢአተኛ አለመስጠት ጉዳይ
ሚያመለክተው ምጽዋት የሚሰጠው ኀጢአተኛ በጣም ወንጀለኛ ሰው
ኾንና በተሰጠው ስጦታ ተጠናክሮ ክፉ ሥራውን የሚያጠናክር
ኾኑን ነው። ይኸውም አባባል በዚሁ በምዕራፍ 12 ቊ.5 ላይ
ያብራራው እንዲህ ብሏል:- ትሑቶች ለኾኑ ሰዎች በጎ አድራጎትን
ድርግ፤ ለመናፍቆች ግን አስትጥ፤ በምትሰጠው ዳቦ እንዳይጠናከርብህ
ኀጢአተኛ አትስጠው፤ ምክንያቱም ባደረግህለት በጎ ተግባር እጥፍ
ፉ መልስ ይሰጥሃል።

ምንም እንኳ ለኹሉም በጎ እንድናደርግ ብንታዘዝ፤ በተለየ ግን
እምነት ወገኖች የተለየ አስተያየት እንዲኖረን ሲያመለክት ሐዋርያው
ውሎስ እንዲህ ብሏል:- "አጋጣሚ ጊዜ ካገኘን ለሰዎች ኹሉ ይልቁንም
ሚያምኑ ቤተ ሰዎች መልካም ነገርን እናድርግ።" (ገላ.ም.6 ቊ.10)

ስለዚህ የመጀመሪያው ጥቅስ የሚያመለክተው ወንጀለኞችን
በመርዳት እንዳናጠናክራቸው ሲኾን ኹለተኛው ጥቅስ ግን ለኹሉም
መልካም እንድናደርግ ነው። የወንጀለኛ ተጠናክሮ ወንጀሉን ማባባስ
ጉዳይ በኹለተኛው ጥቅስ ውስጥ ስለሌለ፥ በዚህም መሠረት ኹለቱ
አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።



www.ethiopianorthodox.org

# ተረፈ ዳንኤል

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሦስቱ ወጣቶች በሚነድድ እሳት ው
ኾነው የዘመሩትን መዝሙር፥ የሶስና ታሪክና፥ እንዲሁም ስለአም
ጣዖት የሚዘረዝረው ታሪክ ይገኝበታል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

143. በተረፈ ዳንኤል ም.13 ቍ.45 ላይ እንደተገለጸው ፍርዱ
ለማካኼድ የፍርዱን ይግባኝ የተረከበው ዳንኤል የተባለው ወጣት ነ
ተብሎአል። እርሱም አስቀድሞ ጉዳዩን ሳያጣራና ለተከሳሾችም የመል
ዕድል ሳይሰጥ በቍ.55 እና በቍ.59 መሠረት ባሳለፈው ፍርድ ሕዝ
መስማማቱ ቀደም ብለው ኹለቱ ሰዎች በሶስና ላይ ካሳለፉት ፍርድ
ምንም ልዩነት የሌለው እንደ መኾኑ የሕዝቡን ሐሳበ ቢስነትና አር
አለማስተዋልእንዲሁምበስሜትብቻ የሚመራ መኾኑን ያመለክታል ይባ
ይኾናል።

በቍ.44 እና 45 ላይ የተመለከትን እንደኾነ :- "ይገድሏት ዘን
ሲወስዷት እግዚአብሔር ጩኸትዋን ሰምቶ ዳንኤል ተብሎ ወደሚጠራ
ወጣት ልቡና መንፈስ ቅዱስን ላከ" ተብሎ እናገኛለን። በዚህም መሠረት
ዳንኤል በኹለቱ ውሸታሞች ከሳሾች ላይ የሞት ፍርድን ያስተላለፈው
በኹለት መንገድ ነው። አንደኛው መንገድ ትንቢት ነው። ይኸውም
የኹለቱን ሽማግሌዎች ተንኰልና የሶስናን በሐሰት መከሰስ በተመለከተ
ጊዜ በወጣቱ በዳንኤል አድሮ በሶስና ላይ የተላለፈው ፍርድ ቀርቶ በሐሰ
ተኞች ከሳሾች ላይ እንዲተላለፍ እግዚአብሔር ዳንኤልን መሣሪያ ማድ
ረጉ ነው። ለዚህም አባባል ምሳሌዎች የሚኾኑት የሚከተሉት ጥቅሶች
ናቸው።

በአንደኛ ነገሥት ም.22 ቍ.28 ላይ ነቢዩ ሚክያስ በአክአብ ላይ
የሞት ፍርድ ፈርዶአል።



በኹለተኛው ነገሥት ም.7 ቍ.2 ላይ የንጉሡ የቅርብ ባለሟል ነቢዩ በኤልሣዕ በተነገረው ትንቢት ስላላገጠ የሞት ፍርድ ፈርዶ ታል። ( ቍ.17)

በትንቢተ ኤርምያስ ም.28 ቍ.16 ላይ ሐናንያ የሐሰት ትንቢት መናገሩ ነቢዩ ኤርምያስ የሞት ፍርድ ፈርዶበታል።

ኹለተኛው መንገድ ደግሞ በኹለቱ ምስክሮች የተለያየ ቃል አማካይነት ሶስና በክሱ ነጻ መኾንዋን ያመለከተው ዘዴ ነው።

በዚህም መሠረት የተላለፈው ውሳኔ በትክክል ስለኾነ በስሜት እንደተላለፈ ኾኖ መቈጠር የለበትም።

144. በትንቢተ ዳንኤል ም.13 ቍ.55 እና 59 ላይ ነቢዩ ዳንኤል መላልሶ እንደተናገረው የእግዚአብሔር መልአክ ኹለቱን ሽማግሌዎች በሰይፍ የሚገድላቸው መኾኑ የተገለጸ ሲኾን እነርሱን ግን የገደላቸው ሕዝብ በድንጋይ ወግሮ ነው። (ቍ.61 እና 62)

እግዚአብሔር ወይም መልአክ ገደላቸው የሚለው አባባል ትእዛዙ የተላለፈበትንና ምክንያት የኾነውን ሲያመለክት ነው።

ለምሳሌ በትንቢተ ሕዝቅኤል ም.25 ቍ.16 እና በትንቢተ ሶፎንያስ ም.2 ቍ.5 ላይ እግዚአብሔር ፍልስጥኤምን እንደሚያጠፋ፥ በትንቢተ ናሆም ም.2 ቍ.13 እና በምዕራፍ 3 ቍ.5 ላይ ነነዌን እንደ ሚያፈርስ ተነግሮአል። ይህም አባባል በእግዚአብሔር ውሳኔና በእርሱ ፈቃድ በጠላቶቻቸው አማካይነት ከመፍረሳቸው በቀር ሌላ ትርጉም የለ ውም። በዚህም መሠረት መላክ ገደላቸው በመባልና የሕዝቡ በግድያ ላይ መሠማራት ልዩነት የለውም።



www.ethiopianorthodox.org

## ትንቢተ ባሮክ

ይህ መጽሐፍ ስድስት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በባቢሎንም ርኮ
ስላሉት አይሁዶች ስለንስሓ ጸሎት አይሁዶችን የሚቀሰቅስና እንዲ
የነቢዩ ኤርምያስ መልእክት ይገኝበታል።

## አንደኛና ኹለተኛ መጽሐፈ መቃብያን

አንደኛው መጽሐፈ መቃብያን 16 ምዕራፎችን ያየዘ ኾኖ ይ
መቃብዮስና ወንድሞቹ የአይሁድን ሃይማኖታዊ ሕግና ሥነ ሥር
ለመጠበቅ ሲባል ከሌሎች መንግሥታት ጋር ያደረጉትን ተጋድ
የሚናገር ታሪክ ነው። ኹለተኛው መጽሐፍ ደግሞ በ15 ምዕራ
ተከፋፍሎ የመጀመሪያው መጽሐፍ ተከታይ ሲኾን በተለየም በግ
የሚኖሩ አይሁዶች በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ላይ ይደርሳል ብለው
ሚፈሩት አደጋ ዘርዝሮ የሚያስረዳ ነው። እነዚህ አንደኛና ኹለተኛ መ
ሐፈ መቃብያን ተብለው የተጠቀሱት መጻሕፈት በትልቁ የአማርኛ መ
ሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ መጽሐፈ መቃብ
የተለዩ ናቸው። የታሪኩም ይዘት የተለየ ነው።

## የይሁዳ ንጉሥ የምናሴ ጸሎት

በኹለተኛ ዜና መዋዕል ም.33 ቍ.19 መሠረት ንጉሥ ምና
በባቢሎን ምርኮኛ በነበረ ጊዜ የጸለየው ጸሎት ነው።



# ፍኖተ ብርሃን

2ኛ መጽሐፍ (ሐዲስ ኪዳን)

አዘጋጅቶ ያቀረበው
ዓሥራት ገብረ ማርያም

አዲስ አበባ
1986 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

ማውጫ

መግቢያ ........................................................ 6
የማቴዎስ ወንጌል ................................................ 9
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው .......................................... 9
የማርቆስ ወንጌል ................................................ 91
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው .......................................... 92
የሉቃስ ወንጌል .................................................. 95
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው .......................................... 96
የዮሐንስ ወንጌል ................................................ 106
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው .......................................... 107
የአራቱ ወንጌሎች ስምምነትና ልዩነት ................................ 119
የሐዋርያት ሥራ .................................................. 130
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው .......................................... 131
ወደሮሜ ሰዎች የተላከ መልእክት .................................... 133
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው .......................................... 134
ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች መጀመሪያ የተላከ መልእክት ........................ 138
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው .......................................... 139
ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላከ ኹለተኛ መልክእት ........................ 144
ጥያቄዎችና መልሶቻቸው .......................................... 145
ለገላትያ ሰዎች የተላከ መልእክት .................................. 153



www.ethiopianorthodox.org

ጥያቄና መልስ ........................................ 15

ወደ ኤፌሶን ሰዎች የተላከ መልእክት ........................................ 15

ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ........................................ 15

ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች የተላከ መልእክት ........................................ 15

ጥያቄና መልስ ........................................ 15

ወደ ቆላስያስ ሰዎች የተላከ መልእክት ........................................ 158

ጥያቄና መልስ ........................................ 159

ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የተላከ የመጀመሪያ መልክእት ........................................ 160

ጥያቄና መልስ ........................................ 161

ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የተላከ ኹለተኛ መልእክት ........................................ 162

ጥያቄና መልስ ........................................ 162

ወደ ጢሞቴዎስ የተላከ የመጀመሪያ መልእክት ........................................ 163

ጥያቄና መልስ ........................................ 164

ወደ ጢሞቴዎስ የተላከ ኹለተኛ መልእክት ........................................ 165

ጥያቄና መልስ ........................................ 165

ወደ ቲቶ የተላከ መልእክት ........................................ 166

ጥያቄና መልስ ........................................ 166

ወደ ፊልሞና የተላከ መልእክት ........................................ 167

ጥያቄና መልስ ........................................ 167

ወደ ዕብራውያን የተላከ መልእክት ........................................ 169





ጥያቄና መልስ ........................................ 170

የሐዋርያው የያዕቆብ መልእክት ........................................ 172

ጥያቄና መልስ ........................................ 172

የመጀመሪያው የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት ........................................ 173

ጥያቄና መልስ ........................................ 174

ኹለተኛው የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት ........................................ 175

ጥያቄና መልስ ........................................ 176

የመጀመሪያው የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ........................................ 177

ጥያቄና መልስ ........................................ 179

ኹለተኛው የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ........................................ 180

ጥያቄና መልስ ........................................ 180

ሦስተኛው የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ........................................ 181

ጥያቄና መልስ ........................................ 182

የይሁዳ መልእክት ........................................ 183

ጥያቄና መልስ ........................................ 183

ራእየ ዮሐንስ ........................................ 1[illegible]

ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ........................................ 185

ለጽሑፉ ድጋፍ የኾኑ መጻሕፍት ዝርዝር ........................................ 187




www.ethiopianorthodox.org

## መግቢያ

ከክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኹለተኛውና መጠኑ አነስ ያለው ክፍል ሐዲስ ኪዳን ይባላል በውስጡም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ታሪክ፥ የቤተክርስቲያ አጀማመር፥የክርስትና እምነትና በጎ ተግባር መሠረት ይገኙበታል ምንም እንኳ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጸሐፊዎች ተገናኝተው በመወያየት የሠሩ ባይኾኑም በመጻሐፋቸው ወደ መሠረታዊ የሐሳብ አንድነት መድረሳቸው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተረዱ መኾናቸውን ያመለክታል የመጻሕፍቱም አከፋፈል እንደሚከተለውነው

## የሕግና የታሪክ መጻሕፍት

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል

የታሪክ መጽሐፍ

የሐዋርያት ሥራ

## የትምህርትና የጥበብ መጻሕፍት

1. ወደ ሮሜ ሰዎች የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
2. መጀመርያ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት



3. ኹለተኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
4. ወደ ገላትያ ሰዎች የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
5. ወደ ኤፌሶን ሰዎች የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
6. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
7. ወደ ቆላስይስ ሰዎች የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
8. መጀመሪያ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
9. ኹለተኛው ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
10. መጀመሪያ ወደ ጢሞቴዎስ የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
11. ኹለተኛ ወደ ጢሞቴዎስ የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
12. ወደ ቲቶ የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
13. ወደ ፊልሞና የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
14. ወደ ዕብራውያን የተላከ መልእክት
15. የሐዋርያው የያዕቆብ መልእክት
16. የመጀመሪያው የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት
17. ኹለተኛው የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት



www.ethiopianorthodox.org

መጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት

ኹለተኛው የዮሐንስ መልእክት

ሦስተኛው የዮሐንስ መልእክት

የይሁዳ መልእክት

የትንቢት መጽሐፍ

ራእየ ዮሐንስ



# የማቴዎስ ወንጌል

ይህ ወንጌል 28 ምዕራፎች አሉት። በጽሑፉ ውስጥ ያለው ዋና ዐላማ ከአይሁድ ወገን ለነብሩ አማንያን የናዝሬቱ ኢየሱስ እነርሱ ሲጠብቁት የነበረው መሲሕ መኾኑን ማሳመን ነው። ይህንንም ለማሳመን የነቢያቶቻቸውን አባባል ጠቅሶላቸዋል።

ጌታ ኢየሱስ መሲሕ መኾኑን ለማስረዳትና ለማሳመን የተጠቀመባቸው ዘዴዎች አራት ናቸው

አንደኛ የጌታን የዘር ሐረግ በመዘርዘር እንዴት አድርጎ የዳዊት ልጅ መኾኑን ማረጋገጥ፥

ኹለተኛ አብዛኛዎቹ የነቢያት ትንቢቶች እንደምን አድርገው በጌታችን በኢየሲስ ክርስቶስ ጊዜ የተፈጸሙ መኾናቸውን ማመልከት፥

ሦስተኛ ጥልቅ የኾኑ ትምህርቶቹ፥ምሳሌዎቹና መለኮታዊ ጥበቡ እንዴት አምላክነቱን እንደሚያረጋግጡ

አራተኛ በእርሱ የተፈጸሙት ታምራት እንዴት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊ ክብር ማረጋገጣቸውን አምልክቷል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

1. እግዚአብሔር የደነገገው የሙሴ ሕግ እንከን የሌለበት ተስማሚ ነው፤ ወይም ጉድለት አለበት። እንከን የሌለበት ከኾነ ለኹል ጊዜ የሚስማማና ለውጥ ወይም ማሻሻያ የማያስፈልገው በመኾኑ የወንጌሉ ሕግ አስፈላጊ ሊኾን አይችልም። ተስማሚ አልነበረም ማለት ጉድለት ነበረበት የምንል ከኾነ ደግሞ እግዚአብሔር ያልተስተካከለና እንከን ያለበት ሥራ ሠራ ማለታችን ስለሚኾን ይህ አባባል ድፍረት የሞላበትና ተገቢ ያልኾነ አባባል ነው የሚሉ ወገኖች አሉ።



www.ethiopianorthodox.org

የሐዲስ ኪዳን ሕግ መምጣት አስቀድሞም ቢኾን በእግዚአብሔር የተወሰነ ነው እንጂ የኦሪቱ ሕግ ያልተሟላ ወይም የማይጠቅም ኾኖ በእርሱ የተተካ አይደለም። እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ አማካይነት ከእስራኤል ቤት ጋር ከቀድሞው የተለየ አዲስ ቃል ኪዳን እንደሚገባ ገልጾአል። (ኤር.ም.31 ቍ:32) ያ የቀድሞው ሕግና ቃል ኪዳን የተሰጠው ለአንድ ወገን ማለት ለእስራኤል ሕዝብ ብቻ ነበር። ወደፊት ግን ሌሎች ወገኖች የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደሚኾኑ በነቢዩ ሆሴዕ አማካይነት እንዲህ ብሏል በምድር ላይ ለእኔ እዘራታለሁ፤ ምሕረትም የሌላትን እምራለሁ፤ ሕዝቤም ያልኾነውን አንተ ሕዝቤ ነህ እለዋለሁ፤ እርሱም አንተ አምላኬ ነህ ይለኛል። (ሆሴ ም.1 ቍ:25)

ስለዚህ የሐዲስ ኪዳን ሕግ በኋላ ዘመን መደንገግ ቀደም ተብሎ በእግዚአብሔር የተወሰነና በነቢያትም የተነገረለት ነው እንጂ እግዚአብሔር ሥራውን አስቀድሞ ሳያስተካክል ቀርቶ በኋላ ዘመን አሻሻለው ለማለት አይደለም። እግዚአብሔር መለወጥና መጸጸት የሌለበት በሚሠራቸው ሥራዎች ኹሉ ፍጹምና ዘላለማዊ ነው።

ይህ ከኾነ ታዲያ ለምን በኋላ ዘመን የደነገገውን የሐዲስ ኪዳንን ሕግ አስቀድሞ በሙሴ አማካይነት ከተሰጠው ሕግ ጋር አብሮ አልደነገገውም ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በሙሴ ጊዜ የነበሩት ሰዎችና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጊዜ የነበሩት ሰዎች ልዩነት አላቸው። በሙሴ ጊዜ የነበሩት ሰዎች ለሃይማኖት ሕግጋት ገና አዲስ በመኾናቸው ጠንካራ ምግብ ለመብላት እንደማይችሉ እንደሕፃናት ነበሩ። በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጊዜ የነበሩት ሰዎች ግን በነቢያትና በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት ሃይማኖትን የመረዳት አቅማቸው ከሕፃንነት ጠንካራ ምግብን ለመብላት እንደሚችል ሙሉ ሰውነት ስለደረሱ በኦሪቱ ሕግ ላይ ለአስተሳሰብ ጠንከር የሚለውን የሐዲስ ኪዳንን ሕግ ጨመረላቸው። የክርስትናን ሃይማኖት ታላቅ ምሥጢርነት ሲያመለክት ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሏል

"የሃይማኖታችን ምሥጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው፤ እርሱም፥ እግዚአብሔር ሰው በመኾን የተገለጠ፥ እውነተኛነቱ በመንፈስ የታወቀ ለመላእክት የታየ ለሕዝቦች ኹሉ የተሰበከ፥ በዓለም ያሉ ሰዎች



ያመኑበት በክብር ወደ ሰማይ የወጣ የሚል [illegible] ቍ. 16) እንዲሁም በመጀመሪያ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. 3 ቍ. 1–2. እንዲህ ብሏል "ወንድሞቼ ሆይ፥ እንደ እውነቱ ከኾነ እኔ ያስተማርኋችሁ ሥጋውያንና በክርስቶስ ገና ያልጠነከራችሁ ሕፃናት እንደመኾናችሁ መጠን ነው እንጂ መንፈሳውያን እንደመኾናችሁ መጠን ላስተምራችሁ አልቻልሁም። ጠንካራ ምግብ መብላት የማትችሉ ስለኾናችሁ እኔ የመገብኋችሁ ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም። " ይህንኑ አባባል ወደዕብራውያን በተላከው መልእክት ም. 5 ቍ. 11–14 እና በሐዋርያው የጴጥሮስ የመጀመሪያ መልእክት ም. 2 ቍ. 2 ላይ ይመለከቷል።

ስለዚህ እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳንንና የሐዲስ ኪዳንን ሕጎች በተለያዩ ጊዜያት የሰጠበት ምክንያት የሰውን ልጅ አስተሳሰብ ለማዘጋጀት እንጂ የጐደለ ወይም ያልተስተካከለ ሕግ ኖሮ ለማሟላት ወይም ለማስተካከል ብሎ አይደለም።

2. በማቴዎስ ወንጌል ም. 1 ላይ የተዘረዘረው የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ በሉቃስ ወንጌል ም. 3 ከቍ. 23 ጀምሮ ከተዘረዘረው ጋር ለምን ተለያየ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የመጀመሪያው ልዩነት ማቴዎስ የዘረዘረው የዮሴፍን የዘር ሐረግ ሲኾን ሉቃስ ግን የዘረዘረው የድንግል ማርያምን የዘር ሐረግ ነው። የዘር ሐረጉም መለያየት የሚጀምረው ከዳዊት ልጆች በኋላ ነው። ማቴዎስ የሰሎሞንን ዘር ሐረግ ሲከተል ሉቃስ ግን የናታንን የዘር ሐረግ ይከተላል።

ኹለተኛው ልዩነት ማቴዎስ ዘር ቆጠራውን የሚጀምረው ከአብርሃም ሲኾን ሉቃስ ግን ከአዳም ይጀምራል።

ሦስተኛው ልዩነት ደግሞ ማቴዎስ ከወደላይ ከአባቶች ጀምሮ ወደታች ወደ ክርስትና ዘመን የሚወርድ ሲኾን ሉቃስ ግን ከክርስትና ዘመን ተነሥቶ ወደ አባቶች ዘመን ይወጣል።



www.ethiopianorthodox.org

በአይሁድ ባህል መሠረት የዘር ሐረግ በሴት በኩል መቁጠር የተለመደ ባለመኾኑ ወንጌላዊው ማቴዎስ የዮሴፍን የዘር ሐረግ የዘረዘረ ሲኾን ወንጌላዊው ሉቃስም ምንም እንኳን የተከተለው የድንግል ማርያምን የዘር ሐረግ ቢኾን በመጨረሻ ላይ ግን በእርስዋ ምትክ የዮሴፍን ስም መዝግቦአል። በዮሴፍም ስም የተመዘገበው ጌታን እንደ አባት ኾኖ ስላሳደገው ነው። (ማቴ. ም. 13 ቍ. 55፥ ሉቃ. ም. 2 ቍ. 48–51)

3. በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ቍ. 3 ፥ 5 ፥ 7 ላይ የጌታችን የመድኅኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ በተዘረዘረበት ጊዜ የሌሎቹ እናቶች ሳይጠቀሱ የፋሬስ፥ የቦኤዝ፥ የኢዮቤድና የሰሎሞን እናቶች መጠቀሳቸው ለምንድነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ታሪክ ይሁዳ ዔር፥ አውናንና ሴሎም የተባሉ ሦስት ወንዶች ልጆች ነበሩት ዔር ባደገ ጊዜ ትዕማር የምትባል ሚስት አጋባው። በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ስለነበረ ልጅ ሳይወልድ ዔርን እግዚአብሔር ቀሰፈው። ለወንድሙ ዘር እንዲያስቀርለት ተብሎ አውናን አገባት። እርሱም ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ስለሠራ ተቀሰፈ። በዚህ ጊዜ ይሁዳ ሦስተኛውም ልጁ እንዳይሞትበት ፈርቶ ልጄ ሴሎም እስኪያድግ ድረስ ወደ አባትሽ ቤት ኼደሽ ተቀመጪ አላት። ሴሎም እንዳላገባት ባየች ጊዜ ሌላ ዘማዊት ሴት በመምሰል አማችዋን ይሁዳን በግብረ ሥጋ ተገናኝታ በመፅነስ ፋሬስንና ዛራን ወልዳለች። (ዘፍ. ም. 38)

የእስራኤል ልጆች ወደ ተስፋ ምድር መግባትን ለማመቻቸት ሰላዮች በተላኩ ጊዜ እነዚያን ሰላዮች ከከነዓናውያን ደብቃ ያዳነቻቸው ራኬብ ወይም ረዓብ የተባለች ዘማዊት ነበረች። እርስዋም ሰልሞንን አግብታ ቦኤዝን ወልዳለች። ቦኤዝ ደግሞ እንዴት ሞዓባዊቷን ሩትን አግብቶ ኢዮቤድን እንደወለደ በመጽሐፈ ሩት ይመለከቷል።

በኹለተኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 11 ላይ በዝርዝር እንደተመለከተው ንጉሥ ዳዊት ኦርዮ የተባለውን ሰው በጦር ሜዳ እንዲሞት አስደርጎ ሚስቱን በመውረስ ሰሎሞንን ወልዳለታለች።



እንግዲህ ከላይ እንደተገለጠው ይሁዳ በዝሙት መልክ ተገናኝቶ ከልጁ ሚስት መንታ ልጆች ወልዷል፤ ሰልሞን ከነዓናዊት ከነበረችው ዘማዊት ሴት ልጅ ወልዶአል ቦኤዝ ሞዓባዊት ከነበረች ሴት ልጅ ወልዶአል፤ ንጉሥ ዳዊት ደግሞ ኦርዮን በማስገደል ሚስቱን ወርሶ ሰሎሞንን ወልዳለታለች። በዚህም መሠረት ከላይ የተጠቀሱት የፋሬስ፣ የቦኤዝ፣ የኢዮቤድና የሰሎሞን እናቶች የተጠቀሱት በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

የመጀመሪያው ምክንያት አይሁዶች ክርስቶስ በሥጋ የተወለደው ከእኛ ዘር ብቻ ነው ብለው እንዳይኩራሩ አይሁድ ካልኾኑ እናቶች የተወለዱ መኖራቸውን ለማመልከት የእናቶች ስሞች ተጠቅሰዋል። ጌታም ዘር የማይለይ መኾኑን ያመለክታል።

ኹለተኛ እኛ ሕግ የተሰጠን የሕግ ሰዎች ነን ብለው እንዳይኩራሩ አባቶቻቸው በጣም የሚመኩበት ዳዊት እንኳ ሳይቀር እንዴት ሕግ አፍራሾች እንደነበሩ ለማመልከት የእናቶች ስሞች ተጠቅሰዋል።

ሦስተኛ ማንም ሰው በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ከተመለሰ ከማንኛውም ኀጢአት ይቅር የሚባል መኾኑን የዘማዊቱን የራኬብን ኹናቴ በምሳሌነት ለማሳየት የእናቶች ስሞች ተጠቅሰዋል። እንዲሁም ዳዊት ኦርዮን አስገድሎ ሚስት እስከመቀማት ማለት ሚስቱን ለመቀማት ሲል ኦርዮንን እስከማስገደል ያኽል ወንጀል ቢሠራም ንስሐ በመግባቱ ይቅርታ የተደረገለት መኾኑን ለማመልከት ከኦርዮ ሚስት ተብሏል።

አራተኛ ክርስቶስ ከእነዚያ ዘር መወለዱ እነርሱን የሚያነጻቸው የሚያከብራቸው ከመኾኑ በቀር እርሱን በምንም የማያስድፈው መኾኑን ያመለክታል። ለምሳሌ የፀሐይ ብርሃን ወይም የፀሐይ ጮራ በማንኛውም እድፍ ላይ ቢያርፍ ያንን እድፍ በተለያየ ዘዴ የሚያጸዳው ከመኾኑ በቀር እድፉ ፀሐዩን ምንም ሊያጐድፈው እንደማይችል ጌታም ኀጢአት ከሠሩ ወገኖች መወለዱ እነዚያን ኀጢአተኞች ከሚያከብራቸውና ከሚያነጻቸው በቀር በእርሱ ላይ ምንም ልዩነትን አያመጣም።

4. በማቴዎስ ወግጌል ም. 1 ቍ. 25 እና በሉቃስ ወንጌል ም. 1 ቍ. 34 – 35 እንደሚነበበው ጌታ ኢየሱስ የተወለደው ያለ ወንድ ዘር



www.ethiopianorthodox.org

በመንፈስ ቅዱስ መኾኑ ተገልጾ ሳለ በማቴዎስ ወንጌል ም. 13 ቊ. 55 ላይ ጌታ ኢየሱስ የዮሴፍ ልጅ ነው የተባለው እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የጌታን ያለወንድ ዘር ከድንግል መወለድ በመጀመሪያ በትንቢተ ኢሳይያስ ም. 7 ቊ. 14 ትንቢት የተነገረለት ሲኾን በመጨረሻም የትንቢቱን ተፈጻሚነት ወንጌላውያን ማቴዎስና ሉቃስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው አረጋግጠውታል።

በማቴዎስ ወንጌል ም. 13 ቊ. 55–56 ላይ፣ "ይህ የዚያ የአን ጨት ጠራቢው ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም አይደለችምን? ወን ድሞቹስ ያዕቆብና ዮሴፍ፥ ስምዖንና ይሁዳ አይደሉምን? እኅቶቹስ ኹሉ ከእኛ ጋር አይደሉምን?» ብለው የተናገሩት አይሁድ አጋንንትን የሚያስወጣው ብዔል ዜቡል ከሚባለው ከአጋንንት አለቃ ጋር በማስማ ማት ነው እንጂ በራሱ ኀይል አይደለም በማለት ደግን ነገር ኹሉ በክፉ የሚተረጕሙ ናቸው። ስለዚህም ነው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ እንደ ዚህ ያለ ጽርፈት የተናገሩት በዚህ ዓለምም ኾነ በሚመጣው ዓለም ለኀ ጢአታቸው ይቅርታ አያገኙም ብሎ ያረጋገጠላቸው። (ማቴ. ም. 12 ቊ. 22–32፥ ማር. ም. 3 ቊ. 20 – 30፥ ሉቃ. ም. 11 ቊ. 14–23)

ክርስቲያን ተብሎ በጌታችን መለኮታዊ ክብር የሚያምን ኹሉ ጌታ ችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተወለደው ያለወንድ ዘር ከድንግል ማርያም ብቻ እንጂ አይሁድ እንዳሉት አለመኾኑን ያምናል። እንዲሁም ሰይጣናትን ከሕመምተኞች ያስወጣ የነበረው በሥልጣኑ እንጂ ከብዔል ዜቡል ጋር ተስማምቶ እንዳልነበረም ያምናል። አይሁድ ከላይ የተጠቀሰውን አባባል የተናገሩት የጌታን ክብር ያዋረዱ መስሎአቸው ነው። በጣም የሚያሳዝነው ጉዳይ ግን አንዳንድ የክርስቲያን ወገኖች ከዚያ ከተጠቀሰው አባባል ግማሹን የሚያምኑ መኾናቸው ነው። ጌታ የዮ ሴፍ ልጅ ነው ተብሎ በአይሁድ የተነገረውን አባባል የማይቀበሉ ሲኾኑ እነ ያዕቆብ የጌታ ወንድሞች ናቸው የሚለውን አባባል ግን እውነት ነው ብለው ይቀበላሉ።



ድንግል ማርያም ጌታን ከወለደች በኋላ ድንግል እንደኾነች ኖረች እንጂ አይሁድና ሌሎች ወገኖች እንደሚሉት የዮሴፍን አግብታ ሌሎች ልጆችን የወለደች አይደለችም። ለዚህ አባባል ትክክለኛነት ከሚቀርቡት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

ሀ. በትንቢተ ኢሳይያስ ም. 7 ቊጥ. 14 ላይ ፡ "እነሆ ፡ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" አለ እንጂ ከዚያ በኋላ ባል ታገባለች አላለም፤ ወይም ደግሞ ድንግል የሚለውን ስም አልነፈጋትም።

ለ. በትንቢተ ሕዝቅኤል ም. 44 ቊ . 1–2 "ወደ ምሥራቅም ወደ ሚመለከተው በስተውጪ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ። በሩም ተዘግቶ ነበር። እግዚአብሔርም ፡ ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፤ ሰውም አይገባበትም፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል አለኝ።" ይህ ትንቢት የድንግል ማርያምን ዘላቂ ድንግልና የሚያመለክት ለመኾኑ የእንዚናዙ ቅዱስ ጐርጐርዮስና እንዲሁም ቅዱስ ኤፍሬም አረጋግጠዋል። (ሃይ አ. ገጽ 212 ፡ ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ)

ሐ. ከምሥራቅ አገር ከመጡት የከዋክብት ተመራማሪዎች በተረዳው ዘመን መሠረት ሄሮድስ በቤተልሔም የሚገኙትን እስከ ኹለት ዓመት ዕድሜ ድረስ ያላቸውን ሕፃናት ማስገደሉ በማቴዎስ ወንጌል ም. 2 ቊ . 16 ላይ ተገልጾአል። ይህም የሚያመለክተው እነዚያ ሰዎች በመጡበት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ከድንግል ማርያም ከተወለደ ኹለት ዓመት ኹኖት ነበር ማለት ነው። ድንግል ማርያም ደግሞ ዮሴፍን የምታገባ ብትኾን ኖሮ እስከዚያን ጊዜ ባገባችው ነበር እንጂ ኹለት ዓመት ሳታገ ባው ባልዘገየችም ነበር። የከዋክብት ተመራማሪዎች መጥተው እስከ ኼዱበት ጊዜ ድረስና የግብጽ ስደት መልስ እስከተደረገበት ጊዜ ድረስ ዮሴፍን ያላገባች መኾንዋ የሚታወቀው በሚከተሉት ጥቅሶች ነው።

"የከዋክብት ተመራማሪዎቹ ከኼዱ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ ሄሮድስ ሕፃኑን ለመግደል ስለሚፈልግ ተነሥ ና ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዘህ ኺድ ... አለው።" (ማቴ. ም. 2 ቊ . 13)



www.ethiopianorthodox.org

"ዮሴፍም በሌሊት ተነሣና ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዞ ወደ ግብጽ
ኼደ።" (ማቴ. ም. 2 ቍ. 14)

"ሄሮድስ ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ በግብጽ አገር
ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ ሕፃኑን ለመግደል የሚፈልጉት ሰዎች ስለሞቱ
ተነሥና ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ኺድ አለው። ስለ
ዚህ ዮሴፍ ተነሣና ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዞ ወደ እስራኤል አገር ተመ
ለሰ።" (ማቴ. ም. 2 ቍ. 19–21)

አሁን እንግዲህ ዮሴፍ ድንግል ማርያምን እንዲጠብቅ በእግዚአ
ብሔር የታዘዘ እንጂ ለእርስዋ ባል እንዲኾን ያልተወሰነ መኾኑ የሚታ
የው ሚስቱን ወይም እጮኛውን በማለት ፈንታ ሕፃኑንና እናቱን ማለቱ
ነው። ድንግል ማርያም ጌታን ከመውለድዋ በፊት በማቴዎስ ወንጌል ም.
1 ቍ. 20 እና 24 ላይ፥ እንዲሁም በሉቃስ ወንጌል ም.1 ቍ 27
እና ም. 2 ቍ . 5 ላይ የዮሴፍ እጮኛ ተብላ ስትጠራ ከቆየች በኋላ
አሁን ያ አባባል ተለውጦ ሕፃኑና እናቱ መባሉ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ
ዮሴፍ ለድንግል ማርያም ጠባቂዋ፥ ለጌታ ደግሞ ሞግዚትና አሳዳጊው
እንዲኾን የተወሰነለት መኾኑን ያመለክተናል። ያለበለዚያ ግን ሕፃኑንና
እናቱን ከማለት ይልቅ እጮኛውን ወይም ሚስቱን ማርያምንና ሕፃን ኢየ
ሱስን ማለት በቀለለ ነበር።

መ. መልአኩ ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም ተልኮ ልጅ እንደ
ምትወልድ ባበሠራት ጊዜ እኔ ድንግል ኾኜ ሳለ ይህ እንዴት ሊኾን
ይችላል ብላ መጠየቅዋ ባል ላለማግባት ቁርጥ ሐሳብ እንደነበራት
ያመለክታል። እንደዚያ ያለ ሐሳብ ባይኖራት ባል ካገባሁ በኋላ ስለምወ
ልደው ልጅ የተነገረኝ ትንቢት ነው ብላ ትቀበለው ነበር እንጂ ያንን
ጥያቄ ባልጠየቀችም ነበር። የመልአኩ ብሥራት በተነገራት ጊዜ የዮሴፍ
እጮኛ እንደነበረች ተገልጾአል። ለድንግል ማርያም ጥያቄ መልአኩ ገብ
ርኤል መልስ ሲሰጥ "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም
ኀይል ይጸልልሻል" ከማለቱ በቀር ምነው እጮኛ አለሽ አይደለም ወይ
አላላትም። (ሉቃ. ም. 1 ቍ . 35) መፅነስዋም እንደታወቀ የእግዚ
አብሔር መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ተገልጾለት ወደ ቤቱ እንዲወስዳት
ያዘዘው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከሰዎች አሉባልታና ከችግር እንዲጠብቃት
ነው እንጂ እንዲያገባት አይደለም። ነፍስጡር ሴትንም ማግባት የተ



ለመደ አይደለምና ወደ ቤቱ የወሰዳት ለጥበቃ እንጂ ለጋብቻ አለመኾኑ
መታወቅ አለበት። ይህም በመኾኑ ነው ከዚያ በኋላ እጮኛውን ማለቱ
ቀርቶ ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ማለት የጀመረው። ጠባቂነቱም በእጮኛነት
ስም የተደረገበት ምክንያት ያው የተፈራው የአይሁድ አሉባልታ እንዳይ
መጣ ጥንቃቄ ለማድረግ ሲባል ነው።

ሠ. በዮሐንስ ወንጌል ም.19 ቍ. 26 እና 27 ላይ ጌታ ተሰቅሎ
በነበረ ጊዜ እናቱን ለሚወደው ደቀ መዝሙር በአደራ ማስረከቡና ደቀ
መዝሙሩም ከዚያን ቀን ጀምሮ ወደቤቱ ይዟት መኼዱ የተነገረው
ሌሎች ልጆች የሌሏት በመኾኑ ነው እንጂ ልጆች እያሏት ልጅዋ ወዳ
ልኾነ ሰው ቤት ባልኼደችም ነበር።

ረ. ወንድሞች የተባሉት ያዕቆብና ይሁዳ በመልእክቶቻቸው መክ
ፈቻ ላይ "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ከኾነው ከያዕቆብ የተላከ
መልእክት፥"

"የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና የያዕቆብ ወንድም ከኾነው ከይሁዳ"
ብለው ከመጀመር ይልቅ የጌታ ወንድሞች ሳይሉ ባላለፉም ነበር። በተለ
ይም ይሁዳ በያዕቆብ ወንድምነቱ ኰርቶ ሲናገር የጌታ ወንድምነቱ የበለ
ጠ ባኰራው ነበር።

ታዲያ ለምን ሀ/ የበኲር ልጅዋ ተባለ?

ለ/ እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ተባለ?

ሐ/ እነ ያዕቆብስ ወንድሞቹ ተባሉ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ
ለማግኘት የትምህርተ መለኮትን መጽሐፍ ምዕራፍ 14 መመልከት ይጠ
ቅማል።

ደግሞስ ከእግዚአብሔር የተላከው መልአክ "አንቺ ጸጋን የተመላሽ
ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ፤ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ
ነሽ" ብሎ ክብርና ምስጋናውን ያቀረበላት የአምላክ እናት እንዴት በእግ
ዚአብሔር ከታደለችበት ከፍተኛ ክብር ተነሥታ ባል ወደ ማግባት ዝቅ
ተኛ ደረጃ የመዛወር ፍላጎት አደረባት ተብሎ ይታመናል?



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ድንግል ማርያም በአምላክ እናትነትዋ ተከብራ የምትኖር ቅድስት እመቤት ነች እንጂ እንደ አይሁድ አሉባልታ ዮሴፍን አግብታ ሌሎች ልጆችን ያልወለደች መኾንዋን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ፡ (ጥያቄና መልስ ቍ. 110 አንደኛ መጽሐፍ )

5. በማቴዎስ ወንጌል ም. 2 ቍ . 6 በትንቢተ ሚክያስ ም. 5 ቍ. 2 ላይ የተነገረውን ትንቢት በመጥቀስ የቀረበው ጥቅስ "አንቺ ቤተ ልሔም የይሁዳ ምድር ከይሁዳ ገገርዎች ከቶ አታንሺም፣ ሕዝቤን እስራ ኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና" የሚለው ነው።

ታዲያ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ የሰውን ልጅ ሥጋ በመልበስ ቤዛ ኾኖ ያዳነው ወገንንና ዘርን ሳይ ለይ የዓለምን ሕዝብ በሙላ መኾኑን የምናምን ከኾነ እንዴት እስራኤልን ብቻ የሚጠብቅ በማለት ትንቢት ተነገረ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ስለጌታችን አምላካችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረ ው አብዛኛው ትንቢት በተነገረ ጊዜ ኹሉ የተያያዘው ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ነው። ምንም እንኳ አመጣጡ ለዓለም ሕዝብ በአጠቃላይ መኾኑ ባይካድ ሥጋ ለብሶ ሰው የኾነው ከአይሁድ ዘር በመኾኑ፣ ትምህ ርቱን ያስፋፋው በአይሁድ አገር በመኾኑና ለደቀ መዛሙርትነት የመረጣ ቸውም የአይሁድ ወገኖች በመኾናቸው አብዛኛዎቹ ትንቢቶች መሠረት ያደረጉት የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ይህም ሲኾን አመጣጡ ለሌሎች መገኖችም መኾኑ አልተካደም። ለዚህም የሚከተለውን ትንቢት እናስተ ውል።

"የጽዮን ልጅ ሆይ፣ እነሆ መጥቼ በመካልሽ እኖራለሁና ዘምሪ፤ ደስም ይበልሽ ይላል እግዚአብሔር በዚያም ቀን ብዙ አሕዛብ ወደ እግዚ አብሔር ይጠጋሉ፤ ሕዝብም ይኾኑኛል፤ በመካከልሽም እኖራለሁ፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም ወደ አንቺ እንደላከኝ ታውቂአለሽ።" (ዘካ ም. 2 ቍ .. 10–11)

እንደሚታወቀው በእውነተኛው አምላክ ማምለክ የተጀመረው በእ ስራኤል ሕዝብና በአባቶቻቸው ጊዜ መኾኑ ግልጽ ነው። ለሐዲስ ኪዳን ማለት ለክርስትና እምነት መሠረቱም ኦሪትና ነቢያት ናቸው። ጌታም



እንዳረጋገጠው ኦሪትን ሊፈጽም እንጂ ሊሽረው [illegible] 50 ላይ 5 ቍ.17) በአንደኛው መጽሐፍ ጥያቄና መልስ ቍ በዝርዝር እንደተገለጠው የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር የተለየ ሕዝብ ኾኖ ተመርጦ የነበረው በደጋግ አባቶች በእነ አብርሃም አማካይነት ቢኾንም በተመራጭነቱ ሊቀጥል የሚችለው ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ረገድ እንደ አባቶቹ ኾኖ ቢገኝ ነበር። ይህ ባለመኾኑ ግን በነቢዩ ሆሴዕ አማካይነት የሚከተለው ትንቢት ተነግሮአል።

"ምሕረት የሌላትን እምራለሁ፣ ሕዝቤ ያልኾነውንም አንተ ሕዝቤ ነህ እለዋለሁ እርሱም አንተ አምላኬ ነህ ይለኛል።" (ሆሴ. ም. 2 ቍ 25)

በእግዚአብሔር ዘንድ አስቀድሞ የታወቀ ከኾነ ለምን ታዲያ በእስ ራኤል ስም ትንቢት ተነገረ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የእግዚአብሔር ሥራዎች ኹልጊዜ የአሠራር ስልቶችን ተከትለው የሚኬዱና ለማንኛውም ጉዳይ ቅደም ተከተልን በመያዝ በየጊዜው የሚ ፈጸሙ ናቸው እንጂ እንደ ሰው ልጅ አሠራር በግብታዊነት የሚከኼዱ አይደሉም።

በዚህም መሠረት ወንጌላዊው ዮሐንስ እንዳለው "ወደ ወገኖቹ መጣ፤ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም፣ ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን መብት [illegible] ዮሐ 1.11–12)

ምንም እንኳ በጸሐፍት፣ ፈሪሳውያንና ካህናት አማካይነት ብዙዎች በጌታ እንዳያምኑ ቢደረጉ በመጀመሪያ አማኞች የተገኙት ከእስራኤል ወገኖች ነው።

በዚህም መሠረት በቅድሚያ ዕድሉ ለእስራኤል ወገኖች ከቀረበ በኋላ የወንጌሉ ትምህርት ወደ ሌሎች ወገኖች እንዲዳረስ ተደርጓል።

ስለዚህ በእግዚአብሔር ላይ እምነት የተጀመረው በኦሪትና ነቢያት ኾኖ እርሱም በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ ብቻ የነበረ በመኾኑ፣ ጌታ የተ ወለደው ከእስራኤል ወገን በመኾኑ፣ የመጀመሪያ ክርስትና እምነት



www.ethiopianorthodox.org

የተጀመረው በእስራኤል አገር በመኾኑና የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ም ከእስራኤል ወገን በመኾናቸው በትንቢተ ሚክያስ የተነገረው ትንቢት ሊያስገርመን አይገባም።

6. በማቴዎስ ወንጌል ም. 2 ቍ. 18 ላይ በትንቢተ ኤርምያስ ም. 31 ቍ .15 ላይ የተነገረውን "የዋይታና የመራራ ልቅሶ ድምፅ በራማ ተሰማ፤ ራሔል ስለልጆችዋ አለቀሰች፤ የሉምና ስለልጆችዋ መጽናናትን እንቢ አለች" የተባለውን ትንቢት ቤተልሔም ሄሮድስ ላስገደላቸው ሕፃናት ትንቢት እንደተነገረ ተደርጎ የተጠቀሰው ትክክል አይደለም፤ ምክንያቱም ይህ አባባል የተነገረው ናቡከደነፆር ስላስፈጃቸው እስራኤላውያን በመኾኑ ሄሮድስ ካስፈጃቸው ሕፃናት ጋር ግንኙነት የለውም ይባል ይኾናል።

በተራ ቍ 123 አንጀኛ መጽሐፍ ውስጥ እንደተገለጸው ትንቢቶች ከአንድ ለበለጡ ጉዳዮች ሊነገሩ ይችላሉ። ናቡከየነፆር በእስራኤል ሕዝብ ላይ ያደረሰው ፍጅት ሄሮድስ በቤተልሄም ሕፃናት ላይ ካደረሰው ፍጅት ጋር ተመሳሳይ አስቃቂ ኹናቴ ስለነበረ ስለኹለቱም ኹናቴዎች በአንድ ትንቢት ተነግሮአል። (ኤር.ም. 39. ቍ – 1 – 12)

ይህ ትንቢት በቤተልሔም ስለተፈጁት ሕፃናትም የተነገረ ትንቢት መኾኑን ለመረዳት የሚከተሉትን ኹናቴዎች እንመልከት:-

ብዙውን ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ወይም የቦታ ስም በሚጠቅሱበት ጊዜ ስለ አካባቢው፥ ስለ ሕዝቡና ስለሌሎችም ጉዳዮች ማለታቸው ነው። በዚህም መሠረት ቤተልሔም፥ ራሔልና ራማ መጠቀሳቸው ከሄሮድስ ፍጅት ጋር ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮች በመኾናቸው ነው።

ለምሳሌ ራሔል ከያዕቆብ ሚስቶች አንድዋ ስትኾን የመጨረሻ ልጅዋን ብንያምን ስትወልድ ሞታ የተቀበረችው በቤተልሔም መኾኑ በኦሪት ዘፍጥረት ም. 35 ቍ. 16–19 ተገልጾአል።

በትንቢቱ ላይ የተጠቀሰው ራማ አንድም ራሔል አሁን የምትገኝበት ቦታ ነው ተብሎ የታመነበት ሰማይ ነው፤ ወይም በመጽሐፈ ኢያሱ



ም. 18 ቍ . 25 ለልጅዋ ለብንያም ነገድ ከደረሱት የርስት ክፍ ያዎች አንዱ ነው።

ቤተልሔምና ኤፍራታ በተመሳሳይነት ወይም አንዳቸው ከተማ ሌላው ክፍለ ሀገር ኾነው ሲቀርቡ ይኸውም የብንያም ነገድ ድርሻ መኾኑ በመጽሐፈ ኢያሱ ም. 18 ቍ. 23 ላይ ተገልጾአል።

አሁን እንግዲህ ድምፅ በራማ ተሰማ ሲል ያንን የለቅሶ ድምፅ ራሔል ከሰማይ አሰማችው ወይም ከብንያም ነገድ ከተሞች አንድዋ በኾነው ተሰማ ማለት ነው። የምታለቅሰውም ራሔል መኾንዋ አንድም በቤተልሔም አካባቢ ከተገደሉት ሕፃናት አብዛኞዎቹ የልጅዋ የብንያም ነገድ ልጆች ስለነበሩ፥ ወይም ሕፃናቱ የተገደሉት እርስዋ በተቀበረችበት በቤተልሔም በመኾኑ ልጆቻቸው በተገደሉባቸው እናቶች ቦታ የእርስዋ ስም ተጠራ፤ ወይም ደግሞ የራሔል ልጆች የሴፍና ብንያም ብቻ ሲኾኑ ሌሎቹ ዓሥሩ ነገዶች ብዙት ስላላቸው የሕፃናቱ ግድያ ለኹለቱ ነገዶች እናት የሚሰማትን ያኽል ሌሎቹ አይሰማቸውም ለማለት ይኾናል። ኹለት ብቻ ከኾኑት ልጆችዋ መቀነስ ስለተሰማት ራሔል አለቀሰች ተባለ።

ስለዚህ የተነገረው ትንቢት ናቡከደነፆር ስላስፈጃቸው እስራኤላውያን የመኾኑን ያኽል እንዲሁም ሄሮድስ ስላስፈጃቸው የቤተልሔም ሕፃናት የተነገረ በመኾኑ የወንጌላዊው ማቴዎስ አቀራረብ ስሕተት የለበትም።

7. በማቴዎስ ወንጌል ም. 3 ቍ. 14 ላይ:- "እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል" ካለ በኋላ በዮሐንስ ወንጌል ም. 1 ቍ. 33 ደግሞ "እኔ አላውቀውም ነበር፤ ዳሩ ግን በውሃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ:- መን ፈስ ቅዱስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው በመንፈስ ቅዱስ የሚያ ጠምቅ እርሱ ነው አለኝ" ይላል። እንዲሁም ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል ም. 11 ቍ. 3 ላይ:-

"የሚመጣው አንተ ነህን? ወይስ ሌላ እንጠብቅ" ብሎ ከደቀ መዛሙርቱ ኹለቱን የላከበት መኾኑ ተገልጾአል።



www.ethiopianorthodox.org

መጥምቁ ዮሐንስ በመጀመሪያው ጥቅስ የጌታን ማንነት እንደሚያውቅ፥ በኹለተኛው ጥቅስ መንፈስ ቅዱስ የገለጸለት ከመኾኑ በቀር እንደማያውቀውና በሦስተኛው ጥቅስ ደግሞ በጌታ ማንነት እርግጠኛ ያልኾነና የተጠራጠረ ይመስላል።

ዮሐንስ የራሱን አቋምና የደረጃውን ወሰን ወይም ምን ያኽል ሥልጣን እንዳለው ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነበር። ሥራውንም በሚሠራበት ጊዜ የሚያጠምቀው ለንስሓ መኾኑን፥ ከክርስቶስ በፊት መምጣቱን፥ መንገድ አስተካካይ መኾኑንና ክርስቶስ በሕዝቡ መካከል የሚገኝ መኾኑን ለአይሁድ ገልጾላቸዋል።

እርሱ ዘንድ ሊጠመቅ ከመምጣቱ በፊት ያላየው ስለኾነ እኔ ከአንተ መጠመቅ ይገባኛል ያለው መንፈስ ቅዱስ ስለገለጸለት ብቻ ነው። በእርግጥ ክርስቶስ በአካባቢው መኾኑን አውቋል። ማንነቱን ግን በዐይኑ አይቶ አላወቀውም ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ብዬ አላውቀውም ነበር ማለቱ ስለ እርሱ የምመሰክረው ስለማውቀው ወይም በዝምድና ምክንያት አይደለም ብሎ ለማረጋገጥ ፈልጎ ነው። ኹለት ደቀ መዛሙርቱን እንዲጠይቁት የላከው መንፈስ ቅዱስ ከገለጸለት በኋላ ተጠራጥሮ ሳይኾን እነዚያ ተላኩት ደቀ መዛሙርት ጌታ ኢየሱስንና ሥራውን አይተው እንዲያምኑ ስለፈለገ ነው። መልእክተኞቹም ወደ ጌታ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ጌታ ራሱ የዮሐንስን ሐሳብ ስላወቀ ለመልእክተኞቹ የሰጣቸው መልስ:- "ኺዳችሁ ያያችሁትንና የሰማችሁትን አውሩለት፤ ዕውሮች ያያሉ፤ አንካሶች ይኼዳሉ፤ ለምጻሞች ይነጻሉ፤ ደንቆሮች ይሰማሉ፤ ሙታንም ይነሣሉ፤ ለድኾች ወንጌል ይሰበካል፤ በእኔም የማይሰናል ብፁዕ ነው" ብሎ ነው። (ማቴ. ም. 11 ቊ. 4–6)

ዮሐንስ በታሰረ ጊዜ ወደ ጌታ ኢየሱስ ከተላኩት ኹለቱ በቀር የእርሱ ደቀመዛሙርት ኹሉ በጌታ አምነው ተከትለውት ነበር። ኹለቱ ግን ገና ሙሉ እምነት ስላልነበራቸው ጌታን አልተከተሉትም ነበር። ዮሐንስም ከዚያ በኋላ ከእስር ቤት በሕይወቱ እንደማይወጣ ስለተሰማው እነዚያ ኹለቱ ደቀ መዛሙርት የጌታ ኢየሱስን ትምህርት ሰምተውና ታምራቱን አይተው በማመን ጌታ ኢየሱስን እንዲከተሉ ስለፈለገ ወደ ጌታ ኢየሱስ ላካቸው እንጂ እርሱስ ቀደም ብሎ አምኖ መስክሮለታል። (ዮሐ.ም. 1 ቊ .. 29) ጌታ ኢየሱስም የዮሐንስን ሐሳብ ስላወቀ



በኹለቱ መልእክተኞች ፊት አስተማረ፥ ብዙ ታምራትንም አደረገ። ከዚያ በኋላ ነው ኺዱና ያያችሁትንና የሰማችሁትን ለዮሐንስ ንገሩት ያላቸው። (ማቴ. ም. 11 ቊ. 5)

በእኔ የማይሰናከል ብፁዕ ነው ያለው የኹለቱን መልእክተኞች ወላዋይነትና እምነተ ቢስነት ለመገሠጽ ፈልጎ ነው እንጂ ስለ ዮሐንስ ትልቅነትማ ኹለቱ መልእክተኞች ከኼዱ በኋላ እንዴት እንደመሰከረለት በማቴዎስ ወንጌል ም. 11 ቊ. 7–11 መመልከት እንችላለን።

8. በማቴዎስ ወንጌል ም.4 ቊ :10 ላይ መድኀኒታችን ፈታኙን ሰይጣን "ኺድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል" ብሎ በኦሪት ዘዳግም ም.6 ቊ:13 — 15 ያለውን ጥቅስ በመጥቀስ መልስ የሰጠው ሲኾን ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.2 ቊ:10 ላይ:. "ለኢየሱስ ስም ክብር በሰማይና በምድር፥ ከምድርም በታች ያሉት ኹሉ በጉልበታቸው ይንበረከካሉ" በመባሉ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል።

በየጊዜው ተመላልሶ እንደተነገረው መድኀኒታችን ሳይጠፋፋ የተዋሐደ የመለኮትና የትስብእት ባሕርይ ያለው በመኾኑ አንዳንድ ጊዜ እንደ ፍጹም አምላክ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንደ ፍጹም ሰው ኾኖ ይነገርለታል። ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.2 ቊ :17 ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኹሉም ነገር ሰዎችን ምምስል እንደተገባው ተገልጾአል። በማቴዎስ ወንጌል ም.12 ቊ.:32 ላይ በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሰነዘረ ኃጢአቱ ይቅር ይባልለታል ማለቱና በሉቃስ ወንጌል ም.2 ቊ:52 ላይ ጌታ ኢየሱስ በጥበብና በቁመት አደገ መባሉ ፍጹም ሰው እንደመኾኑ ስለማንኛውም ሰው የሚነገር አባባል ነው።

ጌታ ለእኛ ቤዛና አርአያ ለመኾን በሚጸልይበት ጊዜ እርሱ ጸሎት የሚያስፈልገው ኾኖ አይደለም። እርሱ በኹሉም ነገር ሰውን ስለመሰለ እንደ ሰው በሚጸልይበትም ጊዜ አምላኬ ብሎ መጸለይ ነበረበት። ሰው ኹሉ የሚጸልየው ለእግዚአብሔር እንደ መኾኑ እርሱም እግዚአብሔርን ብቻህን እውነተኛ አምላክ ብሎ ለአብ የጸለየ መኾኑ በዮሐንስ ወንጌል ም.17 ቊ:3 ላይ ተገልጾአል። ምንም እንኳን ጌታ ወደዚህ ዓለም መጥቶ



www.ethiopianorthodox.org

የእኛን ሥጋ የለበሰው እኛን በቤዛነቱ ለማዳን ፈቅዶ መኾኑ ቢታወቅ ሕማምን ተቀብሎ የሚሞትበት ጊዜ ሲቃረብ ያቺ የመከራ ጽዋ ትቀርለት ዘንድ መጸለዩ በችግር ጊዜ ከችግርና ከመከራ እንዲያድነን የእግዚአብ ሔርን ርዳታ መለመን እንደሚገባን ለእኛ አርአያ ለመኾን ነው። በዚህም ጊዜ የሚያበረታታው መልአክ መታየቱ የእርሱን ፍጹም ሰውነትና የሰው ልጅ ደግሞ ያለ እግዚአብሔር ርዳታ ደካማ መኾኑን ሲያመለክተን ነው። (ሉቃ. ም.22 ቍ:42 — 43)

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ልዩ ልዩ ምሳሌዎች የሚያመለክቱት መድኀኒታችን ያልተጠፋፋ ፍጹም የመለኮትና ፍጹም የሰውነት ባሕርይ ያለው በመኾኑ እንደማንኛውም ሰው የሰውነትን ግብር የሚፈጽም መኾኑ ን ነው። ሰውም በመኾኑ ከኀጢአት በቀር የሰው ልጅ በሰብአዊ ተፈ ጥሮው የሚከተሏቸውን ርምጃዎች ኹሉ ተከትሎ አልፎአል ማለት ነው።

ቀደም ብሎ በቀረበው ጥቅስ "ለአምላክህ ብቻ ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል" ብሎ መልስ በሰጠበት ጊዜ እኔ አምላክ አይደለሁምና ለእኔ አትስገድ፤ ወይም እኔን አታምልክ አላለም። ይህም በመኾኑ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ አይደሉም። ጥያቄና መልስ ቍ:18፥ 27፥ 36፥ 39፥ 48፥ 58፥ 61፥ 63፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 102 እና ከ1ኛው መጽሐፍ ቍ:102፥ 104፥ 112፥ ይመለከ ቷል።

9. በማቴዎስ ወንጌል ም.4 ቍ :18 — 22 እና በማርቆስ ወንጌል ም.1 ቍ:16 – 20 እንደተገለጸው የጌታ ደቀ መዛሙርት አመራረጥ ቀደም ተከተል በመጀመሪያ ጴጥሮስንና ወንድሙን እንድርያስን ከመረጠ በኋላ ቀጥሎ ያዕቆብንና ወንድሙን ዮሐንስን የመረጠ መኾኑ ተገልጾ ሳለ በዮ ሐንስ ወንጌል ም.1 ቍ:35 — 36 በተነገረው ቅደም ተከተል ደግሞ አመ ራረጡ ለየት ያለ በመኾኑ ይህ እንዴት ሊኾን ቻለ ተብሎ ይጠየቅ ይኾና ል።

ኹለት የተለያዩ ጊዜያትና የተለያዩ ኹኔታዎች ናቸው እንጂ በኹ ለቱ አቀራረቦች መካከል ልዩነት ተፈጥሮ አይደለም። በማቴዎስ ወንጌ ልና በማርቆስ ወንጌል የተነገረው የሐዋርያት አመራረጥ ታሪክ ሲኾን



በዮሐንስ ወንጌል የተነገረው ግን ከምርጫው በፊት የተደረገ የመተዋወቅ ግንኙነት ታሪክ ነው።

የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት የነበሩት ዮሐንስና እንድርያስ ከጌታ ጋር ያደረጉት የመተዋወቅ ግንኙነት ነው እንጂ የመመረጥ ጉዳይ አይደለም።

በዚህም መሠረት ኹለቱ አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይ ደሉም።

10. በማቴዎስ ወንጌል ም.5 ቍ:16 ላይ"መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲ ሁ በሰው ፊት ይብራ"ካለ በኋላ በምዕራፍ 6 ቍ:1 ላይ "ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ" በቍ 5 ላይ አንተ ግን ስትጸልይ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስው ር ላለው አባተህ ጸልይ እንዲሁም በቍ 18 ላይ ደግሞ በስውር መጦምን በማዘዙ ትእዛዛቱ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አልኾኑም ወይ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እግዚአብሔር አምላክ የተለያዩ ትእ ዛዞችን በሚያስተላልፍበት ጊዜ እንደየጉዳዩ ኹናቴ የሚለያዩ ከመኾ ናቸው በቀር እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ትእዛዞችን አያስተላልፍም።

በዚህም መሠረት መልካሙን ሥራችሁን አይተው ሰዎች እግዚአ ብሔርን እንዲያመሰግኑ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ በሚልበት ጊዜ በድብቅ ሊፈጸሙ የሚገቡትን በጎ ተግባሮች ማለቱ አይደለም። ሰዎች ከሌሎች ጋር በሚያደርጉአቸው ማኅበራዊ ግንኙነቶች ሰውን ሊያስደስቱ ወይም ሊያሳዝኑ ይችላሉ። ከሌሎች ጋር በምናደርጋቸው የውል ስም ምነቶች መበላለጥ ሳይኾን የጋራ ጥቅምን በሚያዳብር ኹናቴ እውነት እንጂ የተደበቀ ዓላማ ሳይታከልበት መፈጸም አንዱ መልካም ተግባር ነው። በአንድ ኀላፊነት ሥራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ ማንኛውንም ባለጉ ዳይ በአግባቡ ማስተናገድ መልካም ተግባር ነው። ማንኛውም ሰው ከእኛ አንድ ዐይነት ርዳታ በሚጠይቅበት ጊዜ ብንችል መርዳት የማይቻል ቢኾን ደግሞ ጉዳዩን በጥሞና ማስረዳት ከበጎ ተግባሮች አንዱ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

በማነኛውም ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ጋር ስንነጋገር ለሌላው ወገን አሳዛኝ የኾ
አነጋገር ከአንደበታችን እንዳይወጣ ጥንቃቄ ማድረግ አስመስጋ
መልካም ሥራ ነው። በአንድ በኩል እነዚህና እነዚህንም የመሳሰሉ ከሰው
ሊደበቁ የማይችሉ በጎ ተግባሮች ናቸው ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ
የተባሉት።

በሌላ በኩል ደግሞ አስተማሪነትን የሚመለከት ነው። አንድ ሰው
አሞልኮተ እግዚአብሔርን ማስተማር የሚችል ከኾነ ትምህርቱን በራሱ
አፍኖ መቀመጥ የለበትም። ትምህርት በብርሃን ይመሰላል። ስለዚህም
ነው በሥራ ላይ ያልዋለ ትምህርት የጋን መብራት ነው የሚባለው።

ሦስቱ ጥቅሶች ማለት በምሥጢር መመጽወት፥ በምሥጢር መጸለ
ይና በምሥጢር መጦም የታዘዙበት ዋና ዐላማ ስሜትና ፍላጎታችን በሰ
ው ብቻ ለመመስገን ከኾነ የሰውን ውስጠ ምሥጢር መርምሮ በሚያ
ውቀው አምላክ ዘንድ ምንም ዋጋ ስለማይሰጠው ድካማችን ኹሉ ከንቱ
ኾኖ እንዳይቀር ለማሳሰብ ነው። ሃይማኖታዊ ተግባር በምናከናውንበት
ጊዜ ሰው ስላየን ወይም ስላወቀብን ብቻ ዋጋችንን እናጣለን ማለት አይደ
ለም። ዋጋችንን እንድናጣ የሚያደርገን ግን ያንን ተግባር በማከናወናችን
በሰው ዘንድ እንድንመሰገን ምኞትና ፍላጎት ያደረብን እንደኾነ ነው። ያ
ስሜት ግን በእኛ ዘንድ ከሌላ ሰውም ቢያየን ብርሃናችን በሰው ዘንድ በር
ቶ እግዚአብሔርን ያስመሰግናል እንጂ ሰማያዊ ዋጋ አያሳጣንም።

በዚህም መሠረት እነዚያ ቀደም ተብሎ የተዘረዘሩት አራት ጥቅሶች
ለተለያዩ ኹናቴዎችና ዐላማዎች የቀረቡ ከመኾናቸው በቀር እርስ በርሳ
ቸው የሚቃረኑ ትእዛዞች አይደሉም።

11. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ም.5
ቍ:17 ላይ "ኦሪትንና ነቢያትን ልፈጽም እንጂ ልሽር የመጣሁ አይም
ሰላችሁ" ያለው አባባል ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ገላትያ ሰዎች በላከው
መልእክቱ ም.2 ቍ:21 ላይ "ሰው የሚጸድቀው የሙሴን ሕግ በመፈጸም
ከኾነማ ክርስቶስ የሞተው በከንቱ ነው ማለት ነው" ካለው ጥቅስ ጋር
የሚቃረን ይመስል ይኾናል።



በኦሪት ከታዘዙት ትእዛዞች መካከል ለምሳሌ አትግደል፥ አታመ
ንዝር፥ በሐሰት አትማል የሚሉት ይገኙባቸዋል።

እነዚህን ትእዛዞች ማፍረስ ሳይኾን ጌታ እንዴት እንደፈጸማቸው
ወይም እንዴት ፍጹማን እንዳደረጋቸው ለመረዳት የማቴዎስን ወንጌል
ም.5 ቍ:21 ብንመለከት ሰውን የሚገድል ብቻ ሳይኾን የሚቈጣ ወይም
የሚሳደብ እንኳ ይፈረድበታል ብሏል።

ከመጀመሪያው በሰው ላይ መቈጣትና ክፉ ቃላት መለዋወጥ ከሌለ
ወደ ግድያ አይደረስም። ወደ መገዳደል የሚያደርሰው የስድብና የቁጣ
መንገድ መጀመሪያውን ከታገደ ከዚያ በኋላ ግድያ አይመጣም። በዚህም
መሠረት ጌታ ይህንን ትእዛዝ ፍጹም አደረገው ተብሏል።

በቍጥር 28 ላይ አታመንዝር የሚለውን ትእዛዝ ፍጹም ሲያ
ደርገው ሴትን ተመልክቶ መመኘትን ከልክሏል፥ ዐይን አይቶ ሰውነት
ከተመኘ በኋላ ነው ሰው የዝሙትን ኃጢአት የሚሠራው ለዝሙት ምክ
ንያት ሊኾን የሚችለውን አይቶ መመኘትን በመከልከል ትእዛዙን ፍጹ
ም እንዲኾን አድርጓል።

በቍጥር 34 ላይ ደግሞ በሐሰት አትማሉ የሚለውን ትእዛዝ በፍ
ጹም አትማሉ በማለት ፍጹም አድርጎታል።

በዚህም መሠረት ጌታ የኦሪትን ሕግ ፍጹም አደረገው እንጂ አልሻ
ረውም።

ኾኖም እነዚህን ሕግጋት መፈጸም ግዴታችን ቢኾንም እነርሱን
በመፈጸማችን ብቻ ጻድቃን እንደኾንን መገመት የለብንም የምንድነው
በእግዚአብሔር ምሕረትና በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
ቤዛነት መኾኑን መርሳት የለብንም። ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ማንም
ፍጹም አለመኾኑንና እኛም ኹላችን ኃጢአተኞች መኾናችንን መዘንጋት
የለብንም። ይህንኑም በትምህርተ መለኮት መጽሐፍ በምሥጢረ ሥጋዌ
ምዕራፍ ውስጥ ሰው ኹሉ ኃጢአተኛ ነው በሚለው ርእስ ሥር ይመለ
ከቷል።



www.ethiopianorthodox.org

ከውስጣዊ ስሜት ያልመነጨና በአፍአዊ ድርጊታችን ብቻ ሕግ
ፈጻሚዎች ነን ብለን የምንመካ ከኾነ ሕጉ ተግባራዊነቱን ይስታል። ስለ
ዚህም ነው አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ፈሪሳ
ዊና በአንድ ቀራጭ ምሳሌነት ባቀረበው ታሪክ ውስጥ ከፈሪሳዊው ይልቅ
ቀራጩ ጸድቆ መመለሱን የገለጸው። (ሉቃ. ም.18 ቍ.14)

የእኛ ኃጢአት ጌታ ከሚያደርግልን ምሕረት ጋር ሲነጻጸር ጽድቃ
ችን ምንም የማ ያስመካ መኾኑን በማመልከት ነቢዩ ኢሳይያስ "እኛ ኹላ
ችን በኃጢአት ረክሰናል፤ ጽድቃችንም እንደመርገም ጨርቅ ኾኗል፤
ከኃጢአታችን ብዛት የተነሣ ደርቀው በነፋስ እንደሚረግፉ ቅጠሎች
ኾነናል" ብሏል። (ኢሳ. ም.64 ቍ.6)

እንግዲህ መድኀኒታችን ከዚህ ችግር ሊያድነን ፈቅዱ ነው ለእኛ
ቤዛ ኾኖ እስከመሞት የደረሰው በሕግ ፈጻሚነት ብቻ ለመዳን የምንችል
ቢኾን ኖሮ ጌታ መሞት ባላስፈለገውም ነበር። ስለዚህም ነው ሐዋርያው
ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በላከው መልእክቱ "ሰው የሚጸድቀው የሙሴን
ሕግ በመፈጸም ከኾነማ ክርስቶስ የሞተው በከንቱ ነው" ያለው። (ገላ.
ም.2 ቍ:21)

ስለዚህ ጌታ ሕግጋቱን ፍጹም ያደረጋቸው መኾኑና ሕግጋቱ ደግሞ
ያለ አምላክ አዳኝነት ብቻቸውን በቂ አለመኾናቸው ኹለቱ የተለያዩ ጉዳ
ዮች ናቸው እንጂ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም ምንም እንኳን
ያለ እግዚአብሔር አዳኝነት ለመዳን የማይቻል መኾኑ ቢታወቅ ለሕግጋ
ቱ ተገዢ መኾን ግን አማራጭ የሌለው ግዴታችን መኾኑ መታወቅ ይኖ
ር በል።

12. በማቴዎስ ወንጌል ም.5 ቍ:44 — 45 "እኔ ግን እላችኋለሁ፥
በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትኾኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤
የሚረግሙአችሁንም መርቁ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፤
ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን
ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኀጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና" ካለ
በኋላ በሉቃስ ወንጌል ም.14 ቍ:26 ላይ "ማንም ወደ እኔ የሚመጣ
ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም፥ ልጆቹንም፥ ወንድሞቹንም፥ እኅቶ
ቹንም፥ የራሱን ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ ደቀመዝሙሬ ሊኾን አይ



ችልም" በማለቱ ጠላትህን አፍቅር ካለ በኋላ እንደ... እንደገና ቤተሰብ
ህን ጥላ ይላል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ጌታ ይህንን አባባል ከማለቱ በፊት እግዚአብሔር ያቀረበላቸውን
ጥሪ ላለመቀበል ልዩ ልዩ ምክንያቶች የሚሰጡትን ሰዎች አባባል በም
ሳሌ ዘርዝሮ አስረድቷል። ወደ እኔ የሚመጣ ሰው ኹሉ ከሌላ ከማ
ኛውም ሰው እኔን ማስበለጥ አለበት ብሎ የምርጫን መጠን ማወዳደሩ
ነው እንጂ ጥላቻን ማዘዙ አይደለም። ይህንኑ ጉዳይ በበለጥ ሲያብራራው
በማቴዎስ ወንጌል ም.10 ቍ :37 ላይ፥ "ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም
እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊኾን አይገባውም" ብሏል።

ስለዚህ ኹለቱ ጥቅሶች ለተለያዩ ምክንያቶች የተጠቀሱ በመኾና
ቸው እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አባባሎች አይደሉም።

13. በማቴዎስ ወንጌል ም.6 ቍ:25 — 33 መድኀኒታችን የሰማይ
ወፎችንና የሜዳ አበቦችን ምሳሌ በመስጠት በምግብ፥ በመጠጥና በልብስ
ጉዳይ እንዳንጨነቅና የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ብቻ እንድ
ንፈልግ ያዘዘን ሲኾን ሐዋርያው ጳውሎስ 2ኛ ወደተሰሎንቄ ሰዎች በላክ
ው መልእክቱ ም.3 ቍ:10 ላይ ሊሠራ የማይወድ ሰው አይብላ በማለቱ
ኹለቱ አባባሎች ርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስሉን ይኾናል።

ጌታ ለምግብ፥ ለመጠጥና ለልብስ አትጨነቁ በሚልበት ጊዜ
ምንም ሥራ አትሥሩ ማለቱ አለመኾኑን የምንረዳው በማቴዎስ ወንጌል
ም. 25 ቍ. 14–30 ስለመክሊት የሰጠውን ምሳሌ በመመልከት ነው።
የተሰጣቸውን መክሊቶች በሥራ ላይ ያዋሉት ሰዎች ሲመሰገኑ
ያልሠሩባቸው ግን ተወቅሰዋል።

ይህም የሚያመለክተው ጌታ አትጨነቁ ባለበት ጊዜ የተቃወመው
ለዚህ ዓለም ኑሮ መጨነቅን ነው እንጂ ሥራ ፍቱ ማለቱ አለመኾኑን
ነው። ከሚያጸድቁ ተግባሮች መካከል በዚህ ዓለም ላይ ሥራዎችን ሠርቶ
በተገኘው ገንዘብ የጽድቅን ሥራ መሥራት ቀዳሚ ነው። እንዲያውም
እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠው መመሪያ በፊቱ ወዝ እንጀራ እንደሚባላ
እንጂ ምንም ሥራ ሳይሠራ የእግዚአብሔርን እጅ እንዲጠብቅ አይደ
ለም። (ዘፍ ም.3 ቍ. 19)



www.ethiopianorthodox.org

ሊታወቅ የሚገባው ጉዳይ ደግሞ ወጪነትና መሥራት ኹለት የተለያዩ ጉዳዮች መኾናቸውን ነው። ለምሳሌ በመዝሙር 127 ቍ. 1 ላይ "እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል" መባሉ ሰዎች ቤትን መሥራትና ከተማን መጠበቅ የለባቸውም ማለት አይደለም። አባባሉ ግን የሚያመለክተው ማንኛውም ሥራ የእግዚአብሔር ፈቃድ ካልታከለበት ውጤቱ ያማረ አይኾንም ለማለት ነው። እንግዲህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ታክሎበት ለሚመጣ ውጤት በራሳችን ኀይል እንደምናገኘው ገምተን መጨነቅ አይገባም። ማሰብ ያለብን ለዘላለማዊው ሕይወት እንጂ ለዚህ ለጊዜያዊው ሕይወታችን አይደለም ለማለት ነው። በማቴዎስ ወንጌል ም.6 ቍ. 32–33 ላይ አትጨነቁ ተብለናል። እንደሚያስፈልገን የሚያውቅ መኾኑንና ሰማያዊውን ጸጋ ብቻ እንድንፈልግና እንደተመለከተው የሰማዩ አባታችን ምግብ መጠጥና ልብስ ምድራዊው ግን እንደሚጨመርልን ተገልጦልናል። ይህም ማለት እኛ ለኑሮአችን አስፈላጊ የኾኑትን ተግባሮች ማከናወን እንጂ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚገኘው ውጤት መጨነቅ የለብንም ማለት ነው።

14. በማቴዎስ ወንጌል ም.7 ቍ. 14 ላይ "ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም አስቸጋሪ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው" ካለ በኋላ በምዕራፍ 11 ቍ. 29–30 ደግሞ "ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔ ተማሩ፤ እኔ የዋህ፥ በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ፥ ሸክሜም ቀላል ነውና" በማለቱ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል።

በኀጢአት ለኖረና የጽድቅን መንገድ ላልተለማመደ ሰው የጌታ መንገድ አስቸጋሪና አስጨናቂ ነው።

የጽድቅን መንገድ የለመደና ጥቅሙንም የተለማመደ ሰው ግን በእግዚአብሔር ርዳታ ልዝብና ሸክሙንም ቀላል ኾኖ ያገኘዋል። የመጀመሪያው የተነገረው ከእግዚአብሔር ለራቁ ሰዎች ሲኾን ኹለተኛው ግን የተነገረው ለእግዚአብሔር ወዳጆች ነው።

15. በማቴዎስ ወንጌል ም. 8 ቍ. 5–13 ልጁ የታመመበት የመቶ አለቃ ልጁን እንዲፈውስለት ጌታ ኢየሱስን የለመነ መኾኑ ሲነገር በሉቃስ ወንጌል ም. 7 ቍ. 2–10 ደግሞ የአይሁድ ሽማግሌዎችን እንደላከ እንጂ እርሱ እንደመጣ አልተነገረም። ለምን ይህ ልዩነት ተፈጠረ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በማቴዎስ ወንጌል የተነገረው የመቶ አለቃው የራሱ መጠየቅ ኹና ቴውን ጉዳዩ ከተፈጸመለት ሰው ጋር ለማያያዝ ነው።

ለምሳሌ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን ሠራ ሲል ማሠራቱን እንጂ እርሱ ራሱ መሥራቱን የሚናገር አይደለም።

ጌታ ያጠምቅ ነበር ሲባል በደቀ መዛሙርቱ አማካይነት ነው እንጂ እርሱ ራሱ የሚያጠምቅ ኾኖ አይደለም። (ዮሐ. ም. 4 ቍ. 3)

ጲላጦስ ኢየሱስን ገረፈው ባለበት ጊዜ እርሱ ራሱ ገረፈው ማለት ሳይኾን ወታደሮቹን አዝዞ አስገረፈው ለማለት ነው። (ዮሐ. ም. 19. ቍ. 1)

በዚሁም ዐይነት የአይሁድ ሽማግሌዎች በአማላጅነት ወደ ጌታ ኢየሱስ መጥተው ስለመቶ አለቃው ልጅ ፈውስ የተናገሩትን ነገር ባለ ጉዳዩ የመቶ አለቃው በመኾኑ እርሱ እንደተናገረው ከመግለጹ በቀር ታሪኩ ግን ወንጌላዊው ሉቃስ እንዳቀረበው ነው። (ጥያቄና መልስ ተራ ቍ. 67 ከአንደኛው መጽሐፍና ቍ 33. ከኹለተኛው መጽሐፍ ይመለከቷል።)

16. በማቴዎስ ወንጌል ም. 8 ቍ. 28 ላይ ጌታ ኢየሱስ ወደ ማዶ ወደ ጌርጌሴኖን በመጣ ጊዜ ጋኔን ያደረባቸው ኹለት ሰዎች አግኝቶ እንደፈወሳቸው ሲነገር በመርቆስ ወንጌል ም. 5 ቍ. 2 እና በሉቃስ ወንጌል ም. 8 ቍ. 27 ላይ ጋኔን አድሮበት የነበረውና ጌታ ኢየሱስ የፈወሰው አንድ ሰው ብቻ መኾኑ ስለተገለጸ እንዴት ወንጌላውያኑ አንድ ታሪክ ሲያቀርቡ ልዩነት ሊኖራቸው ቻለ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ማርቆስና ሉቃስ በጣም የባሰበትንና በመፈወሱም የጌታ ክብር የተገለጸበትን ሰው ብቻ በመናገር ያልጸናበትን ሕመምተኛ ጉዳይ አስፈላጊ ኾኖ ስላላገኙት ሳይናገሩ ቀርተዋል። ወይም ደግሞ ማቴዎስ የተ


www.ethiopianorthodox.org

ናገረላቸው ኹለት ሰዎችና ኹለቱ ወንጌላውያን የተናገሩለት አንድ ሰው በተለያየ ጊዜ የተፈወሱ የተለያዩ ሰዎች ሊኾኑ ይችላሉ።

17. በማቴዎስ ወንጌል ም. 8 ቍ. 31–33 እንደተገለጸው ከኹለቱ ሰዎች የወጡት አጋንንት ወደ ዐሣማ መንጋዎች እንዲገቡ ይፈቅድላቸው ዘንድ ጌታ ኢየሱስን ለምነውትና እርሱም ፈቅዶላቸው በዐሣማዎቹ ውስጥ በገቡ ጊዜ ዐሣማዎቹን በመላ ባሕር ውስጥ ገብተው እንዲመቱ አደርዋቸዋል።

ታዲያ ባለቤቶቻቸው ለፍተው ያረቡአቸውና ለኑሮአቸው መዳበር ጠቃሚ ሊኾኑ የሚችሉት ያሣማ መንጋዎች ባሕር ውስጥ ገብተው በሚሞቱበት ጊዜ የባለቤቶቹ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እንዴት ጌታን ሳያሳዝነው ቀረ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ጌታ ኹሉን ነገር የፈጠረና ኹሉም የእርሱ የኾነ ነው። መላእክት የእግዚአብሔር ፍጥረቶች እንደ መኾናቸው አጋንንትም የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ናቸው። በፈጠረው ፍጥረት ኹሉ ላይ ወይም ለፈጠረው ፍጥረት የሚያደርጋቸውን ድርጊቶች እርሱ ብቻ በሚያውቀው ምክንያት ያደርጋል እንጂ ማንም የሚያማክረው ወይም የሚጠይቀው የለም። በአንድ ጊዜና በአንድ ቦታ ላይ ተሰቦ፥ ወረርሽኝ፥ ጐርፍ፥ የመሬት መንቀጥቀጥ፥ ማዕበል፥ አውሎ ነፋስና ሌሎችም ችግሮች ደርሰው ብዙ ሕዝብና ብዙ እንስሳትን የሚያጠፉት በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። የዐሣማዎቹም በባሕር ውስጥ መስጠም ከዚያ የተለየ አይደለም። የዚህ የዐሣማዎቹ ጥፋት ውጤት ምንድነው?

በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው ሰው ከባለ ደመ ነፍስ እንስሳት በጣም የበለጠ በመኾኑ በሰው ምትክ እንስሳዎቹ እንዲጠፉ ተደርገዋል። በዚህም ታምራት ክብደት የእግዚአብሔርን ክብርና ኀያልነቱን ልንገነዘብ እንችላለን። በሌላ በኩል ደግሞ በኦሪት ዘሌዋውያን ም. 11 ቍ.7 መሠረት ዐሣማ ለእስራኤሎች የተከለከለ እንስሳ መኾኑ ተመልክቷል። ጌታም ለክብሩና ለትእዛዙ ቀናተኛ በመኾኑ በቤተ መቅደስ የገንዘብ ለዋጮችን ጠረጴዛዎችንና የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች እንደገለበጠ ኹሉ ከሃይማኖታዊ ትእዛዝ ተቃራኒ የኾነውን ሥራ ዐሣማ ማርባትን ባለመፍቀዱ ዐሣማዎቹ ኹሉ ወደ ባሕር ውስጥ ገብተው



እንዲመቱ አድርጓል። (ማቴ. ም. 21 ቍ. 12) ጌታ ኢየሱስም ይህንን ያደረገው አጋንንቱ ስለለመኑት ለእነርሱ ፈቃድ ለመስጠት ብቻ ሳይኾን ለባለቤቶቹ ደኅንነት ሲል ነው። ምክንያቱም በማቴዎስ ወንጌል ም. 16 ቍ. 26 ላይ ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በጥያቄ መልክ ሲያስተምራቸው :- "ሰው ዓለሙን ኹሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጐድል ምን ይጠቀማዋል?" ባለው መሠረት ከምድራዊው ሀብት ይልቅ መንግሥተ ሰማያትን መርጦላቸዋል።

ስለዚህ በተሰጣቸው ሃይማኖታዊ ሕግ መሠረት ዐሣማ አርብቶ መብላቱ ኀጢአት ስለሚኾንባቸው ለኀጢአቱ መንሥኤ የነበሩትን አጠፋላቸው እንጂ አላጠፋባቸውም።

18. ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ም. 9 ቍ. 25 ላይ የመኰንኑን ልጅ፥ በሉቃስ ወንጌል ም. 7 ቍ. 15 ላይ የመበለቲቱን ልጅ፥ በዮሐንስ ወንጌል ም.11 ቍ. 44 ላይ ደግሞ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣቱ የተገለጸ ከመኾኑም በላይ በማቴዎስ ወንጌል ም.27 ቍ. 53 ላይ ጌታ ነፍሱን በሰጠ ጊዜ ሞተው ከነበሩት ቅዱሳን ብዙዎች ከመቃብር ወጥተው መታየታቸው ተገልጾአል።

ታዲያ ይህ ኾኖ ሳለ መጀመሪያ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. 15 ቍ. 20 ላይ፥ እንዲሁም ወደ ቆላስያስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. 1 ቍ. 18 እና በራእየ ዮሐንስ ም. 1 ቍ. 5 እንደተገለጸው ክርስቶስ የሙታን ትንሣኤ በኵር ነው በመባሉ አባባሎቹ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስሉን ይኾናል።

እነዚያ ከሞት ተነሡ ተብሎ የተነገረላቸው ሰዎች ኹሉ ለየተወሰኑ ጊዜያት ከኖሩ በኋላ ሞቱ እንጂ እንደተነሡ የቀሩ አይደሉም። በመጨረሻው ትንሣኤ ሙታን ጊዜ እንደሌሎቹ ኹሉ እንደገና ይነሣሉ። የጌታ ትንሣኤ ግን እንደገና ላለመሞት በመጨረሻው ዘመን ለሚደረገው የሙታን ትንሣኤ የመጀመሪያ በመኾኑ ለሙታን ትንሣኤ በኵር ተባለ። ጥያቄና መልስ ቍ:8፥ 27፥ 36፥ 39፥ 48፥ 58፥ 61፥ 63፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥ 102 እና ከ1ኛው መጽሐፍ ቍ:102፥ 104፥ 112፥ ይመለከቷል።



www.ethiopianorthodox.org

19. በማቴዎስ ወንጌል ም.9 ቍ:14 — 17፡ በማርቆስ ወንጌል ም.2 ቍ.18 — 22፡ በሉቃስ ወንጌል ም.5 ቍ:33 — 39 ላይ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርበው ለምን እነርሱና ፈሪሳውያን ሲጾሙ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ግን እንደማይጾሙ ጠይቀውት ነበር። ጌታም አለመጾማቸውን አልተቃወመም። በማቴዎስ ወንጌል ም.17 ቍ:21 ላይ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ መልስ ሲሰጥ እንደዚህ ዐይነቱ ጋኔን በጾምና በጸሎት ካልኾነ በቀር አይወጣም ብሎ አቸዋል። ይህ ከኾነ ለምን ታዲያ የጌታ ደቀ መዛሙርት ሳይጾሙ ቀሩ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ለዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ጌታ ኢየሱስ መልስ ሲሰጥ ሙሽራ ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎች የማይጾሙ መኾናቸውንና ሙሽራው ከእነር ሱ ሲለይ ግን የሚጾሙ መኾናቸውን ነው። እንዲሁም በአረጀ ልብስ ላይ አዲስ ዕራፊ የሚጥፍና ባረጀ አቁማዳ ደግሞ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያ ኖር አለመኖሩን በምሳሌ ገልጾላቸዋል።

በዚህም በጌታ ኢየሱስ አባባል እንደምንረዳው ጌታ ከእነርሱ ተለይ ቶ ካረገ በኋላ ሐዋርያት መጾም የጀመሩ መኾናቸውንና የአሪቱ የጾም ሥነ ሥርዐት ከሐዲሱ የጾም ሥነ ሥርዐት የሚለይ መኾኑን ነው።

20. በማቴዎስ ወንጌል ም.10 ቍ:5 — 6 ጌታ ደቀ መዛሙርቱን በላከ ጊዜ ከእስራኤል ወደጠፉት በጎች ብቻ ኼደው እንዲያስተምሩ ያዘዛቸው ሲኾን በማርቆስ ወንጌል ም.10 ቍ:15 ደግሞ ወደ ዓለም ኹሉ ኼደው ወንጌልን ለፍጥረት ኹሉ እንዲሰብኩ በማዘዙ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።

ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በመጀመሪያ ለእስራኤል እንዲ ሰብኩ የነገራቸው እነርሱ ከኹሉ በፊት በእግዚአብሔር ያመኑ ሰዎች ኾነው ሳለ አስቀድሞ ለእነርሱ የክርስትና ትምህርት ሳይሰጣቸው ቀርቶ ክርስቲያንነትን ላለመቀበላቸው ምክንያት እንዳይኾን ነው። የሚቀጥሉት ጥቅሶች ይህንን አባባል ያጠናክራሉ።



"ወደ ወገኖቹ መጣ፡ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑ ኹሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን መብት ሰጣቸው።" (ዮሐ. ም.21 ቍ:11 — 12)

"ዕውሮች ብትኾኑማ ኖሮ ኀጢአት ባልኾነባችሁም ነበር፤ አሁን ግን እናያለን ስለምትሉ ኀጢአተኞች ኾናችሁ ትቀራላችሁ አላቸው" (ዮሐ. ም.9 ቍ:41)

"እኔ መጥቼ ባልነግራቸው ኖሮ ኀጢአት ባልኾነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን ለኀጢአታቸው ምክንያት የላቸውም።" (ዮሐ. ም.15 ቍ:22)

ስለዚህ በትንቢተ ሆሴዕ ም.2 ቍ:23 ላይ በነቢዩ እንደበት "ምሕረት የሌላትን እምራለሁ፤ ሕዝቤም ያልኾነው አንተ ሕዝቤ ነህ እለ ዋለሁ፤ እርሱም አንተ አምላኬ ነህ ይለኛል" ባለው መሠረት ከእስ ራኤሎች እምቢተኛነት በኋላ ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ለአሕዛብ ኹሉ እንዲሰብኩ ያዘዛቸው መኾኑን በማርቆስ ወንጌል ም.16 ቍ:15 ተመ ልክተናል።

21. በማቴዎስ ወንጌል ም.10 ቍ:19 — 20 "አሳልፈው ሲሰጡአችሁ የምትናገሩት በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና እንዴት ወይም ምንስ እንድ ትናገሩ አትጨነቁ፤ በእናንተ ኾኖ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ የምትናገሩት እናንተ አይደላችሁምና" ያለ ኾኖ ሳለ በሐዋርያ ት ሥራ ም.23 እንደተዘረዘረው ሐዋርያው ጳውሎስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቆሞ ሲናገር ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ አፉን እንዲመቱት ባዘዘ ጊዜ "አንተ በኖራ የተለሰነ ግድግዳ እግዚአብሔር ይምታህ" ብሎ ቢሰድው:- "እንዴት የእግዚአብሔርን ሊቀ ካህናት እንደዚህ ትሳደባለህ?" ብለው ባጠገቡ የነበሩ ሰዎች ላቀረቡለት ወቀሳ "ወንድሞች ሆይ፥ ሊቀ ካህናት መኾኑን ባላውቅ ነው" ሲል መልስ ሰጥቶአቸዋል። (ዮሐ. ም.23 ቍ:1—5) ታዲያ በዚያን ጊዜ እንዴት መንፈስ ቅዱስ ከስሕተት አልጠ በቀውም ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በሕጉ መሠረት አንድ ሊቀ ካህናት ከሌዊ ነገድ የሚሾም ኾኖ በሹመቱም ላይ እስከ ዕለተ ሞቱ ቆይቶ በሞተ ጊዜ ደግሞ ሌላ ከሌዊ ነገድ የኾነ ሰው ብቻ ይተካበታል። ይህ ሐናንያ ግን ከሌዊ ነገድ ለመኾኑ

www.ethiopianorthodox.org

እርግጠኛ ባለመኾኑና የተሾመውም በጉቦና በሌላ መንገድ እንጂ በእግ ዚአብሔር ፈቃድ ባለመኾኑ ሊቀ ካህናት መኾኑን አላወቅሁም ነበር ብሎአቸዋል። እንደነዚህ ያሉት ሊቃነ ካህናት ደግሞ በየጊዜው የሚ ሾሙና የሚሻሩ እንጂ በሕጉ መሠረት ዕድሜ ልካቸውን በሹመት የሚቆዩ አልነበሩም"።

ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረው የስድብ አነጋገር ሊቀ ካህናት መኾኑን ስላላመነበት ነው እንጂ በኦሪት ዘጸአት ም.22 ቍ:28 ላይ "ፈራጆችን አትስደብ፣ የሕዝብህንም አለቃ አትርገመው" የሚለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የማያውቅ ኾኖና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የስሕተት ንግግር እንዳይናገር ሳይጠብቀው ቀርቶ አይደለም።

22. በማቴዎስ ወንጌል ም.10 ቍ :23 ላይ "እውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ እስኪመጣ ድረስ የእስራኤልን ከተሞች አታዳርሱም፤" በም.16 ቍ:28 ላይ "እውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ እዚህ ከሚቆሙት ሞትን የማይቀምሱ አሉ፤" በም. 24 ቍ:34 ላይ "እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ኹሉ እስኪኾን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም።"

እነዚህ ሦስቱ አባባሎች ምን ማለት ናቸው?

የሰው ልጅ አስኪመጣ ድረስ የእስራኤልን ከተሞች አታዳርሱም ያለው እኔ መጥቼ እስካድርባችሁ፥ ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስን እስክልክላችሁ ማለት ነው። ወይም ደግሞ እስራኤላውያን በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ስለተበታተኑና የወንጌልንም ትምህርት ለመቀበል ፈቃደኞች ስላልኾኑ እነርሱ ባሉበት ኹሉ የወንጌልን ትምህርት ለማዳረስ አይቻልም ማለት ነው። ይህም እስከ ዕለተ ምጽአት ነው ማለት ይኾናል።

የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ እዚህ ከቆሙት መካከል ሞትን የማይቀምሱ አሉ ያለው ይህንን ከተናገረ ከስድስት ቀን በኋላ መንግሥታዊ ክብሩን በታቦር ተራራ ላይ ስለአሳያቸው ስለ ደቀ መዛሙርቱ ስለ ጴጥሮስ፥ ስለ ያዕቆብና ስለ ዮሐንስ ማለቱ ነው። (ማቴ. ም.17)



ጌታ የተናገራቸው ትንቢቶች ኹለት ገጽታዎችን የሚመለከቱ ናቸው።

በመጀመሪያ ይህ ኹሉ እስኪኾን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም ያለው የአይሁድ ሕዝብ ተበታትኖም ቢኾን ተሰብስቦ ጌታ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ በሕዝብነት ይኖራል ማለት ነው። ትውልድ የሚለው ቃል ሕዝብ የሚለውን ቃል ተክቶ የሚገባ መኾኑን ለመረዳት የሚከተሉትን ጥቅሶች መመልከት እንችላለን። (ማቴ. ም.12 ቍ:45፡ ም.17፡ ቍ:17፥ ሉቃ ም.16 ቍ.8፡ ም.17 ቍ:25፡ የሐ.ሥ.ም.2 ቍ.40)

ሌላው ትርጓሜ ደግሞ ስለቤተ መቅደስ መፍረስ ተናግሮ ስለነበረ ቤተ መቅደስ የፈረሰው በ70 ዓ.ም. በመኾኑና የዚያን ጊዜ ትውልድ የደረሰበት ስለኾነ ይህ ኹሉ እስኪኾን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም ብሎአቸዋል።

23. በማቴዎስ ወንጌል ም.10 ቍ:28 ላይ "ሥጋን እንጂ ነፍስን ለመግደል የማይችሉትን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንና ሥጋን በገሃነም ሊያጠፋ የሚችለውን ፍሩ" የሚለው አባባል በመጽሐፈ መክብብ ም.12 ቍ.7 ላይ "አፈር ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ" ከሚለው አባባል ጋር ልዩነት ያላቸው በማስመሰል ነፍስ ለሚለው ቃል ከሃይማኖት ውጪ የኾነ ትርጓሜ ስጥተው ከዋነኛው ክርስቲያናዊ ተስፋ የሚርቁ ወገኖች አሉ።

በመሠረቱ ነፍስ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደየኹናቴው የተለያዩ ትርጉሞች አሉት።

በመጀመሪያ ነፍስ ሲባል የእንስሳ ሕይወት ማለት ለመኾኑ የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

"እግዚአብሔርም አለ:- ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ።" (ዘፍ.ም.1 ቍ:20)



www.ethiopianorthodox.org

"አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ኹሉ በስሙ እንደጠራው ስሙ ያው ኾነ።" (ዘፍ. ም.2 ቍ:19)

ኹለተኛ/ ነፍስ ሲባል ሰው ወይም ሰውነት ማለት ለመኾኑ የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

"በእርስዋም ያሉትን ነፍሳት ኹሉ በስለት ገደሉ።" (ኢያ.ም.11 ቍ:11)

"ነፍሴን በጾም አደከምኋት።" (መዝ.35 ቍ:13)

"አንተን በድያለሁና ነፍሴን ፈውሳት አልሁ።" (መዝ.41 ቍ.4/

"ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፤ በዚያም ቀን ሦስት ሺሕ የሚያኽሉ ነፍሳት ተጨመሩ።" ዮሐ. ሥ.ም.2 ቍ:41)

"ያንም ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ኹሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች አለ።" (የሐ.ሥ. ም.3 ቍ:23)

"ነፍስ ኹሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ።" (ሮሜ ም.13 ቍ:1(

ሦስተኛ ነፍስ ሲባል ስሜት ማለት ለመኾኑ የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

"የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሰረች።" (1ኛ ሳሙ. ም.18 ቍ:1)

"ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች።" (ሉቃ. ም.1 ቍ:47)

አራተኛ ነፍስ ሲባል እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው በአፍንጫው እፍ ያለበት መለኮታዊ እስትንፋስ በመኾኑ ከሥጋ ተለይቶ ከመኼድ በቀር የማይሞተው የእግዚአብሔር ስጦታ ለመኾኑ የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት።



"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ኾነ።" (ዘፍ.ም.2 ቍ:7)

"አፈር ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ፥ ነፍስም ወደሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ።" (መክ.ም.12 ቍ:7)

"እነሆ፥ ነፍሳት ኹሉ የእኔ ናቸው፤ የአባት ነፍስ የእኔ እንደኾነች ደግሞ የልጅ ነፍስ የእኔ ናት። ኀጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ራስዋ ትሞታለች።" (ሕዝ.ም.18 ቍ:4)

"ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።" (ማቴ.ም.10 ቍ:28)

"ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ :- አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ።" (ሉቃ. ም.23 ቍ:46)

"እስጢፋኖስም ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር።" (ዮሐ.ሥ. ም.7 ቍ:59)

"ኼዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው።" (1ኛ ጴጥ. ም.3 ቍ:19)

ከላይ እንደተዘረዘረው ነፍስ ለሚለው ቃል የተለያዩ ትርጉሞች ያሉት ኾኖ ሳለ አንደኛውንና ኹለተኛውን ማለት የሰውና የእንስሳ ሕይወት እንዲሁም ሰው ወይም ሰውነት የሚሉትን ትርጉሞች ብቻ በመውሰድ፤ ስለዚህ የሰው ነፍስ ከእንስሳት ነፍስ ምንም ልዩነት የሌለውና ሰው ሲሞት ደግሞ ነፍስም ጭምር እንደምትሞት አምነው ለማስተማር የሚሞክሩ ወገኖች አሉ። ለዚህም እምነታቸው ማስረጃዎች ናቸው ብለው ከሚያቀርቡአቸው ጥቅሶችና ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል። "እኔ በልቤ ስለ ሰው ልጆች እንደ እንስሳ መኾናቸውን እንዲያዩ እግዚአብሔር ይፈትናቸዋል አልሁ። የሰው ልጆችና የእንስሳ እድል ፈንታ አንድ ነው፤ ድርሻቸውም ትክክል ነው፤ አንዱ



www.ethiopianorthodox.org

እንደሚሞት ሌላውም እንዲሁ ይሞታል፤ የኹሉም እስትንፋስ አንድ ነው፤ ኹሉም ከንቱ ነውና ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም። ኹሉ ወደ አንድ ቦታ ይኼዳል፤ ኹሉ ከአፈር ነው፤ ኹሉም ወደ አፈር ይመለሳል። የሰው ልጆች ነፍስ ወደ ላይ እንደምትወጣ የእንስሳም ነፍስ ወደ ታች ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማነው?" (መክ.ም.3 ቍ:18 – 21)

"ኀጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ራስዋ ትሞታለች።" (ሕዝ.ም. 18 ቍ.4)

"ነፍስንም ሥጋንም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።" (ማቴ.ም.10 ቍ.28)

በቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃነት ሳይኾን በቃል የሚቀርቡ ክርክሮች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

ኀጢአተኞች የሚቀጡት በሚቃጠል እሳት ውስጥ እንዲጣሉ በመደረግ እስከኾነ ድረስ በሚነድ እሳት ውስጥ የተጣለ ማንኛውም ነገር ተቃጥሎ ይጠፋል፥ ማለት አመድ ይኾናል እንጂ ከዚያ በኋላ አይኖርም ይላሉ።

ሌላው የቃል ክርክር ደግሞ እግዚአብሔር ደግና ርኅሩኅ በመኾኑ አንድ ጊዜ አቃጥሎ አንድን ኀጢአተኛ ለዘላለም እየቀጣው አይኖርም። እንዳልነበረ በማድረግ ያጠፋዋል እንጂ ዘላለም አያስቃየውም ይላሉ።

ከዚህ ቀጥሎ በተከራካሪዎቹ ለቀረቡት ምክንያቶች መልስ ይሰጥ ባቸዋል።

በመጽሐፈ መክብብ ም.3 ቍ.18 – 21 ስለተጠቀሰው ጥቅስ በአን ደኛው መጽሐፍ በጥያቄና መልስ ተራ ቁጥር 106 ላይ ተተን ትኗል። በጥቅሱ መጀመሪያ ማለት በቁጥር 18 ላይ እንደተመ ለከተው የሰው ልጆች ይህ ከእንስሳት ልዩነት የሌላቸው መኾኑ እንዲመስላቸው እግዚአብሔር እንደሚፈትናቸው ጸሐፊው ገልጾአል። ይህም ማለት ከዚ ያ ቀጥሎ የተዘረዘረው የሰው ልጅና የእንስሳ ነፍስ ተመሳሳይነት



በእውነት እንደዚያ መኾኑን አምኖ ያቀረበው ሳይኾን ለሰው ልጆች እን ዲመስላቸው የቀረበ ፈተና ነው ለማለት ነው። በቀረበው ዝርዝር ላይ ጸሐፊው አምኖበት ቢኾን ኖሮ በዚሁ መጽሐፍ በምዕራፍ 12 ቍ.7 ላይ የዚህኛው ዝርዝር ተቃራኒ የኾነ አስተሳሰብ ባላቀረበም ነበር።

በክርስትና ሃይማኖት ኹለት ዐይነት ሞት አለ። የመጀመሪያው የነፍስና የሥጋ መለየት ሲኾን ኹለተኛው ደግሞ በፍርድ ቀን ዘላለማዊ ስቃይ ተግባራዊ በሚኾንባቸው ሰዎች ላይ የሚደርሰው ኹናቴ ነው።

ስለ መጀመሪያው ሞት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች

"አፈር ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ።" (መክ.ም.12 ቍ.7)

"ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ፡- አባት ሆይ፡ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ።" (ሉቃ.ም.23 ቍ.46)

"እስጢፋኖስም፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር።" (የሐ.ሥ. ም.7 ቍ.59)

ስለ ኹለተኛው ሞት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች

"መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል የነሣው በኹለተኛው ሞት አይጐዳም።" (ራ.ዮሐ. ም.2 ቍ.11"

"ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ፡ የርኩሳንም፡ የነፍሰ ገዳዮችም፥ የሴሰኞዎችም፥የአስማተኞዎችም፥ጣዖትንም የሚያመልኩ፥ ሐሰተኞችም ኹሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ኹለተኛ ሞት ነው።" (ራ.ዮሐ.ም.21 ቍ.8)

ኀጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ራስዋ ትሞታለች በሚልበት ጊዜ ኹለተኛው ሞት ማለቱ ነው እንጂ ከመጀመሪያው ሞት ጋር ተመሳሳ ይነት ያለው ኹኖ አይደለም።



www.ethiopianorthodox.org

በዮሐንስ ወንጌል ም.5 ቍ.29 ላይ ጌታ እንዳረጋገጠው "መል ካም የሠሩ ከሞት ተነሥተው በሕይወት ይኖራሉ፤ ክፉ የሠሩ ግን ከሞት ተነሥተው ይፈረድባቸዋል።" በዚህ ጥቅስ መሠረት የሞተው ሥጋችን ከአልሞተው ነፍሳችን ጋር ተዋሕዶ ካደረገ በኋላ ለመንግሥተ ሰማይ የሚያበቃ ተግባር የፈጸምን እንደኾነ ዘላለማዊ ሕይወትን ስንታደል ያለበለዚያ ግን ዘላለማዊ ስቃይ ማለት ኹለተኛው ሞት ይፈረድብናል። በዚያን ጊዜና ከዚያም በኋላ የነፍስና የሥጋ መለያየት ስለማይኖር "ነፍስንና ሥጋን በገሃነም ሊያጠፉ የሚችለውን ፍሩ" ተባለ እንጂ ነፍስና ሥጋ የመጀመሪያውን ሞት ሞቱ ማለት አይደለም።

እኛ በዚህ ዓለም ሳለን የምናውቀው እሳትና በመጨረሻው ዘመን ኀጢአተኞች የሚቀጡበት እሳት ምን ዐይነት ልዩነት እንዳላቸው ለመረዳት የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

በሉቃስ ወንጌል ም.16 ቍ.19 – 26 ጌታ ባቀረበው የድኻው አልዓዛርና የባለጸጋው ሰው ምሳሌ ባለጸጋው በነበልባሉ ቃጠሎ እየተሰቃየ የነበረመኾኑን እንጂ ተቃጥሎ እንዳለቀ ወይም እንደጠፋ አልተገለጸም።

«ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግምባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ደግሞ በቁጣው ጽዋ ሳይቀላቀል ከተዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል፤ በቅዱሳንም መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሠቃያል። የሥቃያቸው ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል፤ ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት የሚቀበል ኹሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም።" (ራ.ዮሐ.ም.14 ቍ.9 – 11)

እነዚህ ኹለት ማስረጃዎች በግልጽ እንዳሳዩት ኀጢአተኛ በገሃነም እሳት ውስጥ በሚቀጣልት ጊዜ ለዘላለም እየተቃጠለ ከመሠቃየት በቀር ተቃጥሎ አመድ በመኾን የሚያልቅ አይደለምና ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

እግዚአብሔር ቸር፥ ደግና ርኅሩኅ በመኾኑ የሰውን ልጅ በዘላለማዊ ሥቃይ አይቀጣውም የሚለው በቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች ያልተ ደገፈ የሰው ልጅ መላ ምት በመኾኑ ምንም ትችት የሚያስፈልገው አይ ደለም። ኾኖም ይህን መሰሉ ጥያቄ በትምህርተ መለኮት መጽሐፍ በምዕ



ራፍ 1 የእግዚአብሔር ደግነት በሚለው ርእስ ሥር የተተቸበት ስለኾነ ያንን መመልከት ጠቃሚ ይኾናል።

በክርስትና እምነታችን መሠረት በመጨረሻው ፍርድ ጊዜ ጻድቃንም ኾኑ ኀጢአተኞች ከሞት ተነሥተው ወደ ጌታ ፊት ለፍርድ የሚቀርቡት ሟቹ በስባሹ ሥጋ ሕያው ከኾነው ከነፍስ ጋር ተዋሕዶ ካደረገ በኋላ ነው። ነፍስ ደግሞ መቼም ቢኾን ስለማትሞት ከሞት መነሣት የሚለው አባባል ስለ እርስዋ ሊነገር አይችልም። ፈጣሪ አምላክ በማይመረው ምሥጢሩ የፈረሰውና የበሰበሰው ገላችን ከነፍሳችን ጋር ተዋሕዶ አድርጎ ዳግመኛ በማይሞት መንፈሳዊ ሰውነት እንዲነሣ ይፈቅድለታል። (1ኛ.ቆሮ.ም.15 ቍ.35 – 50) ከዚያ በኋላ ማለት ከትንሣኤ ሙታን በኋላ ሰው ኹሉ በጌታ ፊት ቀርቦ የመጨረሻ ፍርዱን ይቀበላል። (2ኛ ቆሮ.ም.5 ቍ.10) በፍርዱም መሠረት ኀጢአተኞች ወደ ገሃነመ እሳት ስለሚላኩና ከዚያ በኋላ የሥጋና የነፍስ መለያየት ስለማይኖር ሥጋንና ነፍስን ማጥፋት የተባለው ኹለተኛ ሞት ይህ ነው እንጂ ሥጋና ነፍስ አብረው የመጀመሪያውን ሞት ይሞታሉ የሚለው አባባል የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አለመኾኑን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ። (ጥያቄና መልስ ቍ.134 አንደኛ መጽሐፍ ይመልከቷል)

24. በማቴዎስ ወንጌል ም.10 ቍ.34 ላይ "በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ። ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት" እንዲሁም በሉቃስ ወንጌል ም.12 ቍ.49 ላይ "በምድር ላይ እሳት ልጥል መጣሁ፤ አሁንም የነደደ ከኾነ ዘንድ ምን እፈልጋለሁ?" የሚል ሲኾን ጌታ በተወለደ ጊዜ የሰማይ መላእክት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ፡- "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይኹን፤ ሰላምም በምድር፥ ለሰውም በጎ ፈቃድ" ብለዋል። (ሉ.ቃ.ም.2 ቍ.14) እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል ም.14 ቍ.27 ላይ "ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም" ብሏል። ሐዋርያው ጳውሎስም ወደ ኤፌሶን ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.2 ቍ.14 ላይ መድኀኒታችን ሰላማችን መኾኑንና በቍ.17 ላይ ደግሞ ለሩቁና ለቅርቡ ሰላምን የሰበከ መኾኑን ገልጾአል። በዚሁም ዐይነት አምላካችን የሰላም አምላክ መኾኑን የሚገልጹ ብዙ ማስረጃዎችን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መጥቀስ ይቻላል።



www.ethiopianorthodox.org

ታዲያ ከላይ የቀረቡት ጥቅሶች ለምን እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ኾኑ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ኀጢአትና ክፉ ነገሮች ሠልጥነውበት በነበረው ዓለም ጽድቅንና ቅድስናን ለማስፈን መምጣቱና ኹለቱ ተፃራሪ ኹናቴዎች ደግሞ በመጨረሻ ጽድቅና ቅድስና እስኪያሸንፉ ድረስ ከኀጢአትና ከክፋት ጋር መጋጨታቸው ስለማይቀር ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም ማለቱ ስለዚህ ነው። ዓለማዊ ኑሮአቸውን ብቻ ደስ በሚያሰኘው መንገድ ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ክርስቲያናዊ ሕይወት ሲሰበክላቸው የእነርሱን አኗኗር የሚቃረንና በአኗኗራቸውም የሚወቀሱበት ስለኾነ ብዙዎቹ ይቃወሙታል እንጂ በሰላም አይቀበሉትም። ይህን አባባሉን ጌታ ኢየሱስ በሌላ ጊዜ ሲያብራራው እንዲህ ብሏል "ፍርዱም ይህ ነው፤ ብርሃን ወደ ዓለም መጣ፤ ሰዎች ግን ሥራቸው ክፉ ስለኾነ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ ክፉ ነገር የሚያደርግ ኹሉ ብርሃንን ይጠላል፤ ክፉ ሥራውም እንዳይገለጥበት ወደ ብርሃን አይመጣም።" (ዮሐ. ም.3 ቍ.19 – 20)

በሌላ በኩል ደግሞ በተጠቀሰው ጥቅስ ላይ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም ያለው ከጌታ በቀረበልን የወንጌል ትምህርት መሠረት የነፍሳችንንና የሥጋችንን ትግል ለማመልከት ብሎ ነው። ይህንኑ ጉዳይ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲያብራራው "ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህ እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም" ብሏል። (ገላ.ም.5 ቍ.17) እንዲሁም ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.7 ቍ.14 – 25 በሥጋዊና በመንፈሳዊ ሰውነታችን መካከል የማያቋርጥ ትግል የሚካኼድ መኾኑን ገልጾአል።

በምድር ላይ እሳትን ልጥል መጣሁ ያለው የወንጌል መልእክት በኀጢአትና በጨለማ ሠራዊት ላይ የሚያመጣው ትግል ማለት ነው። የወንጌሉም መልእክት ለአማንያን ሰላም ሲኾን ለኀጢአትና ለኀጢአተኞች ግን ሰላም አይደለም ማለት ነው። እንዲያውም ወደ ኢየሩሳሌም በመኼድ ላይ እያሉ የአንድ የሳምራውያን መንደር ሰዎች የማይቀበሉት በኾነ ጊዜ ያዕቆብና ዮሐንስ በነዚያ ሰዎች ኹናቴ ተበሳጭተው"ኤልያስ እንዳደረገው ከሰማይ እሳት ወርዶ እንዲያጠፋቸው እንበል" ብለው ቢጠይቁት "ከምን ዐይነት መንፈስ እንደኾናችሁ አታውቁም፤ የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም" ብሎ ገሥጻቸው" ይላል። (ሉቃ.ም.9 ቍ.51 – 54) በሌላ ትርጓሜ ደግሞ እሳትን ልጥል መጣሁ ማለት ሃይማኖትን ለማስተማር መጣሁ ማለት ነው። እሳትም በመንፈስ ቅዱስ ይመስላል።

ስለዚህ አባባሎቹ የተለያየ ትርጓሜ አላቸው እንጂ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

25. በማቴዎስ ወንጌል ም.11 ቍ.14 እና ም.17 ቍ.10 ላይ ኤልያስ ይመጣል ተብሎ የተነገረው ስለ ዮሐንስ መጥምቁ መኾኑን ጌታ ኹለት ጊዜ ሲያረጋግጥ ዮሐንስ ራሱ ግን እኔ ኤልያስ አይደለሁም ብሏል። (ዮሐ.ም.1 ቍ.20 – 21) እነዚህ ኹለት አባባሎች ለምን ተለያዩ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በትንቢተ ሚልክያስ ም.4 ቍ .5 ላይ "እነሆ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ" ተብሎ የተነገረውን ትንቢት ቃል በቃል በመውሰድ ራሱ ኤልያስ የሚመጣ ስለመሰላቸው አይሁድ ዮሐንስን አንተ ኤልያስ ነህ ወይ ብለው ለጠየቁት ጥያቄ ነው እኔ ኤልያስ አይደለሁም የሚል መልስ የሰጣቸው። ጌታ ግን ኢየሱስ የትንቢቱን ትርጓሜ በነገራቸው ጊዜ ስለ ዮሐንስ የተነገረ መኾኑን ገልጾላቸዋል።

ስለዚህ ኹለቱ ጥቅሶች በተለያየ ኹናቴ ከመቅረባቸው በቀር እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አባባሎች አይደሉም:

26. በማቴዎስ ወንጌል ም.12 ቍ.1 – 8 ፈሪሳውያን ስለሰንበት መከበር ጉዳይ የጠየቁት የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በሰንበት ቀን የስንዴ እሸት እየቀጠፉ በመብላታቸው ነው። በኦሪት ዘጸአት ም.20 ቍ.8 ላይ ስለሰንበት መከበር ጉዳይ የታዘዘ ኾኖ ሳለ ለምን የጌታ ደቀ መዛሙርት ሰንበትን አላከበሩም ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ጌታ የሰንበትን አከባበር ሥነ ሥርዐት በመዘርዘር አስረድቶአል። በጌታ አባባል ሰንበትን ማክበር ማለት በጎ ተግባርን ማከናወን ነው እንጂ እጅንና እግርን አጣጥፎ መቀመጥ አይደለም። የጌታ ደቀ መዛሙርት



www.ethiopianorthodox.org

በራባቸው ጊዜ በሰንበት ቀን እሸት ቀጥፈው መብላታቸው እንደ ኀጢአት እንደማይቆጠርባቸው በምሳሌ ገለጸላቸው። ከዚያም ኹሉ በላይ ደግሞ ያ ሰንበት እንዲከበር በመጀመሪያ ትእዛዝ ያስተላለፈው እርሱ ራሱ የሰንበት ጌታ መኾኑን ገለጸላቸው። በዚህም መሠረት እርሱ የሰንበት ጌታ እንደመኾኑ የሰንበትን አከባበር የገለጸላቸው በመኾኑ ጥቅሶቹ ርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

27. "በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ኹሉ በደሉ ይቅር ይባል ለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ኹሉ ግን በዚህ ዓለምም ኾነ በሚመጣው በደሉ ይቅር አይባልለትም።" (ማቴ.ም.12 ቍ.32)

ይህ አባባል ከሦስቱ የመለኮት አካሎች በአንዱ ላይ ብቻ የስድብ ቃል የሰነዘረ ማለት ሳይኾን መንፈስ ቅዱስ ተብሎ በሚነገርበት ጊዜ እግዚአብሔር ወይም አምላክ የሚለውን መለኮታዊ መጠሪያ ተክቶ ስለሚገባ ነው። በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ኹሉ በደሉ ይቅር ይባልለታል ማለቱ ተሳዳቢው ሰው የጌታ ኢየሱስን ዘላለማዊ አምላክነት ሳያውቅ ተራ ሰው መስሎት ከኀጢአተኞች ጋር የሚበላና የሚጠጣ የኀጢአተኞች ወዳጅ ብሎ የሚሳደብ ሰው ስለበደሉ በልቡ እስከተጸጸተ ድረስ ኀጢአቱ ይቅር ይባልለታል። ነገር ግን በእግዚአብሔር ኀይል በቀር በሰው ኀይል ሊፈጸሙ የማይችሉትን የመንፈስ ቅዱስን ክንዋኔዎች ጸሓፍትና ፈሪሳውያን እንዳደረጉት የሰይጣን ሥራ አድርጎ ማውራት ወይም የስድብ ቃል መሰንዘር ይቅርታ የማይደረግለት ኀጢአት ነው። ጌታም ሊል የፈለገው ይህንኑ አባባል ነው።

ጌታ ኢየሱስ የሰው ልጅ በሚልበት ጊዜ ስለራሱ መናገሩ እንደመ ኾኑና የተዋሐደ እንጂ ያልተቀላቀለና ያልተጠፋፋ የመለኮትና የትስ ብእት ባሕርይ ያለው እንደመኾኑ ከኀጢአት በቀር በዚህ ዓለም በሰዎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮች ደርሰውበታል። ጌታ ኢየሱስ በዚህ ዓለም እንደማንኛውም ሰው ይኖር በነበረበት ዘመን በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ መለኮታዊ ክብሩ ያልታወቀ በመኾኑ ነው ሕማም አድሮ ሰውበት በሚሰቅሉት ጊዜ እንኳ "አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁ ትምና ይቅር በላቸው" ብሎ የጸለየው። (ሉ.ቃ.ም.23 ቍ.34) ይህንኑ የጌታን



አባባል በመመርኰዝ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ መጀመሪያ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.2 ቍ.8 ላይ "ባውቀውትስ ቢኾኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር" ያለው።

በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጅ በሚልበት ጊዜ ስለ ራሱ ማለቱ ሳይኾን ምናልባት ስለማንኛውም ሰው ማለቱ ሊኾን ስለሚችል በእግዚአ ብሔር ላይ ሳይኾን በሰው ላይ ለተሰነዘረ ስድብ በንስሓ የእግዚአብሔር ይቅርታ ይገኛል ማለቱ ሊኾን ይችላል። ጥያቄና መልስ ቍ.8፥ 18፥ 36፥ 39፥ 48፥ 58፥ 61፥ 63፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥ 102፥ እና ከ1ኛ መጽሐፍ ቍ .102፥ 104፥ 112 ይመለከቷል።

28. አንዲት ከአይሁድ ወገን ያልኾነች ሴት ወደ ጌታ ቀርባ ርኩስ መንፈስ የሚያሰቃያትን ልጅዋን ይፈውስላት ዘንድ በለመነችው ጊዜ "የልጆችን እንጀራ ወስዶ ለውሾች መጣል የተገባ አይደለም" ሲል የመለሰላት መኾኑ በማቴዎስ ወንጌል ም.15 ቍ.26 ላይ ተገልጾአል።

በመዝሙር 145 ቍ.8 እግዚአብሔር ርኅሩኅ ነው ተብሎአል። በማቴዎስ ወንጌል ም.5 ቍ.45 ላይ እግዚአብሔር ጻድቃንንና ኀጢ አተኞችን ሳይለይ ለኹሉም ዝናቡን እንደሚያዘንብ የተገለጸ በመኾኑና ጌታ ኢየሱስም የሰውን ልጅ ለማዳን ሲል ሕማምንና ሞትን የተቀበለ መኾኑ ግልጽ ኾኖ ሳለ እንዴት አንዲት ሴት ርዳታ ስትለምነው አይሁዳዊት ስላልኾነች ብቻ የማይረዳት መኾኑን ከመግለጹም በላይ ውሻ ብሎ የስድብ ቃል ሰነዘረባት ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በአንደኛው መጽሐፍ በተራ ቍጥር 50 ላይ የአይሁድ ሕዝብ እንዴትና ለምን እንደተመረጠ ተዘርዝሮ የተገለጸ በመኾኑ አሁን ያንን ትችት መድገም አስፈላጊ አይደለም።

ጌታ ርኅሩኅ፥ ትክክለኛን ፍርድ ፈራጅና ለማንም የማያዳላ በመኾኑ ግዴታቸውን ካለማሟላታቸው የተነሣ የአይሁድን ተመራጭነት የሻረው መኾኑና ማንንም ሳይለይ ለዓለም ኀጢአት የተቤዠ መኾኑ የማይካድ እውነት ነው። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆላስይስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.3 ቍ.11 ላይ "በዚህ ሁኔታ



www.ethiopianorthodox.org

በግሪካዊና በአይሁዳዊ፥ በተገረዘና ባልተገረዘ፥ በሠለጠነ አረመኔና ባልሠለጠነ አረመኔ፥ ነጻነት በሌለውና ነጻነት ባለው ሰው መካከል ልዩነት የለም፤ ክርስቶስ ኹሉ ነው፥ በኹሉም ነው" ያለው።

በጌታ ርኅሩኅነትና ለማንም አለማዳላት የምናምን ከኾነ ለምንድነው ታዲያ ለከነዓናዊትዋ ሴት ያንን መልስ የሰጣት?

ወደ ኋላ መለስ ብለን የአብርሃምን ታሪክ የተመለከትን እንደኾነ እግዚአብሔር ልጁን ይስሐቅን ለሚቃጠል መሥዋዕት እንዲያቀርበው ያዘዘው እርሱ ራሱ ያዘዘውን ትእዛዝ ማለት የሰውን ልጅ ለመሥዋዕትነት አለማቅረብ እንዲሻር ብሎ ወይም የአብርሃምን ታማኝነትና ታዛዥነት የማያውቅ ኾኖ አይደለም። ነገር ግን የአብርሃም ያዛዥነትና ታማኝነት ለእኛ ትምህርት እንዲኾነን ስለፈለገ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው። (ሮሜ.ም.11 ቍ.33፥ ዕብ.ም.4 ቍ.13)

በዚሁም ዐይነት የከነዓናዊትዋ ሴት እምነት ምን ያኽል ከብዙዎቻቸው እምነት የበለጠ መኾኑን ለማሳየት ሲል ከነዓናዊትዋን ሴት ፈተናት። እርሱ ለተናገረው ንግግር ውሾችም እኮ ከጌቶቻቸው ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ የሚለውን መልስ እንደምትሰጠው አስቀድሞ ያውቅ ነበር። በዚህ ጊዜ ጌታ የሴትየዋን እምነት በማድነቅ እንደ እምነትዋ ይኾንላት ዘንድ ፈቀደላት።

ስለዚህ ማናችንም ብንኾን በትሕትናና በእምነት የምንለምነው ልመና ኹሉ እንደሚፈጸምልን ሊያስተምረን ፈልጎ ነው እንጂ ጌታ ርኅሩኅና ለማንም የማያዳላ ሳይኾን ቀርቶ አይደለም።

29. በማቴዎስ ወንጌል ም.16 ቁጥር 17 ላይ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ቅዱስ ጴጥሮስን የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማይ ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ" ካለ በኋላ በቁጥር 23 ላይ "ወደ ኋላዬ ኺድ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ኾነህብኛል" ብሎ መገሠጹ እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።



ጌታ ኢየሱስ ስለራሱ ማንነት ደቀ መዛሙርቱን በጠየቀ ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ የሚል መልስ ስለሰጠው ብፁዕ ነህ ብሎ ካመሰገነው በኋላ አንተ ዐለት ነህ በዚህች ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እመሠርታለሁ ብሎታል። ለዚህ አባባል ከሚሰጡት ትርጓሜዎች መካከል ዓለት የተባለው በክርስቶስ ላይ ያለው እምነት ነው የሚል ነው። ይህም ማለት በክርስቶስ መለኮታዊ ክብር እምነት ላይ ቤተ ክርስቲያን ትመሠረታለች ማለት ነው።

ዲያብሎስ ጌታ ኢየሱስን በተፈታተነ ጊዜ ከነበረው ዐላማ ዋነኛው ጌታ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን የሰውን ልጅ የመቤዠት ዕቅድ ማዘናጋት ነበር። በዚህም መሠረት ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለሕማሙና ስለሞቱ በትንቢት መልክ ላደረገላቸው ገለጻ ይህስ ኹናቴ አይድረስብህ፤ ይህ ችግር ካንተ ይራቅ ብሎ ቅዱስ ጴጥሮስ የሰነዘረውን ሐሳብ ነው ጌታ ሰይጣን ያለው። የሰውን ልጅ በኀጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት ወደዚህ ዓለም መምጣቱ በመለኮታዊ ውሳኔ መሠረት እንደመኾኑ ይህን መለኮታዊ ውሳኔ የሚቃወም ሐሳብ ኹሉ ከሰይጣን እንደመኾኑ የጴጥሮ ስን የማከላከያ ሐሳብ ሰይጣን ብሎ ሰይሞታል።

በዚህም መሠረት በመጀመሪያ ብፁዕ ነህ ያለው በጌታ ላይ ያለውን እምነት በተመለከተ ሲኾን ሰይጣን ነህ ያለው ደግሞ የጌታን የቤዛነት ዕቅድ የሚቃወመውን ሐሳብ በመኾኑና ምስጋናውም ኾነ ወቀሳው በቀጥታ የጴጥሮስን ሰብእና የማይመለከቱ ስለኾኑ ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

30. በማቴዎስ ወንጌል ም.16 ቍ.25 ላይ "ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ኹሉ ያጠፋታል፤ ስለእኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ኹሉ ያገኛታል" የተባለው አባባል በኦሪት ዘጸአት ም.20 ቍ.13 ላይ አትግደል የሚለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አይቃረንም ወይ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ነፍሱን ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል ሲል ጌታ ኢየሱስ የተናገረው እነጋገር ራስን መግደል ማለት ሳይኾን ሥጋዊ ምኞትንና ፍላጎትን መግደል ማለት ነው። ይህም የተባለበት ምክንያት ሥጋዊ ምኞታችንና ፍላጎታችን ለመንፈሳዊ ደኅንነታችን የማይበጅ በመኾኑ ለጥፋቱ



www.ethiopianorthodox.org

ምክንያት የኾነውን ነገር አስወግዱ ወይም አጥፉ ለማለት ነው። ብዙውን ጊዜ ተመሳሳይ አነጋገሮች ሲቀርቡ የኾነውን ወይም የተደረገውን ነገር ለድርጊቱ ምክንያት ከኾነው ነገር ጋር ማያያዝ፥ ማገናኘት፥ ወይም ማዛመድ የተለመደ ነው። ለምሳሌ በማቴዎስ ወንጌል ም.27 ቍ.7 ላይ የካህናት አለቆች ይሁዳ በመለሰው በሠላሳው ብር የእንግዶች መቃብር የገዙበት መኾኑ ሲነገር በሐዋርያት ሥራ ም.1 ቍ.18 ላይ የመቃብሩን መሬት የገዛው እርሱው ራሱ ይሁዳ መባሉ ተገልጾአል። ይህም ማለት መሬቱን ለመግዛት ምክንያት የኾነው እርሱ እስከኾነ ድረስ እርሱ ራሱ እንደገዛው ይቈጠራል ማለት ነው። በዚሁም ዐይነት ነፍሱን የሚያጠፋ ያገኛታል የተባለው ሥጋዊ ፍላጎቱንና ምኞቱን የሚገታ ዘላለማዊውን ሕይወት ይታደላል ማለት ነው። ከሰውነትህ ያካል ክፍሎች አንዱ ቢያስትህ ቈርጠህ ጣለው የሚለው አባባል ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት አለው። (ማቴ.ም.5 ቍ.30) ነገር ግን ይህንን በማቴዎስ ወንጌል የተመዘገበውን የጌታን አባባል ቃል በቃል ተርጕመው ሰውነታቸውን አካለ ጎደሎ ያደረጉ ሰዎች እንደነበሩ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል። ለምሳሌ የእስክንድርያው መንፈሳዊ ኮሌጅ መሪዎች ከነበሩት አንዱ ኦርጌኖስ የተባለው ሊቅ በዝሙት ኀጢአት ላለመውደቅ ሲል ራሱን ስልብ ማድረጉ ተገልጾአል።

በመንፈሳዊ ቋንቋ የደኅንነታችን ጠላት ሥጋዊ ምኞትና ፍላጎት የሚያስገድዱት ክፉ ተግባር መኾኑን ሐዋርያው ጳውሎስ በሚከተለው ኹናቴ ገልጾታል

"ስለዚህ በእናንተ የሚገኙትን የምድራዊ ምኞት ኹሉ ግደሉ፤ እነርሱም ዝሙት ርኩሰት፥ ፍትወት፥ ክፉ ምኞት፥ ጣዖትን ማምለክ የኾነ ንፍገት ናቸው። በእነዚህ ነገሮች ምክንያት በማይታዘዙ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ቊጣ ይመጣል። እናንተም ራሳችሁ ከዚህ በፊት እነዚህን ነገሮች በማድረግ ትኖሩ ነበር።" (ißላ.ም.3 ቍ.5 – 7)

ከምሁራን አንዱ እንዳለው በዚህ ዓለም ላይ ኹለት የሞት ዐይነቶች አሉ። እነርሱም እውነተኛ ሞትና የፍላጎት ሞት ናቸው። እውነተኛ ሞት የነፍስ ከሥጋ መለየት ሲኾን የፍላጎት ሞት የሚባለው ደግሞ ምኞትንና ፍላጎትን ገድሎ ለእነርሱ አለመሸነፍ ነው።



አሁን እንግዲህ ጌታ የተናገረው ነፍስን ማጥፋፋት የሥጋዊ ፍላጎትንና ዝንባሌን መግታት ማለት እንጂ ራስን መግደል ማለት አይደ ለም። ለእኔ ሲል ነፍሱን የሚያጠፋ ያገኛታል ማለት በሌላ ትርጓሜ ደግሞ ለክርስቶስ በመመስከሩ የሰማዕትነት ዕድል ቢያጋጥመው ዋጋውን በመንግሥተ ሰማያት ያገኛል ማለት ነው።

31 በማቴዎስ ወንጌል ም.17 ቍ:1 እና በማርቆስ ወንጌል ም.9 ቍ:2 ላይ ጌታ ከስድስት ቀኖች በኋላ ከሦስት ደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ተራራ ወጣ ሲል በሉቃስ ወንጌል ም.9 ቍ:28 ደግሞ ወደ ስምንት ቀኖች ያህል ቆይቶ ወጣ በማለቱ ኹለቱ አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስለን ይኾናል።

ማቴዎስና ማርቆስ ከስድስት ቀኖች በኋላ ብለው ትክክለኛ አነጋገር ሲናገሩ ሉቃስ ግን ወደ ስምንት ቀኖች ያኽል በማለት ነው እንጂ ትክክለኛዎቹን ቀኖች ቈጥሮ አይደለም። በሌላ በኩል ደግሞ ምናልባት ማቴዎስና ማርቆስ ጌታ የተናገረበትን ቀንና ከነሙሴ ጋር የተገለጠበትን ቀን ሳይቈጥሩ ስድስት ቀኖች ብቻ ቈጥረው ከኾነ ሉቃስ ግን ኹለቱን ቀኖች በመጨመር ስምንት ኾኖለት ሊኾን ይችላል።

32 በማቴዎስ ወንጌል ም.19 ቍ:17፥ በማርቆስ ወንጌል ም.10 ቍ:18፥ በሉቃስ ወንጌል ም.18 ቍ.19 ላይ "ደጉ መምህር ሆይ" ብሎ ለጠራው ሰው ጌታ ኢየሱስ "ለምን ደግ ትለኛለህ? ከአንድ ከእግዚአብ ሔር በቀር ደግ የለም" ካለ በኋላ በዮሐንስ ወንጌል ም.10 ቍ:11 ላይ ደጉ እረኛ እኔ ነኝ" ከማለቱም በላይ በቍጥር 30 ላይ ደግሞ "እኔና አብ አንድ ነን" በማለት ከአብ ጋር ያለውን እኩልነት በማረጋገጡ ኹለቱ አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስለን ይኾናል።

ከናትናኤል ጋር አብሮ ባልነበረበት ጊዜ "ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ኾነህ አየሁህ ያለውና የሰማርያዊቱ ሴት ባል የለኝም ባለችው ጊዜ አምስት ባሎች የነበሩአት መኾኑን የገለጸላት ጌታ በኹሉም ቦታ ሙሉ ኾኖ ልብ ያሰበውን በትክክል የሚያውቅ እንደመኾኑ ደጉ መምህር ሆይ ብሎ ጌታን ያናገረው ሰው በጌታ መለኮታዊ ክብር የማያምን መኾኑን ስላወቀ እኔን ደግ ለማለት አንድም በእኔ መለኮታዊ ባሕርይ ማመን አለብህ ያለ በለዚያ ግን ደግ ልትለኝ አይገባህም ማለቱ ነው እንጂ እኔ



www.ethiopianorthodox.org

ደግ አይደለሁም፥ ወይም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁም ማለቱ አይደለም። (ዮሐ. ም.1 ቍ:49፥ ም.4 ቍ:18)

33. በማቴዎስ ወንጌል ም.19 ቍ:24 ላይ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢገባ ይቀላል" ያለ ሲኾን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለምሳሌ እንደ አብርሃም፥ ኢዮብና ዮሴፍን የመሳሰሉ በጻድቅነታቸው የታወቁ ሰዎች ሦስቱም በጣም ባለጠጎች ነበሩ። ታዲያ ጌታ ከተናገረው አባባል ጋር እንዴት ለማስታረቅ ይቻላል ተብሎ ይጠይቅ ይኾናል።

የግመልና የመርፌ ቀዳዳውን በተመለከተ ሦስት አማራጭ ትርጓሜዎች አሉ።

የመጀመሪያው ትርጓሜ ግመልና የመርፌውን ቀዳዳ እንዳለ በመውሰድ ነው።

ኹለተኛው ትርጓሜ የመርፌው ቀዳዳ እንዳለ ኾኖ ግመል የተባለው ገመድ ለማለት ነው የሚል ነው።

ሦስተኛው ትርጓሜ ደግሞ ግመል የተባለው እንዳለ ተወስዶ የመርፌ ቀዳዳ የተባለው ግን ከኢየሩሳሌም ከተማ ከዋናው በር ጐን ያለው ትንሹ በር ነው። ይህም በር ግመል ጭነቱ ከወረደለት በኋላ ተንበርክኮ ካልኾነ የማያስገባ ነው። ያውም ተገፍቶ መኾን አለበት።

የግመልና የመርፌው ቀዳዳ ጉዳይ እንዳለ ኾኖ ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢገባ ይቀላል መባሉ ባለጠጋ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም ለማለት ሳይኾን በቁጥር 21 እና በቁጥር 22 ላይ እንደተገለጠው ያ ባለጠጋ ሰው ያለውን ኹሉ ሸጦ ለድኻ ከሰጠ በኋላ እንዲከተለው ቢጠይቀው ንብረቱን መሸጥ ያሳዘነው መኾኑ ከተገለጠ በኋላ ነው ከባለጠጋ በእግዚአብሔር መንግሥት ተቀባይነት የግመል በመርፌ ቀዳዳ ማለፉ እንደሚለቀል የተነገረው። ይህም ማለት አንድ ባለጠጋ ለጽድቅ ብሎ ማለት ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ብሎ ንብረቱን በመሸጥ ለድኻ ከሚሰጥ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል ማለት ነው እንጂ



ባለጠጋ የኾነ ኹሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ተቀባይነት የለውም ለማለት አይደለምና አለመኾኑን ተገንዝበን በመሳሳት እንጠንቀቅ።

34 በማቴዎስ ወንጌል ም.19 ቍ:28 ላይ "እውነት እላችኋለሁ, እናንተስ የተከተላችሁኝ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ እናንተም ደግሞ በዓሥራ ኹለቱ የእስራኤል ነገድ ላይ ትፈርዳላችሁ" ብሏል።

በአንድ በኩል ይሁዳ የሚከዳውና ከዓሥራ ኹለቱ በመለየት የሚቀሩት ዓሥራ አንድ ብቻ እንደሚኾኑ አስቀድሞ የሚያውቅ ኾኖ ሳለና በሌላ በኩል ደግሞ በዮሐንስ ወንጌል ም.5 ቍ:22 መሠረት የፍ ርዱ ሥልጣን ያለው ወልድ ብቻ መኾኑና ወደ ሮሜ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.14 ቍ:10 መሠረት ደግሞ ኹላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንደምንቆም የተገለጸ ኾኖ ሳለ ዓሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ይፈርዳሉ የተባለው እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የመጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር አንዳንዴ ቃል በቃል ሌላ ጊዜ ደግሞ በምሳሌ እንጂ ኹልጊዜ ቃል በቃል መወሰድ የሌለበት መኾኑ መታወቅ ይኖርበታል። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚሰጣቸው ተስፋዎች ከግዴታ ጋር እንጂ እንዲሁ ያለምንም ግዴታ አይደለም። ለምሳሌ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ግዴታን ያዘለ ተስፋ የሰጣቸው መኾኑን ቀጥለን እንመልከት

በመጀመሪያ በኦሪት ዘዳግም ም.7 ቍ:6 ላይ "ለአምላክህ ለእግዚ. አብሔር አንተ ቅዱስ ሕዝብ ነህና በምድር ፊት ከሚኖሩ አሕዛብ ኹሉ ይልቅ ለእርሱ ለራሱ ሕዝብ ትኾንለት ዘንድ አምላክህ እግዚአ ብሔር መረጠህ" ካለ በኋላ በምዕራፍ 30 ቍ.:15 – 18 ደግሞ፣ "ተመ ልከት፤ ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን፣ ሞትንና ክፋትን አኑሬለሁ። በሕይወትም እንድትኖር እንድትበዛም፣ አምላክህም እግዚአብሔር ልት ወርሳት በምትገባባት ምድር እንዲባርክህ፣ አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድድ ዘንድ፥ በመንገዱም ትኼድ ዘንድ ትእዛዙንና ሥርዓ ቱን ፍርዱንም ትጠብቅ ዘንድ ዛሬ እኔ አዝዝሃለሁ። ልብህ ግን ቢስት አንተም ባትሰማ ብትታለልም፣ ለሌሎችም አማልክት ብትሰግድ ብታመልካ



www.ethiopianorthodox.org

ቸውም ፈጻሚችሁ እንድትጠፉ እኔ ዛሬ እነግራችኋለሁ፤ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ትወርሳት ዘንድ በምትገባባት ምድር ዘመናችሁን አታስረዝሙም" ብሏል።

አሁን እንግዲህ ለዓሥራ ኹለቱ ሐዋርያት የተሰጡት ተስፋዎች ኹሉ ከእነርሱ በፊት በዘመነ አሪት ለነበሩ ደጋግ ሰዎች ተስፋ በተሰጠ ጊዜ ከግዴታዎች ጋር እንደነበረ ኹሉ የእነርሱም ከእነዚያ የተለየ አይደለም። ለምሳሌ እግዚአብሔር ለዳዊት ቃል ኪዳን ሲገባለት በመዝሙር 132 ቍ:11 እና 12 ላይ:- "ልጆችህ ይህንን የማስተምራቸውን ምስክሬንና ኪዳኔን ቢጠብቁ በዙፋንህ ላይ ለዘላለም ይቀመጣሉ» ብሏል። እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል ም.15 ቍ:6 ላይ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎአቸዋል፤ «በእኔ የማይኖር ቢኾን እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጪ ይጣላል፤ ይደርቅማል፤ እነርሱንም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሉአቸዋል፤ ያቃጥሉአቸውማል።" (ዮሐ. ም.15 ቍ:6) ስለዚህም ይሁዳ ግዴታውን ስለአላሟላ በእርሱ ምትክ ማትያስ ተተክቷል። (የሐ.ሥ. ም.1 ቍ:26)

ዓሥራ ኹለቱ ሐዋርያት በዓሥራ ኹለት ዙፋን ተቀምጠው ይፈርዳሉ የተባለው በዚህ ዓለም ያስተማሩት ትምህርት ውጤት ለመጨረሻው የፍርድ ውሳኔ መሠረት መኾኑን ለማመልከት ነው። ስለዚህም ነው በራእየ ዮሐንስ ም.22 ቍ:12 ላይ "እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለያንዳንዱም እንደየሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ" ያለው። ጌታም ለፍርዱ መመዘኛ የሚያደርገው ሐዋርያት ያስተማሩትን ትምህርት በመኾኑ በዓሥራ ኹለት ዙፋን ተቀምጠው እንደሚፈርዱ ገልጾላቸዋል።

35 በማቴዎስ ወንጌል ም.20 ቍ:20 — 21 የዘብዴዎስ ልጆች እናት ወደ ጌታ ኢየሱስ ቀርባ ለኹለቱ ልጆችዋ በጌታ ግራና ቀኝ የመቀመጥ ክብር እንዲሰጥላት መለመንዋ የተገለጸ ሲኾን በማርቆስ ወንጌል ም.10 ቍ:35 — 37 መሠረት ግን ልመናውን ያቀረቡት ያዕቆብና ዮሐንስ ናቸው በመባሉ ኹለቱ አባባሎች ለምን ተለያዩ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።



ቀደም ተብሎ በጥያቄና መልስ ተራ ቁጥር 13 በተተቸው ትችት መሠረት አንድን ጉዳይ በሌላ ሰው አማካይነት ያስፈጸመ ራሱ እንደፈጸመው ተደርጎ ይነገራል ተብሏል።

ስለዚህ የዘብዴዎስ ልጆች እናት ራሳቸው ሊናገሩ ያፈሩትን ልመና እናታቸውን መላካቸው በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የተገለጸው አገላለጽ ትክክለኛ አባባል ኾኖ በማርቆስ ወንጌል ራሳቸው ጠየቁ የተባለው ግን እናታቸው እንድትጠይቅላቸው ቢያደርጉም ራሳቸው እንደጠየቁ ተቈጥሮ ነው እንጂ ልዩነት ኖሮት አይደለም። (ጥያቄና መልስ ተራ ቍ:6 አንደኛ መጽሐፍ ቍ:15 ኹለተኛ መጽሐፍ)ይመለከቷል

36 "በቀኜና በግራዬ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም።" (ማቴ. ም.20 ቍ:23)

በማቴዎስ ወንጌል ምመ.25 ቍ:30 — 46፤ በዮሐንስ ወንጌል ም.5 ቍ.:22, ኹለተኛ ወደ ጢሞቴዎስ በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. 4 ቍ:8፤ በዮሐንስ ራእይ ም.22 ቍ:12 እና እንዲሁም በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለሰው ኹሉ እንደየሥራው ዋጋውንና ፍርዱን የሚሰጠው ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑ በግልጽ ተጠቅሶአል።

ለሰው ኹሉ እንደየሥራው ዋጋውን የሚሰጠው እርሱ ራሱ ኾኖ ሳለ ከአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም ያለባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

የመጀመሪያው ምክንያት የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከድንግል ማርያም ጋር የነበራትን የሥጋ ዝምድና ተገን በማድረግና የጌታን ማንነት ባለመገንዘብ ምድራዊ ገገር ለመኾን እንደተዘጋጀ ገምታ አንተ በምትነግሥበት ጊዜ ለአንዳቸው በቀኝህ ለአንዳቸው ደግሞ በግራህ የመቀመጥን ሥልጣን ለኹለቱ ልጆቼ ስጥልኝ ብላ በመለመንዋ የምትለምኑትን አታውቁም ብሎ ይጀምርና በዚህ ዓለም ለእርሱ ተዘጋጅቶ የሚጠብቀው በምድራዊ ዙፋን ላይ ተቀምጦ የመንገሥ ምድራዊ ክብር ሳይኾን የመከራ ጽዋና የመከራ ጥምቀት መኾኑን ገለጸላቸው። የምትለምኑትን አታውቁም ያለው በማቴዎስ ወንጌል ም.6 ቍ.33 ላይ "እናንተ ግን



www.ethiopianorthodox.org

አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ፈልጉ" ብሎ በተናገረው መሠረት መለመን የነበረባችሁ የሰማዩን እንጂ የምድሩን ክብር አልነበረም ሲላቸው ነው። እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል ም.18 ቊ.36 ላይ "መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለም" በማለት የፊተ ኛውን አባባል አጠናክሮአል።

በቀኜና በግራዬ መቀመጥ ከአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም ማለቱ እናንተ እንዳሰባችሁት የዚህን ዓለም ክብር የምሰጣችሁ ሳይኾን ለወዲያኛው ዓለም ክብር ከኾነ ግን ያ ክብር የሚገ ኘው ለዚያ ክብር ብቁ በመኾን ነው እንጂ በዝምድናና በደጅ ጥናት አይ ደለም ብሎ ሲያረጋግጥላቸው ነው።

ኹለተኛው ምክንያት ደግሞ የሦስቱን የመለኮት አካሎች ግብር የሚመለከት ነው። አፍአውያን ግብሮች የመለኮታዊ አንድነት ግብሮች ቢኾኑም እነዚህ አፍአውያን ግብሮች በያንዳንዳቸው ስም ለሦስቱም አካሎች ይከፋፈላሉ። ለምሳሌ ከሃሊነትና አዘጋጅነት የአብ፥ ጥበብ የወልድ፥ ስጦታ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ግብሮች ናቸው ቢባልም ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከሃሊነት የላቸውም ማለት አይደለም፤ አብና መንፈስ ቅዱስ ጥበብ የላቸውም ማለት አይደለም። እንዲሁም አብና ወልድ መንፈሳዊ ስጦታን አይሰጡም ማለት አይደለም። ይኹን እንጂ እነዚህ አፍአዊ ግብሮች ለአብ፥ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ተከፋፍለው ስለሚነገሩና ማዘጋጀት ደግሞ የአብ ግብር ስለኾነ መድኀኒታችን ይህንኑ ለማመልከት ሲል ከአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ በሚልበት ጊዜ ዝግጅት የአብ ግብር መኾኑን ይጠቁምና በወዲያኛው ዓለም በጌታ ግራና ቀኝ የመቀመጥን ክብር ለመስጠት የግድ መለኮታዊ ውሳኔና ዝግጅት እንደሚያስፈልገው ለመግለጽ ነው። ዝግጅቱ የአብ ግብር ነው ይባል እንጂ ለሰው ኹሉ ዋጋውን የሚሰጠው እርሱ ራሱ መኾኑን አልካደም። እንዲያውም በዮሐንስ ወንጌል ም.5 ቊ.22 ላይ "አብ በማንም ላይ አይፈርድም፤ ፍርድን ኹሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ" በማለት አረጋግጧል። ጥያቄና መልስ ቊኢ.8፥ 18፥ 27፥ 39፥ 48፥ 58፥ 61፥ 63፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥ 102፥ እና ከ1ኛው መጽሐፍ ቊ.102፥ 104፥ 112፥ ይመለከቷል።



37. በማቴዎስ ወንጌል ም.20 ቊ.29 – 34 መድኀኒታችን ከኢያሪኮ ከተማ ሲወጣ ሁለት ዕውሮችን ፈወሰ ይላል። በማርቆስ ወንጌል ም.10 ቊ 46 – 52 ከኢያሪኮ ሲወጣ የፈወሰው ዕውር አንድ እንደኾነ ተገልጾአል። በሉቃስ ወንጌል ም.18 ቊ.35 – 43 ደግሞ ጌታ ወደ ኢያሪኮ ከተማ ሲገባ አንድ ዕውር እንደፈወሰ ተገልጾአል። ይህንን ታሪክ በማቅረብ ረገድ ሦስቱ ወንጌላውያን ለምን ተለያዩ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ማቴዎስ በአጠቃላይ ባቀረበው መሠረት የተፈወሱት ዕውሮች ኹለት ናቸው። ማርቆስ የተፈወሰውን ሰው ስም በርጤሜዎስ ብሎ በመ ጥራትና በብዙ ሰዎች ዘንድ ይታወቅ ስለነበረው ዕውር መፈወስ ጉዳይ ብቻ በመናገር ስለኹለተኛው ዕውር መፈወስ ጉዳይ ሳያነሣ ቀርቷል። ሉቃስ ደግሞ ጌታ ወደ ኢያሪኮ ሲገባ ስለፈወሰው ዕውር ጉዳይ በመናገሩ ለጥያቄው መልስ እንዲገኝ አድርጓል።

አሁን እንግዲህ ሉቃስ እንዳለው ጌታ ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ ሲገባ አንድ ዕውር ፈውሶአል። ከኢያሪኮ ሲወጣ ደግሞ ማርቆስ እንዳለው ሌላ ዕውር ፈውሶአል ማለት ነው። የኹለቱን ዕውሮች መፈወስ ግን ማቴዎስ ባጠቃላይ ስላቀረበው ሦስቱ አባባሎች ልዩነት የላቸውም።

38. በማቴዎስ ወንጌል ም.21 ቊ.1 – 8 ጌታ ከቀደ መዛሙርቱ ኹለቱን ልኮ አንድ አህያና አንድ ያህያ ግልገል እንዲያመጡለት ካደረገ በኋላ ልብሳቸውን በእነርሱ ላይ ጭነው እንደተቀመጠባቸው ተገልጾ አል። በማርቆስ ወንጌል ም.11 ቊ.1 – 8 እና በሉቃስ ወንጌል ም.19 ቊ.29 – 36 ኹለቱን ደቀ መዛሙርት ያዘዛቸውና ያመጡለት ያህያዋን ግልገል ብቻ እንደኾነ ተገልጾአል። የማርቆስና የሉቃስ አቀራረብ ለምን ከማቴዎስ አቀራረብ ተለየ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ማቴዎስ ባቀረበው ታሪክ መሠረት ደቀ መዛሙርቱ ይዘውት የመ ጡት አንድ አህያና አንድ ያህያ ግልገል ነው። በወንጌሉም እንደተ ገለጸ ው ጌታ በኹለቱም አህዮች ላይ ተቀምጦአል። ከቤተፋጌ እስከ ኢየሩሳ ሌም ባለው መንገድ ወጣ ገባ በኾነው ቦታ ግልገልዋ አቅም ስለማይ ኖራት በአህያዋ ላይ የተቀመጠ ሲኾን በቀጥተኛው መንገድ በውርን ጫዋ ላይ እየተቀመጠ ኼድዋል። ወደ ኢየሩሳሌም ሲደርስ ግን መን



www.ethiopianorthodox.org

ገዱ ወጣ ገባነት የሌለው ቀጥተኛ በመኾኑ በውርንጫዋ ላይ ብቻ ተቀ ምጦ ስለነበረ ያንን ለማመልከት ሲሉ ነው ማርቆስና ሉቃስ ስለርንጫዋ ብቻ የተናገሩት።

39. በማቴዎስ ወንጌል ም.21 ቍ.18 – 19 ጌታ ኢየሱስ በተራበ ጊዜ አንዲት በለስ አይቶ ፍሬ ይገኝባት እንደኾነ ብሎ ቢጠጋት ከቅጠል በቀር ምንም በማጣቱ ስለረገማት ወዲያው መድረቋን የሚናገር ሲኾን በማርቆስ ወንጌል ም.11 ቍ.13፥ 14 እና 20 ላይ ደግሞ በለሲቱ ደርቃ የተገኘችው በሌላ ቀን ነው።

ወንጌላዊው ማርቆስ እንደገለጸው ጊዜው የበለስ ማፍሪያ ጊዜ አልነ በረም።

ታዲያ ጌታ በአንድ በኩል የበለስ ጊዜ አለመኾኑን እያወቀ በሌላ በኩል ደግሞ ውሱን ባልኾነው መለኮታዊ ዕውቀቱ እንዴት በዚያች ዛፍ ላይ ፍሬ አለመኖሩን ሳያውቅ ቀርቶ ለመፈለግ ኼደ? ማቴዎስና ማርቆስስ ለምን የተለያየ ታሪክ አቀረቡ? ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ፍሬ ፍለጋ መኼዱ በአንድ በኩል ያልተጠፋፋና በመለኮት ባሕርይ ያልተዋጠ የትስብእት ባሕርይ ያለው መኾኑን ለማመልከትና ደቀ መዛሙርቱም እምነት ካላቸው ትላልቅ ታምራትን ለማድረግ እንደሚ ችሉ ሊገልጽላቸው ስለፈለገ ነው። ለምሳሌ አዳም የተከለከለውን ፍሬ በልቶ ራቁትነት በተሰማውና ከእግዚአብሔር መደበቅ በሞከረ ጊዜ እግ ዚአብሔር አዳምን ወዴት ነው ያለኸው ብሎ መጠየቁ አዳም ያለበትን ቦታ የማያውቅ ኾኖ አይደለም። (ዘፍ.ም.3 ቍ.9) ወንድምህ አቤል ወዴት ነው ብሎ ቃየንን መጠየቁ ቃየን አቤልን እንደገደለው የማያውቅ ኾኖ አይደለም። (ዘፍ.ም.4 ቍ.9) ልብሱን ብቻ ከነካሁ እድናለሁ ብላ በማመን በብዙ ግፊያ መካከል አንዲት ሕመምተኛ ከጌታ በስተኋላ መጥታ ልብሱን በነካች ጊዜ ልብሴን የነካ ማነው ብሎ መጠየቁ ማን እን ደነካው የማያውቅ ኾኖ አይደለም። እንዲያውም ኀይል ከእኔ እንደወጣ ተሰምቶኛል በማለት ያላወቀ አለመኾኑን ገልጾአል። (ሉቃ.ም.8 ቍ.45 – 46)



ጌታ ግን እነዚህን ጥያቄዎች የጠየቀባቸው ምክንያቶች በአንድ በኩል ጥፋታቸውን ዐውቀው እንዲናዘዙ ስለፈለገና በሌላ በኩል ደግሞ እርሱ ኹሉን ነገር የሚያውቅና እንዳችም ከእርሱ ሊደበቅ የሚችል ነገር እንደሌለ ሊያመለክታቸው ፈልጎ ነው።

በዚህም መሠረት የበለሱ ዛፍ ፍሬ የሌለበት መኾኑን ሳያውቅ ቀርቶ ሳይኾን የደቀ መዛሙርቱ እምነት እንዲጠናከር ፈልጎ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ፍሬ ተፈልጎ ያልተገኘባት የበለስ ዛፍ የጌታን ትምህርት ላልተ ቀበሉትና ባዶ የአምልኮ ሥርዐትን ብቻ በመያዝ የበጎ ተግባር ፍሬ ለሌ ለባቸው ለአይሁድ ሕዝብ ምሳሌ ነው።

የማቴዎስንና የማርቆስን የታሪክ አቀራረብ ልዩነት በሚመለከት ደግሞ ማቴዎስ የኾነውን ኹናቴ አጠቃልሎ የተናገረው ሲኾን ማርቆስ ግን ስለበለሲቱ ዛፍ በየጊዜው የታየውንና የተተቸውን በዝርዝር አቅርቦታል። ምናልባትም ጌታ በለሲቱን እንደረገማት መድረቅ ጀምራ በሌላ ጊዜ ሲመለሱ ሙሉ በሙሉ ደርቃ ያገኘዋት ሊኾን ይችላል። በዚህም አድናቆታቸውን ገልጸዋል። ጥያቄና መልስ ቍ.8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥ 58፥ 61፥ 63፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥ 101 እና በ1ኛው መጽሐፍ ቍ.102፥ 104፥ 112 ይመለከቷል።

40 በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23 ቍ:23 ላይ "እናንተ ግብዞች የሙሴ ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ፡ ከአዝሙድ፡ ከከሙንና ከእንስላል ዓሥራት ትሰጣላችሁ" የሚለው አባባል ዓሥራት የእግዚአብ ሔር ድርሻ ነው ተብሎ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከተሰጠው አገላለጽ ጋር እንዴት ይታረቃል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

እግዚአብሔር እንደ እኛ እንደ ውሱኖቹ ፍጥረቶች የተወሰነ ድርሻ ብቻ ያለው አይደለም። ኹሉ ነገር የተፈጠረው በእርሱ ነው፡ ኹሉም የእርሱ ነው። ይኹን እንጂ በዚህ ዓለም በምንኖርባቸው ዘመናት ልንከተላቸው የሚገቡ ደንቦችንና ሥነ ሥርዓቶችን በሰጠን ጊዜ የእርሱ ድርሻዎች መኾናቸውን ከገለጸልን ጉዳዮች መካከል ከገቢአችን ኹሉ ከዓሥር አንዱን እጅ መክፈል ያለብን መኾኑን ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ዓሥራትም ኹነ ሌላ ጉዳይ በተለየ ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ጠቀሜታ ኖሮት ሳይኾን ለምን ይህን ትእዛዝ እንዳዘዘ ለመረዳት የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት።

«እግዚአብሔር አሮንን እንዲህ አለው፤ ለትውልድ የሚተላለፍ ምንም ዐይነት ርስት አትቀበልም፤ ከእስራኤልም ምድር የትኛውም ክፍል ለአንተ አይኾንም፤ እኔ እግዚአብሔር ራሴ ለአንተ ርስትህ ነኝ። እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ የእስራኤል ሕዝብ ለእኔ የምታመጡትን ዓሥራት ኹሉ የሌዋውያን ድርሻ እንዲኾን ሰጥቼአቸዋለሁ፤ ይህም እኔ በምመለክበት ድንኳን ውስጥ ለሚሰጡት አገልግሎት ደመወዝ ይኾንላቸዋል።" (ዘኍ. ም.18 ቍ:20 — 21)

ከላይ እንደተመለከተው ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት የተመደቡት ሌዋውያን የሚተዳደሩት የእስራኤል ልጆች ከገቢአቸው ኹሉ ላይ ከዓሥር አንዱን እጅ አንሥተው ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡ በታዘዙት በዓሥራት ክፍያ ነበር። ከገቢ ኹሉ ከዓሥር አንዱ ክፍል የእግዚአብሔር ድርሻ መኾኑ በሚከተለው ኹናቴ ተገልጾአል።

"ምድሪቱ የምታስገኘው እህልም ኾነ ፍራፍሬ ከዓሥር አንዱ ለእግዚአብሔር የተለየ ነው።" (ዘሌ. ም.27 ቍ:30)

ከገቢአችን ከዓሥር አንዱ እጅ የእግዚአብሔር ድርሻ እንጂ የእኛ አለመኾኑን ተገንዝበን ሳንዘገይ መክፈል አለብን እንጂ ግዴታችንን መርሳት የለብንም። ይህን የዓሥራት ክፍያ ግዴታችንን በምንወጣበት ጊዜ ምን ዐይነት ስሜት ሊኖረን እንደሚገባና በዚህም አድራጎታችን እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግልን የሚያስረዳውን የቃለ እግዚአብሔር ምስክርነት ቀጥለን እንመልከት።

"ለስጦታዎችህ ኹሉ የፈገግታ ገጽታ አክልባቸው፤ የዓሥራት ግዴታህንም ደስ ብሎህ ክፈል። አስቀድሞ ለሰጠህ ለልዑል እግዚአብሔር ዐቅምህ በሚችለው መጠን በልግስና ስጥ፤ ምክንያቱም ጌታ መልካም ውለታ ከፋይ ስለኾነ ሰባት ጊዜ አስበልጦ ይከፍልሃል።" (ሢራ. ም.35 ቍ:9 — 11)



ከእኛ ምንም ጥቅም ሳይጠብቅ ብዙ ውለታ የሚያደርግልን ሰው እርሱ ባለጸጋ ቢኾንም እንኳ አንዳች ነገር ቢጠይቀን ውለታውን እያስታወስን የሚቻለንን ኹሉ ለማድረግ እንጣደፋለን እንጂ ወደኋላ አንልም። ይህንንም የምናደርገው በአንድ በኩል የዚያ ሰው ውለታ ስለሚከብደን እኛም በበኩላችን የምንችለውን በማድረግ የደስታ ስሜትና የኅሊና ዕረፍት ለማግኘት፥ ወይም ደግሞ በሌላ በኩል ምንም ዐይነት ጥቅም ከእኛ ሳይጠብቅ ውለታ የሚውልልን ሰው ጥቅማችን የሚችለውን ያኽል ፈቃዱን ብንፈጽምለት የበለጠ ውለታ እንደሚውልልን በመተማመን ሊኾን ይችላል። በዚሁም ዐይነት እኛ ክርስቲያኖች ብንኾንም ኹሉን ነገር ለሰጠን ፈጣሪ አምላክ በትእዛዙ መሠረት እርሱው ራሱ ከሰጠን በረከት ላይ የዓሥራት ግዴታችንን ብንከፍል ምን እንደሚያደርገልንና እንደሚያደርግልንና ሳንከፍል ብንቀር ግን ምን እንደሚ ደርስብን በነቢዩ አማካይነት የተሰጠንን ማስጠንቀቂያ ቀጥለን እንመ ልከት።

"ከቀድሞ አበቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከሥርዐቴ ፈቀቅ ብላችኋል፤ ሕጌንም አልጠበቃችሁም፤ ይልቅስ ወደ እኔ ተመለሱ፤ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። እናንተ ግን ወደ አንተ ለመመለስ በቅድሚያ ምን ማድረግ አለብን ብላችሁ ትጠይቃላችሁ። ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም የሰረቅንህ በምንድነው ብላችኋል። የሰረቃችሁኝማ በዓሥራትና በበኩራት ነው። እናንተ ይህ ሕዝብ ኹሉ እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ። ይልቅስ በቤቴ ሲሳይ ይበዛ ዘንድ ዓሥራቴንበሙሉወደ ጐተራ አግቡ፤ እናንተ ይህን ብታደርጉ እኔ ደግሞ የሰማይን መስኮቶች ከፍቼ በረከትን አትረፍርፌ ባልሰጣችሁ በዚህ ፈትኑኝ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።" (ሚል. ም.3 ቁ:7 — 10)

አንዳንድ ሰዎች ዓሥራት ይከፈል የነበረው በዘመነ ኦሪት ነበር እንጂ በሐዲስ ኪዳን ግን ግዴታ አይደለም ይላሉ።

በብሉይ ኪዳን ከታዘዙት ትእዛዞች መካከል በሐዲስ ኪዳን ለሚከሠቱ ጉዳዮች በምሳሌነት፥ በምልክትነት ማለት በጥላነት የቀረቡ ካልኾኑ በቀር ተሰርዘዋል ወይም ቀርተዋል ለማለት አይቻልም። የዓሥራ ት ክፍያም ቋሚ ትእዛዝ ነው እንጂ ለምንም ነገር ምሳሌ ወይም ጥላ ኾኖ የቀረበ አይደለም።



www.ethiopianorthodox.org

በሌላ በኩል ደግሞ የዓሥራት ግዴታ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ያልተ
ሻረ መኾኑን ለመረዳት የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት።

አንደኛ/በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23 ቁጥር 23 ላይ ጌታ አይሁ
ድን በገሠጸበት ትምህርቱ "እናንተ ግብዞች የሙሴ ሕግ መምህራ ንና
ፈሪሳውያን ወዮላችሁ፤ ከአዝሙድ፥ ከከሙንና ከአንስላል ዓሥ ራት
ትሰጣላችሁ፡ ነገር ግን በሕግ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ነገሮች ትተ
ዋላችሁ፡ እነርሱም ፍርድ፥ ምሕረትና ታማኝነት ናቸው፤ ያንን ሳት
ተው ይህንንም ማድረግ ይገባችሁ ነበር" ብሎአቸዋል።

በጥቅሱ ላይ ግልጽ ኾኖ እንደተመለከተው ፈሪሳውያንና የሙሴ
ሕግ መምህራን የተወቀሱት የዓሥራት ግዴታቸውን በጥንቃቄ ቢከፍ
ሉም ፍርድን፡ ምሕረትንና ታማኝነትን በመተዋቸው ነው። ፍርድ፥
ምሕረትና ታማኝነት ከዓሥራት ክፍያ ጋር አብረው መቀጠል
የነበረባቸው መኾኑ ተነግሮአቸዋል።

በዚህም መሠረት የዓሥራት ክፍያ ግዴታ መኾኑን መድኀኒታችን
አረጋግጦልናል።

ኹለተኛ/ ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ምዕራፍ 7 ላይ
የመልከጼዴቅ ለክርስቶስ ምሳሌነት በተዘረዘረ ጊዜ እንደ ካህንነቱ
ለአብርሃም ዓሥራት የተቀበለ መኾኑ ተገልጾአል። መልከጼዴቅ ትል
ቅነቱ የተነገረለት ከሌዊ ቅድመ አያት ከአብርሃም ዓሥራት በመ ቀበሉ
ነው ተብሎ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ እንደማስረጃ መቅረቡ የዓሥራት
ግዴታ በሐዲስ ኪዳንም የቀጠለ እንጂ ያልቀረ መኾኑን ያመለክተናል።

ሦስተኛ/ የዓሥራት ክፍያን በሚመለከት የሐዋርያት ትምህርት
በኾነው በዲድስቅልያ የተሰጠውን መግለጫ ቀጥለን እንመልከት።

"የተመረጠች የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሆይ፥
ስሙ፡- ሕዝቡ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ሕዝብ፥ ምርጥ ሕዝብ ይባል
ነበር፤ እናንተም አሁን በሰማይ የተመዘገበችው የእግዚአብሔር ቤተ ክር
ስቲያን፥ የእግዚአብሔር መንግሥትና ካህናት፥ ንጹሕ ሕዝብ፥ የጌታ
ሕዝብ፥ ታላቋ ቤተ ክርስቲያን፥ አማኝዋ ቤተ ክርስቲያን ናችሁ። በመ



ጀመሪያ የተነገረውና እኛም ደግመን የምንነግራችሁ ከቀድሞ ጀምሮ
ስለት፥ ዓሥራትና በኩራት ለኢየሱስ ክርስቶስ ካህናት እንዲቀርቡ
የተወሰነ መኾኑን ነው።" (ዲድስቅልያ አንቀጽ 6)

አራተኛ/የዓሥራት ክፍያ በሐዲስ ኪዳን ያልተሻረ መኾኑን
ለማመልከት ተብሎ ነው በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 18 ላይ "የቄሳርን
ለቄሳር፥ የእግዚአብሔርን ደግሞ ለእግዚአብሔር ስጡ" ብሎ ጌታ
የሰጠው መመሪያ የተጠቀሰው (ማቴ. ም.22 ቁ:21)

ስለ ዓሥራት ለእግዚአብሔር የተለየ ድርሻነት ሌሎችም
ማስረጃዎች ካስፈለጉ ዘፍ. ም.28 ቁ:22፥ ዘጸ. ም.12 ቁ:5 — 18፥
ም.14 ቁ:22 — 29፥ 2ኛ ዜመ. ም.31 ቁ:5፥ ነህ. ም.10 ቁ:37
ይመለከቷል።

ስለዚህ ከላይ በቀረቡት ማስረጃዎች መሠረት የዓሥራት ክፍያ
ቋሚ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ሲኾን ለጥያቄ የቀረበው ጥቅስ የተሟላ
በለመኾኑ ነው እንጂ አባባሎቹ ርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ኾነው
አይደሉም።

41 በማቴዎስ ወንጌል ም.24 ቁ.:26 — 51፥ በማርቆስ ወንጌል ም.13
ቁ:32 — 37፥ በሉቃስ ወንጌል ም.17 ቁ:26 — 30, 34 — 36 እና
በ1ኛ ተሰሎንቄ ም.5 ቁ:1 እና 2 እንደተመለከተው ጌታ ዳግመኛ
የሚመጣበት ጊዜ በድንገት መኾኑና ያንን ጊዜ ደግሞ ከእግዚአብሔር
በቀር ማንም ሊያውቀው የሚችል አለመኖሩ ተገልጾ ሳለ በራእየ ዮሐንስ
ም.20 ቁ:1 — 10 ስለ ጌታ ምስክርነትና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶ
ቻቸው የተቈረጡባቸው ተነሥተው ከክርስቶስ ጋር ሺ ዓመት ነገሡ
የሚለውን ራእይ ቃል በቃል በመውሰድ ጌታ ከመጨረሻው ፍርድ በፊ
ት ወደዚህ ዓለም መጥቶ ለሺ ዓመት ምድራዊ ንግሥ ይነግሣል የሚሉ
ወገኖች አሉ።

በወንጌልና በልዩ ልዩ መልእክቶች ስለጌታ ዳግመኛ መምጣት
በተነገረበት ጊዜ ኹሉ ማንም ሊያውቀው በማይችልበት ጊዜ ለመጨረ
ሻው ፍርድ አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚመጣ እንጂ በቅድሚያ ለሺ ዓመት
ምድራዊ ንግሥ እንደሚመጣ አልተነገረም።



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሕማሙና ስለ ሞቱ፥ በሦስተኛው ቀን ከሞት የሚነሣ ስለመኾኑ የአስቆሮቱ ይሁዳ አሳልፎ የሚሰጠው ስለመኾኑ፥ ሐዋርያው ጴጥሮስ አላውቀውም ብሎ የሚክድ ስለመኾኑ፥ ስለኢየሩሳሌም መፍረስ፥ ከዕርገቱ በኋላ መንፈስ ቅዱስን የሚልክላቸው ስለመኾኑ፥ በመጨረሻው ዘመን ለፍርድ ተመልሶ የሚመጣ ስለመኾኑና ስለ ሌሎችም ልዩ ልዩ ጉዳዮች አስቀድሞ በግልጽ የተናገረ መኾኑን በመመስከር ወንጌላውያን መዝግበውታል። አንዳንዶቹን ጉዳዮች አንድ ጊዜ ብቻ ሳይኾን በየጊዜው መላልሶ ተናግሯቸዋል። ማንም እንደፈለገ ሊረዳው በማይችለው በራእይ መጽሐፍ ማስረጃነት ተነሥተው ጌታ ለሺ ዓመት ምድራዊ ንገሥ ይነግሣል የሚሉት ወገኖች አባባል ትክክል ቢኾን ኖሮ ይህን የሚያኽል ታላቅ ሃይማኖታዊ ትንቢት አንድ ጊዜ እንኳን በጌታ ሳይነገር ባልታለፈም ነበር። ምናልባት እርሱ ተናግሮት ወንጌላውያን ሳያቀርቡት ቀሩ እንዳይባል አራታቸውም ረሱት ለማለት የማይመስል አባባል ከመኾኑም በላይ የመንፈስ ቅዱስ ጥበቃ ያልተለያቸው መኾኑንም መዘንጋት የለብንም (2ኛ ጢሞ. ም.3 ቍ:16) ይህም ብቻ ሳይኾን ከጳውሎስ መልእክቶች፥ ከጴጥሮስ መልእክቶች፥ ከዮሐንስ መልእክቶች፥ እንዲሁም ከያዕቆብና ከይሁዳ መልእክቶች በአንዳቸው ስንኳ የሺ ዓመ ምድራዊ ንግሥ ጉዳይ አልተጠቀሰም።

ወንጌላዊው ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ የጠቀሰው የሺ ዓመት ምድራዊ ንግሥ ጉዳይ ቃል በቃል የሚወሰድ መኾኑን አምኖበት ቢኾን ኖሮ በወንጌሉ ወይም ከሦስቱ መልእክቶች በአንዳቸው ሳይጠቅሰው ባላለፈም ነበር። እንዲያውም በዮሐንስ ወንጌል ም.5 ቍ28 እና 29 ላይ "በዚህ ነገር አትደነቁ፤ ምክንያቱም በመቃብር ውስጥ ያሉት ኹሉ የእርሱን ድምፅ የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል፤ መልካም የሠሩ ከሞት ተነሥተው በሕይወት ይኖራሉ፤ ክፉ የሠሩ ግን ከሞት ተነሥተው ይፈረድባቸዋል" ብሎ የጌታን ቃል በሚመዘግብበት ጊዜ አነ ኖበትና በመንፈስ ቅዱስም ተመርቶ መኾኑ ግልጽ ነው። የጥቅሱን አባባል የተመለከትን እንደኾነ በመቃብር ውስጥ ያሉት ኹሉ አንድ ጊዜ ተነሥተው ጻድቃን እንደጽድቃቸው ኀጢአተኞችም እንደኀጢአታቸው ዋጋቸውን ከመቀበላቸው በቀር የተወሰኑ ጻድቃን ቀደም ብለው ተነሥተው ከጌታ ጋር ሺ ዓመት ይነግሣሉ አልተባለም። ይህም አባባል የዮሐንስን ትክክለኛ እምነት ያመለክተናል።



ጌታም በዚህ ዓለም ላይ ምድራዊ ንግሥ እንደማይነግሥ ለጲላጦስ ሲያረጋግጥለት መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለም ብሎታል። (ዮሐ. ም.18 ቍ:36) ይህንንም አባባል የመዘገበው ሐዋርያው ዮሐንስ መኾኑን እናስተውል።

በራእየ ዮሐንስ ውስጥ የተመዘገበው ትንቢት በመኾኑና ትንቢትን፥ ራእይንና ሕልምን ደግሞ ማነኛውም ሰው ባሻው ሊተረጉመዉ ስለማይችል በዚሁ ምክንያት ራእይን የአንድ መሠረታዊ እምነት መነሻ ማድረግ አግባብ አይደለም፤ ምክንያቱም ራእይና ትንቢት መንፈስ ቅዱስ የገለጸላቸው ሰዎች ካልተረጉሙት በቀር ትንቢቱ የሚፈጸምበት ጊዜ ደርሶ ከመፈጸሙ በፊት ሊታወቅ አይችልምና። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ የሚከተለውን ማብራሪያ የሰጠው "ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ኹሉ ማንም በገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩ።" (2ኛ ጴጥ. ም.1 ቍ:20 – 21)

የትንቢትም ትርጉም በጣም ከባድ ከመኾኑ የተነሣ አንዳንድ ጊዜ ትንቢቱን ለተናገሩት ሰዎች እንኳ ምሥጢር የሚኾንበት ጊዜ መኖሩን ለመገንዘብ በትንቢት ዳንኤል ም.12 ቍ:8 – 9 እና በትንቢተ ዘካርያስ ም.4 ቍ:4 – 6 መመልከት እንችላለን።

ራእይንና ሕልምን ማንም ሰው ሊተረጉማቸው ባለመቻሉ ነው የፈርዖንን ሕልም ለመተርጎም ጻድቁ ዮሴፍና የናቡከደነፆርን ሕልም ለመተርጎም ደግሞ ነቢዩ ዳንኤል ያስፈለጉት። (ዘፍ.ም.41፥ ዳን. ም.2)

በትንቢተ ሚልክያስ ም.4 ቍ:5 – 6 በኤልያስ ስም የተነገረው ትንቢት ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የተነገረ መኾኑን ጌታ ኢየሱስ የገለጸው የትንቢት አባባል ቃል በቃል የሚወሰድ ባለመኾኑ ነው። (ማቴ. ም.17 ቍ:10 – 12)

አንዳንድ አባቶች እንደተረጎሙት ይህ ሺ ዓመት የተባለው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በምእመናን አድሮ ከፍተኛ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ



www.ethiopianorthodox.org

የሚፋጠንበትና በዚህም ሰይጣን ድል የሚኾንበት አንድ የተወሰነ የጊዜ ርዝመት በመኾኑና በክርስቶስ ትምህርትና በክርስቲያናዊ እምነት አማካይነት የሰይጣን ተንኰል ድል በመነሣቱ ክርስቶስ በምድር ላይ ነገሠ ተባለ። ይህም ማለት ሕግጋቱና ትእዛዛቱ በዚህ ዓለም በተግባር ላይ ዋሉ ማለት ፈቃዱ በሰማይ እንደኾነች እንዲሁም በምድር ኾነች ማለት ነው። ቅዱሳኑም በክርስቶስ ትምህርት ተግባራዊነት ሰይጣንን ድል በመንሣታቸው ከክርስቶስ ጋር ነገሡ ተባለ እንጂ ምድራውያን ነገሥታት የሚነግሡት ምድራዊ ንግሥ ይነግሣሉ ማለት አይደለም።

ሌሎች ምሁራን ደግሞ በራእየ ዮሐንስ የአንድ ሺ ዓመት ንግሥ ምን ማለት እንደኾነ በትክክል ለማወቅ የሚቻለው ወደፊት ጊዜው ደርሶ ሲፈጸም ነው እንጂ አሁን እኛ በፈቃዳችን እንደዚህ ነው ወይም እንደ ዚያ ነው ብለን ለመተርጐም እንችልም ብለዋል።

42. በማቴዎስ ወንጌል መ.26 ቍ.6–9:- "ኢየሱስ በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት ሳለ አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ የበዛ ሽቱ የሞላው የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ይዛ ወደ እርሱ ቀረበች፤ በማዕድም ተቀምጦ ሳለ በራሱ ላይ አፈሰሰችው። ደቀ መካሙርቱም ይህን አይተው ተቈጡና:- ይህ ጥፋት ለምንድነው? ይህ በብዙ ዋጋ ተሸጦ ለድኾች ሊሰጥ ይቻል ነበርና አሉ" ይላል።

በማርቆስ ወንጌል ም.14 ቍኢ.3–5 "እርሱም በለምጻሙ በስም ዖን ቤት በነበረ ጊዜ በማዕድ ተቀምጦ ሳለ አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ የከ በረ ጥሩ የናርዶስ ሽቱ የመላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ ይዛ መጣች፤ ቢልቃጡንም ሰብራ በራሱ ላይ አፈሰሰችው። አንዳንዶችም። ይህ የሽቱ ጥፋት ለምንድነው? ይህ ሽቱ ከሦስት መቶ ዲናር በሚበልጥ ዋጋ ተሸጦ ለድኾች ሊሰጥ ይቻል ነበርና ብለው በራሳቸው ይቈጡ ነበር፤ እርስዋንም ነቀፉአት" ያለ ሲሆን በዮሐንስ ወንጌል ም.12 ቍ.3–5:- "ማርያምም ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፤ በጠጉርዋም እግሩን አበሰች፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ። ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ፤– ይህ ሽቱ በሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድኾች ያልተሰጠ ስለምን ነው? አለ።"



ሦስቱ ወንጌላውያን በሦስት ነጥቦች ተለያይተዋል። የመጀመሪያው ልዩነት ማቴዎስና ማርቆስ ሽቱውን በራሱ ላይ አፈሰሰችው ሲሉ ዮሐንስ ግን እግሩን ቀባችው ብሏል። ኹለተኛው ልዩነት ማቴዎስ ነገሩን የተቃወሙት የጌታ ደቀ መዛሙርት ናቸው ይላል። እንደማርቆስ አባባል ተቃዋሚዎቹ ከነበሩት አንዳንድ ሰዎች ናቸው። ዮሐንስ ደግሞ ተቃ ዋሚው የአስቆሮቱ ይሁዳ ነው ብሏል። ሦስተኛው ልዩነት ደግሞ ማቴ ዎስ የሽቱውን ዋጋ አልተመነውም፤ ማርቆስ ከሦስት መቶ ዲናር ይበ ልጣል ሲል ዮሐንስ ግን ሦስት መቶ ዲናር ያወጣል ብሏል።

ታዲያ ወንጌላውያኑ ይህን ታሪክ በሚያቀርቡበት ጊዜ ለምን ተለ ያዩ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ከሌሎቹ ወንጌላውያን ዘግየት ብሎ በመኾኑና የሌሎቹን ጽሑፍ የተመለከተ በመኾኑ አንዳንድ እነርሱ ሳይ ጽፉአቸው ያለፉአቸውን ድርጊቶች እያሟላ ስለጻፈ የእርሱ አቀራረብ ከእነርሱ ለየት የሚልበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ በዚህ ታሪክ ውስጥ ኹለቱ ወንጌላውያን ሽቱውን በጌታ ራስ ላይ እንዳፈሰሰችው ሲናገሩ ዮሐንስ ግን እግሩን ቀባችው ብሏል። እነርሱ አንዲት ሴት ሲሉ ዮሐንስ ግን ማርያም መኾንዋን ገልጾአል። በቦታው የተገኙት ሰዎችና ደቀ መዛ ሙርቱ ቅሬታቸውን የገለጹ መኾናቸውን ማቴዎስና ማርቆስ ቢገል ጹም ዮሐንስ ግን በበለጠ ቅሬታውን የገለጸው ይሁዳ መኾኑን ሳይጠ ቍም አላለፈም።

የተለመደው አሠራር ሽቱ የሚቀባው ጸጉር ላይ በመኾኑ ያቺ ሴት በራስ ጸጉሩ ላይ ካፈሰሰችበት በኋላ እግሩንም የቀባችው ስለኾነ ዮሐንስ ያንን የታወቀውንና የተለመደውን አሠራር ትቶ የእግሩን መቀባት ብቻ አወራ። ከተደረጉት ድርጊቶች አንደኛው ሳይናገረው ሌላው አሟላው እንጂ ልዩነት ተፈጠረ ማለት አይደለም።

ሌሎች ተርጓሚዎች ደግሞ ሴትዮዋ በጌታ ራስ ላይ ያፈሰሰችው ሽቱ በጣም ብዙ ስለነበረ እስከ እግሩ ድረስ በመውረዱ እግሩ ላይ እንዳ ፈሰሰች ተቈጠረ እንጂ እግሩ ላይ አፍስሳው አይደለም ብለዋል።



www.ethiopianorthodox.org

ዮሐንስ ዋና ሊናገር የፈለገው የማርያም መግደላዊትን ትሕትናና የይሁዳን ገንዘብ ወዳድነት ነው። ማቴዎስና ማርቆስ ስም ሳይጠቅሱ በሚናገሩበት ጊዜ ዮሐንስ ግን በስም ጠርቶ መናገርን አስፈላጊ ኾኖ ያገኘው ይመስላል።

ስለዚህ አንዱ የተወውን ሌላው ያሟላው ከመኾኑ በቀር ልዩነት የላቸውም።

43. በማቴዎስ ወንጌል ም.26 ቍ.29 ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በአባቱ መንግሥት ከወይኑ ፍሬ አዲሱን እንደሚጠጣ ቃል የገባ ሲኾን በሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ም.14 ቍ.17 ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት መብልና መጠጥ አለመኾኑ በመገለጹ እነዚህ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስል ይኾናል።

በሰማይ ምግብንና መጠጥን የመሳሰሉ የሥጋ ፍላጎቶች የሉም። በመዝሙር 78 ቍ.25 ላይ:- "የሰው ልጅ የመላእክትን ምግብ በላ" የሚል እንደመኾኑ እንዴት በሰማይ ምግብ የለም እንላለን ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ከሰማይ ስለወረደ የመላእክት ምግብ መሰላቸው እንጂ መላእክትስ እንደሰው ምግብ የሚመገቡ ኾነው አይደለም። ለምሳሌ ከጦቢያ ጋር የነበረው መልአክ ማለት መልአኩ ሩፋኤል ለሽማግሌው ጦቢትና ለጦቢያ ማንነቱን በገለጸላቸው ጊዜ በእነርሱ ፊት የበላ የመሰላቸው ከማስመሰሉ በቀር እንዳልበላ ነግሮአቸዋል። (ጦቢ.ም.12 ቍ.19) ስንኳንስ መልአክ ይቅርና በእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋን የተጐናጸፉ ማለት ጻድቃንም ቢኾኑ የማይራቡና የማይጠሙ መኾናቸው በራእየ ዮሐንስ ም.17 ቍ.16 መመልከት እንችላለን። ካልተራቡና ካልተጠሙ ደግሞ መብላትና መጠጣት አያስፈልጋቸውም። በሌላ በኩል ደግሞ በእስራኤሎች ዘንድ ወይን የሚጠጣው ከግብጽ ባርነት ነጻ የወጡበትን ቀን አስታውሶ ለመደሰትና በዐሉም ከብዙ ጥረትና ድካም በኋላ ዕረፍት የሚወሰድበት ጊዜ በመኾኑና የወዳጆች መሰባሰቢያና መደሰቻ ስለኾነ ከኀጢአት ባርነት ድኖ በሰማያዊው ፈቃድ ደስታን ከመጐናጸፍ ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህም ማለት በሕማሙና በሞቱ እኛን ከኀጢአት ባርነት ነጻ አውጥቶ ከሞት ከተነሣ በኋላ ማለት ነው።



የኑሲሱ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ይህን ጥቅስ በተረጐመበት ድርሳኑ እንዲህ ብሏል:- "ደቀ መዛሙርቱ ቅድስት ንጽሕት ትንሣኤውን በችንካር የተቸነከረ የእጁን የእግሩን አትራት ካዩ በኋላ፣ በጦር የተወጋ የጎኑንም አትራት ከዳሰሱ በኋላ አርባ ቀን ያኽል አብሮቸው ከበላ ከጠጣ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ። ...በአባቴ መንግሥት (ትንሣኤ) አዲስ አድርጌ ከእናንተ ጋር እስከምጠጣበት ቀን ድረስ እኔ ከዚህ የወይን ፍሬ ማቴ አልጠጣም ያላቸው መጠጥ ይህ ነው። ነገር ግን ለሰው ከትንሣኤ በኋላ ሥጋዊ መብል መጠጥ አለ ብሎ ማንም አያስብ፤ በሥጋው መፍረስ መበስበስ አለ ብለው እንዳያስቡ ጌታችን የሥጋውን መነሣት ያስረዳ ዘንድ በላ ጠጣ እንጂ ከትንሣኤ በኋላ ሥጋዊ መብል ሥጋዊ መጠጥ እንደሌለ ዕወቁ።" (ሃይ:አ:ገጽ 127)

እንዲሁም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህንኑ የጌታ ኢየሱስን አባባል በተረጐመበት ድርሳኑ እንዲህ ብሏል:- "ሐዲስ ያለው ይህ ነገር ምንድነው? ይህ ነገር ድንቅ ነው፤ መዋቲ ሥጋ እንዳለኝ ታያላችሁ፤ ነገር ግን ከትንሣኤ፣ በኋላ የማይሞት ነው፤ አይለወጥም፤ ሥጋዊ መብልንም መሻት የለበትም፤ ከትንሣኤ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ቢበላም፣ ቢጠጣም መብልን ሽቶ አይደለም፤ እርሱ ከሙታን ተለየቶ እንደተነሣ ያምኑ ዘንድ፤ በላ፤ ጠጣ እንጂ።" (ሃይ. አበ. ገጽ 236)

የመላእክትን ምግብ በሉ በሚልበት ጊዜ ደግሞ በመላእክት እጅ የወረደውን ምግብ በሉ፤ ወይም ደግሞ የመላእክትን ምስጋና አመሰገኑ ማለት ይኾናል።

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት አባባሎች የተለያዩ ትርጓሜዎች አሉአቸው እንጂ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አባባሎች አይደሉም።

44. በማቴዎስ ወንጌል ም.26 ቍ.39 ላይ ያቺ ጽዋ ትቀርለት ዘንድ ጌታ ኢየሱስ ለአብ የጸለየ ሲኾን በዮሐንስ ወንጌል ም.10 ቍ.17 እና 18 ላይ ደግሞ:- "ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ ፈቃደኛ ስለኾንኩ አብ እኔን ይወደኛል። ሕይወቴን በፈቃዴ አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ መብት አለኝ" ከማለቱም በላይ ይህን አባባሉን በተግባር ሲገልጸው ነፍሱ ከሥጋው በምትለይበት ጊዜ "አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ" በማለት በአደራ መልክ አብ ዘንድ



www.ethiopianorthodox.org

እንዲቈይለት ከማድረጉ በቀር ነፍሱን ለማንም አሳልፎ አልሰጠም። (ሉቃ.ም.23 ቍ.46)

እነዚህ ኹለት አባባሎች እርስ በርሳቸው ይቃረኑ ይመስለን ይኾናል።

በዕለተ ዓርብ ዋዜማ ጌታ በጌቴሴማኒ ያትልክት ቦታ ያደረጋቸው ድርጊቶች ኹሉ በጭንቀት ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባን ለእኛ ትምህርት ሊሰጠን ፈልጎ ብቻ ነው። ወደፊተና አታግባን የሚለውን ጸሎት ባስተማረን መሠረት በተፈጥሮ ደካማነታችን ምክንያት በፍላጎታችን ሕማማትን ለመቀበል እንዳንቸኩል ሊያስተምረን ፈልጎ ነው እንጂ የሕማማቱና የሞቱ ጽዋ እንዲቀርለት ለመጸለይ አይደለም። ሕማሙን ላለመቀበልና ላለመሞት ቢፈልግ ኖሮ ምንም ባላስቸገረውም ነበር ለምሳሌ ከምኵራብ ራብ አስወጥተው ከተማቸው ከተሠራችባት ከተራራው አፋፍ ወደታች ሊጥሉት ሲፈልጉ በመካከላቸው አልፎ የኼደ መኾኑ በሉቃስ ወንጌል ም.4 ቍ.30 ላይ ተገልጾአል። አብርሃም ሳይ ወለድ እኔ አለሁ ባላቸው ጊዜ ሊወግሩት ድንጋይ ሲያነሡ ተሠውሮባቸው ከመቅደስ ወጥቶ በመካከላቸው አልፎ የኼደ መኾኑን በዮሐንስ ወንጌል ም.8 ቍ.59 ለመመልከት እንችላለን። እርሱ በፍላጎቱ ራሱን ሰጠ እንጂ ሊይዙት የመጡት ሰዎች ኢየሱስን እንፈልጋለን ባሉት ጊዜ እኔ ነኝ በማለት መለኮታዊ መልስ ሲሰጣቸው ወደኋላ አፈግፍገው በምድር ላይ የወደቁ እንደመኾናቸው እርሱ ቢፈልግ ኖሮ ራሱን ማዳን ባላቃተውም ነበር። (ዮሐ.ም.18 ቍ.6) እንዲያውም ጴጥሮስ ጌታን ሊይዙ ከመጡት ሰዎች መካከል ማልኮስ የተባለውን የሊቀ ካህናቱን አሽከር በሰይፍ ጆሮውን በቈረጠው ጊዜ ሰይፍን የሚመዝዙ በሰይፍ የሚጠፉ መኾናቸውን ገልጾ ጴጥሮስን ከገሠጸው በኋላ የተቈረጠውን ጆሮ እንደነበረ መልሶለታል። (ሉቃ.ም.22 ቍ.50–51፥ ዮሐ..18 ቍ.10–11) ይህም ብቻ ሳይኾን የመጻሕፍት አባባል ይፈጸም ዘንድ የግድ ሕማም ተቀብሎ መሞት ስላለበት ነው እንጂ እርሱ ቢፈልግ ብዙ የመላእክት ሠራዊት አብ ሊልክለት እንደሚችል ገልጾአል። (ማቴ.ም.26 ቍ.52–54፡ ሉቃ.ም.22 ቍ.51)



በጌቴሴማኒ ኾኖ ባደረገው ጸሎት በኹሉም ነገር እኛን እንደሚመስል ያስተምረናል። ባይጸልይ ኖሮ አባቱን ብቻ እንጂ እኛን አይመስልም ነበር።

በዚህም መሠረት ፈተና በሚያጋጥመን ጊዜ ኹሉ በጸሎት እንድንተጋ ሊያስተምረን ፈልጎ ነው እንጂ ጽዋው እንዲቀርለት ፈልጎ አይደለም።

45. በማቴዎስ ወንጌል ም.26 ቍ.52 ላይ፡ "ሰይፍ የሚያነሡ ኹሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስገባው ክተት" ብሎ ሰይፉን የከለከለ ሲኾን በሉቃስ ወንጌል ም.22 ቍአ..35 እና ቍ.36 ላይ "ያለ ኮረጆና ያለ ከረጢት፥ ያለጫማም በላክኋችሁ ጊዜ አንዳች ጐደለባችሁን አላቸው እነርሱም ምንም አልጐደለብንም አሉ። እርሱም አሁን ግን ኮረጆ ያለው ከእርሱ ጋር ይውሰድ፥ ከረጢትም ያለው እንደዚሁ፡ የሌለው ልብሱን ሸጦ ሰይፍ ይግዛ" በማለቱ ከፊተኛው አባባል ጋር ተቃራኒ ትእዛዝ የሰጣቸው ይመስል ይኾናል።

መድኀኒታችን በዚህ በሉቃስ ወንጌል ላይ በተጠቀሰው አባባሉ ደቀ መዛሙርቱ ወደፊት የሚደርስባቸውን ችግር በማመልከት ምክርና መመሪያ ሊሰጣቸው የፈለገ መኾኑን ያመለክታል። በዚህም የመጀመሪያውንና ኹለተኛውን አላላካቸውን ለማነጻጸር እንችላለን። በመጀመሪያ ለአገልግሎት በተላኩበት ጊዜ "በትርም ቢኾን፥ ከረጢትም፥ እንጀራም ቢኾን፥ ብርም ቢኾን፥ ለመንገድ ምንም አትያዙ ኹለት እጀ ጠባብ አይኹንላችሁ» ተብለው ነበር። (ሉቃ.ም.9 ቍ.3) ይህም የኾነበት ምክንያት ጉዞአቸው አጭር፥ የሚኼዱባቸው ሰዎች እነርሱን ለመቀበል ዝግጁዎች የነበሩ ዘመዶቻቸው በመኾናቸው ለጉዞ የሚያስፈልጉአቸው ጉዳዮች ባይኖሩአቸውም ችግር እንደማይደርስባቸው ስለታመነ ነው። የኹለተኛው የአገልግሎት ጉዞአቸው ግን የወንጌልን ትምህርት ለማስፋፋት ወደባዕድ አገር የሚኼዱት ረጅም ጉዞ በመኾኑና ብዙም ችግር ሊያጋጥማቸው ስለሚችል በቂ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባቸው ለማመልከት ነው። የሌለው ሰው ልብሱን ሸጦ ሰይፍ ይግዛ ማለቱ ግን በምእመናን ሊደርስ የሚችለውን ችግር መጠንና ለዚያም በቂ መከላከያ ማድረግ የሚገባ መኾኑን ሊገልጻላቸው ፈልጎ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

የጌታ ኢየሱስ ንግግር የሚያመለክተው ወደፊት በምእመናን ላይ ስላለው የችግር ዘመን፥ አደጋ፥ ስደትና ሞት አስፈላጊ የሚኾነውን የመከላከያ ዘዴ ማመቻቸት እንደሚገባ ለመግለጽ ነው በዚህም መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ አይሁድ ሊያደርሱበት ካቀዱት የአደጋ ተንኰል ለመከላከል በሮማዊ ዜግነቱ ዘዴ የተጠቀመ መኾኑን በሐዋርያት ሥራ ም.22 ቍ.25–28 እና ም.25 ቍ11 ለመመልከት እንችላለን። ከጌታ ዕርገት በፊትና በኋላ የነበረው የደቀ መዛሙርቱ ኹናቴ የእስራኤል ልጆችን ኹናቴ ይመስላል። የእስራኤል ልጆች ምድረ ከነዓን ከመግባታቸው በፊት እግዘአብሔር መና ከሰማይ አውርዶ ይመግባቸው ነበር፤ ቀን በደመና ሌሊት ደግሞ በብርሃን ዓምድ ይመራቸው ነበር። (ዘደ.ም.13 ቍ .21) ወደ ምድረ ከነዓን በደረሱ ጊዜ ያ ኹሉ የሚደረግላቸው ድርጊት ቀርቶ ጥረው ግረው የኑሮ ፍላጎታቸውን እንዲያሟሉ ተገደዱ። ይህም የኾነበት ምክንያት ከዚያ በኋላ ለኑሮአቸው አስፈላጊ የኾነውን ምርት የሚያስገኝ ለምለም የኾነ አገር የሰጣቸው በመኾኑ ከሰማይ መና ማዝነብን አስፈላጊ ኾኖ ስላላገኘው ነው። በተጨማሪም በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንተው የሚኖሩ ከኾነ በረከቱን እንደሚያበዛላቸው የገለጸላቸው መኾኑን በኦሪት ዘዳግም ም.30 መመልዘት እንችላለን ። በዚህም ዐይነት ከዕርገቱ በፊት ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ልክ እንደ ወላጅ አባት ይመራቸው፥ ይረዳቸውም ነበር። ከዕርገቱ በኋላ ግን እንደቀድሞው በኹሉም ነገር እጆቻቸውን ይዞ መምራቱን አስፈላጊ ኾኖ ስላላገኘው አመቺ በኾነ ዘዴ ኹሉ ለራሳቸው መከላከያ እንዲያዘጋጁ የተዋቸው ረዳት መንፈስ ቅዱስን የላከላቸው በመኾኑና የመንፈስ ቅዱስንም ትምህርት በሚገባ ከተከታተሉት በማንኛውም ችግር ጊዜ የሚረዳቸው በመኾኑ ነው። (ሮሜ ም.10 ቍ .13 እና 14፥ ዕብ.ም.6 ቍ.4–6) ጌታም ኮረጆ፥ ከረጢትና ሌሎችንም አስፈላጊ ነገሮችን ያዙ ማለቱ ክርስቲያኖች ኹሉ በሥራቸው አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ አለባቸው እንጂ በየድርጊታቸው የእግዚ አብሔርን በረከት መጠበቅ የለባቸውም ለማለት ነው። የሌለው ልብሱን ሸጦ ሰይፍ ይግዛ ባላቸው ጊዜ ጌታ ሆይ እዚህ ኹለት ሰይፎች አሉ ቢሉት ይበቃል ማለቱ የእርሱ አባባል ያልገባቸው በመኾናቸው በሉ የዚህን ጉዳይ መነጋገር ይበቃልና እናቁም ማለቱ ነው። በዚሁ በተመሳሳይ ቋንቋ ነው ሙሴ እግዚአብሔር ይቅርታ አድርጎለት ወደ ተስፋ ምድር ገብቶ ለማየት እንዲችል በጸለየ



ጊዜ "ይበቃሃል በዚህ ነገር ደግመህ አትነጋገረኝ" ያለው። (ዘዳ..3 ቍ.26)

46. በማቴዎስ ወንጌል ም.27 ቍ .5 ይሁዳ ታንቆ የሞተ መኾኑ ሲነገር በሐዋርያት ሥራ ም.1 ቍ.18–19 ደግሞ በግንባሩ ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰንጥቆና እንዲሁም አንጀቱ ኹሉ የተዘረገፈ መኾኑ በመገለጹ በኹለቱ ጥቅሶች መካከል ልዩነት ያለ ይመስል ይኾናል።

የማቴዎስ ወንጌል ይሁዳ መታነቁን ከመናገሩ በቀር ከዚያ በኋላ የኾነውን ኹናቴ አልገለጸም። ከሐዋርያት ሥራ አገላለጽ እንደሚገመተው ይሁዳ ታንቆ የተሰቀለው በአንድ ተራራማ ወይም ዳገት በኾነ ቦታ ላይ ኾኖ ገመዱ ተበጥሶበት በድንጋያማው ቦታ ስለወደቀ ያ ከላይ የተጠቀሰው ኹናቴ ደርሶበታል።

47. በማቴዎስ ወንጌል ም.27 ቍ.9 ላይ ኤርምያስ ተብሎ የተጠቀሰው ጥቅስ የሚገኘው በትንቢተ ዘካርያስ ም.11 ቍ.12 ነው እንጂ በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ ባለመኾኑ ለምን ጥቅሱ የማይገኝበት መጽሐፍ ስም ተጠራ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

አይሁድ ብሉይ ኪዳንን በሕግ፥ በመዝሙርና በነቢያት መጻሕፍት ይከፋፍሉአቸው ነበር። የነቢያትን መጻሕፍት በአጠቃላይ ኤርምያስ የሚል ስም ይሰጡአቸው ስለነበረ ኤርምያስ ብሎታል። ይህም የኾነው የኤርምያስ ትንቢት ከሌሎቹ የትንቢት መጻሕፍት በፊት ስለነበረ ነው። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ደግሞ ወንጌላዊው ኤርምያስ ያለው በዕብራይስጡ ቋንቋ የኤርምያስና የዘካርያስ ስም የሚቀራረብ በመኾኑ ነው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ጥቅሱ ቀድሞ በትንቢተ ኤርምያስ የተጻፈ ኾኖ በኋላ ዘካርያስ ሲጽፍ ወስዶት ነው ብለዋል።

48. "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ" (ማቴ.ም.27 ቍ.46) ይህ አባባል የተነገረው በደካማነቱ ምክንያት ወይም መለኮቱ ከእርሱ በመለየቱ እርዳታ ለመጠየቅ ተብሎ ሳይኾን ችግር በሚያጋጥመን ጊዜ የእግዚአብሔርን እርዳታ መለመን እንደሚገባን እኛን ደካማዎቹን ፍጥረቶች ለማስተማር ብሎ ነው። ስለዚህም ነው በማቴዎስ ወንጌል ም.11 ቍ.29 ላይ "ከእኔ ተማሩ" ያለው።



www.ethiopianorthodox.org

በሌላ በኩል ደግሞ ሰው የኾነ አምላክ ማለት ያልተጠፋፋ የመለኮ
ትና የትስብእት ተዋሕዶ በመኾኑ ሕማም ሊሰማው እንደሚችል ግልጽ
ነው። ለእኛ ለሰው ልጆች ድኅነት ሲል ሕማም የተቀበለ መኾኑን ለመ
ረዳት በትንቢተ ኢሳይያስ ም.53 ቍ.4–5 እና በመጀመሪያው የሐዋ
ርያው የጴጥሮስ መልእክት ም.2 ቍ.21 እንዲሁም በምዕራፍ 3 ቍ.18
ላይ ያሉትን ጥቅሶች ለመመልከት እንችላለን። ጌታችንና መድኀኒታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ከኀጢአት በቀር በኹሉም ነገር የሰውን ልጅ መስሏል።
እንደዚህ መኾኑንማ ካላመንን የደረሰበትን ሕማም ኹሉ በም ትሐት
መልክ አሳለፈው እንጂ ሌላ ሰው ቢኾን ኖሮ ሊሰማው የሚችለው
የሕማም ስሜት አልደረሰበትም ብለው የጌታን መሥዋዕትነት ዋጋ ከሚ
ያሳጡት መናፍቃን ከነማኒና ከነመርቅያኖስ ጋር አብሮ እንደመሰለፍ ይቈ
ጠርብናል። በእርግጥ ሕማምና ሞት መቀበልን በፈቃዱ አደረገው እንጂ
ማንም አላስገደደውም። ስለዚህ ነው ጌታ "መልካም እረኛ እኔ ነኝ መል
ካም እረኛ ስለበጎቹ ሕይወቱን አሳልፎ ይሰጣል" ያለው። (ዮሐ.ም.10
ቍ.11)– ይህም ማለት ጌታን እስከ ሞት ድረስ ሊያደርሰው የቻለው
የሰውን ልጅ ለማዳን ያለው ፍላጎትና በሰው ልጅ ላይ ያለው ፍቅር ነው
እንጂ ማንም አስገድዶት አለመኾኑን በዮሐንስ ወንጌል ም.10
ቍ.17–18 ገልጾአል። በምዕራፍ 2 ቍ.19–23 ደግሞ "ይህንን ቤተ
መቅደስ አፍርሱትና እኔ በሦስት ቀኖች እሠራዋለሁ በማለት ስለሞቱና
ስለትንሣኤው በምሳሌ ተናግሮአል። እንዲሁም በሌሎች ጊዜያት
ወደፊት ስለሚደረስበት ሕማምና ሞት ከዚያም ሞትን ድል አድር
እንደሚነሣ በማቴዎስ ወንጌል ም.26 ቍ.17–23፡ በማርቆስ ወንጌል
ም.10 ቍ.17–28፥ በሉቃስ ወንጌል ም.22 ቍ 14–22 እንደተ
ለጸው አስቀድሞ መናገሩ ሕማሙንና ሞቱን አስቀድሞ ራሱ የወሰናቸው
ና በፍላጎቱ የተፈጸሙ ኹነቶች ናቸው እንጂ በሕማሙና በሞቱ ጊዜ
የተናገራቸው አነጋገሮች እኛን ለማስተማር የተነገሩ ከመኾናቸው በቀር
እርሱ የማንንም እርዳታ የማይጠይቅ መኾኑን ተረድተን ከመሳሳት
እንጠንቀቅ። ጥያቄና መልስ ቍ.8፡ 18፡ 27፡ 36፡ 57፥ 61፥ 63
74፥ 75፥ 84፡ 89፡ 91፡ 92፡ 93፡ 102 እና በ1ኛው መጽሐፍ
ቍ:102፥104፥112 ይመለከቷል።

49. በማቴዎስ ወንጌል ም.28 ቍ.9 ላይ መግደላዊት ማርያም
ኹለተኛይቱ ማርያም ወደ ጌታ ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት ይላል



በዮሐንስ ወንጌል ም.20 ቍ.16–17 ላይ ጌታ ኢየሱስ ለማርያም
መግደላዊት በተገለጠ ጊዜ "ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ" ያላት
መኾኑ ተገልጾአል።

ከላይ በተገለጹት ጥቅሶች መሠረት ኹሉ፡ ወንጌላውያን ይህን ታሪ
ክ በሚያቀርቡበት ጊዜ እንዴት ተለያዩ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል። ሴቶች
ወደመቃብሩ ቦታ የመጡበትን ጊዜና ያዩትን ትርኢት በተመለ ከተ
ወንጌላውያን የተለያየ ታሪክ አቅርበዋል።

ማቴዎስ:-"በሰንበት መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት
ማርያምና ኹለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ" ይላሉ (ማቴ.
ም.28 ቍ.1)

ማርቆስ:-"ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም፥ የያዕቆብም
እናት ማርያም ሰሎሜም መጥተው ሊቀቡት ሽቱ ገዙ። ከሳምንቱም
በፊተኛው ቀን እጅግ በማለዳ ፀሐይ ከወጣ በኋላ ወደ መቃብሩ መጡ"
ይላል (ማር.16 ቍ.1–2)

ሉቃስ: "ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው
ከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ" ይላ
ል። (ሉቃ.ም.24 ቍ.1)

ዮሐንስ: "ከሳምንቱ በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም ገና
ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች" ይላል። (ዮሐ.ም.20 ቍ.1)

እንዲሁም ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል ም.28 ከቍጥር አንድ እስከ
ዘጠኝ ድረስ ማርያም መግደላዊትና ሌላይቱ ማርያም መጀመሪያ አንድ
መልአክ ከዚያ በኋላ ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳዩ ተገልጾአል።

በማርቆስ ወንጌል ም.16 ከቍጥር አንድ እስከ ዘጠኝ መግደላዊት
ማርያም የያዕቆብ እናት ማርያምና ሰሎሜ አንድ መልአክ እንዳዩና
ጌታም ለማርያም መግደላዊት እንደተገለጠላት ተነግሮአል።



www.ethiopianorthodox.org

በሉቃስ ወንጌል ም.24 ቍ.1–8 ወደ መቃብሩ የኼዱት ሴቶች ኹለት መላእክት አይተዋል ተብሏል።

በዮሐንስ ወንጌል ም..20 ቍ 11–16 ማርያም መግደላዊት ኹለት መላእክት እንዳየችና ጌታም እንደተገለጠላት ተነግሮአል።ይህ ከላይ የተዘረዘረው አቀራረብ የሚያመለክተው እያንዳንዱ ወንጌላዊ የተናገረው ታሪክ ሌላው ያልተናገረውን መኾኑን ነው። ሴቶች ወደ መቃብሩ ቦታ የኼዱት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይኾን ለብዙ ጊዜና በየጊዜውም የተለያዩ ስብስብ ኾነው ነው። አንድ ጊዜ አንድ ብቻ በሌላ ጊዜ ኹለትና ሦስት እንዲሁም በሌላ ጊዜ ብዛታቸው ያልተገለጠ ሴቶች አብረው ኾነው ወደ መቃብር ቦታ ኼደዋል።

በዚህ መሠረት በማቴዎስ ወንጌልና በዮሐንስ ወንጌል የተመለከቱት ጥቅሶች የተለያዩ ታሪኮችን ከመግለጻቸው በቀር ርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

የጌታን መቃብር ይጠብቁ የነበሩት ሰዎች ከሊቃነ ካህናቱ ጋር ስምምነት ከማድረጋቸው በፊት ስለ ጌታ ከሞት መነሣት በከተማው ኹሉ አዳርሰውት የነበረውን ኤና እያሰላሰለች ማሪያም መግደላዊት በእውነትና በጥርጣሬ መካከል ሐሳብዋ ተበታትኖባት በምታለቅስበት ጊዜ ጌታ ተገልጦላት መምህር ብላ በእግሩ ልትወድቅ ስትል "ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ " ብሏታል።

በተግሣጽ አነጋገር አትንኪኝ ሲላት የሰጠው ምክንያት ገና ወደ አባቱ ያልኼደ መኾኑን ነው። ሞቶ የተነሣ እስከኾነ ድረስ ከእንግዲህ ወዲያ ከእነርሱ ተለይቶ ወደ አባቱ የሚያርግ መኾኑን ገምታ የመሰናበቻ ሰላምታ ለመስጠት ቢቃጣት የመኼጃዬ ማለት የመሰነባበቻው ጊዜ ገና ነው ለማለት ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና ለመሰናበት አትቸኩይ ለማለት አትንኪኝ ብሏታል።

ሌላው ትርጓሜ ደግሞ የልብን ጥልቅ ሐሳብ የሚያውቀዉ ጌታ ማርያም መግደላዊት በኹኔታው ጥርጣሬ ያደረባት መኾኑን በማወቅ ሊገሥጻት ስለፈለገ አትንኪኝ ብሏታል የሚለው ነው።



50. በማቴዎስ ወንጌል መ.28 ቍ.19 ላይ መድኀኒታችን ደቀ መዛሙርቱን ባዘዛቸው ትእዛዝ ላይ:- "ኺዱና የዓለምን ሕዝብ ኹሉ አስተምሩ፤ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁአቸው" በማለት የገለጸው የሦትነት ምሥጢር ቀደም ተብለው በኦሪት ዘዳግም ም.4 ቍ.39፡ ም.6 ቍ.4–5፡ በትንቢተ ኢሳይያስ ም.43 ቍ10፡ ም.44 ቍ.6፥ ም.45 ቍ.21 ላይ እግዚአብሔር አንድ ብቻ መኾኑንና ከእርሱም በቀር ሌላ አምላክ የሌለ ኾኖ አምላክና ስግደትም መደረግ የሚገባው ለዚሁ ለአንድ አምላክ ብቻ መኾን እንዳለበት አጥ ብቆ የሚያስጠነቅቅ በመኾኑ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒ የሚመስሉአቸው ወገኖች አሉ።

ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ፥ ከመጀመሪያዎቹና በኋላም ከተነሡት ቅዱሳን የቤተ ክርስትያን አባቶች በተላለፈልን እምነትና ትምህርት መሠረት እግዚአብሔርን በአንድነትና በሦስትነት እናምነዋለን። የእግዚአብሔርን አንድነት የምናምነው በፈጣሪነት፥ በአምላክነት፥ ማለት በመለኮት በአገዛዝ፥ በፈቃድ፥ በሥልጣንና እነዚህ ንም በመሳሰሉ የመለኮት ባሕርያት ሲኾን ሦስትነቱን የምናምነው ደግሞ በስም፥ በውሳጣዊ ግብርና በአካል ነው።

በስም አብ፥ ወልድ፥መንፈስ ቅዱስ በመባል ሦስት ስሞች ናቸው መውለድና ማሥረጽ የአብ፥መወለድ የወልድ፥ መሥረጽ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ግብሮች ናቸው:: አብ መውለድና ማሥረጽ እንጂ አይወለድም፥ ወይም አይሠርጽም፥ መንፈስ ቅዱስም መሥረጽ እንጂ አይወልድም፥ አያሠርጽም ወይም አይወለድም። በዚህም ምክንያት እነዚያ ግብሮች ውሳጣዊያን ግብሮች ይባላሉ። ሌላው የሦስትነት እምነታችን ደግሞ አካል ነው። አብ የራሱ አካል፥ወልድ የራሱ አካል መንፈስ ቅዱስም የራሱ አካል አለው እንዲሁም አብ ልብ፥ ወልድ ቃል፥ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እስትንፋስ ስለኾኑ አብ የወልድና የመንፈስ



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ልባቸው ወልድ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የአብና የወልድ ሕይወታቸው ወይም እስትንፋሳቸው ማለት መንፈሳቸው ነው እንላለን።

በማቴዎስ ወንጌል ም.13 ቍ.17 ላይ አብ፡ ስለ ወልድ ሲናገር:-"በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" ማለቱ፥ በዮሐ ንስወንጌል ም.11 ቍ .41 ላይ ወልድ አብን ሲያናግረው:- "አባት ሆይ ስለሰማኸኝ አመሰግንሀለሁ" ማለቱና በዮሐንስ ወንጌል ም15 ቍ.26 ጌታ ኢየሱስ ማለት ወልድ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር:- "ነገር ግን ከአብ የሚወጣና እኔም ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኙ የእውነት መንፈስ ሲመጣ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል" በማለት አንዱ ካንዱ ጋርና ሌላው ደግሞ ስለሌላው መናገሩ በአካል ሦስት ስለኾኑ ነው እንጂ ያለበለዚያ ግን እኔ የሚለውን እንጂ አንተ እና እርሱ የተባሉትን ተውላጠ ስሞች ባልተጠቀሙባቸውም ነበር።

በአርዮሳውያንና በሰባልዮሳውያን ዘንድ የሦስትነት እምነት በቅዱሳት መጻሕፍት የተደገፈ አይደለም መባሉ የተለመደ ትችት ነው።

ከሦስቱ መለኮታዊ አካሎች ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በሚገባን ቋንቋ የሦስትነትን ምሥጢር እንድናውቅ ከማድረጉ በፊት በኦሪትና በነቢያት መጻሕፍት በልዩ ልዩ ኹናቴ ተገልጾ ሕገ እግዚአብሔር የተሰጣቸው የእስራኤል ወገኖች ሳይረዱት ቀርተዋል።

እነዚህም ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው:-

"ሰውን በመልካችንና እንደምሳሌያችን እንፍጠር።" (ዘፍ.ም.1 ቍ.26)

"እነሆ ሰው መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ኾነ።" (ዘፍ.ም.3 ቍ.22)

"ኑ እንውረድና ቋንቋቸውን እንደባልቀው።" (ዘፍ.ም.11 ቍ.7)



"አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት። ዐይኑንም አነሣና እነሆ፣ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ፤ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ።" (ዘፍ.ም.18 ቍ.1 እና 2)

"እግዚአብሔርም:- አንተ ልጄ ነህ፤ እኔ ዛሬ ወለድሁህ አለኝ።" (መዝ.2 ቍ.7)

"በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፤ ሠራዊቶቻቸውም ኹሉ በአፉ እስትንፋስ።" ( መዝ.33 ቍ.6)

"ወደ ሰማይ የወጣ የወረደስ ማነው? ነፋስን በእጁ የጨበጠ ማን ነው? ውሃንስ በልብሱ የቋጠረ ማነው? የምድርን ዳርቻ ኹሉ ያጸና ማን ነው? ይህን ታውቅ እንደ ኾንህ ስሙ ማን የልጁስ ስም ማን ነው?" (ምሳ.ም.30 ቍ.4)

"ያዕቆብ ሆይ፥ የጠራሁህም እስራኤል ሆይ፣ ስማኝ፤ እኔ ነኝ፤ እኔ ፊተኛው ነኝ፤ እኔም ኋለኛው ነኝ። ወደ እኔ ቅረቡ፤ ይህንንም ስሙ፤ እኔ ከጥንት ጀምሮ በስውር አልተናገርሁም፤ ከኾነበት ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበርሁ፤ አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል።" (ኢሳ.ም.48 ቍ.12 እና 16)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና:- "ከክብሩ በኋላ ወደ በዘበዙአችሁ አሕዛብ ልኮኛል፤ የሚነካችሁ የዓይኑን ብሌን የሚነካ ነውና። እነሆ፥ እጄን በላያቸው አወዛውዛለሁ፤ ለገዟቸው ለነበሩት ብዝበዛ ይኾናሉ፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም እንደላከኝ ታውቃላችሁ። የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እነሆ መጥቼ በመካከልሽ እኖራለሁና ዘምሪ ደስም ይበልሽ ይላል እግዚአብሔር።" (ዘካ.ም.2 ቍ.8–10)

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ጥቅሶች ከጌታ ልደት በፊት በኦሪት መጻሕፍት የነበሩ ቢኾኑም አይሁድ ግን ስለ ሦስትነት ትምህርት በእምነታቸውም ኾነ በአስተሳሰባቸው የተከሠተበት ጊዜ አልነበረም።



www.ethiopianorthodox.org

ስለ ምሥጢረ ሥላሴ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

በማቴዎስ ወንጌል ም.3 ቍ16–17 ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆ ከውሃ ውስጥ ሲወጣ:- አብ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ በማሰማት መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል በመውረድ የሦስትነትን ምሥጢር ገልጸዋል።

"መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት:- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑል ኀይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።" (ሉቃ.ም.1ቍ.35)

"በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።" (ዮሐ.ም.1 ቍ.1)

"እኔ በአብ፥ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ።" (ዮሐ.ም.14 ቍ.11)

"እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚሠርጽ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ አርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል።" (ዮሐ. ም.15 ቍ26)

"የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የእግዚአብሔርም ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከኹላችሁም ጋር ይኹን።" (2ኛ ቆሮ.ም.13 ቍ.14)

የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ከኾነው ከጴጥሮስ፥ እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው፥ በመንፈስም እንደሚቀደሱ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት በጳንሶ ነና በገላትያ፥ በቀጰዶቅያም፥ በእስያም፥ በቢታንያም ለተበተኑ መጻተኞች" (1ኛ ጴጥ.ም.1 ቍ.1–2)

"በሰማይ የሚመሰክሩ ሦስት ናቸው፤ እነርሱም አብ፥ ቃልና መንፈስ ቅዱስ፥ እነዚህም ሦስቱ አንድ ናቸው።" (1ኛ ዮሐ.ም. 5 ቍ.7)



ታዲያ እግዚአብሔር አንድ ጊዜ አንድ ነው ሌላ ጊዜ ደግሞ ሦስት አካል አለው የምንለው እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ይህንን ጥያቄ በምሳሌ ለማስረዳት:- አንድ ሰው ሐሳብ፥ ንግግርና እስትንፋስ አሉት። በማሰብ ኀይሉ ያስባል፤ በቃሉ ይናገራል፤ በእስትንፋሱ ደግሞ ይተነፍሳል። ይህም ኾኖ አንድ ሰው ነው እንጂ ሦስት ሰዎች አይደሉም። በዚሁም ዐይነት አብ በልብነት፥ ወልድ በቃል ነት፥ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በሕይወትነት ይታወቃሉ። እምነታችንም ሦስትነት በአንድነት፥ አንድነት ደግሞ በሦስትነት ያለ መኾኑ ነው። በውሱኑ አስተሳሰባችን ደግሞ ከዚያ ይበልጥ ልናውቅ አንችልም።

የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት (በአጭሩ)

ሐዋርያዊው ቅዱስ አትናቴዎስ:- " ወንድሞቻችን እኛስ እንዲህ እናምናለን፤ ያልተወለደ እግዚአብሔር አብ በተለየ አካሉ አንድ ነው፤ የተወለደ እግዚአብሔር ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስም በተለየ አካሉ አንድ ነው፤ በወደደው የሚያድር የአብ የወልድ እስትንፋስ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም በተለየ አካሉ አንድ ነው እንላለን። አብ አልተወለደም፤ ዓለም ኹሉ ሳይፈጠር ወልድን የወለደ ነው እንጂ፤ ወልድም ዓለም ኹሉ ሳይፈጠር ከእግዚአብሔር አብ ተወለደ፤ መንፈስ ቅዱስም ዓለም ኹሉ ሳይፈጠር ከእግዚአብሔር አብ ሠረፀ። አብ አምላክ ነው፤ ወልድም አምላክ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው። ግን ሦስት አማልክት አይባሉም አንድ አምላክ እንጂ" (ሃይ አበ: ገጽ 74)

የቂሣርያ ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ባስልዮስ:- "አብ ወልድ ባሉበት በታ በዚያ መንፈስ ቅዱስን እናየዋለን፤ በአብ በወልድ ያለ የአምላክነት ክብር ለመንፈስ ቅዱስም ገንዘቡ ነው፤ ይኸውም ቸርነት ይቅርታ ዕውቀት፥ ቅድስና ሕይወት፥ ንጽሕና ነው።" (ሃይ አበ ገጽ 114)

ከሥራው ኹሉ አስቀድሞ ሦስት አካላት ባሉት በአንድ መለኮት እንመን፤ በባሕርይ አንድ፥ በአካል ሦስት የሚኾኑ አብ፥ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ሲኾኑ ሦስት ናቸው፤ ሦስት ሲኾኑ አንድ ናቸው። አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ እንዲት ሰዓት እንደ ዓይን ጥቅሻ



www.ethiopianorthodox.org

ያኽል ስንኳ አልነበረም፤ ኹልጊዜ ከነርሱ ጋር የነበረ፥ የሚኖር ነው እንጂ።" (ሃይ. አበ: ገጽ 116)

የእንዚናዙ ቅዱስ ጎርጎርዮስ:- "ከኹሉ አስቀድሞ በአካል ልዩ በክብር አንድ የሚኾን ሦስትነትን እናስተምራለን፡ እሊህም አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፤ ሥላሴ በመለኮት አንድነት መለየት የለባቸውም፡ አካላት ግን በባሕርይ መለየት ሳይኖር እያንዳንዱ አካል በገጽ፤ በመልክ ፍጹም ነው። ለአብ የአባትነት ስም፥ የአባትነት ክብር አለው፥ ለወልድም በባሕርይ ክብሩ ከአብ ሳያንስ የልጅነት ስም የልጅነት ክብር አለው፤ መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ በክብር አይለይም፤ ነገር ግን ተለውጦ አብ ወልድ አይባልም፤ በዚህ ጊዜ ተገኘ አይባልም፤ በመለኮት እንደ አብ እንደ ወልድ ነው፤ እንጂ፤ እስትንፋሳቸው ነውና፤ ሦስቱም ትክክል ናቸውና።" (ሃይ. አበ: 210—211)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ:- "ሥሉስ ቅዱስ በመለኮት አንድነት የተካከሉ በሦስት አካላት ፍጹማን እንደኾኑ እንዲህ እናምናለን፤ እነዚህም አንዱ ቅዱስ አብ፥ አንዱ ቅዱስ ወልድ፥ አንዱ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፤ ከዓለም አስቀድመው የነበሩ ዓለምን አሳልፈው የሚኖሩ ናቸው አሜን በእውነት።" (ሃይ: አበ: ገጽ 220)

የእስክንድርያው ቅዱስ ቄርሎስ:- "አንድ ባሕርይ፡ አንድ ኀይል፤ አንድ ልዕልና አንድ ጌትነት፥ አንድ ክብር ከጥንት አስቀድሞ የነበረ አንድ ቀዳማዊነት ነው፤ በሦስት አካላት በሦስት ገጻት ፍጹማን ናቸው፤ ግዙፋን አይደሉም፤ ያልተፈጠሩ ናቸው፤ ድካም የማይስማማቸው የማይለወጡ ናቸው፤ ለመገኘት ጥንት፤ ለዘመን ፍጻሜ የላቸውም፤ አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ በአካል ሦስት በባሕርይ አንድ ነው ብሎ ማመን ይህ ነው የማይመረመር፤ በቅድምና የነበረ አብ በገጹ በአካሉ ፍጹም ነው ፍጹም ነው፡- በቅድምና የነበረ ወልድም በገጹ በአካሉ ፍጹም ነው የማይመረመር በቅድምና የነበረ መንፈስ ቅዱስም በገጹ በአካሉ ፍጹም ነው ቅዱሳት መጻሕፍትም እንደተናገሩ።" (ሃይ:አበ:ገጽ 256)

ቅዱስ ሳዊሮስ (የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት) "በሦስቱ አካላት ውስጥ መገዛዛት፥ መታጠቅ መፍታት የለም፤ በመዓርግ መለኮት አንዱ ካንዱ አይበልጥም፤ አንዱ አንዱን እንደመልክተኛ አድርጎ በሥልጣ



አያዝዘውም፤ በአንድ መለኮት ክብር፥ በአገዛዝ የኹሉ ፈጣሪ ገንዘብ በሚኾን በባሕርይ ዕውቀት አንድ ናቸው እንጂ። አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ የዓይን ጥቅሻ ጊዜ ያኽል እንኳ አልኖረም፤ ወልድም ከአብ፥ ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ የዓይን ጥቅሻ ጊዜ ያኽል እንኳ አልኖረም፤ መንፈስ ቅዱስም ከአብ፡ ከወልድ ተለይቶ የዓይን ጥቅሻ ጊዜ ያኽል እንኳ አልኖረም፤ ሥሉስ ቅዱስ ጥንት ፍጻሜ ሳይኖራቸው ዘላለም በአንድነት ጸንተው ይኖራሉ እንጂ።" (ሃይ. አበ.ገጽ:357)

ምሥጢረ ሥላሴን በሚቃወሙ ወገኖች በሚቀርቡት የመከራከሪያ ሐሳቦች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

ከክርስትና በፊት የነበሩ የአረማውያን ሃይማኖቶች የሦስት አማልክት እምነት ስለነበራቸው ከእነርሱ የተቀዳ እምነት ነው እንጂ በሥላሴ እናምናለን የሚሉት ክርስትያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንም ማስረጃ የላቸውም ይላሉ። ይህንንም በሚሉበት ጊዜ ማስረጃ አድርገው የሚያቀርቡአቸው የእነርሱን እምነት የሚከተሉ ሰዎች የጻፉአቸውን መጻሕፍትና መዝገበ ቃላትን ነው።

እኛ ግን ለእምነታችን ማስረጃ አድርገን የምናቀርበው ቅዱሳት መጻሕፍትንና ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶችን አባባል ነው እንጂ ዓለማውያን መጻሕፍትን አይደለም። ለዚህም ቀደም ተብለው የቀረቡትን ማስረጃዎች ይመለከቷል።

ሌላው ተቃውሞአቸው መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን አንድ አካል ነው ብሎ ያስተማረበት ጊዜ የለም የሚለው ነው። መንፈስ ቅዱስ በዮሐንስ ወንጌል ም.14 ቍ 16 ላይ «አጽናኝ» መባሉ፤ በቍጥር 26 ላይ አስተማሪ መባሉ፡ በም.15 ቍ. 26 ላይ መስካሪ መባሉና በም.16 ቍ · 13 ላይ ደግሞ ኹሉን ነገር የሚናገር መኾኑ የተገለጠው ለእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ምሳሌያዊ አካል በመስጠት ገለጻ ለማድረግ ስለተፈለገ ነው እንጂ አካል ያለው ኾኖ አይደለም ይላሉ ይኸውም ለጥበብ፥ ለኀጢአት፥ ለሞት፥ለውሃና ለደም አካል እንዳለው አስመስሎ እንደ መናገር ያለ ነው ብለዋል። የተቃውሞ ማስረጃቸውንም በመቀጠል እስጢፋኖስ አይሁድ በድንጋይ እየወገሩት ሳለ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ በአብ በስተቀኝ ኾኖ በሰማይ ላይ



www.ethiopianorthodox.org

ራእይ ባየ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን እንዳየ አለመነገሩ መንፈስ ቅዱስ አንድ ተመሳሳይ አካል አለመኾኑን ያመለክታል ይላሉ የሐዋ: ሥ: ም: 7 ቍ 55 ተመሳሳይ የተቃውሞ ማስረጃም በራእየ ዮሐንስ ም:7 ቍ 10፥ ም: 22 ቍ 1 እና 3 ይመለከቷል። ስለዚህ በእነርሱ አባባል መንፈስ ቅዱስ አንድ ነገር ነው እንጂ አንድ አካል አይደለም ባዮች ናቸው።

እነርሱ እንደሚሉት ሳይኾን መጽሐፍ ቅዱስ ለመንፈስ ቅዱስ አካል እንዳለው በግልጽ አመልክቶአል። ለምሳሌ ጌታ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ አብ በስማይ ኾኖ ድምፁን ሲያሰማ፥ ወልድ በመጠመቅ እያለ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በመውረድ ሦስትነትን ገልጸዋል፡ (ማቴ:ም:3 ቍ: 16—17)። ጌታችን፥ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዕርገቱ በፊት ደቀ መዛሙርቱን ያዘዛቸው በአብ፥በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ ነው እንጂ በአብና በወልድ ስም ብቻ እንዲያጠምቁ አይደለም። (ማቴ:ም: 28 ቍ. 16–17)

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ኹለተኛ በጻፈው መልእክት ም13 ቍ. : 14 ላይ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የእግዚአብሔር ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከኹላችሁም ጋር ይኹን በሚልበት ጊዜ ስለአንድ አካል እንጂ ስለ አንድ ነገር ያልተናገረ መኾኑ ግልጽ ነው።

ወደ ትንቢተ ኢሳይያስ መለስ ብለን ም:48 ቍ: 16 ብንመለከት የተጻፈውን እግዚአpሔርና መንፈሱ ልከውኛል ተብሎ ስለመድኀኒታችን የተነገረውን ትንቢት ስንመለከት መንፈስ ቅዱስ አካል ያለው መኾኑን ልንረዳ እንችላለን። እንደተቃዋሚዎቹ አስተሳሰብ ቢኾን ኖሮ የእግዚአብሔር መንፈስ ልኮኛል በተባለ እንጂ እግዚአብሔርና መንፈሱ ተብሎ ባልተነገረም ነበር። በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርታችን አብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ልቦናቸው፥ ወልድ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ መንፈሳቸው ወይም ሕይወታቸው ነው እንላለን።

መንፈስ ቅዱስ ምእመናንን የሚያጽናና በመኾኑ አጽናኝ ተባለ፥ የክርስቶስን ማንነት ስለ ዕውቀትን የሚሰጥ በመኾኑ አስተማሪ ተባለ፥ እንዲሁም ትንቢትን የሚያናግር መኾኑ ገልጥላቸው መስካሪ ተባለ፥



ለመግለጥ ልዩ ልዩ ስሞች ተሰጡት እንጂ እነርሱ እንደሚሉት አካል የሌለው ኾኖ አይደለም።

ከአንድ ሰው በላይ ባለበት አካባቢ የሚገኘን ሰው ለማመልከት በአ ጠገቡ የሚገኘውን ሰው ስም መጥራት የተለመደ ነው። ለምሳሌ ጴጥሮስ ያዕቆብና ዮሐንስ የተባሉ ሦስት ሰዎች በዚሁ በስማቸው አጻጻፍ ተራ ከቀ ኝ ወደ ግራ በቅደም ተከተል ቆመው ቢኾኑና ጴጥሮስ የትኛው እንደኾነ ሊጠቈም ቢፈለግ ከያዕቆብ በስተቀኝ የቆመው ነው ይባላል እንጂ የዮ ሐንስ ስም መጥራት አስፈላጊ አይኾንም። ዮሐንስ የትኛው እንደኾነ ለማ መለከት ቢፈለግ ደግሞ ከያዕቆብ በስተግራ የቆመው ይባላል እንጂ የጴ ጥሮስን ስም መጥራት አስፈላጊ አይኾንም። በዚሁም ዐይነት እስጢፋኖስ ስለጌታ ራእይ ባየ ጊዜ ሦስቱን አካላት ማለት መንፈስ ቅዱስን በስተግራ አብን በመሐል ወልድን ደግሞ በስተቀኝ ስላየ ወልድን በአብ በስተቀኝ የቆመ መኾኑን ለማመልከት ተናገረ እንጂ የመንፈስ ቅዱስን መታየት መናገር አስፈላጊ ኾኖ አላገኘውም። እስ ጢፋኖስ ሊናገር የፈለገው ያ እናንተ የሰቀላችሁት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንትተም አምላካችን ነው ብላችሁ በምታምኑበት በእግዚአብ ሔር አብ በስተቀኝ ቆሞ አየሁት ለማለት ነው። ይህም በመኾኑ እስጢ ፋኖስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በአብ በስተቀኝ ቆሞ አየሁት ብሎ መናገሩ መንፈስ ቅዱስ በአካል አልነበረም ለማለት ማስረጃ ሊኾን አይችልም።

በስም፥ በአካልና በውሳጣዊ ግብር ካልኾነ በቀር አብና ወልድ አንድ ናቸው የሚለው የክርስቲያኖች አስተሳሰብ በማቴዎስ ወንጌል ም.26 ቍ. 39 ላይ ከተገለጠው የፈቃድ ልዩነትና፡ በዮሐንስ ወንጌል ም.8 ቍ:17 እና 18 ላይ ወልድ አብን በምስክርነት ከመቍጠሩ ጋር እንዴት ይታረቃል ብለው ይጠይቃሉ።

ጌታ በጌታሴማኒ ያትክልት ቦታ ያደረጋቸው ድርጊቶች የሚያ መለክቱት ተመሳሳይ ኹናቴ በሚያጋጥመን ጊዜ ኹሉ እኛ ደካማዎቹ ፍጥረቶች ምን ማድረግ እንደሚገባን ሊያስተምረን የፈቀደ መኾኑን ነው። በሚጸልይበትና ሰብአዊ እንቅስቃሴ በሚያደርግበት ጊዜ ኹሉ ከመለኮት ጋር ተዋሕዶ ባልተጠፋፋ ትስብእቱ መኾኑ መረሳት የለበትም። ሦስቱ አካላት አንድ ናቸው ማለት ሦስቱም አካላት ሥጋ



www.ethiopianorthodox.org

ለብሰዋል ማለት አይደለም። ወልድ በትስብእቱ ለመለኮት ተገቢ ክብሩን ይሰጣል። ጌታ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ የሚለየው የእኛን ሥጋ ለብሶ ከኀጢአት በቀር በኹሉም ነገር እኛን መምሰሉ ነው። በኹሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው የተባለውን ቃል እግዚአብሔር መርሳት የለብንም። (ዕብ:ም:2 ቍ:17) ያንተ ፈቃድ እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን በሚልበት ጊዜ በመለኮታዊ ውሳኔ መሠረት እንጂ እንደ ሥጋ ደካማነት አይሁን ማለቱ ነው። የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነት ለማዳን ሥጋ ለብሶ የመለኮታዊውን ውሳኔ በሥራ ላይ ያዋለው ወልድ በተለየ አካሉ እንደመኾኑና ሰብአዊ ተግባርም በሚያከናውንበት ጊዜ በትስብእቱ እንደመኾኑ ከመለኮታዊ አንድነት ተለየ አያሰኘውም። አባቱን በምስክርነት መጥራቱ ደግሞ ምንም ሊያስገርመን አይገባም። በዮርዳኖስ ጥምቀትና በደብረ ታቦር መገለጥ ጊዜ የምወደው ልጄ ይህ ነውና እርሱን ስሙት ብሎ አብ ከሰማይ የምስክርነት ቃል የሰጠ መኾኑን በማቴዎስ ወንጌል ም:3 ቍ:17 እና ም:17 ቍ:5 መመልከት ይቻላል።

ስለዚህ የሥላሴ አማኞች በማለት እንደማላገጥ የሚቃጣቸው ወገኖች በጌታ ጸሎትና አብን በምስክርነት መጥራቱ ምክንያት የመለኮት አንድነት እንደሌለ ማስረጃ ሊያደርጉት የማይችሉ መኾናቸውን ሊገነዘቡት ይገባል።

ወደ ቈላስይስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ም:1 ቍ:15 ላይ፥ "እርሱ ለማይታየው አምላክ ምሳሌ ኾኖ የፍጥረት ኹሉ በኵር ነው" በመባሉ ከሦስቱ አካላት አንዳቸው ዘላለማዊ አይደለም ይላሉ።

የፍጥረት ኹሉ በኵር ነው ማለት ፍጥረቱ ኹሉ ከመፈጠሩ በፊት የነበረ መኾኑን እንጂ መፈጠሩን የሚያመለክት አይደለም። ለማይታየው አምላክ መሳሌ ነው ማለት እርሱ ሥጋ በመልበሱ ቀድሞ የማይታይ የነበረው በእርሱ አማካይነት ለመታየት የቻለ አምላክ መኾኑን ያመለክተናል። የሚቀጥለውን ቍጥር ማለት ቍጥር 16 ብንመለከት "የሚታዩትና የማይታዩት፥ ዙፋናት ቢኾኑ ወይም ጌትነት፥ ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ኹሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ኹሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል" ይላል።



ክርስቶስ የፍጥረቱ ኹሉ በኵር ነው የሚለውን ጥቅስ እርሱ በመጀመሪያ የተፈጠረ ነው ብለው በሚተረጕሙበት ጊዜ በኦሪት ዘፍጥረት ም:1 ቍ:1 ላይ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ የሚለውን ቃል እግዚአብሔር ሲመለከቱ ምን ትርጕም ሊሰጡት ይኾን?

እንዴትስ ኹሉን የፈጠረ እርሱ ከኾነ በኵር በመባሉ ብቻ ከፈጣሪነት ወደ ፍጡርነት ሊያሸጋግሩ በቁ? በዚሁ ትችታቸው በመጽሐፈ ምሳሌ ም:8 ቍ:22 ላይ:- "ጥበብ ጌታ ፈጠረኝ አለች" የሚለውንም ጥቅስ በማቅረብ የጌታችንን ፍጡርነት ሊያረጋግጡ ሞክረዋል። ይህን በተመለከተ ግን በአንደኛ መጽሐፍ ጥያቄና መልስ ተራ ቍ:104 ይመለከቷል።

ስለዚህ የፍጥረት በኵር ማለት ከፍጥረት ኹሉ በፊት የነበረ ማለት ነው እንጂ ፍጡር ማለት አለመኾኑን ተረድተው ተሳስተው ባያሳስቱ መልካም ነው።

በሦስቱ አካላት መካከል መበላለጥ የለም ኹሉም እኩል ናቸው ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራልን ብለው [illegible] የማርቆስ ወንጌል ም:13 ቍጥር : 32 ፥ የማቴዎስ ወንጌል ም:20 ቍ:20–23፥ ም:12 ቍ:31–32፥ የዮሐንስ ወንጌል ም:14 ቍ:28፥ 1ኛ ቆሮ:ም: 11 ቍ:3፥ ም:15 ቍ:27–28 ጥቅሶችን ጠቅሰው [illegible] ለማብራራት ይሞክራሉ።

በማርቆስ ወንጌል ም:13 ቍ:32 ላይ:- ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ከአብ በቀር ወልድ እንኳን አያውቅም ለሚለው ጥቅስ በጥያቄና መልስ ተራ ቍጥር: 51 ይመለከቷል።

በማቴዎስ ወንጌል ም:20 ቍ.23 ላይ በቀኜና በግራ መቀመጥ ግን ከአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም ለሚለው ጥቅስ በጥያቄና መልስ ቍጥር 35 ይመለከቷል።

በማቴዎስ ወንጌል ም:12 ቍ:31–32 በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተሰነዘረ የስድብ ቃል በዚህም ኾነ በወዲያኛው ዓለም የማይሰረይ ሲኾን በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ይሰረይለታል ብሎ ለሚገልጸው ጥቅስ በጥያቄና መልስ ተራ ቍ 27 ይመለከቷል።



www.ethiopianorthodox.org

በዮሐንስ ወንጌል ም:14 ቍ28 ላይ:-አብ ከእኔ ይበልጣል ለሚለው ጥቅስ በጥያቄና መልስ ተራ ቍጥር 71 ይመለከቷል።

በ1ኛ ቆሮንቶስ ም:11 ቍ:3 ላይ የክርስቶስ ራስ እግዚአብሔር እን ደኾነ ልታውቁ እወዳለሁ በመባሉ ክርስቶስ እግዚአብሔር እንዳልኾነና የእርሱ የበላይ እግዚአብሔር መኾኑን ያመለክታል ይላሉ።

በመሠረቱ ክርስቶስ በሚባልበት ጊዜ መለኮትንና ትስብእትን ያለ ማቀላቀል ያዋሐደ አምላክ ማለት እንደመኾኑ አንዳንድ ጊዜ እንደፍጹም አምላክ የሚነገርለት የመኾኑን ያኽል አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንደፍጹም ሰው ይነገርለታል። እንደዚያማ ካልኾነ መለኮት ትስብእትን በመዋጥ አጥፍቶታል የሚለውን የአውጣኬን ክሕደት እንደማደስ ይኾንብናል። ክርስቶስ በትስብእቱ ከኀጢአት በቀር በኹሉም ነገር የሰውን ልጆች መስሏል። ለሰው ልጆች የበላያቸው እግአብሔር እንደመኾኑ ክርስቶስም በትስብእቱ እግዚአብሔር የበላዩ ነው ቢባል ሊያስገርመን አይገባም።

በ1ኛ ቆሮንቶስ ም:15 ቍ:28 ላይ:-"ኹሉ ነገር ከተገዛለት በኋላ እግዚአብሔር ኹሉ በኹሉ ይኾን ዘንድ በዚያን ጊዜ ወልድ ደግሞ ኹሉ ን ላስገዛለት ተገዥ ይኾናል» ለሚለው ጥቅስ በጥያቄና መልስ ተራ ቍጥ ር 84 ይመለከቷል።

በዮሐንስ ወንጌል ም:17 ቍ:3 ላይ "እውነተኛው አምላክ የኾንከውን አንተንና የላክኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ:" በማለቱ፥ በ1ኛ ቆሮንቶስ ም:8 ቍ 6 ላይ:-"ለእኛስ ነገሩ ኹሉ ከእርሱ የኾነ እኛም ለእርሱ የኾንን አንድ አምላክ አብ አለልን፤ ነገር ኹሉም የኾነ እኛም በእርሱ በኩል የኾንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን» በማለቱ፥ በ1ኛ ጴጥሮስ ም:1 ቍ:3 ላይ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ" በማለቱ አምላክ የሚለው ስም የአብ ብቻ ኾኖ ስለቀረበና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአምላክነት ውጪ እንደኾነ ስለተገለጠ በምሥጢረ ሥላሴ ላይ ያለው እምነት ትክክል አይደለም ይላሉ።

የዮሐንስ ወንጌል ም:17 ቍ:3 በተመለከተ ጥያቄና መልስ ተራ ቍ:74 ይመለከቷል።



በአንደኛ ቆሮንቶስ ም:8 ቍ:6 ላይ:- አንድ አምላክና አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማለቱ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ አይደለም ሊሉ ይቃ ጣቸዋል። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር፥ አምላክ፥ መድኀኔዓለም አማኑኤል፥ወልድ፥ቃል የተባሉ የተለያዩ መጠ ሪያዎች አሉት። ከነዚህ ኹሉ ግን በዚህ ዓለም ላይ ከእኛ ጋር እንደ እኛ በነበረበት ጊዜ ኢየሱስና ክርስቶስ በማለት ይታወቅ ስለነበረ ኹሉም የሚ ቀናው በዚሁ ስም መጥራት ነው እንጂ በዚህ በተለየ ስሙ በመጠራቱ ግን አምላክ አይደለም ማለት ሊኾን አይችልም። ለምሳሌ በኹለተኛው ቆሮንቶስ ም:13 ቍ:14 ላይ የሦስቱን አካላት ስሞች በመጥራት የመሰናበቻ ቡራኬ ሲሰጥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የእግዚአብ ሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከኹላችሁም ጋር ይኹን ብሏ ል። በዚህም መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው የአምላክ ስም እንጂ የተራ ሰው ስም አለመኾኑን ቢገነዘቡት መልካም ነው።

ወደ ኤፌሶን ሰዎች በተላከው መልእክት ም. ቍ.17 እና በመጀ መሪያው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት ም:1 ቍ:3 ላይ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ስለሚለው ጥቅስ ማብራሪያ በጥያቄና መልስ ተራቍ:89 ይመለከቷል።

በእነዚህም ማብራሪያዎች መሠረት ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል መኾኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

ከላይ የቀረቡት ልዩ ልዩ ጥቅሶች ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ከአብ በማሳነስና እንዲያውም መንፈስ ቅዱስን እንደ አንድ አካል ሳይኾን እንደ አንድ ነገር በማቅረብ የምሥጢረ ሥላሴን እምነት ለመካድ አርዮሳውያን የሚያቀርቡአቸው መከራከሪያዎች ናቸው።

እኛ ክርስቲያኖች ግን ቅዱሳት መጻሕፍትንና የቅዱሳን አባቶችን ትምህርት መሠረት በማድረግ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድ ነትና ሦስትነት አምነን ይህንኑም እናስተምራለን። በቀረቡትም ልዩ ልዩ ማብራሪያዎች መሠረት በመጀመሪያ የቀረቡት ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉምና አለመኾናቸውን ተረድተን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።



www.ethiopianorthodox.org

51. በማቴዎስ ወንጌል ም:28 ቁ:19 ላይ:- "ኺዱና በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም አሕዛብን ኹሉ አጥምቁአቸው:" የሚል ሲኾን በሐዋርያት ሥራ ም:2 ቁ38፥ ም:8 ቁ:16፥ም:10 ቁ:48 ም:19 ቁ:5 እና በሌሎችም የሐዲስ ኪዳን ክፍሎች በሥላሴ ስም ሳይኾን በኢየ ሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ የተባለው እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ክርስቶስ ስም መጠመቅ የሚሉትን ጥቅሶች በማስ ይኾናል። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ ያለብን በኢየ ሱስ ባሰብና እነዚያን ማስረጃ አድርጎ በማቅረብ መጠመቅ ያለብን በኢየ ሱስ ክርስቶስ ስም ነው እንጂ በሥላሴ ስም አይደለም ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ።

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ ተብሎ የተጠቀሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ስምና የክርስትና እምነት ገና ሐዋርያት የጀመሩት አዲስ ስምና አዲስ ሃይማኖት በመኾኑና የእኛን ሥጋ ለብሶ ሰው ኾኖ በሰዎች መካከል የተገኘውን የእግዚአብሔር ወልድን አምላክነት ማመን ደግሞ ለክርስ ቲያን ሃይማኖት አማራጭ የሌለው ግዴታ መኾኑን ለማመልከት ነው እንጂ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ስም ሳይጠራ ተጠመቁ ለማለት አይደ ለም። በጊዜው የነበረው የሥራ ጥድፊያ እግዚአብሔር ወልድ በትሕትና ራሱን ዝቅ አድርጎ ፍጥረቱ ከኾነው ከሰው በመወለድ ሰው ኾኖ ሕማምን ተቀብሎ በመሞትና ሞትንም ድል ነሥቶ በመነሣት ለሰው ልጅ ቤዛ ከኾነ በኋላ ወደ ሰማያዊ ዙፋኑ የወጣ መኾኑን ማስተማርና ይህም እግዚ አብሔር ወልድ ሕዝቡ ኢየሱስ በሚል ስም የሚያውቀው እንጂ ሌላ አለመኾኑን ማሳወቅ ስለነበረ ይህንኑ ትምህርት ለማጠናከር በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ ተባለ።

ጌታ ራሱ በአብ፥ በወልድ ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ብሎ ያዘዛቸው እንደመኾኑ ደቀ መዛሙርቱ የጌታቸውን ትእዛዝ እንደሚያከ ብሩ እርግጠኞች እንኹን፤ ምክንያቱም "ብትወዱኝስ ትእዛዜን ጠብቁ" ብሎአቸዋልና (ዮሐ:ም:14 ቁ:15)

በሌላ በኩል ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ የተባለው ከዮሐንስ ጥምቀት የተለየ መኾኑን ለመግለጽ ታስቦ ነው። ዮሐንስ መጥምቁም የርሱ ጥምቀት ከጌታ ጥምቀት የተለየ መኾኑን ሲያመለክት "እኔስ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን እርሱ ከእኔ የበረታ ነው፤ እርሱ



በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል" ብሏል። (ማቴ.ም.3 ቁ.11) እንዲሁም በኤፌሶን የተገኙ አማኞች የዮሐንስን ጥምቀት ተጠምቀው እንደነበርና በኋላ ግን በጌታ አምነው እንዲጠመቁ የተደረገ መኾኑን በሐዋርያት ሥራ. ም.19 ቁ.1–7 ማንበብ እንችላለን። የጌታ ጥምቀትና የዮሐንስ ጥምቀት ልዩነትም የጌታ ጥምቀት በመንፈስ ቅዱስ ኾኖ የኀጢ አት ስርየትንና ልጅነትን የሚያድል ሲኾን የዮሐንስ ጥምቀት ግን ለንስሓ በውሃ ነው።

ጌታ ደቀ መዛሙርቱን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ በግልጽ ያዘዛቸው ከመኾኑም በላይ ምንም እንኳን እርሱ ጥምቀት የማያስፈልገው ቢኾን የእኛን ሥጋ መልበሱን ለማመልከትና ለእኛ አርአያ ለመኾን በተጠመቀ ጊዜ የሥላሴ ቅዱስ በሥነ ሥርዐቱ ላይ መከሠት የጥምቀት ሥርዐት ምን ዐይነት መኾን እንዳለበት የሚያሳይ ምልክት ነው። አብ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምፅ ሲያሰማ፥ ወልድ በመጠመቅ ላይ ኾኖ፥ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል መውረዱ በሉቃስ ወንጌል ም.3 ቁ 21–22 ላይ ተገልጾአል። ይህም ክሥተት የሚያመለክተው መጠመቅ ያለብን በሥላሴ ስም መኾኑን ነው።

ስለዚህ በክርስቶስ ስም መጠመቅ ተብለው የተገለጡት ጥቅሶች የሚ ያመለክቱት በክርስቶስ ማመንን እንጂ በሥላሴ ስም ሳይኾን በኢየሱ ስ ክርስቶስ ስም ብቻ መጠመቅ ማለት አለመኾኑንም ተረድተን ከመሳ ሳት እንጠንቀቅ።

## የማርቆስ ወንጌል

ይህ ወንጌል 16 ምዕራፎች አሉት። ጽሑፉም በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፋፈለ ነው። የመጀመሪያው ክፍል ከም.1 ቁ.1 እስከ 13 የዮሐንስ መጥምቁ ማስተማርና የጌታ ጥምቀት፥ ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 1. ቁ.14 እስከ ምዕራፍ 10 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ማስተማርና ታምራቱ በመጨረሻ የፋሲካ በዓል ወደኢየሩሳሌም እስከኼ ደበት ጊዜ ድረስ፥ ሦስተኛው ክፍል ከምዕህራፍ 11 እስከ ምዕራፍ 16 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እንደንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ፥ ስለኢየሩሳሌምና ስለቤተ መቅደስዋ መፍረስ መናገሩ፥ከዚያም በአይሁድ



www.ethiopianorthodox.org

አለቆች ተፈርዶበት መገደሉ፡ ከሞት መነሣቱና ለደቀ መዛሙርቱ መገለጹ እንዲሁም ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር መላኩ ተገልጾአል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

52. በማርቆስ ወንጌል ም:6 ቍ:5 ላይ:-"በዚያም በጥቂቶች ድውዮች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወስ በቀር ሌላ ተአምር ማድረግ አልቻለም" ማለቱ ከጌታችን ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ኹሉን ቻይነት እምነታችን ጋር እንዴት ሊታረቅ ይችላል። ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል።

በተለያዩ አርዕስት ተመላልሶ እንደተገለጠው እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከፈጠረው በኋላ ጠቃሚና ጐጂ የኾኑ ድርጊቶችን ለይቶ በማመልከት የፈቃድና የፍላጎት ነጻነት ሰጠው እንጂ የማይፈቅደውን ድርጊት እንዲያደርግ ወይም እንዳያደርግ አላስገደደውም። ጌታ በዚህ ዓለም ላይ ባሳለፋቸው ዘመናት ብዙዎቹን ሕመምተኞች ከሕመማቸው የፈወሳቸው ለመፈወስ እምነትና ፍላጎት ያላቸው መኾናቸውን ካረጋገጠ በኋላ ነው እንጂ ማንንም ሰው ያለፍላጎቱ አልፈወሰውም።

ሰው ኹሉ ይድን ዘንድ የእግዚአብሔር ፍላጎት ቢኾንም ማንኛውም ሰው እግዚአብሔር ያመለከተውን የመዳኛ መንገድ ካልተከተለ ሊድን የማይችል መኾኑን ሲያመለክት መድኀኒታችን የሚከተለውን ማስጠንቀቂያ ተናግሮአል:- "ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ፥ አንቺ ነቢያትን የምትገድይ፥ ወደ አንቺ የተላኩትንም በድንጋይ የምትወግሪ ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ ሥር እንደምትሰበስብ እኔም ያንቺን ልጆች ልሰበስብ ስንት ጊዜ ፈለግሁ እናንተ ግን አልፈለጋችሁም።" (ማቴ.ም: 23 ቍ:37) ይህም ማለት የእነሱ ፍላጎት እስካልታከለበት ድረስ እግዚአብሔር ምንም አያደርግም ማለት ነው። ይህም የማይለወጠው የአምላካችን አሠራር ነው።

ጌታ ኢየሱስ ወደ አደገበት አገር በመጣ ጊዜ የእርሱን ትምህርትና ፈውስ አድንቆ በእምነት በመቀበል ፈንታ ይህ የእንጨት ጠራቢ ልጅ ይህን ዕውቀት ከወዴት አመጣው እያሉ የንቀትና የማጥላላት ትችት ስለጀመሩ ብዙ ተአምራት የሚያደርግበት ኹናቴ ሳይመቻች በመቅረቱ



ሌላ ተአምር ሊያደርግ አልቻለም ተባለ እንጂ እርሱ ከፈለገ ምንም የሚሳነው ነገር እንደሌለ መገንዘብ ይኖርብናል። እንደሚታወቀው የአምላካችን አሠራሮች ኹሉ ሥርዓትን የተከተሉ ናቸው እንጂ እንደ ሰው ልጆች አሠራሮች በግብተኝነት የሚፈጸሙ አይደሉም። ቀደም ብሎ ለሰው ልጅ ሙሉ የፈቃድና የፍላጎት ነጻነትን ስለሰጠው ፈጣሪአችን የሚያደርጋቸው ድርጊቶች ኹሉ ከዚሁ ጋር የተያያዙ ናቸው። በአደገበት አገር ያሉ ሰዎች በጌታና በትምህርቱ ላይ ያላቸው እምነት ሌሎች ተአምራትን እንዲያደርግ ስለማይጋብዝ ሌላ ተአምር ሊያደርግ አልቻለም አሰኝቶአል እንጂ የማድረግ ችሎታም ኾነ ፈቃድ የለውም ማለት አይደለምና አለመኾኑን ተረድተን ከመሳሳት እንጠንቀቅ

53. በማርቆስ ወንጌል ም:10 ቍ:29—30:- "እውነት እላችኋለሁ ስለእኔና ስለወንጌል ቤትን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ:- አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን ወንድሞችንም እኅቶችን፥ እናቶችንም ልጆችንም እርሾችንም መቶ እጥፍ፥ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም" ተብሎ የተሰጠው ተስፋ በእውነት ተግባራዊ የሚኾን ነውን ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ይህ አባባል ቃል በቃል ተወስዶ በዚህ ዓለም ላይ አንድ ቤቱን የተወ መቶ ቤት አንድ አባቱን የተወ መቶ አባት አንድ እናቱን፥ ወንድሙን፥ እኅቱን የተወ መቶ ያገኛል ማለት ሳይኾን ነገር ግን ስለጌታና ስለወንጌል ሲል ምኞትንና ፍላጎቱን የሠዋ ሰው በመቶ እጥፍ የሚኾን መንፈሳዊ ሀብትን ያገኛል ማለት ነው። ሃይማኖተኛነት ደግሞ በዚህ ዓለምም ኾነ በወዲያኛው ዓለም ተስፋ የተሞላ በመኾኑ ጌታ የሰጠው ተስፋ በመንፈሳዊ በረከት ብቻ የተወሰነ አይደለም። የክርስትና እምነትም ለምእመናኑ የእውነተኛነትን፥ የታማኝነትን፥ የቀጥተኛነትንና በራስ የመተማመንን መንገድ ስለሚያስተምር የአባሎቹን የዚህ ዓለም ሕይወት የተሳካ ያደርገዋል።

የዚህኛው ዓለም ጊዜያዊ ሀብት ደገሞ ከወዲያኛው ዓለም ዘላለማዊ ጸጋና በረከት ጋር ሲወዳደር ኢምንት እንደመኾኑ ዘላለማዊው ሀብት መቶ እጥፍ ድርብ ነው ቢባል የሚያስገርም አይኾንም። ያም የሚገኘው



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ዓለም ባለንበት ጊዜ በምናከናውነው እምነትና በጎ ተግባር እንደመኾኑ በሙቶ እጥፍ ድርብ ይመለስናል የሚያስኘው ይኼ ነው።

54. በማርቆስ ወንጌል ም.13 ቍ.32 ላይ፡- "ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም፤ የሰማይ መላእክትም አያውቁም፤ ወልድም አያውቅም" ያለ ሲሆን በዮሐንስ ወንጌል ም.10 ቍ.30 ላይ፡- "እኔ በአብ "እኔና አብ አንድ ነን፥ "በምዕራፍ 14 ቍ.11 ላይ፡- "እኔ በአብ እንዳለሁና አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፡" በምዕራፍ 16 ቍ.15 ላይ፡- "የአብ የኾነው ኹሉ የእኔ ነው" ከማለቱም በላይ በማቴዎስ ወንጌል ም.24 ቍ.29–35 እና በሉቃስ ወንጌል ም.21 ቍ.25–22 ዳግመኛ ስለሚመጣበት ጊዜ ኹናቴ ልዩ ልዩ ምልክቶችን በመዘርዘር አስረ ድቷል። እንግዲህ በአንድ በኩል ዳግመኛ የሚመጣበትን ጊዜ ከነመ ልክቱ ዘርዝሮ ያስረዳና በሌላ በኩል ደግሞ ከአብ ጋር ያለውን እኩልነት መላልሶ ያረጋገጠ ከኾነ ለምንድነው ታዲያ ወልድም አያውቅም የተባ ለው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ለዚህ ጥያቄ ኹለት አማራጭ መልሶች አሉ።

አንደኛ ወልድ ቢያውቅም ይህን ዕውቀት ለሰው ልጆች አይገ ልጽላቸውም። ይህም የሚኾንበት ምክንያት ተመልሶ የሚመጣበት ጊዜ ሩቅ መኾኑን ካወቁ ነቅተውና ተዘጋጅተው በመጠበቅ ፈንታ ችላ ሊሉ ስለሚችሉና ጊዜው ቅርብ መኾኑን ካወቁ ደግሞ በጣም ከመፍራትና የመደንገጣቸው የተነሣ የጌታን ዳግመና መምጫ ጊዜ ብቻ በማሰብ የዚህን ዓለም ኀላፊነታቸውን እንዳይዘነጉ ታስቦ ነው። ኹለተኛው ትር ጓሜ ደግሞ ወልድ በመለኮቱ ወይም በትስብእቱ የሚያውቀው መኾኑን ለመካድ ሳይኾን የዕውቀቱ ምንጭ ያለመለኮት ትስብእት ብቻ አለመኾ ኑን ለመግለጽ ነው። ያልተጠፋፋ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ባሕርይ ያለው በመኾኑ ወልድ ስንል ሰው የኾነ አምላክ ማለታችን ነው፤ ስለዚህ እዚህ ላይ ወልድም አያውቅም የተባለው ወልድ በትስ ብእቱ ለማለት ነው።

55. በማርቆስ ወንጌል ም.16 ቍ.7 ላይ መልአክ ወደ ጌታ መቃብር ኼደው ለነበሩት ሴቶች በነገራቸው መሠረት ጌታ ወደ ገሊላ እንደሚቀ ድማቸው ከተናገረ በኋላ ከቁጥር 9 እስከ 14 ደግሞ ወደ ገሊላ ከመኼዱ



በፊት ከአንድ ጊዜ በላይ በኢየሩሳሌም እንደተገለጸላቸው የተነገረ በመኾ ኑ የመልአኩ አባባል ትክክል አይደለም ይባል ይኾናል።

ስለገሊላ የተጠቀሰበት ምክንያት በገሊላ በተገለጸላቸው ጊዜ ከእነ ርሱ ጋር ረዘም ያለ ጊዜ ስለቈየና በኢየሩሳሌም የተገለጸባቸው ጊዜ ዎች ግን በጣም አጭጭር ስለነበሩ ነው።

## የሉቃስ ወንጌል

ይህ ወንጌል 24 ምዕራፍ ያሉት ኾኖ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፋፈለ ነው።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 3 ድረስ ሲኾን በውስጡም የጌታና የመጥምቁ ዮሐንስ ልደት፡ የጌታ መሬቱን፡ የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤል ለዘካር ያስና፥ ለድንግል ማርያም መገለጥ፥ መልአክ ለእረኞች ማብሠሩና መላእክት በሰማይ ላይ ኾነው እግዚአ ብሔርን ሲያመስግኑ መታየታቸው ታሪክ ተገልጾበታል።

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 4 እስከ ምዕራፍ 9 ድረስ ሲኾን በውስጡም ለ3 ዓመቶች ጊዜያት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ማስተማርና ታምራቱ፡ የመጨረሻውን የፋሲካ በዓል ለማክበር ወደ ይሁዳ መምጣቱ ታሪክ ይገኝበታል።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 10 እስከ ምዕራፍ 21 ሲኾን ይህም ጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትና ምሳሌዎች፡ ሰባዎቹን አርድዕት መርጦ ለማስተማር መላኩ፥ ጌታ ኢየሱስ ከተናገራቸው ምሳሌዎች መካከል ስለደኻው አልዓዛርና ስለ ባለጸጋው ሰው፡ ስለትዕቢተኛው ፈሪሳዊና ስለትሑቱ ቀራጭ፡ ስለ ግፈኛው ዳኛ፡ ስለወይን አትክልት ሠራተኞች እንዲሁም ስለኢየሩሳሌም ጥፋት ናቸው።

አራተኛው ክፍል ከምዕራፍ 22 እስከ ምዕራፍ 24 ድረስ ሲኾን በውስጡም ስለጌታ ሕማማት፥ ስለሞቱ፡ ከሞት ስለመነሣቱና ወደሰማይ ስለማረጉ ታሪክ ይገኛል።



www.ethiopianorthodox.org

የግል ቤተ መጻሕፍት

## ጥያ ቄዎችና መልሶቻቸው

56. በሉቃስ ወንጌል ም.1 ቁ.18 ላይ ካህኑ ዘካርያስ ሚስቱ ኤልሣቤጥ ወንድ ልጅ እንደምትወልድለት መልአኩ ገብርኤል ባበሠረው ጊዜ "እኔ ሽማግሌ ነኝ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ" ብሏል።

እንደገና መልአኩ ገብርኤል ድንግል ማርያምን ወንድ ልጅ እንደ ምትወልድ ባበሠራት ጊዜ :- "ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይኾናል" ብላዋለች። (ሉቃ.ም.1 ቁ.34)

በመጀመሪያይቱ በሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ም.4 ቁ.1 ላይ "ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ኹሉ አትመኑ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚ አብሔር ኾነው እንደኾነ መርምሩ" ተብሏል።

በአንድ በኩል የእርሱም ኾነ የባለቤቱ ዕድሜ የገፉ በመኾኑና የመውለጃ ጊዜአቸው ስላለፈ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ቃለ እግዚአብሔር መንፈስን ከመመርመራችሁ በፊት አትመኑ በማለቱ የተነገረኝ ብሥራት እንዴት ትክክል መኾኑን ለማወቅ እችላለሁ ብሎ ስለጠየቀ ልጁ እስ ኪወለድ ድረስ በዱዳነት መቀጣቱ አግባብ ነው ወይ? ከዚያም በላይ ደግሞ ድንግል ማርያም ለጠየቀችው ጥያቄ መልስ ከማግኘትዋ በቀር እን ደ ዘካርያስ ያልተቀጣች ስትኾን እንዴት እርሱ ብቻ ቅጣት ተፈረ ደበት ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ስለዘካርያስ በምንነጋገርበት ጊዜ መልአክ ተልኮ የሚያነጋግረው ሰው እስከኾነ ድረስ የተለየ ማለት ቅዱስ ሰው መኾኑን እንረዳለን፤ ቅዱስ በእርሱ ደረጃ ያለ ጻድቅ እንደዚህ ያለ ኹናቴ ሲያጋጥመው ወይም ርኩስ መንፈስ መኾኑን ለይቶ የማወቅ ችሎታ እንደሚኖረው ይገመታል። በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚከናወን ጸሎትና ስብሐተ እግዚአ ብሔር ከእግዚአብሔር ጋር እንደመነጋገር ይቈጠራል። በእንደዚህ ያለ ቦታ ደግሞ ጸሎትን በመምራት ላይ የሚገኝን እንደ ዘካርያስ ያለውን ካህን ለማሳሳት አንድ ርኩስ መንፈስ ድፍረትም ኾነ ችሎታ አይኖ ረውም። ዘካርያስም ይህን ማወቅ ስለሚኖርበት መጠራጠር ባልተገባ ውም ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ከእርሱ ብዙ ዘመን በፊት አብር ሃምና ሣራ በስተእርጅና ዕድሜአቸው ልጅ እንዲወልዱ መደረጋቸውን ዘካርያስ የማያውቅ አይደለም። ለእግዚአብሔርም ምንም የሚሳነው ነገር እንደሌለ ዐውቆ ብሥራቱን በእምነት መቀበል ነበረበት እንጂ መጠራጠር ባልነበረበትም። ይህ ግን ባለመኾኑና ከእርሱ የማይጠበቅ ጥርጣሬ በማሳየቱ ልጁ እስኪወለድ ድረስ በዱዳነት ሊቀጣ በቅቷል።



በሌላ በኩል ደግሞ እመቤታችን ድንግል ማርያም ወንድ ልጅ ትወ ልጂአለሽ ብሎ መልአኩ ገብርኤል ባበሠራት ጊዜ ወንድ ሳላውቅ ይህ እንዴት ይኾናል ብላ ለጠየቀችው ጥያቄ እንደ ዘካርያስ ያልተ ወቀሰችው ወይም ያልተቀጣችው እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ከእርስዋ በፊት መቼም ቢኾን አንዲት ሴት ወንድ ሳታውቅ ልጅ የወለደች መኾንዋ በታሪክ ተሰምቶ ስለማይታወቅ ጥያቄዋ ተገቢነት ያለው ነው። እርስዋም በጠየቀች ጊዜ ስለኹናቴው ለመረዳት ካልኾነ በቀር ጥርጣሬ አድሮባት ያልነበረ መኾኑ የሚታወቀው መልአኩ ገብር ኤል ለጥያቄዋ መልስ በሰጣት ጊዜ እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይኹ ንልኝ ብላ እምነቷን መግለጽዋ ነው።

ሌሎች ምሁራን እንደሚሉት ደግሞ እመቤታችን በጠየቀችው ጥያቄ እንደ ዘካርያስ ያልተወቀሰችው ወይም ያልተቀጣችው ክብር የሚገ ባት የአምላክ እናት ለመኾን የተዘጋጀች በመኾንዋ ነው።

በዚህም መሠረት ከላይ የቀረቡት ጥቅሶች የተለያየ ትርጓሜ አላቸ ው እንጂ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

57 "ኢየሱስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የተወደደ ኾኖ በጥበብና በቁመት እያደገ ይኼድ ነበር።" (ሉቃ. ም.2 ቁ:52 ) ጌታችንና መድ ኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ሰው መኾን እንዳስፈለገው በሚያ ስረዳበት ጊዜ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ እንዲህ ብሏል: - "ልጆች ሥጋና ደም ያላቸው ሰዎች እንደመኾናቸው ኢየሱስም እንደ እነርሱ ሰው ኾነ። ይህንንም ያደረገው በሞቱ አማካይነት በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ዲያብሎስን ለመሻር ነው። እንዲሁም ሞትን በመፍራት ምክ ንያት ዕድሜ ልካቸውን በባርነት ይገዙ የነበሩትን ለመዋጀት ነው፤



www.ethiopianorthodox.org

ምክንያቱም የኢየሱስ ፍላጎት መላእክትን ለመርዳት ሳይኾን የአብርሃምን ዘር ለመርዳት አስቦ ነው። ስለዚህ በኹሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው።" (ዕብ. ም.2 ቁ:14 — 17)

በም.4 ቁ:15 ላይ ደግሞ :- "እኛ ያለን ሊቀ ካህናት በድካምችን ሊራራልን የሚችል ነው፤ ምንም እንኳ እርሱ በኹሉ ነገር የተፈተነ ቢኾን ምንም ኀጢአት አልሠራም" ይላል።

እነዚህ ኹለቱ ጥቅሶች የሚያመለክቱት መድኀኒታችን የሰውን ልጅ ከሞት ለማዳን ከሰው ከተወለደ በኋላ ከኀጢአት በቀር የሰው ልጅ በሰብአዊ ተፈጥሮው የሚያልፍባቸውን እርምጃዎች ኹሉ ተከትሎ አል ፎአል ማለት ነው። ማነኛውም የሰው ልጅ የቁመትና የጥበብ ዕድገቱ ከዕድሜው ጋር አብሮ የሚኼድ እንደመኾኑ መለኮታዊ ተዋሕዶው ባይለ የውም እንኳ መድኀኒታችን ከሰው የተለየ ኹናቴ ማሳት አላስፈለገውም እንጂ እርሱ ከፈለገ ምንም የሚሳነው ነገር እንደሌለ መገንዘብ አለብን።

በኹሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው በተባለውም መሠረት መለኮትን በተዋሐደ ትስብእቱ በቁመትና በጥበብ ማደግን ገንዘብ አደረ ገ። ዲያብሎስን በመሻር የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነትና ከሞት ፍርድ ነጻ ለማውጣት ሲል ከሰው ተወልዶ ከኀጢአት በቀር በኹሉም ነገር ከሰው ልጆች ያልተለየ ኑሮ በመኖሩ ስለ እርሱ በሚነገርበት ጊዜ ስለማነኛውም የሰው ልጅ የሚነገረው የንግግር ዐይነት በመኾኑ ሊያስገር መን አይገባም፤ ሰው የኾነ አምላክ ነውና። ጥያቄና መልስ ቁ:8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥ 57፥ 61፥ 63፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥102 እና በ1ኛው መጽሐፍ ቁ:102፥ 104፥ 112፥ ይመለከቷ ል።

58 በሉቃስ ወንጌል ም.16 ቁ:1 — 9 ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ በነገራቸው ምሳሌ በእምነተ ቢስነቱ ከመጋቢነቱ የተባረረው ዐመፀኛ የራሱ ባልኾነ በጌታው ገንዘብ ለወደፊት ይጠቅሙኛል ብሎ ያመነባቸውን ወዳጆች ያፈራበት በመኾኑ ጌታው ዐመፀኛውን መጋቢ በልባምነት ስላደረገ አመስገነው፤ የዚህ ዓለም ልጆች ለትውልዳቸው ከብርሃን ልጆች ይልቅ ልባሞች ናቸውና ካለ በኋላ እኔም እላችኋለሁ የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ



በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሉአችው በዓመፅ ገንዘብ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ ብሎአቸዋል።

ታዲያ ጌታ የጠቀሰው መጋቢ ዓመፀኛ መኾኑን እየተናገረ የዓመፅ ሥራውን ያመስገነለትና በዓመፅ ገንዘብ ደግሞ እኛም ወዳጆችን እንድናዘጋጅ መምከሩ እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በመሠረቱ ብዙ ምሳሌዎች በሚነገሩበት ጊዜ ሌላ ትርጉም አላቸው እንጂ ቃል በቃል በቀጥታ የሚወሰዱ አይደሉም። እኛ በዚህ ዓለም ውስጥ በምንኖርበት ዘመን ጊዜያዊ እንጂ ዘላለማዊ መኖሪያችን ስላልኾነ የምንቈጠረውም እንደ መጻተኛ ነው። ለምሳሌ ፈርዖን ዕድሜህ ስንት ነው ብሎ ያዕቆብን በጠየቀው ጊዜ ዕድሜዬ በማለት ፈንታ የእንግድነቴ ዘመን መቶ ሠላሳ ዓመት ነው ብሎ መልስ ሰጥቶታል። (ዘፍ. ም.47 ቁ:9) ገንዘባችንም ኾነ ንብረታችን የጊዜያዊ ኑሮ ንብረት በመኾኑ እንደ ባለአደራ እንጂ እንደ ባለቤት ኾነን የምንቆጠር አይደለንም። በዚህም መሠረት ከላይ በተገለጸው ምሳሌ መጋቢና የዓመፅ ገንዘብ መባሉ በዚህ ዓለም ላይ የሚኖረን ገንዘብ በባለአደራነት ነው ለማለት ነው። እንግዲህ በዓመፅ ገንዘብ ወዳጆች እንድናፈራበት መባሉም ለመንግሥት ስማያት የሚያበቃ ሥራ እንድንሠራበት ማለት ነው። ስለዚህ ነው በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሎአችሁ በዓመፅ ገንዘብ ወዳጆችን አድርጉ ብሎ የመከረ ን።

በመጨረሻም የዚህ ዓለም ልጆች ከብርሃን ልጆች ይልቅ ልባሞች ናቸው የተባለው በጽድቅ ሥራ ብቻ ተጠምደው በዚህ ዓለም ምንም ዓለማዊ ንብረት ከሌላቸው ሰዎች ሀብት ኖሮአቸው በዚያ በሀብታቸው የዚህን ዓለም የተደላደለ ኑሮ ከማሳለፋቸውም በላይ በገንዘባቸው ማለት በዓመፅ ገንዘብ የጽድቁንም ሥራ ስለሚሠሩበት በዚህም ዓለም፥ በወዲያኛውም ዓለም የሚጠቀሙ በመኾናቸው ከብርሃን ልጆች ይልቅ የዚህ ዓለም ልጆች ልባሞች ናቸው ተብለዋል።

59. በሉቃስ ወንጌል ም.16 ቁ:19 — 31 በተሰጠው የጌታ ምሳሌ እንደተዘረዘረው አልዓዛር የተባለው ድኻና ሀብታሙ ሰው ከሞቱ በኋላ በተለያዩ ቦታዎች እንዲያርፉ የተደረጉ ሲኾኑ አብርሃም ለሀብታሙ ሰው ላመና በሰጠው መልስ "በእኛና በእናንተ መካከል ትልቅ ገደል አለ፤



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ከእኛ ወደ እናንተ፥ ከእናንተም ወደ እኛ መሻገር የሚችል ማንም የለም" ብሎታል። በሌላ በኩል ደግሞ በአንደኛ ሳሙኤል ም.28 ቁ:19 ላይ ነቢዩ ሳሙኤል ለሳኦል በነገረው ትንቢት:- "ነገ አንተና ልጆችህ ከእኔ ጋር ትኾናላችሁ" ባለው መሠረት በምዕራፍ 31 ላይ እንደ ተገለጸው የሳኦል ልጆች በፍልስጥኤማውያን ተገደሉ፤ ሳኦልም ወድቆ ሞተ።

ታዲያ ለጻድቃንና ለኀጠአተኞች የተለያዩ ቦታዎች መኖራቸው በሉቃስ ወንጌል ላይ የተለገጸ ከኾነ እንዴት ተደርጎ ነው ነቢዩ ሳሙኤል በኀጢአታቸው ምክንያት በጠላት ተሸንፈው የተገደሉትን ሳኦልንና ልጆቹን ከሞቱ በኋላ ከእርሱ ጋር እንደሚኖሩ የተናገረው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ሞት ሲባል ነፍስ ከሥጋ መለየት እንደመኾኑ የመጽሐፈ መክብብ ጸሐፊ በምዕራፍ 12 ቁ:7 ላይ እንዳመለከተው አፈር ማለት ከአፈር የተፈጠረው ሥጋችን ወደ ተፈጠረበት ምድር እንደሚመለስና ነፍስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንደምትመለስ ገልጾአል። ለዚህም አባባሉ መሠረት ያደረገው በኦሪት ዘፍጥረት ም.2 ቁ:7 እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር አበጅቶ በአፍንጫው የሕይወት እስትንፋስ እፍ ካለበት በኋላ ሕያው ነፍስ ያለው መኾኑንና ኀጢአት ከሠራ በኋላ ደግሞ በኀጢአቱ ምክንያት በምዕራፍ 3 ቁ:19 ላይ አፈር ስለኾነ ወደ አፈር እንዲመለስ የተፈረደበት በመኾኑ ነው። ስለዚህም ሰው ኹሉ ከሞተ በኋላ በመሬት ውስጥ የሚቀበር ያም ባይኾን ከመሬት የማይቀር መኾኑን ለማመልከት አፈር ወደነበረበት እንደሚመለስ አመልክቶአል።

እንግዲህ ሰው ኹሉ ከሞተ በኋላ ሥጋው ማለት በድኑ የሚቀበር በመኾኑ የሚሞቱት ኹሉ ቀድመው ከሞቱት ጋር ይቀላቀላሉ መባል የተለመደ አነጋገር ነበር። ለምሳሌ በኦሪት ዘፍጥረት ም.25 ቁ:9 ላይ አብርሃም ሲሞት "ወደ ወገኖቹ ተከማቸ» ተባለ። በምዕራፍ 35 ቁ:29 ላይ "ይስሐቅም ወደ ወገኖቹ ተከማቸ" ተብሎአል። በም.49 ቁ:33 ላይ "ያዕቆብ ወደ ወገኖቹ ተከማቸ" ተብሎአል። እንዲሁም በመጽሐ መሳፍንት ም.2 ቁ:10 "ትውልድ ኹሉ ወደ አባቶቻቸው ተከማቹ" ተ ሎአል። ሌሎች ብዙ ተመሳሳይ ምሳሌዎችን መጥቀስ የሚቻል ቢኾን ለጊዜው የቀረቡት ምሳሌዎች በቂ እንደኾኑ ይገመታል።



ከአባቶቻቸው ወይም ከወገኖቻቸው ጋር ተከማቹ የሚለው አባባል የሚጸድቁ ወይም የሚኰነኑ መኾናቸውን የሚያመለክት ሳይኾን ከእነርሱ በፊት እንደሞቱት ወገኖቻቸው ሞቱ ማለት ከእነርሱ ጋር በሞት አብረው ኾኑ ማለት ነው።

በዚህም ዓይነት ነቢዩ ሳሙኤል ለንጉሥ ሳኦል አንተና ልጆችህ ነገ ከእኔ ጋር ትኾናላችሁ ማለቱ እንደኔው ነፍስና ሥጋችሁ ተለይቶ እንደ እኔው ሥጋችሁ ይቀበራል ወይም መሬት ላይ ይወድቃል ማለቱ ነው እንጂ ሰማያዊ ኑሮአችን አንድ ዐይነት ይኾናል ማለቱ አይደለምና ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

60. በሉቃስ ወንጌል ም.22 ቁ:42 ላይ አባት ሆይ ፈቃድህ ቢኾን ይህን ጽዋ ከእኔ አርቅልኝ፤ ነገር ግን የአንተ ፈቃድ ይኹን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይኹን" ብሎ ጌታ የጸለየው ጸሎት በዮሐንስ ወንጌል ም.10 ቁ:17 — 18 "ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠና መልሼም ለመውሰድ ፈቃደኛ ስለኾንኩ አብ እኔን ይወደኛል፤ ሕይወቴን በፈቃዴ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ የሚወሰዳት ማንም የለም፤ ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ መብት አለኝ።» ከሚለው ማረጋገጫ ጋር እንዴት ይታረቃል።

በዚህ ጸሎቱ ጌታ ሞትን ፈርቶና የሚደርስበትም ሕማም ያስፈራቶና ያልፍላኀቱ እንደሚደርስበት ተደርጎ ይገመት ይኾናል።

መድኀኒታችን የሰውን ዘር ለመቤዠት የግድ መሞት እንደነበረበት ስለፈቀደ ነው እንጂ ሊይዙት የመጡት ሰዎች ለመያዝ አልደፈሩም ነበር። የምትፈልጉኝ እኔ ነኝ በማለት ካደፋፈራቸው በኋላ ነው የያዙት። ሐሙስ ዕለት ማለት በተሰቀለበት ዋዜማ በአይሁድ እንደሚያዝና ሕማማትና ሞት እንደሚያደርሱበት ለደቀ መዛሙርቱ ነግሮአቸዋል። ለመሞት የፈራ ወይም የማይፈልግ ቢኾን ኖሮ ተዘጋጅቶ ባልጠበቃቸውም ነበር? ኹሉን ነገር ከማወቅ ጊዜና ቦታ የማይወስነው በመኾኑ ጴጥሮስ የሚክደው መኾኑን በማቴ. ም.26 ቁ:34፥ አህያዋንና ውርንጫዋን እንዲያመጡ ያዘዛቸው ደቀ መዛሙርት ምን እንደሚያጋጥማቸው በማቴ. ም.21 ቁ:1 — 4, ጴጥሮስ በዓሣው ሆድ ውስጥ ምን እንደሚያገኝ በማቴ. ም.17 ቁ:27፥ በደቀ መዛሙርቱ መካከል ከእነርሱ



www.ethiopianorthodox.org

ማን እንደሚበልጥ ይከራከሩ የነበረውን ሐሳብ ማወቁ በማርቆስ ወንጌል ምዕ.9 ቁ:33፥ የሠማርያይቱን ሴት ምሥጢር በዮሐ. ም.4 ቁ:18፥ የአልዓዛርን ሞት በዮሐ. ም.11 ቁ:11፥ የፋሲካን ምግብ እንዲያዘጋጁ ለላካቸው ኹለት ደቀ መዛሙርቱ ምን እንደሚያጋጥማቸው በማር ም.14 ቁ:13፥ ናትናኤልን በበለሱ ሥር ኾኖ ማየቱ በዮሐ. ም.1 ቁ:48፥ የኢየሩሳሌምና የቤተ መቅደስ መፍረስ ለደቀ መዛሙርቱ መንገሩ በማቴ. ም.24 ቁ:2፥ የትንሣኤ ሙታንና የዓለም ኅልፈት ምልክቶች ለደቀ መዛሙርቱ መንገሩ በማቴ. ም.24 ቁ:29 — 31 የገለጠ እንደመኾኑ ወንጌላዊው ዮሐንስ እንዳለው እርሱ በሰው ልብ ያለውን ኹሉ ያውቅ ስለነበር ስለ ሰው ማንም እንዲነግረው አያስፈልገውም ነበር" (ዮሐ. ም.2 ቁ:25) ስለዚህ በእርሱ ላይ የሚደርሰውን ሕማምና ሞት አስቀድሞ ስለሚያውቅ ሞትን ፈርቶ ቢኾን ወይም ለመሞት ፈቃደኛ ባይኾን ራሱን ለማዳን ባልተሳነውም ነበር።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያን ጸሎት በጸለየበት ጊዜ አንድ የክፍል መምህር ለተማሪዎቹ ትምህርት የሚሰጠው በገለጻና በሠርቶ ማሳየት ነው። መድኀኒታችን ለደቀመዛሙርቱ ምን ዐይነት ጸሎት መጸለይ እንደሚገባቸው ቀደም ብሎ ገለጸ አድርጎላቸው ነበር፡ አሁን በጌተሴማኒ ያትክልት ቦታ ግን የሠርቶ ማሳየት ትምህርቱን አስተማራቸው። ይህም ማለት ተመሳሳይ ችግር በሚያጋጥማቸው ጊዜ እንዴት መጸለይ እንደሚገባቸው አሳያቸው ማለት ነው እንጂ ጌታ ምንም ሕማማትን ላልመቀበልና ላለመሞት ፈልጎ ቢኾን ኖሮ ባልተሳነውም ነበርና ይህንኑ ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ። /ጥያቄና መልስ ቁ:8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥ 57፥ 61፥ 63፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥ 102 እና በ1ኛው መጽሐፍ ቁ:102፥ 104፥ 112 ይመለከቷል።

61 "በዚያን ጊዜ የሚያበረታታው መልአክ ከሰማይ መጥቶ ታየው።" (ሉቃ. ም.22 ቁ:43) መልአክ ሊያበረታታው የሚችለው አንድን ፍጡር እንጂ ፈጣሪን ስለማይኾን ይህ ኹናቴ እርሱ ፍጡር መኾኑን የሚያመለክት በቂ ማስረጃ ነው ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ።

የመላእክት ተፈጥሮ ርኅራኄ የተመላበት በመኾኑና በችግር ላይ የሚያገኙትን ማነኛውንም ሰው ለመርዳት ዝግጁ ኾነው ስለሚገኙ በጌታ



ላይ የደረሰው ሕማም በፍላጎቱና በፈቃዱ መኾኑን ባለማወቁ ይህ የተጠቀሰው መልአክ የማንም እርዳታ የማያስፈልገውን ጌታን ለመርዳት ብቅ አለ። ኾኖም ሊያበረታታው ታየ አለ እንጂ አበረታታው አላለም። በሌላ በኩል ደግሞ ጌታ በትስብእቱ መልአክ አበረታታው ቢባል ምንም የሚያስገርም አይደለም። ምክንያቱም መድኀኒታችን በዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜ ከኀጢአት በቀር በኹሉም ነገር የሰውን ልጅ መስሎአል ና።

የዚህ መልአክ ጌታን ለማበረታታት መታየት ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሰይፉን መዝዞ ማልኮስ የተባለውን የሊቀ ካህናቱን አሽከር ጆሮ ከመቁረጥ ጋር ተመሳሳይ ነው። ጌታ ግን ለቅዱስ ጴጥሮስ አድራጎት የነበረው አስተሳሰብ እንደሚከተለው ነው። "ሰይፍን የሚያነሡ በሰይፍ ይጠፉሉና ሰይፍህን መልሰህ ወደ ሰገባው ክተት። ለመኾኑ እኔ አባቴን ብለምን እርሱ በብዙ ሺ የሚቈጠሩ የመላእክት ሠራዊት ሊልክልኝ የማይችል ይመስልሃልን? እንዲህ ከተደረገ ደግሞ መከራ መቀበል አለበት የሚለው የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል እንዴት ይፈጸማል?" (ማቴ. ም.26 ቁ.52 – 54) ይህንንም ከተናገረ በኋላ የተቈረጠውን ጆሮ በመፈወስ ቀድሞ እንደነበረ የመለሰለት መኾኑን በሉቃስ ወንጌል ም.22 ቁ:51 እንመልከት። ጥያቄና መልስ ቁ:8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥ 63፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥ 102፥ እና ከ1ኛው መጽሐፍ ቁ:102፥ 104፥ 112 ይመለከቷል።

62. በሉቃስ ወንጌል ም.24 ቁ:36 — 40 "እነርሱም ይህንን ሲናገሩ ሳሉ ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ ሰላም ለእናንተ ይኹን አላቸው። እነርሱ ግን መንፈስ የሚያዩ መስሎአቸው ደንገጡና ፈሩ። ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው ስለምን ትደነግጣላችሁ? ስለምንስ በልባችሁ ትጠራጠራላችሁ? እጆቼንና እግሮቼን አይታችሁ እኔ ራሴ መኾኔን ዕወቁ፤ ዳስሳችሁም እዩኝ፤ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውም። ይህንንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው" ካለ በኋላ በመጀመሪያው የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት ም.13 ቁ:18 ላይ ክርስቶስም ራሱ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን ፈልጎ እርሱ ጻድቅ ኾኖ ሳለ በኀጢአታችን ምክንያት በማያዳግም ኹኔታ አንድ ጊዜ ሞቶአል፤ እርሱ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ኾነ» በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስለን ይኾናል።



www.ethiopianorthodox.org

ኹለተኛውን ጥቅስ ማለት የሐዋርያው የጴጥሮስን አባባል መሠረት በማድረግ ጌታ የተነሣው በመንፈስ ብቻ እንደኾነና ለሐዋርያትም የተገለጸባቸው ኹኔታዎች ኹሉ ለእነርሱ ለማስመሰል ብሎ ነው እንጂ ከሞት በተነሣ ጊዜ ሰውነት አልነበረውም የሚሉ ወገኖች አሉ። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ ሙታን በኩር የተባለበት ምክንያት በትንሣኤ ሙታን ጊዜ ዳግመኛ የማይሞትና የማይበሰብስ ሰውነትን ይዘን ከመነሣታችን ጋር ተመሳሳይ የኾነ ሰውነት ይዞ በመነሣቱ ነው። ይኹን እንጂ የእኛና የእርሱ ልዩነት የእኛ ሰውነት ከፈረሰና ከበሰበሰ በኋላ የሚነሣ ሲኾን የእርሱ ግን መፍረስና መበስበስ ሳይደርስበት ተነሥቶአል። (መዝ.16 ቁ:10፥ 1ኛ ቆሮ. ም.15 ቁ:23፥ ቆላ.ም.1 ቁ:18)

ሐዋርያው ጴጥሮስ በመንፈስ ሕያው ኾነ ያለው ሰውነት የሌለው መንፈስ ለማለት አይደለም። መንፈሳዊ ሰውነት ለማለት ነው። መንፈስ የማይሞት እንደመኾኑ ጌታም ሲነሣ ዳግመኛ በማይሞት ሰውነት በመነሣቱ ነው በመንፈስ ሕያው ኾነ የተባለው እኛም ብንኾን በትንሣኤ ሙታን ጊዜ የምንነሣው በመንፈሳዊ ሰውነት ነው። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ መጀመሪያ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.15 ቁ:15 ቁ:42 እና 44 የሚከተለውን ማረጋገጫ የሰጠው "ከሞት የሚነሡ ሰዎች ኹኔታ ይህንኑ ይመስላል፤ የሚጠፋ፥ ሟች አካል ኾኖ የተዘራው የማይጠፋ ሕያው አካል ኾኖ ይነሣል። ሥጋዊ አካል ኾኖ የተዘራው መንፈሳዊ አካል ኾኖ ይነሣል።" በዚሁም ዐይነት ሐዋርያው ጴጥሮስ በመንፈስ ሕያው ኾነ በሚልበት ጊዜ በመንፈሳዊ ሰውነት ማለቱ ነው እንጂ መንፈስ ብቻ ተነሣ ማለቱ አይደለም። መንፈስ ደግሞ መቼም ቢኾን የማይሞት እንደመኾኑ ከሞት መነሣት የሚለው ቃል አይስማማውም።

ጌታ የተነሣው በመንፈሳዊ ሰውነት ሳይኾን በመንፈስ ብቻ ነበር የሚሉ ሰዎች ስለትንሣኤው የተናገረውን ትንቢት፥ ከተነሣም በኋላ የተናገራቸውን አነጋገሮችና ያደረጋቸውን ድርጊቶች ትክ ብለው ያስተዋሉአቸው አይመስልም።



ነቢዩ ዳዊት የጌታን በሰውነቱ መነሣት ትንቢት ሲናገር [illegible] "ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፥ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም" ብሏል። (መዝ.16 ቁ:10)

በሉቃስ ወንጌል ም.24 ቁ:36 — 40 እንደተመለከተው ጌታ ከሞት ከተነሣ በኋላ በደቀ መዛሙርቱ መካከል ተገኝቶ ከሙሉ ሰውነቱ ጋር ያለእርሱ ራሱ እንጂ መንፈስ አለመኾኑን የዘረዘረው የራሱ ማረጋገጫ በቂ ማስረጃ ኾኖ ሳለ ለምን ተከራካሪዎቹ እኔ መንፈስ አይደለሁም ያለውን ጌታን ካንተ ይበልጥ እኛ እናውቃለንና አንተ መንፈስ ነህ ለማለት ይሞክራሉ?

ጌታም እኔ መንፈስ አይደለሁም በማለት ብቻ አላቆመም እጆቹንና እግሮቹን ከማሳየቱም በላይ የተጠበሰ ዓሣ አቅርበውለት በእነርሱው ፊት በላ።

ወደፊት ሞቶ በሰውነቱ እንደሚነሣ በዮሐንስ ወንጌል ም.2 ቁ:19 ላይ ትንቢት ሲናገር "ይህንን ቤተ መቅደስ አፍርሱትና እኔ በሦስት ቀን እሠራዋለሁ" ብሎአል።

ሌላው የማያወላውለው ማስረጃ ደግሞ ከቀደ መዛሙርቱ አንዱ የኾነው ቶማስ በምስማር የተቸነከሩትን እጆቹንና በጦር የተወጋውን ጐኑን ካልዳሰስሁ አላምንም ብሎ ስለነበረ ጌታ እጆቹንና ጐኑን እንዲዳስ
ስ ለቶማስ የፈቀደለት መኾኑን በዮሐንስ ወንጌል ም.20 ቁ:27 እንመ
ልከት። መንፈስ የማይዳሰስ መኾኑን እናውቃለን።

እንግዲህ ተከራካሪዎች እንደሚሉት ጌታ በሰውነቱ ሳይኾን በመን
ፈስ ብቻ ኾኖ ተነሥቶ ቢኾን ኖሮ እንዴት የሚዳሰስ ሰውነት ሊኖረ ው
ይችል ነበር? እንዴትስ ምግብ ለመብላት በቻለ ነበር?

ደግሞስ እኔ መንፈስ አይደለሁም ብሎ እርሱ ራሱ ያረጋገጠ ከመኾ
ኑ በላይ እንዴት ሌላ የተሻለ ማስረጃ አለ ብለን እንከራከራለን?



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ወንጌል 21 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ምዕራፍ 1 ሲኾን ስለ መጥምቁ ዮሐንስና የዓለምን ኀጢአት ለማስወገድ የጌታችን ሰው መኾን ታሪክ ይገኙበታል።

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 2 እስከ ምዕራፍ 12 ድረስ ሲኾን የጌታ ንግግሮችና ሥራዎች፥ ውሃን ወደ ወይንነት መለወጡ፥ ከኒቆዲሞስ ጋር ያደረገው ንግግር፥ ከሰማርያዩቱ ሴት ጋር ያደረገው ንግግር፥ ጥበብ የተመላባቸው ንግግሮቹና ከአይሁድ ጋር ያደረጋቸው ክርክሮች፥ እንዲሁም አልዓዛርን ከሞት የማስነሣቱ ታሪክ ይገኙበታል።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 13 እስከ ምዕራፍ 17 ድረስ ሲኾን የደቀ መዛሙርቱን እግሮች በማጠብ የትሕትናን ትምህርት በተግባር ማስተማሩ፥ ደቀ መዛሙርቱን ያሳዘናቸው ንግግሩና ትእዛዙ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን እንደሚልከላቸው ተስፋ መስጠቱ፥ ስለ ደቀ መዛሙርቱና ስለምእመናኑ ጸሎት ማቅረቡ ታሪክ ይገኙበታል።

አራተኛው ክፍል ምዕራፍ 18 እና 19 ሲኾን በውስጡም አይሁድ በጌታ ላይ የሞት ፍርድ ማሳለፋቸውና ፍርዱንም በተግባር ላይ ማዋላቸው፥ ጌታም እናቱን ለሚወደው ደቀ መዝሙር ለዮሐንስ አደራ የመስጠቱ ታሪክ ይገኙበታል።

አምስተኛው ክፍል ምዕራፍ 20 እና 21 ሲኾን በእርሱም ስለ ጌታ ከሞት መነሣትና በመጨረሻ ለደቀ መዛሙርቱ ያደረገው ንግግር ታሪክ ይገኙበታል።





63. በዮሐንስ ወንጌል ም.1 ቁ.3 ላይ ማንኛውም የተፈጠረው ፍጥረት ኹሉ ያለወልድ ፈጣሪነት የተፈጠረ እንደሌለ የተገለጸ ሲኾን ወደ ቆላስይስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.1 ቁ:15 ላይ "ክርስቶስ ለማይታየው እግዚአብሔር እውነተኛ ምሳሌ ነው። እርሱ ኹሉ ነገር ከመፈጠሩ በፊት የነበረ የፍጥረት ኹሉ በኩር ነው" በመባሉ ኹለቱ አባባሎች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል።

ኹለተኛውን ጥቅስ መሠረት በማድረግ አንዳንድ ወገኖች ጌታን ፍጡር ነው የማለት ድፍረትን የተመላ ክርክር ያቀርባሉ።

የፍጥረት ኹሉ በኩር ማለት በመጀመሪያ የተፈጠረ ነው ሊባል የማይቻልበት ምክንያት በኦሪት ዘፍጥረት ም.1 ቁ.1 ላይ እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠረው ሰማይንና ምድርን መኾኑ የተገለጸ በመኾኑ ነው። በመጀመሪያው ጥቅስ መሠረት ኹሉን ነገር የፈጠረ እርሱ ነው ተብሏል። ይህም ኹሉን ነገር የፈጠረው በኦሪት ዘፍጥረት ም.1 ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ነው። ታዲያ ኹሉን ነገር የፈጠረው እግዚአብሔር በኩር በመባሉ ብቻ እንዴት ከፈጣሪ አምላክነት ወደ ፍጡርነት ሊያዛውሩት በቁ? ችግራቸው በኩር የሚለው ቃል በጥቅሱ ውስጥ እንዴት ሊገባ ቻለ የሚል ከኾነ እዚህ ላይ በኩር ማለት ከተፈጠረው ፍጥረት ኹሉ በፊት የነበረ መኾኑን የሚያመለክት ነው እንጂ ፍጡር መኾኑን የሚያመለክት አይደለም። ይህም ለመኾኑ ከዚያ ቀጥሎ በቁጥር 16 እና 17 ላይ በሰማይም ኾነ በምድር ከተፈጠሩት ነገሮች ኹሉ አንዳችም ያለ እርሱ ፈጣሪነት የተፈጠረ ነገር እንደሌለ ተገልጾአል። ይህም የሚያመለክተው እርሱ ከፍጥረት ኹሉ በፊት የነበረ መኾኑንና ኹሉንም ነገር የፈጠረ መኾኑን ነው እንጂ ፍጡር መኾኑን አይደለም። ፈጣሪ እስከኾነ ድረስ ደግሞ ፍጡር ሊኾን አይችልም። ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.1 ቁ.2 ላይ እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በልጁ አማካይነት ነው ስለተባለ እግዚአብሔር የመፍጠርን ሥልጣን ብቻ ስለሰጠው ነው እንጂ እርሱ መለኮታዊ ክብር ኖሮት አይደለም ይላሉ። ይህ አስተሳሰብ ግን ትክክል አለመኾኑን የምንገነዘበው በዮሐንስ ወንጌል ም.1 ቁ.2 እና ወደ ቆላስይስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.1 ቁ.16



www.ethiopianorthodox.org

– 17 ላይ ያለእርሱ ፈጣሪነት ምንም ነገር ያልተፈጠረ መኾኑ ከመገለጹ በቀር የመፍጠር ሥልጣን ከሌላ እንደተቀበለ አልተገለጸም።

እዚህ ላይ የሥላሴን ያንድነትንና የሦስትነትን ግብር በምንዘ ረዝርበት ጊዜ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአብ ልብነት ያስባሉ፤ አብና መንፈስ ቅዱስ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ፤ አብና ወልድ ደግሞ በመን ፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ይተነፍሳሉ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ሕይወ ትነት ይኖራሉ እንላለን። በዚህም መሠረት በወልድ ቃልነት ማለት ይኹን በማለት ስለተፈጠረ በወልድ አማካይነት ተፈጠረ ተባለ። እግዚ አብሔር ማለት ደግሞ የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ የአንድነት ስም መኾኑን ማወቅ አለብን። ጥያቄና መልስ ቁ.8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥ 57፥ 61፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥ 102፥ እና ከ1ኛው መጽሐፍ ቁ.102፥ 104፥ 112፥ ይመለከቷል።

64. በዮሐንስ ወንጌል ም.1 ቁ.52 ላይ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ" ተብሎ በጌታ የተገለጸው የወደፊት ትርእይት መቼም ቢኾን ሰማያት ሲከፈቱና መላእክት ሲወጡና ሲወርዱ መታየቱ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አልተመዘገበም። ታዲያ ለምን በጌታ ተነገረ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ማየት የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኹለት የተለያዩ ትርጉሞች አሉት። አንዱ ትርጉም በዓይን ማየት ነው። ኹለተኛው ትርጉም ደግሞ አንድን ነገር ማወቅ ማለት ነው። ለምሳሌ ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ ም.5 ቁ:11 ላይ "እነሆ፥ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደታገሠ ሰምታችኋል፤ ጌታም እንደፈጸመለት አይታችኋል" ብሏል። በዚህ መሰሉ የማየት ትርጉም ነው ጌታ ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔር መላእክት ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ ያለው። የሰማይ መከፈትም ምሳሌያዊ አነጋገር ነው።፡ መላእክት ረቂቆች የሰማይ መናፍስት እንደመኾናቸው እንደሚዳሰስ ነገር ሰማይን ከፍተውና ዘግተው የሚወጡና የሚገቡ አይደሉም። ሰማይም እንደበር የሚከፈትና የሚዘጋ አይደለም። በሰማይ መከፈትና መዘጋት ባይኖርም አንድ ደጅ በሚከፈትበት ጊዜ ኹሉን ነገር ግልጽ አድርጎ ለማሳየት እንደሚችል እናንተም የሰማይን ምሥጢር እንድታውቁ

www.ethiopianorthodox.org



ይደረጋል ማለቱ ነው። ይህም አባባል ጌታ በማቴዎስ ወንጌል ም.5 ቁ:8 ላይ ንጹሕ ልብ ያላቸው ብፁዓን ናቸው፤ እግዚአብሔርን ያዩታልና ብሎ ከሰጠው ትምህርት ጋር ግንኙነት አለው። በዮሐንስ ወንጌል ም.1 ቁ:48 ላይ ናትናኤል ወደ እርሱ ሲመጣ ባየ ጊዜ እነሆ፥ ተንኮል የሌለበት እውነተኛ የእስራኤል ሰው ብሎ አመስግኖታል። ተንኮል የሌለበት ሰው ማለትም ልቡ ንጹሕ የኾነ ሰው ማለት እንደመኾኑ እግዚአብሔርን የማየት ዕድል ከሚሰጣቸው ሰዎች መካከል አንዱ እርሱ ይኾናል ማለት ነው።

65. በዮሐንስ ወንጌል .2 ቁ.4 – 5 ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እመቤታችን የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም ብላ ለነገረችው ማሳሰቢያ መልስ ሲሰጣት "አንቺ ሴት፥ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ ጊዜዩ ገና አልደረሰም" ስላላት እናቱን እንደማያከብራት የሚመስላቸው ወገኖች አሉ።

አንቺ ሴት የተሰኘው አባባል የአነጋገር ዘይቤ እንጂ አክብሮት የመንሣት አለመኾኑ የሚታወቀው ጌታ ተሰቅሎ ሳለ እናቱን ለሚወደው ደቀ መዝሙር አደራ በሰጠበት ጊዜ የሚወደውን ደቀ መዝሙር እያመለከተ "አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ" ብሎአታል። (ዮሐ. ም.19 ቁ.26) በዚያን ጊዜ ደግሞ የአክብሮትና የኀዘኔታ እንጂ ምንም ክብርን የመንሣት ኹናቴ አልነበረም።

"ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዩ ገና አልደረሰም" ለተሰኘው አረፍተ ነገር የተለያዩ ትርጓሜዎች ይሰጣሉ።

አንደኛ/ የእግዚአብሔር ሥራዎች ኹሉ በሰዓታት የተወሰኑ በመኾናቸው ያንን ተአምር የማደርግበት ሰዓትና ደቂቃ ገና አልደረሰም እንጂ አንቺ ጠይቀሽኝ የጠየቅሽኝን የማላደርግበት ምን ምክንያት አለኝ ለማለት ነው።

ኹለተኛ/ አንድን ድርጊት ፈቅዶ ያደርጋል እንጂ ማንም አዝዞት ወይም ምክር ሰጥቶት የማያደርግ መለኮታዊ ባሕርይ ያለው መኾኑን ለማመልከት ነው። የእግዚአብሔር ሥራዎች ደግሞ ለኹሉም ጊዜ አላቸው።

ሦስተኛ/ ቀድሞ የነበረው ጠጅ ገና ያላለቀ በመኾኑ ያ እስኪያልቅ ድረስ እንጠብቅ ለማለት ጊዜዬ ገና አልደረሰም ብሎአታል።

ይኹን እንጂ አነጋገሮቹ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖራቸውም የእናቱን የእመቤታችንን አማላጅነት እንቢ ብሎ የቀረ አይደለም። ይህም ለአገልጋዮቹ እንደማይኾን እመቤታችን ደኅና አድርጋ ስለምታውቅ ለአገልጋዮቹ የሚላችሁን ኹሉ አድርጉ ብላቸዋለች። ከዚያም ጋኖቹን ኹሉ ውሃ እንዲሞሉባቸው ካዘዛቸው በኋላ ውሃውን ወደ ወይንነት በመለወጥ የእመቤታችንን አማላጅነት አረጋግጦአል። ይህም የሚያመለክተው ጌታ እናቱን የሚያከብራት መኾኑንና የእርስዋንም አማላጅነት የሚቀበል መኾኑን ስለኾነ ይህንኑ ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

66. በዮሐንስ ወንጌል ም.5 ቁ.19 ላይ"እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፤ ያ የሚያደርገውን ኹሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋል" በማለቱ ወልድ የሚያደርጋቸው ድርጊቶች ኹሉ በአብ ተቈጣጣሪነት እንደሚደረጉ በመገመት ይህን ጥቅስ አብ ከወልድ የሚበልጥበት ማስረጃ አድርገው የሚያቀርቡ ወገኖች አሉ።

ይህ አባባል ግን የመለኮት አንድነትንና የምሥጢረ ሥጋዌን ኹናቴ የሚገልጽ እንጂ የወልድን የበታችነት የሚያምለክት አይደለም። በቁጥር 17 ላይ አባቴ እስከ ዘሬ ይሠራል፤ እኔም እሠራለሁ ብሎአቸዋል። ቀደም ተብሎ በተለያዩ አርእስት እንደተገለጠው አፍአዊ የሥላሴ ግብሮች ኹሉ የመለኮታዊ አንድነት ግብሮች ናቸው ተብሎአል። ስለዚህ መውለድ፥ ማሥረጽ፥ መወለድና መሥረጽ የተባሉት ውሳጣዊ ግብሮች ካልኾኑ በቀር ሌሎቹ ግብሮች ኹሉ የመለኮታዊ አንድነት ግብሮች ናቸው። ስለዚህ ነው "አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም" የተባለው ወልድ ከራሱ ምንም ማድረግ አይችልም ማለት ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የጋራ ማለት የመለኮታዊ አንድነት ግብር ነው እንጂ የወልድ ግብር ብቻ አይደለም ለማለት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ የሰውን ሥጋ ሲለብስ መለኮትንና ትስብእትን ያዋሐደ ው ያለማጠፋፋት በመኾኑ አንዳንድ ጊዜ ወልድ በትስብእቱ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወልድ በመለኮቱ ማለቱ ስለሚኾን በአንድ ፍጡር ደረጃ ራሱን ዝቅ አድርጎ በሚናገርበት ጊዜ ወልድ በትስብእቱ ማለቱ መኾኑን መገንዘብ ይኖርብናል።



በዚህም መሠረት አይችልም የሚለው ቃል አንድም የመለኮታዊ አንድነት ግብር ነው እንጂ የአንድ አካል ግብር ብቻ አይደለም ለማለት ነው፤ ወይም ደግሞ ወልድ በተዋሕዶ ባሕርይ እንጂ በትስብእቱ ብቻ አይችልም ለማለት ነውና ከዚህ የተለየ አለመኾኑን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

67. በዮሐንስ ወንጌል ም.5 ቁ.31 ላይ "እኔ ስለራሴ ብመሰክር ምስክርነቴ እውነት አይደለም" ካለ በኋላ በምዕራፍ 8 ቁ.14 ላይ ደግሞ "እኔ ስለራሴ ብመሰክር ምስክርነቴ እውነት ነው" በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል።

ስለራሴ ብመሰክር ሐሰተኛ ነኝ ማለቱ በሕጉና በእነርሱ አስተያየት መሠረት ማለቱ ነው። (ዘዳ. ም.19 ቁ.15) በዚህም መሠረት ምስክሮቹ ናቸው ያላቸው እግዚአብሔር አብ፥ ዮሐንስ መጥምቁና እንዲሁም ሥራዎቹ ናቸው። (ዮሐ. ም.5 ቁ.32 – 37) ስለራሴ ብመሰክር ምስክርነቴ እውነት ነው ያለው "ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም" በተባለው መሠረት አምላክነቱን ሊገልጽላቸው ስለፈቀደ ነው። (ዘኍ. ም.23 ቁ.19)

እንግዲህ የጌታ አባባል እኔ ፈጣሪ አምላክ እንደመኾኔ ምስክርነቴ ትክክል ቢኾንም አንተ ለራስህ መመስከርህ በቂ አይደለም የሚል እምነት ያላችሁ ከኾነ ሦስት ምስክሮች አሉኝ። እነርሱም አብ፥ ዮሐንስና ሥራዬ ናቸው ማለቱ ነው።

68. በዮሐንስ ወንጌል ም.7 ቁ.16 ላይ ትምህርቴ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም ካለ በኋላ በምዕራፍ 10 ቁ.30 ላይ "እኔና አብ አንድ ነን፤" በምዕራፍ 16 ቁ.15 ላይ ደግሞ "የአብ የኾነው ኹሉ የእኔ ነው" በማለቱ ጥቅሶቹ ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።



www.ethiopianorthodox.org

ጌታ የመጀመሪያውን አባባል የተናገረው ይህ ሰው ሳይማር መጻ
ሕፍትን እንዴት ያውቃል ብለው አይሁድ እርስ በርሳቸው ለተጠያየቁት
ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነው። በአይሁድ ዘንድ አንዳንድ የታወቁና
ዝነኞች ምሁራን ነበሩ። የሰውም ዐዋቂነቱ የሚገመተው በአስተማሪው
ዝነኛነት ነበር። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ የራሱን ማንነት ሲያስተዋ
ውቅ በገማልያል እግር አጠገብ አንዳደገ ማለት ገማልያል የተባለው
ዝነኛ መምህር እንዳስተማረው ይገልጻል። (የሐ.ሥ. ም.22 ቁ.3) ጌታ
የገለጸላቸው አገላለጽ የእርሱ መምህር ምድራዊ አለመኾኑና እንደ
እነርሱ በምድራዊ መምህር የማይመካ መኾኑን ለማመልከት ነው እንጂ
የአብ የኾነው ኹሉ ማለት ሥልጣኑ፥ ገዢነቱና ዕውቀቱ የእርሱም
ሳይኾኑ ቀርተው አይደለም።

69 በዮሐንስ ወንጌል ም.9 ቁ.35 መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
የእግዚአብሔር ልጅ ሲባል፥ በአንደኛው የዮሐንስ መልእክት ም.3
ቁ.38 ላይ አዳም የእግዚአብሔር ልጅ ተብሏል።

ጌታ የእግዚአብሔር ልጅ መባሉ ከሦስቱ አካላት አንዱ በመኾኑ
ነው። ሌላው አካል አባት መባሉ ወልድ ልጅ ስለተባለ ነው። አብ
በአባትነቱ ዘላለማዊ ነው፤ ወልድም በልጅነቱ ዘላለማዊ ነው። ወልድ
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቃል፥ የእግዚአብሔር መልክና ክብር መግለጫ
ይባላል። በሕሊና ውስጥ ያለውን ሐሳብ ቃል እንደሚገልጠው ኹሉ አብ
በወልድ አማካይነት ይታወቃል የፀሐይ ብርሃን የፀሐይን ጠባይ
ቢገልጽም ራሱ አካሉ ነው። በዚሁም ዐይነት ክርስቶስ የእግዚአብሔርን
ክብር ቢገልጥም የመንፈሳዊ መለኮታዊ ክብሮችን ይገልጥልናል። (ማቴ.
ም.11 ቁ.27፥ ሉቃ. ም.10 ቁ.22)

ወልድም የአብ አንድያ ልጅም ተብሏል። (ዮሐ. ም.1 ቁ.14፥
ም.3 ቁ.16) ይህም አባባል የሚያመለክተው እርሱ የሚጋራው የሌለ
የተለየ አንድያ ልጅ መኾኑን ነው።

የሰው ልጆች ግን የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት እግዚአብሔር
በመልኩ ስለፈጠራቸው ነው። ክርስቲያኖችም የእግአብሔር ልጆች
የተባሉት በዳግም መንፈሳዊ ልደት በጸጋ ልጆቹ ይኾኑ ዘንድ ተቀባይነት
አግኝተው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ስለተሰጣቸው ነው። ይህም



ልጅነት በአጠቃላይ መላእክትንም የሚጨምር ሲኾን የባሕርይ ልጅነት
ግን ለወልድ ብቻ የተጠበቀ ነው።

አዳም የእግዚአብሔር ልጅ መባሉ የመጀመሪያው ሰው በመኾኑና
ያለ ሰው አባት በእግዚአብሔር በመፈጠሩ ነው።

70. በዮሐንስ ወንጌል ም.9 ቁ.39 ላይ "የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩ ግን
እንዲታወሩ ለፍርድ ወደዚህ ዓለም መጣሁ" ይልና በምዕራፍ 12 ቁጥር
47 ላይ ደግሞ "ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁም"
በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።

በመጀመሪያው ጥቅስ የማያዩ እንዲያዩና የሚያዩ ደግሞ
እንዲታወሩ የተባለው ኹሉን ነገር እናውቃለን፥ ከእኛ እኩል ዐዋቂ
የለም የሚሉት ጸሓፍትና ፈሪሳውያን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ሊገነ
ዘቡ አለመቻላቸውና ቀራጮችና ዓሣ አጥማጆች ግን የጌታ ተታዮች
መኾናቸውን የሚመለከት ነው። በጌታ ያመኑ ይፈረድላቸዋል፤ በጌታ
ያላመኑ ግን ይፈረድባቸዋል። (ማር. ም.16 ቁ.16) ይህም የኾነው ጌታ
ወደዚህ ዓለም መጥቶ በመገለጹ ነውና ለፍርድ ወደዚህ ዓለም መጣሁ
አለ። ኹለተኛው አባባል ደግሞ እኔ ዓለምን ለማዳን እንጂ በዓለም ላይ
ልፈርድ አልመጣሁም ካለ በኋላ ቃሌን ሰምቶ የማይጠብቀው ቢኖር
የሚፈርድበት ቃሌ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም በማለቱ ከመጀመሪያው
ጥቅስ ጋር ልዩነት የለውም። ጌታ ዓለሙን ለማዳን መምጣቱና ኹሉም
እንዲድን እንጂ ማንም እንዳይጠፋ መፈለጉ የታወቀ ቢኾንም አዳኝነቱን
የማንቀበል ከኾነ ግን የሚፈረድብን እንጂ የሚፈረድልን አይደለም።

የጌታም አመጣጥ ለሰዎች ኹሉ ፈተና ነበረ። ይህም ጻድቁ ስምዖን
ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም "ይህ ሕፃን ለብዙዎቹ የመጥፋትና
የመዳን ምክንያት ይኾናል" ብሏታል። (ሉቃ. ም.2 ቁ.34) ወደዚህ
ዓለም በመጣ ጊዜ የብርሃን ልጆች ከእርሱ ጋር ተባባሩ፤ የጨለማ ልጆች
ግን ጠላቱ ኾኑ። ለፍርድ አልመጣሁም ማለቱ እርሱ ባለፈው የመጣው
ለዓለም ቤዛ ኾኖ ዓለምን ለማዳን ሲኾን ለፍርድ ግን የሚመጣው በዳግም
ምጽአቱ ነው። በዚህም መሠረት ኹለቱ ጥቅሶች ርስ በርሳቸው
የሚቃረኑ አይደለም።



www.ethiopianorthodox.org

71. "አብ ከእኔ ይበልጣል።" (ዮሐ. ም.14 ቁ.28) በዚህ አነጋገሩ መድኀኒታችን ከአብ ያነሰ ክብር እንዳለው እርሱው ራሱ አረጋገጠ ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ።

አባቴ ከእኔ ይበልጣል ማለቱ በመለኮታዊ ክብር ከአባቱ ጋር እኩል ቢኾንም የፈጠረውን የሰውን ሥጋ ለብሶ በለበሰው ሥጋ ለሕማምና ለሞት የተዳረገ መኾኑን ለመግለጽ ነው እንጂ ከአብ የሚያንስ መኾኑን ለመግለጽ አይደለም።

አባቴ ከእኔ ይበልጣል ከማለቱ በፊት ብትወዱኝስ ኖሮ ወደ አብ እኼዳለሁ ስላችሁ ደስ ባላችሁ ነበር ብሎአቸዋል። ይህም ማለት እኔ በዚህ ዓለም ላይ እንደማነኛውም ተራ ሰው ኾኜ ባለሁበት ጊዜ ሕማም፥ ውርደትና ሞት የሚጠብቀኝ ሲኾን ወደ አባቴ በምኼድበት ጊዜ ግን ከአብ ቀኝ የመቀመጥ ክብር ይጠብቀኛል ማለቱ ነው። ኾኖም ግን ይህን ሕማም ተቀብሎ በመጨረሻ ለሞት የበቃው በገዛ ፈቃዱ እንጂ ማንም አስገድዶት አይደለም። (ዮሐ. ም.10 ቁ.17 – 18)

ለደቀ መዛሙርቱ ወደ አብ እኼዳለሁ ብሎ በነገራቸው ጊዜ ከእነርሱ መለየቱ ስላሳዘናቸው ሊያጽናናቸው ፈልጎ ምንም እንኳ በመለኮታዊ ክብሬ ከአብ ጋር እኩል ብኾን የሰውን ሥጋ በመልበሴና በለበስኩት ሥጋም ሕማምና ሞት የሚደርስብኝ ስለኾነ በዚህ ምክንያት አባቴ ከእኔ ይበልጣልና ከአብ ጋር ባለኝ ዘላለማዊው የክብር ዙፋኔ ላይ ኾኜ ወደምመለክበት ወደ አብ እኼዳለሁ ስላችሁ የምትወዱኝስ ከኾነ ልትደሰቱ እንጂ ልታዝኑ ባልተገባችሁም ነበር ብሎአቸዋል ማለት ነው።

ከአብ ጋር ያለውን እኩልነት በተለያዩ ጊዜያት የገለጸ ቢኾንም በተለየ ሕማማትንና ሞትን ለመቀበል ተዘጋጅቶ በነበረበት ዋዜማ "አባት ሆይ፥ ልጅህ እንዲያከብርህ ልጅህን አክብረው" ብሎ የእኩልነት ውል የሚደራደር መኾኑን በዮሐንስ ወንጌል ም.17 ቁ.1 እንመልከት።

72. "እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ አትክልተኛውም አባቴ ነው።» (ዮሐ. ም.15 ቁ.1) አትክልተኛው የወይኑን ግንድ ተክሎና ተንከባክቦ እንደሚያሳድገው አብም ወልድን ፈጥሮና ሥልጣንን ሰጥቶ ከፍ በማድረግ በአትክልተኛ እና በወይን ግንድ መካከል ባለው የክብር ልዩነት



መጠን የአብ ክብር ከወልድ ክብር ይበልጣል ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ።

እዚህ ላይ ጌታ ስለራሱ የወይን ግንድነትና ስለ አባቱ አትክልተኛነት በሚገልጽበት ጊዜ "እኔና አብ አንድ ነን" ያለውን የራሱን አባባል ለመቃረን ሳይኾን ምሳሌነቱ በመዝሙር 80 ቍ. 8 -15 ላይ እንደ ተገለጸው እስራኤላውያን ከምድረ ግብጽ ሲወጡ ፍሬ የሚያፈሩ የወይን ግንዶች እንዲኾኑ ታስቦ የነበረ መኾኑን የሚመለከት ነው። ይኹን እንጂ እነዚህ የወይን ግንዶች በትንቢተ ኢሳይያስ ም. 5 ቁ.1 – 7 እንደተገለጸው ወይን በማፍራት ፈንታ ሖምጣጣ ፍሬዎችን አፍርተዋል። ጌታ ግን በዚህ ዓለም ላይ እንደሰው በኖረባቸው ዘመናት ተገቢውን ፍሬ የማፍራት ምሳሌ ስለኾነ "እኔ እውነተኛው የወይን ግንድ ነኝ፤ አትክል ተኛውም አባቴ ነው" ካለ በኋላ በቁጥር 5 ላይ ደግሞ "እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ" ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ገልጾላቸዋል። ይህም ቅርንጫፍነት የሚያመለክተው አንድ የዛፍ ቅርንጫፍ በዛፉ ግንድ ላይ እንዳለ ካልቀጠለ በቀር ሊለመልምና ፍሬ ሊያፈራ እንደማይችል ኹሉ ማነኛውም ምእመን በጌታችንና በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ካልኾነ በቀር ሃይማኖታዊ ፍሬ ሊያፈራ አለመቻሉን ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ደሙን በወይን አማካይነት ስለሰጠን ራሱን በወይን ግንድ ምሳሌነት ገልጾልናል።

እንደሚታወቀው አብና ወልድ የሚለያዩት በመለኮታዊ ክብር በመበላለጥ ሳይኾን ወልድ ከሰው በመወለዱና አብ ግን ከሰው ባለመወለዱ ነው። ወልድ የሰውን ልጅ ከሰይጣን ተገዢነት ነጻ ለማውጣት ሰው መኾን ስለነበረበት መለኮትንና ትስብእትን ባዋሐደ ጊዜ ያልተጠፋፋ ተዋሕዶ በመኾኑ አምላኬ፥ አባቴ ከእኔ ይበልጣል፥ አባቴ አትክልተኛ እኔ የወይን ግንድ ነኝ፥ እኔ የአባቴን ፈቃድ እፈጽማለሁ ብሎ በየጊዜው የተናገራቸው የትሕትና አነጋገሮች ሊያስገርሙን አይገባም በትስብእቱ ለመለኮት ተገቢውን ክብር መስጠቱ ነውና። ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.2 ቁ.14 – 17 በሚነበበው ቃል እግዚአብሔር እንደተገለጸው ጌታ ሰው የኾነበት ምክንያት የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት ስለኾነ በኹሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው ተብሏል። (ጥያቄና መልስ ቍ:18፥ 27፥ 36፥ 48፥



www.ethiopianorthodox.org

57፥ 61፥ 63፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥ 102 እና በ1ኛው መጽ: ቍ:102፥ 104፥ 112 ይመለከቷል።

73. በዮሐንስ ወንጌል ም.16 ቁ.12 – 15 ላይ "ገና የምነግራችሁ ብዙ ነገር አለኝ፤ ነገር ግን አሁን ይከብዳችኋል። የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ኹሉ ይመራችኋል፤ ምክንያቱም እርሱ የሚናገረው የሰማውን እንጂ የራሱን አይደለም። እርሱ ወደፊት የሚኾኑትን ነገሮች ይነግራችኋል። የእኔ የኾነውን ወስዶ ስለሚነግራችሁ እኔን ያከብረኛል። የአብ የኾነው ኹሉ የእኔ ነው፤ የእኔ የኾነውን ወስዶ ይነግራችኋል ያልሁት ስለዚህ ነው" በሚለው አባባል አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ክብራቸውና ሥልጣናቸው በተዋረድ ነው የሚሉ ሰዎች እንደ ማስረጃ አድርገው ያቀርቡታል። ይህም ማለት በእነርሱ አባባል አብ ከኹሉ በላይ ነው፤ ወልድ ቀጥሎ ያለውን ደረጃ ይይዛል መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከወልድ ቀጥሎ ነው ይላሉ።

አብ ፥ወልድ፥መንፈስ ቅዱስ በስም፥ በአካልና በውስጣዊ ግብር ካልኾነ በቀር በመለኮታዊ ክብርና፥ በአፍአዊ ግብር አንድ ናቸው።

ጌታ ኢየሱስ በዚህ ዓለም ላይ በነበረበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ስለ ጌታ ትክክለኛ ማንነት ገና ሙሉ በሙሉ አልገባቸውም ነበር። ለምሳሌ የዘብዴዎስ ልጆች ማለት ያዕቆብና ዮሐንስ ጌታ በዚህ ዓለም ላይ ምድራዊ ንግሥ የሚነግሥ መስሎአቸው አንተ በምትነግሥበት ጊዜ ለአንዳችን በቀኝህ ለአንዳችን ደግሞ በግራህ የመቀመጥን ክብር ስጠን ብለው መለመናቸው የጌታን ማንነት ገና ያልተገነዘቡት መኾናቸውን ያመለክታል። እንዲሁም ጌታ በተያዘ ጊዜ ኹላቸውም ጥለውት መሸሻቸው ከማነኛውም ችግር ሲጠብቃቸው የሚችል አዳኛቸው መኾኑን ገና ያልተገነዘቡት መኾናቸውን ያሳያል። ስለዚህ ነው ጌታ የእኔ የኾነውን ወስዶ ስለሚነግራችሁ እኔን ያከብረኛል ያለው። ይህም ማለት የጌታን ማንነት መንፈስ ቅዱስ በዝርዝር ስለሚገልጥላቸው ከቀድሞው የበለጠ ጌታን ማክበር ይጀምራሉ ማለት ነው። የአብ የኾነው ኹሉ የእኔ ስለኾነ የእኔ የኾነውን ወስዶ ይነግራችኋል ማለቱ ስለዚህ ነው በሚልበት ጊዜ አፍአዊ ግብር ኹሉ የአብ፥ የወልድ፥ የመንፈስ ቅዱስ ነው ማለቱ ነው። የአብ የኾነው ኹሉ የወልድም ነው ከተባለ ያንኑ ደግሞ መንፈስ



ቅዱስ አምጥቶ ለጌታ ደቀ መዛሙርት የሚነግራቸው ከኾነ ያ እንግዲህ የመለኮታዊ አንድነት ዕውቀት መኾኑ ነው።

መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ርዳታውን ሲያበረክትላቸው የቱን ያኽል ቀድሞ ከነበሩበት ኹናቴ የተለዩ እንደሚኾኑ ሲያመለክታቸው ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በተነጋገረበት ጊዜ "እውነት እውነት እልሃለሁ አንተ ጎልማሳ ሳለህ ቀበቶህን በገዛ እጅህ ታጥቀህ ወደ ፈለግህበት ትኼድ ነበር፤ በሸመገልህ ጊዜ ግን አንተ እጆችህን ትዘረጋና ሌላ ሰው ያስታጥቅሃል፤ ወደማትፈልግበትም ይወስድሃል" ብሎታል (ዮሐ. ም.21 ቁ.18)

ይህን ኹሉ ድርጊት ነው የእኔ የኾነውን ወስዶ ይነግራችኋል ያልኩት የአብ የኾነው ኹሉ የእኔ ስለኾነ ነው በማለት የመለኮታዊ አንድነት ግብር መኾኑን የገለጠው።

ስለዚህ በዮሐንስ ወንጌል ም.16 ቁ.12 – 15 ያለው አባባል የመለኮታዊ አንድነትን ግብር ለማመልከት ነው እንጂ በሦስቱ አካላት መካከል የክብር ልዩነት ያለ መኾኑን ለማመልከት እንዳልኾነ ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

74. "የዘላለም ሕይወትም ብቻህን እውነተኛ አምላክ የኾንከውን አንተንና የላክኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው።" (ዮሐ. ም.17 ቁ.3) ብቻህን እውነተኛ አምላክ የኾንከውን አንተንና የላክኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን በሚልበት ጊዜ ራሱን ከአምላክነት በማግለል አምላክነት የአብ ብቻ መኾኑንና እርሱ ከአብ እንደሚያንስ ማረጋገጡ ነው ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ።

ቀደም ተብሎ በሌሎች አርእስት እንደተመለከተው መድኀኒታችን የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት መለኮትንና ትስብእትን ባዋሐደ ጊዜ ከኀጢአት በቀር የሰው ልጅ በሰብአዊ ተፈጥሮው የሚያ ልፍባቸውን እርምጃዎች ኹሉ ተከትሎ አልፎአል። (ዕብ. ም.2 ቁ.14 – 17፥ ም.4 ቁ.15) እንደ ሰው ጥቂት በጥቂት አድጓል፤ እንደ ሰው ተርቧል እንደ ሰው ተጠምቶአል፤ እንደ ሰው በልቶአል፥ ጠጥቶአል፤ እንደ ሰው ተኝቷል፤ እንደ ሰው ከእንቅልፉ ነቅቶአል፤ እንደ ሰው ወደ



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ጸሎት አቅርቧል፤ እንደ ሰው ሕማምና ሞት ደርሶበታል። በዚህ ኹሉ ጊዜ መለኮቱ አልተለየውም። ይህም አባባላችን መለኮት ታመመ ወይም መለኮት ሞተ ማለታችን አይደለም። አባባላችን ግን ግልጽ መኾን ያለበት ወልድ በሰውነቱ ሞተ ማለታችንና መለኮት ከትስብእት የተለየበት ጊዜ አለመኖሩን ነው።

ጌታ እንደ ሰው በሚጸልይበት ጊዜ ሰው ኹሉ የሚጸልየው ለእግዚአብሔር እንደመኾኑ እርሱም ለአባቱ አንተ ብቻ እውነተኛ አምላክ ነህ ሲል ጸለየ። የዚህም ጸሎት ዋና ዐላማ ጣዖት አምልኮትን ለማውገዝ ነው። እንደ ሰው አምላኬ ወይም እግዚአብሔር ብሎ ካልጸለየ በእርሱ ዘንድ ትስብእት የለም፤ ወይም መለኮት ትስብእትን ውጦ አጥፍቶታል፤ ወይም መለኮትና ትስብእት ተቀላቅለዋል በሚለው በአውጣኬ ክሕደት እንደማመን ይቈጠርብናል።

በሌላ በኩል ደግሞ በቅዱሳት መጻሕፍት ልዩ ልዩ ክፍሎች አንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር አብ ሌላ ጊዜ ለእግዚአብሔር ወልድ በሌላ ጊዜ ደግሞ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ የአምላክነት ክብር ተሰጥቶ የሚነገርበት ምክንያት በመለኮታዊው ሥልጣን አንድ ስለኾኑ ነው።

በዮሐንስ ወንጌል ም.17 ቁ.3 እግዚአብሔር አብ ብቻውን እውነተኛ አምላክ እንደኾነ ተገልጾአል። በመልእክተ ይሁዳ ቁ.25 ላይ እግዚአብሔር ወልድ ብቸኛ አምላክ ነው ተብሏል። በማቴዎስ ወንጌል ም.12 ቁ.32 ላይ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተደረገ ስድብ ብቻ ምሕረት እንደማይደረግለት ተገልጾአል። ስለዚህ ተመሳሳይ ጥቅሶች በሚያጋጥሙን ጊዜ ሊያስናክሉን አይገባም። (ጥያቄና መልስ ቁ. 8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥ 57፥ 61፥ 63፥ 72፥ 75፥ 84፥ 89፥ 90፥ 91፥ 92፥ 101 እና በአንደኛው መጽሐፍ ቁ.102፥ 104፥ 112) ይመለከቷል።

75. በዮሐንስ ወንጌል ም.20 ቁ.17 ላይ "ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ" ይልና በሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ም.9 ቁ.5 ላይ "ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ፤ እርሱም በኹሉ በላይ ኾኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው" በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል።



አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር ኹለት የተለያዩ ኹኔታዎች ሲኖሩት ኹለት ዐይነት ስሞች ይኖሩታል። ሰው ነፍስና ሥጋ የተባሉ ኹለት ስሞች ያሉት ቢኾንም ኹለቱ ግን በሕይወት ዘመኑ አብረው እንጂ ተለያይተው አይኖሩም። በዚሁም ዐይነት መድኀኒታችን መለኮትና ትስብእት ያለው እንደመኾኑ አንዳንድ ጊዜ እንደ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንደ ሰው ኾኖ ይናገራል ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ያለውም እንደ ሰውነቱ ነው። (ጥያቄና መልስ ቁ.8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥ 57 ፥ 61፥ 63፥ 72፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥ 102 እና በአንደኛው መጽሐፍ ቁ.102፥ 104፥ 112) ይመለከቷል።

## የአራቱ ወንጌሎች ስምምነትና ልዩነት

ቅዱሳት መጻሕፍት በሕግ፥ በታሪክ፥ በጥበብና በትንቢት መጻሕፍት የሚከፋፈሉ ኾነው በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የሕግ መጻሕፍት የሚባሉት አራቱ ወንጌሎች ናቸው። የወንጌል ጸሐፊዎችም በሚጽፉበት ጊዜ ስሕተት እንዳያደርጉ መንፈስ ቅዱስ የጠበቃቸው መኾኑን የምናምን ብንኾንም እንኳን እያንዳንዱ ጸሐፊ የራሱ በኾነ የአጻጻፍ ዘዴ እንዲጽፍ ተወው እንጂ የሚጽፈውን ጉዳይ ኹሉ መንፈስ ቅዱስ ቃል በቃል ያነበበለት አይደለም። በዚህም መሠረት አራቱ ወንጌላውያን ስለአንድ ጉዳይ በሚጽፉበት ጊዜ በተለያየ አቀራረብ አቅርበውታል። ይህም ብቻ ሳይኾን አራታቸውም ያቀረቡአቸው ትምህርቶች ይኑሩ እንጂ ብዙዎቹ የወንጌል ሕጎች ከአራቱ በሦስቱ ብቻ ወይም በኹለቱ ብቻ፥ ወይም ደግሞ በአንዳቸው ብቻ የቀረቡ ናቸው። እነዚህንም ልዩ ልዩ አቀራረቦች በዝርዝር ለማሳየት እንዲቻል በዐሥር ክፍሎች አከፋፍሎ ማቅረብ የተሻለ ዘዴ ኾኖ ተገኘ።

የመጀመሪያው ክፍል አራቱም ወንጌሎች ተስማም ተውባቸው የቀረቡ ትምህርቶች

1/ ጌታ ወደገሊላ ኼዶ ማስተማሩ:- (ማቴ. ም.4 ቁ:12፥ ማር. ም.1 ቁ.14፥ ዮሐ.ም.4 ቁ.1 – 3)



www.ethiopianorthodox.org

2/ የጌታ በንጉሣዊ ግርማ ወደ ኢየሩሳሌም መግባት (ማቴ.ም.21 ቁ.1 – 17 ፥ ማር.ም.11 ቁ.1 – 11፥ ሉቃ.ም.19 ቁ.29 – 40፥ ዮሐ.ም.12 ቁ.12 – 19)

3/ ይሁዳ አሳልፎ የሚሰጠው መኾኑን ጌታ የተነበየው ትንቢt (ማቴ.ም.26 ቁ.21 – 25፥ ማር.ም.14 ቁ.18 – 21፥ ሉቃ.ም.22 ቁ.21 – 23፥ ዮሐ.ም.13 ቁ.21 – 30)

4/ ጌታ ስለጴጥሮስ ክሕደት የተናገረው ትንቢt (ማቴ.ም.26 ቁ.31 – 35፥ ማር.ም.14 ቁ.27 – 31፥ ሉቃ.ም.22 ቁ.31 – 34፥ ዮሐ.ም.13 ቁ.36 – 38)

5/ ይሁዳ አይሁድን እየመራ ጌታ ወደነበረበት ወደጌቴሴማኒ ያትክልት ቦታ መምጣቱ፥ የጌታ መያዝና በቀያፋ ቤትም እንዳለ የጴጥሮስ መካድ (ማቴ.ም.26 ቁ.47 – 75፥ ማር.ም.14 ቁ.43 – 72 ሉቃ.ም.22 ቁ.47 – 62፥ ዮሐ.ም.18 ቁ2 – 27)

6/ በሮማ ዊው ገዢ ቤት በጌታ ላይ የተፈረደው ፍርድ፥ (ማቴ.ም.27 ቁ.1 – 14፥ ማር.ም.15 ቁ.1 – 5፥ ሉቃ.ም.23 ቁ.1 – 5፥ ዮሐ.ም.18 ቁ.28 – 38)

7/ ጌታን ንጹሕ ኾኖ ስላገኘው ጲላጦስ ሊፈታው ቢፈታው ቢፈልግም አይሁድ ግን ሌላ ወንጀለኛ የኾነ ሰው እንዲፈታላቸው መጠየቃቸው /ማቴ.ም.27 ቁ.15 – 26፥ ማር.ም.15 ቁ:6 — 15፥ ሉቃ.ም.23 ቁ.13 — 25፥ ዮሐ.ም.18 ቁ.29 — 40)

8/ አይሁድ ጌታን ወደሚሰቅሉበት ቦታ መውሰዳቸው (ማቴ. ም.27 ቁ.1 – 38፥ ማር.ም.15 ቁ.29 – 37፥ ሉቃ.ም.23 ቁ.26 – 38፥ ዮሐ.ም.19 ቁ.16 – 24)

9/ የጌታ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ መሞትና ወ ርዶ መቀበር(ማቴ.ም.27 ቁ.45 – 61፥ ማር.ም.15 ቁ.33 – 47፥ ሉቃ.ም.23 ቁ.44 – 56፥ ዮሐ.ም.19 ቁ.27 – 42)



10/ የማርያም መግደላዊት በእሁድ ማለዳ ወደጌታ መቃብር መኼድ (ማቴ.ም.28 ቁ.1፥ ማር.ም.16 ቁ.1 – 2፥ ሉቃ.ም.24 ቁ.1፥ (ዮሐ.ም.20 ቁ.1 እና 2)

ኹለተኛው ክፍ ሦስቱ ወንጌሎች ማለት ማቴዎስ፡ ማርቆስና ሉቃስ ያቀረቡአቸው ትምህርቶች

1/ የዮሐንስ መጥምቁ በዮርዳኖስ በረሓ ማስተማር፥ የጌታ በዮሐንስ መጠመቅና በዚያን ጊዜ የተፈጸመው ተአምት ማለት የአብ ከሰማይ ምስክርነትና የመንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መውረድ (ማቴ.ም.3 ቁ.1 – 17፥ ማር.ም.1 ቁ.4 : 11፥ ሉቃ.ም.3 ቁ.2 — 22)

2/ የጌታ በሰይጣን መፈተን (ማቴ.ም.4 ቁ.1 – 11፥ ማር.ም.1 ቁ.12 – 13፥ ሉቃ.ም.4 ቁ.1 – 13)

3/ የጴጥሮስና የእንድርያስ፥ እንዲሁም የያዕቆብና የዮሐንስ ለደቀመዛሙርትነት በጌታ መጠራትና በገሊላም ማስተማሩ:- (ማቴ.ም.4 ቁ.18 – 25፥ ማር.ም.1 ቁ.16 – 20፥ ሉቃ.ም.5 ቁ.1 – 20)

4/ የጴጥሮስ አማትና የሌሎችም ከሕመማቸው መዳው (ማቴ.ም.8 ቁ.14: 17፥ ማር.ም.1 ቁ.29 – 34፥ ሉቃ.ም.4 ቁ.38 – 41)

5/ በገሊላ የለምጻሙ መንጻትና በቅፍርናሆም የሽባው መፈወስ (ማቴ.ም.8 ቁ.2 – 13፥ ማር.ም.1 ቁ.40 – 45፥ ም.2 ቁ.1 – 12፥ ሉቃ.ም.5 ቁ.12 – 14፥ ም.5 ቁ.17 – 26)

6/ የማቴዎስ ለደቀ መዝሙርነት መጠራትና ለጌታ ግብር የደገሰው ግብዣ:- (ማቴ.ም.9 ቁ.9 – 13፥ ማር.ም.2 ቁ.14 – 17፥ ሉቃ.ም.5 ቁ.27 — 32)

7/ በቅዳሜ ቀን የደቀ መዛሙርቱ እሸት መቅጠፍና የጌታም እጁ የሰለለችውን ሰው መፈወስ ( ሉቃ.ም.6ቁ.1–11)



www.ethiopianorthodox.org

8/ የዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት ለደቀ መዛሙርትነት መጠራት:6 (ማቴ.ም.10 ቁ.2 – 4፥ ማር.ም.3 ቁ.13 – 19፥ ሉቃ.ም.6 ቁ.12 : 16)

9/ አይሁድ በጌታ ላይ የሰነዘሩት ጽርፈት፥ እርሱም ሰይጣን ሰይጣንን የማያስወጣ መኾኑንና እንድ መንግሥት ደግሞ እርስ በርሱ ከተከፋፈለ እንደሚወድቅና አንድም ቤት እርስ በርሱ ከተለያየ ጸንቶ ሊኖር የማይችል መኾኑን ገለጸላቸው (ማቴ.ም.12 ቁ.22 – 32፥ ማር.ም.3 ቁ.22 – 30፥ ሉቃ.ም.11 ቁ.14 – 23)

10/ የጌታ ወንድሞች ደቀ መዛሙርቱ ናቸው። (ማቴ.ም.12 ቁ.46 – 50፥ ማር.ም.3 ቁ.31 – 35፥ ሉቃ.ም.8 ቁ.19 – 21)

11/ የዘሪውና የዘሩ ምሳሌ:- (ማቴ.ም.13 ቁ.1 – 23፥ ማር.ም.4 ቁ.1 – 20፥ ሉቃ.ም.8 ቁ.4 – 15)

12/ የጌታ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በጀልባ ተሳፍሮ መኼድ፥ የማዕበል መነሣትና ጌታም ማዕበሉን ጸጥ ማሰኘቱ :- (ማቴ.ም.8 ቁ.18 – 27፥ ማር.ም.4 ቁ.35 – 41፥ ሉቃ.ም.8 ቁ.22 – 25)

13/ ጌታ ኹለት ዕብዶችን በጌርጌሴኖን መፈወሱ:- (ማቴ.ም.8 ቁ.28 – 34(፥ አንድ ዕብድ ብቻ (ማር.ም.5 ቁ.1 – 20፥ ሉቃ.ም.8 ቁ/26 – 40)

14/ የሽባው ሰው ሥጋና ነፍስ በጌታ መፈወሱ (ማቴ.ም.9 ቁ.2 – 8፥ ማር.ም.2 ቁ.3 – 12፥ ሉቃ.ም.5 ቁ.18 – 26)

15/ ኢያኢሮስ የተባለው የምኵራብ አለቃ ልጅ ከሞት መነሣትና ደም ይወርዳት የነበረችው ሴት መፈወሱ (ማቴ.ም.9 ቁ.18 – 26፥ ማር.ም.5 ቁ.22 – 43፥ ሉቃ.ም.8 ቁ.41 – 56)

16/ የጌታ በገሊላ መዘዋወርና ደቀ መዛሙርቱን በማስተማር ሥራ ማሐልጠኑ (ማቴ.ም.9 ቁ.35 – 38፥ ማር.ም.6 ቁ.6 – 13፥ ሉቃ.ም.9 ቁ.1 – 6)



17/ ሄሮድስ ስለጌታ በሰማ ጊዜ ራሱን አስቆርጦ ያስገደለው መጥምቁ ዮሐንስ ከሞት የተነሣ መሰለው። (ማቴ.ም.14 ቁ.1 – 12፥ ማር.ም.16 ቁ.14 – 29 ሉቃ.ም.9 ቁ.7 – 9)

18/ የጴጥሮስ እምነት ምስክርነት (ማቴ.ም.16 ቁ.13 – 20፥ ማር.ም.8 ቁ.27 – 30፥ ሉቃ.ም.9 ቁ.18 – 21)

ስለሕማሙ፥ ስለሞቱና በሦስተኛው ቀን የሚነሣ ስለመኾኑ ጌታ የተናገረው ትንቢት (ማቴ.ም.16 ቁ.21 – 28፥ ም.17 ቁ.22 – 23፥ ም.20 ቁ.17 – 19፥ ማር.ም.8 ቁ.31 – 38፥ ም.9 ቁ.30 – 32፥ ም.10 ቁ.32 – 34፥ ሉቃ.ም.9 ቁ.22 – 44፥ ም.18 ቁ.31 – 34)

20/ በተራራ ላይ የጌታ ክብር መገለጽ:- (ማቴ.ም.17 ቁ.1 – 8፥ ማር.ም.9 ቁ.2 – 8፥ ሉቃ.ም.9 ቁ.28 – 36)

21/ ደቀ መዛሙርቱ በመበላለጥ ጉዳይ የሚከራከሩ መኾናቸውን በተረዳ ጊዜ ጌታ ትሕትናን ያስተማራቸው መኾኑ:- (ማቴ.ም.18 ቁ.1 – 5፥ ማር.ም.9 ቁ.33 – 37፥ ሉቃ.ም.9 ቁ.46 – 48)

22/ የክርስትና ጋብቻ፥ መፋታት የተከለከለ መኾኑ:- (ማቴ. ም.19 ቁ.3 – 12፥ ማር. ም.10 ቁ.2 – 12፥ ሉቃ. ም.16 ቁ.18)

23/ ሕፃናት ወደጌታ ቀርበው የባረካቸው መኾኑ:- (ማቴ. ም.19 ቁ.13 – 15፥ ማር. ም.10 ቁ.13 – 16 ሉቃ. ም.18 ቁ.15 – 17)

24/ ስለድኅነት የሃብታሙ ወጣት ጥያቄ:- (Lv. N.19 f.16 – 30፥ ማር. ም.10 ቁ.17 – 31፥ ሉቃ. ም.18 ቁ.18 – 30)

25/ ጌታ የኹለት ዕውሮችን ዓይን ማብራቱ:- (ማቴ. ም.20 ቁ.29 – 34)፥ የአንድ ዕውር ዓይን ብቻ /ማር. ም.10 ቁ:46 – 52፥ ሉቃ. ም.18 f.35 – 43)

26/ ጌታ ከቤተ መቅደስ ገዢና ሻጮችን ማባረሩ:- (ማቴ. ም.21 ቁ.12 – 13.: ማር. ም.11 ቁ.15፥ ሉቃ. ም.19 ቁ.45 – 46)



www.ethiopianorthodox.org

27/ የአይሁድ ካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ጌታ የሚሠራቸው ሥራዎች በምን ሥልጣን እንደኾነ መጠየቃቸዉ (ማቴ. ም.21 ቁ.23 – 27፥ ማር. ም.11 ቁ.27 – 33፥ ሉቃ. ም.20 ቁ.1 – 8)

28/ የወይን አትክልት ገበሬዎች ምሳሌ:- (ማቴ.ም.21 ቁ.33 – 46፥ ማር. ም.12 ሉቃ. ም.20 ቁ.9 – 19)

29/ ስለግብር መክፈል የቀረበ ጥያቄ:- (ማቴ. ም.22 ቁ.15 – 22፥ ማር.ም.12 ቁ.13 – 17፥ ሉቃ. ም.20 ቁ.20 – 26)

30/ ስለትንሣኤ ሙታን (ማቴ. ም.22 ቁ.23 – 32፥ ማር. ም.12 ቁ.18 – 27፥ ሉቃ. ም.20 ቁ.27 – 40)

31/ ስለመሲሕ የቀረበ ጥያቄ:- (ማቴ. ም.22 ቁ.41 – 46፥ ማር. ም.12 ቁ.35 – 37፥ ሉቃ. ም.20 ቁ.41 – 43)

32/ ስለጸሐፍትና ፈሪሳውያን ተንኰል ለደቀ መዛሙርቱ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ:- (ማቴ. ም.23 ቁ.1 – 36፥ ማር. ም.12 ቁ.38 – 40፥ ሉቃ. ም.20 ቁ.46 – 47፥ ም.11 ቁ.39 – 52)

33/ ስለኢየሩሳሌም መፍረስ የጌታ ትንቢት (ማቴ. ም.24 ቁ.1 – 2፥ ማር. ም.13 ቁ.1 – 2፥ ሉቃ. ም.21 ቁ.5 – 7)

34/ ጌታን ለመግደል የአይሁድ አለቆች ማሴራቸውና የአስቆሮቱ ይሁዳም በአድማው ውስጥ መግባቱ:- (ማቴ. ም.26 ቁ.3 – 4፥ 14 – 15፥ ማር. ም.14 ቁ.1፡ 10፥ 11፥ ሉቃ. ም.22 ቁ.2 – 6)

35/ የፋሲካ በዐል ዝግጅት የደቀ መዛሙርቱም ከጌታ ጋር የፋሲካን በዐል ምግብ መብላትና እንዲሁም የምሥጢረ ቁርባን ምሥረታ:- (ማቴ. ም.26 ቁ.17 – 30፥ ማር. ም.14 ቁ.12 – 26፥ ሉቃ. ም.22 ቁ.7 – 20)



36/ በጌታ ሞት ጊዜ የቤተ መቅደሱ መጋረጃ መቀደድ፡ ነፍሱን በሚሰጥበት ጊዜ በከፍተኛ ድምፅ መጮኹ፡ ከወታደሮቹም አንዳንዶቹ በጌታ መለኮታዊ ክብር ማመናቸውና በሩቅ ቆመው አጠገብ ሴቶች የነበሩ ሐቅናቸዉ (ማቴ. ም.27 ቁ.51 – 56፡ ማር. ም.15 ቁ.38 – 41፡ ሉቃ. ም.23 ቁ.45 – 49)

37/ በጌታ መቃብር አጠገብ መላእክት ለሴቶች ተገልጸው ስለጌታ ትንሣኤ መልካም ዜና ማብሠራቸዉ (ማቴ. ም.28 ቁ.5 – 7፥ ሉቃ. ም.24 ቁ.1 – 8)

ሦስተኛው ክፍል ሦስቱ ወንጌሎች ማለት ማቴዎስ፡ ሉቃስና ዮሐንስ ያቀረቡአቸው ትምህርቶች

1/ ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ይቈረጣል (ማቴ. ም.3 ቁ.10፥ ም.7 ቁ.19፥ ሉቃ. ም.13 ቁ.7 – 9፥ ዮሐ. ም.15 ቁ.6)

2/ ስለመከሩና ስለሠራተኛው ምሳሌ:- (ማቴ. ም.9 ቁ.37፥ ሉቃ. ም.10 ቁ.2፥ ዮሐ. ም.4 ቁ.35)

3/ ተማሪ ከአስተማሪው የማይበልጥ መኾኑ:- (ማቴ. ም.10 ቁ.24፥ ሉቃ. ም.6 ቁ.40፥ ዮሐ.ም.13 ቁ.16 ም.15 ቁ.20)

4/ የጠፋው በግ ምሳሌ:- (ማቴ. ም.18 ቁ.12፥ ሉቃ. ም.15 ቁ.4 – 6፥ ዮሐ. ም.10 ቁ.11 – 18)

5/ ጌታ ሊያገለግል እንጂ ሊገለገል አለመምጣቱ ለአለቆች ምሳሌ ኾኗል (ማቴ. ም.20 ቁ.28፥ ሉቃ. ም.22 ቁ.27፡ ዮሐ. ም.13 ቁ.4 እና 14)

6/ በአይሁድ አስተያየት ጌታ እንደ ነቢይ ነበር (ማቴ. ም.21 ቁ.11 እና 46፥ ሉቃ. ም.7 ቁ.16፥ ዮሐ. ም.6 ቁ.14፡ ም.7 ቁ.40)

አራተኛው ክፍል ሦስት ወንጌሎች ማለት ማቴዎስ፡ ማርቆስና ዮሐንስ ያቀረቡት ትምህርት



www.ethiopianorthodox.org

1/ ጌታ በባሕር ውሃ ላይ መራመዱ:- (ማቴ. ም.14 ቁ.22 – 36፥ ማር. ም.6 ቁ.45 – 51፥ ዮሐና ም.6 ቁ.16 – 21)

2/ ጲላጦስ ጌታን ማስገረፉና ወታደሮቹም ያፌዙበት መኾኑ:- (ማቴ. ም.27 ቁ.26 – 30፥ ማር. ም.15 ቁ.15 – 19፥ ዮሐ. ም.19 ቁ.1 – 3)

አምስተኛው ክፍል ኹለት ወንጌሎች ማለት ማቴዎስና ማርቆስ ያቀረቡአቸው ትምህርቶች

1/ ስለአበቶች ወደ (ማቴ. ም.15 ቁ.1 – 20፥ ማር.ም.7 ቁ.1 – 23)

2/ የከነዓናዊትዋ ሴት እምነት (ማቴ. ም.15 ቁ.21 – 28፥ ማር. ም.7 ቁ.24 – 30)

3/ ሴቶችና ልጆች ሳይቈጠሩ በሰባት ዳቦና በጥቂት ዓሣ ጌታ አራት ሺ ሰዎችን መግቦ ሰባት መሶብ መትረፉ:- (ማቴ. ም.15 ቁ.32 – 39፥ ማር. ም.8 ቁ.1 – 9)

4/ ከአንድ ሚስት በቀር ማግባት እንደማይገባ ጌታ ያስተማረው ትምህርት (ማቴ. ም.19 ቁ.3 – 12፥ ማር. ም.10 ቁ.2 – 12)

5/ የዘብዴዎስ ልጆች ልመና:- (ማቴ. ም.20 ቁ.20 – 28፥ ማር. ም.10 ቁ.35 – 45)

ስድስተኛው ክፍል ኹለት ወንጌሎች ማለት ማቴዎስና ሉቃስ ያቀረቡአቸው ትምህርቶች

1/ የጌታ ሥጋዊ ትውልድ በድንግል ማርያምና በእጮኛዋ በዮሴፍ የዘር ሐረግ ተዘርዝሮ መታየቱ (ማቴ. ም.1 ቁ.1 – 16፥ ሉቃ. ም.3 ቁ.23 – 38)



2/ የጌታ በቤተልሔም መወለድ (ማቴ. ም.2 ቁ.1፥ ሉቃ. ም.2 ቁ.4 – 7)

3/ የተራራው ላይ ስብከት (ማቴ. ም.5 – 7፥ ሉቃ. ም.6 ቁ.20 – 49)

4/ የመቶ አለቃው አገልጋይ መፈወስ:- (ማቴ. ም.8 ቁ.5 – 13፥ ሉቃ. ም.7 ቁ.1 – 10)

5/ መጥምቁ ዮሐንስ ኹለት ደቀ መዛሙርቱን ወደ ጌታ መላኩ:- (ማቴ. ም.11 ቁ.2 – 19፥ ሉቃ. ም.7 ቁ.18 – 35)

ሰባተኛው ክፍል ኹለት ወንጌሎች ማለት ማቴዎስና ዮሐንስ ያቀረቡአቸው ትምህርቶች

1/ ጴጥሮስ የሊቀ ካህናቱን አሽከር ጆሮ በሰይፍ ስለቈረጠ ጌታ የገሠጸው መኾኑ:- (ማቴ. ም.26 ቁ.52፥ ዮሐ. ም.18 ቁ.11)

2/ በገሊላ አካባቢ የጌታ ለደቀ መዛሙርቱ መገለጹ:- (ማቴ. ም.28 ቁ.16፥ ዮሐ. ም.21 ቁ.1)

ስምንተኛው ክፍል ኹለት ወንጌሎች ማለት ማርቆስና ሉቃስ ያቀረቡአቸው ትምህርቶች

1/ የመበለቲቱ ስጦታ:- (ማር. ም.12 ቁ.41 – 44፥ ሉቃ. ም.21 ቁ.1 – 4)

2/ በጉዞ ላይ ለነበሩት ደቀ መዛሙርት የጌታ መገለጽ (ማር. ም.16 ቁ.12፥ ሉቃ. ም.24 ቁ.31)

ዘጠነኛው ክፍል: ኹለት ወንጌሎች ማለት ሉቃስና ዮሐንስ ያቀረቡአቸው ትምህርቶች



www.ethiopianorthodox.org

1/ ከሕማሙና ከሞቱ ጥቂት ቀኖች በፊት የጌታ ወደ ኢየሩሳሌም መኼድ:- (ሉቃ.ም.9 ቁ.51 – 56፥ ዮሐ. ም.7 ቁ.2 – 10)

2/ እሁድ በማለዳ ጴጥሮስ እየሮጠ ወደጌታ መቃብር መኼ (ሉቃ. ም.24 ቁ.12፥ ዮሐ. ም.20 ቁ.3 – 10)

3/ ጌታ ከሞት የተነሣው እርሱ ራሱ መኾኑን ሊያረጋግጥላቸው ለደቀ መዛሙርቱ እጁንና እግሩን ማሳየቱ:- (ሉቃ. ም.24 ቁ.40፥ ዮሐ. ም.20 ቁ.20)

አሥረኛው ክፍል እያንዳንዱ ወንጌላዊ ከሌሎቹ ወንጌላውያን ጓደኞቹ ተለይቶ እርሱ ብቻ ያቀረባቸው ትምህርቶc

1/ ማቴዎስ (አንደኛ) የምሥራቅ ጠቢባን (ሰብአ ሰገል) መጥተው ለጌታ ስጦታ ማቅረባቸው፥ የድንግል ማርያምና የዮሴፍ ሕፃን ኢየሱስን ይዘው ወደ ግብጽ ስደት፥ ሄሮድስ የቤተልሔምን ሕፃናት ማስገደሉ (ም.2) (ኹለተኛ) የእንክርዳድ ምሳሌ (ም.13 ቁ.24 : 30) (ሦስተኛ) የአምስት ብልኆችና የአምስት ሞኞች ደናግል ምሳሌ (ም.25 ቁ.1 –13) (አራተኛ) ስለጲላጦስ ሚስት ሕልም (ም.27 ቁ.19) (አምስተኛ) ሞተው ከነበሩ ቅዱሳን መካከል በጌታ ሞት ጊዜ ተነሥተው ከትንሣኤው በኋላ ለብዙዎች መታየታቸው (ም.27 ቁ.52 – 53) (ስድስተኛ) የአይሁድ አለቆች ከተመካከሩ በኋላ ለወታደሮች ጉቦ በመስጠት ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት እኛ ተኝተን ሳለን ሰርቀው ወሰዱት ብለው እንዲያወሩ ነገሩአቸው (ም.28 ቁ.12 – 13)

2/ ማርቆስ (አንደኛ) የዘር ምሳሌ (ም.4 ቁ.26) (ኹለተኛ) ድዳና ደንቆሮ የነበረው ሰው ስለመፈወሱ (ም.7 ቁ.31 – 35) (ሦስተኛ) በቤተ ሳይዳ አንድ ዕውር መፈወሱ:- (ም.8 ቁ.22 – 2?) (አራተኛ) አምኖ የሚጠመቅ ይድናል፤ የማያምን ግን ይፈረድበታል (ም.16 ቁ.16)

3/ ሉቃስ (አንደኛ) የመጥምቁ ዮሐንስና የጌታ መፀነስና መወለድ ታሪክ፥ እንዲሁም ጌታ በጥበብ ማደጉና ለወላጆቹም የነበረው ታዛዥነት (ም.1 እና 2) (ኹለተኛ)( የጌታ ተአምራዊ ድርጊቶች ሲኾኑ እነርሱም ናይን በምትባል ከተማ የመበለቲቱን ልጅ ከሞት ማስነሣት (ም.7 ቁ.11 – 17)፥ የአንዲት ሴት ከጉብጠት በሽታ መ..ወስ (ም.13 ቁ.10 – 17)፥ ዐሥር ለምጻሞች መፈወሱ (ም.17 ቁ.11 – 19)፡ ከትንሣኤው በኋላ ኢማሁስ ወደምትባል መንደር ይጓዙ ለነበሩ ኹለት ደቀ መዛሙርቱ መገለጹና እንደገና ከዓይናቸው መሠወሩ (ም.24 ቁ.13 – 35)፥ (ሦስተኛ) ምሳሌዎc ርኅሩኅ ሣምራዊ (ም.10 ቁ.30 – 37)፡ የሀብታሙ ሰው ሞኝነt (ም.12 ቁ.16 – 20)፡ የማታፈራ የበለስ ዛፍ (ም.13 ቁ.6 – 9)፥ ጠፍቶ የተገኘው ልጅ (ም.15 ቁ.11 – 32)፥ ብልኍ መጋቢ:- (ም.16 ቁ.1 – 8) ሀብታሙ ሰውና ድኻው አልዓዛር (ም.16 ቁ.19 – 31) ድኻዋ መበለትና ዓመፀኛው ዳኛ:- (ም.18 ቁ.1 – 5)፥ ትዕቢተኛው ፈሪሳዊና ትሑቱ ቀራጭ (ም.18 ቁ.9 – 10) (አራተኛ) ከሞቱ በፊት ወደሄሮድስ መወሰዱ፥ ለሚሰቅሉት ሰዎች መጸለዩና አብሮ ተሰቅሎ የነበረውን ወንበዴ ንስሐ መቀበሉ:- (ም.23)

4/ ዮሐንስ ለአንዳንድ ደቀ መዛሙርቱ መጥምቁ ዮሐንስ ጌታን እንዲከተሉ ያመለከታቸው መኾኑ:- (ም.1 ቁ.37 እና 40) በቃና ዘገሊላ ሠርግ ላይ ውሃውን ወደወይን ጠጅነት መለወጡ (ም.3 ቁ.1 – 19)፡ ጌታና አንዲት ሣምራዊት ሴት (ም.4 ቁ.1 – 42)፡ የሹሙ ልጅ መፈወስ (ም.4 ቁ.46 – 54)፥ በቤተሳይዳ አንድ ሽባ ሰው መፈወሱና ስለመለኮታዊ ክብሩም ለፈሪሳውያን ያደረገው ገለጻ (ም.5)፡ ለደቀ መዛሙርቱና ለሌሎችም ስለምሥጢረ ቁርባን ያደረገው ገለጻ (ም.6)፡ ዕውር ኾኖ የተወለደውን ሰው መፈወሱ (ም.9)፥ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣቱ (ም.11 ቁ.1 – 40)፥ በሕማሙና በሞቱ ዋዜማ ለደቀ መዛሙርቱ ያደረገው ንግግርና የጸለየው ጸሎt (ም.14 – 17)፥ በገሊላ ባሕር አጠገብ ለደቀ መዛሙርቱ መገለጹና ትወደኛለህን? በማለት ጴጥ ሮስን ሦስት ጊዜ መላልሶ መጠየቁና በጎቼን ጠብቅ ብሎ ማዘዙ (ም.21)

የቅዱሳት መጻሕፍት ደሐፊዎች መንፈስ ቅዱስ ከስሕተት የሚ ጠብቃቸው ቢኾንም እያንዳንዳቸው በአላቸው ያቀራረብ ዘዴ አቀረቡት እንጂ መንፈስ ቅዱስ ቃል በቃል አልመራቸውም። በዚህም መሠረት በጌታ ጊዜ የተደረጉትን ድርጊቶች ሲመዘግቡ አራቱም የመዘገቡአቸው፥ ሦስቱ ብቻ፥ ወይም ኹለቱ ብቻ የመዘገቡአቸውና እንዲያውም አንዳ ንዳቸው ብቻ የመዘገቡአቸው ጉዳዮች መኖራቸውን ከላይ በዝርዝር ተመልክተናል። አንድን ድርጊት ከአንድ ሰው በላይ ማለት ኹለት





www.ethiopianorthodox.org

ወይም ከኹለት የበለጡ ሰዎች በየበኩላቸው ሲመዘግቡት የተለያየ አቀራረብ የሚኖራቸው እያንዳንዱ ሰው የተለያየ አስተሳሰብ ስላለው ነው። በዚህም ምክንያት አራቱ ወንጌላውያን በጌታ ዘመን ስለተደረጉት ድርጊቶች አቀራረባቸው የተለያየ በሚመስለን ጊዜ ሊያስገርመን አይገባም።

## የሐዋርያት ሥራ

ይህ መጽሐፍ በወንጌላዊው ሉቃስ ተጽፎ 28 ምዕራፎች ያሉትና በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፋፈለ ነው።

የመጀመሪያው ክፍል ምዕራፍ 1 ሲኾን ከጌታ ዕርገት በኋላ የደቀ መዛሙርቱ በአንድ ቦታ መሰባሰብና በይሁዳ ምትክ ማትያስን የመምረጣቸው ታሪክ ይገኝበታል።

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 2 እስከ ምዕራፍ 7 ድረስ ሲኾን በውስጡም መንፈስ ቅዱስን ስለመቀበላቸው፥ ሦስት ሺ ነፍስ ወደ ክርስትና እምነት መግባቱ፥ በጴጥሮስና በዮሐንስ ስለተፈጸመው ተአምር፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመስበካቸው መታሰራቸውና ከእስር ቤትም የእግዚአብሔር መልአክ ያስወጣቸው መኾኑ፥ ወደ አማንያን ማኅበር የሚገባው ሕዝብ እያደገ መኼዱና እንዲሁም የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ሰማዕት እስጢፋኖስ የመገደሉ ታሪክ ይገኝበታል።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 8 እስከ ምዕራፍ 12 ድረስ ሲኾን በአማኞች መበታተን ምክንያት ከኢየሩሳሌም ውጪ ኹለተኛ ቤተ ክርስቲያን በሠማርያ መመሥረቱ፥ የሕንደኬው ጃንደረባ በፊልጶስ እጅ መጠመቁ፥ የጳውሎስ ወደ ክርስትና ሃይማኖት መግባት፥ አረማውያን ወደ ክርስትና ሃይማኖት መግባታቸው፥ አይሁድን ለማስደሰት ብሎ ሄሮድስ የዮሐንስን ወንድም ያዕቆብን ማስገደሉ ታሪክ ይገኝበታል።

አራተኛው ክፍል ከምዕራፍ 13 እስከ ምዕራፍ 15 ድረስ ሲኾን ጳውሎስንና በርናባስን ለአገልግሎት ሥራ ለመለየት የተደረገ የጾምና የጸሎት አምልኮ፥ በጳውሎስ አማካይነት የተከናወነ ተአምር፥ ጳውሎስ



በድንጋይ ከተወገረ በኋላ ከሞት መዳኑና እንዲሁም የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ታሪክ ይገኝበታል።

አምስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 16 እስከ ምዕራፍ 20 ድረስ ሲኾን ወንጌል በብዙ ቦታዎች መሰበኩ፥ ጳውሎስና ሲላስ በፊልጵስዩስ የደረሰባቸው እስራትና ድብደባ፥ ከጳውሎስና ከሲላስ ጸሎት የተነሣ የእስር ቤቱ በር መከፈቱና እስረኞቹ የታሰሩበት ሰንሰለት መፈታቱ፥ የእስር ቤቱ ጠባቂ ከነቤተሰቡ መጠመቁ፥ በጳውሎስ እጅ ብዙ ታምራት መደረጋቸው ታሪክ ይገኝበታል።

ስድስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 21 እስከ ምዕራፍ 28 ድረስ ሲኾን ጳውሎስ በአይሁድ ተከስሶ ፍርድ ፊት መቅረቡ ለቄሳር ይግባኝ በማለቱ ወደ ሮማ እንዲኼድ መደረጉና ሮማም ውስጥ የወንጌልን ትምህርት ማስፋፋቱ ታሪክ ይገኝበታል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

76. ወንጌላዊው ሉቃስ በሐዋርያት ሥራና እንዲሁም በወንጌሉ መግቢያ ላይ ከመጀመሪያ ጀምሮ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ታሪክ ተከታትሎ የጻፈ መኾኑን ገልጾአል። (ሉቃ. ም.1 ቁ.1 – 4፥ የሐ.ሥ. ም.1 ቁ.1 – 2)

በሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌል ም.21 ቁ.25 ላይ "ኢየሱስ ያደረጋቸው ሌሎች ብዙ ነገሮች ደግሞ አሉ። እኔ እንደሚመስለኝ እርሱ ያደረጋቸው ነገሮች ኹሉ አንድ በአንድ ቢጻፉ ኖሮ የሚጻፉትን መጻሕፍት ዓለም ራሱ መሸከም ባልቻለም ነበር" በማለቱ ኹለቱ አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስለን ይኾናል። የሉቃስ አባባል አጠቃላይ ኹናቴዎችን የሚዘረዝር ሲኾን የዮሐንስ አባባል ግን የምሥራቅ አገር ሰዎችን ያነጋገረ ባህል የተከተለ ቢኾንም በጽሑፍ ከተገለጹት ድርጊቶች ሌላ ጌታ የፈጸማቸው ድርጊቶች ያሉ መኾናቸው ግን አይካድም። በአንደኛው መጽሐፍ ጥያቄና መልስ ተራ ቁጥር 91 እንደተገለጸው የምሥራቅ አገር ሰዎች ስለአንድ ጉዳይ በሚናገሩበት ጊዜ ኹናቴውን ማጋነን ልማዳቸው ነው። ለምሳሌ በኦሪት ዘፍጥረት ም.11 ቁ.4 ላይ



www.ethiopianorthodox.org

"እስከ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ ተብሏል። እንዲሁም በትንቢተ አሞጽ ም.7 ቁ.10 ላይ" የቤትኤል ካህን የኾነው አሜድያ እንዲህ የሚል መልእክት ወደ እስራኤል ንጉሥ ወደ ኢዮርብዓም ላከ: -" እነሆ፥ አሞጽ በእስራኤል ሕዝብ መካከል ኾኖ በአንተ ላይ እያሤረብህ ነው፤ በንግግሩ አገር ሊያጠፋ ተነሥቶአል"

ስለዚህ ዮሐንስ ያቀረበው አቀራረብ እውነት ቢኾንም በባህሉ መሠረት የተጋነነ ከመኾኑ በቀር ከሉቃስ አጠቃላይ አቀራረብ ጋር የሚቃረን አይደለም።

77. በሐዋርያት ሥራ ም.9 ቁ.6 ላይ "አሁን ግን ተነሥና ወደ ከተማ ግባ፤ ልታደርገው የሚገባህም ይነገረሃል አለኝ"፥ በም.22 ቁ.10 ላይ "ተነሥተህ ወደ ደማስቆ ኺድ፤ ልታደርገው የታቀደልህ ነገር ኹሉ እዚያ ይነገርሃል አለኝ፥ በሐዋርያት ሥራ ም.26 ቁ.16 ላይ "አሁን ግን ተነሥና በእግርህ ቁም፤ እኔ የተገለጥሁልህ አሁን እኔን ባየህበትና ወደፊት ም እኔ ለአንተ በምገለጥበት ነገር አገልጋይና ምስክር እንድት ኾነኝ ልሾምህ ፈልጌ ነው" ተብሎአል።

አንድ ጸሐፊ ለአጻጻፉ ወይም አንድ ተናጋሪ ለንግግሩ ምክንያቶች ይኖሩታል። ለምሳሌ ስለአንድ ኹናቴ ታሪክ በሚተረክበት ወይም በሰብከት መልክ፥ ወይም ሰውን ለማሳመን አንድ ዐይነት ንግግር በሚደረግበት ጊዜ የሚቀርበው አቀራረብ የተለያየ ነው።

በዚህም መሠረት የመጀመሪያዎቹ ኹለት ጥቅሶች የቀረቡት የድርጊቱን ቅደም ተከተል በታሪክ መልክ ለማቅረብ ሲኾን ሦስተኛው ጥቅስ ግን የቀረበው ምንም እንኳን ያ ኹናቴ የተከሠተበት ወቅት ከሌሎች ጋር ግንኙነት ባይኖረው በስብከት መልክ በመቅረቡ ሰሚውን ለማሳመን ከመጀመሪያው ታሪካዊ ኹናቴ ጋር ማገናኘት አስፈላጊ ኾኖ በመገኘቱ ነው።

ስለዚህ ኹለቱ አባባሎች ለተለያየ ዓላማ ከመቅረባቸው በቀር እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።



78. በሐዋርያት ሥራ ም.9 ቁ.7 ላይ "ከሳውል ጋር ይኼዱ የነበሩት ሰዎች ድምፅ እየሰሙ ማንንም ባለማየታቸው የሚናገሩትን አጥተው ዝም ብለው ቆሙ" የተባለ ሲኾን በምዕራፍ 22 ቁ.9 ደግሞ:- "ከእኔ ጋር የነበሩት ሰዎች ብርሃኑን አዩ እንጂ እርሱ ሲያነጋግረኝ ድምፁን አልሰሙም" በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስል ይኾናል። በመጀመሪያው ጥቅስ ላይ ሰዎቹ የሰሙት ድምፅ የጳውሎስን ድምፅ ሲኾን በኹለተኛው ጥቅስ ላይ ደግሞ ሊሰሙት ያልቻሉት የጌታን ድምፅ ነው።

ሌሎች ተርጓሚዎች እንደሚሉት ደግሞ በኹለተኛው ጥቅስ ላይ መስማት የሚለው ቃል መረዳት ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው በሌላ ቋንቋ በሚናገርበት ጊዜ ያ ሰው የተናገረበትን ቋንቋ የማናውቀው ኾነን ድምፁን እየሰማን ምን ማለቱ እንደኾነ በማይገባን ጊዜ አልሰማነውም ማለት የተለመደ አነጋገር ነው። ለዚህ አባባል ምሳሌ ይኾኑ ዘንድ የሚከተሉትን ኹለት ጥቅሶች እንመልከት "ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ።" (ማቴ. ም.13 ቍኢ. 9) "ያን ነቢይ የማይሰማ ኹሉ ከሕዝብ ተለይቶ ይጥፋ።" (የሐ:ሥ. ም.3 ቍ. 23)

በዚህም መሠረት ኹለቱ ጥቅሶች በተለያዩ ኹናቴዎች ከመነገራቸው በቀር እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

## ወደ ሮሜ ሰዎች የተላከ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት

ይህ መልእክት 16 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በኹለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 11 ድረስ ሲኾን በሮማ የነበሩ ክርስቲያኖች ቀድሞ አይሁዶች የነበሩና እንዲሁም ቀድሞ አረማውያን የነበሩ መኾናቸውን ይገልጽና አረማውያን የነበሩት ክርስቲያኖች ቀድሞ አይሁዶች በነበሩት ክርስቲያኖች ላይ የሚሰነዝሩት ነቀፌታ እግዚአብሔር ለአይሁዶች ብዙ ውለታ የዋለላቸው መኾኑንና



www.ethiopianorthodox.org

እነርሱ ግን ለእግዚአብሔር ውለታ የሰጡት መልስ ጣዖት ማምለክና ሌላም ብዙ ኀጢአት የተመላበት ክፉ ተግባር ነው ብለዋል። አረማውያን የነበሩት ክርስቲያኖች እንደ አይሁዶች በነቢያት አማካይነት የክርስቶስ መምጫ ጊዜ ተነግሮአቸው ቢኾን ኖሮ እርሱን ለመቀበል ከመዘጋጀታቸው በቀር እንደአይሁድ አባቶች ሕማማትና ሞት እንዲደርስበት ባላደረግንም ነበር ብለዋል። ቢኾንም እኛ ግን የፍልስፍና ትምህርታችን የክርስትናን ሃይማኖት ለመቀበል ስላዘጋጀን በቀላሉ ለመቀበል በቅተናል በማለት አይሁድ በነበሩ ክርስቲያኖች ላይ የኵራት አነጋገራቸውን ሰንዝረዋል።

ከአይሁድ ሃይማኖት ወደክርስትና የገቡት ወገኖች ደግሞ በበኩላቸው የሙሴ ሕግና ነቢያት ለክርስትናው ሃይማኖት እንዳዘጋጁአ በነበ ቸውና እነርሱም ምርጥ ሕዝብ መኾናቸውን በመናገር አረማውያን ሩት ክርስቲያንኖች ላይ ኵራታቸውንና ነቀፌታቸውን ገልጸዋል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ግን አይሁድም ኾኑ አረማውያን ኀጢአተኞች መኾናቸውንና የክርስትና ሃይማኖት ጸጋ የተገኘው ተገቢ በመኾን ሳይኾን በነጻ መኾኑን አስረድቷል።

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 12 እስከ ምዕራፍ 16 ድረስ ሲኾን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ስለመኾንዋ፥ በአንድ ጠባቂ ሥር ያሉ ወገኖች መኾናቸውን ለመግለጽ ለምእመናን የሚያስፈልጋቸው ምክር መመሪያና ትእዛዞች ይገኙበታል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

79. በምዕራፍ 3 ቁ.10 ላይ አንድም ጻድቅ ሰው የሌለ መኾኑ ተገልጾ ሳለ በምዕራፍ 7 ቁ.8 ላይ ደግሞ "ኀጢአት ያለሕግ ምውት ነው" መባሉ ሕግ ከመስጠቱ በፊት ሰው ኹሉ ጻድቅ የነበረ ስለሚያስመስል ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።

ከሕግ በፊት ኀጢአት አልነበረም ማለት ሳይኾን ሰው የኀጢአት ሥራውንም እየሠራ ያ የሠራው ሥራ ኀጢአት መኾኑን የሚነግረው ሕግ



ባለመኖሩ ኀጢአተኛ መኾኑን አያውቅም ነበር ማለት ነው። ኀጢአት የሚያስቀጣ መኾኑን ሕግ ከገለጸላቸው በኋላ ሰው ልጆች የኀጢአት ሥራ ዝንባሌአቸው እየጨመረ ኼደ፡ ዋናው ምክንያት ከዚያ በኋላ የሚፈጽሙአቸው ሥራዎች ኀጢአት መኾናቸውን በሕጉ አማካይነት ሊያውቁ በመቻላቸው ነው። ስለዚህ ኹለተኛው አባባል ኀጢአት ሕግ ከመደንገጉ በፊት የነበረ መኾኑን የሚክድ አይደለም።

80. በምዕራፍ 3 ቁ.28 ላይ ሰው ያለሥራ በእምነት ብቻ እንደሚጸድቅ የተገለጸ ሲኾን በሐዋርያው የያዕቆብ መልእክት ም.2 ቁ.24 ላይ ደግሞ ሰው የሚጸድቀው በበጎ ተግባርም ጭምር ነው እንጂ በእምነት ብቻ አይደለም በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል።

ኹለቱ አባባሎች የተለያዩ ምክንያቶች አሉአቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ ሰው በእምነት እንጂ በሥራው አይጸድቅም ያለበት ምክንያት የኦሪቱን ሕግ በመፈጸማቸው ብቻ ጻድቃን የኾኑ ይመስላቸው የነበሩትን የፈሪሳውያንን አስተሳሰብ ለመቃወም እንጂ ሃይማኖታዊ ሕግን ፈጻሚነት ጠቃሚ አይደለም ለማለት አለመኾኑ በዚሁ መልእክት ም.2 ቁ.6 ላይ "እግዚአብሔር ለያንዳንዱ እንደየሥራው ይሰጠዋል፡" ለኤፌሶን ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.6 ቁ.8 ላይ "አገልጋይም ኾነ ጌታ እያንዳንዱ በሠራው መልካም ሥራ ከጌታ ኢየሱስ ዋጋውን የሚቀበል ለመኾኑ እርግጠኞች ኹኑ" የሚሉት ኹለት ጥቅሶች በቂ ማስረጃዎች ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ በፈሪሳውያን ላይ ያቀረበውን ዐይነት ተቃውሞ መድኀኒታችንም በምሳሌ መልክ አቀርቦታል። በዚህም ምሳሌ አንድ ፈሪሳዊና አንድ ቀራጭ ሊጸልዩ ወደ ቤተ መቅደስ ወጥተው ፈሪሳዊው ሕግጋቱን እንደሚፈጽም በመዘርዘር በሚመጻደቅበት ጊዜ ቀራጩ በትሕትና ስለኀጢአቱ ይቅርታ ከእግዚአብሔር ይለምን እንደነበረ ያስረዳና በመጨረሻ ግን ከፈሪሳዊው ይልቅ ቀራጩ እንደጸደቀ ይገልጻል። (ሉቃ. ም.18 ቁ.9 – 14)

የሐዋርያው ያዕቆብ አባባል ግን እምነት አለን እያሉ የእግዚአብሔርን ሕግጋት የማይፈጽሙትን ሰዎች የሚመለከት ነው። ማመንማ አጋንንትም እንደሚያምኑ በጎ ተግባር ግን ስለማይሠሩ እንደ ተፈረደባቸው ያመለክታል። በዚህም ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ አለመኾናቸውን እንገነዘባለን። ጥያቄና መልስ ቁ.86 ይመለከቷል።



www.ethiopianorthodox.org

81. ወደ ሮሜ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.9 ቁ.15 – 24 እግዚአብሔር ሲፈልግ ሰውን እንደሚያጸድቀውና ሳይ ፈልግ ደግሞ እንደሚኰንነው የተለገለጸ ሲኾን በራእየ ዮሐንስ ም.22 ቁ.12 ላይ ደግሞ "እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለያንዳንዱም እንደየ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ" በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉ ይኾናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ከሃሊነት መነሻ በማድረግ እርሱ ከፈለገ አንዱን ለጽድቅ ሌላውን ደግሞ ለፍዳ እንደሚያዘጋጀው የገለጸው በያዕቆብና በኤሳው መካከል ያዕቆብን መምረጡና የፈረዖንን ልብ አጸናለሁ ማለቱን በምሳሌነት በመውሰድ ነው። እንዲያውም አባባሉን የበለጠ በማጠናከር በሸክላ ሠሪና በሸክላ ጭቃ መካከል ያለውን ኹናቴ በምሳሌነት አቅርቦአል። ከምዕራፍ 9 እስከ ምዕራፍ 11 ድረስ ያለውን ትችት ትክ ብለን ያስተዋልን እንደኾነ ከአይሁድ ሃይማኖት ወደ ክርስትና በገቡትና ከአሕዛብ ወገን ደግሞ ወደ ክርስቲያን ሃይማኖት በተመለሱት ክርስቲያኖች መካከል አንድ ዐይነት መናናቅ የነበረ መኾኑን ያመለክተናል። አይሁዳውያን የነበሩት ወገኖች እኛ የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ ልጆች ኾነን የተመረጥን ዘር በመኾናችንና ቀደም ተብሎ ሕግ የተሰጠው ለእኛ ስለኾነ የኦሪቱ ሕግና ሥርዓት እኛን ለክርስትና ለክርስትናው ሃይማኖት አዘጋጅቶናል ከማለታቸውም በላይ ለክርስትና ሕይወታችን የኦሪቱ ሥርዓት መመሪያ መኾን አለበት በማለት ከአረመኔነት ወደ ክርስትና የገቡትን ክርስቲያኖች ማስቸገርና ማስጨነቅ ብቻ ሳይኾን ይንቁአቸውም ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ አረማውያንን ወደ ክርስትና ሃይማኖት ለመመለስ አይሁዶችን እንደመመለስ አስቸጋሪ ባለመኾኑ እነርሱ ደግሞ በበኩላቸው አይሁዳውያን በነበሩት ላይ ያቀርቡት የነበረው ወቀሳ እንዴት የአይሁድ አባቶች ብዙ ያደረገላቸውን እግዚአብሔርን ትተው ጣዖት በማምለክና ነቢያትን በመግደል ፈጣሪያቸውን እንዳስቀየሙና በመስ በመጨረሻም የእግዚአብሔርን ልጅ መሲሑን ለሞት አሳልፈው በመስ ጠት የእግዚአብሔርን ወንጌል አለመቀበላቸውን በመዘርዘር ከአይሁድ ወገኖች ይልቅ እነርሱ እንደሚሻሉ በማመን ነቀፌታቸውን ይገልጹ ነበር።



አሁን እንግዲህ እነዚህን ኹናቴዎች ለመቃወም ሲል ነው ሐዋርያው ጳውሎስ አባቶቻቸው ነቢያትን በመግደል፥ ጣዖትን በማምለክና ክርስቶስን ለሞት አሳልፎ በመስጠት የበደሉት፥ ልጆቻቸውን የእግዚአብሔርን ልጅ ቤዛነት አምነው እስከተቀበሉ ድረስ እግዚአብሔር ይቅርታ አድርጎ ቢምራቸው አንተ ማነህ እግዚአብሔርን የምትፋረድ ማለቱ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ሲል ምርጥ ሕዝብ ያደረጋቸው የአይሁድ ወገኖች እያሉ እንዴት ከአረማውያን ወገን የኾኑ የልጅነትን ዕድል አገኙ ለሚለው ጥያቄ ከአይሁድ ወገኖች ብዙዎቹ ያላመኑ ሲኾኑ አረማውያን የነበሩት ግን በልጁ ቤዛነት አምነው እስከተመለሱ ድረስ እግዚአብሔር ከተመራጮቹ መካከል ቢያደርጋቸው አንተ ማነህ እግዚአብሔርን የምትፋ ረድ ማለቱ ነው። የእግዚአብሔርም ምርጫ በዘር ሳይኾን በእምነት ለተ ቀበለው ለማንኛውም ወገን የሚበጥ የእግዚአብሔር ልጅነት ነው። እግዚአብሔር ከፈለገ ማንንም ይመርጣል የሚለውን ሐሳብ ከማቅረቡ በፊት ሐዋርያው ጳውሎስ ከቁ.1 እስከ 5 እንደገለጸው ወገኖቹ አይሁድ የክርስቶስን ቤዛነት አምነው የዳኑ ባለመኾናቸው ኀዘንና ጭንቀት ያደረበት መኾኑን ይዘረዝራል። እስራኤላውያን ሳይኾኑ ሌሎች ወገኖች የተመረጡ መኾናቸውን በቁ.26 ላይ ነቢያት በመጥቀስ እንዲህ ይላል "ሕዝቤ ያልኾነውን ሕዝቤ ብዬ ያልተወደደችውንም የተወደደች ብዬ እጠራለሁ፤ እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም በተባለባቸውም ስፍራ በዚያ የሕያው እግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉ። "በቁ.30 – 33 ላይ ደግሞ ይህንኑ ጉዳይ በበለጠ ሲያብራራው፡- "እንግዲህ ምን እንላለን? ጽድቅን ያልተከተሉት አሕዛብ ጽድቅን አገኙ። እርሱ ግን ከእምነት የኾነ ጽድቅ ነው። እስራኤል ግን የጽድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ሕግ አልደረሱም። ይህስ ስለምንድነው? በሥራ እንጂ በእምነት ጽድቅን ስላልተከተሉ ነው። እነሆ፥ በጽዮን የእንቅፋት ድንጋይና የመሰናከያ ዐለት አኖራለሁ፤ በእርሱም የሚያምን አያፍርም ተብሎ እንደተጻፈ በእንቅፋት ድንጋይ ተሰናከሉ" ብሏል።

እግዚአብሔር ለሰዎች የሚሰጠውን ውሳኔ በሚመለከት ከመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን አንዱ እንዲህ ብሏል "እግዚአብሔር ለክፉ ሥራ ቅጣትን የሚሰጠው ትክክለኛ ዳኛ በመኾኑ ነው፤ ለክፉ ሥራ ደግን የሚሰጠው ደግ ስለሆነ ነው፤ ለደግ ሥራ ክፉን የማይሰጠው ግፈኛ ባለመኾኑ ነው።" ይህም ማለት አንድ ሰው ምንም ያኽል ኀጢአተኛ ቢኾን በንስሓ



www.ethiopianorthodox.org

እስከተመለሰ ድረስ እግዚአብሔር ይቀበለዋል፤ ምንም ያህል እግዚአብሔር በትዕግሥት ቢጠብቀው በንስሓ የማይመለሰውን ሰው ግን ተገቢ ቅጣቱን ይሰጠዋል ማለት ነው።

እንግዲህ የሐዋርያው ጳውሎስ የምርጫ ትችት በሰው ዘንድ እንደ ጻድቃን የሚገመቱትን ለማጽደቅና እንደኀጢአተኞች የሚገመቱትን ለመኰነን ሳይኾን የሰውን ውስጠ ምሥጢር የሚያውቀው እግዚአብሔር ለኹሉም እንደየሥራው ዋጋውን በሚሰጥበት ጊዜ ማነው ከፈጣሪ ይበልጥ ዐውቃለሁ በሎ ሊፋረደው የሚጀምር ለማለት ነው እንጂ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ያለምንም የፍርድ መመዘኛ ያጸድቀዋል ወይም ይፈርድበታል ለማለት አይደለም።

## ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላከው የመጀመሪያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት

ይህ መልእክት 16 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 6 ድረስ ሲኾን የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መከፋፈልና መለያየት እንዲሁም የተለያዩ የኀጢአት ርኩስቶች ስለተሰማባቸው ሐዋርያው የወቀሳቸው መኾኑ ተገልጾአል።

ኹለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 7 እስከ ምዕራፍ 15 ድረስ ሲኾን በውስጡም ለጣዖት ስለተሠዋ ሥጋ መብላትና አለመብላት ጉዳይ መልስ ሰጥቶበታል። እንዲሁም የቅዱስ ቁርባንን ሥነ ሥርዓት በዝርዝር አስረድቶአል።

ሦስተኛው ክፍል ም.16 ሲኾን ሐዋርያው ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ክርስቲያኖች የገንዘብ መዋጮ እንዲደረግላቸው ሕዝቡን ያዘዘ መኾኑ ተገልጾአል።





82. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በመጀመሪያ በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.1 ቁ:25 ላይ "የእግዚአብሔር ሞኝነት ከሰው ጥበብ ይበልጣል፤ የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ኀይል ይበረታል" የሚለው አባባል በትንቢት ኤርምያስ ም.32 ቁ.17 ላይ "አቤቱ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ እነሆ አንተ ሰማይንና ምድርን በታላቅ ኀይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል ለአንተም የሚሳንህ ነገር የለም" እንዲሁም ወደ ሮሜ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.11 ቁ.33 ላይ "እግዚአብሔር በጥበብና በዕውቀት ምንኛ ባለጸጋ ነው ፍርዱና መንገዱስ ተመርምሮ ለመታወቅ የማይቻል ምንኛ ጥልቀት አለው" ተብለው ከተገለጡት አድናቆቶች ጋር እንዴት ይታረቃል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የእግዚአብሔር ኀያልነትና ጥበበኛነት ምንም የሚያከራክር ጉዳይ ስላልኾነ ነው እንጂ ብዙ ማስረጃዎችን ለመጥቀስ በተቻለ ነበር።

አሁን ወደ ዋናው ጥያቄ እንመለስና ለጥያቄው መልስ ለማቅረብ ወደ ቁጥር 22 መለስ ብለን የተመለከትን እንደኾነ "አይሁዶች ምልክት ይጠይቃሉ፤ ግሪኮችም ጥበብን ይሻሉ" የሚለው ጥቅስ የጥያቄው መነሻ ኾኖ እናገኘዋለን። አይሁዶች በጌታ ለማመን ቅድመ ኹኔታ አድርገው ያቀረቡት ተአምር እንዲያሳያቸው ነበር። (ማቴ. ም.12 ቁ.38፥ ም.16 ቁ.1) በሌላ በኩል ደግሞ በሥልጣኑ አጋንንትን የማስወጣት ተአምር ሲየዩ በብዔልዜቡል በአጋንንት አለቃ አማካይነት ካልኾነ በቀር አጋንንትን አያወጣም ሲሉ የጽርፈት ንግግር ተናግረዋል። (ማቴ. ም.12 ቁ.24፥ ሉቃ. ም.11 ቁ.15) ከዚያም ሕማም አድርሰውበት በሰቀሉት ጊዜ ያለምንም ተቃውሞ ዝም ብሎ ራሱን አሳልፎ በመስጠቱ እንደ ድከመት ቈጠሩት። በግሪኮችም በኩል አንድ ሕማምና ሞት የደ ረሰበትን ሰው አምላክ ነው ማለት እንደሞኝነት ተቈጠረ። እነርሱ በዓለማዊ ፍልስፍና የተራቀቁ ነበሩ። በዚህም ምክንያት ነው ቀጥለው ባሉት ተከታታይ ቁጥሮች ማለት በ23 እና በ24 ላይ "እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአ ሕዛብም ሞኝነት ነው። ለተጠሩት ግን አይሁድ ቢኾኑ የግሪክ ሰዎችም ቢኾኑ የእግዚአብሔር ኀይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የኾነው ክርስቶስ ነው" ተብሎ



www.ethiopianorthodox.org

የተገለጠው። ከዚህ በኋላ ነው "የእግዚአብሔር ሞኝነት ከሰው ጥበብ ይበልጣል፤ የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ኀይል ይበረታል" የተባለው። ይህም ማለት ያ እናንተ እንደ ሞኝነትና ድካመት የቈጠራችሁት ኹናቴ የእግዚአብሔር ኀይልና ጥበብ ነው ብሎ ሊያስረዳቸው ፈልጎ ነው። ይህን ኹናቴ ሐዋርያው ጳውሎስ መጀመሪያ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክቱ ሲገልጠው "የሃይማኖታችን ምሥጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው። እርሱም እግዚአብሔር ሰው ኾኖ የተገለጠ፥ እውነተኛነቱ በመንፈስ የታወቀ፥ ለመላእክት የታየ፥ ለሕዝቦች ኹሉ የተሰበከ፥ በዓለም ያሉ ሰዎች ያመኑበት፥ በክብር ወደ ሰማይ የወጣ የሚል ነው" ብሏል። (1ኛ ጢሞ: ም.3 ቁ.16)

ሰውን ያዳነበትን ታላቁን ጥበብ ነው እነርሱ እንደሞኝነትና እንደድካመት የቈጠሩት። ይህም የእግዚአብሔር ጥበብ ዐዋቂዎች ነን ከሚሉት ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ተሰውሮ ቀድሞ ምንም ትምህርት ላልነበራቸው ማለት በዓለማዊ ዕውቀታቸው እንደሕፃናት ለሚቈጠሩት ለሐዋርያት በመገለጡ በማቴዎስ ወንጌል ም.11 ቁ.25 እና በሉቃስ ወንጌል ም.10 ቁ.21 ላይ እንደተገለጠው መድኀኒታችን ለአብ ባቀረበው ምስጋና:- "አባት ሆይ፥ የሰማይና የምድር ጌታ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ" ብሏል።

ስለዚህ የእግዚአብሔር ሞኝነትና ድካም የተባለው በአይሁድና በግሪኮች አስተሳሰብ ለማለት ነው እንጂ አምላክ ሞኝነትና ድክመት አለበት ለማለት አይደለም።

83. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው በመጀመሪያው የጳውሎስ መልእክት ምዕራፍ 7 ቁ.1 ላይ "ስለጻፋችሁልኝ ጥያቄ ሰው ከሴት ጋር በግብረ ሥጋ ባይገናኝ ወይም ሚስት ባያገባ መልካም ነው" የሚለው በኦሪት ዘፍጥረት ም.2 ቁ.18 ላይ "ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለምና ረዳት እንፍጠርለት" በምዕራፍ 1 ቁ.27 ላይ ደግሞ:- "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት" ከሚሉት ከእግዚአብሔር አባባሎች ጋር አይቃረኑም ወይ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የቅዱስ ጳውሎስ አባባል የተሰነዘረው የቆሮንቶስ ሰዎች ከጠየቋቸው ጥያቄዎች መካከል ስለድንግልና ኑሮ የተጠየቀውን ጥያቄ መልስ



ለመስጠት ነው። ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም ስላይደለ ነው ሔዋን የተፈጠረችለት። ይህም የማኅበራዊ ኑሮን አስፈላጊነት የሚያመለክት ነው።እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ አስተሳሰብ ኅብረትን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ በጋብቻ ከሚገኘው ኅብረት የበለጠ ነው። በዚሁ መልእክት ም.7 ቁ.7 ላይ እንደገለጸው "ሰው ኹሉ እንደ እኔ ሚስት ሳያገባ ቢኖር በወደድሁ ነበር፤ ነገር ግን ለያንዳንዱ እግዚአብሔር የተለየ ስጦታ ሰጥቶታል። አንዱ አንድ ዐይነት ስጦታ ሌላው ሌላ ዐይነት ስጦታ አለው" ብሏል። ይህን አባባል በማጠናከር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዝሙት ምክንያት ካልኾነ በቀር ማንም ሰው ሚስቱን መፍታት እንደ ማይገባው በገለጸላቸው ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ከኾነስ ሚስት አለማግባት ይሻላል ላሉት አባባል መልስ ሲሰጣቸው ልዩ ችሎታ ለተሰጣቸው ነው እንጂ ይህ ነገር ለኹሉም አይኾንም ብሎአቸዋል። (ማቴ. ም.19 ቁ.9 – 11)

ይህ የጌታና የቅዱስ ጳውሎስ አባባሎች የሚያመለክቱት ከሴት ርቆ የመኖር ልዩ ችሎታ የተሰጣቸው ሰዎች የአሉ ማኾናቸውን ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስም ምክሩን ሲለግስ "በሥጋ ምኞት ከመቃጠል ይልቅ ማግባት የተሻለ ነው" ብሏል። (1ኛ. ቆሮ. ም.7 ቁ.9)

በዚህም መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ስለድንግልና ኑሮ ምክር የሰጠው ልዩ ስጦታ ለተሰጣቸው ሰዎች ነው እንጂ ለኹሉም ስላልኾነ በኦሪት ዘፍጥረት ከተፈቀደው የእግዚአብሔር ቃል ጋር ተቃራኒ አይደለም። የኦሪት ዘፍጥረቱ አባባል ደግሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ የእግዚአብሔር ትእዛዝ አይደለም። ስለዚህ ነው ጌታ ሚስት ስላለማግባት ምርጫ በተጠየቀ ጊዜ "ልዩ ችሎታ ለተሰጣቸው ነው እንጂ ይህ ነገር ለኹሉም አይኾንም" የሚል መልስ የሰጠው (ማቴ. ም.19 ቁ.11)

84. «በኋላም መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ኹሉና ሥልጣንን ኹሉ፥ ኀይልንም በሻረ ጊዜ ፍጻሜ ይኾናል። ኹሉ ነገር ከተገዛለት በኋላ እግዚአብሔር ኹሉ በኹሉ ይኾን ዘንድ በዚያን ጊዜ ወልድ ደግሞ ኹሉን ላስገዛለት ይገዛል ይኾናል።" (1ኛ. ቆሮ. ም.15 ቁ.24 እና 28)



www.ethiopianorthodox.org

ጌታ በትንሣኤው ጊዜ እንደሰውነቱ ሥልጣን ተሰጥቶት እንደነበረ ገልጾአል። ይህም ሥልጣን የተሰጠው የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነት ነጻ እንዲያወጣበት ነበር። በመጨረሻ ግን በዚያ በተሰጠው ሥልጣን ለሰው ልጅ ቤዛ ኾኖ ነፍሳትን ኹሉ የቀደሰ በመኾኑና ከዚያ በኋላ ያ ያማላጅነት ሥልጣን አስፈላጊ ባለመኾኑ ያንን ሥልጣን አስረክቦ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለው መለኮታዊ ክብሩ ለዘላለም ይኖራል ማለት ነው። (ማቴ. ም.28 ቁ.18) ያስረከበው ወይም አሳልፎ የሰጠው በለበሰው ሥጋ እንደ ሰውነቱ ነው።

እግዚአብሔር ኹሉን ነገር በክርስቶስ እግር ሥር ካስገዛለት በኋላ ወልድ ኹሉን ላስገዛለት ተገዢ ይኾናል የተባለው በመለኮታዊ ባሕርዩ ከአብ የሚያንስ ኾኖ ሳይኾን ራሱን ዝቅ አድርጎ በለበሰው የሰው ልጅ ሰውነት ተገዢ ለመኾን ስለፈቀደ ነው። የሰውን ልጅ ሥጋ ከለበሰ በኋላ ከኀጢአት በቀር በኹሉም ነገር የሰውን ልጅ መስሏል እንደተባለው የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር ተገዢ እንደሚኾን ኹሉ ጌታም በለበሰው ሥጋ ተገዢ ኾኗል። ጥያቄና መልስ ቁጥር 8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥ 57፥ 61፥ 63፥ 72፥ 74፥ 75፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥ 102 እና በአንደኛው መጽሐፍ ቁ.102፥ 104፥ 112፥ ይመለከቷል።

85. "ሙታን በፍጹም የማይነሡ ከኾነ ስለሙታን የሚጠመቁ ምን ያደርጋሉ? ስለሙታንስ የሚጠመቁት ለምንድነው? (1ኛ. ቆሮ. ም.15 ቁ.29)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለጥምቀት በሚነገርበት ጊዜ ስለራስ ሳይኾን ስለሌላ ሰው መጠመቅ የሚያዝዝ ትምህርት የተሰጠበት ቦታ በፍጹም አይገኝም። በቤተ ክርስቲያን ቀኖናም ኾነ በሥርዐተ ቤተ ክርስ ቲያን አንድ ሰው ስለሙታንም ኾነ ስለሕያዋን ማለት ስለሌሎች መጠ መቅ አልታዘዘም።

ኹናቴው እንደዚህ ከኾነ ለምንድነው ታዲያ ሐዋርያው ቅዱስ ጳው ሎስ ስለሙታን ስለሚጠመቁ ሰዎች የተናገረው?

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች መጀመሪያ በላከው መልእክቱ ም.15 ላይ ያቀረበው ትምህርት ስለ ትንሣኤ ሙታን እምነት



ትክክለኛነት ዘርዝሮ የሚያስረዳ ነው። በዚሁ ምዕራፍ በቁጥር 31 – 32 ላይ "በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለኝ በእናንተ ትምክህት እየማልሁ፥ ወንድሞች ሆይ ዕለት ዕለት እሞታለሁ።እንደ ሰው በኤፌሶን ከአውሬ ጋር ከታገልሁ ሙታንስ የማይነሡ ከኾነ ምን ይጠቅመኛል" ይላል። ስለ ትንሣኤ ሙታን አጥብቆ በተናገረበት በዚሁ ምዕራፍ ቁ.12 – 14 ላይ "ክርስቶስ ከሞት እንደተነሣ የምናስተምር ከኾነ ግን እንዴት ከእናንተ አንዳንዶቹ ትንሣኤ ሙታን የለም ይላሉ? ትንሣኤ ሙታን ከሌለማ ክርስቶስ ከሞት አልተነሣም ማለት ነዋ ክርስቶስ ከሞት ካልተነሣ ደግሞ የእኛም ትምህርት ኾነ የእናንተም እምነት ከንቱ መኾኑ ነው።"

የትንሣኤ ሙታንን እምነት ትክክለኛነት በምክንያታዊ ትንተና ካቀረበባቸው መንገዶች አንዱ ጥምቀትንና ሞትን አለመነሣትን በማገናዘብ ነበር።

እኛ የምንጠመቀው ከጥንቱ የአዳም ኀጢአት ነጻ ለመኾን፥ ከኀ ጢአት ይቅር ለመባል፥ ዳግመኛ ማለት የመንፈስ ልደት ለመወለድና የእግዚአብሔር ልጆች ለመኾን ነው። በአጠቃላይ ግን የክርስቶስ ቤተ ሰብ ለመኾን በቅድሚያ መጠመቅ ይኖርብናል። በጥምቀት አማካይነት እነዚህን ኹሉ ጸጋዎች የምንታደለው ለዘላለማዊው ሕይወታችን እንጂ በዚህ ዓለም ላይ ለምንኖራት ለአጭርዋ ዕድሜአችን ብቻ አይደለም። ይህን አባባል ሲያጠናክር ሐዋርያው ጳውሎስ በክርስቶስ ተስፋ የምናደርገው ለዚህ ዓለም ሕይወት ብቻ ከኾነ ከሰዎች ኹሉ ይበልጥ የሚታዘንልን ምስኪኖች ነን" ብሏል። (1ኛ. ቆሮ. ም.15 ቁ.19)

አሁን እንግዲህ ከቅዱስ ጳውሎስ አባባል እንደምንረዳው የምን ጠመቀው ለዘላለማዊ ሕይወታችን ጠቀሜታ ካልኾነ ሞተው ለሚቀሩት ሰውነቶቻችን ይህም ለሙታን ነው ማለት ይኾናል።

ወደ ቈላስይስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.2 ቁ.12 ላይ "በጥ ምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ" ብሏል። ይህ አባባል የሚያመለክተው መጠመቁ የሚረዳው ተቀብሮ ለመነሣት እንጂ ተቀብሮ ለመቅረት አይደለም። ተጠምቆ ከተቀበሩ በኋላ መነሣት ከሌለ ግን የተጠመቅነው ለሚቀሩት ሰውነቶቻችን ማለት ለሙታን መኾኑ



www.ethiopianorthodox.org

ነው። ታዲያ ለሙታን መጠመቁ ለምን አስፈለገ ተብሎ የተጠየቀውም ስለዚህ ነው።

ሌሎች ምሁራን እንደሚሉት ደግሞ በዚያን ዘመን ክርስቲያን መኾን ማለት ሕይወትን ለሞት አደጋ አሳልፎ እንደመስጠት ይቈጠር ነበር። ስለዚህ ያን ኹሉ የሞት አደጋ እያወቁ ለችግሩ መጋለጡ ትንሣኤ ሙታንን ተስፋ በማድረግ ነው እንጂ ሞቶ ለሚቀረው ሰውነት ማለት ለሙታን ለምን መቸገር አስፈለገ ለማለት ነው።

## ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላከው ኹለተኛው የቅዱስ ጳውሎስ መል እክት

ይህ መልእክት 13 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 7 ድረስ ሲኾን የመጀመሪያው መልእክቱ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ ፍሬ በማፍራቱ የተሰማውን ደስታ ገልጾአል። በእነርሱ ዘንድ ያለው ችግር የሚወገድበትን መንገድ እርሱ ራሱ ተገኝቶ ለመርዳት ቃል ከገባ በኋላ ለመኼድ ባለመቻሉ ይቅርታ ጠይቆአል።

ኹለተኛው ክፍል ምዕራፍ 8 እና 9 ሲኾን በመጀመሪያው መልእክቱ እንዳሳሰበው አሁንም ምእመናን በይሁዳ ለሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ምጽዋት በመስጠት በጎ ተግባር እንዲያከናውኑ አሳስቦአቸዋል።

ሦስተኛው ክፍል ደግሞ ከምዕራፍ 10 እስከ ምዕራፍ 13 ድረስ ሲኾን በዚህ ክፍል ከሐዋርያዊ ደረጃው ዝቅ ሊያደርጉት ከተነሡት ሐሰተኞች ሐዋርያት ራሱን ለመከላከል ጥረት አድርጓል።





86. ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው ኹለተኛ መልእክት ም. 3 ቁ. 5–11 ላይ :- "ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ እኛ በራሳችን ብቃት እንዳለን የምናስብ አይደለም፤ እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይኾን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንኾን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል። ሕግ የተቀረጸው በድንጋይ ጽላት በፊደል ነበር፤ ሕግ በተሰጠበት ጊዜ ስለ ሕጉ ክብር የሙሴ ፊት በማንጸባረቁ እስራኤላውያን ትኩር ብለው ሊመለከቱት አልቻሉም፤ እንግዲህ ሞትን ያመጣ ሕግ በእንዲህ ዐይነት ክብር ከተገለጠ በመንፈስ አማካይነት የሚገኘው አገልግሎት እንዴት የበለጠ ክብር ይኖረው! ሰዎች የተኰነኑበት አገልግሎት ይህን ያህል ክብር ካለው ሰዎች የሚጸድቁበት አገልግሎትማ እንዴት የበለጠ ክብር ይኖረው! የአሁኑ ክብር ካለፈው ክብር ጋር ሲወዳደር ያለፈው ክብር ከአሁኑ ክብር ያነሰ ኾኖ ተገኘ። ያ ጠፊ የነበረው ነገር ይህን ያህል ክብር ከነበረው ለዘላለም ጸንቶ የሚኖረው ነገርማ የበለጠ ክብር አለው ማለት ነው።" የሚለውና ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. 3 ቁ. 19–24 ላይ ደግሞ "አፍም ኹሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ኹሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይኾን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ኹሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፤ ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ኹሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኀጢአት በሕግ ይታወቃልና። አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብ ሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፤ እርሱም ለሚያምኑ ኹሉ የኾነ በኢየ ሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፤ ኹሉ ኀጢአት ሠርተ ዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎ አቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስም በኾነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ" የተባለው በማቴዎስ ወንጌል ም.5 ቁ. 17 ላይ "ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም" ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካቀረበው ማረጋገጫ ጋር እንደምን ለማስታረቅ ይቻላል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።



www.ethiopianorthodox.org

በሌላ በኩል ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. 7 ቁ. 12 ላይ "ሕጉ ቅዱስ ነው፤ ትእዛዙም ቅድስትና ጻድቅ በጎም ናት" ብሏል። በዚሁ ወደ ሮሜ ሰዎች በተላከው መልእክቱ ም.3 ቁ. 31 ላይ "ታዲያ በእምነት ሕግን እናስወግዳለን ማለት ነውን? እናስወግድም እናጸናዋለን እንጂ" ብሎአል። እንዲሁም መጀመሪያ ወደ ጢሞቴዎስ በላከው መልእክቱ ም. 1 ቁ. 8–10 ላይ "ሰው በሚገባ ከሠራበት ሕግ መልካም መኾኑን እናውቃለን፤ ሕግም የተሠራው ለጻድቃን ሳይኾን ለዓመጸኞችና ለወንጀለኞች ፥ለከሐዲዎችና ለኀጢአተኞች፥ ቅድስና ለሌላቸውና መንፈሳዊ ነገርን ለሚንቁ፥ አባትንና እናትን ለሚገድሉና ለነፍሰ ገዳዮች፥ ለአመንዝሮችና ግብረሶዶማውያን ከወንዶች ጋር ለሚያደርጉ ወንዶች፥ በሰዎች ለሚነግዱና ለውሸተኞች ፥ በሐሰት ለሚምሉና የእውነተኛ ትምህርት ተቃራኒ የኾነውን ነገር ኹሉ ለሚያደርጉ መኾኑ የታወቀ ነው" በማለት ከላይ የተገለጡትን ኹለት አባባሎች አጠናክሮአል።

ስለ እምነትና ስለ ሕግ ከላይ የቀረቡት በሌሎችም የተለያዩ ቦታዎች ከቅዱስ ጳውሎስ የተሰጡት መግለጫዎች እርስ በርሳቸውና ከጌታችን ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ማረጋገጫ ጋር የሚቃረኑ ይመስለን ይኾናል።

ቅዱስ ጳውሎስ አንድም ጻድቅ የለም በሚልበት ጊዜ ሕግጋቱን ሙሉ በሙሉ የፈጸመና ለመፈጸምም የቻለ ሰው ስለሌለ ጽድቅ የሚገኘው ሕግጋትን በመፈጸም ብቻ ከኾነ ኹሉም ተኰንነዋል ማለት ነው የሚል አመለካከት እንዳለው ለማስተዋል የሚቻለው በሚከተለው አባባሉ ምክንያት ነው "ሕግን በመፈጸም እንጸድቃለን የሚሉ ኹሉ ጸንቶ የማይኖርና የማይፈጽማቸውም ኹሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና። ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ ስለተጻፈ ሕግን በመፈጸም ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንደማይጸድቅ ግልጥ ነው፤ ሕግም ከእምነት አይደለም ነገር ግን የሚፈጽመው ይኖርበታል። በእንጨት ላይ ተሰቅሎ የሚሞት ኹሉ የተረገመ ነው ተብሎ ስለተጻፈ ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ኾኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን" (ገላ ም. 3 ቁ. 10–13)

በዚህም ምክንያት ነው ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. 8 ቁ.3 ላይ "ከሥጋ ደካማነት የተነሣ ሕግ ሊፈጽም ያልቻለውን



እግዚአብሔር ልጁን በኀጢአተኛው ሥጋ ምሳሌ ልኮ ኀጢአትን በሥጋ ኾኖ ፈረደበት" ያለው።

በዚህ ጉዳይ ላይ በእግዚአብሔር መንፈስ እየተመራ ነቢዩ ኤርምያስ የተናገረው ትንቢት ከቅዱስ ጳውሎስ አባባል ጋር ተመሳሳይ ነው። የሚከተለውን የነቢዩ የኤርምያስን ትንቢት እንመልከት "እነሆ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ይላል እግዚአብሔር፤ ይህም ቃል ኪዳን እነርሱን ከግብጽ ለማውጣት እጃቸውን በያዝሁ ጊዜ እንደገባሁት ቃል ኪዳን ያለ አይደለም፤ እነርሱ በቃል ኪዳኔ ስላልጸኑ እኔም ችላ አልኳቸው፤ እነሆ ከዚህ ጊዜ በኋላ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነው:- ሕጌን በልቦናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፤ አምላካቸውም እኾናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይኾናሉ። እግዚአብሔርን ዕወቅ ብሎ ባልንጀራውንም ኾነ ወንድሙን የሚያስተምር ማንንም አይኖርም፤ ምክንያቱም ከትልቁ ጀምሮ እስከ ትንሹ ኹሉም ያውቁኛል፤ ክፋታቸውን ይቅር እልላቸዋለሁ፤ ኀጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስታውሳቸውም፤ እኔ እግዚአብሔር ይህን ተናግሬአለሁ። (ኤር. ም. 31 ቁ. 31–34)

እንዲሁም ነቢዩ ሕዝቅኤል እንዲህ ብሏል :- "ለሚፈጽመው ኹሉ ሕይወት የሚያስገኝለትን ትእዛዛቴን ሰጠኋቸው፤ ሕግጋቴንም አስተማርኳቸው :- ነገር ግን በበረሃ ሳሉ እንኳ በእኔ ላይ ዐመፁ፤ ለሚፈጽመው ኹሉ ሕይወትን የሚያስገኝለትን ትእዛዜን አፈረሱ፤ ሕጌንም ጣሱ።" (ሕዝ ም. 20 ቁ. 11–13)

ሙሴ ዐሥሩ ትእዛዛት የተጻፉባቸውን ኹለት ጽላቶች ይዞ ከሲና ተራራ ላይ በወረደ ጊዜ ፊቱ በማንጸባረቁ የእስራኤል ልጆች ትክ ብለው ሊመለከቱት አልቻሉም። ይህም የኾነው በዚያን ጊዜ ለተሰጠው ሕግ ክብር ነበር። ያ ሕግ ግን በሥራ ላይ መዋል ሲገባው ማንም ሰው ሥራ ላይ ሊያውለው ባለመቻሉ ሞትንና ኵነኔን አምጥቶአል ተብሏል። የአምላካችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቢዛት ግን በጸጋ ጽድቅ ንና ሕይወትን ማስከተሉን በመዘርዘር ቅዱስ ጳውሎስ ብሉይ ኪዳንንና ሐዲስ ኪዳንን አነጻጽሮአል።



www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ገላትያ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. 2 ቁ. 21 ላይ "ሰው የሚጸድቀው ሕግን በመፈጸም ከኾነማ ክርስቶስ የሞተው በከንቱ ነው ማለት ነው" በሚለውና በሌሎችም የተለያዩ ጥቅሶች ምክንያት እኛ ክርስቲያኖች በፍጹም ሕግ የማያስፈልገንና በእምነታችንና በእግዚአብሔር ጸጋ የዳንን በመኾናችን ሕገ እግዚአ ብሔርን ብንጠብቅም ባንጠብቅም ምንም ልዩነት የሌለው ይመስለን ይኾናል። ይህ ላለመኾኑ ግን ብዙ ማስረጃዎች ያሉ ቢኾንም ለጊዜው ጥቂቶቹ ብቻ የቀረቡ ስለኾነ እንመልከታቸው።

"በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ የሚለኝ ኹሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።" (ማቴ. ም. 7 ቁ. 21)

"ወደ ሕይወት ትገባ ዘንድ ብትፈልግ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ።» (ማቴ. ም. 19 ቁ.17)

"ብትወዱኝ ትእዛዞቼን ጠብቁ" (ዮሐ. ም. 14 ቁ. 15)

"እያንዳንዱ በሥጋው ላደረገው ክፉም ኾነ ደግ ነገር እንደየሥራው ዋጋውን ለመቀበል ኹላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መቅረብ አለብን።" (2ኛ. ቆሮ. ም. 5 ቁ. 10)

"አገልጋይም ኾነ ጌታ እያንዳንዱ በሠራው መልካም ሥራ ከጌታ ኢየሱስ ዋጋውን የሚቀበል ለመኾኑ እርግጠኞች ኹኑ።" (ኤፌ. ም. 7 ቁ. 8)

ታዲያ በአንድ በኩል ያለ ሕግ ሥራ በነጻ እንደዳንን እየተገለጠ በሌላ በኩል ደግሞ የሚፈረድልን ወይም የሚፈረድብን በተግባራችን መኾኑ የተነገረው እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በትንቢተ ኢሳይያስ ም. 64 ቁ. 7 ላይ:- "የአንተን ርዳታ ለማግኘትና ለመጻለይ ከእኛ ወደ አንተ የተመለሰ ማንም የለም፤ ከኀጢአታችን ብዛት የተነሣ ተውከን፤ ፊትህንም ሰወርክብን።"



በትንቢተ ሆሴዕ ም. 7 ቁ. 7 ላይ "ኹሉም በቁጣ እንደምድጃ ግለው ገዢዎቻቸውን ፈጁ፤ ነገሥታቶቻቸውንም በየተራ አጠፉ፤ ይህም ኹሉ ሲኾን ከእነሱ አንድ እንኳ የእኔን እርዳታ የጠየቀ የለም።"

በትንቢተ ሶፎንያስ ም. 1 ቁ. 6 ላይ "ከእኔ የራቁትን እኔን መከተል የተውትንና ወደ እኔም መጥተው እኔ እንድመራቸው ያልጠየ ቁኝን አጠፋለሁ።"

በማቴዎስ ወንጌል ም. 23 ቁ. 37 ላይ :- "ኢየሩሳሌም፥ ኢየሩሳሌም ሆይ ፥ ነቢያትን የምትገድዪ ወደ አንቺ የተላኩትንም በድንጋይ የምትወግሪ ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ ሥር እንደምት ሰበስብ እኔም ያንቺን ልጆች በአንድነት ለመሰብሰብ ስንት ጊዜ ፈለግሁ እናንተ ግን አልፈለጋችሁም።"

በማቴዎስ ወንጌል ም. 6 ቁ. 13 ላይ ለደቀ መዛሙርቱ ባስተማረው ጸሎት ውስጥ "ወደፈተና አታግባን ከክፉ አድነን እንጂ" የሚለው ዐረፍተ ነገር ይገኝበታል።

በማቴዎስ ወንጌል ም. 7 ቁ. 7–8 ላይ:- "ለምኑ ይሰጣችኋል ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያ አንኳኩ ይከፈትላችሁማል፤ የሚለምነው ኹሉ ይቀበላልና፤ የሚፈልገውም ያገኛል፤ መዝጊያም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል።"

በዮሐንስ ወንጌል ም.1 ቁ. 29 ላይ:- "እነሆ የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ይህ ነው።"

በሐዋርያት ሥራ ም. 22 ቁ. 16 ላይ "ታዲያ አሁን ለምን ትዘገያለህ? ተነሥና የእርሱን ስም በመጥራት ተጠመቅ፤ ከኀጢአትህም ታጠብ።"

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከጥንቱ በደል ለመቤዠት ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ የእኛን ሥጋ በመልበስ ከሰው ልጆች ጋር ተዛምዷል። የሰው ልጆች ከጥፋት የሚድኑበትንም ኹናቴ አመቻችቶላቸዋል። የሚጠበቅብንን ድርሻ ካልተወጣን ግን



www.ethiopianorthodox.org

ፈተናና ችግር እንደሚገጥመን የታወቀ ነው። ፈተና ደግሞ በማንም ላይ የማይቀር መኾኑን ሲያመለክት ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. 7 ቁ. 14 ፥15፥17–20 እና 24 ላይ እንዲህ ብሏል።

"ሕግ መንፈሳዊ መኾኑን እናውቃለን። እኔ ግን የኀጢአት ባሪያ ለመኾን የተሸጥሁ ሥጋዊ ነኝ። እኔ የማደርገውን አላውቅም፤ ምክን ያቱም የምወደውን ነገር ማድረግ ትቼ የምጠላውን ነገር አደርጋለሁ ማድረግ የማልፈልገውን ነገር የሚያደርገው በእኔ ውስጥ ያለው ኀጢአት ነው እንጂ እኔ አይደለሁም። በእኔ (በእኔ ሥጋዊ ባሕርይ) ምንም መልካም ነገር እንደሌለ ዐውቃለሁ፤ ምክንያቱም ምንም እንኳ መልካም ነገር የማድረግ ፍላጎት ቢኖረኝ ያንን መልካም ነገር የማድረግ ችሎታ የለኝም። ማድረግ የምፈልገውን መልካም ነገር አላደርግም፤ ነገር ግን የማልፈልገውን ክፉ ነገር አደርጋለሁ። እንግዲህ ማድረግ የማል ፈልገውን ክፉ ነገር የማደርግ ከኾንኩ ይህን የሚያደርገው በእኔ ውስጥ ያለው ኀጢአት ነው እንጂ እኔ አይደለሁም ማለት ነው። እኔ ምንኛ ጐስ ቋላ ሰው ነኝ! ወደ ሞት ከሚወስደኝ ከዚህ ሰውነትስ ማን ያድነኛል?" ይህን የጻፈው ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ነው።

ቀደም ብለው የቀረቡት የተለያዩ ጥቅሶች የሚያመለክቱት እኛ በራሳችን ጥረት ብቻ ለመዳን ችሎታ የሌለን መኾኑን ነው። በችግራችን ኹሉ የእግዚአብሔርን ርዳታ መጠየቅ እንዳለብን ያመለክተናል። በትን ቢተ ኢሳይያስ፥ በትንቢተ ሆሴዕና በትንቢተ ሶፎንያስ ላይ የእስራኤል ልጆች የተወቀሱት የእግዚአብሔርን ርዳታ ባለመጠየቃቸው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈሳዊና በሥጋዊ ሰውነታችን መካከል ምን ያኽል ትግል የሚካኼድ መኾኑን አመልክቷል። ጌታ ደግሞ ኢየሩ ሳሌምን ለማዳን ምን ያኽል ይፈልግ እንደነበረና እነርሱ ግን በተሰ ጣቸው የፈቃድ ነጻነት መሠረት አለመፈለጋቸውን ገልጾአል። ሥጋዊ ሰውነታችን መንፈሳዊውን ሰውነታችንን ድል ነሥቶት ወደ ሞት እንዳናመራ የእግዚአብሔርን ርዳታ የምንጠይቀው ወደፈተና አታግባን ከክፉ አድነን እንጂ ብለን እንድንጸልይ መድኀኒታችን ባስተማረን መሠረት ነው። ጸሎታችንም ተሰሚነትን እንደሚያገኝ አረጋግጦልናል።



ከቀድሞዎቹ የአሪት አማኞች የተሻለ ዕድል ያለን መኾናችን አይካድም። በጌታ ቤዛነትና በዳግማዊ ልደት ከጥንቱ የአዳም ኀጢአት ነጻ ኾነናል። እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጆች ለመኾን በቅተናል። በሜሮኑም ቅባት አማካይነት ከኀጢአት የሚጠብቀንን መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል።

ምንም እንኳ ከሥጋ ደካማነት የተነሣ ሰውነታችን የኀጢአት ዝንባሌ ቢኖረው ከጌታችን ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በኋላ በተለያዩ ኹናቴዎች ወደ ራሱ ስላቀረበን ከፈተናና ከክፉ ኹና ቴዎች እንዲጠብቀን ብንለምነው በቃሉ ታማኝ ስለኾነ በእምነታችን ያጠነክረናል፤ ሕጉንም ለመታዘዝ ችሎታውን ይሰጠናል። በዚህም መሠረት ቅዱስ ጳውሎስ ከብሉይ ኪዳን ሐዲስ ኪዳን የሚበልጥ መኾኑን መግለጹ ሊያስገርመን አይገባም።

87. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው በኹለተኛው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. 11 ቁ. 17 ላይ :- "የምናገረው እንደ ጌታ ፈቃድ ሳይኾን እንደሞኝ ኾኜ ነው" ካለ በኋላ ለጢሞቴዎስ ኹለተኛ በጻፈው መልእክቱ ም. 3 ቁ. 16 ላይ "ቅዱስ መጽሐፍ በሙሉ በእግዚ አብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ ነው" በማለቱ ኹለቱ አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃ ረኑ ይመስለን ይኾናል።

እንደ ጌታ ፈቃድ ሳይኾን እንደሞኝ ኾኜ ነው ማለቱ ራስን ማመ ስገን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም ለማለት ነው እንጂ ጽሑፎቹ ኹሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ወይም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ያልተጻፉ ናቸው ለማለት አይደለም።

እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ "ራሱን የሚያዋርድ ኹሉ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው" የሚሉትን የጌታን አባባሎች ወደጐን በመተው ስለራሴ ሥራ ከሌሎች ጋር በማወዳደር መናገሬ የራሴ ሞኝነት እንጂ እግዚአብሔር ፈቅዶልኝ ያደረግሁት ድርጊት አይደለም ማለቱ ነው። ማቴ ም. 16 ቁ. 24 ፥ ም. 18 ቁ. 41)



www.ethiopianorthodox.org

ታዲያ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለራሱ መናገር ለምን አስፈለገው? ሐዋርያው ጳውሎስ ስለራሱ መናገር ግድ የኾነበት ምክንያት የሐሰተኞች መምህራንን ሐሳብ ለመቃወም ብሎ እንጂ ራሱን ለማመስገን በማሰብ አይደለም። በዚሁ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው ኹለተኛ መልእክቱ ምዕራፍ 16 ላይ ትክ ብለን ብናስተውል ሐሰተኞች መምህራን ተነሥተው በአንድ በኩል የሐዋርያውን የጳውሎስን ስም የሚያጠፉና በሌላ በኩል ደግሞ ሐሰተኛ ትምህርትን ለማስፋፋት የሚሞክሩ እንደነበረ ልናስተውል እንችላለን።

የሐሰተኞች መምህራን ትምህርት ምእመናንን ይጐዳ ይኾናል ብሎ የነበረውን ስጋት ሲገልጥ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- "እባብ ሔዋንን በተንኰሉ እንዳታለላት፥ ምናልባት የእናንተም አሳብ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ያላችሁን ቅንነትና ንጽሕና ትተዋላችሁ ብዬ እፈራለሁ። ምክንያቱም አንድ ሰው ወደ እናንተ መጥቶ እኛ የሰበክነውን ሳይኾን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክላችሁ ወይም የተቀበላችሁትን መንፈስ ሳይኾን ሌላ መንፈስ ብትቀበሉ ወይም የተቀበላችሁትን የምሥራች ቃል ሳይኾን ሌላ ብትቀበሉ ዝም ብላችሁ ትታገሣላችሁ።" (2ኛ ቆሮ. ም. 11 ቁ. 3–4)

ሐሰተኞች መምህራን በመጀመሪያ ሐዋርያውን ካጥላሉና ስሙን ካጠፉ በኋላ የክርስቶስ ቤተሰብ ኾነው የነበሩትን ምእመናን ለማሳሳት በሚሞክሩበት ጊዜ ምእመናንን ላለማስነጠቅ ቅዱስ ጳውሎስ የነበረው ምርጫ በእርሱ ላይ የተደረገው የስም ማጥፋት ተንኰል ትክክል አለመኾኑንና እርሱ ግን እንዴት ያለ ሰው መኾኑን መግለጽ ነበር። በእርግጥ ማንነቱን ሌላ ሰው ሲገልጥለት በተገባ ነበር። ነገር ግን በምዕራፍ 12 ቁ. 11 ላይ እንደገለጸው የእርሱን ማንነት አብራርቶ የሚገልጽ ሌላ ሰው ባለገመገኘቱ ነው ስለራሱ መናገር ግድ የኾነበት።

በዚህም መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ያለጌታ ፈቃድ እንደሞኝ ሰው እናገራለሁ ማለቱ ከንግግሩ አስቀድሞ ትሕትናውን መግለጹ ከመኾኑ በቀር ቅዱሳት መጻሕፍት ኹሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፉ ናቸው የሚለውን አባባል የሚቃረን አይደለም።



# ወደገላትያ ሰዎች የተላከ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት

ይህ መልእክት ስድስት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በኹለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 3 ድረስ ሲኾን የወንጌል ትምህርቱን የተቀበለው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ እጅ እንጂ ከሐዋርያት አለመኾኑንና በዚህም ከማንኛውም ሐዋርያ የማያንስ መኾኑን ገልጾአል።

ኹለተኛው ክፍል ደግሞ ከምዕራፍ 4 እስከ ምዕራፍ 6 ድረስ ሲኾን በዚህ ክፍል ድኅነት የተገኘው በነጻ እንጂ የሙሴን ሕግ በመፈጸም አለመኾኑን ገልጾአል።

## ጥያቄና መልስ

88. ወደ ገላትያ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. 6 ቁ. 2 ላይ "እርስ በርሳችሁ በመተጋገዝ ከእናንተ እያንዳንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም ይሸከም ካለ በኋላ በቁ. 5 ላይ :- "እያንዳንዱ የራሱን ሸክም መሸከም አለበት" በማለቱ ኹለቱ አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስላሉ።

በቁጥር ኹለት ላይ የተገለጸው ራስ ወዳድ ላለመኾንና የጌታን ቃል መፈጸም ሲኾን በቁጥር 5 ላይ የተገለጸው ግን ንግግራችን፥ ሥራችንና እንቅስቃሴአችን ኹሉ ክርስቲያናዊ ኺደት እንዲኖረው የግል ኀላፊነትን ሸክም እንድንሸከም ግዴታችን መኾኑን ያመለክተናል።

በዚህም መሠረት ኹለቱ አባባሎች ለኹለት የተለያዩ ጉዳዮች ከመነገራቸው በቀር እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።



www.ethiopianorthodox.org

## ወደ ኤፌሶን ሰዎች የተላከ የሐዋርያዉጳውሎስ መልእክት

ይህ መልእክት 6 ምዕራፎች ያሉት ኹኖ በኹለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 3 ድረስ ሲኾን በእርሱም ስለመሠረታዊ እምነት ሥርዐት፥ መጽደቅና መዳን በክርስቶስ ደም መኾኑ ተገልጾበታል።

ኹለተኛው ክፍል ደግሞ ከምዕራፍ 4 እስከ ምዕራፍ 6 ድረስ ሲኾን በውስጡም መከተል የሚኖርብን በጎ ተግባር፥ ለምሳሌ ርኩሳን መናፍስትን ለመዋጋት የሚረዳን መሣሪያ የኾነውን ጸሎት እንድናካኼድ ይመክረናል።

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

89. ወደ ኤፌሶን ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. 1 ቁ. 17 እና በመጀመሪያይቱ የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት ም. 1 ቁ. 3 ላይ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ የተባለ ሲኾን በዮሐንስ ወንጌል ም. 1 ቁ. 1፥ በሐዋርያት ሥራ ም. 20 ቁ. 28፥ ወደ ሮሜ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. 2 ቁ. 13 እና በመጀመሪያይቱ የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ም.5 ቁ. 20 ላይ ጌታ ራሱ እግዚአብሔርና አምላክ በመባሉ አባባሎቹ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስል ይኾናል።

ቀደም ተብሎ በሌሎች አርእስት እንደተገለጸው ጌታ የሰውን ልጅ ሥጋ በለበሰ ጊዜ መለኮት ትስብእትን የተወሐደው ያለመጠፋፋት፥ ያለመቀላቀልና ያለመለዋወጥ ስለኾነ ስለጌታ በሚነገርበት ጊዜ እንደፍ ጹም አምላክነቱ ወይም እንደፍጹም ሰውነቱ ስለሚነገር ሊያስገር መንና ሊያስደነግጠን አይገባም። ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው መኾኑን መገንዘብ አለብን። ለምሳሌ በዮሐንስ ወንጌል ም. 15 ቁ. 1 ላይ እርሱ



ስለራሱ "እኔ እውነተኛ የወይን ግንድ ነኝ፤ አትክልተኛውም አባቴ ነው" በሚልበት ጊዜ የክርስትና እምነት በእርሱ አዳኝነት ላይ ተመሥርቶ የማይቀበለው ካለ የሚፈረድበት መኾኑንና አባቴ በሚልበት ጊዜ መለኮትን የሚያመለክት ሲኾን የወይን ግንድነቱ ግን ትስብእቱ ነውና የወልድ ከአብ ማነስ ኹኖ መገመት የለበትም። እንዲሁም በሐዋርያት ሥራ ም. 10 ቁ.38 ላይ እግዚአብሔር ጌታን ቀባው በሚልበት ጊዜ ትስብእቱን እንጂ መለኮቱን አይደለም። አንድ ሰው የሹመት ቅባት የሚቀባው አንድ የተወሰነ መንፈሳዊ ወይም መንግሥታዊ ክብር ሲሰጠው ነው። ሟች፥ ፈራሽና በስባሽ የኾነው የሰው ልጅ ሥጋ ከመለኮት ጋር ተዋሕዶ እንዲያደርግ እግዚአብሔር አከብሮ የእግዚአ ብሔር ልጅ ለመባል ስላበቃው ተቀባ ተባለ እንጂ መለኮትማ የክብር ጌታ ነው።

በሌላ ጊዜ ደግሞ በዮሐንስ ወንጌል ም. 5 ቁ. 19 ላይ "አብ ሲሠራ ያየውን ከመሥራት በቀር ወልድ በራሱ ሥልጣን ምንም አይሠራም። አብ የሚያደርገውን ወልድም እንዲሁ ያደርጋል" ማለቱ ወልድ ከአብ ያነሰ ክብር አለው ማለት ሳይኾን አብና ወልድ ፍጹም መለኮታዊ አንድነት ይኸውም የፈቃድ አንድነት ስላላቸው ስለመለኮታዊ አንድነ ታቸው መናገሩ ነው።

ታዲያ ከላይ የተጠቀሱትን አባባሎች እንደማስረጃነት በማቅረብ አብ ከወልድ በላይ እንደኾነና ጌታ ደግሞ መቼም ቢኾን ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል አድርጎ እንዳልገመተ በማስመሰል የሚከራ ከሩ ወገኖች አሉ።

ጌታ ግን መለኮታዊ ክብር ያለው መኾኑን በልዩ ልዩ ኹናቴዎች የገለጸ ሲኾን ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

በሲና ተራራ ላይ የሃይማኖት ሕግጋትን የሰጠው የሕግጋቱ ባለቤት እግዚአብሔር አምላክ መኾኑ የታወቀ ነው። ታዲያ ከሕግጋት አንዱ ስለኾነው ስለሰንበት መከበርና መሻር ጉዳይ ፈሪሳውያን ባነጋገሩት ጊዜ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነው የሚል መልስ መስጠቱ ቀድሞውንም ቢኾን ሰንበት እንዲከበር ትእዛዝ ያስተላለፍሁ እኔው ነኝ ማለቱ ነው። (ማቴ. ም. 12 ቁ.8)



www.ethiopianorthodox.org

አይሁድ ጌታን ሊገድሉ የፈለጉበት ዋነኛው ምክንያት ቅዳሜን በመሻሩ ብቻ ሳይኾን ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር በማስተካከሉ ነው ተብሏል። (ዮሐ.ም. 5 ቁ. 18)

ጌታ የተቸነከሩ እጆቹንና የተወጋ ጐኑን ባሳየው ጊዜ ሐዋርያው ቶማስ ጌታዬ አምላኬ ብሎ መልስ ሲሰጠው ለምን አምላክ ትለኛለህ ብሎ የገሠጸው ሳይኾን እንዲያውም በእኔ አምላክነት የምታምነው ስላየኸኝ ነውን? ሳያዩኝ በእኔ የሚያምኑ ግን የተመሰገኑ ናቸው በማለት አምላክነቱን አረጋግጦለታል። (ዮሐ. ም. 20 ቁ. 28–29)

ስለዚህ በመጀመሪያ ላይ የተጠቀሰውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ የሚለው አባባል አንድም ትስብእቱን በሚመለከት የተነገረ ነው ያለበለዚያም ቀድሞ ሳናውቀው ኖረን ጌታችን እንድናውቀው ያደረገን አምላክ ማለት ነውና አባባሎቹ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም። (ዮሐ. ም.1 ቁ. 18) ጥያቄና መልስ ቁ. 8 ፥ 18 ፥ 27 ፥ 36 ፥ 48 ፥ 57 ፥ 61 ፥ 63 ፥ 72 ፥ 74 ፥ 75 91 ፥ 92 ፥ 93 ፥ 102 እና በአንደኛው መጽሐፍ ቁ. 102 ፥ 104 ፥ 112 ይመለከቷል።

90. ወደ ኤፌሶን ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ የጳውሎስ መልእክት ም.4 ቁ. 26 ላይ ቁጣን የሚፈቅድ ሲኾን በቁጥር 31 ላይ ደግሞ ቁጣን የሚከለክል ስለኾነ አባባሎቹ ርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስላል።

በመጀመሪያው ጥቅስ ላይ ተቈጡ ካለ በኋላ ኀጢአትን አታድርጉ ይላል። ይህም ማለት ቁጣችሁም ወደ ኀጢአት የሚመራችሁ አይኹን ማለቱ ነው። እንዲያውም በሚቀጥለው ቁጥር ማለት በቁጥር 27 ላይ "በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፤ ለዲያብሎስም ፋንታ አትስጡት" ይላል። ቁጣው የተፈቀደው ኀጢአት ወደ መሥራት የማያመራ እንደኾነ ብቻ ነው። ለኀጢአት ሳይኾን ለእግዚአብሔር ክብር ከኾነ ቁጣው ይፈቀዳል። ለምሳሌ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበት ቀን አንዱን ሕመምተኛ ለመፈወስ ተዘጋጅቶ በነበረበት ጊዜ ለክስ ምክንያት ለማግኘት ይጠባበቁት የነበሩትን ፈሪሳውያን በቁጣ እንደ ተመለከታቸው በማርቆስ ወንጌል ም.3 ቁ. 5 ላይ ተገልጾአል።



በቁጥር 31 ላይ የተከለከለው ቁጣ ደግሞ እንዲህ ተብሎ ነው፦ "መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም፥ መሳደብም ኹሉ ከክፋት ኹሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ።" የተከለከለውን ቁጣ በተመለከተ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሦስት ደረጃ ከፍሎታል።

1/ በወንድሙ የሚቆጣ ኹሉ ፍርድ ይገባዋል።

2/ ወንድሙን ጨርቃም የሚለው ኹሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል።

3/ ደንቆሮ የሚለውም ኹሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል። (ማቴ. ም. 5 ቁ. 22)

አሁን እንግዲህ መቆጣት የተከለከለው ቁጣው ወደ ኀጢአት የሚያመራ እንደኾነ ነውና ኹለቱ ጥቅሶች ርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

## ወደ ፊልጵስዮስ ሰዎች የተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት

ይህ መልእክት 4 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ ክሐስተኞች መምህራን እንዲጠነቀቁና በመካከላቸው ያለውን ጠብና መለያየት አስወግደው በፍቅር እንዲኖሩ ምክር ተሰጥቶበታል።

## ጥያቄና መልስ

91. "እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፤ ነገር ግን የባርያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ኾኖ ራሱን ባዶ አደረገ።" (ፊልጵ. ም. 2 ቁ. 6–7)



www.ethiopianorthodox.org

ከእግዚአብሔር አብ ጋር በመለኮታዊ ባሕርዩ እኩል ነው እንጂ በመቀማት የሚያገኘው አይደለም። ኾኖም በትሕትና ራሱን ዝቅ አድርጎ ሰው በመኾን ሕማምና ሞት እንዲደርስብት ስለፈቀደ ራሱን ባዶ አደረገ አሰኝቶታል። ሕማምና ሞት የማይደርስበት አምላክ በለበሰው ሥጋ ሕማምና ሞት ደርሰውበታል። ይህንንም ያደረገው እርሱ ምንም የሚያስፈልገው ነገር ኖሮት አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው እርሱ ሀብታም ሲኾን እኛ በእርሱ ድኽነት ባለጠጎች እንኾን ዘንድ ስለ እኛ ድኻ ኾነ (2ኛ. ቆሮ. ም. 8 ቁ. 9) ጥያቄና መልስ ቁ. 8፥18 ፥27፥ 36፥ 48፥ 57፥ 61፥ 63፥ 72፥ 74፥ 75፥ 84 ፥ 89 ፥ 91 ፥ 93 ፥102 እና ከአንደኛው መጽሐፍ ቁ. 102 ፥ 104 ፥ 112 ይመለከቷል።

## ወደ ቆላስይስ ሰዎች የተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት

ይህ መልእክት አራት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በኹለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 3 ድረስ ሲኾን በውስጡ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ክብር፥ ከአብ ጋር ስላለው እኩልነትና ኹሉም ነገር በእርሱ የተፈጠረ ስለመኾኑ፥ የሙሴ ሕግ በምሳሌነት የነበረና በሕግጋቱ ፈጣሪ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ያበቃ መኾኑና ከእንግዲህ ወዲያ አስፈላጊ አለመኾኑ ተገልጾአል።

ኹለተኛው ክፍል ምዕራፍ አራት ሲኾን በእርሱም ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ለሌላው ሰው ያለበትን ግዴታ የሚያመለክት ነው።





92. ወደ ቆላስይስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም.1 ቁ.18 – 19 ስለመድኀኒታችን መለኮታዊ ክብር በተሰጠው ገለጻ ላይ "እርሱ አካሉ የኾነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፤ በኹሉ ነገር የመጀመሪያ እንዲኾን ከሞት በመነሳትም ፊተኛና መጀመሪያ ነው። ይህም የኾነው የመለኮት ሙላት በልጁ እንዲኖር የእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ስለኾነ ነው" የሚለው አባባል በራእየ ዮሐንስ ም.22 ቁ.12 እና 13 ላይ "እነሆ እኔ በቶሎ እመጣለሁ ለያንዳንዱ እንደ ሥራው የምሰጠውን ዋጋ ይገኛለሁ፤ አልፋና ዖሜጋ፤ ፊተኛውና ኋለኛው፤ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ" ከሚለው አባባል ጋር ተቃራኒ ይመስለን ይኾናል።

በራእየ ዮሐንስ ም.1 ቁ:8 እና 11 እንዲሁም በምዕራፍ 22 ቁ:13 ላይ የተነገረው አልፋና ኦሜጋ ወይም የመጀመሪያና የመጨረሻ ነኝ ያለው ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑ ግልጽ ሲኾን ይህን ቋንቋ ከድሮ ጀምሮ የሚናገርበት ፈጣሪ አምላክ መኾኑን በትንቢተ ኢሳይያስ ም.41 ቁ:4፥ ም.44 ቁ:6 እና ም.48 ቁ:12 ለመመልከት እንችላለን።

ከድሮ ጀምሮ የእግዚአብሔር ገንዘቡ የኾኑት ስሞችና አነጋገሮች የመድኀኒታችንም ስሞችና አነጋገሮች ከኾኑ እንዴት ታዲያ የመለኮት ሙላት በልጁ እንዲኖር የእግዚበአሔር አብ ፈቃድ ኾነ ተባለ?

ከምሥጢረ ሥጋዌ እንደተማርነው እግዚአብሔር ወልድ መለኮትንና ትስብእትን ባዋሐደ ጊዜ ያልተቀላቀለና ያልተጠፋፋ ተዋሕዶ በመኾኑ ስለ ጌታችን፥ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲነገር እንደ ፍጹም አምላክነቱ ወይም እንደ ፍጹም ሰውነቱ ሊነገር ሊያስገ ርመን አይገባም፤ ሰው የኾነ አምላክ ነውና። የመለኮት ግብር ለእግዚ አብሔር አብ ገንዘቡ ኾኖ በሚነገርበት ጊዜ የአብ፥ የወልድ፥ የመንፈስ ቅዱስ ግብር እንጂ የአብ ግብር ብቻ እንደኾነ ተደርጎ መታየት የለ በትም። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም በመወለድ መለኮትን ከትስብእት ጋር ያዋሐደው በአብ፤ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ



www.ethiopianorthodox.org

ፈቃድ እንጂ በአብ ፈቃድ ብቻ አይደለም። በዚህም በመለኮታዊ ፈቃድ መሠረት የመለኮት ሙላት በትስብእት እንዲኖር የሦስቱም ፈቃድ ኾነ። የመለኮታዊው ግብር የአብ ግብር ብቻ አለመኾኑን ሲያመለክት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል "አባቴ ኹልጊዜ ይሠራል፤ እኔም እሠራለሁ።" (ዮሐ.ም.5 ቁ:17)

ስለዚህ ወደ ቆላስይስ ሰዎች በተላከው መልእክት ም.1 ቁ.19 ላይ የመለኮት ሙላት በልጁ እንዲኖር የእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ኾነ በሚልበት ጊዜ የመለኮት አፍአዊ ግብር እንደመኾኑ የሦስቱም ፈቃድ እንጂ የእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ብቻ አለመኾኑን ተረድተን ከመሳሳት እንጠንቀቅ። ጥያቄና መልስ ቁ.8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥ 57፥ 61፥ 63፥ 72፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 93፥ 102፥ እና ከአንደኛው መድሐፍ ቁ.102፥ 104፥ 112 ይመለከቷል።

## በመጀመሪያ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት

ይህ መልእክት 5 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በኹለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ ሦስት ድረስ ሲኾን ምእመናን በእምነታቸው ስለጸኑ ካመሰገናቸው በኋላ ይህን ለማድረግ የረዳቸውን እግዚአብሔርን አመስግኗል። እንዲሁም በእምነ ታቸው ጸንተው እንዲኖሩና ፈተናን እንዲቋቋሙ መክሮአቸዋል።

ኹለተኛው ክፍል ምዕራፍ 4 እና ምዕራፍ 5 ሲኾን በዚህ ክፍል ስለትንሣኤ ሙታን፥ ስለጌታ ዳግመኛ መምጫ ጊዜና ስለፍርድ ቀን እም ነት ተዘርዝሮአል።





93. ወደተሰሎንቄ ሰዎች በተላከው በመጀመሪያው መልእክት ም.1 ቁ:10 ላይ "እግዚአብሔር ከሞት ያስነሣውን... የልጁን የኢየሱስን ከሰማይ መምጣት"፥ በምዕራፍ 4 ቁ:14 ላይ "በኢየሱስ አምነው የሞቱትን እግዚአብፅሔር ከኢየሱስ ጋር ያመጣቸዋል» የተባለውንና በሐዋርያት ሥራ ም.2 ቁ:24፥ 32፥ ም.2 ቁ:15፥ ም.4 ቁ:10፥ ም.10 ቁ.40፥ ም.13 ቁ:30 – 34፥ ም.17 ቁ:31፥ ሮሜ ም.4 ቁ:24፥ ም.8 ቁ:11፥ 1ኛ ቆሮ. ም.6 ቁ:14፥ ም.15 ቁ:15፥ 2ኛ ቆሮ. ም.4 ቁ:14፥ ገላ.ም.1 ቁ:1፥ ኤፌ. ም.1 ቁ:20፥ ቆላ.ም.2 ቁ:12፥ 1ኛ ተሰ.ም.1 ቁ:10፥ ዕብ.ም.13 ቁ:20፥ 1ኛ ኮጥ.ም.1 ቁ:21 የተነገሩትን ተመሳሳይ አባባሎች በመመልከት ጌታ በራሱ ከሞት የመነሣት ኀይልና ሥልጣን እንደሌለው የሚመስላቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችሉ ይኾናል።

በተለያዩ ጥያቄዎች ተመላልሶ እንደተገለጸው ጌታ ሰው የኾነ አምላክ በመኾኑ ስለእርሱ በሚነገርበት ጊዜ እንደፍጹም ሰውነቱ ወይም እንደ ፍጹም አምላክነቱ ይነገራል። ትስብእት ብቻውን ከሞት ሊነሣ የማይችል በመኾኑ በመለኮት ኀይልና ሥልጣኑ የተዋሐደውን ትስብእት ከሞት አስነሣው እንጂ በሦስቱ አካሎች መካከል የሥልጣን መበላለጥ ኖሮ አይደለም።

ጌታም በራሱ ፈቃድ እንደሚሞትና በራሱም ፈቃድ ከሞት እንደሚነሣ በግልጽ ሲያብራራ በዮሐንስ ወንጌል ም.2 ቁ:19 ላይ "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱትና እኔ በሦስት ቀን እሠራዋለሁ" በምዕራፍ 10 ቁ.18 ላይ ደግሞ "ሕይወቴን በፈቃዴ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ የሚወስዳት ማንም የለም፤ ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ መብት አለኝ" ብሏል።

እግዚአብሔር የሚለው ቃል የሥሉስ ቅዱስ የጋራ ስም እንደመኾኑ የእግዚአብሔር አፍአዊ ድርጊት ኹሉ የሥሉስ ቅዱስ መለኮታዊ አንድነት ግብር መኾኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ጥያቄና መልስ ቁ.8፥ 18፥ 27፥ 36፥ 48፥ 57፥ 61፥ 63፥ 72፥ 74፥ 75፥ 84፥ 89፥



www.ethiopianorthodox.org

91፥ 92፥ 102 እና ከአንደኛው መጽሐፍ ቁ.102፥ 104፥ 112 ይመለከቷል።

## ኹለተኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት

ይህ መልእክት ሦስት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ትንሣኤ ሙታን እንደሚኾንና ጌታም ለፍርድ እንደሚመጣ በማመን ሥራን ኹሉ አቁመው ስለነበረ ይህንኑ የተሣሣተ እምነት የሚያርም ነው። ስሕተቱ ሊደርስ የቻለው አንድም የመጀመሪያውን መልእክት በትክክል ስላልተረዱት ነው ወይም ደግሞ ሐሳውያን መምህራን ስላሳሳቱአቸው ነው።

### ጥያቄና መልስ።

94. በምዕራፍ 2 ቁ:11 — 12 "እውነት ያልኾነውን እንዲያምኑ የሚያሳስታቸውን ኀይል እግዚአብሔር የሚልክባቸው ከፋትን መርጠው እውነትን እንቢ ባሉት ኹሉ ላይ ለመፍረድ ነው" ካለ በኋላ በመጀመሪያ ወደ ጢሞቴዎስ በላከው መልእክቱ ም.2 ቁ:3 — 4 "ሰዎች ኹሉ ሊድኑና እውነትን ወደማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኀኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው" በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ ይመስሉን ይኾናል።

በኹለቱ ጥቅሶች መካከል ልዩነት የለም። እግዚአብሔር ኹሉም ይድን ዘንድ ስለፈቀደ ነው አንድያ ልጁን ለዓለም ቤዛነት አሳልፎ የሰጠው። (ዮሐ.ም.3 ቁ:16) እንዲሁም ንስሐን፥ እምነትንና በጎ ተግባርን የመሳሰሉ ልዩ ልዩ ኹኔታዎችን ላሰው ልጆች ያመቻቸላቸው እግዚአብሔር ሰው ኹሉ ይድን ዘንድ ፈቃዱ ስለኾነ ነው። ማንም ይጠፋ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ባለመኾኑ የክርስቶስን ቤዛነት ቢያቀርብለትም የሰው ልጅ ግን በተሰጠው ነጻ ፈቃድ አማካይነት የድኅነትን መንገድ ላለመቀበል እንቢተኛ መኾኑ የተገለጸው በሚከተለው ኹናቴ



ነው። "ፍርዱም ይህ ነው፤ ብርሃን ወደ ዓለም መጣ፤ ሰዎች ግን ሥራቸው ክፉ ስለኾነ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ" (ዮሐ.ም.3 ቁ:19)

በሌላ ጊዜ ደግሞ "ሕይወት ይኾንላችሁ ዘንድ ወደ እኔ መምጣት አትፈልጉም" ብሏል። (ዮሐ.ም.5 ቁ:40)

ሰው ኹሉ ይድን ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢኾንም ለሰው ልጅ ነጻ ፈቃድን የሰጠው በመኾኑ ለመዳን ፍላጎት ኖሮት እስፈላጊውን ግዴታ ካላሟላ በቀር ኹሉም ይድናል ማለት አይደለም። እውነት ያልኾነውን እውነት በማስመሰል የሚያባስት ኀይል ይልክባቸዋል የተባለው የሰይጣንን ኀይል ለመቋቋም የእግዚአብሔርን እርዳታ ስለማይጠይቁ ወይም ሊጠይቁ ስለማይፈልጉ እግዚአብሔር ርዳታውንና ጸጋውን ይነሣቸዋል ማለት ነው። እግዚአብሔር አሳሳቹን ኀይል አለመከላከሉና ለእነርሱም ከአሳሳቹ ኀይል የሚደርስባቸውን ጥፋት ለመከላከል የሚያስችል ድጋፍ አለመስጠቱ ነው አሳሳች ኀይል ይልክባቸዋል የተባለው። በራሳችን ኀይል ብቻ ተመክተን ያለ እግዚአ ብሔር ዕርዳታ ልንፈጽም የምንሞክረው ነገር ኹሉ መልካም ውጤት እንደ ማይኖረው ሲያመለክት ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ብሏል "እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል። በማለዳ መገሥገሣችሁ ከንቱ ነው።" (መዝ.127 ቁ:1) ጥያቄና መልስ ቁ.113፥ 114፥ 118፥ቀ 120፥ 140 አንደኛ መጽሐፍ ይመለከቷል።

## ወደ ጢሞቴዎስ የተላከ የመጀመሪያው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት

ይህ መልእክት 6 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ምዕራፍ 1 እና ምዕራፍ 4 ሲኾን በዚህ ክፍል ለጢሞቴዎስ ምክርና መመሪያ የተሰጠበት ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ኹለተኛው ክፍል ምዕራፍ 2 ሲኾን በዚህ ክፍል ስለ ኤጲስ ቆጶሳትና ስለዲያቆናት ግዴታዎች ተዘርዝሮአል።

አራተኛው ክፍል ምዕራፍ አምስትና ምዕራፍ ስድስት ሲኾን በዚህ ክፍል ለምእመናን ትምህርትና ደንቦች፡ ከሐሰተኞች መምህራን እንዲጠነቀቁ ምክርና እንዲሁም ለጢሞቴዎስ ምክር ተሰጥቶበታል።

## ጥያቄና መልስ

95. ለጢሞቴዎስ በተላከው በመጀመሪያው መልእክት ም.3 ቁ:2 ላይ አንድ ኤጲስ ቆጶስ አንዲት ሚስት ብቻ ያገባ መኾን አለበት የሚለው አባባል ወደ ቆርንቶስ ሰዎች መጀመሪያ በተላከው መልእክት ም.7 ቁ:32 — 34 ላይ:- "ስለዚህ በምንም ሐሳብ ሳትጨነቁ እንድትኖሩ እወዳለሁ ሚስት ያላገባ ሰው ጌታ ኢየሱስ የሚደሰትበትን ነገር ስለሚፈልግ ሐሳቡ የሚያተኩረው ጌታ ኢየሱስን በሚመለከት ሥራ ነው። ሚስት ያገባ ሰው ግን የሚያስበው ስለዚህ ዓለም ነገርና ሚስቱንም የሚያስደስትበትን ነገር ነው። በዚህ ኹኔታ ሐሳቡ በኹለት ተከፍሎአል ማለት ነው። እንዲሁም ባል ያላገባች ሴት ወይም ልጃገረድ በሥጋዋና በነፍስዋ ተቀድሳ የእግዚአብሔር ለመኾን ስለምትፈልግ ሐሳቧ የሚያተኩረው ጌታ ኢየሱስን በሚመለከት ሥራ ነው። ያገባች ሴት ግን ባልዋን ለማስደሰት ስለምትፈልግ የምታስበው የዓለምን ነገር ነው።" በቁጥር 37 እና 38 ላይ ደግሞ "ነገር ግን ለማግባት የሚያስገድደው ነገር ከሌለ፥ ላለማግባት ችሎታ ካለውና ላለማግባትም ቁርጥ ውሳኔ ካደረገ አለማግባቱ መልካም ነው። ስለዚህ ሚስት የሚያገባ መልካም ያደርጋል፤ የማያገባ ግን የተሻለ ያደርጋል" ከሚሉት አባባሎች ጋር እንዴት ይታረቃል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የሐዋርያውን አባባል ትክ ብለን የተመለከትን እንደኾነ ኤጲስቆጶስ የሚኾን ሰው የግድ ሚስት ያገባ መኾን አለበት አላለም። ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ላይ እንደገለጸው የሚቻል እስከኾነ ድረስ የቤተክርስቲያን መሪ የሚኾነው ሰው ሚስት ያላገባ ቢኾን ይመረጣል ብሏል።



ለጢሞቴዎስ በተላከው መልእክት ምዕራፍ 3 ቁ.2 ላይ ከኤጲስቆጶስ ግዴታዎች አንዱ አንዲት ሚስት ብቻ ያገባ መኾን አለበት ካለ በኋላ በምዕራፍ 5 ቁ. 11 ላይ :- "በዕድሜአቸው ያልገፉትን መበለቶች ግን መዝገብ አትጻፋቸው፡ ምክንያቱም እነርሱ ሥጋዊ ምኞታቸው አሸንፎአቸው ለክርስቶስ ያላቸው ፍቅር ሲቀንስ፡ ባል ማግባት ይፈልጋሉ" ማለቱ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የኾነ ሰው ኹሉ ያላገባ ወይም ያላገባች ቢኾን ወይም ብትኾን መምረጡን ያመለክታል።

ስለዚህ ኤጲስቆጶስ አንዲት ሚስት ያገባ መኾን አለበት ያለው ሌላ ሚስት ያላገባ ሰው ሊገኝ ያልተቻለና እርሱም ሚስት ላለማግባት ያልቻለ እንደኾነ ብቻ ነው።

## ለጢሞቴዎስ ኹለተኛ ጊዜ የተላከ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት

ይህ መልእክት አራት ምዕራፎች ያሉት ኾኖ አብዛኛዎቹ ክፍሎች ለጢሞቴዎስ ምክር የሰጠባቸው ናቸው።

## ጥያቄና መልስ

96 ወደ ጢሞቴዎስ ኹለተኛ በተላከው መልእክት ም.3 ቍ.12 ላ[illegible] "የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ኾነው በመንፈሳዊ ሕይወት መኖ[illegible] የሚፈልጉ ኹሉ ስደት ይገጥማቸዋል" ካለ በኋላ በምዕራፍ 4 ቍ.1[illegible] ላይ: "ጌታ ከማንኛውም ክፉ ነገር ያድነኛል" በማለቱ ኹለቱ አባባሎ[illegible] እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስለን ይኾናል።

በተከታዮቹ ላይ ስለሚደርስባቸው ችግር አስቀድሞ ጌታ የ[illegible]ገረው በሚከተለው አባባል ነው:- "ሰዎች ለፍርድ አሳልፈው ይ[illegible] አችኋል፤ በየምኩራባቸውም ይገርፉአችኋል፡.... በእኔ ምክንያት [illegible] ገዢዎችና ወደ ነገሥታት ለፍርድ ትወሰዳላችሁ፡ በእነርሱና በአ[illegible]ውያን ፊት ምስክሮቼ ትኾናላችሁ።" (ማቴ.ም.10 ቍ.17–18)



www.ethiopianorthodox.org

ምንም እንኳ የወንጌል አገልጋዮች ስደት ይደርስባቸዋል ቢባልና የዚህም እውነተኛነቱ የታመነ ቢኾን አልፎ አልፎ ግን አምላክ አስፈላጊ ኾኖ በሚያገኘው ጊዜ ሐዋርያቱን ከሞትና ከእስራት ያዳነባቸው ጊዜዎች አሉ። ለምሳሌ የእግዚአብሔር መልአክ ሐዋርያትን ከታሰሩበት እስር ቤት አስወጥቶአቸዋል። (የሐ.ሥ.ም.5 ቊ.19)፡ እንዲሁም ጴጥሮስን ከእስር ቤት አስወጥቶታል። (የሐ.ሥ.ም.12 ቊ.7–9)

በዚሁም ዐይነት ሐዋርያው ጳውሎስ "ጌታ ከማናቸውም ክፉ ነገር ያድነኛል" ማለቱ የጌታ ተከታዮች ስደት የሚደርስባቸው ከመኾኑም ጋር ያድነናል ማለቱ ቢሆንም ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ መታ ተቃራኒ አይደለም። እንደሚታወቀው ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ መታ ሰር፥ ብዙ መወገርና ብዙ መደብደብ ቢደርስበትም እግዚአብሔር ግን ለረጅም ጊዜ ከሞት አድኖታል።

## ወደ ቲቶ የተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት

ቲቶ አንድ የግሪክ ሰው የነበረና በቅዱስ ጳውሎስ አማካይነት ወደ ክርስትና ቤተሰብ የገባ ነው። (ገላ.ም.2 ቊ.3) ሐዋርያው ጳውሎስ የቀርጤስ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሾሞታል።

ይህ መልእክት 3 ምዕራፎች ያሉት ሲኾን አብዛኛው ክፍል ለቲቶ መመሪያና ምክር የተሰጠበት ነው።

### ጥያቄና መልስ

97. ወደ ቲቶ በተላከው መልእክት ም.3 ቊ.9 ላይ:- "ነገር ግን ከከንቱ ክርክር.....ከጭቅጭቅ፡ በሙሴ ሕግ ምክንያት ከሚነሣው ጠብ ራቅ፤ ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ጥቅም የሌላቸውና ዋጋ ቢሶች ናቸው" ያለ ሲኾን በመጀመሪያው የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት ም.3 ቊ.15 ላይ:- "ጌታ የኾነውን ክርስቶስን በልባችሁ አክብሩት፤ በእናንተ ስላለው ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቃችሁ ኹሉ መልስ ለመስጠት ዝግጁዎች



ኹኑ» በመባሉ ኹለቱ አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስለን ይኾናል።

ስለአንድ ጉዳይ እንሥቶ መከራከር ወይም መጨቃጨቅና ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ መስጠት ኹለቱ የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው።

አንድ ጠያቂ ምንም ዐይነት ዐላማ ቢኖረው ስለ እምነታችን በሚጠይቀን ጊዜ መልስ ለመስጠት ዝግጁዎች ኾነን መገኘት ይኖር ብናል። የሌላውን ሰው እምነት በሚመለከት ክርክር ማንሣት ግን አስፈላጊ አይደለም።

## ወደ ፊልሞና የተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት

ይህ ፊልሞና የተባለ ሰው የቆላስይስ ሰው የነበረና በሐዋርያው ጳውሎስ አማካይነት ወደ ክርስቶስ ቤተሰብ ት የገባ ነው። ፊልሞና ኮብልሎ የኼደ አናሲሞስ የተባለ ባሪያ ነበረው። እንደ አጋጣሚ ይህ አናሲሞስ ወደ ሮማ ኼዶ በቅዱስ ጳውሎስ አማካይነት የክርስትናን ሃይማኖት ተቀብሎአል። ከዚህ በኋላ ለፊልሞና የጻፈውን ደብዳቤ እንዲያደርስ አናሲሞስን ሲልከው ይቅርታ እንዲያደርግለትና በክር ስቲያኖች መካከል ልዩነት ሊኖር ስለማይገባ እንደ አገልጋዩ ሳይኾን እንደ ወንድሙ እንዲቀበለው አሳስቦታል።

### ጥያቄና መልስ

98 ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልሞና በጻፈለት መልእክቱ ላይ በክርስትና እምነት ባሪያና ጌታ ኹሉም በክርስቶስ ወንድም መኾኑን የሚገልጽ ሲኾን ወደ ኤፌሶን ሰዎች በተላከው መልእክት ም.6 ቊ.5 ላይ:- "ባሪያዎች ሆይ፥ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ በፍርሃት በመንቀጥቀጥ በልባችሁ ቅንነት በሥጋ ጌቶቻችሁ ለኾኑ ታዘዙ" በማለቱ ኹለቱ አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስለን ይኾናል።



www.ethiopianorthodox.org

ኹሉም ሰው እኩል መኾኑና በክርስቲያኖች መካከል ምንም ልዩነት አለመኖሩን ከሚገልጹት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ጥቅሶች ይገኙባቸዋል:-

ኹላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ስለኾናችሁ በአይሁዳዊና በግሪካዊ፥ በባሪያና በጌታ፥ በወንድና በሴት መካከል ምንም ልዩነት የለም።" (ገላ.ም.3 ቍ.28)

"በዚህ ኹኔታ በግሪካዊና አይሁዳዊ፥ በተገረዘና ባልተገረዘ፥ በሠለጠነ አረመኔና ባልሠለጠነ አረመኔ፥ነጻነት በሌለውና ነጻነት ባለው ሰው መካከል ልዩነት የለም፤ ክርስቶስ ኹሉም ነው፤ የኹሉም ነው።" (ቆላ.ም.3 ቍ.11)

እንዲሁም ወደ ጢሞቴዎስ በተላከው የመጀመሪያው መልእክት ም.1 ቍ.10 ላይ በሰው መነገድ ወንጀል መኾኑን ይገልጻል።

የክርስትና ሃይማኖት በዚህ ዐይነት የባሪያና የጌታን ኹናቴ የማይደግፍ ከኾነ ለምንድነው ታዲያ ጌታም ኾነ ሐዋርያት በግልጽ ያል ተቃወሙት ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል። በአንደኛው መጽሐፍ ጥያቄና መልስ:ቍ:37 እንደተገለጸው በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የታወጀው የባሪያና የባሪያ አሳዳሪ ሕግ የአሠሪና የሠራተኛን ውል ስለሚመስል የክርስትና ሃይማኖት በተዋዋዮች መካከል ያለውን የሥራ ስምምነት የሚያሻሽል ወይም የሚቃወም አይደለም።

ጌታና ደቀ መዛሙርቱም መንፈሳዊ ትምህርት ከማስተማራቸውና ኹሉም ሰው በያለበት ተስማምቶ በፍቅር እንዲኖር ከመምከራቸው በቀር በዓለማዊው አገዛዝ ውስጥ እጃቸውን አላስገቡም። እንዲያውም ስለዓለማዊ አስተዳዳር ጉዳይ በጠየቁት ጊዜ ጌታ የሰጠው መልስ የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ከማለቱ በቀር ምንም አስተያየት ለመስጠት አልፈቀደም። (ማቴ.ም.22 ቍ.21)

ስለዚህ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የባሪያና የጌታ ግንኙነትን በተመለከተ በአንዳንድ ቦታዎች የሚታየው አነጋገር ሰዎች በሰላም እንዲኖሩ ምክር



ለመስጠት ካልኾነ በቀር የነበረው ኹናቴ እንዲቀጥል ድጋፍ ለመስጠት አይደለም።

## ወደ ዕብራውያን የተላከ መልእክት

የዚህን መልእክት ደራሲ በተመለከተ ከጥንት ጀምሮ የተለያዩ አስተያየቶች ተሰጥተውበታል።

ደራሲው ቅዱስ ጳውሎስ ሳይኾን ሌላ ሰው ነው የሚሉት ሰዎች ከሚያቀርቡአቸው ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

ሀ/ በመልእክቱ መጀመሪያ ላይ በሌሎቹ በቅዱስ ጳውሎስ መልእክቶች የተለመደው የሰላምታ አሰጣጥና ስሙን መጥቀስ በዚህ መልእክት ውስጥ አለመታየቱ ይህ መልእክት የእርሱ አለመኾኑን ያመለክታል።

ለ/ መልእክቱ የተላከው ለዕብራውያን እንደመኾኑ መዘጋጀትም የነበረበት በዕብራይስጥ ቋንቋ ነበር። መልእክቱ ግን የተዘጋጀው የግሪክን ቋንቋ፥ የፕሌቶና የፊሎን ፍልስፍና አጠናቅቆ በሚያውቅ ሰው የተጻፈ መኾኑን ያመለክታል።

ሐ/ አጻጻፉ ከቅዱስ ጳውሎስ አጻጻፍ የተለየ ነው።

መ/ የማስረጃ አቀራረቦቹ ከቅዱስ ጳውሎስ የማስረጃ አቀራረቦች የተለዩ ናቸው።

ሠ/ ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌልን የተቀበለው ከእግዚአብሔር መኾኑን ሲያረጋግጥ በዚህ መልእክት ግን ከሌላ ሰው እንደተቀበለ ይገልጻል። (ገላ.ም.1 ቍ.11–19፡ ዕብ.ም.2 ቍ.3)

ረ/ የቅዱስ ጳውሎስ ፊርማ የለበትም።



www.ethiopianorthodox.org

መልእክቱ የቅዱስ ጳውሎስ ነው የሚሉት ወገኖች ደግሞ የሚሰጡአቸው ምክንያቶች:-

ሀ/ አጻጻፉ የግሪክ አጻጻፍን የመሰለው በመጀመሪያ በዕብራይስጥ ቋንቋ ከጻፈው በኋላ ወንጌላዊው ሉቃስ ወደግሪክ ቋንቋ በሚተረጉምበት ጊዜ ያጻጻፉንም ዘይቤ ለውጦታል።

ለ/ በመልእክቱ መጀመሪያ ላይ ስሙን ያልመዘገበበት ምክንያት በብዙዎቹ ዕብራውያን ዘንድ የሙሴ ሕግ ጠላት ተደርጎ ይታይ ስለነበረና የእርሱን ስም በማየታቸው ሳያነቡት እንዳይቀሩ ጥንቃቄ ለማድረግ ሲል ስሙን ሳይመዘግብ ቀርቶአል።

ሐ/ በመልእክቱም መጨረሻ ላይ ፊርማውን ያላስፈረው ጸሐፊው እርሱ መኾኑን ላለማሳወቅ ነው።

መ/ በምዕራፍ 13 ቍ.23 ላይ: "ወንድማችን ጢሞቴዎስ ከእስር ቤት እንደወጣ እንድታውቁ እወዳለሁ" በማለት የጢሞቴዎስን ስም መጥቀሱ ጸሐፊው ቅዱስ ጳውሎስ መኾኑን ያመለክታል።

ከቀድሞዎቹ አባቶች መካከል ተርቱልያኖስ መልእክቱን ያዘጋጀው በርናባስ ነው ሲል የእስክንድርያዎቹ ኦሪጌኖስና ቀሌሚንጦስ ደግሞ ያዘጋጀው ቅዱስ ጳውሎስ ነው ብለዋል።

ቅዱስ ጳውሎስ አልጻፈውም የሚሉት ወገኖች መልእክቱን ጻፈ ብለው የተለያየ ሰሞችን ይጠቅሳሉ። በተለያዩ ሰዎች ስሞቻቸው ከተ ጠቀሱት ሰዎች መካከል:- አጵሎስ፥ ሉቃስ፥ ፊልጶስ አኪላስ፥ ጵርስ ቅላ እንዲሁም የሮማው ቀሌሚንጦስ ይገኙባቸዋል።

## ጥያቄና መልስ

99.ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.6 ቍ.4–6 ላይ:- አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸው፥ ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱት፥ ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ኾነው የነበሩትን፥ መልካሙንም የእግዚአብሔርን



ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል ቀምሰው በኋላ የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፤ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና ያዋርዱትማልና ከተባለ በኋላ በመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት ም.2 ቍ.1–2 «ማንም ኀጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቅ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም የኀጢአታችን ማስተሰረያ ነው፤ ለኀጢአታችንም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ለዓለሙ ኹሉ ኀጢአት እንጂ» በማለቱ ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስለን ይኾናል።

ለዚህ አባባል ኹለት ትርጓሜዎች ይኖሩታል።

የመጀመሪያው ትርጓሜ ከአይሁድነት ወደ ክርስትና የተመለሱት ምእመናን ማንኛውም ሰው ኀጢአት በሠራ ጊዜ ኹሉ መጠመቅ የሚገባው ይመስላቸው ነበር። የጥምቀት ሥነ ሥርዓት በጌታ ስቅለት፥ በሞቱ፥ በመቃብሩና በትንሣኤው ስለሚመስል፥ ጌታ ደግሞ እንደገና የማይሰቀል፥ የማይሞት፥ የማይቀበርና የማይነሣ ስለኾነ በዚሁም ዐይነት ጥምቀት አይደገምም ማለቱ ነው እንጂ ስለንስሐና ስለጥቀሙ ማለቱ አይደለም።

ኹለተኛውትርጓሜ ደግሞ በቀጥታ አባባሉን የሚከተል ነው። ለዚህም በዕብ ራውያን መልእክት ም.6 ቍ.7 እና 8 ላይ ያለውን ጥቅስ እንመልከት:- "ብዙ ጊዜ በእርስዋ ላይ የሚወርደውን ዝናም የጠጣች መሬት ተክል ለተከለባት ሰው ጥቅም የምትሰጥ በመኾንዋ እግዚአብሔር ይባርካታል። እሾህና አሜከላ ብታበቅል ግን ጥቅመቢስ ትኾናለች፤ ለመረገምም ቀርባለች፤ መጨረሻዋም በእሳት መቃጠል ነው።" ይህም ማለት ወደክ ርስትና ፍጹምነት የደረሰ ሰው የሕሊናውን ተግሣጽ አሻፈረኝ ብሎ ሃይማኖትን ወደመቃወምና ወደ መንፈስ ቅዱስ ጽርፈት ደረጃ ከደረሰ በዚህ ዓለምም ኾነ በሚመጣው ዓለም በደሉ ይቅር አይባልለትም።

ሐዋርያው ሊል የፈለገው በኀጢአት የወደቁትን ሰዎች በአጠቃላይ ሳይኾን በክርስትና ሃይማኖት ብዙ ወደፊት ከተራመዱ በኋላ የክርስቲያን ሃይማኖት ጠላት ወደመኾኑ ደረጃ የተዛወሩትን ማለት ነው። ለምሳሌ ስለአይሁድ በሚናገርበት ጊዜ:- "ዐውቀውትስ ቢኾኑ የክብርን ጌታ



www.ethiopianorthodox.org

ባልሰቀሉትም ነበር" ብሏል። (1ኛ ቆሮ.ም2 ቍ.8.) ካወቁት በኋላ የካዱት ግን ኀጢአታቸው የከፋ ነው።

## የሐዋርያው የያዕቆብ መልእክት

ይህ መልእክት 5 ምዕራፎች አሉት። የመጀመሪያው ምዕራፍ ችግርን በትዕግሥት ማሳለፍ ታላቅ ዋጋ እንደሚያሰጥ፥ አንዳንድ ፈተናዎች ሰዎች በራሳቸው ላይ የሚያመጡአቸው መኾናቸውን ይዘረዝራል።

ኹለተኛው ምዕራፍ በክርስቲያን ሃይማኖት ውስጥ በድኻና በባለ ጸጋ መካከል ልዩነት አለመኖሩን እምነት ደግሞ ያለበጎ ተግባር ዋጋ የሌለው መኾኑን ይገልጻል።

በሦስተኛው ምዕራፍ ምላስን መቈጣጠር እንደሚገባና ሰማያዊ ጥበብን ብቻ መከተል እንደሚገባ ተገልጾአል።

አራተኛው ምዕራፍ የክፋት ምንጮችና ከክፋት መጠበቅ የሚገባን መኾኑ፥ እንዲሁም በሰው ላይ መፍረድ እንደማይገባን ምክር ተሰጥቶበታል።

አምስተኛው ምዕራፍ ስለ ስስታሞች ሀብታሞች ማስጠንቀቂያና ሌሎችም ልዩ ልዩ ምክሮች ተሰጥተውበታል።

## ጥያቄና መልስ

100. በሐዋርያው የያዕቆብ መልእክት ም.1 ቍ.9 ላይ:- "በኑሮው ዝቅተኛ የኾነ ወንድም እግዚአብሔር ከፍ ስለሚያደርገው ደስ ይበለው" ካለ በኋላ በቁጥር 10 ላይ:- ደግሞ "በኑሮው ከፍ ያለ ወንድም እግዚአብሔር በኑሮው ዝቅ ቢያደርገውም ደስ ይበለው፤ ምክንያቱም የሰው ሀብት እንደ ሣር አበባ ይረግፋል" በማለቱ ኹለቱ አባባሎች እን ዴት ሊታረቁ ይችላሉ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።



ድኻውና ሀብታሙ ደስ እንዲላቸው የተነገራቸው አማኞች በመኾናቸው ነው። አማኝ የኾነ ሰው ደግሞ በድኻና በባለጸጋ መካከል ልዩነት አያደርግም። አሁን እንግዲህ ድኻው ሰው ምንም በዓለማዊ ድኽነቱ በሌሎች ዘንድ የተናቀ ቢኾን አማኝ በመኾኑ አማኙ ባለጸጋ በእኩልነት ስላየው ደረጃው ከፍ ብሎ መታየቱና ባለጸጋው ደግሞ አማኝ ኾኖ የሰው ሀብት እንደ ሣር አበባ የሚረግፍ መኾኑን በማመኑና ድኻውን በእኩልነት ደረጃ በመመልከት ዓለማዊ ደረጃው ዝቅ እንዳለ ቢገመትም ይህ ትሕትናው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ስለሚያገኝ ደስ እንዲለው ተነግሮታል።

በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ ዓለም ድኽነት ለወዲያኛው ዓለም ብልጽግና እንደሚያበቃ ስለሚታመን በዚህም አንጻር ድኻው ሰው ደስ እንዲለው ተነግሮታል። እንዲሁም ደግሞ ራሱን ያዋረደ በእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚከብር ስለሚታመን ባለጸጋው ሰው በትሕትናው ደስ እንዲለው ተነግሮታል።

## የመጀመሪያው የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት

ይህ መልእክት 5 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

በመጀመሪያው ክፍል ያለምንም ምክንያት ሊደርስ ከሚችል ፈተናና ችግር ጌታ እንደታገሠ እንድንታገሥ ምክር ተሰጥቶበታል።

በኹለተኛው ክፍል በንጹሕ ደም የተዋጁ ስለኾነ በንጽሕና እንዲኖሩ፥ በክርስቶስ ላይ እንደተመሠረቱ ካህናትና ቤተ መቅደስ እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ ምክር ተሰጥቶበታል።

ሦስተኛ ከሥጋ ምኞት እንዲጠበቁ ተነግሮአቸዋል።

አራተኛ ከምእመናን ኹሉ ጋር ባላቸው ግንኙነት ትሑቶች እንዲኾኑ ተመክረዋል።



www.ethiopianorthodox.org

## ጥያቄና መልስ

101. በአንደኛ ጴጥሮስ ም.4 ቍ.18 ላይ:- ጻድቅ ሊድን የሚችለው በጭንቅ መኾኑን የሚገልጽ ሲኾን ወደ ሮሜ ሰዎች በተላከው መልእክት ም.3 ቍ.28 ላይ ሰው የሚጸድቀው በእምነት ብቻ መኾኑን ስለሚገልጽ ኹለቱ አባባሎች ለምን እርስ በርሳቸው ተቃረኑ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

እዚህ ላይ ጻድቅ የተባለው ምእመን በክርስቶስ ላይ ያለው እምነት በእግዚአብሔር ሙሉ ጸጋ ወደ ፍጹምነት የደረሰ ነው። (ኤፌ.ም.2 ቍ.8–10) ፍጹምነቱን ለማሙአላት ሌላ ጥረት አያስፈልገውም።

ይኹን እንጂ የመዳንን መንገድ ተከትሎ ጻድቅ ወደመኾን ክብር ከመድረሱ በፊት በእምነት ጐዳናው ላይ ተደንቅረው ከሚያሰናክሉት ሦስት ጠላቶች ማለት ከዲያቢሎስና ከሠራዊቱ፥ ከዓለምና ከአታላይነቱ፥ ከሥጋና ከፍትወቱ ጋር እንደ ጀግና ወታደር ተጋድሎ ያደርጋል። ለዚህም አባባል የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት:- "እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ ካለ በመንፈስ ፈቃድ እንጂ በሥጋ ፈቃድ አትኖሩም፤ የክርስቶስ መንፈስ የሌለውም ሰው የክርስቶስ ወገን አይደለም።... ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ፥ በሕይወታችን ግዴታ አለብን፤ ነገር ግን ይህ ግዴታ በሥጋ ፈቃድ ለመኖር አይደለም። በሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትጠፋላችሁ፤ ነገር ግን በመንፈስ እርዳታ ሥጋዊ ሥራችሁን ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ።" (ሮሜ ም.8 ቍ.9፡12፡13)

"ስለዚህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙት፤ ከእናንተም ይሸሻል።" (ያዕ.ም.4 ቍ.7"

"በመጠን ኑሩ፤ ንቁም፤ ምክንያቱም ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሳ አንበሳ በዙሪያችሁ ያደባል።" (1ኛ ጴጥ.ም.5 ቍ.8)



"የእግዚአብሔር ልጅ የኾነ ኹሉ ዓለምን ያሸንፋል፤ ዓለምን የምናሸንፈውም በእምነታችን ነው። ዓለምን የሚያሸንፈው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መኾኑን የሚያምን ብቻ ነው።" (1ኛ ዮሐ.ም.5 ቍ.4–5)

ስለዚህ የእግዚአብሔርን የማዳን ጸጋ ለመቀበል የእኛ በጎ ተግባር ብቁ ባይኾንም የሚጠበቅብንን ግዴታ ካላሟላን ግን የመዳንን ዕድል ለማግኘት አስቸጋሪ ይኾንብናል።

ይህን አባባል ጌታ በሚከተለው ኹኔታ ግልጽ አድርጎታል:- "በጠባብዋ በር ግቡ፤ ምክንያቱም ወደ ጥፋት የሚያስገባው በር ሰፊ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደውም መንገድ ትልቅ ነው። ወደዚያ የሚገቡበትም ሰዎች ብዙዎች ናቸው። ወደ ሕይወት የምታስገባዋ በር ግን ጠባብ ናት፤ መንገዱም አስቸጋሪ ነው፤ ስለዚህ እርስዋን የሚያገኙዋት ሰዎች ጥቂቶች ናቸው። (ማቴ.ም.7 ቍ13–14)

## ኹለተኛው የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት

ይህ መልእክት 3 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በኹለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከወንድሙ ከጳውሎስና ከሌሎቹም ሐዋርያት ትምህርት ጋር በማስማማት በክርስቲያናዊ እምነት ላይ የጸኑ መኾናቸውን የሚያመለክተውን በጎ ተግባር እንዲያከናውኑ መምከሩ:- ይህም ትምህርት ክብሩን ባዩት በክርስቶስ አማካይነት ከሰማይ የወረደላቸው መኾኑን ገልጾአል።

ኹለተኛው ክፍል ደግሞ ጌታ የሚመጣበት ዘመን አልፎአል ብለው ከሚናገሩት ሐሰተኞች ነቢያትና ሐሰተኞች መምህራን እንዲጠነቀቁ ነግሮአቸዋል። እነዚህም ሐሰተኞች መምህራንና ሐሰተኞች ነቢያት ርኩሳን መናፍስት፥ የጥፋት ውሃ ጊዜ ሰዎች፤ የሰዶምና የገሞራ ሰዎችና በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ትንቢት ለመናገር የተገዛው በልዓም የደረሰባቸው ቅጣት ይደርስባቸዋል።



www.ethiopianorthodox.org

102. በኹለተኛው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት ም.1 ቍ.17 ላይ:- "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምፅ ከታላቁ ክብር በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ምስጋናንና ክብርን ተቀብሎ አል" የሚለው አባባል በዚሁ ምዕራፍ ቍ.1 ላይ:- "አምላካችንና አዳኛ ችን ኢየሱስ ክርስቶስ» ከሚለው ጋር እንዴት ይታረቃል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በተመሳሳይ አባባል በዮሐንስ ወንጌል ም.7 ቍ.39 ላይ:- "ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበር" ተብሎአል። እንዲሁም በምዕራፍ 12 ጀ.16 ላይ:- "ደቀ መዛሙርቱም ይህን ነገር በመጀመሪያ አላስተዋሉም፤ ነገር ግን ኢየሱስ ከከበረ በኋላ በዚያን ጊዜ ይህ ስለእርሱ እንደተጻፈ፥ ይህንም እንዳደረጉለት ትዝ አላቸው።" ተብሏል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኀጢአት በቀር እንደማነኛውም ሰው በዚህ ዓለም ይኖር በነበረበት ጊዜ ሕማማትን ተቀብሎ፥ ተሰቅሎ፥ ሞቶ፥ ተቀብሮ፥ ከሙታን ተለይቶ በመነሣት ለተከታዮቹ እስከተገለጠ በት ጊዜ ድረስ ሐዋርያቱም ኾኑ ሌሎች ስለመለኮታዊ ክብሩ እርግጠ ኞች አልነበሩም።

ለምሳሌ ለጌታ በጣም ቅርብ መኾናቸው ከሚነገርላቸው ከጴጥሮስ ከያዕቆብና ከዮሐንስ መካከል ወንድማማቾቹ ያዕቆብና ዮሐንስ ወደ ጌታ ቀርበው በሚነግሥበት ጊዜ አንዳቸውን በቀኙና አንዳቸውን ደግሞ በግራ ው የመቀመጥን ክብር እንዲሰጣቸው መለመናቸው በምድራዊ ክብሩ እንጂ በሰማያዊ ክብሩ ያላመኑበት መኾናቸውን ያመለክታል። (ማር. ም.10.ቍ35–37)

በዮሐንስ ወንጌል ም.11 ላይ ሞቶ የነበረው የአልዓዛር እኅቶች ማርታና ማርያም ጌታን ባገኙት ጊዜ እርሱ አጠገባቸው ቢኾን ኖሮ ወን ድማቸው ባልሞተም ነበር በማለት አሁንም ሊያስነሣበት የሚችል መለ ኮታዊ ኀይል እንዳለው አለማመናቸው ተፀ ልክቶአል።



በማቴዎስ ወንጌል ም.26 ቍ.56 ላይ እንደተገለጠው ጌታ በተያዘ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ኹሉ ጥለውት መሸሻቸው እምነታቸው በጌታ ምድ ራዊ ክብር ላይ ብቻ የነበረ መኾኑን ያመለክታል።

ስለዚህ ጌታ ከሞት በመነሣትና በዐይናቸው እያዩትም ወደ ሰማይ በማረጉ በጌታ ተራ ሰውነት ላይ ብቻ የነበረው አስተሳሰባቸው ተለውጦ በአምላክነቱ አመኑበት። መክበር የተባለውም ለትስብእት ነው እንጂ መለኮትማ የክብር ጌታ ነው። አብ አከበረው የተባለውም ወልድ ከት ስብእት ጋር ቢዋሐድም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተለየ ክብር ያለው መኾኑን መሰከረለት ማለት ነው እንጂ በፊት ያልነበረውን ክብር ሰጠው ለማለት አይደለምና አለመኾኑን ተረድተን ከመሳሳት እንጠንቀቅ። በጥያቄና መልስ:ቍ:8፥ 18፥ 27፥ 36 ፥ 48፥ 57፥ 60፥ 61፥ 63፥ 72፥ 75፥ 84፥ 89፥ 91፥ 92፥ 93፥ 102 እና ከአንደኛው መጽሐፍ ቍ:102፥ 104፥ 112 ይመለከቷል።

## የመጀመሪያው የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት

ይህ መልእክት 5 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዘረዝራል።

የመጀመሪያው ዓላማ የጌታን መለኮታዊ ክብርና ሥጋዌውን ማረ ጋገጥ ነው።

ኹለተናው ዓላማ ድኅነት የሚገኘው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመንና ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለእርሱ አምልኮ በማቅረብ መኾ ኑ ነው።

ሦስተኛው ዓላማ በኀጢአታቸው የተጸጸቱ ወንጀላቸውንም የተና ዘዙ ክርስቲያናውያን ኀጢአተኞች ጌታ የተቤዣቸው ስለኾነ የእግዚአ ብሔርን ምሕረት የሚያገኙ መኾናቸው ተገልጾአል።

አራተኛው ዓላማ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። ልጅነታቸው የሚረጋገጠው ትእዛዛቱን በመጠበቅና እርስ በርሳቸው በመ



www.ethiopianorthodox.org

ዋደድ ነው። እነዚህም ኹለት ምልክቶች በእግዚአብሔር ልጆችና በሰ ይጣን ልጆች መካከል መለያዎች ናቸው።

አምስተኛው ዓላማ ሥጋ የለበሰውን የጌታን መምጣት ከሚክዱ ሐሳዊ መሲሖች ማስጠንቀቅ ነው።

ስድስተኛው ዓላማ የምእመናን ጸሎት ከንስሓ ጋር አንዳንድ ኀጢ አትን ለማስተሰረይ ችሎታ እንዳለው ተገልጾበታል።





103. በመጀመሪያው የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ም.1 ቍ.8 እና 10 ላይ:- "ኀጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናታልላለን። እውነትም በእኛ ውስጥ የለም።... ኀጢአት አልሠራንም ብንል እግዚአብሔርን ሐሰተኛ እናደርገዋለን፤ ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም" ካለ በኋላ በምዕራፍ 3 ቍ.6 እና 9 ደግሞ:- "ስለዚህ በክርስቶስ የሚኖር ሰው ኹሉ ኀጢአት አይሠራም። ኀጢአት የሚሠራም ሰው ክርስቶስን አላየውም ወይም አላወቀውም።... የእግዚአብሔር ልጅ የኾነ ኀጢአት አይሠራም፡ ሊሠራም አይችልም፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ባሕርይ በውስጡ ስለሚኖርና ከእግዚአብሔርም ስለተወለደ ነው" በማለቱ እንዴት ሐዋርያው እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አባባሎችን መዘገበ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በኹለተኛው ጥቅስ ላይ የእግዚአብሔር ልጅ የኾነ ኀጢአት አይሠራም የተባለው ኀጢአት ቢሠራ ያን ኀጢያት የሚሠራው የእግዚአብሔር ልጅ በመኾኑ ወይም የእግዚ አብሔር ጸጋ በመልበሱ አይደለም፤ ማለት የኀጢአቱ ምክንያት የእግዚአብሔር ልጅ መኾኑ አይደለም ማለት ነው። ስለዚህም ነው በክርስቶስ የሚኖር ሰው ኹሉ ኀጢአት አይሠራም የተባለው። የኀጢአቱ ምክንያት ግን በተበላሸው የአዳም ኀጢአት ተወልዶ የኀጢአት ዝንባሌ ስለሚኖረው ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የኾነ ኀጢአት ሊሠራ አይችልም የተባለው በፍጹም ምንም ዐይነት ኀጢአት አይሠራም ለማለት አይደለም። ነገር ግን በፈተና ተሸንፎ ለጊዜው ከመውደቁ በቀር በፍላጎቱ ኀጢአተኛ አይኾንም ወየም ደግሞ ሳይመለስ እስከመጨረሻው የጠፋ ኾኖ አይቀርም ለማለት ነው። ወይም ደግሞ ራሱን ለጠላት ሰይጣን አያስረክብም ማለት ነው።

በመጀመሪያ ጥቅስ ላይ የተጠቀሰው የኹሉም ሰው ኀጢአተኛነትን በሚለከት ሐዋርያው ዮሐንስ መፍትሔ ሲሰጥ በምዕራፍ 1 ቍ.9 ላይ:- "ኀጢአታችንን ለእግዚአብሔር ብንናዘዝ እርሱ ታማኝና ጻድቅ ስለኾነ ኀጢአታችንን ኹሉ ይቅር ይልልናል፤ ከበደላችንም ኹሉ ያነጻናል" ብሏል።



www.ethiopianorthodox.org

ምንም እንኳ ሰው ኹሉ ኀጢአተኛ ቢኾን በእግዚአብሔር ልጅነቱ በክርስቶስ ጸንቶ እስከኖረ ድረስ ማለትም ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ተገዢ በመኾን በእምነቱ ጸንቶ በኖረ ጊዜ ኀጢአት አይሠራም ያሰኘዋል። ለጊዜው እንኳ ጊዜያዊ ድቀት ቢያጋጥመው በንስሓ ስለሚመለስ፥ እግዚአብሔርም ልጅነቱን ስለሚያድስለትና ጸጋውን ስለሚያጐናጽፈው ኀጢአትን ሊሠራ አይችልም ተብሏል።

## ኹለተኛው የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት

ይህ መልእክት አንድ ምዕራፍ ብቻ ያለው ኾኖ ለአንዲት ለተከበረች ሴት የተጻፈ ነው። ምናልባት ከትንሽዋ እስያ ከተሞች አንድዋ ትኾን ይኾናል። ምክንያቱም ሐሰተኛ ነቢያት ይበዙ የነበሩት በዚያ አካባቢ ስለነበረ ነው።

በመልእክቱም ውስጥ ስለፍቅርና ስለሐሰተኞች ነቢያት ምክርና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶበታል።

## ጥያቄና መልስ

104. በኹለተኛው የዮሐንስ መልእክት ቍ.9–11"በክርስቶስ ትምህርት ጸንቶ የማይኖር ከእርሱም ርቆ የሚኼድ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የለም፤ በክርስቶስ ትምህርት ጸንቶ የሚኖር ሰው ግን አብና ወልድ ከእርሱ ጋር አሉ። ይህን ትምህርት ሳይዝ ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፤ ሰላምታም እንኳ አትስጡት። ምክንያቱም ሰላምታ የሚሰጠው ሰው የክፉ ሥራው ተካፋይ ይኾናል ያለ ሲኾን ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ገላትያ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.6 ቍ.10 ላይ ለኹሉም ደግ እንድናደርግ ከመምከሩም በላይ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች መጀመሪያ በላከው መልእክቱ ም.9 ቍ .21–22 "ምንም እንኳ እኔ የእግዚአብሔር ሕግ ያለኝና ከክርስቶስ ሕግ ሥር ብኾን ሕግ የሌላቸውን አረማውያንን ለማዳን ስል ሕግ እንደሌለው ሰው ኾንሁ።... በተቻለ መጠን አንዳንዶችን ለማዳን ከኹሉም ኹሉን ነገር ኾንሁ" በማለቱ



ከሐዋርያው ዮሐንስ አባባል ጋር እንዴት ለማስታረቅ ይቻላል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

የሐዋርያው ዮሐንስና የሐዋርያው ጳውሎስ አባባሎች የተለያዩ ትርጓሜዎች አሏቸው እንጂ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

ሐዋርያው ዮሐንስ ካላማኒ ጋር መወዳጀትን የተቃወመው አማኝ በእምነቱ እንዳይሰናከል በመፍራት ነው እንጂ ጠላትነትን ለማስተማር አይደለም። በተመሳሳይ ኹኔታ በዘመነ አሪት ለአማንያት ከነበሩ ሴቶች ጋር መጋባት ያልተደገፈ ቢኾንም ሴቶቹ ግን በእግዚአብሔር አምነው በተመለሱ ጊዜ ጋብቻዎቹ ተቀባይነት አግኝተዋል። ለምሳሌ የዳዊት አያት የኢዮቤድ እናት ሞዓባዊትዋ ሩት ነች። (ሩት.ም520 ቍ.5)

ሐዋርያው ጳውሎስ ግን ሌሎችን በመምሰል የተጠቀመበት ዘዴ የወንጌልን ትምህርት በማስተማር ነፍሳትን ለማዳን ብሎ ነው።

በዚህም መሠረት ኹለቱ አባባሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።

## ሦስተኛው የዮሐንስ መልእክት

ይህ መልእክት ጋይዮስ ለተባለው ሰው የተላከ ነው። ይህም ጋይዮስ የተባለ ሰው ወደሮሜ ሰዎች በተላከው መልእክት ም.16 ቍ.23 እና ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው በመጀመሪያው መልእክት ም.1 ቍ.14 ላይ ስሙ ተጠቅሶአል። እርሱም የወንጌል አገልጋዮችን እንደሚረዳ ስለተነገረለት አመስግኖታል። በዚህም መልእክት ውስጥ ዲዮጥራጢስ በክፉ ሥራው ሲወቀስ ድሜጥሮስ ግን በበጎ ተግባሩ ተመስገነ። በመጨረሻም ለጋይዮስ ምክር ከተሰጠው በኋላ መልእክቱ ተጠናቋል።



www.ethiopianorthodox.org

105. በሦስተኛይቱ የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ቍ. 7 ላይ የወንጌል መልእክተኞች ከአሕዛብ ምንም ሳይቀበሉ በመውጣታቸው ጋይዮስ ይረዳቸው ዘንድ አደራ ማለቱ በማቴዎስ ወንጌል ም.10 ቍ:10 ላይ ለሠራተኛ ዋጋው ይገባዋል ተብሎ በጌታችን በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰጠው መመሪያ ጋር አይቃረንም ወይ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

በዮሐንስ መልእክት የተጠቀሱት የወንጌል መልእክተኞች ምግባቸውን ከአሕዛብ አለመጠየቃቸው እነዚያ አሕዛብ ገና የወንጌሉ መልእክት ደርሶአቸው ያላመኑበት በመኾኑ ቢጠየቁም ፈቃደኞች እንደማይኾኑ ስለተገነዘቡ ነው። መቼም የወንጌል መልእክተኞችን ለመርዳት በቅድሚያ በወንጌሉ መልእክት ማመን ያስፈልጋል። ጌታም ቢኾን በማቴዎስ ወንጌል ም:10 ቍ:9—11 ድረስ ደቀ መዛሙርቱን ወንጌል ለማስተማር በላካቸው ጊዜ በሰጣቸው መመሪያ ለጉዞአቸው ምንም ነገር እንዳይዙና በሚገቡበትም በማንኛይቱም ከተማ ወይም መንደር በዚያ የሚገባው ማን እንደኾነ በጥንቃቄ እንዲመረምሩና እስኪወጡም ድረስ በዚያ እንዲቀመጡ ብሎ ነው ያዘዛቸው። ይህም ማለት እነርሱን ለመቀበል ዝግጁ ኾኖ በተገኘ ሰው ቤት እንዲቈዩ እንጂ በማንኛውም ቤት አይደለምና ስለዚህ ኹለቱ አባባሎች ርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም።





በዚህ መልእክት ውስጥ የሙሴን ሥጋ በተመለከተ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ከዲያብሎስ ጋር መከራከሩንና ስለጌታ ለመጨረሻው ፍርድ መምጫ ጊዜ የሔኖክ ትንቢት ተነግሮአል። የይሁዳም መልእክት አንድ ምዕራፍ ብቻ ያለው ኾኖ ከቅዱሳን ሐዋርያት የተረከቡትን የቀና እምነት ይጠብቁ ዘንድ ለምእመናን ምክር ተሰጥቶበታል። ኹለተኛም ከሐሰተኞች ነቢያት ይጠነቀቁ ዘንድ ለምእመናን ምክር ተሰጥቶበታል። በመጨረሻም ስለ ጌታ መለኮታዊ ክብርና ስለምሥጢረ ሥላሴ ተገልጾአል።

## ጥያቄና መልስ

106 በመልእክተ ይሁዳ ቍ:22—23 ላይ:- "ለሚጠራጠሩ ሰዎች ርኅራኄ አድርጉላቸው፡ አንዳንዶችን ከእሳት አውጥታችሁ አድኑአቸው፤ ሌሎችን በፍርሃት ራሩላቸው፡ ኾኖም በኀጢአት የረከሰውን ሰውነታቸውን የነካውን ልብስ እንኳ ሳይቀር ጥሉ" በሚልበት ጊዜ በአንድ በኩል ራሩላቸው ከእሳት አውጡአቸው እያለ በሌላ በኩል ደግሞ በኀጢአት የረከሰውን ሰውነታቸውን ብቻ ሳይኾን የለበሱትን ልብስ እንኳ ሳይቀር ጥሉ ሲል መጀመሪያ ፍቅር ከዚያ በኋላ ደግሞ ጥላቻ በማስተማር ርስ በርሱ ተቃራኒ የኾነ ትምህርት ማስተማሩ እንዴት ነው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።

ጥቅሱ የሚያመለክተው ለኀጢአተኛው ርኅራኄ እንዲደረግለትና ከእሳት አውጥቶ እንዲድን ማድረግ ሲኾን ኀጢአቱን ግን መጥላት እንደሚገባን ነው።

ለኀጢአተኛ ማዘንና ከኀጢአቱ በንስሓ እንዲመለስ ማድረግ የቱን ያህል በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ ያለው መኾኑን ለማመልከት ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ንስሐ መግባት ከማያስፈልጋቸው ዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሓ በሚገባ አንድ ኀጢአተኛ ምክንያት በመንግሥተ ሰማይ ደስታ ይኾናል" ብሎአል። (ሉቃ:ም:15 ቍ:7)



www.ethiopianorthodox.org

በሌላ በኩል ደግሞ:- "እግዚአብሔርን የምትወድዱ ክፋትን ጥሉ" (መዝ:97 ቍ:10፥ "እግዚአብሔርን መውደድ ክፋትን ይጠላል" (ምሳ:ም:8 ቍ:13) ፥ "ክፋውን ጥሉ መልካሙን ውደዱ:" (አም:ም:5 ቍ:15) ተብለው በተዘረዘሩት ጥቅሶች ውስጥ ክፋት ወይም ክፉ የተባለው ኀጢአት ለማለት ስለኾነ ሐዋርያው ይሁዳ ኀጢአትን ጥሉ ማለቱ ለኀጢአተኛ ራሩ ካለው ጋር ተቃራኒ አይደለምና አለመኾኑን ዐውቀን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

## ራእየ ዮሐንስ

ይህ የራእይ መጽሐፍ 22 ምዕራፎች ያሉት ኾኖ በአራት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 3 ድረስ ሲኾን በዚህ ክፍል ውስጥ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተሰጠ ስብከት፥ መመሪያና ምክር ይገኝበታል።

ኹለተኛው ክፍል ምዕራፍ 4 እና ምዕራፍ 5 ሲኾን በዚህ ክፍል እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ኾኖ ኻያ አራት ሽማግሌዎች በዙሪያው አራት እንስሳት በፊትና በኋላው ሐዋርያው ያየው ትርእይት ነው።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 6 ምስከ ምዕራፍ 18 ድረስ ሲኾን በዚህ ክፍል ውስጥ በአይሁድና በአረማውያን ጠላቶችዋ በኩል በቤተ ክርስቲያን ላይ ሊደርስ ያለው ተቃውሞ፥ በሚካኤል ከመላእክቱ ጋርና በሰይጣን ከመላእክቱ ጋር በሰማይ የተደረገው ጦርነትና የሰይጣን ከመላእክቱ ጋር መሸነፍ፥ የሐሳዊ መሲሕ መነሣትና የምእመናን ለሦስት ዓመት ተኩል መሰደድ በመጨረሻም በክርስቶስ አማካይነት የሐሳዊ መሲሕ ድል መኾን ይገኝበታል።

አራተኛው ክፍል ከምዕራፍ 19 እስከ ምዕራፍ 22 ድረስ ሲኾን በዚህ ክፍል በቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ይ ጌታ ስለተቀዳጀው ድል፥ ስለፍርድና ቅዱሳን በሰማይ ስለተሰጣቸው ክብር ተገልጾአል።





107 በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 1 ቍ:10—11 ላይ:- "በጌታ ቀን በመንፈስ ኾኜ በኋላዬ እንደ መለከት ያለ እንዲህ የሚል ታላቅ ድምፅ ሰማሁ እኔ አልፋ ኦሜጋ ፥ የፊተኛውና የኋለኛው ነኝ፤ የምታየውን በመጽሐፍ ጽፈህ ወደ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፥ ወደ ኤፌሶን፥ ወደ ሰምርኔስ፥ ወደ ጴርጋሞን፥ ወደ ትያጥሮን፥ ወደ ሰርዴስ፥ ወደ ፊላዴ ልፍያና ወደ ሎዶቅያ ላክ።"

ይህ አልፋና ኦሜጋ የሚለው አባባል በራእየ ዮሐንስ መጽሐፍ ውስጥ በብዙ ቦታ ተደጋግሞአል። ለምሳሌ በም:1 ቍ:8፥ 17፥ በም.2 ቍ:8 በም.22 ቍ:13 የተደጋገመ እንደ ሠኾኑ የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ዘላለማዊነት ያመለክተናል። እነዚህንም ቃላት ፈጣሪ አምላክ በዘመነ ኦሪት በነቢያት አማካይነት ተጠቅሞባቸዋል። ለምሳሌ በትንቢተ ኢሳያስ ም.14 ቍ:4፥ ም:44 ቍ:6፥ ም፥48 ቍ:12 እግዚአብሔር አምላክ እነዚሁኑ አባባሎች ተጠቅሞባቸዋል።

ታዲያ የራእይ ዮሐንስን መጽሐፍ ለመሠረተ እምነታቸው ዋና ማስረጃ አድርገው የሚያቀርቡ አንዳንድ ወገኖች ከጥንት ጀምሮ እኔ አልፋ ኦሜጋ የመጀመሪያና የመጨረሻ ነኝ ያለውን ጌታ ኢየሱስ ክር ስቶስን ፍጡር ነው የሚል ድፍረት የተመላበት ክርክር ሲያቀርቡ መጽ ሐፉን አገናዝበውት ነው ወይስ ልብ ብለው አልተመለከቱት ይኾን?

108 በራእየ ዮሐንስ ም:12 ቍ:7—9:- "በሰማይ ጦርነት ተነሣ፤ ሚካኤልና የእርሱ መላእክት ከዘንዶውና ከመላእክቱ ጋር ተዋጉ፤ ነገር ግን ዘንዶውና መላእክቱ ተሸነፉ። ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም። ታላቁም ዘንዶ ወደ ምድር ተጣለ። እርሱ ሰዎችን ኹሉ የሚያስተው ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን ተብሎ የሚጠራው የቀድሞው እባብ ነው። እርሱ ወደ ምድር ተጣለ፤ የእርሱም መላእክት ከእርሱ ጋር አብረው ተጣሉ" ተብሎ የተነገረው ታሪክ ይህ ሚካኤል የተ ባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብለው የተለመደውን የድፍረት አነጋ ገራቸውን የሚሰነዝሩ ወገኖች አሉ። ይህም አባባል ወልደ እግዚአብ ሔርን ወደ ፍጡርነት ደረጃ ለማውረድ ከሚሞከረው ሙከራ አንዱ



www.ethiopianorthodox.org

ነው። ሚካኤል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በሚሉበት ጊዜ ለአባባላቸው ምንም ተጨባጭ ማስረጃ የላቸውም።

በትንቢተ ዳንኤል ም.10 ቍ:13፥ ም.12 ቍ:1 እና በመልእክተ ይሁዳ ቍ:9 ላይ የቅዱስ ሚካኤል ስም በተነሡበት ጊዜ ኹሉ እንደ ሊቀ መላእክትነቱ እንጂ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስነቱ አልተነገረም።

ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ወልደ እግዚአብሔር፥ ቃለ:እግዚአብሔር፥ ጥበበ እግዚአብሔር፥ መድኃኔዓለም፥ አማኑኤል የተባሉ ስሞች ያሉት ከመኾኑ በቀር የሊቀ መላእክቱን ስም ወስዶ ሚካኤል የተባለበት ጊዜ ከቶ አይገኝም።



## ለጽሑፉ ድጋፍ የኾኑ መጻሕፍት ዝርዝር


ሐርፐር: የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት የወንድማማች አታሚ ዎች ድርጅት፥ እ.ኤ.አ.1955 ዓ.ም፥ ኒውዮርክ (በእንግሊዝኛ)

ሐና አላህ ጊርጊስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው፥ እ.ኤ.አ 1950 ዓ.ም ካይሮ (በአረብኛ)

መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት) የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሚው፥ አዲስ አበባ፥ 1948 ዓ.ም

መዝሙረ ዳዊት፥ ከነትርጓሜው:- አዲስ አበባ፡ 1973 ዓ.ም

መጽሐፍ ቅዱስ፥ (በአማርኛ፥ በእንግሊዝኛና በአረብኛ ቋንቋዎች)

ሚናዮሐና (ቄስ) የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች መልስ፥ ካይሮ እ.ኤ.አ1940ዓ.ም (በአረብኛ)

ብራውን (ዶክተር) የሐዋርያት ሥራ ትርጓሜ ወደ አረብኛ የተተረጐመ፥ ካይሮ።

ብራውን (ዶክተር)፥ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች መልእክት ትርጓሜ ወደ አረብኛ የተተረጐመ።

ኢብራሂም ሰዒድ (ቄስ) ወደ ኤፌሶን ሰዎች መልእክት ትርጓሜ፥ ካይሮ እ.ኤ.አ. 1937 ዓ.ም (በአረብኛ)

ክሎው ወ.ም. (ቄስ፥ ዶክተር) የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፥ ሎንደንና ኒውዮርክ፥ (በእንግሊዝኛ)

ወንጌል ቅዱስ፥ ንባብና ትርጓሜው፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ 1966 ዓ.ም




www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፥ አዲስ አበባ፥ 1972 ዓ.ም።

የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምሁራን፡ የሮሜ መልእክት ትርጓሜ፥ ካይሮ፥ (በአረብኛ)

የጽዮን መጽሔት ባለቤት፥ የተጠራጣሪዎች ጥያቄዎችና መልሶቻቸው፥ ካይሮ፥ እ.ኤ.አ. 1929 ዓ.ም (በአረብኛ)

ዴቪድሰን (ፕሮፌሰር)፥ አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ፥ ሚቺጋን፥ እ.ኤ.አ. 1963 ዓ.ም (በእንግሊዝኛ)

ጋርድነር (ቄስ) ወደ ፊልጰስዩስ ሰዎች መልእክት ትርጓሜ፥ ካይሮ፥ እ.ኤ.አ. 1931 ዓ.ም (በአረብኛ ትርጉም)

ሐፍዝ ዳውድ: ዲድስቅልያ፥የሐዋርያት ትምህርት፥ እ.ኤ.አ 1940 ዓ.ም፥ ካይሮ (በአረብኛ)

ፍትሐ ነገሥት፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ (በግዕዝና በአረብኛ)



www.ethiopianorthodox.org